ስካን በማድረግ ያግኙን
Scan and contact us on

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሣኔዎች ቅጽ-28

ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
FEDERAL SUPREME COURT

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሣኔዎች

ለላቀና ተደራሽነት ላለው የዳኝነት አገልግሎት እንተጋለን!
We strive for an efficient and accessible judicial service!

ቅጽ - 28

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

ሰበር ሰሚ ችሎት ውሣኔዎች

ቅጽ-28

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍ/ቤት

ምርምርና ሕግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት

ህዳር 2018 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ድህረ-ገፅ፡-www.fsc.gov.et
ስልክ፡-+251-11-1-55-34-00/011-1-11-04-32
ፋክስ፡-+251-111-56-55-33
የመ.ሣ.ቁ. 6166
ነፃ የስልክ መስመር፡- 992

ክቡር የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት መልዕክት

የተከበራችሁ አንባብያን

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር 1234/2017 አንቀጽ 10 (3) አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተሰጠባቸውን ውሳኔዎች በኤሌክትሮኒክስ እና በሕትመት የማሰራጨት ኃላፊነት ለመወጣት ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ ላለፉት 21 ዓመታት በ27 ቅጾች 2,424 አስገዳጅ ሕግ ትርጉም የተሰጠባቸውን ውሳኔዎች በመምረጥ እና በማሳተም ለሕብረተሰቡ እንዲደርሱ አድርጓል፡፡ ይህን ጥረቱን በመቀጠል 28ኛው ቅጽ ለእናንተ ለተከበራችሁ አንባብያን እነሆ ብለን ስናቀርብ በታላቅ አክብሮት ነው፡፡ ከዚህ ቀደም እንደታተሙት ቅጾች በዚህ ቅጽም የተለያዩ ጉዳዩች ላይ የተሰጡ 51 አስገዳጅነት ያላቸውን የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎችን በመምረጥ እንዲታተሙ ተደርገዋል፡፡ እነዚህ ውሳኔዎች በተከራካሪ ወገኖች መካከል ያለውን አለመግባባት እልባት ከመስጠት ባለፈ በቀጣይ በሚኖሩ ክርክሮች የሚኖራቸው አስገዳጅነት ምክንያት ተደራሽ መደረጋቸው አስፈላጊነት በተጨማሪ ለሕግ አስተምሕሮ፣ ለመማር ማስተማርና ለምርምር ፋይዳ ያላቸው በመሆኑ ህትመቱ ከዚህ አንጻር የሚኖረው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው፡፡

እነዚህ ውሳኔዎች በሕግ ትርጉም አማካኝነት ለሕጉ ሕይወት የሚዘሩ ከመሆኑም በላይ በዕለት ተዕለት ሕይወት በተመሳሳይ ጉዳዮች ተፈጻሚ የሚደረጉ በመሆናቸው ተደራሽነታቸውን

ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው። በኤሌክትሮኒክስ መንገድ ተደራሽ ከማድረግ ጎን ለጎን የተጠራቀሙ ያልታተሙ ውሳኔዎች በተመሳሳይ ሁኔታ በተከታታይ ለማሳተም ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል። እነዚህ ውሳኔዎች ውይይትን ጋብዘው፣ ተመራማሪዎችን ስበው፣ ተቺዎችንም አነሳስተው የአገራችንን የህግ አስተምሮ ለማዳበር፣ ለማበልጸግ የሚኖራቸው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ በዚህ ረገድ የሚደረጉ ገንቢ ጥረቶች ሊበረታቱ ይገባል። ከዚህም በላይ እነዚህ ውሳኔዎች ለሕብረተሰቡ እንዲዳረሱና ግንዛቤ እንዲፈጠር መስራትም ሰዎች መብታቸውን ለማስከበር የሚያደርጉትን ግለሰባዊ ጥረትም ሆነ በአጠቃላይ ለሕግ የበላይነት መስፈን አስተዋጽዖ ያደርጋል።

የተከበራችሁ አንባብያን!

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአሁኑ ወቅት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ እና በተሻለ ደረጃ የዳኝነት አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓቱን ከእጅ ንክኪ እና ተለምዷዊ አሰራር ወደ ዲጂታል ስርዓት በማሸጋገር ተገልጋዮች ውሳኔዎቹን በቀላሉ እንዲያገኙ ከማድረግ በተጨማሪ ከውሳኔ በፊት ባሉት የክርክር ሂደቶች ውስጥ ገንዘባቸውን ጉልበታቸውን እና ጊዜያቸውን ሳያጠፉ ባሉበት ቦታ ሆነው በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመታገዝ ፍትሕ የማግኘት ሕገ-መንግስታዊ መብታቸው እንዲከበር በማድረግ ላይ ይገኛል። በዚህም ጥራት እና ከፍ ያለ ተደራሽነት ያለውን የዳኝነታዊ ፍትሕ አገልግሎት መስጠት ዓላማውን ለማሳካት ሌት ተቀን ጥረት በማድረግ ላይ የሚገኝ በመሆኑ ይህንን ጥረት በማገዝና ግቡን እንዲመታ የበኩላችሁን አስተዋጽኦ እንድታበረክቱ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስም አደራ እላለሁ።

አመሰግናለሁ።

ቴዎድሮስ ምህረት ከበደ

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ፕሬዝደንት

<u>የሕግ ጥናት እና ምርምር ዳይሬክቶሬት መልዕክት</u>

<u>የተከበራችሁ አንባብያን</u>

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80 እንደዚሁም አሁን ስራ ላይ ባለው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 በተለይም በአንቀጽ 10 (2) እና (3) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት ሰበር ሰሚ ችሎት የሚሰጠው የሕግ ትርጉም ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በየትኛውም ደረጃ በሚገኝ የፌዴራልም ሆነ ክልል ፍርድ ቤት አስገዳጅነት ያላቸውን እና አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተሰጠባቸውን ውሳኔዎች በኤሌክትሮኒክስ ወይም በሕትመት ሚዲያዎች አሳትሞ ማሰራጨት ከጀመረበት ከ1997 ዓም አንስቶ እነሆ 21 ዓመት አስቆጥሯል።

በእነዚህ ሁለት አስርት ዓመታት ውስጥም 27 መደበኛ ቅጾችን አንድ የሴቶች መብት ላይ የተሰጡ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የያዙ ውሳኔዎች ቅጽ' የሕጻናት መብቶችን የሚመለከቱ አስገዳጅ የሰበር ውሳኔዎችን የያዘ አንድ ቅጽ ሰባት ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጡ የተመረጡ የሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ ውሳኔዎችን የያዘ ልዩ እትም ቅጽ እንደዚሁም አሁን በቅርቡ የሕጻናት መብቶችን የሚመለከቱ አስገዳጅ የሰበር ውሳኔዎችን ሁለተኛ ቅጽ በማሳተም ለሕብረተሰቡ ለማዳረስ ጥረት ተደርጓል በመደረግም ላይ ይገኛል። እነሆ አሁንም መደበኛው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተሰጠባቸውን የተመረጡ የሰበር ውሳኔዎችን የያዘው 28ኛ ቅጽ ለአንባብያን እና ለሕጉ ማህበረሰብ ስናቀርብ ከፍ ያለ ደስታ ይሰማናል። በዚህም የሕግ ባለሙያዎች የሕግ መምህራን እና ተማሪዎች ጠበቆች እና ነገረ ፈጆች ዓቃብያነ ሕግ እና ዳኞች ብሎም ማንኛውም በፍትሕ እና ሕግ ዙሪያ እውቀት ግንዛቤ እና መረጃን የሚፈልጉ የሕብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ እየሆኑ እንደሆነ ተስፋ እናደርጋለን። በቀጣይም የሕትመቶቹን ዝግጅት ጥራት እና ይዘት እንደዚሁም የተደራሽነት አድማስ ከዚህ በተሻለ መንገድ ለማሻሻል ፍርድ ቤቱ ከመቼውም ጊዜ በላይ ጠንክሮ አየሰራ መሆኑንን እየገለጽን ለዚህም የእናንተ የአንባብያን አስተያየት እና ጥቆማ ወሳኝ በመሆኑ እንዳይለየን በአክብሮት እየጠየቅን በቀጣይ በቅጽ 29 እስከምንገናኝ ድረስ መልካም ንባብ እንዲሆንላችሁ እንመኛለን። እናመሰግናለን !!!

አሮን ደጎል ሐብቱ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሕግ ጥናት እና ምርምር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሕግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎች ማውጫ ቅፅ 28

ተ.ቁ	የሕግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ				**1**
1.	ንብረት እንዲከበር የሚሰጥ ጊዜያዊ ትእዛዝ በዘፈቀደ የሚሰጥ ሳይሆን ፍርድ ቤት የተሰጠው ትእዛዝ እንዲነሳለት አቤቱታ ያቀረበበት ትእዛዝ ልክ ሲሆን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 154 ስር በተደነገገው መሰረት የሚሰጥ ጊዜያዊ እግድም ሆነ ቢበዛ ፍርድ እስከሚሰጥ ድረስ ካልሆነም ፍርዱ ከመሰጠቱ በፊት በማንኛውም ጊዜ ሊነሳ የሚችል ቢሆንም እንኳን በግራ ቀኙ ጥቅምና በአጠቃላይ የክርክር ሂደትና ኢኮኖሚው ላይ ከሚያስከትለው ውጤት አንጻር ሲታይ በዋናው ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ በመጠበቅ ከዋናው ጉዳይ ጋር ይግባኝ የሚባል ሳይሆን እንደመጨረሻ ውሳኔ የሚቆጠርና በዚያው ፍርድ ቤት እንደገና እንዲታይ በተዘረጋው ሥርዓት መሰረት እንደገና እንዲታይ ከተደረገ በኋላ ይግባኝ ሊባልበት የሚቻል ስለመሆኑ። በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁጥር 158 መሰረት የእግድ ትእዛዝ እንዲነሳ	208397	በእምነት ኤሌክትሮ ሜካኒካል ኢንጂነሪንግ እና የሞጣ ከተማ አስተዳደር አገልግሎት ጽ/ቤት	የካቲት 30 ቀን 2014 ዓ.ም	1

ተ.ቁ	የሕግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ትእዛዙን ለሰጠው ፍርድ ቤት አቤቱታ የሚቀርብበት ምክንያት ጊዜያዊ እግድ ጸንቶ እንዲቀጥል እንዲነሳ ወይም እንዲሻሻል የሚያደረግ ምክንያት መኖር አለመኖሩን ጉዳዩ ከሚፈልገው አጣዳፊነት ባህርይ የተነሳ ራሱ ፍርድ ቤቱ ትእዛዙን እንደገና ተመልክቶ በትእዛዙ ላይ ይግባኝ ከመባሉ በፊት እንዲመረምር ሥርዓት ለመዘርጋት እንጂ ይግባኝ እንዳይቀርብበት ለመከልከል ባለመሆኑ ጊዜያዊ እግዱ እንዲነሳ ትእዛዙን ለሰጠው ፍርድ ቤት አቤቱታ ቀርቦ ተቀባይነት ባያገኝ እንኳን ይግባኝ ከማቅረብ የሚያግድ የሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌ ስለሌለ ጉዳዩ ላይ አቤት ማለት ይቻላል። በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 151 መሰረት ከፍርድ በፊት ለክርክሩ መነሻ ያልሆነውን ንብረት (ገንዘብ) በማስከበር የሚሰጥ ትእዛዝ ደግሞ በሕጉ በቁጥር 153/5 አነጋገር መሰረት እስከ ፍርድ አፈጻጸም ድረስ ፀንቶ ሊቆይ የሚችል በመሆኑና ትእዛዙ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ከሚያስከትለው ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ውጤት እና የሚታገደውም ንብረት (ገንዘብ) ለክርክሩ መነሻ ያልሆነ ከመሆኑ አንጻር ሲታይ				

ተ.ቁ	የሕግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	በዋናው ጉዳይ ላይ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ተጠብቆ ይግባኝ የሚባልበት ነው ወይም እንደጊዜያዊ ትዕዛዝ (interlocutory decision/order) የሚቆጠር ባለመሆኑ ዋናው ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ሳይጠበቅ ይግባኝ ሊባልበት የሚቻል ስለመሆኑ፡፡				
2.	በአንድ ውሳኔ ላይ ሁለት ተከራካሪ ወገኖች በተለያዩ መዝገቦች ይግባኝ አቅርበዉ ሁለቱ መዝገቦች ሳይጣመሩ የተለያየ ዉሳኔ ከተሰጠ እርስ በርሱ የሚጋጭ ዉሳኔዎች የተሰጡ በመሆኑ አንዱ ዉሳኔ እሰከ ሰበር ሰሚ ችሎት የፀና እንደሆነ እና ሌላኛው ዉሳኔ በከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ በመቀበል የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔን በመሻር የተሰጠው ውሳኔ ሁለት የተለያዩ ውሳኔዎች በአንድ ጉዳይ የተሰጡ በመሆኑ ሊፈጸም ስለማይችል ማስተካከያ ሊደረግበት የሚገባ ስለመሆኑ እና ቀድሞ የጸናው ውሳኔ የአመልካቾችን መብት የሚነካ በመሆኑ ተሽሮ በፍርድ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ዉሳኔ ማጽናት የሚገባ ስለመሆኑ፡፡ ፍ/ሥ/ሥ/ሕግ 11(5)	221472	እነ ወ/ሮ ሐረግነሽ መኮንን 2 (ሰዎች) እና አቶ ዓለም ገ/ሚካኤል ገብራት	ህዳር 30 ቀን 2014	8

ተ.ቁ	የሕግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
3.	ተከሳሹ በተያዘለት ቀነ ቀጠሮ የጽሑፍ መልሱን ባለማቅረቡ መብቱ የታለፈ ከሆነ ክሱ በሚሰማበት ቀነ ቀጠሮ ቀርቦ የሚያነሳውን የይርጋ መቃወሚያ ተቀብሎ ማስተናገድ በሥነ ሥርዓት ሕጉ የተመለከተውን የክርክር አመራር ሥርዓት የሚቃረን እና ክርክሮችን የሚያወሳስብ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ።	158462	አቶ ጠሃ አብዶ እና አቶ አብደላ ከዲር	ታህሳስ 11 ቀን 2011 ዓ.ም	13
4.	ከሳሽ ወገን ክስ ካቀረበ በኋላ በማናቸውም ጊዜ ያቀረበውን ክስ በማንሳት ወይም ክሱን በማቋረጥ ከተከሳሾቹ አንዱን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑትን ከክሱ ውጭ ለማድረግ ወይም ያቀረበውን ክስ በሙሉ ወይም በከፊል ለመተው የሚችል ሲሆን ጉዳዩ ላይ በሌላ ጊዜ ግን አዲስ ክስ ለማቅረብ የሚችል ቢሆንም ፍርድ ቤት ክሱ ሲቋረጥ የሰጠው ትዕዛዝ ግልጽ ባልሆነበት ጊዜ ከሳሽ አዲስ ክስ ማቅረብ ይችላል ወይስ አይችልም ለማለት በወቅቱ የቀረበውን የአቤቱታ ይዘት ጭምር መመርመር አስፈላጊ ሲሆን ይህም ከሳሽ ክሱን የተወው ሌላ ጊዜ አዲስ ክስ ለማቅረብ ከፍርድ ቤቱ ፈቃድ ለማግኘት ከሆነ ፍርድ ቤቱ አቤቱታውን ተቀብሎ ክሱን ለማንሳት ወይም ለማቋረጥ የጠየቀበትን ምክንያት መርምሮ ከሳሹ አዲስ ክስ ለማቅረብ	202737	አቶ ረጋሳ ጉርሙ እና ወ/ሮ ዘነበች ገ/መንፈስ	ሕዳር 29 ቀን 2014 ዓ.ም	16

ተ.ቁ	የሕግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	እንደሚችል መብት የጠበቀለት ከሆነ አዲስ ክስ ለማቅረብ የሚያግደው ነገር የለም፡፡ ነገር ግን ከሳሽ ያለ ፍርድ ቤት ፈቃድ ክሱን በሙሉ ወይም በከፊል የተወ እንደሆነ ክሱን ማቋረጡን ፍርድ ቤቱ እንዲያውቀው ለማድረግ የቀረበ ከሆነ በጉዳዩ ላይ አዲስ ክስ ማቅረብ የማይችል ስለመሆኑ፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 278/1/2/ እና 289/1/				
5.	ፍርድ ቤቶች ክስ ተሻሽሎ በቀረበ ጊዜ ቀድሞ የነበረውን ክስ ቀሪ ማድረግ ውጤት ያለው በመሆኑ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ሊሰጥ የሚችለው ተሻሽሎ በቀረበው ክስ እና ተከሳሹ የሰጠውን መልስ መሠረት በማድረግ ሲሆን አስፈላጊ ማስረጃ ከበፊቱ ክስ ጋር ተያይዞ ነገር ግን ከተሻሻለው ክስ ወይም መልስ ጋር ተያይዞ በለማቅረቡ ብቻ ማስረጃ እንዳልቀረበ ተደረጎ ውድቅ ሊደረግ የማይገባ ስለመሆኑ፡፡ ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 91	198902	እነ ወ/ሮ ካሕሳ ተስፋይ 2(ሰዎች) እና ቃለአብ አብርሃ	መስከረም 27 ቀን 2014 ዓ.ም	22
6.	በፍ/ቤቶች ውሳኔ በተከራካሪ ወገኖች መካከል የተፈፀመው ውል ፈራሽ ነው ከተባለ ግራ ቀኙ ወደ ነበሩበት ቦታ እንዲመለሱ ሳይወሰን የታለፈበት ውሳኔ ሊፈፀም ስለማይችል ቅሬታ ያለው ወገን በይግባኝ	204195	ወ/ሮ ጽጌ ወርቁ እና አቶ ኢሳያስ ተገኝ	የካቲት 30 ቀን 2014 ዓ.ም	27

ተ.ቁ	የሕግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	እንዲታረም ከመጠየቅ በስተቀር ለአፈጻጸም ችሎት በትዕዛዝ ወይም ውሳኔ ለሰጠው ፍ/ቤት ለማሳረም አቤቱታ ማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ።				
7.	ፍርድ ቤቶች ከተካራካሪ ወገኖች መካከል ጣልቃ ገብ ተከራካሪው በሥነ ሥርዓት ሕጉ መሰረት ወደ ክርክሩ እንዲገባ እና ክርክሩን እንዲያቀርብ ባላደረገበት ሁኔታ፣ ዳኝነት ባልተከፈለበት፣ለክርክር ምክንያት የሆነዉ ንብረት የዉርስ ሀብት ሳይሆን የ3ኛ ወገን ንብረት ነዉ በማለት መወሰን የማይቻል ስለመሆኑ። የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.182 (2)፤40 (2)	162628	አቶ ፍቅሩ ክብካብ እና እነ ወ/ሮ ኑኑሽ ክብካብ 2(ሰዎች) ጣልቃ ገብ፡- የመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል አስተዳደር ጽ/ቤት	ህዳር 24 ቀን 2012 ዓ.ም	31
ውል					35
8.	በፍርድ ቤት በክርክር ላይ ባለ ጉዳይ ተከራካሪ ወገኖች ነገሩን በእርቅ ለመጨረስ ተስማምተው እርቁም በጽሑፍ ተደርጎ ፍርድ ቤት ቀርቦ ለሕግና ለሞራል ተቃራኒ አለመሆኑ ተረጋግጦ ከመዝገቡ ጋር	143086	አቶ አፈወርቅ ያለው እና እነ አቶ በላይ ኢሳያስ	መጋቢት 25 ቀን 2010 ዓ.ም	35

ተ.ቁ	የሕግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	እንዲያያዝ ከተደረገ የእርቁ ስምምነት እንደ ፍርድ ተወስዶ የአፈጻጸም ክስ ሊቀርብበት የሚችል ሲሆን ከጉዳዩ ጋር ተያይዞ በተከራካሪ ወገኖች መካከል አለመግባባት ቢፈጠር እንደ መደበኛ ውል፤ ውል እንዲፈርስ አዲስ ክስ ማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ። ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ/386፣ 392		2(ሰዎች)		
9.	የውጭ ሀገር ገንዘብ (ዶላር) ኢትዮጵያ ውስጥ በአደራ የማስቀመጥ ውልን በተመለከተ ተዋዋዮች የመዋዋል ነጻነት ቢኖራቸውም በወንጀል ሕግ እና በብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሰረት የውጭ ሀገር ዶላር ከተቀመጠው ገደብ በላይ መያዝም ሆነ ማስቀመጥ በሕግ የተከለከለ መሆኑ በሕግ የተመለከተውን አስገዳጅ ሁኔታ አልፎ የሚፈጸም ውል ሕገ-ወጥ ተግባር በመሆኑ ፍርድ ቤቶች ሕገ-ወጥ ውል የሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት የሌለ በመሆኑ የውጭ ሀገር ገንዘቡ በዚህ መጠን እና ለረጅም ጊዜ በግለሰብ እጅ እንዲቆይ በአደራ ዉል የማስቀመጥ ህገ ወጥ እና ሊፈጸም የማይችል ዉል ስለመሆኑ። ፍ/ሕ/ቁ. 1716 (1)፣1678 (ለ)፣ወንጀል ሕግ አንቀጽ 346 ፣አዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀጽ 26 ፣ የብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር	219931	አቶ ዮናስ ደስታ እና አቶ ነጋሽ ኃይሌ	ሰኔ 28 ቀን 2014 ዓ.ም	39

ተ.ቁ	የሕግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ኤፍ.ኤክስ.ዲ. 49/2017				
10.	የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ባለቤትነትን ከማስተላለፍ ጋር በተያያዘ የሚደረግ ስምምነት ድርድር ወይም በእርቅ በፍ/ብ/ሕግ/ቁ. 1723/2 ድንጋጌ ማዕቀፍ ውስጥ ሊገባ እንደሚገባ ከድንጋጌው ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻል በመሆኑ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነትን ለማስተላለፍ የሚደረግ እርቅ ስምምነት በጽሑፍ እና ውል እንዲያዋውል ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት ካልተደረገ ሕጋዊ ውጤት የማይኖረው ስለመሆኑ። ፍ/ብ/ሕግ/ቁ 1723/2 ፣ 3318 - 3324 ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁ 274-277	173623	እነ ቂስ መንግስት እምሩ 2/ሰዎች/ እና እና መሪጌታ አስማማው መንግስት 2/ሰዎች/	የካቲት 24 ቀን 2012 ዓ.ም	43
ንብረት					**50**
11.	መንግሥት በሚያስተዳድረው ይዞታ ላይ በመንግሥት ዕውቅናም ይሁን ሳያውቅ ይዞታው ላይ ግንባታ መፈፀሙ የንብረቱ ባለቤትነትን የማያሳናጽፍ በመሆኑ በዚህ አግባብ የሚቀረብ ክርክር ተቀባይነት የሌለዉ ስለመሆኑ።	217447	አቶ አለሙ ታፈሰ እና የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን	ጥቅምት 03 ቀን 2014 ዓ.ም	50

ተ.ቁ	የሕግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
12.	ይዞታቸው ወደ ከተማ አስተዳደር ውስጥ የተካለለበቸው ሰዎች በገጠር መሬት ላይ ያላቸውን የይዞታ እና የመጠቀም መብት በተመለከተ ለባለይዞታዎቹና ለልጆቻቸው የቤት መስሪያ ቦታ ሳይሰጥ እና የቀረው ይዞታ ላይ ካሳ ሳይከፈላቸው ይዞታቸው ለሌሎች ግለሰቦች የተሰጠባቸው ሰዎችን አቤቱታ ተቀብሎ የማየት የሥረ ነገር ሥልጣን የወረዳው ፍርድ ስለመሆኑ።	217195	ወ/ሮ ፍርኑስ ፈንቱ እና የደብረማዊ ንዑስ ማዘጋጃ ቤት	ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ.ም	56
13.	የከተማም ሆነ የገጠር መሬት ድንበር መገፋት ጋር ተያይዞ የሚቀርበውን ጉዳይ ከሳሽ ወገን መጠኑን ገልጾ ከጠየቀው ዳኝነት እና በምስክሮች ወይም አስተዳዳሪ አካል አጣርቶ የቀረበው መጠን ከተጠየቀው ዳኝነት በላይ በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መስጠት ያለባቸው ግዴታ ከሳሽ ወገን በጠየቀው ዳኝነት ልክ በመሆኑ በአስተዳዳሪ አካል ተጣርቶ የቀረበውን በማለፍ በተጠየቀው ዳኝነት ልክ መወሰን የሚገባ ስለመሆኑ። ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.182 (1) እና 224 (1)	165593	ወ/ሮ ውቤ በላይነህ እና እነ ወ/ሮ ሰናይት ሃብተሥላሴ 2(ሰዎች)	ሚያዝያ 28 ቀን 2011 ዓ.ም	60
14.	ከገጠር መሬት ይዞታ ጋር በተያያዘ የባለ ይዞታ ልጅ ትዳር ሲይዝ	197998	አቶ ክቢ ሂርጴ	ግንቦት 24 ቀን	65

ተ.ቁ	የሕግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ለመተዳደሪያ የሚሆን በተለምዶ ለጎጆ መውጫ ተብሎ የሚደረግ የመሬት ስጦታ ጥብቅ የሆነ የአጻጻፍ ሥርዓት ወይም የስጦታ ውል ፎርም ባያሟላም በማኅበረሰቡ የዳበረውን ልማድ እና ጠቃሚ እሴት ከግምት ውስጥ በማስገባት የጎጆ መውጫ ስጦታው ሕጋዊነት እንዲኖረው ማድረግ ተገቢ ስለመሆኑ፡፡		እና ወ/ሮ ደጊቱ ባሌሳ	2013 ዓ.ም	
ውርስ					**72**
15.	የውርስ ሀብት ድርሻን በተመለከተ ወራሾች በስምምነት ንብረቱን በዓይነት ለማከፋፈል የማይቻል ከሆነ ፍርድ ቤት የውርስ ድርሻ ክፍያ የሚፈጸመው ንብረቱን በባለሙያ ግምት (Book Value) መሰረት በማድረግ ሳይሆን በገበያ ዋጋ (Market Value) በሐራጅ ተሽጦ ለወራሾች የክፍያ ድርሻ መፈጸም የሚገባው ስለመሆኑ፡፡ ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.132-136፣250 - ፍ/ብ/ሕ/ቁ.1079፣1083፣1084	222271	እነ አቶ ዳንኤል አወቀ 3 (ሰዎች) እና እነ ወ/ሮ ሐውልቱ ታምር 4(ሰዎች)	ሐምሌ 26 ቀን 2014 ዓ.ም	72
16.	ሚች ከአብራካቸው የተወለደ ልጅ ስለሌላቸው በሕይወት እያሉ የሚንከባከባቸውና ከጎናቸው ሆኖ የሚያስፈልጋቸውን የሚያሟላላቸው እና ሲሞቱም የቀብር ሥነ-ሥርዓታቸውን የሚያስፈጽምላቸውን	217114	እነ አቶ ወልዴ ወልደገብርኤል 2(ሰዎች) እና አቶ ደጀኔ በቀለ 4	ሐምሌ 25 ቀን 2014 ዓ/ም	78

ተ.ቁ	የሕግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	በማሰብ በእርሳቸው እና በበላቤታቸው ስም ተመዝግቦ የሚገኘውን የማይንቀሳቀስ ሆነ የሚንቀሳቀስ በየትኛውም ቦታ በስማቸው ያለውን ንብረት ድርሻቸውን ሁሉ ለባለቤታቸው ተናዘው እያሉ ኑዛዜ ተቀባዩ ከተናዛዢ ቀድሞ ቢሞት እና ተናዛዢም በኋላ ስትሞት ኑዛዜ ተቀባዩ የጠቅላላ ሀብት ወራሽ ቢሆንም የተደረገው ኑዛዜ ቅድመ ሁኔታ ያለበት በመሆኑ ኑዛዜ ተቀባዩ የተመለከተው ቅድመ ሁኔታ ሳይሟላ አስቀድሞ በመሞቱ ኑዛዜው ቀሪ ስለሆነ የኑዛዜ ተቀባዩ ወራሾች ኑዛዜ መሠረት አድርጎ ሚች አሳታቸውን ተክተው ሊወርሱ የማይቻል ስለመሆኑ። ፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 916 ፣ 918(2)፣826(2) እና 844(2)		(ሰዎች)		
17.	በውርስ ሕግ ኑዛዜውን የመቃወም ይርጋን በተመለከተ የወራሽ ኑዛዜ ሲነበብ ወይም የውርሱ ኑዛዜ ከፈረሰበት ጊዜ በራሱም ሆነ በውክልና ያልተገኘ ወይም ስለ ውርሱ ድልድል፣አመዳደብ ሐሳብ በውርስ አጣሪው ባይገለጽለትም የኑዛዜውን መጽናት በመቃወም ክስ ማቅረብ የሚቻለው በአምስት ዓመት የጊዜ ገደብ ውስጥ ብቻ ሲሆን ይኸውም የይርጋ ግዜ ፍጹም (absolute) ይርጋ ስለመሆኑ።	217691	የሚች ወ/ሮ ዋጋዬ ወ/ማርያም ሕጋዊ ወራሾች 3/ሰዎች/ እና ወ/ሮ የሺሐረግ ከበደ	ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም	84

ተ.ቁ	የሕግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 974(2)				
18.	አውራሹ በህይዎት እያለ በስጦታ ለወራሾቹ አንዱ ወይም ለተወሰነ ወራሾቹ ለመታዳደሪያነት የተሰጠ እንደሆነ አውራሹ ሲሞት አስቀድሞ ንብረት በስጦታ ያገኘዉ ወራሽ ዉርስ ክፍፍል ላይ ለመሳተፍ የሚፈልጉ ከሆነ አስቀድሞ በስጦታ የተቀበሏቸዉን ወደ ዉርሱ ሀብት መመለስ አለበለዚያም አስቀድሞ በስጦታ ያገኟቸዉን ንብረቶች እንደያዙ ቀሪዉን የዉርስ ሀብት ከሌሎች ወራሾች ጋር ለመከፋፈል የማይቻል ስለመሆኑ። የፍ/ሕ/ቁጥር 1065-1067	113247	እነ ወ/ሮ የሺ አካሉ 2(ሰዎች) እና እነ ማርታ ደበበ (2ሰዎች)	መስከረም 26 ቀን 2009 ዓ.ም	94
ቤተሰብ					98
19.	ከልጅ አስተዳደግ ክርክር ጋር በተያያዘ ልጁ ፍላጎቱን መግለጹን ብቻ መሰረት በማድረግ የሚወሰን ሳይሆን በማኅበራዊ ሳይንስ ባለሙያ የልጁ አስተዳደግና መልካም ደህንነት፣ጥቅምን (the best interests of	210403	አቶ ገዛኸኝ ይልማ እና	የካቲት 28 ቀን 2014 ዓ.ም	98

ተ.ቁ	የሕግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	the child) በሕገ መንግሥቱና በዝርዝር ሕግ የተመለከተው በቀዳሚነት ታሳቢ ተደርጎ የሚወሰን ስለመሆኑ። የኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 36 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 218 የሕጻናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 3		ወ/ሮ ድንቅነሽ ስለሺ		
20.	ተጋቢዎች በጋብቻ ወቅት ባፈሩት የጋራ ንብረት ላይ የይገባኛል ክስ በቀረበ ጊዜ አንደኛው ቀርቦ ንብረቱ የባልና ሚስቱ የጋራ ንብረት ሳይሆን የከሣሹ ወይም የ3ኛ ወገን ነው ሲል አምኖ በመከራከሩ ንብረቱ የ3ኛ ወገን ነው በማለት የተሰጠው ውሳኔ ሌላኛው ተጋቢ የመቃወም አቤቱታ አቅርቦ በክርክር ሒደቱ ንብረቱ በጋብቻ የተፈራ የጋራ ንብረት መሆኑ ቢረጋገጥም ከተጋቢዎች መካከል አንደኛው ንብረቱ የእርሱ አለመሆኑን በማመኑ ጋብቻው ሳይፈርስ የጋራ ንብረቱን ሳይከፋፈል አንደኛ ተጋቢ በማመኑ ብቻ ድርሻውን ለከሳሹ ወይም ለ3ኛ ወገን እንደለቀቀ ይቆጠራል ማለት ሌላኛው ተጋቢ	179231	ወ/ሮ ተሚማ ሬድዋን በሸር እና እነ አቶ በድሩ ሰማን 2(ሰዎች)	መስከረም 27 ቀን 2013 ዓ.ም	103

ተ.ቁ	የሕግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ድርሻዬን ትውሰድ/ይውሰድ ማለት የማይቻል ስለመሆኑ። የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀፅ 62(1) እና 66				
21.	ከባልና ሚስት በአንዱ በተፈጸመና ለፍቺው ምክንያት ሆኖ በተገኘ ጥፋት በሌላኛው ተጋቢ ላይ ጉዳት አስከትሎ የተገኘ እንደሆነ በዳዩ ላደረሰው ጉዳት ተመጣጣኝ የሆነ ካሳ በተጠየቀ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ጉዳቱ መድረሱን ካረጋገጠ ከጋራ ንብረት በካሳ መልክ የአንደኛውን ተጋቢ ድርሻ አብዛኛውን ወይም ሙሉውን በደል ለተፈጸመበት ወገን እንዲከፈል ሊወስን የሚችል ስለመሆኑ። በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 69/95 እንደተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 83/96 አንቀጽ 111	152968	ሲ/ር ሐምዚያ ሱለይማን እና አቶ አያለው በቀለ	መስከረም 21 ቀን 2011 ዓ.ም	111
22.	በሃይማኖታዊ ሥርዓት መሰረት በእንደራሴው አማካኝነት ጋብቻ ሊፈጸም የሚችለው ተጋቢው ፈቃዱን በማያሻማ ሁኔታ በፍትሕ ሚኒስትር ወይም በክልል ፍትሕ ቢሮ ቀርቦ ሲረጋገጥ ብቻ ቢሆንም እንኳን ተጋቢዎች ጋብቻ ሳይመሰርቱና ለአንድ ቀን እንኳን አብሮ የመኖር ግዴታቸውን ሳይወጡ አለመግባባት ቢፈጠር በግራቀኙ	213864	ወ/ሪት ካስሪያ ተካ እና ረጆቦ ከድር	ሚያዝያ 28 ቀን 2014 ዓ/ም	115

ተ.ቁ	የሕግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	መካከል በሕግ ፊት የፀና የሚፈርስ ጋብቻ የሌለ ስለመሆኑ። የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 12 በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ የቤተሰብ ሕግ ቁጥር 75/1996 አንቀጽ 16 የኢ/ፌ/ዲ/ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 34(2) የሲቪልና የፖለቲካል መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን አንቀጽ 23(2) በሴቶች ላይ የሚደረግ ማንኛውንም አድሏዊ ልዩነትን ለማስወገድ የተደረገ ስምምነት አንቀጽ 16 (1) (ለ) የፍትሐብሔር ሕግ/ቁ 579-580				
23.	በተጋቢዎች መካከል ጋብቻ ፈርሶ የሐብትና ንብረት ክፍፍል ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ክፍፍሉን በስምምነት ጨርሶ የጋራ እዳዉንም በግላቸው ከሚደርሳቸው ድርሻ ለመክፈል ተስማምተው ንብረት ክፍፍል ካለቀ በኋላ አንደኛው ተጋቢ እዳዉን ላለመክፈል ፍቃደኛ ካልሆነ ሌላኛዉ ተጋቢ በውሉ መሰረት እንዲፈፅም ይወሰንልኝ በማለት መጠየቅ የሚችለው የተደረገው የግልግል ስምምነት ፍርድ	204514	አቶ ሰይድ ተስፋ እና ወ/ሮ ሉባባ ጀማል	የካቲት 30 ቀን 2013 ዓ.ም	124

ተ.ቁ	የሕግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ቤት ቀርቦ ከፀደቀ ብቻ ስለመሆኑ።				
	የዳኝነት ስልጣን				130
24.	ተበዳሪ ባንክ የሚያካሒደውን ሐራጅ በተመለከተ መደበኛ ፍርድ ቤት ባንኮች ለዕዳ በመያዣ የያዘውን ንብረት በሐራጅ በመሸጥ ዋናውን ገንዘብ እና ወለድ ለመሰብሰብ የሚያካሂደው የሐራጅ ሽያጭ ሂደት አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሐራጅ ሽያጩ ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚሉትን ነጥቦች ዐይቶ የመወሰን ሥልጣን የለውም ነገር ግን አንድ ባለዕዳ የሐራጅ ሽያጭ በአግባቡ ባለመደረጉ ምክንያት የደረሰበትን ጉዳት ለይቶ አግባብነት ባለው ማስረጃ በማስደገፍ የጉዳት ካሰ እንዲከፈለው ሥልጣን ላለዉ መደበኛ ፍ/ቤት አቅርቦ መጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ። አዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 6፣7	127995	ብርሃን ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ እና እነ አቶ ዳንኤል ተስፋዬ 2 (ሰዎች)	ጥር 24 ቀን 2009 ዓ.ም	130
25.	በተዋዋይ ወገኖች መካከል ከተደረገ ውል ጋር ታያይዞ በመካከለቸው አለመግባባት ቢፈጠር በግልግል ዳኝነት ጉባዔ ለመፍታት የተስማሙ እነደሆነ በመካከለቸዉ አለመግባባት ሲፈጠር ተዋዋዮቹ በተስማሙት	158634	ዳሸን ባንክ አ.ማ እና ሪቼል ተስፋዬ ትሬዲንግ	ህዳር 28 ቀን 2011 ዓ.ም	138

ተ.ቁ	የሕግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	መሰረት በእርቅ ወይም በግልግል ዳኛ ከሚታይ በስተቀር መደበኛው ፍርድ ቤት ቀጥታ ክስ ተቀብሎ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ። በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.315 እና .3325 በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.9 (2)፣ 244 (2፣ ሀ) እና 245 (2) የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1731(1) እና.2945		ኃ/የተ/የግ/ማህበር		
26.	የግልግል ዳኝነት ስምምነቱ ዋጋ ያለዉ መሆን አለመሆኑን (ፈራሽ ነው ተብሎ የሚቀርብ ክርክር /validity of arbitration agreement) በተመለከተ የሚነሳ ክርክር ጭምር ሰምቶ የመወሰን ስልጣን ያለው ገላጋይ ዳኛው ወይም የግልግል ዳኝነት አካሉ ሳይሆን መደበኛ ፍርድ ቤት ስለመሆኑ። በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 3330/3 UNCITRAL Model Law እ.ኤ.አ በ1985 ወጥቶ በ2006 አንቀጽ 16	171335	እነ ሜሮል ኢንኮርፖሬትድ 2(ሰዎች) እና ስዊዲሽ ኢንተርናሽናል ሮድ ኮንሳልቲንግ ኤቢ	ሕዳር 30 ቀን 2012 ዓ.ም	142
27.	በፌዴራል ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ የፍርድ ባለዕዳ ንብረት የሚገኝበት ክልል ውስጥ ያለው የወረዳ ፍርድ ቤት እንደፍርዱ እንዲያስፈጽም ሲላክለት የወረዳ ፍርድ ቤቱ ውሳኔውን ለማስፈጸም የሚሰጠው ትዕዛዝ ለመቃወም የሚቀርብ የይግባኝ አቤቱታ ለክልሉ	138405	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሞጆ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት	ጥቅምት 20 ቀን 2010 ዓ.ም	155

ተ.ቁ	የሕግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሳይሆን ለፌዴራል ፍርድ ቤት ሲሆን ይህ ማለት የሚፈጸም ውሳኔን ከላከው ፍርድ ቤት ቀጥሎ ባለው እርከን ደረጃ ላይ ያለዉ ፍርድ ቤት ስለመሆኑ። የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.372/1/ እና 374/1/		እና እነ ዳሸን ባንክ አ.ማ 3(ሰዎች)		
28.	መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች ውስጥ በሆኑ ሰዎች መካከል በሚነሱ ክርክሮች ላይ የመዳኘት ሥልጣን ያለው የፌደራል ፍርድ ቤት ቢሆንም ጉዳዩ የተነሳው በክልሉ ሲሆን በሕገ-መንግሥቱ በተሠጠው ውክልና መሠረት መታየት ያለበት በክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስለመሆኑ። አዋጅ ቁጥር 25 /1988 አንቀጽ 3፣ 4 እና 5 የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 47(1)፣78(2)፣50-52፣80(1)(2)	181923	የቡራዩ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ጽ/ቤት እና አቶ ከበደ አበበ	ግንቦት 26 ቀን 2012 ዓ.ም	160
29.	ባልና ሚስት ኢትዮጵያውያን ሆነው በውጭ ሀገር ሕግ መሰረት በዚያው ሀገር ጋብቻ በመካከላቸው እንደተደረገ በመግለጽ አንደኛው ተጋቢ ጋብቻ በሐገር ውስጥ እንዲፈርስ እና ንብረት ክፍፍል እንዲደረግ ዳኝነት ሲጠይቅ ጉዳዩ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግን	200482	ወ/ሮ ሐቢባ ሸምሱ ስሩር እና አቶ ቴዎድሮስ ገብሩ	ህዳር 27 ቀን 2014 ዓ.ም	169

ተ.ቁ	የሕግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	(private international law) የሚመለከት በመሆኑ ጉዳዩን ተቀብሎ የመዳኘት የሥረነገር ሥልጣን የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ስለመሆኑ። አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 5 (1፣ ሀ) እና 11 (1፣ ሀ)		ብዛ		
	ጉምሩክ				**174**
30.	የተሽከርካሪን አካል ዕቃዎችን ለመደበቅ የሚያስችል እንዲሆን ለውጦ ወይም ሻግ ተሰርቶ የኮንትሮባንድ ዕቃ ጭኖ የተገኘ ተሽከርካሪ የባለቤቱ እውቅና ያለው አለመሆኑን ግምት ውስጥ ሳያስገባ ተሽከርካሪው ውርስ ሆኖ ለመንግሥት ገቢ የሚደረግ ስለመሆኑ። ጉምሩክ አዋጅ ቁ.859/2006 አንቀጽ 1479(3)(ሀ)	204922	ኢንተርስቴት ኤክስፕሬስ ትራንስፖርት ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና የሚሌ አዋሽ ጉምሩክ ጽ/ቤት	የካቲት 28 ቀን 2014 ዓ.ም	174
31.	አገር ውስጥ የገባ ዕቃ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ከገባበት ቀን ጀምሮ ተቀምጦ ሊቆይ የሚችልበት ጊዜ ለውስን ቀናት ብቻ ስለሆነ በሕግ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ካልወጣ በዕቃው ላይ በሚደርሰው	207462	መገል አይንትአቨን ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር	የካቲት 30 ቀን 2014 ዓ.ም	180

ተ.ቁ	የሕግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ጉዳት ተጠያቂነት የማያስከትል ስለመሆኑ። አዋጅ ቁ.1160/2011 አንቀጽ 28/1/ አዋጅ ቁ.859/2006 አንቀጽ 28/5/		እና የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክ አገልግሎት ድርጅት		
ባንክ፣ንግድና ኢንሹራንስ					**190**
32.	አበዳሪ ባንክ በመያዣ የያዘውን ንብረት እዳውን የሚከፍልበት ጊዜ እና ሁኔታ አለመከበር ወይም መጣሱን ሳያረጋግጥ በመያዣ የያዘውን ንብረት በሐራጅ የሸጠ እንደሆነ ተግባሩ የውል ጥሰት ስለሚሆን እና መያዣ ሰጪው ከሕግ ውጪ የባለቤትነት መብቱን ሊያጣ ስለማይገባ የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ ክስ ለመደበኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ እና ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን ተቀብሎ ማየት የሚችል ስለመሆኑ። በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 3 እና 4	216672	ወ/ሮ ወርቅነሽ ጀቤሳ እና እነ የኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ አክስዮን ማህበር /ሰዎች/	ግንቦት 1 ቀን 2014 ዓ.ም	190
33.	ባንክ የገባው የዋስትና ውልና የዋስትና ግዴታ ሰነድ/ቦንድ በቅድመ ሁኔታ ወይስ ያለቅድመ ሁኔታ የተደረጉ ናቸው የሚለው ጉዳይ ክሱን	211694	አቶ ታደሰ ዓለምሰገድ	የካቲት 28 ቀን 2014 ዓ.ም	197

ተ.ቁ	የሕግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	በሚመረምረው ፍርድ ቤት እልባት የሚያገኙ ሲሆን የዋስትና ግዴታ ሰነዶች የሦስትዮሽ ውል በመሆናቸው በዋነኛነት ያለቅድመ ሁኔታ በመሆኑ የሚጠቅመው የዋስትና ግዴታው የተገባለት ተጠቃሚ በመሆኑ የዋስትና ግዴታው ሰነድ ያለቅድመ ሁኔታ የተደረገ ቢሆን እንኳን እግድ መሰጠቱ የሰነዱ ውጤት ላይ የሚያመጣው ለውጥ ባለመኖሩ እግዱ ሊነሳ የሚገባ አይደለም፡፡ አዋጅ ቁጥር 97/1990 አንቀጽ 4፣ ፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 154 እና 155		እና ቡና ኢንተርናሽናል ባንክ አ/ማ		
34.	ማኅበሩ በፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፈርስ ከማኅበርተኞቹ አንዱ ማኅበሩ እንዲፈርስ በሚያቀርበው አቤቱታ መነሻነት ፍርድ ቤት የማኅበሩን መፍረስ ሊወስን እንደሚችል ሥራ ላይ ከነበረው የንግድ ሕግ የሚደነግግ ቢሆንም የንግድ ማኅበሩ በፍርድ እንዲፈርስ ስለተጠየቀ ብቻ የሚፈርስ ሳይሆን ማኅበሩን ለማፍረስ የሚያበቃ በቂና ትክክለኛ ምክንያት መኖሩ ሊረጋገጥ የሚገባ ሲሆን፡፡ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ሥራ አስኪያጅ በሕጉ፣በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ፣ በመተዳደሪያ ደንብ፣ እንዲሁም በጠቅላላ ጉባኤዎች በሚተላለፉ ውሳኔዎች የተጣለበትን ኃላፊነት መወጣት	212593	ሚስ ሻሮን አና ኢሸተን እነ ዶ/ር መላኩ መንግስቱ 2 (ሰዎች)	ሐምሌ 4 ቀን 2014 ዓ.ም	206

ተ.ቁ	የሕግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ባለመቻል፤ የማኅበሩን የዕለት ከዕለት ተግባራት በቅርበት በኃላፊነት አለመምራት፣ ማኅበሩ የተቋቋመበትን ዓላማ ዳር ለማድረስ አለመቻል፣ የማኅበሩንና የማኅበርተኞችን መብትና ጥቅም የሚጎዱ ተግባራት የፈጸመ መሆኑ ከተረጋገጠ ከማኅበርተኞቹ አንዱ ክስ ለፍርድ ቤት በማቅረብ ሥራ አስኪያጅ ለመሻር የሚችል ስለመሆኑ። ሥራ ላይ የነበረውን የንግድ ሕግ አንቀጽ 527(3) እና (5)፤ 218፣ 258፣ 278፣ 303፣ 495፣ 542፣ 543				
35.	በባንክ የገንዘብ ሐዋላ መላኪያ ወረቀት ሰነድ ገንዘብ መላኩን ከማስረዳት ውጪ በምን ምክንያት ገንዘቡ መላኩን ወይም ገንዘቡ በብድር፣በአደራ የተሰጠ መሆኑን ሊያስረዳ የማይቻል ስለመሆኑ። የፍ/ሕ/ቁጥር 2472፣ 2782/1/2/፣2802/2	150290	አርቲስት ንዋይ ደበበ እና አቶ ኤፍሬም ኤርሚያስ	ሐምሌ 23 ቀን 2010 ዓ.ም	215
36.	በውጭ አገር የንግድ ምልክቱን በአግባቡ አስመዝግቦ ሕጋዊ ሰውነት የተሰጠው የንግድ ድርጅት ከኢትዮጵያ ጋር የእንካ ለእንካ ስምምነት ቢኖር ወይም ባይኖር ኢትዮጵያ አባል የሆነችበት ዓለም አቀፍ ውል ቢኖርም ባይኖርም ኢትዮጵያ ውስጥ የንግድ ምልክቱን ወይም የንግድ	109032	እነ አጂ.ኤች.ሲ.ሚክስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና ኢንተርኮንቲኔታል	መስከረም 30 ቀን 2009 ዓ.ም	221

ተ.ቁ	የሕግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ምልክቱን በሚመስል መለያ ሕዝብን ሊያሳስት በሚችል አኳሀን አላግባብ እንዳይጠቀሙበት ለማድረግ የሚያስችል መብት ያለው ስለመሆኑ።። በአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 2/4 እና 3 እና አንቀጽ 26/1/2/ አዋጅ ቁጥር 686/2002 አዋጅ ቁጥር 501/98 ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.23626		ሆቴልስ ኮርፖሬሽን		
37.	አበዳሪ ባንክ ለዕዳው መልካም አመላለስ ሲል መስፈርቶቹን በማሟላት በመያዣነት የያዘውን ንብረት/የተሸከርካሪ/ ባለቤት በሙስና ወንጀል ስለተከሰሰ ወይም በተጠረጠረ ጊዜ ንብረቱ በሙስና ወንጀል የተገኘ ወይም በሙስና በተገኘ ንብረት የተፈራ ነው በሚል ባንኩ ባስከበረው ንብረት ላይ ዕግድ መሰጠቱ ብቻ ባንኩ የቀደምትነት መብቱን የሚያጣበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ በመሆኑ ንብረቱ በሙስና ወንጀል የተገኘ ወይም በወንጀል በተገኘ ንብረት የተፈራ ነው በሚል ውሳኔ ያላረፈበት ቢሆን እንኳን ንብረቱ/ተሸከርካሪው/ ተሸጦ የዕዳ ተመላሽ	182772	ቡና ኢንተርናሽናል ባንክ እና የፌዴራል ፖሊስ የምሥራቅ ቀጠና ወንጀል ምርመራ	ታህሳስ 29 ቀን 2013 ዓ.ም	226

ተ.ቁ	የሕግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ተደርጎ የሚተርፍ ገንዘብ ካለ ከመጠየቅ በስተቀር የባንኩን የቀደምትነት መብቱን የማያሳጣ ስለመሆኑ። አዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 3 የፍ/ሕ/ቁ.2828፣2857/1/ እና 3059				
38.	ባንኮች በቼኩ ላይ የተፈረመው ፊርማ ናሙና ላይ ከተመለከተው ጋር ተመሳሳይ መሆኑን በማረጋገጥ ክፍያ ሲፈጽሙ ፊርማ ከናሙና ፊርማ ጋር መመሳሰሉ ማስረዳት ከቻሉ ከተጠያቂነት ነጻ የሚያደርግ ባለመሆኑ በገለልተኛ አካል ታይቶ የሚረጋገጥ እንጂ የተሰየሙት ዳኛ ራሳቸው አይተው ግምት ሊወስዱበት የሚገባ ስላለመሆኑ።	213835	የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ-እና እነ ሲ ጂ ሲ አቨርሲስ ኮንስትራክሽን ሊሚትድ ወጋገን ባንክ አ.ማ	መጋቢት 27 ቀን 2014 ዓ.ም	231
39.	ኢንሹራንስ ኩባንያ የኢንሹራንስ ካሳ ክፍያ ይርጋ ጥያቄ የሚቋረጥ ከባለ እዳዎች በአንደኛው ባለእዳ የተፈጸመው ተግባራት በሁሉ ሌሎችን ባለእዳዎች መብት የማስጠበቅ ወይም ይርጋውን ቀሪ የሚያደርግ ስለመሆኑ። ፍትሐብሄር ሕግ ቁ.1852/1 1851ሐ 1901	237038	ሕብረት ኢንሹራንስ አ.ማ እና ኦሮሚያ ኢንሹራንስ አ.ማ	ሚያዚያ 30 ቀን 2014 ዓ/ም	242

ተ.ቁ	የሕግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	አፈጻጸም				247
40.	በጨረታ በሚሸጠው ንብረት ላይ የጋራ ባለሀብት በመሆኑ ምክንያት በሕግ የቀዳሚነት መብት የተጠበቀለት ወገን ንብረቱን ለመግዛት በጨረታ ተወዳዳሪ ሆኖ ካልቀረበ በቀር ጨረታው ተከናውኖ አሸናፊው ከታወቀ በኃላ የጨረታውን ውጤት አውቆ የሚያቀርበው የቀዳሚነት መብት ጥያቄ በጨረታው አሸናፊ መብት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ስለሚኖረው አቤቱታው ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ። የፍ/ሕግ/ቁ.126(1)፤/1386-1409 ፤ ፍ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁ.430(1)443	205594	አቶ ኪነጥበብ አዳነ እና እነ ከድጃ መሐመድ 4/ሰዎች/	ጥር 27 ቀን 2014 ዓ.ም	247
41.	ተከራካሪ ወገኖች በአፈጻጸም ክርክር የቅድሚያ መብት ይጠበቅልኝ ጥያቄ ላይ ካልተስማሙ ፍርድ ቤቶች የግዢ ቅድሚያ መብት ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ ንብረቱ በጨረታ ተሸጦ ክፍፍል የሚደረግ ሲሆን ግራ ቀኙ እንደ ማንኛውም ተጫራች በጨረታ ተወዳድረው ንብረቱን ማስቀረት የሚችሉ ስለመሆኑ።	215842	ወ/ሮ ቀመሪያ አህመድ እና እነ አቶ የሱፍ ሰኒ 6/ሰዎች/	ሚያዝያ 25 ቀን 2014 ዓ.ም	255
	የወንጀል ሕግ				261

ተ.ቁ	የሕግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
42.	በወታደራዊ ፍ/ቤት የሚሰጥ ውሳኔን በተመለከተ የቅጣት መጠኑን በወንጀል ሕግ ስለ ወታደራዊ ወንጀሎች የተደነገገውን የቅጣት አወሳሰን መርሕን በመከተል እንጂ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያወጣቸውን የወንጀል ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች አወሳሰን መመሪያዎች መሠረት እንዲወስኑ የማይገደዱ ስለመሆኑ።	118227	ኮሎኔል ዓለም ትኩዕ እና የምዕራብ እዝ ወታደራዊ ዓቃቤ ሕግ	መጋቢት 29 ቀን 2009 ዓ.ም	261
43.	አንድ ሰው በፈፀመው የወንጀል ድርጊት የተጎጂው አጥንት መሰበሩ የተረጋገጠ ቢሆንም ስብራቱ ታክሞ መዳኑ በባለሙያ ከተረጋገጠና በስብራቱ ምክንያት የተጎጂ ሰውነትም ሆነ በአዕምሮው ላይ ለዘወትር ጠንቅ የሚያተርፍ መሆኑ ፤ከአካሉ ወይም አስፈላጊ ከሆኑ ብልቶች መካከል አንዱ ወይም ከዚያ በላይ መጉደሉ እና በጉዳቱ ምክንያት አስፈላጊው ብልት አገልግሎት አለመስጠቱ ወይም በሚያሳቅቅ ጉልህ ሆኖ በሚታይ ሁኔታ የተጎጂው መልክ መበላሸቱ፤ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ሌላ ከባድ የሆነ ጉዳትን ወይም በሽታን የሚያስከትል መሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር ተጎጂ ላይ የደረሰው አጥንት ስብራት ታክሞ መዳኑ ከተረጋጠ ድርጊቱ የሚሸፈነው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 556(2) በመሆኑ ቅጣቱ ሊጣልበት የሚገባ	219862	ተድላ ክፍሌ ኦሻ እና ኦሮሚያ ጠቅላይ ዐ/ሕግ	ግንቦት 26 ቀን 2014 ዓ.ም	271

ተ.ቁ	የሕግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	በአንቀጽ 556(2) መሰረት ስለመሆኑ።				
44.	የማታለል ወንጀል የሚፈጽም ሰው ተግባሩን የሚፈጽመው በማታለል ተግባር ምክንያት የራሱን ወይም የሶስተኛ ወገንን የንብረት ጥቅም የሚጎዳ አድራጎት የሚፈጽም ከሆነ የማታለል ተግባሩን የፈጸመው ሰው ለድርጊቱ ተጠያቂ ሲሆን ነገር ግን የማታለል ድርጊቱ ተፈጽሞብኛል የሚለው ሰው አብሮ የወንጀሉን ፍሬ ተጠቃሚ ለመሆን ከሆነ የማታለል ወንጀል ተፈጽሞበታል ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ። የወ/ሕግ አንቀጽ 692/1	231232	አቶ ሳምሶን ተሾመ እና የፍትሕ ሚኒስቴር ዓቃቤሕግ	የካቲት 30 ቀን 2014	276
		አሠሪና ሠራተኛ			281
45.	የሥራ ውሉ ከሕግ አግባብ ውጪ መቋረጡን ተከትሎ የሰራተኛ ስንብት ክፍያ የሚመለከት ከሆነ ግዴታ የሰራተኛ የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ መሆን የሚገባ ስለመሆኑ። አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 39/1/ለ/	195390	አቶ ኃይሉ ምትኩ እና ሬየስ ኢንጂነሪንግ አክሲዮን ማህበር	የካቲት 26 ቀን 2013 ዓ.ም	281

ተ.ቁ	የሕግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
46.	ከአሠሪ ድርጅት ጋር ተያይዞ በሙስና ወንጀል ተጠርጥሮ ለረዥም ጊዜ እስር ላይ ቆይቶ በነጻ ሲሰናበት የሥራ ውሉ የተቋረጠ ሰራተኛ የሚያቀርበው አቤቱታ ላይ የሥራ ውሉ በሕገ-ወጥ መንገድ የተቋረጠ መሆኑ ከተረጋገጠ ሠራተኛው ወደ ሥራው ተመልሶ ለመስራት ፍላጎት ያለው መሆኑ እና ሠራተኛው ወደ ሥራው ሲመለስ በአሠሪው ላይ የሚያደርሰው ችግር መኖሩ እስካልተረጋገጠ ድረስ ለረዥም ጊዜ ታስሮ መቆየቱን ብቻ ምክንያት በማድረግ ሠራተኛውን የሥራ ስንብት ክፍያ ከፍሎ ማሰናበት የማይቻል ስለመሆኑ፡፡ አዋጅ ቁጥር 377/96 እንቀፅ 43(3)	202341	አቶ ሀብታሙ አሻግሬ እና የኢትዮጵያ አየር መንገድ	ሐምሌ 30 ቀን 2013 ዓ.ም	287
የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ					292
47.	የሙስና ወንጀሎችን በግበረ-አበርነት የፈፀሙ ሰዎች የወንጀሉ ምርምራ ተጠናቆ ወደ ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት ጠቃሚ ማስረጃ የሰጡ ሰዎች ክስ ተቋርጦላቸዉ ከተከሻስነት ወደ ምስክርነት ቃል ክብደት ማንኛውም ምስክር ከሚሰጠው ምስክርነት እኩል ዋጋ እንዳለውና በሕጉ ጥበቃ የተደረገለት ሲሆን ነገር ግን ክስ ከቀረበና	197540	አቶ አበበ ብርሃን አድማሴ እና የፌደራል ጠቅላይ ዐ/ህግ የቀረበ	ጥቅምት 29 ቀን 2014ዓ/ም	292

ተ.ቁ	የሕግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ማስረጃ መሰማት ከጀመረ በኋላ የተወሰኑትን ተከሳሾች ክስ ተነስቶ ክስ ባልተነሳላቸው ተከሳሾች ላይ ምስክር እንዲሆኑ ማድረግ ምስክሮች ለማስረዳት የሚጠቀሙት የምስክርነት ቃል ወይም ሐሳብ ቀደም ሲል በግበረ-አበርነት በተከሰሱበት ወቅት የተከሳሽ ማስረጃዎችን አዳምጠው ያገኙትን ግንዛቤ እንዲሁም የከሳሽ ወገንን የማስረጃ ክፍተት እና ፍላጎት ከተረዱ በኋላ የተገባላቸውን የተስፋ ቃል እያሰቡ የሚሰጡት የምስክርነት ቃል የተገባላቸው የክስ መነሳት ቀርቶ በተከሳሽነት እንደሚቀጥሉ እያሰቡ በጫና ውስጥ ሆነው የሰጡት ምስክርነት ቃል በመሆኑ በዚህ መልክ የተዘጋጀው የምስክርነት ቃል ተቀባይነት ሊያገኝ የማይችል ስለመሆኑ። የአዋጅ ቁጥር 434/1997 እንደተሻሻለ አዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀፅ 8(1)፣41(5)፤ወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 141 እና 142(1)				
48.	በወንጀል ተከሶ ክሱን እንዲከላከል የተነገረው ተከሳሽ የሚጠበቀው ዐቃቤ ሕግ ባስረዳው ልክ በመከላከያ ማስረጃው በቂ እና አሳማኝ በሆነ መልኩ ማረጋገጥ ሳይጠበቅ በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የተረጋገጠበትን ክስ እና ማስረጃን እንዲያስተባብል ሲሆን ማስተባበል ማለት ደግሞ	212950	አቶ ቶቹኖ ቶማ እና የደቡብ ክልል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ	ሕዳር 30 ቀን 2014 ዓ.ም	301

ተ.ቁ	የሕግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የተከሳሹን የወንጀል ድርጊት እና ጥፋተኝነት አረጋግጠዋል በተባሉት ማስረጃዎች ላይ በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ ጥርጣሬ እንዲፈጠር በማድረግ ብቻ ስለመሆኑ። ወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 141 እና 142				
49.	በወንጀል ክስ ክርክር ተከሳሽ ባለመቅረቡ ምክንያት ተከሳሹ እስኪቀርብ ድረስ በሚል የፍርድ ሒደቱ ሲቋረጥ በኤግዚቪትነት የተያዘው ንብረት ላይ ውሳኔ ሳይሰጥ ማቆየት ባለንብረቱ በንብረቱ እንዳይጠቀሙ የሚያደርግ ውጤት በማስከተል የንብረት መብት የሚጥስና ንብረቱ በሐገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ አበርክቶ እንዳይኖረው የሚያደረግ በመሆኑ ፍርድ ቤቶች መዘገቡ መንቀሳቀስ ሳያስፈልግ በኤግዚቪትነት የተያዘ ንብረት ለባለቤቱ እንዲመለስ ትዕዛዝ መስጠት የሚገባ ስለመሆኑ። የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 97፤በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40/1	176890	አቶ ቢንያም አብዱልቃድር እና የኦሮሚያ ክልል ፍትህ ቢሮ ዓቃቤ ሕግ	ግንቦት 25 ቀን 2012 ዓ.ም	305
50.	ከአንድ በላይ በዋና ወንጀል አድራጊነት በተከሰሱ ሰዎች ላይ በተሰጠ	203253	አቶ በሪሁን አጥናፍ	መስከረም 28 ቀን	314

ተ.ቁ	የሕግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሳኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ውሳኔ ከተከሰሱ ሰዎች መካከል አንዱ ይግባኝ ካለ እና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ለተከሳሹ የሚጠቅም ውሳኔ ከተሰጠ፤ሌሎቹ ይግባኝ ያላቀረቡ ተከሳሾች ይግባኝ ካቀረበው ተከሳሽ ጋር የተቀጠበት ወንጀል አንድ ከሆነ እና ውሳኔው የግል ሁኔታን መሰረት ያደረገ ሳይሆን በቀጥታ ከሕግ አተረጓጎም እና አተገባበር ጋር የተያያዘ መሆኑ ከተረጋገጠ ይግባኝ ያላቀረቡት ተከሾች ይግባኝ ባያቀርቡም ውሳኔው በወንጀል ሕግ ሥነ-ሥርዓት ቁጥር 196(1)(ሀ) እና (ለ) መሰረት ተፈጻሚ ሊሆንላቸው የሚገባ ስለመሆኑ፡፡		እና የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ዐ/ሕግ	2014 ዓ.ም	
			ልዩ ልዩ		**319**
51.	አንድ ሰው በማጎበር ተደራጅቶ የቤት መሥሪያ ቦታ በመጠባበቅ ላይ እያለ ወደ ሌላ አካባቢ በመዘዋወሩ ምክንያት የማጎበሩን መብትና ግዴታ የማያጣ ስለመሆኑ፡፡ ሕገ መንግስት 32/2 (32/1 እና 41/1 13/1)	208865	ወ/ሮ እቴነሽ መለሰ መከተ አዘናው እና ማራናታ የቤት ህብረት ሥራ ማኅበር	የካቲት 29 ቀን 2014 ዓ/ም	319

ፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ሰበር ሰሚ ችሎት

የሠ/መ/ቁጥር 208397

የካቲት 30 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች ፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች ፡-በእምነት ኤሌክትሮ ሜካኒካል ኢንጂነሪንግ

ተጠሪ ፡- የሞጣ ከተማ አስተዳደር አገልግሎት ጽ/ቤት

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከፍርድ በፊት ንብረት(ገንዘብ) ለማስከበር ትእዛዝ የሚሰጥበትን አግባብ የሚመለከት ነዉ፡፡ አመልካች በተጠሪ ላይ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ላይ በመሰረተዉ ክስ ከተጠሪ ጋር የተፈጸመዉን የመንገድ መብራት ዝርጋታ ሥራ ዉል ተጠሪ በሕጋዊ መንገድ ሳያቋርጥ ሥራዉን በከተማ አስተዳደሩ ስር ለተደራጁ ወጣቶች ሰጥቷል፡፡ አመልካች ለሠራዉ ሥራ በዉሉ መሰረት መክፈል ያለበትን ተከታታይ ክፍያዎችንም አልከፈለም፡፡ስለሆነም አመልካች

ሠርቶ ተጠሪ ያልከፈለዉን ክፍያ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡ይህንን ተከትሎም ለፍርድ ቤቱ ባቀረበዉ አቤቱታ ክስ እስከቀረበበት ብር 2,500,000.00 ድረስ በተጠሪ የባንክ ሒሳብ ዉስጥ የሚገኘዉ ገንዘብ ታግዶ እንዲቆይ እና ተጠሪ ለሦስተኛ ወገን የሠጠዉ ግንባታ ታግዶ እንዲቆይ እንዲታዘዝለት ጠይቋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 252475 ላይ በቀን 15/10/2012ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዋናዉ ቅርንጫፍ በባንኩ በተጠሪ ስም ከተከፈተዉ ሂሳብ ላይ እስከ ብር 2,500,000.00 ድረስ አግዶ እንዲያቆይ እና ግንባታ እንዲታገድ በተጠየቀዉ ላይ ግን ተጠሪ አስተያየት እንዲሰጥ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ተጠሪ ለፍርድ ቤቱ ባቀረበዉ አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 158 መሰረት እግዱ እንዲነሳለት ቢጠይቅም ፍርድ ቤቱ በመዝገቡ ላይ በቀን 13/11/2012ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ እግዱ ሊነሳ አይገባም በማለት አቤቱታዉን ዉድቅ አድርጓል፡፡

በመቀጠል ተጠሪ ይግባኙን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ችሎቱም በመ/ቁጥር 195667 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 30/06/2013ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪ እግዱ ሊነሳ ይገባል ያለበትን ምክንያቶች ዘርዝሮ ያቀረበ ቢሆንም የስር ፍርድ ቤት የተጠሪን አቤቱታ በደፈናዉ ዉድቅ ከማድረጉ በስተቀር አቤቱታዉን እንደትና በምን ምክንያት እንዳልተቀበለዉ በሰጠዉ ትእዛዝ ያሰፈረዉ ምክንያት ስለሌለ ትእዛዙ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 182 አንጻር ሲታይ ስህተት ያለበት ነዉ፡፡በተጨማሪም በግራ ቀኙ መካከል የተደረገዉ ዉል የአስተዳደር ዉል መሆኑ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡የአስተዳደር መስሪያ ቤት የሥራ ተቋራጩ ጥፋት ቢኖርበትም ባይኖርበትም ዉሉን ማቋረጥ እንዲችል በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 3180 ላይ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡ይህ ሲሆን አመልካች ጉዳት ደርሶበት ከሆነ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 3181 መሰረት ካሳ መጠየቅ ከሚችል በስተቀር በፍርድ ኃይል የአስተዳደር ዉሉን ማስቀጠል አይችልም፡፡በዚህ አግባብ የአስተዳደር ዉል ለማስቀጠል ተብሎ የሚቀርብ ክስም የክስ ምክንያት ያለዉ አይደለም፡፡አመልካችም በክሱ ዉሉ ሳይቋረጥ በመካከላችን እንዲቀጥል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት አልጠየቀም፡፡የአመልካች መሰረታዊ የዳኝነት ጥያቄ ሠራሁኝ ላለዉ ሥራ ተጠሪ ክፍያ እንዲፈጽም ማስወሰን ነዉ፡፡ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት ከተጠየቀዉ ዳኝነት ዉጭ በሆነ አኳኋን እና ተጠሪ በመሰረታዊ ሕግ ዉሉን ለማቋረጥ የተሰጠዉን መብቱን በጣሰ ሁኔታ የግንባታ ሥራዉ ለሌላ ሦስተኛ ወገን ተላልፎ እንዳይሰጥ እና የተጠሪ የሥራ ማስኬጃ ገንዘብ እንዲታገድ የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 154 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች እና

በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 3180 እና 3181 የተደነገገዉን የሚቃረን ነዉ በማለት የሥር ፍርድ ቤት እግዱ ሊነሳ አይገባም ሲል በቀን 13/11/2012ዓ/ም የሰጠዉን ትእዛዝ በመሻር የስር ፍርድ ቤት በቀን 15/10/2012ዓ/ም የሰጠዉ እግድ እንዲነሳ ወስኗል፡፡

አመልካች በቀን 27/09/2013 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ ከላይ በተገለጸዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታዉ ይዘት በአጭሩ፡- በስር ፍርድ ቤት የተሰጠዉ የእግድ ትእዛዝ ጊዜያዊ አገልግሎት ያለዉ በመሆኑ ይግባኝ የማይባልበት ሆኖ እያለ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በትእዛዙ ላይ የቀረበለትን ይግባኝ ተቀብሎ ዉሳኔ የሰጠዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 320/3ን በሚቃረን አኳኋን ነዉ፡፡ተጠሪ እግዱ እንዲነሳለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 158 መሰረት አቤቱታ አቅርቦ ተቀባይነት ካጣ ይግባኝ የማቅረብ መብት ስለሌላዉ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ይግባኙን መቀበል አልነበረበትም፡፡ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት የስር ፍርድ ቤት የሰጠዉ ትእዛዝ በዋናዉ ጉዳይ የተሰጠ ባልሆነበት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 182ን በመጥቀስ የደረሰበት ድምዳሜ የተሳሳተ ነዉ፡፡ተጠሪ ሥራዉን ለሶስተኛ ወገን ያስተላለፈዉ በአመልካች የተሰራዉ ሥራ ቆጠራና ርክክብ ሳይከናወን እና ለአመልካች ሊከፈል የሚገባ ተከታታይ ክፍያ ሳይፈጸም በመሆኑ እና ሥራዉ በሶስተኛ ወገን ሊሰራ የሚችለዉ ለዚሁ ተብሎ በሚመደብ በጀት ከመሆኑ አንጻር ገንዘቡ ለሶስተኛ ወገን ሊተላለፍ ስለሚችል ይህንን ለመከላከል ከፍትህ አንጻር የተሰጠዉ እግድ ተገቢነት ያለዉ ነዉ፡፡ዉሉ የአስተዳደር ዉል ነዉ በሚል መነሻ ብቻ የአመልካችን መብትና ጥቅም በሚጎዳ መልኩ እግዱ እንዲነሳ የተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በማለት አቤቱታዉን አቅርቧል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ የአመልካች ዳኝነት ጥያቄ ለተሰራዉ ሥራ ያልተከፈለ ገንዘብ እንዲከፈለኝ የሚል ስለሆነ ፍርድ እስከሚሰጥ ድረስ ተጠሪ ከባንክ ገንዘቡን አዉጥቶ እንዳያሸሽ በባንክ ያለዉ ገንዘብ በጊዜያዊነት ሊታገድ ይገባል ወይስ አይገባም የሚለዉን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 154 አንጻር ተጠሪ ባለበት እንዲመረመር ትዕዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 15/02/2014 ዓ/ም የተጻፈ መልስ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱ በአጭሩ፡- በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 158 መሰረት እግድ አይነሳም ተብሎ በተሰጠ ትእዛዝ ላይ ይግባኝ ሊቀርብ አይችልም የሚል የሕግ ክልከላ የለም፡፡የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ እግዱ እንዲነሳ ያቀረበዉን አቤቱታ ዉድቅ ያደረገዉ ምክንያት ሳያሰፍር በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ትእዛዝ መሻሩ ተገቢ ነዉ፡፡ተጠሪ የመንግስት መስሪያ ቤት ስለሆነ ክስ የቀረበበት ገንዘብ ለአመልካች

ከተወሰነ በማንኛውም ጊዜና ሁኔታ እንደፍርዱ ለመፈጸም የሚችል መሆኑ እየታወቀ ንብረት ሊያሸሽ ነዉ ተብሎ ተጠሪ በባንክ ያለዉ ገንዘብ እንዲታገድ መታዘዘዉ ስህተት ነዉ፡፡እንዲሁም ዉሉ በመፍረሱ ምክንያት ለሶስተኛ ወገን የተሰጠዉ ሥራ ይቁም በሚል የተሰጠዉ እግድ ዉሉ የአስተዳደር ዉል እንደመሆኑ በማንኛውም ጊዜ ሥራ በአግባቡ እየተሰራ እንዳልሆነ ካመነበት ዉሉን ሊያቋርጥ ይችላል በሚል በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 3180 እና 3181 ስር የተደነገገዉን የሚቃረን በመሆኑ በይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በመታረሙ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለ መልኩ የተመለከተዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት የየዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድረግ በይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በተሰጠ ዉሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ የመሰረተዉ ከተጠሪ ጋር በፈጸመዉ ዉል መነሻ ለሠራዉ ሥራ ሊፈጸምለት የሚገባዉን ክፍያ ተጠሪ ሳይከፍለዉ ዉሉን አቋርጦ ሥራዉን ለሦስተኛ ወገን ሰጥቷል በሚል ሥራ ሠርቶ አልተከፈለኝም ያለዉን ክፍያ ለማስከፈል እንደሆነ ከክርክራቸዉ ተረድተናል፡፡ አመልካች በዉሉ የተመለከተዉን ሥራ ተጠሪ ለሦስተኛ ወገን እንዳያስተላልፍ እና ክስ የቀረበበትን ብር 2,500,000.00 የሚያክል ገንዘብ ከተጠሪ የባንክ ሂሳብ ላይ ለተጠሪ ሳይከፈል ታግዶ እንዲቆይ እንዲታገድ የሥር ፍርድ ቤት መጠየቁን ተከትሎ ፍርድ ቤቱ በቀን 15/10/2012ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ በዉሉ የተመለከተዉ የግንባታ ሥራ እንዲታገድ ወዲያዉ የሰጠ ትእዛዝ ስለመኖሩ የትዕዛዙ ይዘት የማያሳይ ቢሆንም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዋናዉ ቅርንጫፍ በባንኩ ዘንድ በተጠሪ ስም ከተከፈተዉ ሂሳብ ላይ እስከ ብር 2,500,000.00 ድረስ አግዶ እንዲያቆይ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ በአመልካች እንዲታገድ የተጠየቀዉ እና በስር ፍርድ ቤት እንዲታገድ ትእዛዝ የተሰጠበት ገንዘብ ተለይቶ የተቀመጠ ክስ የቀረበበት ገንዘብ ስለመሆኑ ተገልጾ የተጠየቀ እግድ ባለመሆኑ የአመልካች ጥያቄ መስተናገድ ያለበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 154 እና ተከታዮቹ መሰረት ክስ በቀረበበት ንብረት ላይ ጊዜያዊ ዕግድ በሚሰጥበት እና በሚነሳበት ሥነ ሥርዓት አግባብ የሚገዛ ሳይሆን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 151-153 ስር በተደነገገዉ መሰረት ከፍርድ በፊት ለክሱ መነሻ ያልሆነ ንብረት(ገንዘብ) በሚከበርበት ሥነ ሥርዓት አግባብ ምላሽ ማግኘት የሚገባዉ ጥያቄ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ከፍርድ በፊት ንብረት ማስከበርን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በቁጥር 151-153 ላይ የተመለከቱ ሲሆኑ፤ መሠረቱ በቁጥር 151 ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌ ነዉ፡፡ ይህ ድንጋጌ የተከሳሽ ንብረት የሚከበርበትን ሁኔታ የሚደነግግ ሲሆን፣ ንብረቱም የሚከበርበት ምክንያት ተከሳሹ ክሱን ለማሰናከል ያቀደ መሆኑ ወይም የተሰጠዉ ትዕዛዝ እንዳይፈጸም ዘዴ መፍጠሩን ከሳሽ ለፍርድ ቤቱ በሚያቀርበዉ ቃለ መሃላ ከተረጋገጠ እና ተከሳሹ ንብረቱን በሙሉ ወይም በከፊል ለማሸሽ ወይም ለማባከን ማቀዱን ወይም ንብረቱን በሙሉ ወይም በከፊል ክሱ ከቀረበበት ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን ክልል ዉጪ ለማሸሽ ማቀዱን ፍርድ ቤቱ የተረዳ እንደሆነ እና የሚጠየቀዉን ዋስትና ያላቀረበ እንደሆነ ንብረቱ ተከብሮ እንዲቆይ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ መስጠት የሚችል መሆኑን የሚያስገነዝብ ነዉ፡፡በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 153/5 መሰረት ለከሳሽ የተፈረደለት እንደሆነ፣ ከሳሹ ለፍርዱ አፈፃፀም ንብረት እንዲከበር ሌላ ማመልከቻ ማቅረብ ሳያስፈልገዉ አፈፃጸሙ በተያዘዉ ንብረት (በተከበረዉ ንብረት) ላይ እንዲቀጥል ማድረግ ይቻላል፡፡ የእነዚህ ድንጋጌዎች አፈጻጸምና ሕጋዊ ዉጤት በተመለከተ ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 173079 ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

ከላይ እንደተመለከተዉ በያዝነዉ ጉዳይ የአመልካች የተጠሪ ገንዘብ ይታገድልኝ ጥያቄ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 154 ተጠቅሶ የተጠየቀና የሥር ፍርድ ቤትም በዚሁ ድንጋጌ መሰረት የዕግድ ትእዛዝ የሰጠ ቢሆንም የአመልካች ጥያቄ ዓላማዉ የሚፈረድለት ቢሆን በተከበረዉ በተጠሪ ሒሳብ ዉስጥ በሚገኘዉ ገንዘብ ፍርዱን ማስፈጸም እንዲችል ዋስትና ይሆንለት ዘንድ ነዉ፡፡ ለተጠሪ በባንክ ዘንድ ያለዉ ገንዘብ ተከብሮ እንዲቆይ እንዲታዘዝለት አመልካች የጠየቀበት ዓላማ ይህ ከሆነ ገንዘቡ ተከብሮ እንዲቆይ ከመታዘዙ በፊት ተጠሪ የመንግስት አስተዳደር መስሪያ ቤት እንደመሆኑ እንደመንግስት አካል ለወደፊት ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ለአመልካች እንዲከፍል የሚወሰንበት ቢሆን ገንዘቡን መክፈል ይችላል ወይስ አይችልም የሚለዉ መመርመር ነበረበት፡፡ እንዲሁም እንዲህ አይነት ገንዘብ ወይም ንብረት እንዲከበር የሚሰጥ ትእዛዝ በዘፈቀደ በተጠየቀ ቁጥር የሚሰጥ ሳይሆን የአሁን ተጠሪም ሆነ ተከሳሽ የሆነ ወገን እንዲታገድ የጠየቀበትን ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ከፍርድ ቤቱ የዳኝነት ሥልጣን ክልል ዉጭ ወዴት ለማሸሽ እንዳቀደ ወይም እንዳሸሸ አሳማኝ ምክንያት መኖሩን ማረጋገጥ ይገባል፡፡ በተለይም በመንግስት አካልነቱ የሚታወቅ መሥሪያ ቤት ዋስትና እንዲያቀርብ የሚጠየቅበት ሕጋዊ ምክንያትና አመክንዮ የለም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በባንክ ያስቀመጠዉ ገንዘብ እንዲከበር በስር ፍርድ ቤት የተሰጠዉ ትእዛዝ እንዲነሳለት አቤቱታ ያቀረበበት ትእዛዝ ልክ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 154 ስር በተደነገገዉ መሰረት የሚሰጥ ጊዜያዊ እግድም ሆነ ቢበዛ

ፍርድ እስከሚሰጥ ድረስ ካልሆነም ፍርዱ ከመሰጠቱ በፊት በማንኛውም ጊዜ ሊነሳ የሚችል ቢሆንም እንኳን በግራ ቀኙ ጥቅምና በአጠቃላይ የክርክር ሂደትና ኢኮኖሚው ላይ ከሚያስከትለው ውጤት አንጻር ሲታይ በዋናው ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ በመጠበቅ ከዋናው ጉዳይ ጋር ይግባኝ የሚባልበት ነው የሚባል ሳይሆን እንደመጨረሻ ውሳኔ የሚቆጠርና በዚያው ፍርድ ቤት እንደገና እንዲታይ በተዘረጋው ሥርዓት መሰረት እንደገና እንዲታይ ከተደረገ በኋል ይግባኝ ሊባልበት የሚችል ነው።እንዲሁም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 158 መሰረት ጊዜያዊ የእግድ ትእዛዝ እንዲነሳ ትእዛዙን ለሰጠው ፍርድ ቤት አቤቱታ የሚቀርብበት ምክንያት ጊዜያዊ እግድ ፀንቶ እንዲቀጥል፣እንዲነሳ ወይም እንዲሻሻል የሚያደረግ ምክንያት መኖር አለመኖሩን ጉዳዩ ከሚፈልገው አጣዳፊነት በህርይ የተነሳ ራሱ ፍርድ ቤቱ ትእዛዙን እንደገና ተመልክቶ በትእዛዙ ላይ ይግባኝ ከመባሉ በፊት እንዲመረምር ሥርዓት ለመዘርጋት እንጂ ይግባኝ እንዳይቀርብበት ለመከልከል ባለመሆኑ ጊዜያዊ እግዱ እንዲነሳ ትእዛዙን ለሰጠው ፍርድ ቤት አቤቱታ ቀርቦ ተቀባይነት ባያገኝ እንኳን ይግባኝ ከማቅረብ የሚያግድ የሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌ የለም። ይህ የያዝነው አይነት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 151 መሰረት ከፍርድ በፊት ለክርክሩ መነሻ ያልሆነውን ንብረት(ገንዘብ) በማስከበር የሚሰጥ ትእዛዝ ደግሞ በሕጉ በቁጥር 153/5 አነጋገር መሰረት እስከ ፍርድ አፈጻጸም ድረስ ፀንቶ ሊቆይ የሚችል በመሆኑና ትእዛዙ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ከሚያስከትለው ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ውጤት እና የሚታገደውም ንብረት(ገንዘብ) ለክርክሩ መነሻ ያልሆነ ከመሆኑ አንጻር ሲታይ በዋናው ጉዳይ ላይ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ተጠብቆ ይግባኝ የሚባልበት ነው ወይም እንደጊዜያዊ ትዕዛዝ(interlocutory decision/order) የሚቆጠር ነው የሚባል አይደለም።ስለሆነም በዋናው ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ሳይጠበቅ ይግባኝ ሊባልበት የሚችል ትእዛዝ ነው በማለት አመልካች ከዚህ አኳያ ያቀረበውን ክርክር አልተቀበልንም።

ሲጠቃለል የስር ፍርድ ቤት በተጠሪ የሥራ ማስኬጃ የባንክ ሂሳብ ውስጥ የተቀመጠው ገንዘብ ታግዶ ወይም ተከብሮ እንዲቆይ ትእዛዝ ሲሰጥ መሰረት ያደረገው የሥነ ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌም ሆነ ተጠሪ እግዱ እንዲነሳ ሲያመለክት እግዱ አይነሳም ብሎ የተጠሪን አቤቱታ ውድቅ ሲያደርግ መሰረት ያደረገው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 154 እና 158 ለጉዳዩ ተገቢነት ያላቸው ድንጋጌዎች ካለመሆናቸውም በተጨማሪ በተጠሪ ሂሳብ ውስጥ ያለው ገንዘብ እንዲታገድ ያዘዘውም ያለሕጋዊ ምክንያት በመሆኑ ሊታረም የሚገባው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው።እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ችሎት የስር ፍርድ ቤትን ትእዛዝ ሲሽር እነዚሁን

ለጉዳዩ አግባብነት የሌላቸዉን ድንጋጌዎች መሰረት ማድረጉ በአዋጅ ቁጥር 2(4/ለ) እና 10(1/ለ) በተደነገገዉ መሰረት ሊታረም የሚገባዉ መሠረታዊ የሆነ የሕግ አተገባበር ጉድለት ነዉ፡፡ሆኖም ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በተጠሪ የባንክ ሂሳብ ዉስጥ የተቀመጠዉ ገንዘብ እንዲታገድ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠዉን የእግድ ትእዛዝ በማንሳት የሰጠዉ ዉሳኔ ከዉጤት አንጻር ሲታይ ተገቢ በመሆኑ የሚከተለዉን ወስነናል፡፡

<u>ዉ ሳ ኔ</u>

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 195667 ላይ በቀን 30/06/2013ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ፀንቷል፡፡

ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ደረጃ ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ብለናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
በመዝገቡ ላይ የተሰጠ የዕግድ ትእዛዝ ካለ ተነስቷል፤ይጻፍ፡፡**መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

መ/ቁጥር 221472

ህዳር 30 ቀን 2015

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ሌሊሴ ደሳለኝ

ደጀኔ አያንሳ

ሀብታሙ እርቅይሁን

እስቲበል እንዱዓለም

አመልካች፡ 1.ወ/ሮ ሐረግነሽ መኮንን -- አልቀረቡም

2. ኢ/ር ጌታቸዉ እሸቱ ደጀኔ -- አልቀረቡም

ተጠሪ፡ አቶ ዓለም ገ/ሚካኤል ገብራት -- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቶበታል

<u>ፍርድ</u>

ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 275555 ላይ በ 24/03/2014 ዓ.ም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ 62359 በ11/10/2013 ዓ.ም የሰጠዉን ዉሳኔ በትዕዛዝ በማጽናቱ ዉሳኔዉ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲታረምላቸዉ የሰበር አቤቱታ የካቲት 14 ቀን 2014 ዓ.ም በተጻፈ በማቅረባቸዉ ነዉ፡፡

ጉዳዩ የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ አመልካቾች እንደቅደም ተከተላቸዉ 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች አሁን በዚህ ሰበር ክርክር የክርክሩ ተካፋይ

ያልሆኑ የቂርቆስ ክ/ከ የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ ፕሮጀክት ጽ/ቤት 3ኛ ተከሳሽ የቂርቆስ ክ/ከ መሬት ባንክና ማስተላለፍ ጽ/ቤት 4ኛ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቤት ክርክር ሲሆን የጉዳዩ መነሻ የሆነዉ በተጠሪ በኩል በ20/04/2012 ዓ.ም በተጻፈ አሻሽለዉ ያቀረቡት ክስ ነዉ፡፡ ይዘቱም፡ በቀድሞዉ አጠራር ዞን 3 ወረዳ 18 ቀበሌ 36 የቤት ቁጥር 766(1) በአሁን አጠራር ቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 2 የቤት ቁጥር 766(1)የሆነ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ስፋቱ 206 ካ.ሜትር ላይ ግብር የከፈሉበት ይዞታቸዉ የሆነዉን ተጠሪ በትዉልድ ኤርትራዊ በመሆናቸዉ በ1993 ዓ.ም በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ምክንያት ከሀገር የወጡ መሆኑን በኢትዮጲያ እና ኤርትራ መካከል በተፈጠረዉ መልካም ግንኙነት ንብረታቸዉን ለመመለስ በመመሪያ የወጣ መሆኑን ይህ ይዞታ የተጠሪ የግል ንብረት መሆኑን እራሱን ችሎ መልማት የሚችል ይዞታ የስር ፍርድ ቤት 3ኛ ተከሳሽ መመሪያ 18/2006 አንቀጽ 5 በመተላለፍ በስር ፍርድ ቤት 4ኛ ተከሳሽ የነበረዉ አላግባብ የአመልካችን ይዞታ አካቶ የሊዝ ዉል ያደረጉ መሆኑን ጠቅሶ የሊዝ ዉሉ ፈርሶ ይዞታቸዉ የሆነዉ የቤት ቁጥር 766 በማካተት የተሰራ ካርታ ካለ መክኖ አመልካቾች ይዞታዉን እንዲያስረክቡ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

አመልካቾችም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና በዋናዉ ጉዳይ ላይ መልስ በ 06/05/2012 ዓ.ም በተጻፈ አቅርበዋል ፡፡ ይዘቱም ተጠሪ ኤርትራዊያን ወደ ሀገራቸዉ ሲሄዱ ንብረታቸዉን ሸጠዉ ወይም ለሀጋዊ ወኪሎቻቸዉ ሰጥተዉ እንዲሄዱ በወቅቱ መመሪያ መንግስት ያወጣ ቢሆንም ተጠሪ ህጋዊ ካርታና ቤት የሌላቸዉ በመሆኑ ይህንን ማድረግ አልቻሉም፤ የቤቱን ካርታና ፕላን እንደማስረጃ አላቀረቡም፤ ይዞታዉን በሊዚ ዉል ከተረከብን በኋላ ግብር ከፈልኩ ያሉት በተጭበረበረ መንገድ ነዉ፤ ተጠሪ 206 ካ.ሜትር ይዞታ የላቸዉም፤ ተጠሪም ወኪላቸዉ የዉጭ ዜጋ ስለሆኑ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት ሊሆኑ አይችሉም፤ የቤት ቁጥር 766(1) አለኝ ያሉት ሀሰት ነዉ፤ ይዞታዉን አመልካቾች በህጋዊ የሊዝ ዉል ያገኘን በመሆኑ ክሱ ዉድቅ ይሁን ሰሉ ተከራክረዋል፡፡

በስር ፍርድ ቤት 3ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች የነበሩት በ06/05/2012 ዓም በተጻፈ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና በዋናዉ ጉዳይ ላይ መልስ አቅርበዋል፡፡ይዘቱም፡ምን ያህል ካሬ ሜትር ከይዞታቸዉ እንደተቀነሰ አልገለጹም፤አመልካቾች ይዞታዉ በሊዝ ዉል ይካተትልኝ ጥያቄ አቅርበዉ የድንበር ክርክር ያለበት በመሆኑ በዚህ ይዞታ ላይ የተዘጋጀ ካርታ የለም፤በመሆኑ ከተጠሪ ላይ ቀንሰን ለአመልካቾች የሰጠነዉ ይዞታ የለም በሚል ተከራክረዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤትም የቀረበዉን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ዉድቅ በማድረግ ግራ ቀኙን በቃል ካከራከረ በኋላ ከአመልካቾች ጋር የተደረገዉ የሊዝ ወል ከመመሪያ ዉጭ የተደረገ በመሆኑ ፈራሽ ነዉ ከተካተተላቸዉ ይዞታ ዉስጥ 206 ካ.ሜትር ቦታ አመልካቾች ለተጠሪ እንዲያስረክቡ ወጭና ኪሳራ አጠቃላይ ብር 37,350 ዉሳኔ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ በ9% ወለድ አመልካቾችን ጨምሮ ተከሳሾች እንዲከፍሉ በመዝገብ ቁጥር 62359 ላይ በ11/10/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት ፍርድ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾች ይህንን ዉሳኔ ተቃዉመዉ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታ ያቀረቡ ሲሆን ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 275555 ላይ በ24/03/2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የይግባኝ ቅሬታቸዉን ሰርዟል፡፡ በአመልከች በኩል ለዚህ ፍርድ ቤት ያቀረበዉ የሰበር አቤቱታም በስር ፍርድ ቤት የተሰጡት ዉሳኔዎች መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልን በሚል ምክንያታቸዉን በመጥቀስ የካቲት 14 ቀን 2014 ዓ.ም በተጻፈ አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም፡አከራካሪ የሆነዉ ይዞታ ባዶ የመንግስት ይዞታ ሆኖ ባለዉ መመሪያ መሰረት በሊዝ ዉል ካርታ አዉጥተዉበት እየተገለገሉ ያሉ ተጠሪ የዉጭ ዜጋ ሆነዉ የማይንቀሳቀስ ንብረት በኢትዮጲያ ዉስጥ ማፍራት የማይችሉ መሆኑን ጠቅሰን ክርክር አቅርበን ባለንበት የስር ፍርድ ቤት የሊዝ ዉሉ ይቋረጥ ይዞታዉን አስረክቡ በማለት ወጭና ኪሳራ እንድንከፍል መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልን ሲሉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አጣሪ ችሎትም የቀረበዉን የሰበር አቤቱታ መርምሮ የግራ ቀኙን ክርክር በተመለከተ የስር ከሳሽ የአሁን ተጠሪ ሆነዉ በአሁን አመልካቾች በስር 3ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች ላይ ባቀረቡት ክስ ፍርድ ቤቱ በሠጠዉ ዉሳኔ የአሁን አመልካቾች ይግባኝ ጠይቀዉ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ቅሬታቸዉን ባለመቀበል ዉድቅ ሲያደርግ የሥር 3ኛና 4ኛ ተከሳሾች ባቀረቡት የይግባኝ ቅሬታ መነሻነት ደግሞ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የሥር ዉሳኔን በመሻር ዉሳኔ በመሰጠቱ በአንድ ጉዳይ ሁለት ዉሳኔ ያለበት በመሆኑ በአንድ ጉዳይ ላይ ሁለት ዉሳኔ ሊኖር የቻለበት አግባብ ለማጣራት በሰበር ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

በዚሁ መሠረት ተጠሪ ነሐሴ 18 ቀን 2014 ዓ.ም በተጻፈ የጽሑፍ ክርክር ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፡ በስር ፍርድ ቤት 3ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች ባቀረቡት የይግባኝ ቅሬታ መነሻነት ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የፌዴራል የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በሻረዉ ላይ በሰበር ችሎት በመቁ፣233206 ላይ ሰበር አቤቱታ ያቀረቡ መሆኑን በይግባኝ ጉዳዩን ያየዉ ፍርድ ቤት

የአመልካቾችን የይግባኝ ቅሬታ መሰረዙ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ዉሳኔ አለመሆኑን ገልጸዉ ተከራክረዋል፡፡

አመልካቾች የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸዉን በማጠናከር አቅርበዉ በስር ፍርድ ቤት 3ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች ያቀረቡት ይግባኝ ክርክር ላይ ተሳታፊ ያልነበሩ መሆኑን ከአመልካቾች ጥያቄ ዉጭ መሆኑን ገልጸዉ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከግራ ቀኙ የቀረበዉ ክርክር ከፍ ሲል የተገለጸዉን ሲመስል ይህ ፍርድ ቤትም የቀረበዉን ሰበር አቤቱታ ከማስቀረብያ ጭብጥ አኳያ መርምረናል፡፡ ምላሽ የሚሻዉ ጉዳይ በአንድ ዉሳኔ ላይ ሁለት ተከራካሪ ወገኖች በተለያዩ መዝገቦች ይግባኝ አቅርበዉ ሁለቱ መዝገቦች ሳይጣመሩ የተለያየ ዉሳኔ ከተሰጠ ዉጤቱ ምን ይሆናል የሚል ሆኖ ተገኝቷል፡፡ አንድ ፍርድ ቤት ከአንድ ዉሳኔ ተከራካሪ ወገኖች በተለያየ መዝገብ የይግባኝ ቅሬታ ያቀረቡ ከሆነ ፍርድ ቤት በፍ/ስ/ስ/ህግ /ቁጥር 11(5)መሰረት አጣምረዉ ጉዳዩን ማስተናገድ ያለባቸዉ ስለመሆኑ ከህጉ ንባብ መረዳት ይቻላል፡፡ የስነ ስርዓቱ ህጉ ዓላማም በአንድ ዘንግ ከሚመደቡ ተከራካሪዎችና በአንድ ጭብጥ ላይ የሚቀርቡ ክርክሮች ተጣምረዉ እንዲታዩ የሚደነግግ በተመሣሣይ ጉዳይ እና ጭብጥ በተለያዩ ችሎቶች የተለያየ ዉሣኔ እንዳይሰጡ ለመከላከል የስራ ቅልጥፍና እና የዉሣኔ ወጥነትን ለማረጋገጥ ነዉ፡፡ ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመጣ በግራ ቀኙ መካከል ባለዉ ክርክር በፈዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተሰጠዉ ዉሳኔ አመልካቾች ባቀረቡት የይግባኝ ቅሬታ በመዝገብ ቁጥር 275555 ላይ አያስቀርብም በሚል የይግባኝ ቅሬታቸዉ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 የተሠረዘ ሲሆን በስር ፍርድ ቤት 3ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች በነበሩት ባቀረቡት የይግባኝ ቅሬታ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ 290602 ሽሮ ጉዳዩ እስከ ሰበር ችሎት ታይቶ አያስቀርብም በሚል ትዕዛዝ የተሰጠ ስለመሆኑ መዝገብ ቁጥር 233206 አስቀርበን ተረድተናል፡፡ ለዚህም ምክንያት የሆነዉ መዝገቦቹ በተለያየ ችሎት በመቅረባቸዉ እርስ በእርሱ የሚጋጭ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ሁለቱን የይግባኝ መዝገቦች ተጣምረዉ እንድታዩ አለማድረጉ አመልካቾች ያቀረቡት የይግባኝ ቅሬታ ሲሰዘረዝ በ3ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች ባቀረቡት የይግባኝ ቅሬታ መነሻነት የፈዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን ዉሳኔ ሽሯል፡፡ ዉሳኔዉም እስከ ሰበር ችሎት ፀንቷል፡፡ እንድዲህ ዓይነት ሁኔታ ሲከሰት ለአፈጻፀም እንዳያስቸግር ማስተካከያ ሊደረግ እንደሚገባ የፈዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 40024 ላይ ሚያዚያ 29 ቀን 2001 ዓ.ም ገዥ ዉሳኔ ሰጥቷል፡ ስለሆነም በተለያዩ

መዝገቦች ላይ በአንድ ጉዳይ ላይ የተለያዩ ዉሳኔዎች መስጠቱ የሥነ ስርዓት ግድፈት የተፈፀመበት ነዉ ብለናል፡፡

ቀጣዩ ጭብጥ መታየት ያለበት የዉሳኔዉ ዉጤት ከአመልካቾች አንፃር ምን ሊሆን ይገባል የሚለዉ ነዉ፡፡ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 62359 ላይ በ11/10/13 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በስር ፍርድ ቤት 3ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች አቅራቢነት በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 290602 በ13/04/2014 ዓ.ም ተሽሮ እስከ ሰበር መሠረታዊ የህግ ስህተት አልተፈጸመበትም በሚል በመዝገብ ቁጥር 233206 ላይ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡ በከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠዉ ዉሳኔ የፀና ዉሳኔ ነዉ፡፡ ፍርድ ቤት ደግሞ ሁለት የተለያዩ ዉሳኔዎች ከተሰጡ ዉሳኔዎቹ ሊፈፀሙ በሚችሉበት ሁኔታ ማስተካከያ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በዚህ ረገድም የፍርድ ቤቶች ሚና ትልቅ ነዉ፡፡ አመልካቾች ይሻርልን መብታችን ተነክቷል የሚሉት ዉሳኔ በሌላ መዝገብ ከፍ ሲል በተገለጸዉ ላይ ተሸሯል፡፡ በፍርዱ አመልካቾች ተጠቃሚ ናቸዉ፡፡ ከፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ዓላማ እና አቀራረፅ አንፃር ወደ ዋናዉ ጉዳይ መግባት ሳያስፈልግ አመልካቾች ባቀረቡት የይግባኝ ቅሬታ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በትዕዛዝ በማፅናት የሰጠዉ ሊሻር ይገባል ብለናል፡፡

ሲጠቃለል እርስ በእርሱ የሚጋጩ ዉሳኔዎች የተሰጡ በመሆኑ አንዱ ዉሳኔ እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፀና በመሆኑ ሌላዉ ዉሳኔ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾች የይግባኝ ቅሬታ አቅርበዉ በትዕዛዝ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ የፀናበት ዉሳኔ ሊሻር ይገባል በሚል ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 275555 ላይ 24/03/2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 348(1) መሠረት ተሸሯል፡፡

2. በዚህ ችሎት ለተደረገዉ ክርክር ላስከተለዉ ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

3. መዝገብ ቁጥር 233206 ወደ መጣበት ይመለስ፡፡

መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ በመሆኑ ተዘግቷል፡፡ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰበር መዝገብ ቁጥር 158462

ታህሳስ 11 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች-፡ አልማው ወሌ

መስጠፉ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡-አቶ ጠሃ አብዶ - ቀረቡ

ተጠሪ፡-አቶ አብደላ ከዲር - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጽሁፍ መልስ የመስጠት መብቱ የታለፈበት ተከሳሽ ወገን ክሱ በሚሰማበት ቀነ ቀጠሮ ቀርቦ የሚያነሳው የይርጋ መቃወሚያ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችል መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ክርክር ሲሆን አመልካቹ የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት ክሱን በይርጋ ውድቅ በማድረግ በጀጁ ወረዳ ፍርድ በመዝገብ ቁጥር 21277 በ05/11/2009 ዓ.ም ተሰጥቶ በአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት እንደቅደም ተከተላቸው በመዝገብ ቁጥር 77305 በ02/02/2010 ዓ.ም እና በመዝገብ ቁጥር 277836 በ15/06/2010 ዓ.ም. በተመሳሳይ ሁኔታ በትዕዛዝ የጸናው ብይን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ አመልካች የጠየቁት የአያታቸው ወ/ሮ ሱሪ ኑራ ውርስ በይርጋ ይታገዳል በሚል ተጠሪው መቃወሚያ ባላቀረቡበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤት የአመልካቹ የተተኪ ወራሽነት ጥያቄ በይርጋ ይታገዳል በማለት የመወሰኑን አግባብነት ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር

ተለዋውጠዋል።የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ብይን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል።

በዚህም መሰረት በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 231 መሰረት ያልተሰረዘ የክስ ማመልከቻ እንዲሁም ተያይዞ የቀረበው ማናቸውም አስረጂ እና የጽሁፍ ግልባጭ ከመጥሪያው ጋር ተያይዞ ለተከሳሽ ወገን ሊላክ የሚገባው ስለመሆኑ በቁጥር 233 ድንጋጌ የተመለከተ ሲሆን በዚህ አግባብ የክስ ማመልከቻ እና ማስረጃ ግልባጭ የተላከለት ተከሳሽ ወገንም በሚያቀርበው መልስ ውስጥ ክሱ በይርጋ ይታገዳል የሚል ከሆነ ይህ የተባለበትን ዝርዝር ምክንያት የሚገልጽ ጽሁፍ የማቅረብ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ በስነ ስርዓት ሕጉ በቁጥር 234 (1) (ሐ) ስር ተመልክቶአል።የጽሁፍ ልውውጡ ተከናውኖ ጉዳዩ ክስ ለመስማት በተቀጠረ ጊዜም ተከሳሹ የይርጋ መቃወሚያን በመከራከሪያነት አንስቶ መከራከር የሚችለው የጽሁፍ መልሱን ሰጥቶ ከሆነ እና የይርጋ መቃወሚያውንም በጽሁፍ መልሱ ውስጥ አካቶ አቅርቦ ከሆነ ነው።ተከሳሹ በተያዘለት ቀነ ቀጠሮ የጽሁፍ መልሱን ባለማቅረቡ መብቱ የታለፈ ከሆነ ወይም መልሱን አቅርቦ ነገር ግን በጽሁፍ መልሱ ውስጥ የይርጋ መቃወሚያን ያላካተተ በሆነ ጊዜ ክሱ በሚሰማበት ቀን የይርጋ መቃወሚያን በመከራከራነት ሊያነሳም ሆነ በዚህ አግባብ የሚነሳው ይርጋ መቃወሚያ በፍርድ ቤቱ ሊስተናገድ የሚችልበት ስነ ስርዓታዊ አግባብ የለም።

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪው በተያዘላቸው ቀነ ቀጠሮ የጽሁፍ መልስ ይዘው ባለመቅረባቸው የጽሁፍ መልስ የመስጠት መብታቸው በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 199 ድንጋጌ መሰረት የታለፈ መሆኑን የወረዳው ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ ያመለክታል።ይህንን ትዕዛዝ አስነስተው የጽሁፍ መልስ እንዲያቀርቡ የተደረገ ስለመሆኑ የመዝገቡ ግልባጭዐም ሆነ የተጠሪው የሰበር መልስ የሚጠቀሙት ነገር የለም።የጽሁፍ መልስ የመስጠት መብቱ የታለፈ ተከሳሽ ክሱ በሚሰማበት ቀነ ቀጠሮ ቀርቦ የሚያነሳውን ይርጋ መቃወሚያ ተቀብሎ ማስተናገድ በስነ ስርዓት ሕጉ የተመለከተውን የክርክር አመራር ስርዓት የሚቃረን እና ክርክሮችን የሚያወሳስብ በመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ አይደለም።

ሲጠቃለል የወረዳው ፍርድ ቤት የተጠሪው የጽሁፍ መልስ የመስጠት መብት በታለፈበት ሁኔታ ክሱ በሚሰማበት ቀን ቀርበው ያነሱትን የይርጋ መቃወሚያ ተቀብሎ በማስተናገድ የሰጠው ብይንም ሆነ ብይኑን በማጽናት በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት እና ሊታረም የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል።

ው ሳ ኔ

በጀጁ ወረዳ ፍርድ በመዝገብ ቁጥር 21277 በ05/11/2009 ዓ.ም. ተሰጥቶ በአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት እንደቅደም ተከተላቸው በመዝገብ ቁጥር 77305 በ02/02/2010 ዓ.ም እና በመዝገብ ቁጥር 277836 በ15/06/2010 ዓ.ም በተመሳሳይ ሁኔታ በትዕዛዝ የጸናው ብይን በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሮአል፡፡

የጽሁፍ መልስ የመስጠት መብቱ የታለፈ ተከሳሽ ክሱ በሚሰማበት ቀነ ቀጠሮ ቀርቦ የሚያነሳው የይርጋ መቃወሚያ ሊስተናገድ የሚችልበት ስነ ስርዓታዊ አግባብ የለም በማለት ወስነናል፡፡

መዝገቡን በማንቀሳቀስ የግራ ቀኙን የፍሬ ነገር ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ በፍትሐብሔር በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 341 (1) መሰረት ለጀጁ ወረዳ ፍርድ ቤት እንዲመለስ ወስነናል፡፡

በውሳኔው መሰረት ተገቢውን መፈጸም ያስችለው ዘንድ የውሳኔው ግልባጭ ለጀጁ ወረዳ ፍርድ ቤት፤እንዲያውቁት ደግሞ ለአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ይላክ፡፡

የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝጉ ተዘግቶአል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሰ/መ/ቁ፡-202737

ቀን፡-29/03/2014ዓ.ም

ዳኞች፡ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡ አቶ ረጋሳ ጉርሙ ጠበቃ ጋዲሳ ቡታ ቀረቡ

ተጠሪ፡ ወ/ሮ ዘነበች ገ/መንፈስ- ጠበቆች ዘበነ ፍቅሬ እና አዲሱ አየነው ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ያለፍርድ ቤት ፈቃድ በተወዉ ጉዳይ ላይ የቀረበዉ ክስ ተቀባይነት የለዉም ተብሎ የተሰጠዉን ብይን ለማስለወጥ ነዉ፡፡የክርክሩ መነሻ የቤት ሽያጭ ውል የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ላይ የአሁኑ አመልካች ከሳሽ በመሆን የአሁኑ ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ተጠሪ ከሟች ባለቤታቸው አቶ ተሾመ አፈወርቅ ጋር በመሆን በቀን 06/12/1996 ዓ.ም በአ/አ/ከ/ቂ/ክ/ከተማ ወረዳ 02 የቤት ቁጥር 047 የካርታ ቁጥር ሴ.ኬ.አሲ/02/31/1229/001040/01 የሚታወቅ መኖሪያ ቤት ለአመልካችና ለአቶ ፀጋዬ ገ/መንፈስ ሽጠዋል፣ቤቱን እንዲለቁ ሲጠየቁ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/153563 ቤትን አንዲለቁልኝ ክስ አቅርቤ ፍ/ቤቱን አስፈቅጄ ያነሳሁት ቢሆንም ተጠሪ ቤቱን ለመልቀቅ ፈቃደኛ ስላልሆኑ ተጠሪ ቤቱን ለቀው እንዲወጡና እንዲያስረክቡኝ እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋዋል፡፡ተጠሪ በበኩላቸዉ በቀን 12/05/2012 ዓ.ም ጽፈው ባቀረበውት መልስ አመልካች በመ/ቁ.153563 ላይ ቤቱን ከተጠሪ ለመረከብ ተመሳሳይ ክስ አቅርቦ አመልካቹ በውሉ በተመለከተው ጊዜ የሽያጭ ገንዘቡን ባለመክፈሉ የውል ግዴታውን ስላልተወጣ የባለቤትነት መብት ስለሌው ለቀን ልናስረክብ እንደማይገባ መከራከሪያ አቅርበን እያለ አመልካች በቀን 10/04/2011ዓ.ም በፍ/ስ/ስ/ሀ/ቁ.278 መሰረት በፈቃዱ ክሱን ለመተው ማመልከቻ አቅርቦ ፍ/ቤቱም በ11/04/2011ዓ/ም ከሻስ ክስ በማቋረጡ

ለተጠሪ ወጪና ኪሳራ እንዲከፍል በማለት መዝገቡን ዘግቷል፣ስለሆነም ያለፍርድ ቤት ፈቃድ በተወዉ ጉዳይ አዲስ ክስ ማቅረቡ ተገቢ አይደለም፣በተጨማሪም የቤት ሽያጭ ውሉ ተፈጽሟል የተባለዉ ከ16 እና ከ17 ዓመታት በፊት ስለሆነ በፍ/ህ/ቁ/1845 መሰረት በ10 ዓመት ይርጋ ይታገዳል፣እንዲሁም በፍ/ህ/ቁ. 2892(3) መሰረት ሻጩ ውሉን እንደ ውሉ ቃል ከመፈፀም መዘግየቱን ከተረዳበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 1(አንድ) ዓመት ድረስ ውሉ እንዲፈፀምለት ካልጠየቀ በቀር ገዢው ውሉ በግዴታ እንዲፈፀም የማድረግ መብቱን ያጣል፣ስለዚህ በ1 (አንድ) ዓመት ውስጥ ስላልጠየቀ በይርጋ ውድቅ ይደረጋል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና በፍሬነገር ረገድ አማራጭ ክርክር ማቅረባቸዉን መዝገቡ ያሣያል፡፡

ፍ/ቤቱም በተጠሪ በኩል የቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ የግራ ቀኝ ክርክር ሰምቶና መርምሮ በመጀመሪያዉ ክስ አመልካች ክሱ እንዲቋረጥ አቤቱታቸውን ሲያቀርቡ ሌላ ጊዜ ክስ ለማቅረብ ፍርድ ቤቱ እንዲፈቀድላቸው የጠየቁ ሳይሆን ክርክሩ እየገፋ በመምጣቱ ውጣ ውረዶች ስለበዛባቸው ክሱን ማቋረጥ እንደፈለጉ የሚያሳይ ነው፡፡ፍ/ቤቱም ከሳሽ(የአሁኑ አመልካች) ያቀረቡትን አቤቱታ በመቀበል ከሳሽ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 278 /2/ መሰረት በማየት ጉዳዩን በተመለከተ አዲስ ክስ እንዲያቀርቡ አልፈቀደም፡፡እንዲህ ከሆነ አመልካች ክሱን የተውት ከፍ/ቤት ፈቃድ ውጭ እንደሆነና አመልካች አስፈላጊውን ኪሳራ ለተጠሪ ከፍለው መዝገቡ መዘጋቱን እንዲሁም አመልካችም ጉዳዩን በተመለከተ አዲስ ክስ ማቅረብ እንደማይችል በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.279(1) ስር ተደንግጓል፣ስለዚህ አመልካች አሁን አዲስ ክስ ማቅረባቸው በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 278(2) እና 279(1) መሰረት አግባብነት የለውም በማለት ክሱን ውደቅ አድርጓል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ ይግባኙ አያስቀርብም በማለት በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 337 መሰት መዝገቡን ዘግቷል፡፡የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ነዉ፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ይዘት ባጭሩ፤ቤቱን እንዲለቁልኝ ሲጠይቅ ተጠሪ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው በከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ.153563 ላይ ክስ መስርቼ ስንከራከር ከቆየን በኋላ ፍ/ቤቱን አስፈቅጄ ክስ ያቋረጥኩበት ምክንያት ተጠሪ የባለቤቱ እህት በመሆናቸው እና ተጠሪ የሽያጭ ውል ይፍረስልኝ ጥያቄም ውሉ ህጋዊ ነው ተብሎ ስለተወሰነ ከዚህ በኋላ ተጠሪ አለቅም የሚሉበት ምንም ህጋዊ ምክንያት የለም በፈለኩ ጊዜ ይለቁልኛል በሚል እሳቤ ፍ/ቤት አስፈቅጄ ክሱ ተቋርጧል፡፡

ፍ/ቤት ሳላስፈቅድ በራሴ ፈቃድ ለመተው ቢፈልግ ኖሮ ፈቃድ ለመጠየቅ አቤቱታ ለፍ/ቤት ባላቀረብኩ ነበር፡፡የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 279(1) የሚመለከተው በራሱ ፈቃድ ፍ/ቤትን ሳያስፈቅድ ክሱን የተወ ወይም ያቋረጠ ከሳሽን ሲሆን እኔ ግን ለፍ/ቤት አመልክቼ ፍ/ቤቱም ክሴን እንዲተው የፈቀደልኝ መሆኑን የቀረበው ማስረጃ ያረጋግጣል፡፡ስለዚህ አዲስ ክስ ማቅረብ አትችልም በማለት የተሰጠው ብይን የንብረት ባለቤት የመሆን መብቴን የሚቃረን ስለሆነ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ብይን ነው በማለት ብይኑ እንዲታረም አመልክተዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ለክርክር ምክንያት በሆነው ቤት ላይ ግራ ቀኙ ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል ሊፈርስ አይገባም በሚል የተሰጠ ውሳኔ ጸንቶ ባለበት ሁኔታ ተጠሪ ቤቱን እንዲለቁ አመልካች በስር ፍ/ቤት ተጠሪ ላይ ያቀረቡትን የክስ አቤቱታ ቀደም ሲል ተጠሪ ቤቱን ይልቀቁልኝ ብለው ክስ አቅርበው በራስዎ ፈቃድ አመለክተው እንዲቋረጥ አድርጓል በማለት አቤቱታቸው ውድቅ የተደረገበትን አግባብነት ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ 278 እና 279 ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ጉዳዩ ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ታዟል፡፡

ተጠሪ በበኩላቸዉ በቀን 30/11/2013ዓ.ም ጽፎ ባቀረቡት መልስ በስር ፍርድ ቤት እየተከራከርን እያለ አመልካች ክሱን መተዋቸውን ለፍ/ቤት አመልክተዋል፣ነገር ግን ወደ ፊት በሙሉ ወይም በከፊል አዲስ ክስ የማቅረብ መብት አልጠየቁም፣አላስጠበቁም፤የጀመርኩት ክስ በሙሉ ፍቃድ ማቋረጠን አረጋግጣለሁ የሚል እንጂ አዲስ ክስ ለማቅረብ አይደለም፣የፍ/ቤቱም ትእዛዝ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 278(1) መሰረት ክስ መቋረጡ ያረጋግጣል፡፡በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 278(1) መሰረት ክስ ሲቋረጥ ወደፊት ክስ ለማቅረብ ያልተፈቀደለት መሆኑን በፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ.116869 እና 158314 ላይ አስገዳጅ ውሳኔ ተሰጥቷል፣አዲስ ክስ ማቅረብ የሚቻለው በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 278(2) መሰረት በፍ/ቤት ፈቃድ ሲቋረጥ ነው፡፡ይርጋን በተመለከተ አመልካች ያቀረበው የመፋለም ክስ ሳይሆን በሽያጭ ውል መነሻ ተገደው ቤቱን እንዲያስረክቡኝ የሚል ስለሆነ እና በስር ፍ/ቤት ያልተነሳና በዚህ ረገድም የህግ ስህተት እንዳልተፈፀመ ስለተረጋገጠ አቤቱታው ውድቅ ሆኖ የስር ፍ/ቤት ውሰኔ እንዲፀና በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካች አቤቱታቸውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ጭብጥ አንጻር የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡መዝገቡ መርምረን እንደተገነዘብነዉ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ተጠሪ የሸጡላቸዉን ቤት ለቀዉ እንዲያስረክቧቸዉ እንዲወሰን የሚል ሲሆን

ከዚህ ቀደም ተመሳሳይ የዳኝነት ጥያቄ በመ/ቁ.153563 ላይ አቅርበዉ አመልካቹ ክሱን ለመተዉ ባቀረቡት አቤቱታ መሰረት መዝገቡ የተዘጋ መሆኑ አላከራከረም፡፡ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም አመልካች ክሱን ሲያቋርጡ አዲስ ክስ እንዲያቀርቡ ፍርድ ቤቱ አልፈቀደላቸዉም በማለት ነዉ፡፡አመልካች አጥብቀዉ የምከራከሩት ክሱን ያቋረጥኩት ፍርድ ቤቱን አስፈቅጀ ስለሆነ አዲስ ክስ ከማቅረብ አያግደኝም በማለት ነዉ፡፡

በህግ በሌላ አካኋን ካልተደነገገ በስተቀር የፍትሓብሔር ክርክር የሚመራዉ በፍትሓብሔር ስነስርዓት ህግ በተደነገገዉ አግባብ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 1 ድንጋጌ ይዘት የምንገዘበዉ ጉዳይ ነዉ፡፡የፍትሓብሔር ስነስርዓት ህግ ዓይነተኛ ኣላማ የፍትሓብሔር ክርክር የሚመራበትን ስርዓት በመደንገግ የፍርድ ሂደት በፍትሃዊነት እንዲመራ በማድረግ የተከራከሪ ወገኖችንም ሆነ የፍርድ ቤቱን ሀብት እና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ ክርክሩ እልባት እንዲያገኝ ማስቻል ነዉ፡፡ይህንኑ ዓላማ ለማስካት ያስችላሉ ተብለዉ ከተዘረጉት ስርዓቶች አንዱ ከሳሽ ወገን በአንድ ጉዳይ ላይ ተደጋጋሚ ክስ እንዳያቀርብ ለመከላከል የተዘረጋዉ ስርዓት የሚመለከት ነዉ፡፡በዚህ መዝገብ ለተያዘዉ ጉዳይ አግባብነት ያለዉ ከሳሽ ወገን ክሱን ለመተዉ መቻሉና ዉጤቱን የሚመለከተዉ ድንጋጌ ነዉ፡፡

አንድ ክስ ከቀረበ በኋላ በማናቸዉም ጊዜ ከሳሹ ያቀረበዉን ክስ በማንሳት ከተከሳሾቹ አንዱን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑትን ከክሱ ዉጭ ለማድረግ ወይም ያቀረበዉን ክስ በሙሉ ወይም በከፊል ለመተዉ የሚችል ስለመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 278/1/ ስር የተመለከተ ሲሆን ፍርድ ቤቱ አቤቱታዉን ተቀብሎ ትእዛዝ በሚሰጥበት ጊዜ ከሳሽ ወገን ክሱን ለማንሳት ወይም ለማቋረጥ የጠየቀበትን ምክንያት መርምሮ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ ከሳሹ አዲስ ክስ ለማቅረብ የሚችልበትን መብት መጠበቅ የሚችል ስለመሆኑ በዚሁ ድንጋጌ ንኡስ አንቀጽ (2) ስር ተመልክቷል፡፡ከዚህ ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለዉ በአንድ በኩል ከሳሹ በግል ጉዳዩ ላይ የመወሰን መብቱን ተጠቅሞ ክሱን ለመተዉ የሚችል መሆኑን በሌላ በኩል ከሳሹ በፈቃዱ በተወዉ ነገር ላይ አዲስ ክስ ለማቅረብ የሚችለዉ ፍርድ ቤት መብቱን የተጠበቀለት ሲሆን ብቻ መሆኑን ነዉ፡፡በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 278/2/ ስር እንደተመለተዉ ከሳሹ በሌላ ጊዜ አዲስ ክስ እንዲያቀርብ ሊፈቅድለት የሚችለዉም በክሱ አቀራረብ ስርዓት ጉድለት ያለበት ሲሆን ወይም አዲስ ክስ ለማቅረብ ሊያስፈቅድለት የሚችል በቂ ምክንያት ሲኖር እና ፍርድ ቤቱ ምክንያቱን ተቀብሎ መብቱን የጠበቀለት እንደሆነ ነዉ፡፡በሌላ አገላለጽ በቁጥር 278/2/ የተነገረዉን ባለመጠበቅ ከሳሹ ከፍርድ ቤት ፈቃድ ሳይቀበል ክሱን በሙሉ ወይም በከፊል

የተወ እንደሆነ አዲስ ክስ ለማቅረብ እንደማይችል በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 289/1/ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ስለዚህም የቀረበዉ አዲስ ክስ ተገቢነት ያለዉ መሆን አለመሆኑ የሚወሰነዉ ክሱ በፍርድ ቤት ፈቃድ ወይም ያለፍርድ ቤት ፈቃድ የተቋረጠ ወይም የተተወ መሆን አለመሆኑ በመመርመር እንደሆነ ያስገነዝበናል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ከስር ፍርድ ቤት መዝገብ ይዘት መገንዘብ እንደተቻለዉ አመልካች ቀደም ሲል በዚሁ ጉዳይ በመ/ቁ/ 153563 ላይ ያቀረበዉን ክስ ለመተዉ መፈለጉን ገልጾ ለፍርድ ቤቱ ባቀረበዉ ማመልከቻ መሰረት መዝገቡ የተዘጋ ስለመሆኑና መዝገቡም የተዘጋዉ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ 278/1/ መሰረት መሆኑን ያመላክታል፡፡የስር ፍርድ ቤትም ይህንኑ መርምሮ አመልካች ክሱን የተወዉ ሌላ ጊዜ አዲስ ክስ ለማቅረብ ከፍርድ ቤቱ ፈቃድ አግኝቶ አለመሆኑንና ያቀረበዉም ማመልካቻ ፈቃድ ለመጠየቅ ሳይሆን ክሱን መቋረጡን ፍርድ ቤቱ እንዲያዉቀዉ ለማድረግ የቀረበ ስለመሆኑ ይዘቱን ጭምር በመመርመር ያረጋገጠዉ ጉዳይ ነዉ፡፡አመልካች አሁንም የሚከራከረዉ ለፍርድ ቤቱ ያቀረበዉ ማመልካቻ ፍርድ ቤቱን ለማሳወቅ ተደርጎ መወሰዱ ስህተት ነዉ የሚል ነዉ፡፡ይሁንና መዝገቡ እንደሚሳየን አመልካች በቀን 10/04/2011ዓ.ም ለፍርድ ቤቱ ያቀረበዉ ማመልከቻ ይዘት ‹‹...ክርክሩ እየገፋ በመምጣቱ ከሳሽ አላስፈላጊ ዉጣ ዉረዶችን በመተዉ የጀመርኩትን ክስ ክርክር በሙሉ ፈቃድ ክሴን ለማቋረጥ ...›› በሚል በቃለ መጎላ ተደግፎ የቀረበ አቤቱታ መሆኑን የሚገልጽ እንጂ በጉዳዩ ላይ ሌላ ጊዜ አዲስ ክስ ለማቀርብ የፍርድ ቤቱን ፈቃድ የጠየቀ መሆኑን የሚያሣይ አይደለም፡፡ክሱን ለማቋረጥ ያቀረበዉም ምክንያትም በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 278/2/ ስር ከተደነገጉት ምክንያቶች አንዱም ስለመኖሩ የማያሳይ ነዉ፡፡ፍርድ ቤቱ ማመልከቻዉን መርምሮ የሰጠዉ ትእዛዝ ይዘትም ክሱ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 278/1 መቋረጡን የሚገልጽ እንጂ አዲስ ክስ ለማቅረብ መብት የተጠበቀለት መሆኑን አያሣይም፡፡የመዝገቡ ይዘት ይህንን የሚያሳይ ሆኖ እያለ አመልካች ፍርድ ቤት ፈቃድ አግኝቻለዉ በማለት ያቀረበዉ አቤቱታ መሰረት ያለዉ ሆኖ አላገኝም፡፡ከዚህ አኳያ በተጠሪ በኩል የቀረበዉን መቃወሚያ መነሻ በማድረግ የስር ፍርድ ቤትም መ/ቁ/153563 ላይ የተጀመረዉ ክርክሩ የተቋረጠበትን አግባብ መርምሮ ከሳሹ ክሱን በራሱ ፈቃድ የተወዉ መሆኑን እንጂ በፍርድ ቤት ፈቃድ የተወዉ መሆኑን የሚያሣይ አይደለም የሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱ ስህተት ነዉ የሚባልበት ምክንያት የለም፡፡እንዲህ በሆነ ጊዜ ደግሞ ከሳሽ ወገን በዚያዉ ጉዳይ ላይ አዲስ ክስ ማቅረብ እንደማይችል የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 289/1 በግልጽ ደንግጓል፡፡የስር ፍርድ ብይን መሰረቱም ይኸዉ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡በመሰል

ክርክሮች ላይ ይህ በሰር ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔም ይህንኑ የሚያጠናክር ነዉ።ሰበር መ/ቁ/116869 ፣158314 እና ሌሎች መመልከት ይቻላል።

ሲጠቃለል በዚህ ጉዳይ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ትእዛዝ ይህንኑ የሥነስርዓት ህግ ድንጋጌ እና በተመሳሳይ ክርክሮች ላይ ሰበር ችሎቱ የሰጠዉን ዉሳኔ ያገናዘበ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚባልበት ምክንያት አልተገኘም።በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል።

<u>ዉሳኔ</u>

1ኛ/የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/236492 ላይ በቀን 29/09/2012ዓ.ም የሰጠዉ ብይን እና ይህንኑ በማጽናት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/194704 ላይ በቀን 30/04/2013ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 348/1/ መሰረት ጽንቷል።
2ኛ/በዚህ ፍርድ ቤት ለተደረገዉ ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል።

<u>መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ።</u>

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

የኢትዮጲያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰ.መ.ቁ 198902

መስከረም 27 **ቀን** 2014 **ዓ.ም**

ዳኞች፡- **እትመት አሠፋ**

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- 1. **ወ/ሮ ካሕሳ ተስፋይ**

2. **አቶ ተስፋይ ንጉሴ** **ቀረቡ**

ተጠሪ፡- ቃለአብ አብርሃ - ጠበቃ ሰለሞን ሀብተየስ - ቀረቡ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች ሕዳር 25 **ቀን** 2013 **ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ** 120444 **የካቲት** 26 **ቀን** 2012 **ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ** 251791 **ሕዳር** 11 **ቀን** 2013 **ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡**

ጉዳዩ የቤት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን ተጠሪ ተክተው የሚከራከሩላቸው ም/ከ/ር አብርሃ እቁባይ ከሳሽ፤ የአሁን አመልካቾች ደግሞ ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የስር ከሳሽ በቀን 20/03/2009 ዓ.ም የተጻፈ የክስ አቤቱታ ካቀረቡ በኋላ ይህ ክስ በቀን 05/07/2010 ዓ.ም የተሻሻለ መሆኑን፤ በቀን 21/06/2011 ዓ.ም ደግሞ በድጋሚ ተሻሽሎ የቀረበ መሆኑን መዝገቡ ያመለክታል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት በሰጠው ፍርድ ላይ ከሳሽ በቀን 05/07/2010 ዓ.ም/ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሻሻለው/ ከመዘገባ በኋላ አሻሽለው ያቀረቡት ክስ ይዘት እና አመልካቾች ለዚሁ ክስ በቀን 05/08/2010 ዓ.ም የሰጡትን መልስ ይዘት ከመዘገበ በኋላ የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ ከከሳሽ በተሰጠ ውክልና መሠረት ቤቱ ከ1ኛ አመልካች ወደ 2ኛ አመልካች በሽያጭ የተላለፈ መሆኑ የተገለጸ ቢሆንም የሽያጭ ውሉ በማስረጃነት አልቀረበም፤ በቤቱ ማሕደር ውስጥ ያሉት ሰነዶች የሚያሳዩት ቤቱ በከሳሽ ስም የሚገኝ መሆኑን እንጂ አመልካቾች አድርገነዋል የሚሉት የሽያጭ ውል የለም፤ ከሚመለከታቸው የአስተዳደር አካላት የቀረቡት የቤቱ ማሕደሮች የቤቱ ባለይዞታ ከሳሽ መሆናቸውን የሚያሳዩ ናቸው፤ ስለሆነም አመልካቾች ቤቱን ለቀው ለከሳሽ ሊያስረክቡ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካቾች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ክሱ ለመጨረሻ ጊዜ የተሻሻለው በቀን 21/06/2011 ነው፤ ክሱ የተሻሻለው ቀደም ሲል ከሳሽ የነበሩት ሰው ስለሞቱ እና ወራሻቸው ስለተተካ ነው፤ ሆኖም በሁለቱም ክሶች ላይ የተጠየቀው ዳኝነት ምንም ዓይነት ለውጥ የሌለው ነው፤ የስር ፍርድ ቤት በቀን 05/07/2010 ዓ.ም የቀረበውን ክስ መነሻ ቢያደርግም ማስረጃው ሲመረመር የአመልካቾች መልስ እና ማስረጃ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ከደረሰበት መደምደሚያ መረዳት ተችሏል፤ አመልካቾች መጋቢት 16 ቀን 2011 ዓ.ም በሰጡት መልስ የሽያጭ ውሉን በማስረጃነት አልጠቀሱትም፤ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት አመልካቾች ቤቱን እንዲያስረክቡ የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው በማለት የአመልካቾችን ይግባኝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት በትዕዛዝ ሰርዞታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- አከራካሪውን ቤት 1ኛ አመልካች ለ2ኛ አመልካች ሠኔ 12 ቀን 2006 ዓ.ም በተደረገ እና በሰነዶች ማረጋገጫ ጽ/ቤት በተመገበ የሽያጭ ውል የሸጡ ስለመሆኑ 2ኛ አመልካች ሚያዝያ 08 ቀን 2010 ዓ.ም ከሰጠሁት መልስ ጋር ተያይዟል፤ ማስረጃው አልቀረበም ቢባል እንኳን ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ሲባል ፍርድ ቤቱ ሊያስቀርበው ይገባ ነበር፤ የስር ፍርድ ቤት የሽያጭ ውሉ በማስጃነት ቀርቦለት ሳለ በግራቀኙ መካከል የሽያጭ

ውል ስለመኖሩ የሚያሳይ ማስረጃ አልቀረበም በማለት ቤቱን ለተጠሪ እንድናስረክብ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በ1ኛ እና በ2ኛ አመልካች መካከል ሰኔ 12 ቀን 2006 ዓ.ም የተፈጸመ የቤት ሽያጭ ውል መኖሩን ሚያዝያ 05 ቀን 2010 ዓ.ም ካቀረቡ መልስ ጋር በማያያዝ ያቀረቡ መሆናቸው በተገለጸበት የሽያጭ ውል አልቀረበም በማለት አመልካቾች ቤቱን ለተጠሪ እንዲያስረክቡ የመወሰኑን አግባብነት ከመሠረታዊ የክርክር አመራር መርሕ ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት በሰጡት መልስ የሽያጭ ውሉን በማስረጃነት አላቀረቡም፤ 1ኛ አመልካች ለመጀመሪያው ክስ በሰጡት ምለሽ ተከሳሽ አከራካሪውን ቤት ታሕሳስ 30 ቀን 2000 ዓ.ም መሸጣቸውን የገለጹ ሲሆን በዚሁ ምላሽ ላይ ሠኔ 12 ቀን 2006 ዓ.ም ቤቱን 2ኛ አመልካች መግዛታቸውን መግለጻቸው ሁለት ውል እንዳለ የሚያሳይ ሲሆን በማስረጃ ዝርዝሩ ላይ ግን አንድም ውል አላያያዙም፤ የተሻሻለው ክስ ከቀረበ በኋላ አመልካቾች ተጣምረው ተከሳሽ ሆነዋል፤ የሁለቱም አመልካቾች ጠበቆች በጋራ ፈርመው በሰጡት ምላሽ ከማን እና መቼ ቤቱን እንደገዙ አልገለጹም የሽያጭ ውሉንም በማስረጃነት አላቀረቡም፤ ስለሆነም ይህንኑ መሠረት በማድረግ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

በዚህ ችሎት ትዕዛዝ መሠረት የቀረበውን የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የመ.ቁ 120444 የሆነውን መዝገብ እንደተመለከትነው፡-የሥር ከሳሽ የነበሩት ም/ኮ/ር አብርሃ እቁባይ በአሁን 1ኛ አመልካች ላይ ብቻ ክስ አቅርበው የነበሩት ሕዳር 20 ቀን 2009 ዓ.ም መሆኑን፤ ይህ ክስ በመጀመሪያ መጋቢት 05 ቀን 2010 ዓ.ም የተሻሻለ መሆኑን፤ የካቲት 21 ቀን 2011 ዓ.ም ደግሞ በድጋሚ ተሻሽሎ የቀረበ መሆኑን፤ አመልካቾች ለመጀመሪያ ጊዜ መጋቢት 05 ቀን 2010 ዓ.ም ተሻሽሎ ለቀረበው ክስ በየፊናቸው መልስ የሰጡት ሚያዝያ 05 ቀን 2010

ዓ.ም መሆኑን እና ከዚህ መልሳቸው ጋር 2ኛ አመልካች በአከራካሪው ቤት ላይ ተደርጓል የተባለውን የሽያጭ ውል እና ቤቱ በስማቸው የተመዘገበ መሆኑን የሚያሳይ የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ ያቀረቡ መሆኑን፤ ለሁለተኛ ጊዜ የካቲት 21 ቀን 2011 ዓ.ም ተሻሽሎ ለቀረበው ክስ ደግሞ አመልካቾች በጋራ በመሆን መጋቢት 16 ቀን 2011 ዓ.ም መልስ የሰጡ መሆኑን እና ከዚሁ መልሳቸው ጋር በ2ኛ አመልካች ስም የተመዘገበ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክርነት ወረቀት በማስረጃነት ያቀረቡ ሲሆን የሽያጭ ውሉ ግን በማስጃነት ያልቀረበ መሆኑን፤ ፍርድ ቤቱም ለመጀመሪያ ጊዜ መጋቢት 05 ቀን 2010 ዓ.ም ተሻሽሎ የቀረበውን ክስ እና አመልካቾች ለዚሁ ክስ ሚያዝያ 05 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጡትን መልስ መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የሰጠ መሆኑን መዝገቡ ያመለክታል፡፡

በመሠረቱ አንድ ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 91 መሠረት ተሻሽሎ እንድቀርብ ፍርድ ቤቱ ፈቅዶ ክሱ ተሻሽሎ በቀረበ ጊዜ ቀድሞ የነበረውን ክስ ቀሪ የማድረግ ውጤት ያለው ሲሆን ፍርድ ቤቱም በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ሊሰጥ የሚችለው የተሻሻለውን ክስ እና ተሻሽሎ በቀረበው ክስ ላይ ተከሳሹ የሰጠውን መልስ መሠረት በማድረግ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 91 ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በያዝነው ጉዳይ የስር ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የሰጠው ለመጀመሪያ ጊዜ መጋቢት 05 ቀን 2010 ዓ.ም ተሻሽሎ የቀረበውን እና ለዚሁ ክስ በየፊናቸው ሚያዝያ 05 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጡትን መልስ መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ሆኖም ተጠሪ ያቀረበው ክስ ለሁለተኛ ጊዜ የካቲት 21 ቀን 2011 ዓ.ም ተሻሽሎ የቀረበ እና ለዚሁ ክስ አመልካቾች በጋራ በመሆን መጋቢት 16 ቀን 2011 ዓ.ም መልስ የሰጡ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ክሱ ከመሻሻሉ በፊት ቀርቦ በነበረው እና ክሱ ከተሻሻለ በኋላ ቀሪ የሆነውን የግራቀኙን ክርክር መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ስለሆነም በዚሁ አግባብ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የክርክር አመራር ሥርዓት ሥሕተት የተፈጸመበት ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ መስጠት የሚገባው ተጠሪ በድጋሚ የካቲት 21 ቀን 2011 ዓ.ም አሻሽለው ያቀረቡትን ክስ እና ለዚሁ ክስ አመልካቾች በጋራ በመሆን መጋቢት 16 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጡትን መልስ መሠረት በማድረግ ሊሆን ይገባል ብለናል፡፡

በሌላ በኩል የሥር ፍርድ ቤት አመልካቾች አከራካሪውን ቤት ለተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰ ቢሆንም 2ኛ አመልካች ቤቱ ከ1ኛ አመልካች በሽያጭ ተላልፎልኛል በማለት የሚከራከሩ ቢሆንም የሽያጭ ውሉን በማስረጃነት አላቀረቡም በማለት

ነው፡፡ ሆኖም አመልካቾች ምንም እንኳን በድጋሚ ተሻሽሎ ለቀረበው ክስ መጋቢት 16 ቀን 2011 ዓ.ም መልስ ሲሰጡ የሽያጭ ውሉን በማስረጃነት ያላቀረቡት ቢሆንም መጋቢት 05 ቀን 2010 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ ተሻሽሎ ለቀረበው ክስ 2ኛ አመልካች ሚያዝያ 05 ቀን 2010 ዓ.ም መልስ ሲሰጡ በቤቱ ላይ ተደርጓል የሚሉትን የሽያጭ ውል እና በ2ኛ አመልካች ስም የተመዘገበ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክርነት ወረቀት በማስረጃነት ያያዙት መሆኑን መዝገቡ የሚያመለክት በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ለትክክለኛ ፍትሕ አሰጣጥ ሲል ይህን ማስረጃ መመልከት እና የማስጃውን ትክክለኛነት አግባብነት ያለውን ትዕዛዝ በመስጠት ማስረጃውን ከሰጠው አካል ተጣርቶ እንዲቀርብለት በማድረግ መወሰን ይገባው ነበር፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን በዚህ አግባብ በማየት መወሰን ሲገባው አመልካቾች የሽያጭ ውሉን በማስረጃነት አላቀረቡም በማለት ቤቱን ለተጠሪ እንዲያስረክቡ ሲል የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጀ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 120444 በቀን 26/06/2012 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 251791 በቀን 11/03/2013 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በውሳኔ የዘጋውን መዝገብ እንደገና በማንቀሳቀስ ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው መንገድ ጉዳዩን አጣርቶ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1 መሠረት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

-የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የመዝገብ ቁጥር 120444 የሆነው መዝገብ ወደመጣበት ይመለስ፡፡

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ. 204195

የካቲት 30 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች - ወ/ሮ ጽጌ ወርቁ፡- ቀርበዋል

ተጠሪ - አቶ ኢሳያስ ተገኝ፡- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርዱ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ የጉዳዩም አመጣጥ ሲታይ በግራ ቀኝ መካከል ተደርጎ የነበረዉ የማይንቀሳቀስ ንብረት የስጦታ እና የሽያጭ ውሎች በአመልካች ጥያቄ መነሻነት ሚያዝያ 02 ቀን 2005 ዓ.ም እንዲፈርስ ተወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላ አመልካች የካቲት 11 ቀን 2012 ዓ.ም ለፍርድ ቤቱ ባቀረቡት አቤቱታ የውሉ መፍረስ ውጤት በውሳኔው ላይ ያልተካተተ እና ይህም ለአፈፃፀም የሚያስቸግር በመሆኑ ለአፈፃፀም ችሎት ትዕዛዝ ይሰጥልኝ ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

የአመልካችን አቤቱታ የመረመረው የስር ፍርድ ቤትም ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ውሳኔ የተሰጠው አመልካች በጠየቁት ዳኝነት መሠረት ሲሆን አመልካች የጠየቁት ዳኝነት ደግሞ ውሉ ይፍረስልኝ የሚል ብቻ እንጂ ቤቱን ተጠሪ ያስረክበኝ የሚል አይደለም፤ አመልካች ቤቱ እንዲለቀቅላቸው ባልጠየቁበትና ይህም ባልተወሰነበት፣ እንዲሁም የአፈፃፀም ችሎቱ ውሳኔው ግልጽ አይደለም የሚል ጥያቄ ባላቀረበበት አመልካች ትዕዛዝ እንዲሰጥ ጥያቄ ማቅረባቸው ተገቢነት የለውም በማለት አቤቱታቸውን ውድቅ አድርታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም አቤቱታቸው ውድቅ ተደርጎባቸዋል፡፡ ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች የካቲት 11 ቀን 2013 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ የስር ፍርድ ቤት ለአፈፃፀም ችሎቱ ትዕዛዝ እንዲሰጥልኝ አቤቱታ ያቀረብኩት ውሳኔ እንዲፈፀምልኝ ለአፈፃፀም ችሎት አቤቱታ አቅርቤ የአፈፃፀም ችሎቱ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ለማስፈፀም እንደማይቻል ገልጾ መዝገቡን የዘጋው በመሆኑ ነው፤ የስር ፍርድ ቤትም በውሳኔው ላይ ያለውን ክፍተት ከፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1815 አንፃር የውሉ መፍረስ ውጤት ምን እንደሆነ በማሳየት የአፈፃፀም ችሎቱ ውሳኔውን የሚያስፈጽምበትን ሁኔታ መግለጽ እየተገባው ትዕዛዝ ሊሰጥ አይገባም በማለት አቤቱታውን ውድቅ ማድረጉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተፈፀመው ውል ፈራሽ ነው ከተባለ በኋላ ግራ ቀኙ ወደ ነበሩበት ቦታ እንዲመለሱ ሳይወሰን መታለፉ ውሳኔው ሊፈፀም የሚችል መሆን አለመሆኑ መጣራት አለበት ተብሎ ስለታመነበት ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቧል፡፡ በዚሁም መሠረት ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ሐምሌ 15 ቀን 2013 ዓ.ም በተፃፈ መልሱ ለአፈፃፀም ክርክሩ መነሻ የሆነው ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ አመልካች ቅሬታ ካላቸው በይግባኝ እንዲታረም ከመጠየቅ በስተቀር ውሳኔውን ለሰጠው ፍርድ ቤት ውሳኔው እንዲቀየር በአቤቱታ መጠየቅ አይችሉም፤ ቤቱን ለመረከብ በግልጽ የተጠየቀ ዳኝነትም አልነበረም፤ ውሉም ፈራሽ ከተደረገ በኋላ ቤቱን ለመረከብ አመልካች በሌላ መዝግብ ክስ አቅርበው የቤቱ ባለቤት የሆነው የቦሌ ክ/ከተማ ጣልቃ ገብቶ በቤቱ ላይ ያለውን መብት አስረድቶ የተወሰነለት በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተው ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀውን ሲመስል ይህ ችሎትም የአመልካችን የሠበር አቤቱታ በሰበር አጣሪ ከተያዘው ጭብጥ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ለዚህ ሰበር መነሻ የሆነዉ አመልካች የካቲት 11 ቀን 2012 ዓ.ም ለስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ፍርድ ቤቱ ሚያዝያ 02 ቀን 2005 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት በዋለዉ ችሎት የቤት ሽያጭ/ስጦታ ዉሉ እንዲፈርስ የወሰነ ቢሆንም ዉጤቱን በተመለከተ በዉሳኔዉ የተገለጸ ነገር ባለመኖሩ ለአፈፃፀም አስቸጋሪ መሆኑን ጠቅሰዉ ፍርድ ቤቱ ለአፈፃፀም ችሎቱ ትዕዛዝ እንዲሰጥ በመጠየቃቸዉ ሲሆን፣ ፍርድ ቤቱ የአመልካችን አቤቱታ ዉድቅ ሲያደርግ የጠቀሰዉ ምክንያትም አመልካች ዉሉ እንዲፈርስ ቀደም ሲል ክስ ሲያቀርቡ ዉሉ ፈራሽ ሆኖ ቤቱንም ተጠሪ

እንዲያስረክባቸዉ እንዲወሰን መጠየቅ ሲገባቸዉ ያልጠየቁ ከመሆኑም በላይ ተጠሪ ቤቱን እንዲያስረክቡ የሚል ዉሳኔም ባልተሰጠበት ሁኔታ የአፈፃፀም ትዕዛዝ ይሰጥልኝ በማለት አቤቱታ ማቅረባቸዉ ተገቢነት የሌለዉ መሆኑን ነዉ።

በእርግጥ ምንም እንኳ ዉል እንዲፈርስ ክስ የሚያቀርብ ሰዉ ተከሳሽ በዉሉ መሠረት የያዘዉን ንብረት እንዲያስረክበዉ ዳኝነት መጠየቅ ሳያስፈልገዉ ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤት ዉሉ እንዲፈርስ ዉሳኔ ሲሰጥ በዉሉ ምክንያት ግራ ቀኝ የተቀባበሉትን ነገር አንዱ ለሌላኛዉ እንዲመልስ ወይም ግራ ቀኝ ከዉሉ በፊት ወደ ነበሩበት ሁኔታ እንዲመለሱ የመወሰን ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1815 ላይ ከተመለከተዉ ድንጋጌ የምንገነዘበዉ ነዉ። ከዚህ አንፃር ሲታይ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ቀደም ሲል የዉል ይፍረስልኝ ክስ ሲያቀርቡ ተጠሪ ቤቱን እንዲያስረክቧቸዉ ጭምር ዳኝነት መጠየቅ ነበረባቸዉ የሚለዉን እንደ አንድ ምክንያት መጥቀሱ ሊታረም የሚገባዉ ነዉ። በሌላ በኩል ፍርድ ቤቱ ሚያዝያ 02 ቀን 2005 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት በግራ ቀኝ መካከል የተደረገዉ ዉል እንዲፈርስ ሲወስን ተጠሪ በዉሉ መሠረት የያዙትን ቤት (ካለ) ለአመልካች እንዲመልሱ የሚል ግልጽ ዉሳኔ አልሰጠም። ፍርድ ቤቱ ይህን አለመወሰኑ ስህተት ነዉ ለማለት ይቻላል። በሌላ በኩል የፍርድ ቤት ዉሳኔ መብቴን ነክቷል የሚል ሰዉ እንደሁኔታዉ በይግባኝ ወይም ፍርዱን/ዉሳኔዉን በሰጠዉ ፍርድ ቤት አቤቱታዉን አቅርቦ ማሳረም የሚችልበት ሥርዓት በሀገራችን የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ተቀርፆ እናገኛለን። በዚህም መሠረት ፍርድን/ዉሳኔን ፍርዱን/ዉሳኔዉን በሰጠዉ ፍርድ ቤት በእራሱ ማሳረም የሚቻልባቸዉ ሥርዓቶችም አንደኛ በህጉ አንቀጽ 6 ላይ በተመለከተዉ አግባብ የሚቀርብ የዳግም ዳኝነት ጥያቄ ሲሆን፣ ሁለተኛ በአንቀጽ 207-211 ላይ የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲኖሩ እና ሦስተኛ በአንቀጽ 358 መሠረት በሦስተኛ ወገን የሚቀርብ የመቃወም አቤቱታ ናቸዉ። ስለሆነም ፍርድ/ዉሳኔ እንዲታረም ፍርዱን/ዉሳኔዉን ለሰጠዉ ፍርድ ቤት የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የሚኖረዉ ከእነዚህ ሦስቱ ዉስጥ አንዱን የሚያሟላ ሆኖ ሲገኝ ነዉ። አመልካች ዉሳኔዉን ቀደም ሲል ለሰጠዉ ፍርድ ቤት ለዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነዉን አቤቱታ መሠረት ያደረጉት በህጉ አንቀጽ 6 እንዲሁም 358 ስር የሚወድቅ አይደለም። በህጉ አንቀጽ 208 ስር የሚወድቅ ነዉ ለማለትም፣ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የሚኖረዉ እና ፍርድ ቤቱም ተቀብሎ ፍርዱን/ዉሳኔዉን ማረም የሚችለዉ ፍርዱ/ዉሳኔዉ የአፃፃፍ ስህተት፣ የቁጥር አፃፃፍ ጉድለት ወይም ያልታሰበ እና ባለማስተዋል የተዘለለ ስህተት የተፈጸመበት ሲሆን ነዉ። ይሁንና በተያዘዉ ጉዳይ ፍርድ ቤቱ ዉል እንዲፈርስ ወስኖ ንብረቱን አስመልክቶ ሳይወስን ማለፉ ስህተት ነዉ ቢባል እንኳ ይህ

ስህተቱ ከአፃፃፍ ጉድለት ወይም ባለማስተዋል የተዘለለ ድንገተኛ የቃል ስህተት ነዉ ለማለት የሚቻል ባለመሆኑ በአንቀጽ 208 ስር የሚወድቅ አይደለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ ባለመቀበል በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በጸናዉ ዉሳኔ ላይ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘንም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

ዉሳኔ

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁጥር 57437 የካቲት 24 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 257496 ታህሳስ 14 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡

በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

የሰ.መ.ቁ.162628

ህዳር 24 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2. ቀነዓ ቂጣታ

3. ደጀኔ አያንሳ

4. ኑረዲን ከድር

5. ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካች፡- አቶ ፍቅሩ ክብካብ - ቀርበዋል

ተጠሪዎች፡-.1. ወ/ሮ ኑኑሽ ክብካብ } - ቀርበዋል

2. ወ/ሮ ሰብለ ክብካብ }

ጣልቃ ገብ፡- የመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል አስተዳደር ጽ/ቤት - ተወካይ ሀዋዝ ገ/ሊባኖስ

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍ ር ድ

ይህ የዉርስ ማጣራት ክርክር የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች 1ኛ ከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪዎች ተከሳሾች፣ እና እንዲሁም በዚህ ችሎት የክርክሩ ተካፋይ ያልሆኑት አቶ ተክለወልድ ክብካብ 2ኛ ከሳሽ፣ ዘርትሁን ተስፋዬ እና መና ግርማ ጣልቃ ገቦች ሆኖ ሲከራከሩ ነበር። ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.205535 በ17/9/2011 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ።

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ ከሳሾች ባቀረቡት ክስ የሟች አቶ ክብካብ ገ/ማርያም እና የወ/ሮ በቀለች ወ/ማርያም የዉርስ ሀብትን በተመለከተ የዉርስ አጣሪ እንዲሾምልን በማለት ዳኝነት ጠይቋል። የሥር ተከሳሾች በዚህ ክስ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና በአማራጭ ፍሬ ነገር ክርክር ያቀረቡ ሲሆን፤ ጣልቃ ገቦችም በበኩላቸዉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና አማራጭ የፍሬ ነገር መልስ አቅርቦ ተከራክሯል። ከዚህ በኋላ የሥር ፍ/ቤቶች ተከሳሾች እና

ጣልቃ ገቦች ያነሱትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ዉድቅ በማድረግ የዉርስ አጣሪ በመሾም የዉርስ ሀብቱን እንዲያጣራ በሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረት የዉርስ አጣሪ በ14/6/2009 ዓ.ም የተጻፈ ሪፖርት አቅርቧል፡፡

የዉርስ አጣሪ ሪፖርት ሲታይ የመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል አስተዳደር ጽ/ቤት በዉርስ አጣሪዉ ዘንድ ጣልቃ ገብቶ አቤቱታ እንዳቀረበ መገንዘብ ተችሏል፡፡ የዉርስ አጣሪዉ የዉርስ ሀብቱን በማጣራት ሪፖርቱን ለፍ/ቤቱ አቅርቧል፡፡ የዉርስ አጣሪዉ ሪፖርቱን ለፍ/ቤቱ ካቀረበ በኋላ በሪፖርቱ ላይ አስተያየታቸዉን የሰጡት ከሳሾች፣ ተከሳሽ እና ጣልቃ ገቦች እንጂ የመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል አስተዳደር ጽ/ቤት እንዳልነበረ የሥር ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በዉሳኔዉ እንደጠቀሰዉ ፣በዚህ መዝገብ ጣልቃ ገብ ሆኖ ያልተመዘገበዉ በዉርስ ማጣራት ሂደቱ ግን ጣልቃ ገብ የነበረዉ የመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል አስተዳደር ጽ/ቤት ዘንድ ያቀረበዉን አቤቱታ በመጥቀስ፣ ክርክሩን በመመርመር ለክርክር ምክንያት የሆነዉ 3 ክፍሎች ቤት የቤተክርስቲያን ንብረት እንጂ የዉርስ ሀብት አይደለም እና የተጠሪዎች አዉራሽ በይዞታዉ ላይ የሰሯቸዉ 7 ክፍሎች ቤት ላይ ወራሾች መብት የላቸዉም በማለት ወስኗል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቤተክርስቲያኑ የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን ሳያደርግ የሰጠዉን ዉሳኔ በተመለከተ የሥር ከሳሽ ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሥር ተከሳሾችን ብቻ መልስ ሰጪዎች በማድረግ ያቀረበ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ ይግባኙን በትዕዛዝ ዉድቅ በማድረግ የሥር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ እና ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካቾች ነሐሴ 14 ቀን 2010 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ በአራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 8 ቀበሌ 15/16 የሚገኘዉ እና በቤት ቁጥር 032 የሚታወቀዉ የዉርስ ሀብት አይደለም እና የኪራይ ገንዘብን በተመለከተ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በማለት ቅሬታቸዉን በመዘርዘር ዉሳኔዉ እንዲታረምላቸዉ ጠይቋል፡፡

ይህ ችሎት የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች እንዲሰጡ ባዘዘዉ መሰረት በ30/2/2011 ዓ.ም በተጻፈ መልስ፡ በዚህ ጉዳይ የመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል አስተዳደር ጽ/ቤት የክርክሩ ተሳታፊ ሆና ለክርክር ምክንያት የሆነዉ ንብረት ተወስኖላታል፤ ስለሆነም ቤተክርስቲያኗ በዚህ ችሎትም የክርክሩ ተካፋይ እንዲትሆን በማድረግ ንብረቱ የዉርስ ንብረት አይደለም ተብሎ እንዲወሰንልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት በ8/4/2011 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ፡ ለክርክር ምክንያት የሆኑት ቤቶች የዉርስ ሀብት ሳይሆኑ የቤተክርስቲያኗ እና በሥር ፍ/ቤቶች እንደተፈረዳለት መሆኑን በመጥቀስ በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ እንዲፈቀድለት ጠይቋል፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ጣልቃ ገብ ቤተክርስቲያን ያቀረበዉን አቤቱታ በመመርመር ጣልቃ ገብ የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን በማዘዝ፤ አመልካች ባቀረበዉ የሰበር አቤቱታ ላይ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት በ6/6/2011 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት ግራ ቀኞቸዉን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ በዚህ ጉዳይ ምላሽ ማግኘት የሚገባዉ ፤በዚህ ጉዳይ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት የክርክሩ ተሳታፍ ሳይሆን ዉሳኔ መስጠቱ እና የሥር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትም ይህን ሳያርም የሥር ዉሳኔ ማጽናቱ በሕጉ አግባብ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በዚህ መሰረት የአሁን ጣልቃ ገብ ለክርክር ምክንያት የሆኑት ቤቶች እና ይዞታዉ የዉርስ ሀብት ሳይሆን የቤተክርስቲያን ንብረት ነዉ በማለት በዉርስ አጣሪ ዘንድ ክርክር እንዳቀረበ ከሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ ግልባጭ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ነገር ግን የዉርስ አጣሪ ሪፖርቱን ለፍ/ቤት በሚያቀርበበት ወቅት የአሁን ጣልቃ ገብ የክርክሩ ተሳታፊ በመሆን በሪፖርቱ ላይ አስተያየቱን እንዳላቀረበ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የዉርስ አጣሪዉን ሪፖርት ተከትሎ ግራ ቀኞቸዉ ያቀረቡትን ክርክር ሲመረምር፣ የአሁን ጣልቃ ገብ ቤተክርስቲያን የክርክሩ ተካፋይ መሆን ለዉሳኔ አሰጣጥ አስፈላጊና ምቹ መሆኑን እስከገነዘበ ድረስ፣ ፍ/ቤቱ በራሱ ተነሳሽነት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.40 (2) መሰረት የመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት ወደ ክርክሩ እንዲገባ በማድረግ በቀረበዉ ሪፖርት ላይ አስተያየቱን እንዲሰጥ በማድረግ ጉዳዩን በመመርመር በሕጉ አግባብ ተገቢ ነዉ ያለዉን ብይን ወይም ዉሳኔ መስጠት ይገባዉ ነበር፡፡ ነገር ግን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን ጣልቃ ገብ የክርክሩ ተካፋይ ባልሆነበት እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.40 (2) መሰረት ወደ ክርክሩ እንደገባ ክርክሩን እንዲያቀርብ ባላደረገበት ሁኔታ፣ ለክርክር ምክንያት የሆነዉ ሶስት ክፍሎች ቤት እና ይዞታዉ የዉርስ ሀብት ሳይሆን የአሁን ጣልቃ ገብ ቤተክርስቲያን ንብረት ነዉ በማለት መወሰኑ፣ የክርክሩ ተካፋይ ላልሆነ እና ዳኝነት ላልጠየቀ አካል ዉሳኔ መስጠቱን የሚያሳይ ነዉ፡፡ ይህ ደግሞ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.182 (2) ድንጋጌ የሚቃረን አካሄድና ዉሳኔ አሰጣጥ

ስለሆነ ተቀባይነት የለዉም፡፡ ከዚህ አንጻር የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የቀረበለትን ይግባኝ በመመርመር የሥር ፍ/ቤት በዉሳኔዉ የፈጸመዉን ስህተት ማረም ሲገባዉ ዉሳኔዉን በትዕዛዝ ማጽናቱ ሕጉን የሚቃረን አካሄድና ዉሳኔ ነዉ ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ጉዳይ የአሁን ጣልቃ ገብ የመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት የክርክሩ ተሳታፊ ሳያደርጉ የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.142796 በ16/2/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.205535 በ17/9/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ በፍርድ ሐተታዉ በተጠቀሰዉ መሰረት የመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.40 (2) መሰረት የክርክሩ ተሳታፊ እንዲሆን በማድረግ፣ የዉርስ አጣሪዉ ባቀረበዉ ሪፖርት ላይ የበኩሉን አስተያየትና ክርክር እንዲያቀርብ በማድረግ፣ ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር፣ በሕጉ አግባብ ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.343 (1) መሰረት ተመልሶለታል፡፡

3. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡

4. ግራ ቀኞቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻላል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፅ/ወ

ዉል

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰበር መ/ቁ/143086

መጋቢት 25 **ቀን** 2010 **ዓ.ም**

ዳኞች ፡ ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አቶ አፈወርቅ ያለዉ

ተጠሪ፡- 1ኛ/ አቶ በላይ ኢሳያስ

2ኛ/አቶ አማኑ ሲናማዉ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ በመሆኑ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ የአፈጻጸም ክርክር መነሻ ያደረገ ሲሆን አመልካች የአፈጻጸም ከሳሽ ተጠሪዎች ደግሞ የአፈጻጸም ተከሳሾች ነበሩ፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የአፈጻጸም ክስ የቀረበዉ በግራቀኙ መካከል በቤትና ቡና ተክል ይዞታ ላይ በነበረዉ የሁከት ይወገድ ክርክር

ጉዳዩ በሽማግሌ እንዲታይ ተደርጎ በሽምግልና ታይቶ አመልካች የሀብት ግምት ብር 71,260 ብር ለተጠሪዎች እንዲከፍል ተጠሪዎችም ይህንኑ ሀብት እንዲያስረክቡ ተስማምተዉ ይኸዉ እርቅ ስምምነት በፍርድ ቤት ተመዝግቦና ጸድቆ ያደረ መሆኑን መሰረት በማድረግ ተጠሪዎች ቀደም ሲል 40,000 ብር ተረክበዉ እያለ ቀሪ ብር ተረክበዉ ሀብቱን እንዲያስረክቡ ፈቃደኛ አልሆኑም በሚል አመልካች የአፈጻጸም ክስ መንገሻ ወረዳ ፍርድ ቤት ላይ ያቀረበ ሲሆን ተጠሪዎች በበኩላቸዉ አመልካች ቀሪዉን ብር በዉሉ/ስምምነቱ/ በተገለጸዉ ጊዜ ዉስጥ አልከፈለም በሚል ስምምነቱ እንዲፈርስ እንዲወሰን ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የወረዳዉ ፍርድ ቤት በሁለቱም መዝገብ ላይ ግራቀኙን አከራክሮ ዉሉ የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት እንደዉሉ ተጠሪዎች ቀሪ ገንዘብ ተቀብለዉ ንብረቱን እንዲያስረክቡ በማለት የአፈጻጸም ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪዎች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ ለማጃንግ ብ/ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ በማቅረባቸዉ ፍርድ ቤቱ ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ በግራቀኙ መካከል የተደረገዉ የእርቅ ስምምነት በፍርድ ቤት የጸደቀ በመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ ህግ ቁ/277 መሰረት የአፈጻጸም ክስ የሚቀርብበት ነዉ በዚሁ መሰረት እንዲፈጸም በወረዳ ፍርድ ቤት መወሰኑ ተገቢ ነዉ በማለት የተጠሪዎችን ይግባኝ ባለመቀበል የወረዳ ፍርድ ቤት ዉሳኔ አጽንቷል፡፡ተጠሪዎች ለክልሉ ሰበር ችሎት አቤቱታ በማቅረባቸዉ ሰበር ችሎቱ ግራቀኙን አከራክሮ እንደዉሉ ካልተፈጸመ አንደኛዉ ወገን ዉል እንዲፈርስ መጠየቅ ይችላል የሚለዉን ተቀብሎ የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 1675-1678 ያለዉን በመጥቀስ ዉሉ እንዲፈርስ ወሳኔ ሰጥቷል፡፡ ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ሲሆን የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አከራካሪዉን ይዞታና ቤት አስመልክቶ ተጠሪዎች ዉል ይፍረስልን በማለት በጠየቁት መሰረት አመልካች ጉዳዩ በሽምግልና አልቋል በፍርድ ቤም የተመዘገበ ነዉ ሲል ያቀረበዉን ክርክር ዉድቅ ተደርጎ ዉል ይፍረስ በማሉግራቀኙ በ26/08/08 ዓ.ም ካደረጉት ዉል እና ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ 277 አንጻር ለመመርምር እንዲቻል ጭብጥ ተይዞ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ተረደርጓል፡፡በተጠሪዎች በኩል የቀረበዉ መልስ ባጭሩ በግራቀቡ መካከል በ26/08/08 ዓ.ም የተደረገዉ ስምምነት አመልካች እስከ ሰኔ 30 ቀን 2008 ዓ.ም ድረስ ቀሪ ገንዘብ ከፍሎ እንዲረከብ እንደነበር እና አመልካች በተገለጸዉ ጊዜ ገንዘብ የለኝም በማለቱ ዉሉ እንዲፈርስ ተጠሪዎች ዳኝነት መጠየቃቸዉ እንዲሁም የክልሉ ሰበር ችሎት ዉሉ እንዲፈርስ መወሰኑ ተገቢ እንደሆነ በመግልጽ ዉሳኔዉ እንዲጸና ተከራክረዋል፡፡አመልካችም የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር ከላይ ባጭሩ የተገለጸ ሲሆን እኛም አቤቱታዉ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድረግ አግባብነት

ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል ። መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ በግራቀኙ መካከል በነበረዉ የሁከት ይወገድ ክስ ላይ ጉዳዩ በሽምግልና እንዲታይ በፍ/ቤት መስማማታቸዉን ተከትሎ ግራቀኙ በሽማግሌ ተስማምተዉ ስምምነቱም በ26/08/08 ዓ.ም ተፈርሞ በፍርድ ቤት ተመዝግቦና ጸድቆ መዝገቡ የተዘጋ ስለመሆኑ ግራቀኙ ያልካዱት እና በስር ፍርድ ቤትም በማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን ነዉ።ስምምነቱ ላይ የተመለከተዉም ጉዳይ ግራቀኙን ያከራከረዉን ቤትና የቡና ተክል ይዞታ ግምት ብር 71,260 አመልካች ለተጠሪዎች እንዲከፍል ተጠሪዎችም ይህንኑ ንብረትና ይዞታ እንዲያስረክቡ የሚል ሲሆን እንደዉሉ አስከ ሰኔ 30 ቀን 2008 ዓ.ም ድረስ ግራቀኙ ግደታዎቻቸዉን ለመፈጸም መስማማታቸዉም አላከራከረም። አመልካች በዚህ ስምምነት መሰረት እንዲፈጸም ሲጠይቅ ተጠሪዎች ቅድሚያ ብር 40,000 ወስደዉ ቆይተዉ ቀሪዉን ብር 31,260 እንዲቀበሉና ንብረቱን እንዲያስረክቡ ፋቃደኛ ስላልሆኑ የአፈጻጸም ትእዛዝ እንዲሰጥለት የሚል ሲሆን በተጠሪዎች በኩል የቀረበዉ ክስና ክርክር አመልካች ሰኔ 30 ላይ ቀሪዉን ብር ስላልከፈለ ዉሉ እንዲፈርስ የሚል ነዉ።

በመሰረቱ በፍርድ ቤት በክርክር ላይ ባለ ጉዳይ ተከራካሪ ወገኖች ነገሩን በእርቅ ለመጨረስ ተስማምተዉ እርቁም በጽሁፍ ተደርጎ ፍርድ ቤት ቀርቦ ለህግና ለሞራል ተቃራኒ አለመሆኑ ተረጋግጦ ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዝ ከተደረገ ይህ እንደፍርድ ቤቱ ፍርድ ተወስዶ የሚፈጸም ወይም የአፈጻጸም ክስ የሚቀርብበት ስለመሆኑ የፍብ/ስ/ስ/ህግ አንቀጽ 277 /1 እና 2/ ድንጋጌ ይዘት ያስገነዝባል። በዚህ ረገድ ይህ ሰበርችሎት በመዝገብ ቁ/52752፣85873 እና ሌሎችም ተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ አስገዳጅ ዉሳኔ መስጠቱ ይታወቃል። በተያዘዉም ጉዳይ በግራቀኙ መካከል በፍርድ ቤት የተመዘገበ ስምምነት መኖሩ አከራካሪ አይደለም ።ይህ ስምምነት እንደፍርድ ቤት ፍርድ የሚወሰድ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ እንደስምምነቱ ካልተፈጸመ ስምምነቱ በዳኝነት አካል ዘንድ ቀርቦ የፍርድ ሃይል ያህል ተወስዶ በዚሁ መሰረት እንዲጸም የአፈጻጸም ክስ ማቅረብ መብት ይኖራቸዋል እንጂ እንደመደበኛ ዉል ዉል እንዲፈርስ አዲስ ክስ የሚቀርብበት ሊሆን አይገባም ።ከዚህ ባለፈ እንደማናቸዉም ፍርድ የአፈጻጸም ክስ ሲቀርብ ፍርዱ/ስምምነቱ/ ሊፈጸም የማይቻልበት ህጋዊ ምክንያት ካለ በክርክር ሂደት ቀርቦ ፍርድ ቤቱ መርምሮ በህጉ አግባብ ዉሳኔ ሊሰጥበት የሚገባ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ/386፣ 392 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል። በዚህ መዝገብ ከቀረበዉ ክርክር መገንዘብ የሚቻለዉ አመልካች የሚከራከረዉ ተጠሪዎች ቀሪ ገንዘብ እንዲቀበሉና ንብረቱን እንዲያስተላልፉ በአፈጻጸም እንዲገደዱ ሲሆን ተጠሪዎች ደግሞ አመልካች በዉሉ በተገለጸዉ ጊዜ ማለትም ሰኔ30/2008 ዓ.ም ቀሪዉን ብር 31,260 ባለመክፈሉ ዉሉ እንዲፈርስ በማለት

ተከራክረዋል፡፡ ከላይ እንደተገለጸዉ ሁለቱም ወገኖች እንደስምምነቱ/በፍርድ/መሰረት እንዲፈጸም ግደታዉን ያልፈጸመ ወገን በፍርድ አፈጻጸም ማስገደድ መብት አላቸዉ፡፡ከዚህ ባሻገር የትኛዉ ወገን ነዉ ግደታዉን ለመወጣት ፈቃደኛ ያልሆነዉ የሚለዉን ክርክር አስመልክቶ የወረዳዉ ፍርድ ቤት ሽማግሌዎቹን አስቀርቦ እንዳረጋገጠዉ ተጠሪዎች ቀሪዉን ብር ለመቀበል ፈቃደኛ ባለመሆናቸዉ አመልካች በአደራ ሽማግሌዎች እጅ እንዳስቀመጠ እና እንደስምምነቱ ላለመፈጸም መሰናክል የፈጠሩት ተጠሪዎች መሆናቸዉን አረጋግጦ ዉሳኔ ስለመስጠቱ የተረጋገጠ ፍሬነገር ነዉ፡፡ስለሆነም የክልሉ ሰበር ችሎት ይህን የተረጋገጠ ፍሬነገር እንዲሁም የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ 277 ይዘት እና ዓላማ ጋር በማያያዝ የፌዴራል ሰበር ችሎት ከላይ በተገለጸዉ መዝገብ የሰጠዉን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ባላገናዘበ ሁኔታ በፍርድ ቤት ተመዝግቦ ያደረ እና እንደፍርድ ቤት ፍርድ ተወስዶ የአፈጻጸም ክስ የሚቀርብበትን ስምምነት የፍ/ብህግ ቁ/1675-1678 መሰረት አድርጎ ዉሉ እንዲፈርስ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተጸመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ዉ ሳ ኔ</u>

1ኛ/ የጋምቤላ ሕ/ብ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ/00603/09 በ18/09/09 ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ/348/1/ መሰረት ተሸሯል፡፡

2ኛ/ የመንገሸ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/00681/08 የሰጠዉ ዉሳኔ እና የማጃንግ ብ/ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/26781 የሰጠዉ ዉሳኔ ጸንቷል፡፡ የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ ብለናል ::ይጻፍ::

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ::

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ. 219931

ሰኔ 28 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- አቶ ዮናስ ደስታ ጠበቃ ተስፋዬ ሙሊሳ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ ነጋሽ ኃይሌ- አልቀረ ቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች የስር 1ኛ ተከሳሽ፣ ተጠሪ ከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ከአመልካች ጋር በተደረገ በአደራ ማስቀመጥ ውል ከውጭ ሀገር ይገቼ የገባሁትን 225,000.00 የአሜሪካን ዶላር በአደራ አስቀምጬ ገንዘቡን የመመለስ ውል ነሀሴ 23 ቀን 2012 ዓ/ም የተፈጸመ ቢሆንም በውሉ መሠረት ያልመለሱት ቀሪ ገንዘብ 126,000.00 ዶላር ወደዶላር ሂሳብ አካውንቱ እንዲያስገቡልኝ እንዲወሰን የሚል ሲሆን አመልካች ባቀረቡት መልስ ውሉ አሜሪካን ሀገር ስለተደረገ ፍርድ ቤቱ የመዳኘት ሥልጣን የለውም፤ ዶላሩን በአደራ የሰጠኝ አሜሪካን ሀገር ሲሆን ያለውን ቀሪ ገንዘብ 90,551.00 ዶላር አሜሪካን ሀገር መጥቶ መውሰድ ይችላል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ ገንዘቡን በአደራ የማስቀመጥ ውሉ የተደረገው በኢትዮጵያ ቢሾፍቱ ከተማ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ የመዳኘት ሥልጣን አለው፤ ነገር ግን የውጭ ሀገር ገንዘቡ ወደኢትዮጵያ ሲገባ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው

መመሪያ ቁጥር 49/2017 መሠረት ሕጋዊ ሥርዓቱን ጠብቆ ያልገባና የውጭ ሀገር ገንዘቡ በዚህ መጠን እና ለረጅም ጊዜ በግለሰብ እጅ እንዲቆይ የማይፈቅድ ስለሆነ በአደራ የማስቀመጥ ውሉ በፍ/ሕ/ቁ. 1716(1) መሠረት ሕገ-ወጥ ነው፤ ሕገ-ወጥ ውል የሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት የሌለ በመሆኑ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል። ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ በፍ/ሕ/ቁ. 1716(1) መሠረት ሕገ-ወጥ ዓላማ ያለው ውል ነው የሚባለው የውሉ ግዴታ በራሱ ሕገ-ወጥ ሲሆን እንጂ ከውሉ በፊት የተፈጸመ ሕገ-ወጥ ተግባር መኖር አለመኖሩ መሠረት በማድረግ የሚወሰን አይደለም። ዶላር በአደራ ማስቀመጥን ሕገ-ወጥ የሚያደርግ የሕግ ድንጋጌ የለም። ዶላሩ በሕገ-ወጥ መንገድ ሀገር ውስጥ የገባ ነው ቢባልና ውሉ ፈራሽ ቢሆን እንኳን አመልካች ገንዘቡን የሚያስቀሩበትና ያላግባብ የሚበለጽጉበት ምንም የሕግ አግባብ የለም በማለት የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር በፍሬ ነገሩ አከራክሮ እንዲወሰን ጉዳዩን መልሷል።

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው። የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም ዶላርን በአደራ ማስቀመጥ በወንጀል ሕግ ቁጥር 346 እና የብሔራዊ ባንክን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀጽ 26(4) መሠረት የወንጀል ድርጊት ሆኖ የተመለከተ ነው። ተግባሩ ወንጀል በመሆኑ ውሉ ሕገ-ወጥና ውጤት የሌለው ነው። በሕግ ወንጀል የተባለን ድርጊት በፍርድ ሕጋዊ ማድረግ አይቻልም፤ ውሳኔው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚል ሲሆን የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ ዶላር በአደራ ማስቀመጥ ውል ሕገ-ወጥ ተግባር አይደለም መባሉ ከመመሪያ ቁጥር 49/2017 እና ከፍ/ሕ/ቁ. 1716 አንጻር ተገቢነቱን ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ ያዘዘ ሲሆን ተጠሪ ያቀረቡት መልስ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ውሉ ሕገ-ወጥ ነው በማለት ያልተከራከሩ ስለሆነ በሥር ያልቀረበ ክርክር በዚህ ችሎት ሊያነሱ አይገባም። የውሉ ግዴታ ሕገ-ወጥ ሳይሆን ከውሉ በፊት የተፈጸመ ሕገ-ወጥ ተግባር መኖር አለመኖሩን የውሉን ዓላማ ሕገ-ወጥ አያደርገውም። የተከፈለው ገንዘብ ሳይመለስ ይቀራል ማለት የፍ/ሕ/ቁ. 1815 የሚቃረን እና አንደኛው ተዋዋይ ወገን ያላግባብ እንዲበለጽግ የሚያደርግ ነው። ውሳኔው ተገቢ ስለሆነ ሊጸና ይገባል ብለዋል። አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል።

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ተጠሪ ያቀረቡት ክስ የክስ ምክንያት ያለው መሆን አለመሆኑን? በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል።

እንደመረመርነው ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ከአመልካች ጋር በተደረገ በአደራ ማስቀመጥ ውል ከውጭ ሀገር ይገቼ የገባሁትን 225,000.00 የአሜሪካን ዶላር በአደራ አስቀምጬ ገንዘቡን የመመለስ ውል ነሀሴ 23 ቀን 2012 ዓ/ም የተፈጸመ ቢሆንም በውሉ መሠረት ያልመለሱት ቀሪ ገንዘብ 126,000.00 ዶላር ወደዶላር ሂሳብ አካውንቴ እንዲያስገቡልኝ እንዲወሰን የሚል ነው፡፡ እንደሚታወቀዉ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37/1 መሰረት ማንኛዉም ሰዉ አንድን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠዉ አካል በማቅረብ ፍርድ ወይም ዉሳኔ(ፍትህ) የማግኘት መብቱን መጠቀም የሚችለዉና በተለይም ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ጉዳዩን ተቀብሎ አከራክሮ ዉሳኔ ወይም ፍርድ ሊሰጥ የሚችለዉ ዳኝነት የተጠየቀበት ጉዳይ በፍርድ ሊወሰን የሚገባ ጉዳይ (justiciable matter) ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነዉ፡፡ ክርክሩን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ሲሆን በተገቢው ሁኔታ ካልተመራ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ዓላማዎች የሆኑትን እንደ አንጻራዊ እውነትን የመፈለግ፣ ሥነ-ሥርዓታዊ ፍትህ፣ ክርክርን ውጤታማ፣ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት የመሳሰሉትን ማሳካት ስለማይቻል የተከራካሪዎችን መብት ይነካል፡፡ ፍርድ ቤት በራሱ አነሳሽነት ከሚመረምራቸው ጉዳዮች መካከል የመጀመሪያው በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 231(1)(ሀ) መሠረት በክስ አቤቱታው የተገለጸው የሚያስከስስ መሆን መሆን አለመሆኑን ነው፡፡ የክስ ምክንያት ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ ግዴታ መኖሩን፣ የተጠየቀው ዳኝነት በፍርድ ቤት የሚዳኝ መሆን አለመሆኑን እና በክሱ ዝርዝር ውስጥ የተመለከቱት ጉዳዮች ቢረጋገጡ የተጠየቀውን ዳኝነት ለከሳሽ ለመወሰን ህግ የሚፈቅድ መሆን አለመሆኑን መመርመርን የሚጠይቅ ነው፡፡ ይህም የክስ ምክንያት የሌለው ጉዳይ የሚለው በዋነኛነት ዳኝነቱን ለመጠየቅ ከህግ የመነጨ ግንኙነት እያለው ግን በፍርድ ቤት ሊዳኙ የማይችሉ ጉዳችን (non-justiciable matters) ፍርድ ቤት አከራክሮ ሊፈጸም የሚችል ውሳኔ ሊሰጥባቸው የማይችሉ በመሆናቸውና ከሳሽ ወገን ክሱን ሲያቀርብ የጠቀሰው ወይም የገለጸው የክሱ መሰረት የሆነው ምክንያት በህግ የክስ መሰረት ሊሆን የማይችል ከሆነ የማያስከስስ ነው ተብሎ ክሱ ውደቅ የሚደረግበት ሥርዓት ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ የጠየቁት ዳኝነት ከአመልካች ጋር ያደረጉት ዶላር የማስቀመጥ የአደራ ውል መሠረት እንዲፈጸምላቸው ነው፡፡ ውል ሊመሠረት የሚገባው ሕጋዊ በሆነ ዓላማና ጉዳይ ላይ እንደሆነ በፍ/ሕ/ቁ. 1678(ለ) ላይ ተመልክቷል፡፡ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 346 ላይ የውጭ ሀገር ገንዘብን በአደራ ማስቀመጥ ወንጀል ሆኖ የተደነገገ ሲሆን በብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀጽ 26 በአዋጁ ሆነ በመመሪያ የተመለከቱ ግዴታዎችን መተላለፍ

ወንጀል ስለመሆኑ ተቀምጧል፡፡ የብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር ኤፍ.ኤክስ.ዲ. 49/2017 በክሱ የተመለከተውን መጠን ያሕል የውጭ ሀገር ገንዘብ መያዝ መከልከሉ የተመለከተ ስለሆነ ድርጊቱ በአዋጁ መሠረት ወንጀል ነው፡፡ ተዋዋዮች የመዋዋል ነጻነት ቢኖራቸውም በሕግ የተመለከተውን አሥገዳጅ ሁኔታ አልፈው መዋዋል አይችሉም፡፡ በዚህ ምክንያት ዶላር በአደራ ማስቀመጥ ውል ሕገ-ወጥ ተግባር በመሆኑ ፍርድ ቤቶች ሕገ-ወጥ ውልን ሊያስፈጽሙ አይችሉም፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 27739 (በቅጽ 06 እንደታተመ) ሕገ-ወጥ ውልን ለማስፈጸም የሚቀርብ ክስ፤ የክስ ምክንያት የሌለውና በፍርድ ቤት ሊስተናድ የማይችል ስለመሆኑ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ የዶላር አደራ ማስቀመጥ ውል እንዲፈጸምላቸው ያቀረቡት ክስ ሕገ-ወጥ ውል እንዲፈጸም ዳኝነት የተጠየቀበት ስለሆነ ጉዳዩ የክስ ምክንያት የለውም ብለናል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሉ ሕገ-ወጥ ውል አይደለም በሚል በሥረ-ነገሩ እንዲታይ መወሰኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ውሳኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 199289 ሕዳር 23 ቀን 2014 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 317094 ጥቅምት 11 ቀን 2013 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በውጤቱ ፀንቷል፡፡

3. ተጠሪ ባቀረቡት ክስ የጠየቁት ዳኝነት የክስ ምክንያት የለውም በማለት ወስነናል፡፡

4. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሠ/መ/ቁጥር 173623

የካቲት 24 ቀን 2012 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካቾች ፡- 1. ቂስ መንግስት እምሩ
2. ወ/ሮ አለሚቱ አንተነህ } የቀረበ የለም

ተጠሪዎች፡- 1. መሪጌታ አስማማው መንግስት
2. ወ/ሮ ሰዋለም ዋለ } አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለው የፍርድ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የማይነቀሳቀስ ንብረት ለማስተላለፍ የሚደረግ የእርቅ ስምምነት ሊያሟላ የሚገባውን ፎርማሊቲ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአማራ ክልል ባሶ ሊበን ወረዳ ፍርድ ቤት ሆኖ በዚህ ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሳሾች በመሆን ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የአሁን አመልካቾች በተጠሪዎች ላይ በመሰረቱት ክስ በጁቤ ከተማ ቀበሌ 01 ሰፈር 3 የሚገኝ 14 ዚንጎ ቆርቆሮ ቤት ያለቤትን በ250 ካሬ ሜትር ላይ የሚገኝ ቤት ከአቶ ፍቃዱ መኮንን እና ፈንታ ከበደ ገዝተው ካርታና ፕላን በጸደቀበት ወቅት በልጃቸው በአሁን 1ኛ ተጠሪ ስም አስመዝግበው በራሳቸው ገንዘብ 52 ዚንጎ ቆርቆሮ አድርገው ያስገነቡትን ቤት ወደ ስማቸው እንዲያዛውሩላቸው ተጠሪዎችን ሲጠይቁ ተጠሪዎች ፈቃደኛ ባለመሆናቸው በሽማግሌ አማካኝነት ተደራድረው በቀን 20/06/2007 ዓ/ም ባደረጉት ስምምነት ተጠሪዎች ቤቱን ሊያስረክቧቸውና አመልካቾች ደግሞ ለተጠሪዎች ብር 60,000.00 ለመክፈል ከተስማሙ በኋላ

ተጠሪዎች ብር 60,000.00 ተቀብለዉ ግምቱ ብር 120,000.00 የሆነዉን ቤት እንዲያስረክቧቸዉ ሲጠይቁ ለማስረከብ ፈቃደኛ አለመሆናቸዉን በመግለጽ ቤቱን እንዲያስረክቧቸዉ እንዲወሰንላቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪዎች ለክሱ ባስሙት ክርክር ለክሱ መሰረት የተደረገዉ በቀን 20/06/2007 ዓ/ም የተጻፈ ዉል ዉላችን አይደለም፡፡ የማይገባ ብልጽግና ለማግኘት ብለዉ በሀሰት በማዘጋጀት አስመስለዉ በመፈረም ያዘጋጁት ዉል በመሆኑ ሕጋዊ ዉል የለም፡፡ የቤቱን ስመ ሀብት ለማዞር ተስማምተን የተዋዋለልነዉ ዉል የለም፡፡አመልካቾች የቤት ግንባታ እንዲገነቡ የፈቀደላቸዉ የለም፡፡ቤቱን በአዲስ ማስተር ፕላን ያሰራነዉ እኛ ነን በማለት ክሱ ዉድቅ እንዲረግላቸዉ በመጠየቅ መከራከራቸዉን የክልሉ ፍርድ ቤቶች ዉሳኔዎች ግልባጭ ያሳያል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን ያየዉ የባሶ ሊበን ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0125799 ላይ የግራ ቀኝ ምስክሮች በመስማትና ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን የእርቅ ስምምነት ሰነድ በመመርመር በቀን 20/10/2009ዓ/ም በዋለዉ ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪዎች ዉሉን አልተዋዋልንም አሻራዉ ይመርመርልን በማለት በተከራከሩት መሰረት ፊርማ ለማስመርመር ለማመሳከሪያ የሚሆን የ2ኛ ተጠሪ ፊርማ ባለመገኘቱ ፊርማዉ ሊመረመር ባይችልም ምስክሮች ከሰጡት ምስክርነት ቃል በቀን 20/06/2007 ዓ/ም በክሱ የተጠቀሰዉን በ1ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኘዉን ቤት አመልካቾች ብር 60,000.00 ለ1ኛ ተጠሪ ከፍለዉ 1ኛ ተጠሪ ደግሞ ቤቱን ለማስረከብ መስማማታቸዉን ማረጋገጡን በመግለጽ ዉሉ የተደረገበትም ፎርም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1719/1 መሰረት ተቀባይነት ያለዉ ነዉ በማለት ተጠሪዎች ቤቱን እንዲያስረክቡና ስመ ሀብቱን በአመልካቾች ስም እንዲያዞሩ አመልካቾችም ብር 60,000.00 እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪዎች በዉሳኔዉ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለምስራቅ ጎጃም ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 0132514 ላይ በቀን 26/11/2009ዓ/ም በዋለዉ ችሎት በሰጠዉ ትዕዛዝ ይግባኙን በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዟል፡፡በመቀጠልም አመልካቾች አቤቱታቸዉን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዉ ችሎቱ በመ/ቁጥር 0371102 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 29/02/2011 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ የማይንቀሳቀስ ንብረት ለማስተላለፍ የሚደረግ ዉል በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723 መሰረት በጽሁፍና ዉል ለመዋዋል ሥልጣን በተሰጠዉ አካል ፊት ቀርቦ መመዝገብ እንዳለበት ስለተደነገገ በተያዘዉ ጉዳይ ግራ ቀኝ ያደረጉት ዉል የቤት ስመ ሀብት ለአመልካቾች

ለማካወርና ብር 60,000.00 ለመክፈል የተደረገ ስምምነት እንደመሆኑ ዉሉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723 መሰረት ስላልተደረገ ሕገወጥ በመሆኑ በዚህ ዉል መነሻ ተጠሪዎች ቤቱን እንዲያስረክቡ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነዉ በማለት የስር ፍርድ ቤቶችን ዉሳኔ ሽሯል፡፡አመልካቾች በቀን 27/05/2011 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት በዚህ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታቸዉ ይዘት በአጭሩ የሚከተለዉ ነዉ፡፡

ለክሱ መሠረት የተደረገዉ በቀን 20/06/2007 ዓ/ም የተፈጸመዉ ዉል በሽማግሌ የተደረገ የእርቅ ዉል ስምምነት በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723 መሰረት በዉል አዋዋይ ፊት እንዲደረግ ሕግ አያስገድድም፡፡የእርቅ ዉል ስምምነት በዉል አዋዋይ ፊት ስላልተደረገና ስላልተመዘገበ ተፈጻሚነት የለዉም መባሉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ቤቱ የአመልካቾች እንደሆነና አመልካቾች እንደገነባን ተማምነን ተጠሪዎች ቤቱን ሊያስረክቡንና በስማችን ሊያዞሩ በሽምግልና ጨርሰናል፡፡ቤቱን ገዝተን በ1ኛ ተጠሪ ስም ያደረግነዉ አመልካቾች አርሶ አደሮች በመሆናችንና 1ኛ ተጠሪ ልጃችን በመሆኑ እንጅ የሸያጭ ዉል ሳይኖረን እንደሸያጭ ዉል ተቆጥሮ መወሰኑ ከክርክሩ ጭብጥ ዉጭ ነዉ ተብሎ ሊታረም ይገባል፡፡ለክሱ መሰረት የሆነዉ የእርቅ ስምምነት ሊፈጸም አይገባም ተብሎ መወሰኑ እርቅን ዋጋ ማሳጣት ስለሆነ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነዉ ተብሎ ሊታረም ይገባል በማለት በመጠየቅ አቤቱታቸዉን አቅርበዋል፡፡

ሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታዉንና የሥር ፍርድ ቤቶችን ዉሳኔዎች መርምሮ የአመልካቾች ዳኝነት ጥያቄ የሸያጭ ዉል ይፍረስልኝ ሳይሆን ተጠሪዎች በሽማግሌ በቀን 20/06/2007 ዓ/ም ለመፈጸም ግዴታ የገቡትን ገንዘብ ይክፈሉኝ የሚል ሆኖ በስር ፍርድ ቤት የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723 ተጠቅሶ ዉድቅ የመደረጉን አግባብነት ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ትእዛዝ መስጠቱን ተከትሎ ተጠሪዎች በቀን 18/02/2012 ዓ/ም የተጻፈ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱ በአጭሩ የሚከተለዉ ነዉ፡፡

ከአመልካቾች ጋር በቀን 20/06/2007 ዓ/ም በሽማግሌ የገባነዉ ምንም አይነት ስምምነት የለም፡፡ዉል አለን በማለት ያቀረቡት ሰነድ በሀሰት የተዘጋጀ ነዉ፡፡በሀሰት አዘጋጅተዉ ዉል አለን በሚል ያቀረቡት እማኝ ሽማግሌ ያደረጓቸዉ ከአመልካቾች ጋር ጥቅም ተካፋዮች የሆኑ ልጆቻቸዉና ጓደኞቻቸዉ ናቸዉ፡፡በዉሉ ላይ ያለዉ ፊርማ የተጠሪዎች አይደለም ብለን የአሻራ ምርመራ እንዲደረግ ጠይቀን ሳይመረር ስለቀረ አሁንም እንዲመረመርልን እንጠይቃለን፡፡ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት ተጠሪዎች በምስራቅ ጎጃም ዞን ፍትህ መምሪያ ሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ የሥራ ሂደት ፊት በተደረገ የሸያጭ ዉል በግል ገንዘባችን 1ኛ

ተጠሪ እማኝ ሆነዉ ከአቶ ፍቃዱ መኮንን እና ከወ/ሮ ፈንታየ ከበደ የገዛነዉ እንጅ የአመልካቾች አይደለም፡፡ቤቱን አመልካቾች አልገነቡም፡፡ዉሉ ሕገወጥ ዉል ስለሆነ እንደዉሉ ለመፈጸም ሕግ ስለማያስገድደን የአመልካቾች አቤቱታ የሕግ መሰረት የለዉም ተብሎ ዉድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካቾች በተጠሪዎች በቀረበ መልስ ላይ በቀን 19/03/2012 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ የተመዘገበዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲል የያዘዉ ጭብጥ ጉድለት ያለበት በመሆኑ ጭብጡን በመለወጥ የማይነቀሳቀስ ንብረት ለማስተላለፍ የሚደረግ የእርቅ ስምምነት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723 ስር በተደነገገዉ መሰረት ካልተደረገ እና የዉሉ መኖር ከተካደ ዉጤቱ ምን ሊሆን ይገባል የሚል ጭብጥ በመያዝ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በተሰጠ ዉሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት አመልካቾች በራሳቸዉ ገንዘብ በልጃቸዉ በ1ኛ ተጠሪ ስም የገዙትና ተጨማሪ ግንባታ በመፈጸም አሻሽለዉ የሰሩት እንደሆነ በመግለጽ የተከራከሩ ቢሆንም የቤቱ ስመ ሀብት በአሁን 1ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑ በግራ ቀኝ የታመነ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡አመልካቾች ከተጠሪዎች ጋር በቀን 20/06/2007 ዓ/ም በአስታራቂ ሽማግሌዎች አስታራቂነት ፈጸምን ባሉት የእርቅ ዉል ተጠሪዎች ቤቱን ለአመልካቾች ለማስረከብና ስመ ሀብቱንም በአመልካቾች ስም አዛዉረዉ ለማስመዝገብ እንዲሁም አመልካቾችም ብር 60,000.00 ለተጠሪዎች ለመክፈል መስማማታቸዉን በመግለጽ በእርቅ ዉሉ መሰረት ተጠሪዎች ቤቱን ለማስረከብና ስመ ሀብቱን ለማስረከብ ፈቃደኛ ባለመሆናቸዉ በፍርድ ኃይል ተገደዉ እንደ ዉሉ እንዲፈጽሙ ለማስወሰን ያቀረቡት ክስ መሆኑን ከክርክሩ ተረድተናል፡፡ የሥር ወረዳ ፍርድ ቤት የግራ ቀኝ ምስክሮች ከሰማ በኋላ በግራ ቀኙ መካከል ለክሱ መሰረት የተደረገዉ የእርቅ ዉል መደረጉን እንዳረጋገጠ በመግለጽ ወስኗል፡፡ ሆኖም ተጠሪዎች አከራካሪዉን ቤት በስማቸዉ በዉል አዋዋይ ፊት በተደረገ ዉል ገዝተዉ በስማቸዉ አስመዝግበዉና አሻሽለዉ ገንብተዉ ይዘዉ የሚገኙት ቤት እንደሆነና ለክሱ መነሻ የሆነዉን የእርቅ ዉል ከአመልካቾች ጋር እዳልተዋዋሉ፤ የእርቅ ዉሉ በሀሰት የተዘጋጀና ፊርማዉም ራሳቸዉ ቤቱን ለአመልካቾች ለማስተላለፍ ተስማምተዉ የፈረሙት ሳይሆን በሀሰት ተመሳስሎ

ተፈርሞ የቀረበ ነዉ በማለት ክደዉ መከራከራቸዉን ከወረዳ ፍርድ ቤት ጀምሮ ያሰሙት ክርክር ያሳያል፡፡

ከዚህ በላይ እንደተመለከተዉ አመልካቾች ለክርክራቸዉ መነሻ ያደረጉት በቀን 20/06/2007ዓ/ም ከተጠሪዎች ጋር አደረግን ያሉትን እና በተጠሪዎች የተካደዉን በሶስተኛ ሰዉ(ሽማግሌ) አስታራቂነት የተዋዋሉት ዉል መሆኑን በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 3322/2 ስር በተደነገገዉ መሰረት ተዋዋይ ወገኖች በአስታራቂ አማካኝነት ሲስማሙ የገቡትን ግዴታ በግልጽ በጽሁፍ በማስፈር ካልተስማሙ በዉሉ ሊገደዱ እንደማይችሉ ተደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ስር የእርቅ ዉሉ የሚፈጸምበትን የአጻጻፍ ስርዓት(ፎርም) በተመለከተ የእርቅ ዉሉ የተዋዋዮችን ግዴታ በግልጽ በሚያሳይ ሁኔታ በጽሁፍ እንዲደረግ የተደነገገ ቢሆንም የእርቅ ዉል በሕግ ሥልጣን በተሰጠዉ ዉል አዋዋይ ፊት(ፍርድ ቤትን ጨምሮ) እንዲደረግ በፍትሐብሔር ሕጋችን ስለእርቅ በሚደነግገዉ ልዩ ክፍል ከቁጥር 3318 እስከ 3324 ድረስ ባሉ ድንጋጌዎች በግልጽ አልተደነገገም፡፡እነዚህ ድንጋጌዎች በዋናነት ተፈጻሚነታቸዉ ተዋዋይ ወገኖች ወደ ፍርድ ቤት ያልመጣን የተጀመረ ክርክር ለማቆም ወይም ለወደፊት የሚፈጠረዉን ክርክር አስቀድመዉ ለማስቀረት በመፈለግ የሚያደርጉትን ዉል በተመለከተ ነዉ፡፡

ከላይ የተመለከተዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በፍርድ ቤት እየታየ ያለን ክርክር ተከራካሪዎች በእርቅ ለመጨረስ ሲፈልጉ የእርቅ ስምምነቱ የሚደረግበት ስነ ስርዓት፣ የእርቅ ስምምነቱ የሚይዛቸዉ ፍሬ ነገሮችና የእርቅ ስምምነቱ ጉዳዩን በያዘዉ ፍርድ ቤት ለሕግና ለሞራል ተቃራኒ አለመሆኑ ተጣርቶ በፍርድ ቤቱ ጸድቆ ከፍርድ ቤቱ መዝገብ የሚያያዝበት ስርዓት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ከቁጥር 274-277 ድረስ ባሉ ድንጋጌዎች ተዘርግቷል፡፡ አከራካሪዉ ጉዳይ በማንኛዉም አይነት መብት ላይ የተመሰረት ቢሆንም በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት የእርቅ ስምምነት ሲፈጸም የእርቅ ዉሉ በግልጽ ጉዳዩን እየዳኘ ባለዉ ፍርድ ቤት ጸድቆ ስለሚመዘገብ በማያሻማ ሁኔታ ተከራካሪዎች በአከራካሪዉ ጉዳይ ላይ ሊፈጸም የሚችል የእርቅ ዉል ስለመፈጸማቸዉ አስረጂ ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723/2 ሥር የማይንቀሳቀስ ንብረቶችን ባለቤትነት… ለማስተላለፍ…የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከቱ የክፍያ ወይም የማዛወር ስምምነቶች ሁሉ በጽሁፍና በሚገባ አኳኋን በፍርድ ቤት መዝገብ ወይም ዉል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠዉ አካል መደረግ እንዳለባቸዉ ተደንግጓል፡፡በዚህ ድንጋጌ " 'የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከቱ

የክፍያ ወይም የማዛወር ስምምነቶች' ተብሎ የተገለጸዉ በእንግሊዝኛዉ ቅጅ ላይ 'Any contract by which an immovable is divided and any compromise relating to an immovable shall be in writing and registered with a court or notary.'" የሚል ይዘት ያለዉ ነዉ፡፡ ይህም በአማርኛዉ ቅጅ ላይ ስምምነቶች ሁሉ ተብሎ የተገለጸዉ በእንግሊዝኛዉ ቅጅ any compromise ተብሎ ከተገለጸዉ ጋር ተያይዞ ስታይ በድርድር ወይም በእርቅ የማይንቀሳቀስ ንብረት ለማስተላለፍ የሚደረግ ስምምነቶችን የሚያካትት እንደሆነ የሚያሳይ ነዉ፡፡ በተያዘዉ ጉዳይ ለክሱ መሰረት የሆነዉ ዉል የእርቅ ስምምነት እንጅ የቤት ሽያጭ ዉል ነዉ የሚል ክርክር በግልጽ ባይቀርብም የእርቅ ስምምነት የለም የሚል ክርክር በተጠሪዎች መቅረቡ እንደተጠበቀ ሆኖ የእርቅ ስምምነት የተደረገበት ዓላማ በተጠሪዎች ስም ተመዝግቦ የሚገኘዉን ቤት ስመ ሀብት ለአመልካቾች ማስተላለፍና ቤቱንም ለማስረከብ በአንጻሩ ደግሞ አመልካቾች ለተጠሪዎች ብር 60,000.00 እንዲከፍሉ ለማድረግ በመሆኑ የዉሉ ዓላማ ክፍያ ተቀብሎ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ማስተላለፍ ነዉ፡፡በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723 መሰረት የቤት ባለቤትነትን ለማስተላለፍ የሚደረጉ <u>ስምምነቶች ሁሉ</u> (ሰረዝ የተጨመረበት)በሕግ ፊት የጸኑ የሚሆኑት በጽሁፍ ሲደረጉ ብቻ ሳይሆን የኸዉ የጽሁፍ ዉል በሕግ ስልጣን በተሰጠዉ አዋዋይ ፊት ወይም በፍርድ ቤት የተፈጸመ ሲሆን ነዉ፡፡ ሕጉ በዚህ አግባብ የተቀረጸበት ዋና ዓላማም የማይንቀሳቀስ ንብረቶችን ለማስተላለፍ የሚደረጉ ስምምነቶች ጠበቅ ያለ ፎርም እንዲከተሉ ልዩ አጽንኦት ለመስጠት መፈለጉን ለማሳየት እና በተዋዋዮች መካከል በሕግ ፊት የሚጸና ዉል እንዲኖር ለማድረግ ካለዉ ዓላማ እንደሆነ ይታመናል፡፡ይህም ተዋዋዮች ትልቅ ጠቀሜታ ያለዉን የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ለማስተላለፍ ያደረጉትን ዉል ፈቅደዉ የፈጸሙት መሆኑን ለማረጋገጥ፣ የንብረቱን ባለቤትነት የሚያስተላልፈዉ ሰዉ በንብረቱ ላይ የጸና የባለቤትነት መብት ያለዉ መሆኑን ለማረጋገጥ፣ዉሉ የተፈጸመበትን ትክክለኛ ቀን ለማረጋገጥ እድል በመስጠት የንብረት ባለቤትነት ለመጠበቅና የዉሎች ዋስትና ለማረጋገጥ የሚሰጠዉ ጠቀሜታ የጎላ ነዉ፡፡ስለሆነም የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነትን ከማስተላፍ ጋር በተያያዘ የተከሰተ ክርክር ነገር ግን ወደ ፍርድ ቤት ያልቀረበ ወይም ለወደፊት የሚፈጠር ክርክር አስቀድሞ ለማስቀረት የሚደረግ የእርቅ ስምምነት በዚህ የሕግ ድንጋጌ ማዕቀፍ ዉስጥ ሊገባ እንደሚገባ የድንጋጌዉ ይዘትና መንፈስ ያስገነዝባል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካቾች ለክሳቸዉ መሰረት ያደረጉት ዉል በአስታራቂ አማካኝነት በተደረገ እርቅ ተጠሪዎች ክፍያ በመቀበል የቤት ባለቤትነትን ለማስተላለፍ ተስማምተዋል የተባለ ዉል የሚመለከት በመሆኑ ሕጉ በሚጠይቀዉ መሰረት በጽሁፍ የተደረገ ቢሆንም በሕግ ሥልጣን

በተሰጠዉ ዉል አዋዋይ ፊት ወይም በፍርድ ቤት የተደረገ ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሕጉ አንቀጽ 1723/2 ስር የተደነገገዉን ዉሉን በሕግ ፊት የጸና የሚያደርገዉን ሁለተኛዉን መስፈርት አያሟላም፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ክፍያ በመቀበል የቤቱን ስመ ሀብት ለማስተላለፍና ቤቱን ለማስረከብ ተደረገ የተባለዉንና ለክሱ መሰረት ተደረገ የተባለዉን ይህንን የእርቅ ዉል ተጠሪዎች አለፈጸምንም በእርቅ ዉሉ ላይ በተጠሪዎች ተፈረመ የተባለዉንም ፊርማ አልፈረምንም በሀሰት የተዘጋጀ ነዉ በማለት በግልጽ ክደዉ የተከራከሩ በመሆኑ በተዋዋዮች መካከል ዉል አለመኖሩን ያሳያል፡፡

ስለሆነም የሥር የባሶ ሊበን ወረዳ ፍርድ ቤት የእርቅ ዉል መደረጉን ምስክሮች እንዲያስረዱ በማድረግ ምስክሮች የሰጡትን ቃል መሰረት በማድረግ በሕግ ፊት በሚጸና አኳኋን ያልተደረገና በተጠሪዎችም የተካደ የቤት ባለቤትነት ለማስተላለፍ የተደረገ የእርቅ ዉል ዉጤት እንዲኖረዉ መወሰኑና በዚህ ዉሳኔ ላይ የቀረበዉን ይግባኝ የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት መሰረዙ መሰረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ይህንን ስህተት ጉዳዩን በሰበር ያየዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ማረሙ ሕጉን ተግባራዊ አደረገ ከሚያስብል በስተቀር የፈጸመዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ባለመኖሩ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ዉ ሳ ኔ

የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 0371102 ላይ በቀን 29/02/2011 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ የባሶ ሊበን ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0125799 ላይ በቀን 20/10/2009ዓ/ም የሰጠዉን ዉሳኔ እና የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0132514 ላይ በቀን 26/11/2009ዓ/ም የሰጠዉን ትእዛዝ በመሻር መወሰኑ ተገቢ በመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡

በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

ት እ ዛ ዝ

የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለክልሉ ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጥ

ንብረት

የኢትዮጲያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰ.መ.ቁ. 217447

ጥቅምት 03 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ አለሙ ታፈሰ -ጠበቃ መንበረ ስላሴ በዛብህ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን -አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ታህሳስ 4 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 259615 ሐምሌ 2 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 212381 ህዳር 17 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የቤት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች ከሳሽ፤ በዚህ

የሰበር ክርክር የሌለው የአራዳ ክ/ከተማ አስተዳደር መሬት ይዞታ አስተዳደር የሽግግር ግዜ አገልግሎት ጽ/ቤት እና የአሁን ተጠሪ ደግሞ በቅደም ተከተላቸው 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል። የአሁን አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- የቤት ቁጥር 388 ተብሎ የሚታወቀውን ባለ ሁለት ክፍል መጋዘን አዋጅ ቁጥር 47/67 ከመውጣቱ በፊት ከብሔራዊ ሀብት ልማት አክስዮን ማህበር በ1956 ዓ.ም የተከራዩ መሆኑን፤ አመልካች ይዞታው ስላልበቃቸው ባለው ክፍት ቦታ ተጨማሪ መጋዘን እንዲሰራላቸው ጠይቀው ስላልተሰራላቸው በራሳቸው ወጭ የቤት ቁጥር 388/2 የሚል መለያ የተሰጠውን ቤት ሰርተው ኪራይ ሲከፍሉ ቆይተዋል፤ አዋጅ ቁጥር 47/67 ከወጣ በኋላ በቤት ቁጥር 388 የሚታወቀውን ቤት ተጠሪ ተረክቦ ለአመልካች አከራይቷቸዋል፤ የቤት ቁጥር 388/2 በተመለከተ በራሳቸው ወጭ የሰሩት ንብረታቸው በመሆኑ አስፈላጊውን ሁሉ አሟልተው የስር 1ኛ ተከሳሽን ካርታ እንዲሰራላቸው ቢጠይቁትም መልስ ሳይሰጥ ቤቱንና የቤቱ አካል የሆነውን 1279 ካ.ሜ ይዞታ በቤት ቁጥር 388 ስር በማካተት ካርታ አዘጋጅቶ ለተጠሪ የሰጠው መሆኑን በመግለጽ ካርታው ተሰርዞ ተጠሪ በ1279 ካ.ሜ ይዞታ ላይ መብትና ጥቅም የለውም ተብሎ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው።

የአሁን ተጠሪ በሰጠው መልስ አመልካች የቤት ቁጥር 388 ተከራይ ሆነው በአገኙት አጋጣሚ ለሰሩት መጋዘን የኪራይ ተመን ተሰርቶላቸው በተከራይነት ሲገለገሉበት የቆዩበት ቤት የመንግስት ቤት ነው፤ አመልካች በይዞታው ላይ የይዞታ ማረጋገጫ የላቸውም፤ በ1956 ዓ.ም ለተሰራ ቤት በወቅቱ በሚመለከተው መስሪያ ቤት ማረጋገጫ አልተሰጠበትም፤ አመልካች ያቀረቡት ማስረጃ የቤት ባለቤት መሆናቸውን አያረጋግጥም፤ በአከራካሪው ንብረቱ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ የያዘው ተጠሪ ነው፤ አመልካች የመጋዘን እድሳት ፈቃድ ተጠሪን መጠየቃቸው ቤቱ የተጠሪ መሆኑን ማመናቸውን የሚያሳይ መሆኑን በመግለጽ አመልካች ያቀረቡት የካርታ ይዘሰረዝልኝ ጥያቄ እና የባለቤትነት መብት ይረጋገጥልኝ ጥያቄ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል።

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም አመልካች ክርክር የቀረበበትን ቤት ስለመስራቱ ተጠሪ አልካደም፤ በወቅቱ አመልካች ቤት ሲሰራ የተቃወመው አካል የለም፤ የቤት ቁጥር 388/2 ራሱን ችሎ ማህደር የተደራጀለት እና የቦታና ቤት ግብር አመልካች የሚከፍልበት እንደሆነ ተረጋግጧል፤ መብራትና ውሃ አመልካች ማስገባታቸው ተረጋግጧል፤ በቅጽ 008 ላይ የቤት ቁጥር 388/2/ በአመልካች ስም እንደተመዘገበ ተረጋግጧል፤ ተጠሪ ያቀረበው የይዞታ

ማረጋገጫ ግራቀኙ አለመግባባታቸውን ሳይፈቱ አመልካችን ሳያካትቱ ለተጠሪ ብቻ እንደተሰጠ የተረጋገጠ እና በስር 1ኛ ተከሳሽ የታመነ ነው፣ ስለሆነም የስር 1ኛ ተከሳሽ ለተጠሪ የሰጠው የይዞታ ማረጋገጫ ተሰርዞ የስር 1ኛ ተከሰሽ ግራቀኙ የይዞታ መጠን ክፍፍሉን ተስማምተው ካላቀረቡለት የግራቀኙን የመጋዘን የይዞታ መጠን መሰረት በማድረግ በፕሮፖርሽን የይዞታ መጠናቸውን ለይቶ እንዲያስተናግዳቸው በማለት ወስኗል።

ተጠሪ ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታውን አቅርቧል። ፍርድ ቤቱም አመልካች አዋጅ ቁጥር 47/67 ከመውጣቱ በፊት ሰርተው እየተጠቀሙ መሆኑን ገለጹ እንጅ ይዞታው ሰነድ አልባ ከመሆኑ አንጻር በመመሪያ ቁጥር 17/2006 መሰረት የራሳቸው ስለመሆኑ የሚያሳይ በ1988 ዓ.ም በተነሳው አየር ካርታ ላይም ሆነ በ1997 ዓ.ም አየር ካርታ ላይ የሚታይ ስለመሆኑ ያቀረቡት ማስረጃ የለም፤ አመልካች ቤቱን እንዲያድስ በደብዳቤ ጠይቆ ቤቱን እንዳሳደሰው እንጅ የባለቤትነት መብት የተሰጠው ስለመሆኑ ማስረጃ አልቀረበም፤ የአራዳ ክ/ከተማ በውዝፍ ይዞታዎች የሽግግር ጊዜ መስተንግዶ ፕሮጀክት ዴስክ በላከው ማስረጃ በአመልካችና በልጆቻቸው ማህድር ከቤት ቁጥር 388/2 ጋር ያላቸውን ግንኙነት የሚገልጽ ሲሆን አራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 1 አስተዳደር ማስረጃ ሲታይ ግን የቤት ቁጥር 388 የሆነ ቤት የተጠሪ ንብረት መሆኑን ገልፀው የላኩ መሆኑን፣ የቤት ቁጥር 388/2/ የቤት ቁጥር 388 አካል የሆነና የተጠሪ ይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የተሰጠበት መሆኑ ተረጋግጧል፤ አመልካች በቤት ቁጥር 388/2 ተጠሪ በንብረቱ ላይ ኪራይ ክፈል እያለ ሁከት እየፈጸመ ነው በማለት ግራ ቀኙ ክርክር አድርገው ጉዳዩ እስከ ፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ደርሶ የሰበር ችሎቱም በመ.ቁ 99451 በቀን26/3/2009 ዓ.ም ተጠሪ አመልካች ኪራይ ክፈል ማለቱ ሁከት አይደለም በማለት የሰጠው ውሳኔ በቤቱ ላይ የባለቤትነት መብት እንዳለው የሚያረጋግጥ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሮታል።

አመልካችም ይህንኑ ውሳኔ በመቃውም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታቸውን ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኙ ተሰርዟል።

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ታህሳስ 4 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በስር ፍርድ ቤት የቀረበውን ማስረጃ በአግባቡ አልመዘነም፤ የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ በስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያላቀረበውን ክርክር መሰረት በማድረግ የሰጠው ውሳኔ ስህተት ነው፤ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአመልካችን የሁከት ይወገድልኝ ጥያቄ ውድቅ ሲያደርግ የአመልካችን የባለቤትነት

መብት የመጠየቅ መብታቸውን በመጠበቅ ነው፤ አመልካች ለክርክር መነሻ የሆነው ቤት አዋጅ ቁጥር 47/67 ከመውጣቱ በፊት በግል ገንዘባቸው ስለመስራታቸው የታመነ በመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 6/2/፣ 7/1/ እና 11/3/ መሰረት አመልካች ከህግ የመነጨ መብት የሚያጎናጽፋቸው ነው፤ አከራካሪው ቤት ራሱን ችሎ ማህደር ተዘጋጅቶለት በቤት ባለቤትነት መመዝገቢያ ቅጽ 008 በአመልካች ስም ተመዝግቦ ግብር ሲከፍሉበት መቆየታቸው ተረጋግጧል፤ አመልካች ቤቱን ሲሰሩ የተቃወማቸው አካል የሌለ በመሆኑ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 105125፣ በመ.ቁ. 30101 እና በመ.ቁ. 36638 በተሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት የቤቱ ባለቤት ናቸው፤ ለተጠሪ ካርታ የተሰራው በግራቀኙ መካከል ያለው አለመግባባት ሳይፈታ ነው፣ የስር 1ኛ ተከሳሽ ካርታ የሰራው በጂአይኤስ ላይ የሚታየውን ይዞታ

አጠቃሎ ለቤት ቁጥር 388 የሰጠ መሆኑን በስር ፍ/ቤት ተረጋግጦ ባለበት ከፍተኛው ፍ/ቤት ይህንን አልፎ የሰጠው ውሳኔ የማስረጃ ምዘናን መርህ የሚጥስ ነው፤ በመሆኑም በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ እና ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ የቤት ቁጥር 388/2 የሆነውን አመልካች መሰራቱ ተረጋግጦ ባለበት እና ተጠሪም መሰራቱን አምኖ ክርክር አቅርቦ ባለበት ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ መሻሩ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ይግባኝ ሰሚ ችሎት የቀረበውን የይግባኝ ቅሬታ መሰረዙ ህጉን የተከተለ መሆን አለመሆኑ ለማጣራት የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል።

ተጠሪ መጋቢት 20 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው መልስ ይዘት በአጭሩ፡- ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያላቀረበውን ክርክር በከፍተኛ ፍርድ ቤት አላቀረበም፤ አመልካች አከራካሪው ቤት የራሳቸው ቢሆን ኖሮ ለማደስ ተጠሪን አያስፈቅዱም ነበር፤ አመልካች ያቀረቡት የግብር ደረሰኝ ያልተሟላና የባለቤትነት መብት ለማረጋጥ በቂ አይደለም፤ በጂአይኤስ ላይ ቤቱ የተጠሪ እንደሆነ ተረጋግጧል፤ በግራቀኛችን መካከል የአከራይ ተከራይ ግንኙነት ያለ ሲሆን አመልካች ቦታ ሲጠባቸው ቤት የሰሩ በመሆኑ ተጠሪ አመልካች ቤት ሲሰራ አልተቃወመም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት የለውም፤ በአዋጅ ቁጥር 47/67 አንቀጽ 5/1

መሰረት ከ500 ካ.ሜ በላይ መያዝ የማይፈቀድ ሆኖ ሳለ አመልካች ተፈቅዶላቸው ስለመስራታቸው አላስረዱም፤ አመልካች በግል የገነቡት ቤት የቤት ቁጥር 388 አካል እንደሆነ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 99451 የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበት እና በአዋጅ ቁጥር 47/67 አግባብ ተወርሶ ለአመልካች በኪራይ የተሰጠው የመንግስት ቤት ነው፤ በመሆኑም በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠው ወሳኔ እና ትዕዛዝ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመለል እኛም የቀረበውን አቤቱታ በግራ ቀኙ መካከል በስር ፍ/ቤት ከተደረገው አጠቃላይ ክርክር እና ከተሰጡ ውሣኔዎች እንዲሁም ከማስቀረቢያ ነጥቡ አኳያ ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች በስር ፍ/ቤት አቅርበውት የነበረው ክስ ከላይ እንደተመለከተው አመልካች ከመንግሥት በኪራይ ይዘውት በሚገኙት ተጨማሪ መጋዘን እንዲሰራላቸው ጠይቀው ስላልተሰራላቸው በራሳቸው ወጭ የቤት ቁጥር 388/2 የሚል መለያ የተሰጠውን ቤት ሰርተው ኪራይ ሲከፍሉ መቆየታቸውን ፤ አዋጅ ቁጥር የሰሩትን ቤት የቤት ቁጥር 388/2 በሚል ተሰይሞ በራሳቸው ወጭ የሰሩት ንብረታቸው በመሆኑ አስፈላጊውን ሁሉ አሟልተው የስር 1ኛ ተከሳሽን ካርታ እንዲሰራላቸው ቢጠይቁትም መልስ ሳይሰጥ ቤቱንና የቤቱ አካል የሆነውን 1279 ካ.ሜ ይዞታ በቤት ቁጥር 388 ስር በማካተት ካርታ አዘጋጅቶ ለተጠሪ የሰጠው በመሆኑ ካርታው እንዲሰረዝላቸው የሚል ነው፡፡

ከማስቀረቢያ ነጥቡ አኳያ የሚያከራክረውን የቤ/ቁ/ 388/2/ የተባለውን መጋዘን አመልካች በግል ገንዘባቸው በመንግሥት ይዞታ ላይ መስራታቸው ባለሀብት ሊያደርጋቸው ስለመቻል አለመቻሉ በስር ፍ/ቤት በአግባቡ ተመርምሮ ስለመወሰን አለመወሰኑ መጣራት የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

አመልካች በክሳቸው እንዳነሱት የቤ/ቁ. 388 የሆነውን መጋዘን ተከራይተው ሲሰሩ የቆዩና መጋዘን ስለጠበባቸው በራሳቸው ወጪ የሚያካራክረውን የቤ/ቁ. 388/2 የተሰኘውን የገነቡና ከመንግሥት ጋር የኪራይ ውል ገብተው ሲጠቀሙ የቆዩ መሆኑን የገለፁ ሲሆን ተጠሪም ይህን በመካድ አልተከራከረም፡፡ የአመልካች ክርክር ይህን በራሴ ወጪ የገነባሁትን መጋዘን አካቶ የተሰራው ካርታ ህገ ወጥ ነው የሚል ነው፡፡ ሆኖም ግን የሚያከራክረው መጋዘን የቤ/ቁ/ 388 አካል ነው በሚል በ2005 ዓ.ም. ለተጠሪ ካርታ ተሰርቶ የተሰጠው ሲሆን፣ የቤ/ቁ. 388 ደግሞ

ተጠሪ የሚያከራየው የመንግሥት ሀብት መሆኑ በአመልካች ያልተካደና አዲሱን መጋዘን የገነቡትም በዚሁ በመንግሥት ይዞታ ስር ባለ ባዶ ቦይ መሆኑን ራሳቸው አረጋግጠዋል፡፡ ለዚሁ ለሚከራከሩበት ገነባሁት ለሚሉትም መጋዘን ከተጠሪ ጋር የኪራይ ውል ተዋውለው ሲጠቀሙ የቆዩ መሆኑን በስር ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠና አመልካችም የሚያምኑት ነው፡፡

ከይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ ለመመልከት እንደተቻለው አመልካች በተጠሪ ላይ በዚሁ በሚያከራክረው መጋዘን ላይ ግብር ልከፍል አይገባኝም በሚል የሁከት ክስ አቅርበው እስከፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ ሁከት የለም ተብሎ ተወስኗል፡፡

በኢፌዲሪ ህግ መንግስት አንቀፅ 80(3)(ሀ) እና በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 10(1) እንደተመለከተው ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው የዳኝነት ስልጣን በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ውስጥ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞ ሲገኝ በሰበር አይቶ የማረም ነው፡፡በዚህ አግባብም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር ሰሚነት ስልጣኑን ተግባራዊ ሲያደርግ ፍሬ ነገርን በተመለከተ በዋነኝነት መነሻ የሚያደርገው ስልጣን ባላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ነው፡፡አሁን በያዝነው ጉዳይከላይ ከተነሱት አጠቃላይ ክርክሮች መገንዘብ የተቻለው አመልካች መንግሥት በሚያስተዳድረው ይዞታ ላይ ግንባታ መፈፀማቸው የንብረቱ ባለቤት የማያደርጋቸው መሆኑን ነው፡ከላይ ከተነሱት አጠቃላይ ክርክሮች መገንዘብ የተቻለው አመልካች መንግሥት በሚያስተዳድረው ይዞታ ላይ ግንባታ መፈፀማቸው የንብረቱ ባለቤት የማያደርጋቸው መሆኑን ያሳያል፡፡ እንዲሁም መንግሥት ሳያውቅም ይሁን በመንግሥት እውቅና በመንግሥት በሚተዳደር ይዞታ ላይ ግንባታ በመገንባት የሚገኝ ባለሀብትንነት የሌለ በመሆኑ የአመልካች ጥያቄ የማስረጃም ሆነ የህግ ድጋፍ የሌለው ከመሆኑ አኳያ የስር ፍርድ ቤቶች ማስረጃን የመስማት፤የመመርመርና የመመዘን ስልጣናቸውን ተጠቅመው የደረሱበት ድምዳሜ በዚህ ችሎት ሊለወጥ የሚችለው የስር ፍርድ ቤቶች በማስረጃ ምዘና ረገድ የፈፀሙት ስህተት ከተገኘ ብቻ ሲሆን ይህ ችሎት ባደረገው ምርመራ በስር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የተፈፀመ የማስረጃ ምዘና መርህ ጥሰት ሆነ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያልተገኘ በመሆኑ የቀረበውን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ውሣኔ</u>

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 259615 በ02/11/2013 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡

በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በግራ ቀኙ የወጣ ወጪ ካለ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
የውሣኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡

<u>መዝገቡ ውሣኔ ስላገኘ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡</u>

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ.መ.ቁ 217195

ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ወ/ሮ ፍርኑስ ፈንቱ -- አልቀረቡም

ተጠሪ፡- የደብረማዊ ንዑስ ማዘጋጃ ቤት -- አልቀረቡም

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍርድ</u>

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሕዳር 17 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 03-102586 ሐምሌ 09 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር ጉዳዩን የማየት የሥረ -ነገር ስልጣን የላቸውም በሚል ሲል የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳየ የሥረ-ነገር ስልጣን ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካች በቀን ሕዳር 18 ቀን 2013 ዓ.ም በተጻፈ የክስ አቤቱታ በይልማና ዴንሳ ወረዳ ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ የነበራቸውን መሬት ለአመልካችና ለልጆቻቸው የቤት መስሪያ ቦታ ሳይሰጥና

በቀሪው ይዞታ ላይ ካሳ ሳይከፈላቸው ተጠሪ ይዞታውን ለሌሎች ግለሰቦች የሰጠባቸው በመሆኑ ለአመልካችና ለልጆቻቸው የቤት መስሪያ እንዲሰጣቸው፣ በቀሪው ይዞታ ደግሞ ተገቢው ካሳ እንዲከፈላቸው ዳኝነት በመጠየቃቸው ነው፡፡

ተጠሪ ታሕሳስ 5/2013 ዓ.ም በተጻፈ መልስ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና በፍሬ ነገር መልስ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱም አመልካች የካሳ ጥያቄ የሚያቀርቡት በአስተዳደራዊ መንገድ ሆኖ በይግባኝ በከፍተኛ ፍ/ቤት መቅረብ ያለበት መሆኑን፣ ሰበር ሰሚው ፍ/ቤት ክስ እንዲያቀርቡ የወሰነላቸው የቦታ ጥያቄ እንጅ የካሳ ጉዳይ ጭምር አለመሆኑን፣ ለአመልካች እና ለ1ኛ ልጃቸው 750 ካ.ሜ ቦታ የተሰጣቸው መሆኑን፣ ሌሎቹ ልጆች ግን መስፈርቱን የማያሟሉ መሆኑን፣ ቀሪውን ይዞታ ተጠሪ የማይፈልገው መሆኑን በመግለጽ መልሱን አቅርቧል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም የግራቀኙን ምስክሮች በማቅረብ የሰማ ሲሆን አመልካች 500 ካ.ሜ፣ 1ኛው የአመልካች ልጅ 250 ካ.ሜ ይዞታ ያገኙ መሆኑን ቀሪ ልጆች መመሪያ ቁጥር 26/2008 ን መስፈርት ማለትም በወቅቱ ከአመልካች ጋር በስፍራው የማይኖሩ በመሆኑ ምክንያት መሬት ያልተሰጣቸው መሆኑን የቀረበው ማስረጃ ያስረዳል በሚል አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ ያልተቀበለው ሲሆን፣ ካሳን በተመለከተ አመልካች ካሳ ያልወሰደች መሆኑ በተጠሪ የታመነና ተጠሪ ትውሰድ በማለት በችሎት የገለጸ በመሆኑ ተጠሪ ለህዝብ አገልግሎት እንዲውል ከወሰደው መሬት ተመጣጣኝ ካሳ ለአመልካች እንዲሰጥ በሚል ወስኗል፡፡

በአመልካች በኩል ይግባኙ የቀረበለት የባህርዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በትዕዛዝ ያጸናው ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በበኩሉ የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ለህዝብ ጥቅም ለማዋል በሚወሰድ ንብረት አስመልክቶ የማከራከር የሥረ-ነገር ሥልጣን ያለው ከፍተኛ ፍ/ቤት ስለመሆኑ ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 15/2/ሠ/ድንጋጌ ለመገንዘብ የሚቻል በመሆኑ የቀረበውን ክርክር የወረዳው ፍ/ቤት የማከራከር የሥረ-ነገር ሥልጣን ሳይኖረው መወሰኑና ከፍተኛው ፍ/ቤት በይግባኝ ማረም ሲገባው ይግባኙን መሰረዙ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት ነው በማለት የአመልካችን ሥልጣን ባለው አካል ክስ የማቅረብ መብቷን ጠብቆ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ሕዳር 17 ቀን 2014 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍ/ቤቶች ትእዛዝ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የሕግ ስሕተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍሬ ቃሉም የስር ወረዳ ፍ/ቤት ተጠሪ ካሳ እንዲከፍል በሰጠው ውሳኔ ላይ ክርክር ባልተነሳበት ሁኔታ የክልሉ ሰበር

ሰሚ ችሎት አመልካች ይግባኝ ባሉበት መዝገብ አመልካችን በሚጎዳ መልኩ የወረዳውን ፍ/ቤት ውሳኔ መሻሩ ተገቢ አይደለም፣ ለህዝብ ጥቅም ሲባል የገጠር መሬት የሚነሳባቸው አርሶ አደሮች ቦታ አሰጣጥና ካሳ አከፋፈል መመሪያ ቁጥር 7/2010 አንቀጽ 36 እና የተሻሻለው መመሪያ ቁጥር 44/2013 አንቀጽ 60 ላይ በተጠቀሰው የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት መሰረት አመልካች ጉዳዩን ወደ ወረዳ ፍ/ቤት ያቀረቡበት አግባብ ተገቢ ሆኖ ሳለ የስር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት የሌለውን የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 15 በመጥቀስ ውሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች ለጠየቁት ዳኝነት የወረዳ ፍ/ቤት የሥረ-ነገር ሥልጣን የለውም የመባሉን አግባብ አርሶ አደር ካሳ አከፋፈል እና ቦታ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 7/2010 እና የተሻሻለው መመሪያ ቁጥር 44/2013 አንጻር ለማጣራት ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል።

ተጠሪ በቀን መጋቢት 22/2014 ዓ.ም በተጻፈ መልስ አመልካች ጉዳዩን ለስር ወረዳ ፍ/ቤት ያቀረቡት መመሪያ ቁጥር 7/2010 ም ሆነ 44/2013 ከመውጣቱ በፊት በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች በወቅቱ በነበረው መመሪያ ቁጥር 26/2008 እና በአዋጅ ቁጥር 455/1997 አንቀጽ 11 እንዲሁም በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 15 ላይ የተቀመጠውን ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ ውሳኔ የሰጡ መሆኑን፣ የክልሉ ሰበር ችሎት አመልካች አግባብ ባለው አካል መብታቸውን የመጠየቅ መብት አላቸው በማለት ወሰነ እንጅ አመልጃች ያቀረቡትን መብት በመመርምር ያሳጣቸው መብትም ሆነ የተጣለባቸው ግዴታ የሌለ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለ ሊባል የማይችል መሆኑን በመግለጽ መልሱን አቅርቧል።

አመልካች በበኩላቸው ከተጠሪ በቀረበው መልስ ላይ ሚያዚያ 13 ቀን 2014 ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ አመልካች ያቀረቡት የካሳ አነሰኝ ጉዳይ ሳይሆን ለአመልካችና ለ3 ልጆቻቸው ትክ መሬት ሊሰጣቸው እንደሚገባ በመግለጽ ዳኝነት የጠየቁ በመሆኑ የሥር ወረዳ ፍ/ቤት የሥረ-ነገር ስልጣነ አለው በማለት ቀድመው ያቀረቡትን መከራከሪያ በማጠናከር ተከራክረዋል።

የግራቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው። ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል።

አመልካች በስር ፍርድ ቤት ካቀረቡት ክስ ይዘት በግልጽ መገንዘብ የቻልነው ሕጋዊ መብታቸው ሳይጠበቅ የገጠር መሬታቸው የተወሰደባቸው መሆኑን በመግለጽ መብታቸው እንዲጠበቅ ክስ ያቀረቡ መሆኑን ነው፡፡ ይህም አመልካች በገጠር መሬት ላይ ያላቸውን የይዞታ እና የመጠቀም መብት መሠረት በማድረግ ክስ ያቀረቡ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 52/2 ድንጋጌ ይዘት በግልጽ መገንዘብ እንደሚቻለው የወረዳው ፍርድ ቤት በገጠር መሬት ይዞታ እና የመጠቀም መብት ላይ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን እና የሚነሱ ክርክሮችን ተቀብሎ የማየት የስረ ነገር ስልጣን አለው፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች ክስ ያቀረቡት በገጠር መሬት ላይ ያላቸውን የይዞታ እና የመጠቀም መብት መሠረት በማድረግ በመሆኑ ከላይ በተገለጸው የአዋጁ ድንጋጌ መሠረት የወረዳው ፍርድ ቤት ጉዳዩን አከራክሮ የመወሰን የስረ ነገር ስልጣን አለው፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በዚህ አግባብ ተመልክቶ የፍሬነገር ክርክሩን መርምሮ መወሰን ሲገባው ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት የሌለውን የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 15/2/ሠ/ ድንጋጌን በመጥቀስ የወረዳው ፍ/ቤት የማከራከር የሥረ-ነገር ሥልጣን የለውም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

4. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 03-102586 ሐምሌ 09 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
5. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በውሳኔ የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ የግራቀኙን ክርክር በስር ፍርድ ቤቶች ከተሰጠው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሮ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341/1 መሠረት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
6. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ.መ.ቁ.165593

ሚያዚያ 28 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡....1. ተክሊት ይመሰል

2. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

3. ቀነዓ ቂጣታ

4. ተሾመ ሽፈራው

5. ፀሐይ መንክር

አመልካች፡..... . . ወ/ሮ ዉቤ በላይነህ፡- ጠበቃ አቶ ነቢያት ግርማ ቀርበዋል

ተጠሪ፡..... . . .1. ወ/ሮ ሰናይት ሀብተስላሴ

2. ወ/ሮ መሰለች መርጊያ } ቀርበዋል

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍርድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች ተከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪዎች ደግሞ ከሳሾች ሁኖ ሲከራከሩ ነበር። ይህ ጉዳይ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.211663 በ30/2/2011 ዓ.ም የሰጠዉን ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከቱ ነዉ።

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ ከሳሾች (የአሁን ተጠሪዎች) ባቀረቡት ክስ በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 1 የቤት ቁጥር 347 የሆነዉን መኖሪያ ቤት እና በ610 ካ.ሜ ይዞታ ላይ የሚያርፈዉን ግብር የሚንገብርበት ሲሆን ሕጋዊ የግንባታ ፈቀድ አዉጥተን ግንባታ የጀመርን ቢሆንም በስተደቡብ ምስራቅ በኩል አዋሳኞችን የሆኑት ተከሳሽ ባቀረቡት አቤቱታ ምክንያት የየካ ክ/ከተማ አስተዳደር ወረዳ 1 ቀን ግንባታ ፍቃድ ክትትልና ቁጥጥር ጽ/ቤት ግንባታዉን እንዲናቆም አድርጎናል። ነገር ግን ተከሳሽ በስተደቡብ ምስራቅ 4 ሜትር ይዞታችን ዉስጥ ገብተዉ ሰርቪስ ቤት መገንባታቸዉ በመሐንዲስ የታወቀ ሲሆን ተከሳሽ ይህን ይዞታ እንዲያስረክቡን

ቢንጠይቅም ፈቃደኛ ስላልሆነ ተከሳሽ በሕገ ወጥ መንገድ የገነቡትን ግንባታ አፍርሰዉ ይዞታዉን እንዲያስረክቡን በማለት ከሷል፡፡

በዚህ ክስ ላይ በተከሳሾች የተያዘ እና የተገነባዉ ግንባታ የለም፤ ተከሳሽ የከሳሽን ግንባታ ያስቆምነዉ ከሳሽ ድንበር አልፈዉ ግንባታቸዉ ነዉ፤ ተከሳሽ ሰርቪስ ቤቱን ከሳሾች ይዞታችን ዉስጥ ገብተዉ ነዉ የገነቡት ያሉት ሀሰት ነዉ፤ ቤቱ የተገነባዉ ከ15 ዓመት በፊት ነዉ፤ ይህም ደግሞ በ2004 ዓ.ም በተሰጠ ካርታ ላይ በግልጽ ይታያል፤ ክሱ ዉድቅ ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን የየካ ክ/ከተማ መሬትና ልማት ማናጅመንት ጽ/ቤት በማጣራት በሰጠዉ ዉሳኔ ተከሳሽ አሁን ግንብተዉ ያለዉ ቤት ወደ ከሳሽ ካርታ ከተሰጣቸዉ ይዞታ ዉስጥ 27.3 ካ.ሜ አልፎ የተገነባ መሆኑን አረጋግጦ ሪፖርት በማቅረቡ ተከሳሽ በከሳሾች ይዞታ ዉስጥ ገብተዉ የገነቡትን ግንባታ እንዲያነሱ እና 27.3 ካ.ሜ ይዞታ ለከሳሾች እንዲያስረክቡ ወስኗል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የቀረበለትን ይግባኝ ዉድቅ በማድረግ የሥር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች ህዳር 12 ቀን 2011 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ የአሁን ተጠሪዎች የአመልካች ወደ እኛ ይዞታ 4 ሜትር አልፋለች የሚል ሆኖ እያለ የሥር ፍ/ቤት ይህን አልፎ ከ15 ዓመት በፊት የተሰራዉን ሰርቪስ ቤት በመስመር ካርታም በ1997 ዓ.ም የተነሳ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ቀርቦ እያለ የሥር ፍ/ቤቶች ይህን ሳይመረምሩ የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የማስረጃ ምዘና ስህተት ስለሆነ ሊታረምልኝ ይገባል፡፡ የአሁን አመልካች ያቀረብነዉን ክርክር ለማስረዳት የሰዉ ምስክሮች ዝርዝር አቅርበን እያለ የሥር ፍ/ቤት ሳይሰማ እና ስለጉዳዩ ከሚመለከተዉ አካል ተጨማሪ ማስረጃ ጠይቀዉ ሳያጣሩት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፤በዚህ ጉዳይ ተጠሪዎች 4 ሜትር ተገፍተናል በማለት ካቀረቡት ክስ አንጻር የሥር ፍ/ቤቶች 27.3 ካ.ሜ ገፍተዋል በማለት የመወሰናቸዉን አግባብነት፤ ለመመርመር ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ባዘዘዉ መሰረት ታህሳስ 5 ቀን 2011 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ በመልሱም ይዘት በአጭሩ፡ የአሁን አመልካች ያለ ተጠሪዎች ፈቃድ በይዞታችን ላይ ቤት መስራቷ

በሕጋዊ ካርታ የተረጋገጠ በመሆኑ የሰዉ ምስክሮች ሊፈርስ የሚችል አይደለም ምስክር መስማት ተገቢ አይደለም፤ ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ጉዳይ የሰጡት ዉሳኔ ሕጋዊና ተገቢ በመሆኑ ጸንቶልን መዝገቡ እንዲዘጋልን የጠበቃ አበል ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች በበኩላቸዉ የሰበር አቤቱታቸዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የማራ ቀኛቸዉን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርመሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የአሁን ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ የጠየቁት ዳኝነት ተጠሪዎች ይዞታቸዉን በስተደቡብ ምስራቅ በኩል 4 ሜትር አልፈዉ ሰርቪስ ቤት በመገንባታቸዉ ይህን ግንባታ አንስተዉ ይዞታዉን እንዲለቁላቸዉ ጠይቋል፡፡ የአሁን አመልካች በበኩላቸዉ ባቀረቡት ክርክር ይህን ክስ ክዳዉ የተከራከሩ ሲሆን፤ በዚህ ይዞታ ላይ ቤቱ የተገነባዉ ከ15 አመት በፊት በመሆኑ የቀረበዉ ክስ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡ በዚህ ረገድ የየካ ክ/ከተማ መሬትና ልማት ማናጅመንት ጽ/ቤት ስለይዞታዉ አጣርቶ ባቀረበዉ ሪፖርት አመልካች በካርታ ከተመለከተዉ የተጠሪዎች ይዞታ መካከል 27.3 ሜትር አልፈዉ ግንባታ መገንባታቸዉን በማረጋገጥ ገልጸዋል፡፡ ይህ በሥር ፍ/ቤት የቀረበ ክርክርና የተረጋገጠ ፍሬ ነገር በመሆኑ በሕጉ አግባብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደሚታወቀዉ ከሳሽ በክስ ማመልከቻዉ ላይ የሚጠይቀዉን ዳኝነት በዝርዝር መግለጽ እንዳለበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.224 ሥር ተመልክቷል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር እንደተመለከተዉ ‹‹ከሳሽ በሚያቀርበዉ የክስ ማመልከቻ ላይ በተለይ ወይም በምትክ ወይም በተለዋዋጭ የሚጠይቀዉን ዳኝነት መግለጽ አለበት፡፡ ነገር ግን ከሳሹ በጉዳዩ ላይ እንዲሰጠዉ የሚጠይቀዉ ዳኝነት ጠቅላላ ሲሆን ፍ/ቤቱ የክስ ጭብጥና የማስረጃዉን አካባቢ ሁኔታ መሰረት በማድረግ ትክክለኛ መስሎ የታየዉን ፍርድ ሊሰጠዉ ይችላል›› በማለት ደንግጎታል፡፡ ፍ/ቤትም እንደጭብጥ በመያዝና በማጣራት ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ መስጠት የሚገባዉ የተጠየቀዉን ዳኝነት መሰረት በማድረግ እንደሆነ ግልጽ ነዉ፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.182 (1) ሥር እንደተመለከተዉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተከራካሪዎቹ ወገኖች በዝርዝር ባላቀረቡት ወይም በግልጽ ባላመለከቱት ጉዳይ ላይ ፍርድ ለማስጠት አይችልም፡፡...በማለት ይደነግጋል፡፡

ከዚህ አንጻር አሁን የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት የአሁን አመልካች የተጠሪዎች ይዞታ አልፈዉ ይዘዉ ግንባታ ማከናወናቸዉ በሚመለከተዉ የከተማ አስተዳደር አካል የተረጋገጠ ቢሆንም የከተማዉ አስተዳደር ያቀረበዉ ሪፖርት አመልካች የተጠሪዎችን ይዞታ 27.3 ካ.ሜ አልፈዉ ይዘዋል የሚል ሲሆን ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ ደግሞ የጠየቁት ዳኝነት አመልካች የተጠሪዎችን ይዞታ ድንበር አልፈዉ ይዘዋል ያሉት በስተደቡብ ምስራቅ በኩል 4 ሜትር ብቻ እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች በሰጡት ዉሳኔ ተጠሪዎች በክሳቸዉ ከጠየቁት ዳኝነት ዉጪ አመልካች 27.3 ካ.ሜ ይዞታ ላይ የገነቡትን ግንባታ አንስተዉ ይዞታዉን እንዲለቁ መወሰናቸዉን የዉሳኔዉ ግልባጭ ያሳያል፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪዎች በክሳቸዉ ከጠየቁት ዳኝነት በላይ መወሰናቸዉን እና ይህ ደግሞ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.182 (1) እና 224 (1) ድንጋጌዎችን የሚጥስ ሆኖ እናገኛለን፡፡ የአሁን አመልካች የተጠሪዎችን ይዞታ 27.3 ካ.ሜ ድንበር አልፈዉ መያዛቸዉ በባለሙያ ሪፖርት የተረጋገጠ ቢሆንም ተጠሪዎች በክሳቸዉ ከጠየቁት ዳኝነት በላይ ስለሆነ አመልካች ወደ ተጠሪዎች ይዞታ በስተደቡብ ምስራቅ በኩል 4 ሜትር ገብተዉ የሰሩትን ግንባታ ሊያነሱና ይህን 4 ሜትር ይዞታ ብቻ ለተጠሪዎች ለቀዉ ሊያስረክቡ ይገባል ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ የጠየቁት ዳኝነት ይዞታቸዉን በስተደቡብ ምስራቅ በኩል አመልካች 4 ሜትር አልፈዉ ስለያዙባቸዉ በዚህ ቦታ ላይ የሰሩትን ግንባታ አንስተዉ ይዞታዉን እንዲያስረክቡ ጠይቀዉ እያለ ከተጠየቀዉ ዳኝነት በላይ 27.3 ካ.ሜ ይዞታ ላይ ያለዉን ግንባታ አፍርሰዉ አመልካች ለተጠሪዎች እንዲያስረክቡ በማለት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.122488 በ19/6/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በ211663 በ30/2/2011 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

የአሁን አመልካች የተጠሪዎችን ይዞታ በስተደቡብ ምስራቅ በኩል 4 ሜትር አልፈዉ የሰሩትን ግንባታ አፍርሰዉ እንዲያነሱ እና ይህንኑ 4 ሜትር ይዞታ ለተጠሪዎች ለቀዉ ሊያስረክቡ ይገባል ብለናል፡፡

የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡

ግራ ቀኛቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ።

በ13/3/2011 ዓ.ም የተሰጠዉ የአፈጻጸም የእግድ ትዕዛዝ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል።

መዝገቡ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

<u>የልዩነት ሀሣብ</u>

ዳኞች በተራ ቁጥር 5 የተሰየምኩት ዳኛ ከሌሎች ባልደረቤቼ በሚከተለው ምክንያት በሃሣብ ተለይቻለሁ። ተጠሪዎች በእርግጠም በሥር ፍ/ቤት ክስ ያቀረቡት በደቡብ ምሥራቅ በኩል 4 ካ.ሜ ይዞታ አመልካች አልፈው ግንባታ ገንብተውብናል አፍርሰው ይልቀቁልን በማለት ክስ አቅርበዋል። የሥር ፍ/ቤት የሚመለከተውን አካል ስለይዞታው ሲጠይቅ ተጠሪዎች ከአመልካች ይዞታ ላይ 27.3 ካ.ሜ የያዙ መሆኑን ነገር ግን አለ የተባለው ግንባታ በ1997 ዓ.ም በተሰጠ የመስመር ካርታ ላይ የሚታይ መሆኑን ቤቱም ካርታ ለከሣሽ ከመስጠቱ በፊት የተገነባ መሆኑን አረጋግጧል።

ይህ ማለት ተጠሪዎች ይዞታውን በአካል ለአመልካች ካርታ ከመስጠቱ በፊት የያዙ እና ግንባታም ገንብተውበት የሚገኙ መሆኑን ያሳያል። እንደገና ተጣርቶ የመጣው የአስተዳደሩ ምላሽም የሥር ከሣሾች ይዞታ በአካል 583.13 ካ.ሜ. መንገድን ጨምሮ መሆኑን፣ በካርታ ግን 610 ካ.ሜ የተከሣሽ ይዞታ እያለ የተሰጣቸው መሆኑን ውሣኔው ያሳያል። ይህ ማለት ተከሣሽ ይዞታውን ይዘው ቤት ሰርተውበት እያለ በካርታ ወደ ከሣሾች ይዞታ ተካቶ መስጠቱን አመልካች ነው።

ከዚህ ክርክር መረዳት የሚቻለው አመልካች ከተጠሪዎች በካርታ እንደተመለከተው ይዞታ ገፍተው የያዙት ይዞታ መኖሩ ተረጋግጧል ። ምን ያህል ይዞታ ገፍተው ያዙ የሚለውን በተመለከተ በሚመለከተው አካል ሲጣራ 27.3 ካ.ሜ. መያዛቸው እውነታ ነው። ነገር ግን አመልካች የጠየቁት ከ15 ዓመት በፊት ይገፍ ቤት ሠርቼ ግብር እየገበርኩ ይዞታ ላይ 27.3 ካ.ሜ. እንድለቅ መወሰኑ ተገቢ አይደለም በማለት ነው።

አመልካች ክርክር ያስነሳውን ይዞታ በእጅ አድርገው ይዘው እያሉ ለተጠሪዎች ካርታ በሚሰጥበት ጊዜ ካርታ የመስጠት ኃላፊነት ያለበት አካል በቦታው ላይ ተገኝቶ ይዞታውን በባለሙያ ለክቶ ካርታ እና ይዞታውን አጣጥሞ ሊሰጥ የሚገባው እንጂ በአየር ላይ ካርታ ሊሰጥ ስለማይገባው፤ ካርታ ይዞታን ይከተላል እንጂ ይዞታ ካርታን ሊከተል ስለማይገባው

ለረጅም ጊዜ ይዞታውን ይዘው የቆዩትን ባለንብረቶች በአየር ላይ ካርታ በመስጠት ቀድሞውኑም በአካል የሌለን ይዞታ ካርታ ላይ በማስፈር ስለተሰጠ ብቻ ባለመብት የሚያደርግ ውሣኔ በሥር ፍ/ቤት መስጠቱ አና በይግባኝም መጽናቱ ተገቢ ባለመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ሊሻር ሲገባው ተሻሽሎ በአብላጫው ድምጽ መወሰኑ በበኩሌ ተገቢ አይደለም ብዬ ስለማምን በሃሣብ ተለይቻለሁ፡፡ የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚ ችሎት

የሠ/መ/ቁጥር 197998

ግንቦት 24 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች ፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች፡- አቶ ክቢ ሂርጴ ጠበቃ ምስጋኑ ሙለታ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ ደጊቱ ባሌሳ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የገጠር እርሻ መሬት ይዞታ ክርክርን የሚመለከት ነዉ፡፡ተጠሪ በኦሮሚያ ክልል በግንደበረት ወረዳ ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ በመሰረቱት ክስ በቂጥሬ ክቹ ቀበሌ በተለያዩ አምስ ቦታዎች የሚገኝ በክሱ በተራ ቁጥር 1-5 የተጠቀሱ የመሬት ይዞታዎችን አዋሳኞቹን

ጠቅሰዉ የባለቤታቸዉ አያት በ1996 ዓ/ም በስጦታ ሰጥቷቸዉ እየተጠቀሙበት እያለ አመልካች በቀን 08/11/2011ዓ/ም በጉልበት ስለያዙብኝ እዲለቁልኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስ ከ1-4ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሰ መሬት መሰረቱ የሂርጴ ቤኛ ሆኖ እሳቸዉ በ2003ዓ/ም ሲሞቱ በአመልካች እጅ ትተዉ ስለሞቱ ወራሽም ከእኔ ዉጭ ሌላ ስለሌለ እስካሁን ድረስ በእጄ የሚገኝ እንጂ ለተጠሪና ለባለቤታቸዉ የተሰጠ አይደለም፡፡ስለሆነም ተጠሪ የመክሰስ መብት የላቸዉም፡፡በ5ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሰዉ መሬት በ1984 ዓ/ም ከመንግስት አግኝቼ እስካሁን ድረስ በስሜ ተለክቶ እየተጠቀምኩበት ያለሁት እንጂ የተጠሪ አይደለም በማለት ክሱ ዉድቅ እንዲሆን በመጠየቅ ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 22860 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮና ምስክሮቻቸዉን በመስማት እንዲሁም ከገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ያስቀረበዉን ማስረጃ ጭምር መርምሮ በቀን14/05/2012 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪ ለክርክሮ መነሻ የሆኑ መሬቶችን የባለቤታቸዉ አያት ለተጠሪና ለባለቤታቸዉ በስጦታ መስጠታቸዉን የጽሁፍ ማስረጃ በማቅረብ አላስረዱም፤ በምስክሮቻቸዉም በክሳቸዉ መሰረት አላስረዱም በማለት ክሱን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዉ ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 30793 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮና ማስረጃዎችን መርምሮና መዝኖ በቀን 27/06/2012ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ለክርክሩ መነሻ የሆኑትን የመሬት ይዞታዎችን ተጠሪና ባለቤታቸዉ ከ16 ዓመታት በላይ ለጎጆ መዉጪያ ተብሎ ተሰጥቷቸዉ ስጠቀሙበት መቆየታቸዉን ማስረጃዎቹ ያሳያሉ፡፡የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 107840 ላይ በሰጠዉ ዉሳኔ የገጠር መሬት ይዞታ ለጎጆ መዉጪያ ተብሎ ለተጋቢዎች የተሰጠዉ የባልና የሚስት የጋራ ይዞታ እንደሆነ ትርጉ ሰጥቷል በማለት ለተጠሪና ለባለቤታቸዉ ለክርክሩ መነሻ የሆኑ ይዞታዎች ለጎጆ መዉጪያነት እንደተሰጠ የቀረበዉ ማስረጃ ያሳያል፡፡እንዲሁም ተጠሪ ከ16 ዓመት በላይ ሲጠቀሙበት የነበረ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም አመልካች የያዙትን አምስቱንም የመሬት ይዞታዎች ለተጠሪ ሊለቁ ይገባል በማለት በመወሰን የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ ሽሯል፡፡

በመቀጠል አመልካች ይግባኝ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዉ ፍርድ ቤቱንም በመ/ቁጥር 323530 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮና ማስረጃዎችን መርምሮ በቀን 28/01/2013ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪ መሬቶቹ በስጦታ እንደተሰጣቸዉ የጽሁፍ ማስረጃ ባያቀርቡም

በአካባቢዉ ልማድ መሰረት የጋብቻ ስርዓት በፈጸሙበት ጊዜ ሚች የባለቤታቸዉ አያት ሰዎች ፊት በቃል እንደሰጧቸዉና ይህንንም ተከትሎ ለ18 ዓመታት መረቶቹን ይዘዉ ሲጠቀሙ እንደነበር ከምስክሮች ቃል እና ከማስረጃዎቹ ተረጋግጧል፡፡በተጠቀሰዉ ስርዓት መሰረት የሚሰጥ ስጦታ በጽሁፍ ባይደረግም የአካባዉን በህል ተከትሎ የተደረገ መሆኑ ስለተረጋገጠ ክርክር የተነሳበትን ይዘታ አመልካች ለተጠሪ እንዲለቁ መወሰኑ ተገቢ ነዉ በማለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡እንዲሁም አመልካች ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታቸዉን ያቀረቡ ቢሆንም ችሎቱ በመ/ቁጥር 336177 ላይ በቀን 22/02/2013ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ ለሰበር የሚያበቃ ስህተት አልተፈጸመም በሚል በአቤቱታዉን ሰርዞታል፡፡ አመልካች በቀን 07/03/2013 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት በተጠቀሰዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታቸዉ ይዘት በአጭሩ የሚከተለዉ ነዉ፡፡

ተጠሪ ባቀረቡት ክስ ላይ የተጠቀሱትን መሬቶችን የባለቤታቸዉ አያት(የአመልካች አባት) ከባለቤታቸዉ ጋር ጋብቻ በፈጸሙበት ጊዜ በ1995 ዓ/ም በስጦታ ጎጆ መዉጪያ አድርገዉ እንደሰጧቸዉ ቢገልጹም የወረዳዉ መሬት እና አካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት የሥጦታ ዉል የለም በማለት በገለጸበትና ተጠሪም የማስረዳት ሸክማቸዉን ባልተወጡበት ጉዳዩን በይግባኝ ያዩ ፍርድ ቤቶች የወረዳዉን ፍርድ ቤት ዉሳኔ መሻራቸዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡የገጠር መሬት በስጦታ ሊተላለፍ የሚችለዉ በኦሮሚያ ክልል ገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀጽ 5/5 እና 9/5 በጽሁፍ ሆኖ ስልጣን ባለዉ አካል መመዝገብ አለበት በሚል በአስገዳጅነት ደንግጎ እያለ ከዚህ በተቃራኒ በምስክሮች ወይም በባህላዊ መንገድ ለጎጆ መዉጫ በስጦታ ሊተላለፍ ይችላል በማለት መወሰናቸዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡የተጠሪ ባለቤት ተጠሪን ካገባ በኋላ የቤተሰብ አባል አልነበረም፡፡ተጠሪ መሬቶቹ በ1995ዓ/ም በስጦታ ተላፎልናል ያሉ ቢሆንም በይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በ1997ዓ/ም የተሰጠዉ ለአመልካች አባት ነዉ፡፡መሬት የማይንቀሳቀስ ንብረት በመሆኑ ባለመብትነት የሚረጋገጠዉ በጽሁፍ ማስረጃ እንጂ በምስክሮች ቃል በስጦታ ተላልፏል በሚል ሊሆን አይችልም፡፡በ5ኛ ተራ ቁጥር ላይ የተጠቀሰዉ የእርሻ መሬት በአመልካች ስም የተመዘገበ ነዉ፡፡ስለሆነም የስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች በሰጡት ዉሳኔ ከማስረጃ ምዘና አንጻርም ሆነ ከሕግ አተገባበር አንጻር መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለፈጸሙ ይታረምልኝ በማለት አቤቱታቸዉን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ተጠሪ አከራካሪዎቹን የመሬት ይዞታዎች ያገኙት በስጦታ እንደሆነ ባመኑበት ሁኔታ ስጦታዉ የክልሉ የገጠር የመሬት አስተዳደር አዋጅ መሰረት በሚመለከተዉ አካል ባልተመዘገበበትና ባልተረጋገጠበት ሁኔታ መሬቶቹ በባህላዊ ስጦታ ለተጠሪ የተላለፉ ናቸዉ በማለት በይባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች በተሰጠ ዉሳኔ የስር የወረዳ ፍርድ ቤት ዉሳኔ የተሻረበትን አግባብ ተጠሪ ባለበት እንዲጣራ ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 30/06/2013 ዓ/ም የተፃፈ በአጭሩ የሚከተለዉን መልስ አቅርበዋል፡፡

ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆኑ የመሬት ይዞታዎችን ከባለቤቴ ጋር ከ16 ዓመት በፊት በጎጆ መዉጫነት ተሰጥቶን እየተጠቀምን የምንገኘዉ እንደሆነ ተረጋግጦ የተወሰነ በመሆኑ በይዞታችን ስር አድርገን በመጠቀም ላይ የሚንገኘዉን መሬት አመልካች እንዲለቅልን በመወሰኑ የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡የገጠር እርሻ መሬት በስጦታ ገቢ ለሌለዉ የቤተሰብ አባል ሊተላለፍ እንደሚችል በአዋጁ በግልጽ ተደንግጓል፡፡የመመዝገብ ግዴታን በተመለከተ ስጦታዉ ለሚች ባለቤት የተላለፈዉ ለጎጆ መዉጫነት እንጂ በቤተሰብ አባልነት ብቻ ስላልሆነ ለጎጆ መዉጫ የተሰጠ ማንኛዉም ስጦታ የግድ መመዝገብ አለበት የሚል ግልጽ ድንጋጌ እስከሌለ ድረስ የመመዝገብ ግዴታ ስለሌለ ከዚህ አኳያ የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡ለክርክሩ መነሻ የሆኑ የመሬት ይዞታዎችን ከባለቤቴ ጋር በጋራ ለጎጆ መዉጪያ እንደተሰጠን በስር ፍርድ ቤቶች በማስረጃ ተረጋግጦ የተወሰነ በመሆኑ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ስለሌለዉና ከማስረጃ ምዘና አንጻርም የተፈጸመ ስህተት ስለሌለ የስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ዉሳኔዎች ይጽኑልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ የተመዘገበዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር የክልሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም ማስቀረቢያ ነጥቡን ከግምት በማስገባት ጉዳዩን በይግባኝ እና በሰበር ባዩት የክልሉ ፍርድ ቤቶች በተሰጠ ዉሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም ጉዳዩ ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆኑ የገጠር እርሻ መሬት ይዞታዎችን ተጠሪ ከባለቤታቸዉ ጋር የባለቤታቸዉ አያት በጎጆ መዉጫነት ሰጥተዋቸዉ ሲጠቀሙበት ቆይተዉ አመልካች አለአግባብ እንደያዙባቸዉ በመግለጽ እንዲለቁላቸዉ እንዲወሰን ዳኝነት በመጠየቅ ያቀረቡትን ክስ መነሻ ያደረገ ሲሆን አመልካችም የተጠሪ ክስ ይዘት ይህንኑ የሚመለከት እንደሆነ አልካዱም፡፡ መሬቶቹን በተጠሪና በባለቤታቸዉ መካከል ጋብቻ ሲፈጸም የባለቤታቸዉ አያት ለጎጆ መዉጫ ስጥታቸዉ ተጠሪ ከባለቤታቸዉ ጋር ሲጠቀሙ የቆዩበት ነዉ ወይስ

አይደለም የሚለዉን አከራካሪ ጭብጥ ለማጣራት በወረዳዉ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ ምስክሮች ተሰምተዋል እንዲሁም ከሚመለከተዉ አስተዳደር አካል ማስረጃ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡የግራ ቀኙን ማስረጃ የመረመረዉ የወረዳዉ ፍርድ ቤት ተጠሪ መሬቶቹን ከባለቤታቸዉ ጋር በስጦታ ዉል ስለማግኘታቸዉ የጽሁፍ ማስረጃ በማቅረብ አላስረዱም በሚል ምክንያት ክሱን ዉድቅ ያደረገ ቢሆንም ጉዳዩን በይግባኝ ያዩት የክልሉ ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የግራ ቀኙን ማስረጃዎች መርምረዉና መዝነዉ ለክርክሩ መነሻ የሆኑትን የመሬት ይዞታዎች የተጠሪ ባለቤት አያት ተጠሪ ከባለቤታቸዉ ጋር ጋብቻ በፈጸሙበት ጊዜ በአካባቢዉ ባህላዊ ልማድ መሰረት በሰዎች ፊት በጎጆ መዉጫነት ሰጥተዋቸዉ ከ16 ዓመት በላይ ተጠሪ ከባለቤታቸዉ ጋር መሬቶቹን ይዘዉ ሲጠቀሙ ስለቆዩ በጎጆ መዉጫነት እንደተሰጣቸዉ የጽሁፍ ማስረጃ በማቅረብ ባያስረዱም የመሬቶቹ ባለመብት ተጠሪ ናቸዉ በማለት የወረዳዉን ፍርድ ቤት ዉሳኔ ሽረዋል፡፡

በመሰረቱ የገጠርም ሆነ የከተማ መሬት እና የተፈጥሮ ሀብት የባለቤትነት መብት የመንግስትና የህዝብ ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40/3 ላይ ተደንግጓል፡፡ይህንኑ ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌ ተከትሎ የወጣዉ የፌዴራል የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 456/1997 አንቀጽ 5/3 እንዲሁም በስራ ላይ ያለዉ የኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 130/99 አንቀጽ 5/5 እና 12 ድንጋጌዎች እንደሚያስገነዝቡት በገጠር መሬት የመጠቀም የይዞታ መብት የሚገኘዉ በመንግስት በሚደረግ ድልድል፣በዉርስ ወይም በስጦታ ወይም የግል ባለሀብት ከሆነ ደግሞ በኢንቨስትመንት ዉል ነዉ፡፡ስለሆነም የገጠር መሬት ላይ የባለይዞታነት መብት አለኝ የሚል ሰዉ ከእነዚህ በአንደኛዉ አግባብ ይዞታዉን ያገኘ ስለመሆኑ ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት የመሬት ይዞታዎች አስቀድሞ የተጠሪ አያት(የአመልካች አባት) የሂርጴ ቤኛ እንደነበር አከራካሪ አይደለም፡፡አከራካሪዉ ጉዳይ ለክርክሩ መነሻ የሆኑ የመሬት ይዞታዎች ለተጠሪና ባለቤታቸዉ በባለቤታቸዉ አያት በጎጆ መዉጫነት ተሰጥታቸዋል ወይስ አልተሰጣቸዉም የሚል እና የገጠር የእርሻ መሬት በጎጆ መዉጫነት መሰጠቱን ለማስረዳት ሊቀርብ የሚገባን ማስረጃ በተመለከተ ነዉ፡፡ በኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀጽ 9/5 ላይ እንደተደነገገዉ የገጠር መሬት የመጠቀም መብት ያለዉ አርሶ አደር ይዞታዉን ለቤተሰብ አባል ወይም ለልጆቹ በስጦታ ማስተላለፍ እንደሚችል ተመልክቷል፡፡የስጦታ ዉል በወረዳዉ ጽ/ቤት መመዝገብ እንዳለበት በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ደንብ ቁጥር 151/2005 አንቀጽ 3/12 ላይ የተደነገገ ቢሆንም

የስጦታ ዉሉ በተለይም በልማድ የዳበረዉ በየአካባቢዉ ማሕብረሰብ ለጎጆ መዉጫነትነት ተብሎ የሚሰጥ የገጠር እርሻ መሬት የተለየ ፎርም እንዲኖረዉ የሚያስገድድ ድንጋጌ በአዋጅ ቁጥር 130/1999 ላይ አልተመለከተም፡፡ ይህም የሆነዉ ይህ እሴት ያለዉን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጠቀሜታ ከግምት በማስገባት ጥብቅ ስርዓት መከተል አስፈላጊ እንደሆነ በማሰብ ነዉ ተብሎ ይመናል፡፡ለጎጆ መዉጫ ተብሎ የሚደረግ የገጠር መሬት ስጦታ የተለየ የዉል ፎርም እንዲኖረዉ ህጉ የግድ የሚለዉ አለመሆኑን ይህ ሰበር ችሎት በመ/ቁ/107840 እና ሌሎች መሰል መዝገቦች ላይ የሰጠዉ ዉሳኔ ያሳያል፡፡ከዚህም የምንገዘበዉ የገጠር መሬት ይዞታ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ በተለይም የባለይዞታዉ ልጅ ወይም ሌላ የባለይዞታዉ የቤተሰብ አባል ትዳር ሲይዝ ለመተዳደሪያ የሚሆን በተለምዶ ለጎጆ መዉጫ ተብሎ የሚደረግ የመሬት ስጦታ ጥብቅ የሆነ የአጻጻፍ ስርዓት ወይም የስጦታ ዉል ፎርም ባያሟላም በየማህበረሰቡ የዳበረዉን ልማድ እና ጠቃሚ እሴት ከግምት በማስገባት ሕጋዊ ዉጤት እንዲኖረዉ ማድረግ ተገቢነት ያለዉ ስለመሆኑ ነዉ፡፡

ሲጠቃለል አከራካሪዎቹ የመሬት ይዞታዎች ለተጠሪና ለባለቤታቸዉ በባለቤታቸዉ አያት ተጠሪና ባለቤታቸዉ በጎጆ መዉጫነት ሰጥተዋቸዉ ተጠሪ ከ16 ዓመታት በላይ ከባለቤታቸዉ ጋር የአመልካች አባት (የተጠሪ ባለቤት አያት) በህይወት እያሉ ጭምር በይዞታቸዉ ስር አድርገዉ ሲጠቀሙበት መቆየቱን የስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ማስረጃዎችን መርምረዉና መዝነዉ ያረጋገጡት ፍሬ ነገር፡፡ በመሆኑ አመልካች አባታዉ ወይም የተጠሪ ባለቤት አያት መሞታቸዉን ተከትሎ እንደልጅ መሬቱ ለእኔ ይገባኛል በማለት የሚያቀርቡት ክርክርም ሆነ ተጠሪ በጎጆ መዉጫነት መሬቶቹ የተሰጣቸዉ ስለመሆኑ የጽሁፍ ዉል በማቅረብ አላስረዱም በማለት የሚያነሱት ክርክር የሕግ ድጋፍ ያለዉ እንዳልሆነ አረጋግጠናል፡፡በመሆኑም ጉዳዩን በይግባኝ እና በሰበር ያዩት የክልሉ ፍርድ ቤቶች መሬቶቹ ለተጠሪ በጎጆ መዉጫነት የተሰጡ ናቸዉ በማለት የደረሱበት ድምዳሜ ከሕግ አተገባበር አንጻርም ሆነ ከማስረጃ ምዘና መርህ አተገባበር አንጻር የተፈጸመ ስህተት ባለመኖሩ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ዉ ሳ ኔ</u>

የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 30793 ላይ በቀን 27/06/2012ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 323530 ላይ በቀን 28/01/2013ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር

336177 ላይ በቀን 22/02/2013ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ፀንተዋል፡፡

በዚህ ችሎት የወጣ ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

በዉሳኔዉ መሰረት እንዲያስፈጽም የውሳኔው ግልባጭ ለክልሉ ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡

በመዝገቡ ላይ የተሰጠ የዕግድ ትእዛዝ ካለ ተነስቷል ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ውርስ

የሰ.መ.ቁ.222271

ሐምሌ 26 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡....1. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2. ቀነዓ ቂጣታ

3. ፈይሳ ወርቁ

4. ደጆኔ አያንሳ

5. ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካቾች፡- 1. አቶ ዳንኤል አወቀ

2. ወ/ሮ መዓዛሽ አወቀ

3. አቶ ታምራት አወቀ

} የቀረበ የለም

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ሀዉልቴ ታምር

2. አቶ ታዲወስ አወቀ

3. ሲ/ር ትልቅሰዉ አወቀ

4. ተማሪ ሚካኤል አወቀ

} የቀረበ የለም

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍ ር ድ

ይህ የዉርስ ሀብት ክርክር የተጀመረዉ በአማራ ክልል በሐዋ ብሔረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካቾች የሥር ከሳሾች፣ የአሁን 1ኛ ተጠሪ የሥር ተከሳሽ፣ የአሁን 2ኛ-3ኛ ተጠሪዎች የሥር ጣልቃ ገቦች ሆኖ ሲከራከሩ ነበር። ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካቾች የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.111575

በ16/6/2014 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ።

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ ከሳሾች በሥር ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ አቤቱታ ሚች ወላጅ አባታችን አቶ አወቀ ተመስገን እና ተከሳሽ በትዳር አብረዉ ሲኖሩ በዳንግላ 05 ቀበሌ ዉስጥ በ500 ካ.ሜ ቦታ ላይ ያረፈ የመኖሪያ ቤት፣ በዚሁ ከተማ ቀበሌ ዉስጥ የሚገኝ ጅምር ፎቅ የንግድ ቤት፣ በዳንግላ ብድርና ቁጠባ አክስዮን ማህበር ድርሻና ትርፍ፣ በዳንግላ ኢንዱስትሪ አክስዮን ማህበር ድርሻና ትርፍ፣ በዳንግላ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ አክስዮን ድርሻና ትርፍ፣ በመንገሻ ጀምበሬ መምህራት ቁጠባ ማህበር የተቆጠበ ገንዘብና ትርፍ፣ በትስኪ አክስዮን ማህበር ድርሻና ትርፍ፣ በአጠቃላይ ብር 10,950,000 የሚገመት ንብረት ላይ የአባታችን ድርሻ 5,975,000 ሁኖ ከዚሁ የከሳሾች ድርሻ 2,987,500 እንዲከፍሉኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል።

ተከሳሽ በዚህ ክስ ላይ ባቀረቡት መልስ መኖሪያ ቤቱንና የዳንግላ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ አክስዮን ማህበር ያለንን ድርሻ ሚች በሕይወት እያለ ለጋራ ልጆቻችን ለጣልቃ ገቦች ስጦታ አድርገንላቸዉ ዉሉም በፍትሕ ተቋም ጸድቋል፣ ስለሆነም ንብረቶቹ የሚች አይደለም። ጅምር ፎቅ የንግድ ቤት በሚችም ሆነ በተከሳሽ ስም የተመዘገበ አይደለም፤ በዳንግላ ብድርና ቁጠባ አክስዮን ማህበር ያለዉ ድርሻ ቤት ለመስራት የተወሰደዉን እዳ ሊሸፍን አይችልም፤ ከዳንግላ ኢንዱስትሪ አክስዮን ማህበር ያለዉ ድርሻም እዳን የሚሸፍን አይደለም፤ በመምህራት ቁጠባ የተቆጠበዉ ገንዘብ በግሌ የቆጠብኩኝ ስለሆነ ሊጠየቁኝ አይገባም፤ በትስኪ አክስዮን ማህበር ድርሻ የለም በማለት ተከራክሯል። ጣልቃ ገቦችም ባቀረቡት አቤቱታ የመኖሪያ ቤት እና የዳንግላ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ የአክስዮን ድርሻ ሚች እና ተከሳሽ በ2007 ዓ.ም በ18/9/2007 ዓ.ም በተደረገዉ ስጦታ የሰጡትን ስለሆነ የሚች ንብረት አይደለም በማለት ተከራክሯል።

ከዚህ በኋላ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰዉ ምስክሮች በመስማት፣ ከማህበራትና ከማዘጋጃ ቤት ማስረጃ በትዕዛዝ እንዲቀርብ በማድረግ ሚች በሕይወት እያለ ከተከሳሽ ጋር ,ሁኖ አከራካሪዉን ቤት እና የጤና ሳይንስ ኮሌጅ አክስዮን ድርሻ ለጋራ ልጆቻቸዉ ለሆኑት ለጣልቃ ገቦች በ18/9/2007 ዓ.ም በተደረገዉ የስጦታ ዉል ሰጥቷቸዉ ዉሉም በወረዳዉ ፍትሕ ጽ/ቤት ጸድቋል። በመሆኑም በስጦታ የተላለፈዉን ንብረትን ጨምሮ አጠቃላይ የሚች ንብረት ግምት ምን ያህል ነዉ ሚች ከሳሾችን ሳያካትት ያደረገዉ የስጦታ ክፍፍል ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም የሚች እዳ ምን ያህል ነዉ ከሚች እዳ ተራፊ ንብረት አለ ወይ ለከሳሾች የሚከፈል የዉርስ ሀብት አለ ወይ የሚሉትን ነጥቦች እንደጭብጥ በመያዝ፣ በዚህ መሰረት አከራካሪዉ

የመኖሪያ ቤት የከተማዉ ማዘጋጃ ቤት ባለሙያ ግምት ብር 194,843.70 መሆኑን፣ በጤና ሳይንስ ኮሌጅ ያላቸዉ አክስዮን ድርሻ ብር 28,000 መሆኑን፣ በዳንግላ ብድርና ቁጠባ አክስዮን ማህበር ብር 21,5594.40፣ በዳንግላ ኢንዱስትሪ አክስዮን ማህበር ብር 10,000፣ በመንገሻ ጀምበሬ መምህራን ቁጠባ ማህበር ብር 101,953.75፣ በመምህራን ማህበር የተቆጠበዉ ገንዘብ የጋራ ሀብት ነዉ፣ በአጠቃላይ የሟች እና የተከሳሽ የጋራ ሀብት 550,391.85 ለሁለት ሲከፈል የሟች ድርሻ ሀብት ግምት ብር 275,195.93 መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡ የሟች እዳ ደግሞ ብር 572,079.05 መሆኑ የተጋገጠ በመሆኑ የሟች የዉርስ ሀብት ከመተላለፉ በፊት የበሰለ እዳ መከፈል አለበት፡፡ በትስኪ አክስዮን ማህበር የድርሻ ሀብት የሌላቸዉ መሆኑ ተረጋገግጧል፡፡ የሟች ሀብት ግምት ካለዉ እዳ ጋር ሲመዛዘን እዳዉ ከፍ ያለ ሆኖ ስለተገኘ ከሳሾች የሚወርሱት ንብረት ስለሌላ ተከሳሽ የምትከፍለዉ ንብረት የለም በማለት ወስኗል፡፡

ከሳሾች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን በማከራከር የሟች ድርሻ ከእዳ ብር 445,135.50 ያነሳ ነዉ በማለት የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበለትን የሰበር አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካቾች በ28/6/2014 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ በዳንግላ ከተማ ቀበሌ 05 ዉስጥ የሚገኘዉ በ325 ካ.ሜ ቦታ ላይ ያረፈዉን የመኖሪያ ቤት በተመለከተ የቤቱ ግምት እንዲቀርብ ባልተጠየቀበት፣ ፍ/ቤቱም የቤቱ ግምት እንዲቀርብ ለየትኛዉም አካል ትዕዛዝ ባልሰጠበት፣ ቤቱ በገበያ ዋጋ መገመት ሲገባዉ የቤቱን የግንባታ ዋጋ ብቻ በመዉሰድ ግምቱ ብር 194,843.70 ነዉ የተባለዉ፣ ከዳንግላ ብድርና ቁጠባ አክስዮን ማህበር ተወስዷል የተባለዉ የብድር ገንዘብ ለቤት ግንባታ አለመዋሉ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ በዳንግላ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ አክስዮን ማህበር፣ በዳንግላ ከተማ ብድርና ቁጠባ አክስዮን ማህበር፣ በዳንግላ ኢንዱስትሪያል አክስዮን ማህበር እና ከመንገሻ ጀምበሬ መምህራን ቁጠባ ማህበር ያለዉ የአክስዮን ድርሻ በተመለከተ የወሰነዉ ዉሳኔ ተገቢ አይደለም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ጉዳይ የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልን በማለት አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ባዘዘዉ መሰረት መጋቢት 23 ቀን 2014 ዓ.ም በተጻፈ መልስ፡ የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ጉዳይ የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ አመልካቾች የጠየቁት የዳኝነት

ጥያቄ የህግ መሰረት የለዉም ተብሎ ዉድቅ እንዲሆንልን የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ እንዲጸናልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ አመልካቾች የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር በ21/8/2014 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ በዚህ ጉዳይ ምላሽ ማግኘት ያለበት ጉዳይ ፣የሥር ፍ/ቤቶች አከራካሪዉን የዉርስ ሀብት ያስገመቱበት አግባብና ይህን ግምት መሰረት በማድረግ ያሳለፉት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነጥብ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በዚህ መሰረት ከሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ መገንዘብ እንደሚቻለ ግራ ቀኞቸዉን ያከራከረዉን የዉርስ ሀብት የሆኑትን የመኖሪያ ቤት እና በተለያዩ ማህበራት የሚገኙትን የአክስዮን ድርሻ በተመለከተ ግምት እንደቀረበና ይህን ግምት መሰረት በማድረግ ዉሳኔ ማሳለፉን ነዉ፡፡ ነገር ግን የመኖሪያ ቤት ግምት በተመለከተ የባለሙያ ግምት መሆኑን እና የአክስዮን ድርሻ ግምት በተመለከተ ግምቱ መቅረቡን እንጂ ግምቱ ምን አግባብ እንዳደረገ የሚያመለክተዉ ነገር የለም፡፡

እንደሚታወቀዉ ለክርክር መነሻ የሆነዉ ሀብት ግምት ወይም ዋጋ በተመለከተ ተከራካሪወ ወገኖች ወይም አንደኛዉ ወገን ባለመስማማት ክርክር ያስነሳ እንደሆነ ፍ/ቤቱ አከራካሪዉን ሀብት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.132–136 ድንጋጌዎች መሰረት የሀብቱ ግምት እንዲታወቅ ማረድግ እንደሚችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.250 ሥር ተመልክቷል፡፡ በሌላ በኩል የዉርስ ሀብት ድርሻ የሚከፋፈልበት አግባብ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1079 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት መሆኑን ተመልክቷል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትና ዓላማ መረዳት እንደሚቻለዉ በሕግ የጸና ኑዛዜ ካለ የዉርስ ሀብት የክፍያዉ ሥራ በዚህ አግባብ የሚፈጸም መሆኑን፣ የዉርስ ሀብቱ ግምት የሚደረገዉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1083 እና 1084 አግባብ መሆኑን፣ የክፍያዉ ሥራ የሚከናወነዉ በወራሾች መካከል በሚደረገዉ ስምምነት መሆኑን፣ የዉርስ ሀብቱ በዓይነት የሚከፋፈል ከሆነ በዚህ አግባብ መፈጸም እንደሚገባዉ፣ ይህ ካልሆነ የዉርስ ሀብቱ በሐራጅ ተሽጦ ለወራሾች የክፍያ ድርሻ መፈጸም እንደሚገባዉ ያመለክታል፡፡ ከዚህ መገንዘብ እንደሚቻለዉ የዉርስ ሀብት የክፍያ ሥራን በተመለከተ በወራሾች መካከል ስምምነት ካለ እና ንብረቱን በዓይነት ማከፋፈል የሚቻል ከሆነ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ይህ የማይቻል ከሆነ ግን የዉርስ ሀብቱ የድርሻ ክፍያ የሚፈጸመዉ የንብረቱን የባለሙያ ግምት {Book Value} መሰረት በማድረግ ሳይሆን

በገበያ ዋጋ {Market Value} መሆን እንደሚገባዉ ያመለክታል። በመሆኑም የዉርስ ሀብቱ በወራሾች ስምምነት ወይም በዓይነት መካፋፈል ያልተቻለ እንደሆነ፣ ክፍያዉ መፈጸም ያለበት በገበያ ዋጋ መሆን እንደሚገባዉ ነዉ።

በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የሥር ፍ/ቤት አከራካሪዉን የዉርስ ሀብት ግምት ወይም ዋጋ መታወቅ ለግራ ቀኞቸዉ ክርክር እልባት ለመስጠት አስፈላጊ መሆኑን እስከተገነዘበ ድረስ፤ በሚመለከተዉ አካል አከራካሪዉ የዉርስ ሀብት የገበያ ዋጋ ተገምቶ እንዲቀርብ በማድረግ፣ የግራ ቀኙን ክርክር ከቀረበዉ የገበያ ዋጋ አንጻር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መወሰን ይገባዉ ነበር። ግራ ቀኙን ያከራካሩት ንብረቶች ሚች አቶ አወቀ ተመስገን በሕይወት እያለ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በጋብቻ ዉስጥ እያሉ ያፈሩዋቸዉ ንብረቶች መሆናቸዉ በማስረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ በመሆኑ፣ የእነዚህ ንብረቶች ግማሽ ድርሻ የአሁን 1ኛ ተጠሪ የሚስትነት ድርሻ ሲሆን፣ የንብረቶቹ ቀሪ ግማሽ ድርሻ ደግሞ የሚች የዉርስ ሀብት ድርሻ በመሆኑ ለሚች ወራሾች የሚገባቸዉ ይሆናል ማለት ነዉ፡ ነገር ግን ሚች በሕይወት እያለ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ሁኖ ለአሁን 2ኛ--4ኛ ያሉት ተጠሪዎች የመኖሪያ ቤቱን እና የጤና ሳይንስ ኮሌጅ አክስዮን ድርሻ በስጦታ አስተላልፏል የሚባል ከሆነ ይህ ስጦታ ከአመልካች መብት አንጻር እንዴት ይታያል? እንዲሁም ከዉርስ ሀብቱ የሚፈለግ የዉርስ እዳ ካለ ዕዳዉን ከፍሎ ወራሾች የሚከፋፈሉት ቀሪ የዉርስ ሀብት ድርሻ አለ ወይስ የለም? የሚለዉን ነጥብ ለይቶ ለመወሰን የዉርስ ሀብቱ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መታወቅ አለበት። በዚህ መሰረት የሥር ፍ/ቤቶች አከራካሪዉን የመኖሪያ ቤት እና በተለያዩ ማህበራት የሚገኘዉን የአክስዮን ድርሻ በሚመለከተዉ አካል በገበያ ዋጋ ተገምቶ እንዲቀርብ በማድረግ፣ የግራ ቀኙን ከዚህ አንጻር በሕጉ አግባብ በመመርመር መወሰን ሲገባቸዉ የቤቱን የባለሙያ ግምት እና የአክስዮን ድርሻ ደግሞ በዚህ አግባብ መገመቱ ባልተገለጸበት ሁኔታ ያሳለፉት ዉሳኔ የህግ ድጋፍ የለዉም ብለናል።

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች አከራከሪዉን የመኖሪያ ቤት እና አክስዮን ድርሻን በገበያ ዋጋ ተገምቶ እንዲቀርብ በማድረግ የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች አንጻር መርምሮ መወሰን ሲገባቸዉ ይህን ሳያደርጉ ያሳለፉት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል።

<u>ዉ ሳ ኔ</u>

የሐዊ ብሔረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.01-19340 በ17/7/2013 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.56134 በ10/2/2014 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.111575 በ16/6/2014 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡

የሐዊ ብሔረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የተዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ በፍርድ ሐተታዉ በተገለጻዉ አግባብ አከራካሪዉን የመኖሪያ ቤት እና የአክስዮን ድርሻ በተመለከተ የሚመለከተዉ አካል በገበያ ዋጋ ገምቶ እንዲቀርብ በማድረግ፣ በቀረበዉ ግምት ላይ የግራ ቀኙን አስተያየት በመቀበል፣ የግራ ቀኖቸዉን ክርክር በሕጉ አግባብ በመመርመር ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.343 (1) መሰረት ተመልሶለታል፡፡

የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡

ግራ ቀኙ የሰበር ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

ይህ ችሎት የካቲት 30 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠዉ የእግድ ትዕዛዝ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጥ

የሰበር መዝገብ ቁጥር 217114

ሐምሌ 25 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካቾች፡- አቶ ወልዴ ወልደገብርኤል } ጠበቃ አቶ በፍቃዱ ስዩም

ወ/ሮ አለምፀሐይ ወልዴገብርኤል ከ2ኛ አመልካች ጋር ቀርቧል

ተጠሪ፡- አቶ ደጀኔ በቀለ

አቶ ፀጋዬ በቀለ

ፓስተር ሙሉቀን በቀለ } ቀርቧል

ወ/ሮ ውድነሽ በቀለ

አቶ እንዳልካቸው በቀለ

አቶ ታዬ በቀለ

ለምርመራ ተቀጥሮ የነበረው መዝገብ ተመርምሮ ቀጣዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ተጠሪዎች ከሚቺ ወ/ሮ መንበረ ወገብርኤል ጋር የዝምድና ትስስር ሳይኖራቸው የሚቺ ባለቤት የነበሩት የተጠሪዎች አባት ለሆኑት ሚች አቶ በቀለ ጅሩ ታህሳስ 6 ቀን 1999 ዓ/ም የተደረገ የቁም የኑዛዜ ሰነድ በማያያዝ አባታቸውን በመተካት የሚች ወ/ሮ መንበረ ወ/ገብርኤል ድርሻ የሆነውን በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 የሚገኘውን ቁጥሩ 817 የሆነው ቤት እና ይዞታ ይገባናል ክርክር ፤ የተጠሪዎች አባት ነሐሴ 8 ቀን 2005 ዓ/ም ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ የቁም ኑዛዜ ሰጪዋ ወ/ሮ መንበረ ወ/ገብርኤል በሕይወት የነበሩ በመሆኑና ኑዛዜውም ሚች አቶ በቀለ ጅሩ የተናዛኟን ወ/ሮ መንበረ ወ/ገብርኤል የቀብር ሥነ ሥርዓት በአዳዲ ማሪያም ቤተክርስቲያን እንዲያስፈፅሙ የሚል ቅድመ ሁኔታ ያለበት ሆኖ ቅደመ ሁኔታው ሳይሟላ የተጠሪዎች አባት የሆኑት አቶ በቀለ ጅሩ ነሐሴ 8 ቀን 2005 ዓ/ም ሚች ወ/ሮ

መንበረ ወ/ገብርኤልን ቀድመው የኑዛዜ ወራሽነታቸውን ሳያረጋግጡ መሞታቸው እና ወ/ሮ መንበረ ወ/ገብርኤልም ህዳር 18 ቀን 2011 ዓ/ም መሞታቸው ያልተካደ እና በማስረጃ የተረጋገጠ ሆኖእያለ ፣ ኑዛዜ የተደረገበት ቤትእና ይዞታ የባልና ሚስቱ የጋራ ንብረት ሆኖ ስምምነቱ በፍርድ ቤት ባልፀደቀበት ፣ ተጠሪዎች የአባታቸው ድርሻ ወራሽ በመሆን የእንጀራ እናታቸው ከሆኑት ሟች ወ/ሮ መንበረ ወ/ገብርኤል ተካፍለው እያለ የአመልካቾች እህት ድርሻ የሆነውን የውርስ ንብረት ተጠሪዎች በምትክነት ሊወርሱ ይገባል በማለት የተሰጠው ውሳኔ የሕግ መሠረት የሌለው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ስህተቱ ታርሞ በአዲስ አበባ ከተማ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 የሚገኘው ቁጥሩ 817 የሆነው ቤት እና ይዞታ አመልካቾች የሟች እህታቸው ድርሻ ወራሾች ናቸው ተብሎ እንዲወሰንላቸው ህዳር 27 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መነሻነት መዝገቡ ተከፍቶ ለችሎት ቀርቧል፡፡

ጉዳዩ ሟቾቹ የተጠሪዎች አባት አቶ በቀለ ጅሩ እና የእንጀራ እናታቸው ወ/ሮ መንበረ ወ/ገብርኤል በጋራ የነበራቸውን በአዲስ አበባ ከተማ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 ውስጥ የሚገኝ ቁጥሩ 817 የሆነ ቤት እና ይዞታ የሟች አባታቸው ድርሻ በውርስ የተላለፈላቸው ሲሆን ፤ የእንጀራ እናታቸው ሟች ወ/ሮ መንበረ ወ/ገብርኤል ከቤቱ ያላቸውን ደርሻቸው ታህሳስ 6 ቀን 1999 ዓ/ም በተደረገ ግልጽ ኑዛዜ ለሟች አባታቸው አቶ በቀለ ጅሩ ስላስተላለፉ የአባታቸው የውርስ ድርሻ እንዲጣራላቸው ተጠሪ በሌለበት ለፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወርስ እንዲጣራ አቤቱታ አቅርበው ፍርድ ቤቱም የሟች የአቶ በቀለ ጅሩ ውርስ ስለተጣራ መጣራት ያለበት የሟች ወ/ሮ መንበረ ወ/ገብርኤል ነው በማለቱ ተጠሪዎች በዚሁ አግባብ ክሳቸውን አሻሽለው አቅርበዋል፡፡ ተጠሪዎች ተጣርቶ በቀረበው የውርስ አጣሪ ሪፖርት ላይ በሰጡት አስተያየት ሟች የእንጀራ እናታቸው ወ/ሮ መንበረ ወ/ገብርኤል ለሟች አባታቸው አቶ በቀለ ጅሩ ድርሻቸውን በኑዛዜ የሰጡ በመሆኑ አመልካቾች በክርክሩ ጣልቃ ገብተው የመከራከር መብት እና ጥቅም የሌላቸው መሆኑን ፤ ሟች ወ/ሮ መንበረ ወ/ገብርኤል ታህሳስ 6 ቀን 1999 ዓ/ም ባደረጉት ግልጽ ኑዛዜ ከሟች የተጠሪዎች አባት ጋራ ያፈሩትን የጋራ ንብረት ድርሻቸውን ሟች የተጠሪዎች አባት ለሆኑት አቶ በቀለ ጅሩ በተናዘዙት አግባብ እንዲጣራ የጠየቁ በመሆኑ አመልካቾች ወ/ሮ መንበረ ወ/ገብርኤል ኑዛዜ ሳታኖር ከዚህ ዓለም በሞት የተለየች በመሆኑ እና እናት እና አባታቸው አስቀድመው ስለሞቱ ተተኪ ወራሽነታችንን አረጋግጠናል በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት ተቃውመዋል፡፡ አመልካችቾም በሰጡት አስተያየት አቶ በቀለ ጅሩ የሞቱት ሐምሌ 8 ቀን 2005 ዓ/ም ሲሆን

ወ/ሮ መንበረ ወ/ገብርኤል ደግሞ ህዳር 18 ቀን 2011 ዓ/ም የሞቱ በመሆኑ ወ/ሮ መንበረ ወ/ገብርኤል ታህሳስ 6 ቀን 1999 ዓ/ም አድርገዋል የተባለውን ኑዛዜ አቶ በቀለ ጅሩ መቀበላቸው ባልተረጋገጠበትና አቶ በቀለ ጅሩ አስቀድሞ ስለሞቱ በኑዛዜው ላይ የተመለከተው ቅድመ ሁኔታ ባለመፈፀሙ አቶ በቀለ ጅሩ የኑዛዜ ግዴታቸውን ያልተወጡ በመሆኑ ሪፖርቱ ውድቅ እንዲሆን ጠይቀዋል፡፡

የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም አቶ በቀለ ጅሩ ከሚች ባለቤታቸው ወ/ሮ መንበረ ወ/ገብርኤል በኑዛዜ ያገኙትን ሀብት ተጠሪዎች አባታቸውን ተክተው መውረስ መቻል አለመቻላቸውን እና ሌሎች አግባብነት አላቸው ያላቸውን ጭብጥ ይዞ የግራቀኙን ምስክሮች ሰምቶ እና ተገቢ ነው ያለውን ማጣራት አድርጎ ጉዳዩን እንደመረመረው፡- በአዲስ አበባ ከተማ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 የሚገኘው ቁጥሩ 817 የሆነው ቤት እና ይዞታ ሚች ወ/ሮ መንበረ ወ/ገብርኤልና የቀድሞ ባለቤታቸው አቶ ደምሴ ወልደማሪያም ጋብቻ ውስጥ ተፈርቶ አቶ ደምሴ ወልደማሪያም ስለሞቱ ወ/ሮ መንበረ ወ/ገብርኤል የአቶ ደምሴ ወልደማሪያምን ድርሻ ለወራሾቻቸው ከፍለው ቤቱን የግላቸው ካደረጉ በኋላ ከአቶ በቀለ ጅሩ ጋር ሲጋቡ በጋብቻ ውል የጋራቸው እንዲሆን ከስምምነት የደረሱ ሲሆን ፤ ሚቺ ወ/ሮ መንበረ ወ/ገብርኤል ታህሳስ 6 ቀን 1999 ዓ/ም ባደረጉት ኑዛዜ በቤቱ ላይ ያላቸውን ድርሻ እና ማንኛውንም የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ፣ በባንክና በማንኛውም ቦታ ያለውን ንብረታቸውን ለአቶ በቀለ ጅሩ መናዘዛቸውን የኑዛዜ ይዘት የሚያመለክት በመሆኑ አቶ በቀለ ጅሩ ጠቅላላ የኑዛዜ ወራሽ ስለሆኑ ተጠሪዎች በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 908(1) (ሀ) ድንጋጌ መሠረት አባታቸውን ተክተው ሚች ወ/ሮ መንበረ ወ/ገብርኤልን ሊወርሱ የሚችሉ በመሆኑ የወ/ሮ መንበረ ወ/ገብርኤል የውርስ ሀብት ለተጠሪዎች እንዲተላለፍ በማለት የወሰነ ሲሆን አመልካቾች በውሳኔው ባለመስማማት ያቀረቡት የይግባኝ ቅሬታ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረዙ በፍርዱ መግቢያ ላይ የተመለከተውን የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

አመልካቾች ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ የመረመረው የሰበር አጣሪ ችሎቱ የኑዛዜ ተጠቃሚው ከተናዛዢ በፊት መሞታቸው ከመረጋገጡ አኳያ ሚች በህይወት እያሉ ያላረጋገጡትን መብት ወራሾች የመጠየቅ ከኑዛዜ የመነጨ ህጋዊ መብት ያላቸው መሆን አለመሆኑ መጣራት አለበት በማለቱ ተጠሪዎች በሰጡት መልስ፡- ሚች የእንጀራ እናታቸው ወ/ሮ መንበረ ወ/ገብርኤል ከሚች አባታቸው አቶ በቀለ ጅሩ ጋር የነበራቸውን ቤት ድርሻቸውን ታህሳስ 6 ቀን 1999 ዓ/ም ባደረጉት ኑዛዜ ለሚች አባታቸው ተናዘው የተጠሪዎች አባት አቶ በቀለ ጅሩ አስቀድሞ

ስለሞቱ ተጠሪዎች ወራሽነታቸውን አረጋግጠው አባታቸው በጠቅላላ የኑዛዜ ወራሽነታቸው ያገኙትን የውርስ ንብረት የእንጀራ እናታቸው ወ/ሮ መንበረ ወ/ገብርኤል ከሞቱ በኋላ አባታቸውን ተክተው የኑዛዜ ወራሽ የመሆን ከሕግ የመነጨ መብት ያላቸው በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾች በመልስ መልስ ክርክራቸው ወ/ሮ መንበረ ወ/ገብርኤል ታህሳስ 6 ቀን 1999 ዓ/ም ባደረጉት ኑዛዜ አቶ በቀለ ጅሩ በሕይወት እያለሁ ይንከባከበኛል ፣ ይጦረኛል ፣ የሚያስፈልገኝን ከኔ በመሆን ያሟላልኛል እንዲሁም የቀብር ሥነ ሥርዓቴን በክብር ያስፈጽምልኛል በማለት ኑዛዜ ያደረጉ መሆኑን የቁም ኑዛዜ ስጦታው በግልጽ የሚያመለክት ሆኖ አቶ በቀለ ጅሩ የተቀመጠውን ቅድመ ሁኔታ ሳይፈጽሙ ከተናዛዢዋ ቀድሞ ስለሞቱ ተጠሪዎች የኑዛዜ ስጦታ ተተኪ ወራሾች ሊሆኑ የሚችሉበት የህግ አግባብ የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመለከት ለሰበር ቅሬታው ምክንያት የሆነው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ሕግ አንፃር መዝገቡ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡ አመልካችቾ ሟች ወ/ሮ መንበረ ወ/ገብርኤል ታህሳስ 6 ቀን 1999 ዓ/ም ያደረጉት ኑዛዜ ቅድመ ሁኔታ ያለበት ሆኖ አቶ በቀለ ጅሩ ከወ/ሮ መንበረ ወ/ገብርኤል ቀድመው በኑዛዜው ላይ የተመለከተውን ግዴታ ሳይፈጽሙ ስለሞቱ ተጠሪዎች አቶ በቀለ ጅሩን ተክተው ወ/ሮ መንበረ ወ/ገብርኤል ታህሳስ 6 ቀን 1999 ዓ/ም ያደረጉት ኑዛዜ ተጠቃሚ መሆኑን አይችሉም በማለት ተከራክረዋል፡፡ በዚህ ፍርድ ቤትም ባደረጉት ክርክርም ወ/ሮ መንበረ ወ/ገብርኤል ታህሳስ 6 ቀን 1999 ዓ/ም ባደረጉት ኑዛዜ አቶ በቀለ ጅሩ በሕይወት እያለሁ ይንከባከበኛል ፣ ይጦረኛል ፣ የሚያስፈልገኝን ከኔ በመሆን ያሟላልኛል እንዲሁም የቀብር ሥነ ሥርዓቴን በክብር ያስፈጽምልኛል በማለት ኑዛዜ ያደረጉ ቢሆንም አቶ በቀለ ጅሩ የተቀመጠውን ቅድመ ሁኔታ ሳይፈጽሙ ከተናዛዢዋ ቀድሞ ስለሞቱ ተጠሪዎች የኑዛዜ ስጦታ ተተኪ ወራሾች ሊሆኑ የሚችሉበት የህግ አግባብ የለም በማለት አመልካቾች ያቀረቡትን ግልጽ ክርክር ተጠሪዎች በማስተባበል ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ ሟች ወ/ሮ መንበረ ወ/ገብርኤል ታህሳስ 6 ቀን 1999 ዓ/ም ያደረጉት ኑዛዜ በሁኔታ ላይ የተመሰረተ መሆን አለመሆኑን ፤ በሁኔታ ላይ ከተመሰረተ ሁኔታው መሟላት አለመሟላቱንና የኑዛዜውን ውጤት ተገቢነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች አንፃር ከፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገቡን በማስቀረብ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ሚቺ ከአብራካቸው የተወለደ ልጅ ስለሌላቸው በእሳቸው እና በሚቹ አቶ በቀለ ጅሩ ስም ተመዝግቦ በአዲስ አበባ ከተማ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 የሚገኘውን የቦታ ስፋቱ 450 ካ.ሜ የሆነውን የቤት ቁጠር 817 መኖሪያ ቤት ፣ ማንኛውንም በስማቸው ተመዝግቦ የሚገኝ የሚንቀሳቀስ እና የማይንቀሳቀስ ንብረት ፣ በባንክም ሆነ በየትኛውም ቦታ በስማቸው ያለውን ንብረት ድርሻቸውን ለሚንከባከቧቸው እና የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ከጎናቸው በመሆን ለሚያሚሉላቸው ባለቤተ አቶ በቀለ ጅሩ መናዘዛቸው ፤ ኑዛዜ ተቀባዩም ከህልፈተ ሕይወታቸው በኋላ የቀብር ሥነ ሥርዓታቸውን በአዳዲ ማሪያም ቤተክርስቲያን እንዲያስፈጽሙላቸው መናዘዛቸውን ሚች ወ/ሮ መንበረ ወ/ገብርኤል ታህሳስ 6 ቀን 1999 ዓ/ም ያደረጉት ኑዛዜ ይዘት ያመለክታል፡፡ ከኑዛዜው ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለው ሚቺ ከአብራካቸው የተወለደ በሕይወት እያሉ የሚንከባከባቸውና ከጎናቸው ሆኖ የሚያስፈልጋቸውን የሚያሚላላቸው ሲሞቱም የቀብር ሥነ ሥርዓታቸውን የሚያስፈጽሚላቸው ልጅ ስለሌላቸው እነዚህን ተግባራት ለሚወጡት ባለቤታቸው ኑዛዜ ማድረጋቸውን ኑዛዜው ያመለክታል፡፡ በተለይም ኑዛዜ ተቀባዩ የተኛዛኟዋን የቀብር ሥነ ሥርዓት በአዳዲ ማሪያም ቤተክርስትያን እንዲያስፈጽሙ ኑዛዜው የሚያመለክት ሲሆን ፤ ኑዛዜ ተቀባይ የሆኑት አቶ በቀለ ጅሩ ይህንኑ በኑዛዜው ላይ የተመለከተው ቅድመ ሁኔታ ሳይሚላ ህዳር18 ቀን 2011 ዓ/ም የሞቱትን ተናዛኟዋ ወ/ሮ መንበረ ወ/ገብርኤልን ቀድመው ነሀሴ 8 ቀን 2005 ዓ/ም የሞቱ መሆኑ ግራቀኙን አላከራከረም፡፡ ምንም እንኳን አቶ በቀለ ጅሩ የሚች ወ/ሮ መንበረ ወ/ገብርኤልን የጠቅላላ ሀብት ወራሽ ቢሆኑም ፤ ሚች ወ/ሮ መንበረ ወ/ገብርኤል ታህሳስ 6 ቀን 1999 ዓ/ም ያደረጉት ኑዛዜ ቅድመ ሁኔታ ያለበት በመሆኑና ሚቹ አቶ በቀለ ጅሩም በኑዛዜው ላይ የተመከለተው ቅድመ ሁኔታ ሳይሚላ አስቀድመው ስለሞቱ በኑዛዜው ላይ የተመለከተው ቅድመ ሁኔታ ባለመሚላቱ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 916 እና 918(2) ድንጋጌ መሠረት ኑዛዜውን ቀሪ የሚያደርገው በመሆኑ ተጠሪዎች መውረስ የሚችሉት በፍትሐ ብሔር ህጉ ቁጥር 826(2) መሠረት ሚች አባታቸው ያላቸውን መብት በመሆኑ ተጠረዎች ሚች ወ/ሮ መንበረ ወ/ገብርኤል ታህሳስ 6 ቀን 1999 ዓ/ም ያደረጉትን ኑዛዜ መሠረት አድርጎ ሚች አባታቸው አቶ በቀለ ጅሩን ተክተው ሊወርሱ የሚችሉበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ሚች ወ/ሮ መንበረ ወ/ገብርኤል ታህሳስ 6 ቀን 1999 ዓ/ም ባደረጉት ኑዛዜ መሠረት ተጠሪዎች ሚች አባታቸው አቶ በቀለ ጅሩን ተክተው ለመውረስ በኑዛዜው ላይ የተመለከተው ሁኔታ ባለመሚላቱ ኑዛዜው ቀሪ በመሆኑ ሚች ወ/ሮ መንበረ ወ/ገብርኤል የአመልካቾች እህት መሆናቸው አከራካሪ ስላልሆነ አመልካቾች በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 844(2) መሠረት

ያለኑዛዜ የሚወርሱ ሆኖእያለ ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ መሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ቀጣዩ ተወስኗል፡፡

ው ሳ ኔ

የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 270576 ጥቅምት 30 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ብይን እንዲሁም የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 63006 የካቲት 19 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ፍርድ ፣ ውሳኔ እና ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት **ተሽራል**፡፡

ሟች ወ/ሮ መንበረ ወ/ገብርኤል ታህሳስ 6 ቀን 1999 ዓ/ም ያደረጉትን በሁኔታ ላይ የተመሰረተ ኑዛዜ ቅድመ ሁኔታው ባለመፈፀሙ ተጠሪዎች አባታቸውን ተክተው በአዲስ አበባ ከተማ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 የሚገኘውን የቦታ ስፋቱ 450 ካ.ሜ የሆነውን የቤት ቁጥር 817 መኖሪያ ቤት የሟች ወ/ሮ መንበረ ወ/ገብርኤል ግማሽ ድርሻ ልወርሱ አይችሉም፡፡ አመልካቾች በአዲስ አበባ ከተማ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 የሚገኘውን የቦታ ስፋቱ 450 ካ.ሜ የሆነውን የቤት ቁጥር 817 መኖሪያ ቤት የሟች ወ/ሮ መንበረ ወ/ገብርኤል ግማሽ ድርሻ ያለ ኑዛዜ ወራሽ ናቸው በማለት ተወስኗል፡፡

በዚህ መዝገብ ላይ ታህሳስ 21 ቀን 2014 ዓ/ም እና የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት መዝገብ በመጣበት አግባብ ይመለስ፡፡

በሰበር ክርክሩ የደረሰውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የግላቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ.መ.ቁ.217691

ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካች፡- የሚች ወ/ሮ ዋጋዬ ወ/ማርያም ህጋዊ ወራሾች

ወ/ሮ አሳበች ፈለቀ ዘርጋዉ
ወ/ሮ አዘሪፍ ፈለቀ ዘርጋዉ ወራሽ ኤፍሬም ሳህሌ ወረታ
አቶ ከበደ ዋጋዬ ዜና
ተጠሪ፡- ወ/ሮ የሺሐረግ ከበደ

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍርድ</u>

ይህ የኑዛዜ ይፍረስልን ክርክር የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች የሥር አመልካቾች፣ የአሁን ተጠሪ የሥር ተጠሪ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካቾች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.279892 በ27/03/2014 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የአሁን አመልካቾች በሥር ፍ/ቤት ባቀረበዉ አክስታቸዉ ወ/ሮ ዋጋዬ ወ/ማርያም በ23/1/2004 ዓ.ም የሞቱ ሲሆን፣ እኛ የሚች አክስታችን ተተኪ ወራሾች መሆናችንን አረጋግጠናል፤ ተጠሪ ሚች አክስታችን በ7/8/98 ዓ.ም በቤት ቁ.1334 ላይ አደረጉልኝ ያሉትን ኑዛዜ አድርገዉልኛል በማለት በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.861/04 በማጽደቅ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የንብረት ክፍፍል የጠየቀ በመሆኑ፣ ሚች ኑዛዜዉን አድርገዋል በተባለበት ጊዜ ሚች ጤነኛ ያልነበሩና ኑዛዜዉ የኑዛዜን ፎርማሊቲ የማያሟላ በመሆኑ፣ ይህ ኑዛዜ እንዲፈርስልን በማለት በአዲስ አበባ

ከተማ ፍ/ቤቶች አቤቱታ አቅርበን ኑዛዜዉ እንዲፈርስ ዉሳኔ የሰጡ ቢሆንም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ.177909 በ30/8/2012 ዓ.ም ጉዳዩ የከተማዉ ፍ/ቤቶች ስልጣን ባለመሆኑ ስልጣኑ ለሆነው የፌደራል ፍ/ቤቶች ነዉ ባለዉ መሰረት ሚች ያደረጉት ኑዛዜ ይፍረስልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የአሁን ተጠሪ በዚህ ክስ ላይ ባቀረበዉ አመልካች ከዚህ በፊት በመ.ቁ.45314 እና 45310 በነበረን ክርክር ስለኑዛዜው መኖር ያዉቁ ነበረ፤ አመልካቾች ስልጣን ለሌለዉ ፍ/ቤት ክርክር አቅርበዉ ከሶስት ዓመት በላይ ሲከራከሩ ቆይተዉ፣ የሰበር ሰሚ ችሎቱ ዉሳኔ ከሰጠ በ8 ወራት በኋላ ያቀረቡት ክስ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.973 (3)፣ 974 እና የፌዴራል ሰበር ችሎት የሰ.መ.ቁ.82585፣ 36604 ኑዛዜዉ መኖሩን ባወቁ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ክስ ማቅረብ ሲገባቸው ያላቀረቡ በመሆኑ እና በፍ/ብ/ሕ/ቁ.973 (2) በማንኛውም ሁኔታ ሚች ከሞቱ ከ5 አመት በኋላ ማቅረብ የማይችሉ በመሆኑ፣ አመልካቾች ያቀረቡት ክስ በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማንሳት ተከራክሯል፤ በአማራጭም ክርክር አቅርቧል፡፡

ከዚህ በኋላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት ባሳለፈዉ ብይን የአሁን ተጠሪ አመልካቾች ከዚህ ቀደም በነበረዉ ክርክር ኑዛዜዉን ያዉቃሉ በማለት ያቀረቡት ክርክር ሲታይ አመልካቾች የክርክሩ ተከፋይ ስላልነበሩ ተቀባይነት የለዉም፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰ.መ.ቁ.177909 በ30/8/2012 ዓ.ም ዉሳኔ የሰጠ ሲሆን፣ አመልካቾች ኑዛዜዉ እንዲፈርስላቸዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቤቱታ ያቀረቡት ጥር 26 ቀን 2013 ዓ.ም በመሆኑ፣ የሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ከሰጠበት እና ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ ያለዉ ጊዜ ከ8 ወር በላይ በመሆኑ፤ ይህ ይርጋን የሚያቋርጠዉ ሁኔታ ካቆመበት እና ሰበር ሰሚ ችሎት ከሰጠ ጀምሮ በሶስት ወር ዉስጥ ኑዛዜዉ ይፍረስልን ክስ ማቅረብ ሲገባቸዉ ያላደረጉ በመሆኑ፣ ክሳቸዉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.973 (3) እና 974 መሰረት በሶስት ዓመት ይርጋ የሚታግድ ነዉ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካቾች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ይግባኙን በትዕዛዝ ዉድቅ በማድረግ የሥር ፍ/ቤትን ብይን በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

አመልካቾች ታህሳስ 7 ቀን 2014 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ የአመልካቾች አክስት የሆኑት ወ/ሮ ዋጋዬ ወ/ማርያም በ7/9/1998 ዓ.ም አድርገዋል የተባለዉ ኑዛዜ እንዲፈርስልን በወቅቱ ተቃዉሞ አቅርበን የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤት ኑዛዜዉ እንዲፈርስ ዉሳኔ የሰጠ ቢሆንም

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.177909 በ30/8/2012 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ ጉዳዩ መታየት ያለበት በፌዴራል ፍ/ቤት ነዉ ብሎ የአመልካቾችን መብት ጠብቅ ክርክሩ እንዲቀጥል በተደረገዉ አግባብ የቀረበ እንጂ አዲስ ተቃዉሞ ያለመሆኑን እና የቀደመዉ ተቃዉሞ ሆኖ ሳለ የሥር ፍ/ቤት ክርክር ላይ የነበርን መሆኑን የቀረበዉን ማስረጃ ሳይገነዘብ የሰጠዉ የአመልካቾች ክስ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.973 (3) እና 974 መሰረት በሶስት ዓመት ይርጋ የሚታገድ ነዉ በማለት ዉድቅ በማድረግ ያሳከፈዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ፣ የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ እንዲሻርልን፣ የፍሬ ነገር ክርክሩ እንዲቀጥል፣ ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልን በዝርዝር አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣ይህ ክርክር የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ በመደበኛ ፍ/ቤት የመክሰስ መብታቸው ተጠብቆ በዉሳኔዉ መሰረት የቀረበ ክስ ሲሆን የስር ፍ/ቤት በ3 ወር ይርጋ ይታገዳል በማለት የወሰነበትን አግባብነት ለማጣራት ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲትሰጥ ባዘዘዉ መሰረት ጥር 9 ቀን 2014 ዓ.ም በተጻፈ መልስ፡ አመልካቾች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ክስ የማቅረብ መብታቸዉን ሲያከብርላቸዉ በፈለጉት ጊዜ መጠየቅ እንዲችሉ እና ከሌላዉ ተከራካሪ ወገን የተለየ መብት ለመስጠት አይደለም፤ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች አመልካቾች ያቀረቡት የኑዛዜ ይፍረስልን ክስ በይርጋ የሚታገድ ነዉ በማለት ያሳለፉት ዉሳኔ በአግባቡ በመሆኑ፣ ዉሳኔዉ እንዲጸናልኝ በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ አመልካቾች ጥር 27 ቀን 2014 ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸዉን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ በዚህ መሰረት አመልካቾች ሟች አክስታችን ወ/ሮ ዋጋዬ ወ/ማርያም በሕይወት እያሉ በ7/8/1998 ዓ.ም አድርገዋል የተባለዉ ኑዛዜ እንዲፈርስልን በማለት ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ.177909 ሚያዚያ 30 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መነሻ በማድረግ ጥር 26 ቀን 2013 ዓ.ም ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የክስ አቤቱታ ማቅረባቸዉን የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ የአሁን ተጠሪ በበኩላቸዉ ባቀረቡት ክርክር አመልካቾች የሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ከሰጠ ጊዜ ጀምሮ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.973 (3) መሰረት በሶስት ወር ጊዜ ዉስጥ አቤቱታቸዉን ያላቀረቡ በመሆናቸዉ

እና በፍ/ብ/ሕ/ቁ.974 (2) መሰረት ሚች ከሞቱ ከአምስት ዓመት በኋላ ክስ ማቅረብ ስለማይችሉ አቤቱታቸዉ በይርጋ የሚታገድ ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ አንጻር በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠዉ ፍሬ ነገር ሲታይ አመልካቾች ከዚህ ቀደም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.45310 ላይ በነበረዉ ክርክር ተካፋይ ባለመሆናቸዉ፣ ሚች አድርጓል የተባለዉ ኑዛዜ መቼ እንዳወቁ መረዳት የማይቻል መሆኑን፤ ተጠሪ ሚች አድርጓል የተባለዉን ኑዛዜ በአዲስ አበባ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ካጸደቁ በኋላ የሚች የንብረት ክፍፍል ክስ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.129905 ያቀረቡ ሲሆን የፍ/ቤቱ መጥሪያ ለአመልካቾች ደርሷቸዉ መልሳቸዉን ያቀረቡት ታህሳስ 3 ቀን 2010 ዓ.ም መሆኑን፤ አመልካቾች ሚች አድርጓል የተባለዉ ኑዛዜ እንዲፈርስላቸዉ ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመቃወሚያ አቤቱታ ያቀረቡት የካቲት 15 ቀን 2010 ዓ.ም መሆኑን፤ ይህ ደግሞ አመልካቾች መልሳቸዉን ካቀረቡት ጊዜ ጀምሮ የመቃወሚያ አቤቱታቸዉን እስካቀረቡበት ያለዉ ጊዜ ሁለት 2 ወር ከ12 ቀናት መሆኑን አመልክቷል፡፡ የሥር ፍ/ቤት ይህን የተረጋገጠዉን ፍሬ ነገር መሰረት በማድረግ ተጠሪ አመልካቾች ኑዛዜዉን ያዉቁ ነበር በማለት ያቀረቡትን ክርክር ዉድቅ ማድረጉን የዉሳኔዉ ግልባጭ ያሳያል፡፡ ከዚህ መገንዘብ እንደሚቻለዉ አመልካቾች ኑዛዜዉን ካወቁበት ጊዜ ጀምሮ በሕግ የተመለከተዉ የጊዜ ገደብ ሳያልፍ ሚች አድርጓል የተባለዉን ኑዛዜ ላጸደቀዉ ፍ/ቤት ኑዛዜዉ እንዲሻርላቸዉ የመቃወሚያ አቤቱታ ማቅረባቸዉን ነዉ፡፡ ይህ ማለት አመልካቾች ሚች አድርጓል የተባለዉን ኑዛዜ ያወቁት ከታህሳስ 3 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ መሆኑን የሥር ፍ/ቤት በፍሬ ነገር ደረጃ አጣርቶ ከደረሰበት ድምዳሜ መገንዘብ እንደሚቻል ነዉ፡፡ በዚህ የተነሳ የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ ያቀረቡትን መቃወሚያ ዉድቅ ማድረጉን መረደት ይቻላል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካቾች ሚች አክስታችን አድርጓል የተባለዉ ኑዛዜ እንዲፈርስልን በማለት ጥር 26 ቀን 2013 ዓ.ም ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡት የክስ አቤቱታ ዉድቅ ያደረጉት፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ.177909 ሚያዚያ 30 ቀን 2012 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ ኑዛዜ ይፍረስልን የሚል አቤቱታ የማየት ስልጣን ያለዉ የፌዴራል ፍ/ቤቶች ናቸዉ በማለት ከወሰነዉ ጊዜ ጀምሮ ሲታሰብ ከ8 ወር በላይ በመሆኑ የአመልካቾች ክስ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.973 (3)፣ 974 መሰረት በ3 ወር ይርጋ የሚታገድ ነዉ በማለት መወሰናቸዉን የሥር ፍ/ቤቶች የዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ አመልካቾች ሚች አድርጓል የተባለዉ ኑዛዜ አዉቀዉ እንዲፈርስልን በማለት ከጠየቁበት ከታህሳስ 3 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ሚያዚያ 30 ቀን 2012 ዓ.ም እስከሰጠበት ድረስ ክርክር ላይ የነበሩ መሆናቸዉ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ አመልካቾች በዚህ ጊዜ ዉስጥ በክርክር ላይ የነበሩ በመሆናቸዉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1851 (ሀ) መሰረት የይርጋ ጊዜ ገደብ የማይመለከታቸዉ መሆኑን የሚያከራክር ጉዳይ አይሆንም፡፡ በሌላ በኩል አመልካቾች ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ከሰጠበት ከሚያዚያ 30 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ሚች አድርጓል የተባለዉ ኑዛዜ እንዲፈርስላቸዉ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የክስ አቤቱታ እስካቀረቡበት ጥር 26 ቀን 2013 ዓ.ም ድረስ ከ8 ወር በላይ መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡ እንግዲህ አመልካቾች ሚች አድርገዋል የተባለዉ ኑዛዜ እንዲፈርስላቸዉ በሕግ በተመለከተ ጊዜ ዉስጥ ጠይቀዉ ክርክሩ ስልጣን በሌላዉ ፍ/ቤት በመቅረቡ ምክንያት ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የከተማዉ ፍ/ቤቶች የሰጡትን ዉሳኔ በመሻር፣ አመልካቾች በዚህ ጉዳይ ለፌዴራል ፍ/ቤቶች ክስ ማቅረብ እንደሚችሉ መብት የጠበቀ በመሆኑ፣ አመልካቾች ይህ ዉሳኔ ከተሰጠ ጊዜ ጀምሮ እስከፈለጉ አመታት ቆይተዉ ክስ ለማቅረብ መብት ይሰጣቸዋል ማለት ስለማይቻል፣ ዉሳኔዉን ተከትሎ ለጉዳዩ አግባብነት ባለዉ የህግ ድንጋጌ ሥር በተመለከተዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ ስልጣን ላለዉ ፍ/ቤት የክስ አቤቱታቸዉን ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ከዚህ አንጻር አመልካቾች ኑዛዜዉ ሲነበብ ያልነበሩ ሰዎች በመሆናቸዉ በዚህ ጉዳይ ላይ ተፈጻሚነት ያለዉ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.974 ድንጋጌ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 974 (2) መሰረት ኑዛዜን መቃወም የሚቻለዉ በድንጋጌዉ ሥር የተመለከቱት ሁኔታዎች መከሰታቸዉ በተረጋገጠ በአምስት አመት የጊዜ ገደብ ዉስጥ መሆን እንዳለበት ያስገነዝባል፡፡ እንግዲህ አመልካቾች ሚች አክስታቸዉ ኑዛዜ አድርጓል መባሉን ካወቁበት ጊዜ ጀምሮ ምንም ዓይነት ዳተኝነት ሳያሳዩ መብታቸዉን ለማስከበር የክስ አቤቱታ አቅርበዉ እስከፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ላይ የነበሩ በመሆናቸዉ፤ ተጠሪ ኑዛዜዉን መሰረት በማድረግ የንብረት ክፍፍል ክስ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.129905 ክስ አቅርበዉ አመልካቾች በዚህ ክስ ላይ ታህሳስ 3 ቀን 2010 ዓ.ም መልስ ሰጥቷል ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ ክርክር ላይ የቆዩትን ጊዜ ጨምሮ እንኳን ቢታሰብ አመልካቾች ኑዛዜዉ እንዲፈርስላቸዉ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የክስ አቤቱታ እስካቀረቡበት እስከ ጥር 26 ቀን 2013 ዓ.ም ድረስ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.974 (2) ሥር በተመለከተዉ የአምስት ዓመት የጊዜ ገደብ አለማለፉን ያሳያል፡፡ በመሆኑም አመልካቾች ከታህሳስ 3 ቀን 2010 ዓ.ም ሆነ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ከሰጠ

ከሚያዚያ 30 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ሲታሰብ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.974 (2) ሥር በተመለከተዉ በአምስት አመት ጊዜ ዉስጥ ሚች አድርጓል የተባለዉ ኑዛዜ እንዲፈርስላቸዉ ክስ ማቅረባቸዉ ተረጋገጦ እያለ፣ የሥር ፍ/ቤቶች የአመልካቾች ክስ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.973 (2) እና 974 (1) መሰረት በ3 ወር ይርጋ የሚታገድ ነዉ በማለት ያሳለፉት ዉሳኔ ተቀባይነት የለዉም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች አመልካቾች ሚች አድርጓል የተባለዉ ኑዛዜ እንዲፈርስላቸዉ በሕግ በተመለከተዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ የክስ አቤቱታቸዉን አቅርበዉ እያሉና መብታቸዉን ለማስከበር ዳተኛ ባልሆኑበት የአመልካቾች ክስ በሶስት ወር ይርጋ የሚታገድ ነዉ በማለት ያሳለፉት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ዉሳኔ

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.168286 ግንቦት 19 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሰኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.279892 በ27/3/2014 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት በአብላጫ ድምጽ ተሽሯል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ በፍርድ ሐተታዉ በተመለከተዉ አግባብ አመልካቾች ያቀረቡት የክስ አቤቱታ በይርጋ የማይታገድ መሆኑን በመገንዘብ፣ ግራ ቀኞቸዉን በዋናዉ ጉዳይ በሕግ አግባብ በማከራከር በማጣራት ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.341 (1) መሰረት ተመልሶለታል፡፡

የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡

ግራ ቀኙ የሰበር ክርክሩ ያደረሰዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

ይህ ችሎት በ15/4/2014 ዓ.ም የሰጠዉ የእግድ ትዕዛዝ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

የልዩነት ሀሳብ

ስሜ በተራ ቁጥር 3ኛ ላይ የምገኘው ዳኛ የልዩነት ሀሳቤን እንደምከተለው አስቀምጫለሁ

ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ምክንያት የሆነው ጉዳይ ከኑዛዜ ጋር ተያይዞ የይርጋ ክርክር ሲሆን ይሄውም የአሁን አመልካቾች ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ የአሁን አመልካቾች ወራሽ የሆንበትን የውርስ ንብረት የአሁን ተጠሪ ኑዛዜ ተደርጎልኛል በሚል የኑዛዜ ወራሽነት ውሳኔ አሰጥታ ለክፍፍል ጥያቄ ስታቀርብ ያወቅን በመሆኑ የኑዛዜ

ወራሽነት ውሳኔው ይሰረዝልን በሚል የጠየቁ ሲሆን የአሁን ተጠሪም የአመልካቾች አቤቱታ በይርጋ ቀሪ ነው ሲል ላቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የአሁን አመልካቾች ኑዛዜ የተባለውን ያወቅነው የአሁን ተጠሪ ለክፍፍል ጥያቄ ስታቀርብ በመሆኑ በይርጋ አይታገድም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የአሁን አመልካቾች ኑዛዜ መኖሩን አውቀው ክስ ያቀረቡት ሶስት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በመሆኑ በይርጋ አይታገድም በሚል ተቃውሞውን አልፎት በፍረ ነገሩ ክርክር ላይ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ጉዳዩ እስከ ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች የኑዛዜ ወራሽነት ይሻርልኝ አቤቱታና ክርክር አይቶ ለመወሰን ሥልጣኑ አይደለም በሚል የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶችን ውሳኔ ሽሮ የአሁን አመልካቾች አቤቱታቸውን ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ማቀርብ እንደሚችሉ መብት በመጠበቅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚሁ ምክንያት የአሁን አመልካቾች የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ከሰጠበት ቀን አንስቶ ስምንት ወር ቆይተው ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክስ አቅርበዋል፡፡ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የአሁን አመልካቾች ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡት አቤቱታ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የታለፈው ኑዛዜ መኖሩን አውቀው ሶስት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ አቤቱታ በማቅረባቸው ሲሆን የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ኑዛዜውን አውቀው ክስ አቅርበው የይርጋው መቆጠር ከተቋረጠ በኋላ እና መቆጠር ከጀመረ ጊዜ ጀምሮ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ክስ ባለማቅረባቸው ክሳቸው በይርጋ ውድቅ ነው ሲል ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካቾችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርበዋል፡፡ ቅሬታቸውም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ክስ ማቅረብ እንደምንችል መብት የሰጠን በመሆኑና ክሳችን በይርጋ ቀሪ የማይሆን ሆኖ እያለ በይርጋ ውድቅ መደረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚል ነው፡፡

ከኑዛዜ ጋር ተያይዞ የተቀመጡት የይርጋ ጊዜዎች በህግ ባለሙያዎች የተለያዩ ትርጉሞች ሲሰጥባቸው ይታያል፡፡ አንድ ኑዛዜ አይጸናም በሚል የሚቀርብ ክስ ይርጋ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 973(1) ድንጋጌ ኑዛዜው ሲነበብ የነበሩ ወይም የተወከሉ ሰዎች ኑዛዜው አይፀናም ወይም አንዱ በኑዛዜው የተነገረው ቃል አይጸናም በማለት ክስ ለማቀረብ ያላቸውን ሀሳብ መግለጫ ወይም ስለ ክፍያው በሂሳብ አጣሪው የቀረበውን የድልድልን አመዳደብ ሀሳብ ለመቃወም ኑዛዜው ከተነበበት አንስቶ የሚቆጠር የአስራ አምስ ቀን ጊዜ እንዳላቸው ይገልጻል፡፡ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 973(3) ይህ መግለጫ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ እስከ ሶስት ወር ጥያቄውን (ክሱን) ለዳኞች ወይም ለሽምግልና ዳኞች ካላቀረበ በቀር የመጠየቅ መብቱን እንደሚያጣ ይደነግጋል፡፡ ይህ ድንጋጌ ኑዛዜው ስነበብ

የነበሩ፣ ኑዛዜው መደረጉን ለሚያውቁ ሰዎች የተቀመጠ የይርጋ ጊዜ ነው። የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 974(1) ደግሞ በኑዛዜው ንባብ ሥነ ሥረዓት ላልነበሩ ወይም በኑዛዜው ንባብ ሥነ ሥርዓት በወኪልነት ላልሰሙ ሰዎችና እንዲሁም ኑዛዜው በሌሉበት (የተነበበ እንደሆነ) ይህ የተባለው ጊዜ የሚቆጠረው መነሻ አጣሪው ስለ ክፍያው የድልድል አመዳደብ ሀሳቡን ከነገራቸው ቀን አንስቶ እንደሆነ ይደነግጋል።

ይህ ማለት አንድ ኑዛዜው አይጸናም ሲል ክስ የሚያቀርበው ሰው የኑዛዜውን ክፍፍል ካሳወቁበት ጊዜ ጀምሮ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ማቅረብ ያለበት መሆኑን የሚገልጽ ነው። እነዚህ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 973 እና 974 ድንጋጌዎች አንድ ኑዛዜው ሊጸና አይገባም የሚል ክስ ለማቀርብ ኑዛዜው መኖሩን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ክሱን ካላቀረበ ክሱ በይርጋ ውድቅ መሆን እነደሚችል የሚገልጽ ነው። የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 794(2) ኑዛዜ ከፈሰሰበት ጊዜ ከአምስት ዓመት በኃላ ወይም ኑዛዜ የሌለ እንደ ሆነ ሚቹ ከሞተ ከአምስት ዓመት በኋላ ስለኑዛዜ መጽናት ፣ ስለ ከፍያው አመዳደብ አጣሪው ያቀረበው የድልድል ሀሳብ በማናቸውም አስተያየት ቢሆን መቃወሚያ ሊቀርብበት እንደማይችል ይደነጋጋል። ይህ ድንጋጌ የአምስት አመት ይርጋ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 973 እና 974(1) ከተቀመጠው የሶስት ወር የይርጋ ጊዜ የሚለየው የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 973(3) እና 974(1) የሶስት ወር የይርጋ ጊዜ ኑዛዜው መኖሩን አውቆ ኑዛዜው የማይጸናበትን ምክንያት አንስቶ ክስ የማቅረቢያ ጊዜ ነው። ኑዛዜው መኖሩን ከማወቅ አለማወቅ ጋር ተያይዞ የሚቀርብ የይርጋ ጊዜ ነው። የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 974(2) ድንጋጌ የሚያስረዳን ደግሞ ኑዛዜውን ከማወቅ አለማወቅ ውጪ በሌላ በማንኛውም በቂ በሆነ ምክንያት ማለትም ኑዛዜ መኖሩን አውቆ ክስ ለማቅረብ ያላስቻሉት ሌላ ማናቸውም በቂ ምክንያቶች አጋጥመውት ቆይቶ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ክስ ካላቀረበ በይርጋ ቀሪ የሚሆንበት መሆኑን የሚገልጽ ነው። የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 973(3)፣ 974(1) እና 974(2) ድንጋጌ ትርጉም የይርጋ ጊዜ ፍ/ቤቶች ሲፈልጉ ሶስት ወር ይርጋ ሲፈልጉ ደግሞ 5 ዓመት ይርጋ እየመረጡ እንዲጠቀሙበት ታስቦ የተቀበጠ ድንጋጌ እንዳልሆነ ሁሉም ሰው የሚስማማበት ጉዳይ ነው። ወይም ቃላት ተመርጦ የሶስት ወር ይርጋ ከኑዛዜ መፍሰስ አለመፍሰስ ጋር በማያያዝ ኑዛዜ ሲፈስ ለነበሩ ሰዎች ነው በሚልና የአምስት ዓመት ይርጋ ደግሞ ከኑዛዜ ሲፈስ ላልነበሩ ሰዎች ነው የሚል ትርጉም ትክክለኛ ትርጉም ነው ብዬ አላምንም። የኑዛዜ መፍሰስ ጉዳይ ኑዛዜ መኖሩን ስለማወቅ አለማወቅ መለያ አንዱ ምክንያት ነው። እንዲሁም የሶስት ወር ይርጋ ከኑዛዜ ፎርማሊት ጋር ተይይዞ ለሚቀርብ ክስ እንደ ሆነና የአምስት ዓመት ይርጋ ደግሞ ከዚህ ውጪ ላሉት ጉዳዮች ነው የሚለውም ትርጉም ከድንጋጌው ትርጉም ውጪ መሆኑን በቀላሉ መገንዘብ የሚቻል ነው። የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 974(2) 5 ዓመት

የይግጋ ጊዜ ኑዛዜ መኖሩን አውቆ በሌላ ማንኛውም በቂ ምክንያት ክስ ማቅረብ ላልቻለ ሰው የተቀመጠ ይርጋ ስለመሆኑ በአንቀጹ ተዘርዝረው የተገለጹ ባይሆንም በተመሳሳይ ሌሎች ድንጋጌዎችም እንዲሁ "በማንኛውም ሌላ ምክንያት ..." በሚል ተደንግጎ እናገኛልን፡፡ እንደ ምሳሌ የተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ህግ 213/92 አንቀጽ 69(2) "...ካወቀበት ቀን ጀምሮ ስድስት ወር በኋላ ወይም በሌላ ማንኛውም ሁኔታ ... ሁለት አመት በኋላ " ሲል የይርጋ ጊዜን ይደነግጋል፡፡ ሌሎችም ብዙ ድንጋጌዎች በዚሁ ሁኔታ ተደንግገው የሚገኙ አሉ፡፡ ሌላው የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 1123(3) ይህ የስጦታ ክፍያ አንዲቀር የሚደረገው ክስ ወደ ላይ የሚቆጠረው ስጦታ አድራጊው ወላጅ በሞተ በሁለት ዓመት ውስጥና የስጦታው መከፋፈል ከተደረገበት ቀን አንስቶ በአስር ዓመት ውስጥ ካልቀረበ በቀር ዋጋ የሌለው መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ይህ ድንጋጌ ከፍ/ብ/ህግ 973(3)፣ 974(1) እና 974(2) ላይ ከተደነገጉት የይርጋ ጊዜዎች የሚለይ ነው፡፡ ይሄውም 1ኛ. ይህ የይርጋ ድንጋጌ ከፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 1117 ጀምሮ ያሉት ድንጋጌዎች የሚያወሩት ወላጆች ወደ ታች ለሚቆጠሩ ልጆቻቸው ሀብታቸውን በስጦታ ያከፋፈሉ እንደሆነ እና ይህን ክፍፍል የሚቃወም ክስ ተወላጅ የሚያቀርበው የይርጋ ጊዜ ሲሆን የፍ/ብ/ህግ 973(3)፣ 974(1) እና 974(2) የይርጋ ጊዜ በውርስ አጣሪ በኑዛዜው መሰረት የሚደረግ ክፍፍል ላይ ከሚቀርብ መቃወሚያ ክሰ ጋር የሚለያይ ነው፡፡ 2ኛ. የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 1123(3) ይርጋ ሁለት ውጤቶች ተጣምረው ሲሟሉ የሚቆጠር ይርጋ ነው፡፡ ይሄውም "ወላጅ በሞተ በሁለት ዓመት ውስጥና የስጦታው መከፋፈል ከተደረገበት ቀን አንስቶ በአስር ዓመት ውስጥ..." ያልቀረበ እንደሆነ ነው፡፡ ይሄውም ሁለቱ ተጣምረው የሚቆጠር የይርጋ ጊዜ ነው፡፡ 3ኛ. የስጦታ ማከፋፈል ድርጊቱ በራሱ በወላጁ የተፈጸመ ሆኖ የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 1123(2) የጉዳቱ መኖር የሚገመተው ደግሞ የስጦታ ክፍያ በተደረገበት ቀን ንብረቱ የነበረው ዋጋ በመመልከት ነው ሲል የሚደነግገው ክፍፍሉ በወላጁ በተደረገበት ጊዜ እንጂ በፍ/ቤት ክፍፍል በሚደረግበት ጊዜ ስለመሆኑ አያሳይም፡፡ ይሁንና የደረሰው ጉዳት ¼ በላይ ነው ተብሎ ሲገመት ከፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 1117 ጀምሮ ያሉት ድንጋጌዎች ክፍፍሉ በፍ/ቤት የተደረገ ዓይነት ድንጋጌ በመውሰድ ወደ ፊት አስር ዓመት በመቁጠርና ጉዳቱንም በአሁን የገበያ ዋጋ እንዲሆን በፍ/ቤት ሲወሰን ይታያል፡፡ ይህ ተገቢ ትርጉም ነው ብዬ አላምንም፡፡ የውርስ ንብረት በፍ/ቤት ክፍፍል ጉዳይ ስለውርስ ክፍፍል የሚደነግጉት ከፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1060 ጀምሮ ተደንግገው ይገኛሉ፡፡ በውርስ አጣሪ ወይም በፍ/ቤት የሚደረጉ የውርስ ንብረት ክፍፍሎች ከፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1060 ጀምሮ ባሉት አንቀጾች ተደንግገው እያለ በድጋሚ ከፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1117 ጀምሮ ባሉት አንቀጾች ተደንግገዋል ለማለት የሚያስችል የህግ ምክንያትም የለም፡፡

በመሆኑም የአሁን አመልካቾች ቀደም ብለው በአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ኑዛዜ መኖሩን ያወቁበት ጊዜ ጠቅሰው ክስ አቅርበው በዚሁ መሰረት ኑዛዜ መኖሩን ካወቁበት ጊዜ ጀምሮ ሲቆጠር ሶስት ወር አልሞላውም በሚል ክሳቸው በይርጋ ውድቅ አንደማይሆን እና መቃወሚያው የታለፈ ሆኖ እየለና ኑዛዜ መኖሩን አውቀው ክስ አቅርበው ይሁን እንጂ ክስ ያቀረቡት በተገቢው ፍ/ቤት ባለመሆኑ በተገቢው ፍ/ቤት ክስ እንዲያቀርቡ ከተነገራቸው በኋላ ክስ ማቅረብ በሚገባቸው ጊዜ ውስጥ ፍ/ቤት ሳያቀርቡ 3 ወር ያለፋቸው መሆኑ ታውቋል፡፡ መጀመሪያ ኑዛዜ መኖሩን ካወቁበት ጊዜ ጀምሮ ተገቢ ባለሆነው ፍ/ቤት ክስ አቅርበው ቢሆንም ክስ በማቅረባቸው የይርጋው መቆጠር የሚቋረጥ ሆኖ፣ በተገቢው ፍ/ቤት ክስ ማቅረብ እንዳለባቸው ከተነገራቸው በኋላ ግን ኑዛዜ መኖሩንም አውቀው ክስ ሳያቀርቡ ከሶስት ወር በላይ ስለሆናቸው ትክክለኛው የይርጋ ጊዜ የህግ ድንጋጌ የፍ/ቤት ህግ ቁጥር 974(1) ኑዛዜ መኖሩን ካወቁበት ጊዜ ጀምሮ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ክስ ባለማቅረባቸው ክሳቸው በይርጋ ውድቅ መደረጉ ተገቢ የሚሆን ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች የአሁን አመልካቾችን ክስ በይርጋ ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢ ሆኖ እያለ ለፍ/ብ/ህግ ቁጥር 973፣ 974 እና 1123 ትርጉም በመውጣት የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ መሻሩ ካለአግባብ በመሆኑ የልዩነት ሀሳቤት አስቀምጫለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ. 113247

ቀን መስከረም 26/2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ተፈሪ ገብሩ

አብርሃ መሰለ

አብዬ ካሳሁን

እትመት አሰፋ

አመልካቾች፡- 1. ወ/ሮ የሺ አካሉ } አልቀረቡም

2. ላምሮት ደበበ

ተጠሪዎች፡- 1. ማርታ ደበበ

2.አማረች ደበበ } አልቀረቡም

3.ሰለሞን ደበበ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ሐብት ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በመኢሶ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት ተጠሪዎች አመልካቾች፤ የአሁን አመልካቾች ደግሞ እንደየቅደም ተከተላቸው 5ኛ እና 3ኛ ተጠሪ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት የሟች አባታቸው አቶ ደበበ ግዛው የውርስ ሐብት እንዲጣራ ዳኝነት የጠየቁ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁን 1ኛ አመልካች ለቀረበባቸው ክስ በሰጡት መልስ ከሟች ጋር በ 1973 ዓ.ም ጋብቻ ፈጽመው አብረው የኖሩ እና ንብረት ያፈሩ መሆኑን በመግለጽ ከሟች ጋር በጋብቻ አብረው በነበሩበት ጊዜ ያፈሯቸው ንብረቶች እንዲጣሩላቸው ጠይቀዋል፡፡ የአሁን 2ኛ

አመልካችም በሰጡት መልስ ሟች አቶ ደበበ ግዛው አባታቸው መሆናቸውን በመግለጽ የግል ንብረታቸው የሆነው መኖሪያ ቤት፤ የእህል ወፍጮ ቤት እና በአንድ ግቢ ውስጥ የሚገኝ መጋዘን ከውርስ ሐብት ጋር እንዳይቀላቀል በማለት ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍ/ቤት ውርስ አጣሪ በመሾም ውርሱ እንዲጣራ አድርጓል፡፡ በውርስ አጣሪ የቀረበለትን ሪፖርት ከመረመረም በኋላ የውርስ ሐብት ናቸው በማለት በተለያዩ ንብረቶች ላይ ውሳኔ የሰጠ ሲሆን ለዚህ የሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነውን ንብረት በተመለከተ፡- በመኢሶ ከተማ ውስጥ የሚገኝ መኖሪያ ቤት ወፍጮ ቤት እና መጋዘን በ 2ኛ አመልካች ስም የተዘዋወረ ቢሆንም 2ኛ አመልካች ግቢ የሌላት መሆኑ እና እንዳልሰራችው ፣ ሟች ይህን ንብረት የሰራው መሆኑን ፍ/ቤቱ የተገነዘበ በመሆኑ እነኝህ ንብረቶች የውርስ ሐብት ናቸው፡፡ ሟች በሕይወት እያለ የጣለት ብር 54,000 /ሃምሳ አራት ሺህ/ የእቁብ ገንዘብ 1ኛ አመልካች የወሰዱት እና ገንዘቡም የውርስ ሐብት በመሆኑ እንዲመልሱ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ግራቀኙ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘታቸው ይግባኝ ለምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራቀኙ ያቀረቡትን ይግባኝ አጣምሮ ከመረመረ በኋላ 1ኛ አመልካች የሟች ባለቤት በመሆናቸው እና ንብረቱም በጋብቻ ጊዜ የተፈራ በመሆኑ የ 1ኛ አመልካች ድርሻ ከወጣ በኋላ ቀሪው ድርሻ የወራሾች ነው፤ በ 2ኛ አመልካች ስም ተመዝግቦ የሚገኘው በመኢሶ ከተማ ውስጥ የሚገኝ መኖሪያ ቤት ወፍጮ ቤት እና መጋዘን የ 2ኛ አመልካች ስለመሆኑ በቂ እና አሳማኝ ማስረጃ ስለሌላቸው እነዚህ ንብረቶች የሟች አቶ ደበበ ግዛው እና የ 1ኛ አመልካች የጋራ ሐብት ናቸው፤ ከዕቁቡ ገንዘብ ብር 54,000 /ሐምሳ አራት ሺህ/ ላይ ግማሹ የ 1ኛ አመልካች ድርሻ፤ ቀሪው የውርስ ሐብት ነው በማለት የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቅሬታ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት በትእዛዝ ተሰርዟል፡፡ በመቀጠልም አመልካቾች ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም በማለት በትእዛዝ ውድቅ ተደርጓል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ሟች በአካባቢው ማህበረሰብ ከነበራቸው ታዋቂነት እና ማህበራዊ ደረጃ የእቁብ ገንዘቡ ለሟች የቀብር ስነ-ስርዓት የወጣ ሆኖ ሳለ ግማሹ የውርስ ሃብት ነው መባሉ እና ሟች ከሞተ በኋላ የተከፈለው የእቁብ ገንዘብ እንደ ውርስ እዳ አለመያዙ ተገቢ አይደለም፡፡ መኖሪያ ቤቱን ወፍጮ ቤቱን እና መጋዘኑን በተመለከተ የተሰጠው ውሳኔ ሕጉ ስጦታ ወደ ውርስ የሚመለስበትን ስርዓት አስመልክቶ ያስቀመጠውን ድንጋጌ ያላገናዘበ በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚል ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ 2ኛ አመልካች ሟች አባታቸው በሕይወት በነበሩ ጊዜ ያገኙትን በውርሱ ውስጥ ይቀላቅለ የመባላቸውን አግባብነት ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1065 እና 1076/2 ድንጋጌ አኳያ ለመመርመር ሲባል አቤቱታ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪዎችም ጥሪ ተደርጎ ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አብይ ነጥብ የበታች ፍ/ቤቶች ሟች በሕይወት እያሉ ለ 2ኛ አመልካች የተላለፈው መኖሪያ ቤት፣ ወፍጮ ቤት እና መጋዘን የውርስ ሐብት ነው በማለት ከውርስ ሐብት ጋር በመቀላቀል መወሰናቸው በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

በመኢሶ ከተማ የሚገኘው መኖሪያ ቤት፣ ወፍጮ ቤት እና መጋዘን ሟች በልጃቸው በ 2ኛ አመልካች ስም ያዘዋወሩት እና ያስመዘገቡት መሆኑ ፍሬ ነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው የበታች ፍ/ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም የበታች ፍ/ቤቶች 2ኛ አመልካች ንብረቱን ወደ ውርስ ሐብት እንዲያስገቡ የሰጡት ተገቢ ነው፡፡ አከራካሪው ጉዳዩ 2ኛ አመልካች ንብረቱን ወደ ውርሱ የሚያስገቡበት ስርዓት እንዴት ሊፈጸም ይገባል? የሚለው ነው፡፡ የጋራ ወራሾች ንብረት የሚመልሱበት ስርዓት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1065-1078 ባሉት ድንጋጌዎች ተደንግጓል፡፡ ሟች ከመሞቱ በፊት በሟች ፈቃድ ንብረት የተላለፈለት ወራሽ የተላለፈለትን ንብረት ወደ ውርስ ሐብት የሚመልሰው ንብቱን በዓይነት ሳይሆን የንብረቱን ዋጋ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1065 እና 1074/1 ድንጋጌ ጣምራ ንባብ ያስገነዝባል፡፡ ይህ የሰበር ሰሚ ችሎትም በተመሳሳይ ጉዳይ በመ.ቁ. 80920 በአዋጅ 454/97 አንቀጽ 2/1 መሰረት በየትኛውም ደረጃ ለሚገኙ ፍ/ቤቶች አስገዳጅ የሆነ

የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ የበታች ፍ/ቤቶች በተዘረጋው የሕግ ስርዓት መሰረት 2ኛ አመልካች ንብረቱን ወደ ውርሱ የሚያስገቡበትን ስርዓት በውሳኔው ላይ መግለጽ ሲኖርባቸው ይህን ሳያደርጉ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በመኢሶ ከተማ የሚገኘውን መኖሪያ ቤት፣ ወፍጮ ቤት እና መጋዘን አስመልክቶ በመኢሶ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 05670 ሰኔ 17 ቀን 2006 ዓ.ም ተሰጥቶ፤ በምእራብ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 33414 ሕዳር 2 ቀን 2007 ዓ.ም በፍርድ ተሻሽሎ የተሰጠው፤ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 189969 ሕዳር 25 ቀን 2007 ዓ.ም በትእዛዝ፤ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በትእዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. 2ኛ አመልካች በመኢሶ ከተማ የሚገኘውን መኖሪያ ቤት፤ ወፍጮ ቤት እና መጋዘን በአይነት የመመለስ ግዴታ የሌለባቸው በመሆኑ የንብረቱን ግምት ይመልሱ ብለናል፡፡
3. የንብረቱ ግምት በመኢሶ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 06725 በተያዘው የአፈጻጸም ክርክር ታይቶ ይወሰን ብለናል፡፡
4. በዚህ መዝገብ የተሰጠው የአፈጻጸም እግድ ተነስቷል፡፡
5. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ የስር ፍ/ቤቶች እንዲያውቁት ይድረሳቸው፡፡
6. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ እና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ይ

ቤተሰብ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰ.መ.ቁ.210403

የካቲት 28 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡....1. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2. ቀነዓ ቂጣታ

3. ፈይሳ ወርቁ

4. ደጀኔ አያንሳ

5. ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካች፡.....አቶ ገዛኽኝ ይልማ፡- የቀረበ የለም

ተጠሪ፡.....ወ/ሮ ዲንቅነሽ ስለሺ፡- ቀርበዋል

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ይህ የፍቺ እና የልጅ አስተዳደግ ክርክር የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች እና የአሁን ተጠሪ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.260816 ግንቦት 4 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የአሁን ተጠሪ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት የክስ አቤቱታ፤ አመልካች እና ተጠሪ ጋብቻ ፈጽመን አንድ ልጅ ወልደን አብረን እየኖርን ሳለ አሁን በመካከላችን በተፈጠረዉ አለመግባባት አብረን መቀጠል ስለማንችል ጋብቻችን ፈርሶ የ7 ዓመት እድሜ የሆነዉ ኢዮኤል ገዛኽኝ ለመልካም አስተዳደጉ ሲባል በአሁን ተጠሪ ዘንድ እንዲያድግና አመልካች ቀለብ እንዲቆርጥ እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የአሁን አመልካች በዚህ ክስ ላይ ባቀረቡት መልስ ከተጠሪ ጋር ባለን ጋብቻ የተጠቀሰዉን ልጅ መዉለዳችን ይታወቃል፤ ለቀረበዉ የፍቺ ጥያቄ ማሰላሰያ ጊዜ እንዲሰጥ፤ ልጁ በመልካም ሥነ-ምግባር እንዲያድግ በአመልካች ዘንድ እንዲያድግ እንዲወሰን በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን በማከራከር በሳለፈዉ ዉሳኔ ግራ ቀኙ ጋብቻ መኖሩ ላይ የተማመኑ በመሆናቸዉ፣ እንዲታረቁ ጥረት ቢደረግም ሊሳካ በለመቻሉ ጋብቻቸዉ በፍቺ ዉሳኔ ፈራሽ እንዲሆን የወሰነ ሲሆን፤ የልጅ አስተዳደግን በተመለከተ ፍ/ቤቱ የማህበራዊ ባለሙያዎች ሕጻን ኢዮኤል ገዛኽኝ ለመልካም አስተዳደጉ ሲባል ማን ቢያድግ ይበጃል የሚለዉን ጥናት አድርገዉ እንዲያቀርቡ ባዘዘዉ መሰረት ባቀረበዉ ሪፖርት ከሕጻኑ ጥቅምና ደህንነት አንጻር ከአሁን ተጠሪ ዘንድ ማደግ ይባል ያለዉን በተመለከተ የአሁን ተጠሪ አስተያየት ያቀረበች ሲሆን የአሁን አመልካች ያቀረበዉ አስተያየት ባለመኖሩ፤ ፍ/ቤቱ ሪፖርቱን በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ የማህበራዊ ባለሙያ ሪፖርት ተጨባጭ ሁኔታን መሰረት በማድግ የቀረበ በመሆኑ ተዓማኒ ነዉ በማለት በመቀበል፣ ለሕጻኑ እድገት የተሻለ የሚሆነዉ በእናቱ ዘንድ በአሁን ተጠሪ ዘንድ እንዲያድግ በማለት በመወሰን፣ የአሁን አመልካች ሕጻኑን የሚጎበኝበት አግባብና ቀለብ በወር ብር 3000 እንዲከፍል ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች የሥር ፍ/ቤት የልጅ አስተዳደግና ቀለብን በተመለከተ ያሳለፈዉን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር ሕጻን ኢዮኤል ገዛኽኝ በእናቱ በአሁን ተጠሪ ዘንድ መወሰኑ የሚነቀፍበት አግባብ የለም፤ ቀለብን በተመለከተ ግን የአሁን አመልካች በወር ብር 2300 ለልጅ ቀለብ እንዲከፍል በማለት የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ30/10/2013 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ የሥር ፍ/ቤት በሕጉ አግባብ የሕጻኑን ጥቅም ብቻ መሰረት በማድረግ ዉሳኔ መስጠት ሲገባዉ የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎቹ በአግባቡና በተሟላ ሁኔታ ጥናት ሳያደርጉ ያቀረቡትን ሪፖርትና ሪፖርቱም ልጁ

ከአመልካች ጋር መኖር እንደሚፈልግ የሚገልጽ ሆኖ ሳለ፣ ሕጻን ኢዮኤል ገዛኽኝ ከአመልካች ዘንድ እንዲያድግ ተስማምተን በዚህ መሰረት ማመልከቻም አቅርበን፤ የሥር ፍ/ቤት ይህን ስምምነት በማለፍ በተጠሪ ዘንድ እንዲያድግ የሰጠዉ ዉሳኔ የሕጻኑን መብትና ጥቅም የሚጎዳና የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣የግራ ቀኙ ልጅ አስተዳደግ በተመለከተ የማህበራዊ ባለሙያ በሥር ፍ/ቤት ባቀረበዉ ሪፖርት ልጁ ከአመልካች ጋር መኖር እንደሚፈልግ ተጠቅሶ እያለ፣ አመልካች በፍ/ቤቱ እና በባለሙያ ላይ አሳይተዋል በተባለዉ ባህርይ ብቻ ልጁ ከተጠሪ ጋር እንዲያድግ በማለት የመወሰኑን አግባብነት፣ ለማጣራት ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ ባዘዘዉ መሰረት ጥቅምት 10 ቀን 2014 ዓ.ም በተጻፈ መልስ፡ የሥር ፍ/ቤቶች የሕጻኑን አስተዳደግ በተመለከተ በማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎች በማስጠናት ሕጻኑ በተጠሪ ዘንድ እንዲያድግ ያቀረበዉን ሪፖርት መሰረት በማድረግ የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የሌለዉ በመሆኑ እንዲጸናልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች የመልስ መልስ ያቀረቡት ባለመኖሩ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ አመልካች ባቀረቡት ክርክር ለሕጻን ኢዮኤል ገዛኽኝ መልካም ሥነ-ምግባር ሲባል አመልካች ዘንድ ማደግ ይገባል በማለት የተከራከሩ ሲሆን፤ ተጠሪ በበኩላቸዉ ባቀረቡት ክርክር ለሕጻኑ መልካም አስተዳደግ ሲባል ከተጠሪ ዘንድ ማደግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍ/ቤት ፍሬ ነገር የማጣራትና ማስረጃ የመመርመርና የመመዘን በሕግ በተሰጠዉ የዳኝነት ስልጣን መሰረት በማድረግ የሕጻኑን ደህንነትና ጥቅም ከግምት በማስገባት ማን ጋር ቢያድግ ይሻሻል የሚለዉን በተመለከተ ተጨባጥ ሁኔታን መሰረት በማድረግ የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎች ጥናት አድርገዉ እንዲያቀርቡ ባዘዘዉ መሰረት ባለሙያዎቹ ባቀረቡት ሪፖርት አመልካች ከሚያሳየዉ በንግግር አለመግባት፣ ቁጡነት እና ሃይለኝነት ባህርይ አንጻር ሲታይ ከእናቱ ከአሁን ተጠሪ ዘንድ ቢያድግ የተሻለ መሆኑን የሚያመለክት ስለሆነ፣ ሪፖርቱም ተዓማኒ በመሆኑ፣ ሕጻኑ ከተጠሪ ጋር እንዲያድግ በማለት መወሰኑን የዉሳኔዉ ግልባጭ ያሳያል፡፡ በዚህ መሰረት አሁን ከግራ ቀኙ የቀረበዉን ክርክር አግባብነት ባላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች አንጻር መመርመሩ ተገቢ ነዉ፡፡

እንደሚታወቀዉ በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 36 ሥር እንደተመለከተዉ ሕጻናት የወላጆቻቸዉን እንክብካቤ የማግኘት መብት ያላቸዉ መሆኑን፣ ማንኛዉም መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ሕጻናትን የሚመለከቱትን እርምጃዎች በሚወስዱበት ጊዜ የሕጻናቱን ደህንነት በቀደምትነት ታሳቢ ማድረግ እንደሚጠበቅባቸዉ አዉጆት እናገኛለን፡፡ የሕጻናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 3 ሥር እንደተመለከተዉ ሕጻናትን አስመልክቶ ማናቸዉም እርምጃዎች የሕጻናቱን ደህንነትና ጥቅምን {the best interests of the child} በቀደምትነት ከግምት ማስገባት እንደሚገባቸዉ ተመልክቷል፡፡ እንዲሁም የፌዴራሉ የተሻሻለዉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 218 እና ሌሎችም ድንጋጌዎች የሕጻናት አስተዳደግን በተመለከቱ የሚወሰኑ ዉሳኔዎችና የሚወሰዱ እርምጃዎች ለልጆች ደህንነት፣ ጥቅምና መልካም አስተዳደግ የሚበጁ መሆን እንዳለበቸዉ ይደነግጋሉ፡፡

በዚህ መሰረት አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የሥር ፍ/ቤቶች የግራ ቀኙን የኑሮ ሁኔታ፣ የሚያሳዩትን ባህርይ እና የልጁን እድሜ ታሳቢ በማድረግ፤ የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎች እነዚህን ሁኔታዎች በማጥናት ያቀረቡትን ሪፖርት በመመርመር፤ ከልጁ ደህንነት፣ ጥቅምና መልካም አስተዳደግ አንጻር ሲታይ ሕጻን ኢዮኤል ገዛኽኝ በአሁን ተጠሪ ዘንድ እንዲያድግ ድምዳሜ ላይ በመድረስ ዉሳኔ ማሳለፉን ማየት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንጻር አመልካች ባቀረቡት ቅሬታ የማህበራዊ ባለሙያዎች በአግባቡና የተሟላ ጥናት ሳያደርጉ ያቀረቡት ሪፖርት መሰረት ተደርጎ ዉሳኔ ተሰጥቷል ይበሉ እንጂ በሪፖርቱ ላይ አስተያየታቸዉን እንዲያቀርቡ ትዕዛዝ ሲሰጥ በዚህ አግባብ ያሉት ነገር አለመኖሩን፤ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በተደረገዉ ክርክርም እንዲህ አይነት ነገር መኖሩ የተረጋገጠበት ሁኔታ የሚያሳይ ነገር የለም፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ባቀረቡት ቅሬታ በዚህ ሪፖርት ሕጻኑ ከአመልካች ጋር ለመኖር ገልጾ እያለ ይህ ፍላጎቱ ከግምት ሳይገባ ከተጠሪ ጋር እንዲያድግ መወሰኑ የሕግ ስህተት ነዉ በማለት የተከራከሩ ሲሆን፣ በሥር ፍ/ቤት የቀረበዉ ሪፖርት ይህን ሁኔታ እንደሚያመለክት ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ ነገር ግን ከግራ ቀኙ ክርክር መረዳት እንደሚቻለዉ የግራ ቀኙ የጋራ ልጅ የሆነዉ ሕጻን ኢዮኤል ገዛኽኝ በወቅቱ እድሜዉ የ7 ዓመት ልጅ ሲሆን፣ የልጁን አስተዳደግ አስመልክቶ ዉሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ሃሳቡን እንዲሰጥ ፍላጎቱን እንዲገልጽና በዚህ አግባብ ተሳታፍ እንደሆነ ማድረግ ተገቢ ቢሆንም፣ አጠቃላይ የግራ ቀኙን የኑሮ ሁኔታ እና የልጁ እድሜ መሰረት በማድረግ ለልጁ ደህንነት፣ ጥቅምና መልካም አስተዳደግ የሚበጃዉን በመመርመር ዉሳኔ የሚሰጥበት ይሆናል እንጂ የልጁን ፍላጎት ብቻ መሰረት በማድረግ

የሚወሰን ከሆነ፣ በሕገ መንግስቱና በዝርዝር ሕግ የተመለከተዉን የልጆች ደህንነት በቀዳምነት ታሳቢ መደረግ አለበት ተብሎ የተደነገገዉን ማሳካት የሚቻል አይሆንም፡፡ የልጁን ፍላጎት ከአጠቃላይ ከግራ ቀኙ የኑሮ ሁኔታና ባህርይ አንጻር ተመዝኖና ተመርምሮ መወሰን የሚገባዉ እንጂ የሕጻኑን ፍላጎት ብቻ መሰረት የሚያደርግ ከሆነ የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎችን መድቦ ጥናት ማስደረግም ባላስፈለገ ነበር፡፡ በመሆኑም የአሁን አመልካች ባቀረቡት ቅሬታ የቀረበዉ ሪፖርት በአግባቡና የተሟላ ጥናት ሳይደረግ የቀረበና የልጁን ፍላጎት ታሳብ ያላደረግ ዉሳኔ ነዉ ያሉት ፍሬ ነገርና የማስረጃ ጉዳይ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም ይህ ችሎት በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80 (3፣ ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 (1) መሰረት ከተሰጠዉ የዳኝት ስልጣን አንጻር አመልካች ያቀረቡት ቅሬታ የፍሬ ነገርና የማስረጃ ጉዳይ መሆኑን ከሚያሳይ በስተቀር የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ መሆኑን የሚያመለክት ስላልሆነ ተቀባይነት የለዉም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች የግራ ቀኙን ክርክር መሰረት በማድረግ የልጅ አስተዳደግን በተመለከተ የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎች ጥናት አድርገዉ እንዲያቀርቡ በማድረግ በማጣራት ለልጁ ደህንነትና መልካም አስተዳደግ ተጠሪ ዘንድ ማደግ ይሻላል በማለት የሰጡት ዉሳኔ በሕግ አግባብ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት ስለማይቻል ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.260816 ግንቦት 4 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ጸንቷል፡፡ የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡

ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

ይህ ችሎት በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በአፈጻጸም መ.ቁ.281096 ላይ የተጀመረዉ የአፈጻጸም ክርክር እንዲታገድ የሰጠዉ ትዕዛዝ እና ከልጅ ጉብኝነት ጋር በተያያዘ ነሐሴ 5 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሰ/መ/ቁጥር 179231

ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መስከረም 27 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ወ/ሮ ተሚማ ሬድዋን በሽር

ተጠሪዎች፡-1ኛ. አቶ በድሩ ሰማን

2ኛ. አቶ ደሊል በድሩ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል::

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት በሆነ ንብረት ላይ ይገባኛል የሚለው ሰው በአንደኛው ተጋቢ ላይ ብቻ ክስ አቅርቦ ተከሣሹም ንብረቱ የከሣሽ ነው ሲል አምኖ መከራካሩን ተክተሎ በክሱ መሰረት ከተወሰነ በኋላ ሌላኛው ተጋቢ የመቃወም አቤቱታ ሲያቀርብ ብቻውን ተከሻስ የነበረው ተጋቢ ቀደም ሲል ያቀረበውን ክርክር ሣይለውጥ በመቀጠሉ የተወሰነው የንብረቱ ክፍል የተጋቢዎች የጋራ ሃብት መሆኑ ቢረጋገጥም በክርክሩ ያመነው ተጋቢ ድርሻ ለከሣሽ ወገን እንዲተላለፍለት መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው ተብሎ እንዲታረም የቀረበን የሰበር አቤቱታ ይመለከታል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እንዲህ ነው፡- ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሰረት ባቀረበችው የመቃወም አቤቱታ መነሻነት

ሲሆን የአሁን ተጠሪዎች እንደ ቅደም ተከተላቸው የመቃወም ተጠሪዎች በመሆን ተከራክረዋል። አመልካችና ሁለተኛ ተጠሪ ባልና ሚስት 1ኛ ተጠሪ ደግሞ የ2ኛ ተጠሪ አባት ናቸው። ለአመልካች መቃወም አቤቱታ ምክንያት የሆነው ውሣኔ የተሰጠው መገኛ ቦታውና አዋሳኙ በክሱ ውስጥ የተጠቀሰውን የከተማ ይዞታ ላይ 1ኛ ተጠሪ የሰሩትን ቤት 2ኛ ተጠሪ ለጊዜው እንዲኖርበት ሰጥተውት እንዲያስረክባቸው ሲጠይቁት ፈቃደኛ ባለመሆኑ እንዲያስረክባቸው እንዲወሰንላቸው ክስ አቅርበው 2ኛ ተጠሪም ቤቱ የአንደኛ ተጠሪ መሆኑንና ለማስረከብ ፈቃደኛ መሆኑን በማመን መልስ መስጠቱን ተከትሎ በዚሁ መሰረት እንዲያስረክብ ተወስኗል። አመልካች ውሣኔ የተሰጠበት ንብረት በጋብቻ የተፈራ የአመልካችና የ2ኛ ተጠሪ የጋራ ንብረት ሆኖ ሣለ በክርክሩ ሣትካፈል የተሰጠው ውሳኔ መብቷን የሚጎዳ መሆኑን በመዘርዘር ቀደም ሲል የተሰጠው ፍርድ እንዲሻር ግንቦት 23ቀን 2009ዓ/ም በተፃፈ የመቃወም አቤቱታዋን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሰረት አቅርባለች።

በመቃወም አቤቱታው ላይ መልስ እንዲሰጡ የታዘዙት ተጠሪዎች የመልስ ክርክራቸውን በተናጠል አቅርበዋል። በዚህም መሰረት 1ኛ ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ይዞታ ቀደም ሲል ከመምህር ምትኩ ወንድማገኝና ከወ/ሮ አስናቀች ካሣሁን የገዛው የራሱ ንብረት መሆኑን የመቃወም አመልካችና 2ኛ ተጠሪ ተጋብተው ቤቱ ውስጥ ሲኖሩ የነበረው በ1ኛ ተጠሪ ፍቃድ በመሆኑ አመልካችና 2ኛ ተጠሪ ቤቱ ላይ ምንም አይነት መብት የሌላቸው መሆኑን፤ 2ኛ ተጠሪ በበኩሉ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት የመቃወም አመልካችና የ2ኛ ተጠሪ የጋራ ንብረት አለመሆኑን ይልቁንም ኪራይ እየከፈሉ እንዲኖሩበት አንደኛ ተጠሪ የሰጣቸው መሆኑን በመዘርዘር ቀደም ሲል የተሰጠው ፍርድ ሊለወጥ አይገባም ሲሉ ተከራክረዋል።

የመቃወም አቤቱታው የቀረበለት የስር ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 በቤት ቁጥር አዲስ ተብሎ የሚታወቀው ይዞታ ላይ አመልካች መብት አላት ወይስ የላትም? የሰራችው ቤት አለ ወይስ የለም? የሚለውን ጭብጥ ይዞ ክርክሩን ከመረመረ በኋላ ሐምሌ 23ቀን011 ዓ.ም በዋለው ችሎት አንደኛ ተጠሪ ይዞታውን በሁለተኛ ተጠሪ ስም ገዝቶ ሁለት ክፍል ቤት ሰርቶ ሲያስተዳድረው የነበረ መሆኑ ስለተረጋጠ እነዚህ ሁለት ክፍል ቤቶች የአንደኛ ተጠሪ የግል ንበረቶች መሆናቸውን፤ በሌላ በኩል አመልካችና 2ኛ ተጠሪ ተጋብተው በቤቱ ውስጥ እየኖሩ አራት ልጆች አፍርተው ሁለት ክፍል ቤቶች መስራታቸውና ቤቶቹን ሲሰሩም አንደኛ ተጠሪ አለመቃወሙ ተረጋግጧል በሚል በአከራካሪው ይዞታ ላይ 2ኛ ተጠሪ በግሉ በመገንባቱ ከተረጋገጡት ሁለት ክፍል ቤቶች

በስተቀር ቀሪዎቹ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት መሆናቸውን ነግር ግን የሁለተኛ ተጠሪን ድርሻ በሚመለከት መብት የለኝም ሲል ክርክር ማቅረቡ መብቱን ለአንደኛ ተጠሪ እንደተወው የሚቆጠር በመሆኑ የሱ ድርሻ ለአንደኛ ተጠሪ የሚገባ መሆኑን በመዘርዘር ቀደም ሲል የሰጠውን ውሣኔ በመለወጥ ብይን ሰጥቷል።

አመልካች ይህን ብይን በመቃወም የይግባኝ አቤቱታዋን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበች ቢሆንም ስለተሰረዘባት የያዝነውን የሰበር አቤቱታ አቅርባለች። አመልካች ሰኔ 13ቀን 2011ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታዋ አመልካችና 2ኛ ተጠሪ በጋራ ያፈሩት ቤት ይዞታ ላይ ሁለት ክፍል በጭቃ የተሰራ ቤት የ1ኛ ተጠሪ መሆኑ በተገቢው ሣይረጋጥ፣ የአመልካችና የሁለተኛ ተጠሪ የፀና ጋብቻ እያለ የጋራ ንብረታቸው የሆነውን ቤት ወደ ሶስተኛ ወገን እንዲተላለፍ መደረጉ፣ 2ኛ ተጠሪ ድርሻ የለኝም ብሎ መከራከሩን ተከትሎ የባልና ሚስት ንብረት ግማሹ ለ1ኛ ተጠሪ እንዲተላለፍ መወሰኑ በጋብቻ የተወለዱ ልጆችን ህጋዊ መብት የሚያሳጣ መሆኑን፣ ከኮ/ቀ/ክ/ከ/ መሬት ልማት ማኔጅመንት ጽ/ቤት ይዞታውና ቤቱ በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ ባልና ሚስት ስም መሆኑን ማስረጃ ቀርቦ እንዲረጋገጥ በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 145 መሰረት የቀረበው ክርክር በማለፍ የተሰጠው ብይን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ተብሎ እንዲታረምላት ክርክሯን አቅርባለች።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ የመረመረው አጣሪ ችሎት የአመልካችና የ2ኛተጠሪ ጋብቻ እንዲፈርስ ባልተወሰነበት የስር ፍ/ቤት የንብረት ክፍፍል ውሳኔ የመስጠቱ ተገቢነት ላይ ግራቀኙ እንዲከራከሩ ትዕዛዝ በመስጠቱ ክርክራቸውን በፅሁፍ አቅርበዋል።

1ኛተጠሪ ጥቅምት06ቀን2012 ዓ.ም ፅፎ ባቀረበው መልስ ክርክር የቀረበበትን ቤት ባልና ሚስቱ ሳይጋቡ መስራቱን መኖሪያ አጥተው ሲቸገሩ ኪራይ እየከፈሉ እንዲኖሩበት ፈቅዶላቸው ሲኖሩበት የቆየውን ቤት እንዲለቁለት ክስ ማቅረቡን፣ ባልና ሚስቱ በቤቱ ውስጥ ሲኖሩ የሰሯቸው ቤቶች በሌላ ሰው ይዞታ ላይ ከባለቤቱ ተቃውሞ ውጭ ቤቱ ከተሰራ የቤቱ ባለቤት ይሆናል ቢባልም 2ኛ ተጠሪ ባመነው መሰረት የተወሰነለት መሆኑን፣ የስር ፍ/ቤት ውሣኔ የሰጠው የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ክፍፍል እንዲደረግ ሳይሆን ተጠሪ በፍ/ህ/ቁ 1257ና ተከታዮቹ ድንጋጌ መሰረት የጋራ ባለሀብቶች ንብረታቸውን ለመከፋፈል ያቀረበውን ክርክር መሰረት በማድረግ መወሰኑን፣ የጋራ ልጆችን መብት ይጎዳል የሚለው የአመልካች ክርክር በሚመለከት ተጋቢዎች ልጆቻቸውን የሚያሣድጉት በራሳቸው ንብረት እንጅ በሌላ ሰው ንብረት

አለመሆኑን በመዘርዘር የስር ፍ/ቤት የወሰነው ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አልተፈፀመም ተብሎ እንዲፀናለት ክርክሩን አቅርቧል፡፡

2ኛ ተጠሪ በበኩሉ መስከረም 6ቀን 2012 ዓ.ም ፅፎ ባቀረበው መልሱ ክርክር የተነሳበት ቤት የ1ኛ ተጠሪ ሲሆን አመልካችና 2ኛ ተጠሪ እንዲኖሩበት በ1ኛ ተጠሪ ፈቃድ የተሰጣቸው መሆኑን፣ በኋላም 1ኛ ተጠሪ ሣይፈቅድ አመልካችና 2ኛ ተጠሪ አንስቶ ለመውሰድ የማያስቸግሩ በላስቲክና በእንጨት ቀላል ቤቶችን መገንባታቸውን፣ ቤቶቹንም የገነቡት 1ኛ ተጠሪ እንዲነሳለት በፈለገ ጊዜ አንስተው ለመውሰድ ከአመልካች ጋር ተስማምተው መሆኑን፣ቤቶቹ በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ የተገነቡ የጋራ ንብረቶች ናቸው ከተባለ ክፍፍሉ ሊደረግ የሚገባው 1ኛ ተጠሪ በአንድ ወገን ሆኖ ቀሪው ወይም ግማሹ አመልካችና 2ኛ ተጠሪ በጋራ ሀብትነት እንጅ ለአመልካች ብቻ የሚከፈልበት ምክንያት ሊኖር አይገባም ሲል ክርክሩን አቅርቧል፡፡

አመልካች ጥቅምት 24ቀን2011 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልሷ 1ኛ ተጠሪ ቤቱን በልጃቸው ስም እንደገዙ የሚገልፁት በለማጭበርበር እንጅ በእርሳቸው ስም ምንም ነገር የሌለና የክፍለ ከተማው አስተዳደር በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ ስም ካርታ ሊሰጣቸው በዝግጅት ያለ መሆኑን፣ በጋብቻ የተፈራን ንበረት ጋብቻው ፀንቶ ባለበት ለ3ኛ ወገን ማስተላለፍ ዳኝነት ባልተጠየቀበት ሁኔታ በመሆኑ ህጋዊ ውጤት ሊኖረው የማይገባ መሆኑን፣ 2ኛ ተጠሪ የአከራካሪው ንብረት ግማሽ ባለድርሻ መሆኑን በመግለፁ ርስ በርሱ የሚጻረር ክርክር ማቅረቡን፣ ጋብቻው በፍች ሳይፈርስ በጋብቻ የተፈራ የጋራ ሀብትን እንዲከፋፈል መወሰን ህጋዊ አለመሆኑን በመዘርዘር የሰበር ክርክሯን አጠናክራለች፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል የአመልካችን ቅሬታ ከስር ፍ/ቤት ውሣኔና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በዚህ ችሎት ውሣኔ እንዲሰጥበት የተፈለገው የክርክር ጭብጥ ተጋቢዎች በጋብቻቸው ወቅት የተፈራ የጋራ ንብረት ላይ የይግባኛል ክስ በቀረበ ጊዜ ከተጋቢዎች መካከል አንደኛው ቀርቦ ንብረቱ

የባልና ሚስቱ የጋራ ንብረት ሣይሆን የከሣሹ ነው ሲል አምኖ በመከራከሩ በዚሁ መሰረት በተሰጠ ውሣኔ ላይ የመቃወም አቤቱታ ቀርቦ በክርክር ሂደቱ ንብረቱ በጋብቻ የተፈራ የጋራ ንብረት መሆኑ ቢረጋገጥም ከተጋቢዎች መካከል አንደኛው ንብረቱ የእሱ አለመሆኑን ማመኑ

ድርሻውን ለከሣሹ እንደለቀቀ የሚያስቆጥረው ነው በሚል ጋብቻው ሣይፈርስ የጋራ ንብረቱን ግማሽ ንብረቱ የኔ ነው ሲል ለጠየቀው ይሰጥ ሲል የመወሰኑን ተገቢነት ነው፡፡

መርምረን እንደተረዳነው አመልካች ያቀረበችውን የመቃወም አቤቱታ ተከትሎ በስር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ይዞታ 1ኛ ተጠሪ በሁለተኛ ተጠሪ ስም ገዝቶ ሁለት ከፍል ቤት መስራቱ፤ አመልካችና 2ኛ ተጠሪ ትዳር መስርተው ልጆችን አፍርተው በአከራካሪው ቤት ውስጥ ከ1995ዓ/ም ጀምሮ እየኖሩ መሆኑና በይዞታው ውስጥም የተለያዩ ቤቶችን መስራታቸውንና እነዚህ ንረብረቶችም በጋብቻው የተፈሩ የጋራ ንብረት መሆናቸው፣ ጋብቻቸውም ያልፈረሰ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡

በመሆኑም በስር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር አንደኛ ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ይዞታ በሁለተኛ ተጠሪ ስም ስለመግዛቱና በዚህ ይዞታ ላይ ሁለት ክፍል ቤት የሰራ የተረጋገጠ ሲሆን ነገር ግን ሁለተኛ ተጠሪ እንደሚያቀርበው ክርክር በይዞታው ላይ የሚገኙት ሁሉም ቤቶች የአንደኛ ተጠሪ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ በማቅረብ አለማረጋጡን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም በሁለተኛ ተጠሪ ስም ከሌላ ሰው በተገዛው ይዞታ ላይ ከሚገኙት ቤቶች መካከል አንደኛ ተጠሪ ከሰራቸው ሁለት ክፍል ቤቶች በስተቀር ሌሎች ቤቶች በአመልካችና በሁለተኛ ተጠሪ በጋራ የተሰሩ የጋራ ሀብቶች መሆናቸው በስር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር ተረጋግጧል፡፡

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 34(4) ድንጋጌን መሰረት በማድረግ በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 መግቢያ ላይ እንደተደነገገው ጋብቻ በሕግ ልዩ ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባ በአንድ ወንድና አንድ ሴት መካከል የሚፈጠር በስሩ የሕብረተሰብ መነሻ የሆነውን ቤተሰብ የሚባለውን ተቋም የሚፈጥር መስተጋብር መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ልዩ ልዩ ዝርዝር ሕግጋት ተደንግጋዋል፡፡ በተጋቢዎች መካከል የተፈፀመው ጋብቻ የሕግ ጥበቃ ይደረግለታል ሲባል ጋብቻ መፈፀሙን ተከትሎ ለሚመጡ ውጤቶች ጥበቃ ማድረግን የሚያጠቃልል ነው፡፡ በአንድ ወንድ እና በአንድ ሴት መካከል የሚፈፀመው ጋብቻ ሕጋዊ ድርጊት በመሆኑ ከሚያስከትላቸው ውጤቶች መካከል በተጋቢዎች መካከል ኢኮኖሚያዊ ውህደትን በመፍጠር የጋራ ንብረትን ማፍራትና በጋራ ማስተዳደር መብትን መፍጠሩ የሚጠቀስ ነው፡፡ የጋራ ንብረትን(ሃብትን) በጋራ ማስተዳደር ሲባል በጋራ ሃብቶቻቸው ላይ የይገባኛል ክስ ወይም ክርክር በቀረበ ጊዜ የሁለቱን ተጋቢዎችና ጋብቻው ያፈራቸውን የቤተሰብ አባላት መብትና ጥቅም ማስጠበቅ የሚችል እውነተኛ ክርክርን ማቅረብን የሚያካተት ሲሆን

ይገባል፡፡ ክርክሩ የቀረበላቸው ፍርድ ቤቶችም በጋብቻ ሣይፈርስ በተጋቢዎች የጋራ ሃብት ላይ የአንደኛውን ተጋቢ መብት ወይም ጥቅም በሚመለከት የሚሰጧቸው ውሳኔዎች የተጋቢዎች የጋራ ሃብት ጋብቻው እስካልፈረሰ በመርህ ረገድ እንደ አንድ ሀብት የሚቆጠር እንጅ የእያንዳዱ ተጋቢ ድርሻ በእርግጠኝነት ተለይቶ የማይታወቅ መሆኑንም ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡

በመሆኑም ተጋቢዎች በጋብቻቸው ወቅት ያፈሩትን የጋራ ሀብት እንደ አንድ ሀብት የሚቆጠር እንጅ ጋብቻው ፀንቶ ባለበት ጊዜ ያለተጋቢዎች ስምምነት የጋራ ሀብት ሆኖ መቀጠሉን የሚያሣጣ ውሣኔ መስጠት ንብረትን በሚመለከት በሕግ ጥበቃ የተደረገለትን የተጋቢዎች መብት የሚጥስ የጋብቻ ተቋማዊ ባህሪ የሚያሣጣ በመሆኑ ተቃባነት ሊኖረው አይገባም፡፡

ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት ክርክር ካስነሣው ቤት እና ይዞታ መካከል አንደኛው ተጠሪ በግሉ መስራቱ በማስረጃ ከተረጋገጠው ሁለት ክፍል ቤቶች በስተቀር ሌሎች ቤቶችን አመልካችና የሁለተኛ ተጠሪ በጋብቻቸው ወቅት የሰሯቸው የጋራ ሀብታቸው መሆኑ በተረጋገጠበት፤ የአመልካችና የሁለተኛ ተጠሪ ጋብቻቸው ፀንቶ ባለበት፣ የእያንዳንዱ ተጋቢ ድርሻ ተለይቶ ስለማይታወቅ እንደ አንድ ሀብት የሚቆጠረውን የጋራ ሃብት የጋራ ሀብት ሆኖ መቀጠሉን በሚያሣጣ ሁኔታ 1ኛ ተጠሪ ከሰራው ሁለት ክፍል ቤት ውጪ ያለው ቤት የአመልካችና የ1ኛ ተጠሪ ነው ሲል መወሰኑ የፌዴራል መንግስቱን የተሻሻለ የቤተሰብ ሕግ አንቀፅ 62(1) እና 66 የደነገገጉትን መርህ የሚጥስ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ውሣኔ ሆኖ ስላገኘነው ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 73512 ሐምሌ 23ቀን 2010ዓ/ም በዋለው ችሎት በአሁን አመልካች የቀረበውን የመቃወም አቤቱታ ተከትሎ የቀረበውን ክርክር ከጣራ በኋላ የሰጠው ብይን እንዲሁም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 230125 መጋቢት 17ቀን 2011ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት አንደሚከተለው ተሻሽለዋል፡፡

ለክርክሩ ምክንያት የሆነው በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 በምስራቅና በምዕራብ መንገድ በሰሜን አቶ አሰፋ ደስታ እና በደቡብ አቶ ንጉሴ ኢርሻ የሚያዋስነው ይዞታና በይዞታው ላይ የተሰሩት ቤቶች መካከል

ሀ) አንደኛ ተጠሪ በግሉ የሰራቸው ሁለት ክፍል ቤቶች የአንደኛ ተጠሪ ናቸው ብለናል፡፡

ለ) በዚህ ውሳኔ ተራቁጥር 2(ሀ) ከተጠቀሱት ሁለት ክፍል ቤቶች በስተቀር በአከራካሪው ይዞታ ላይ የሚገኙት ሌሎች ቤቶች(ግንባታዎች) በሙሉ አመልካችና ሁለተኛ ተጠሪ በጋብቻቸው ያፈሯቸው የጋራ ሀብታቸው ናቸው ብለናል፡፡

በዚህ ክርክር ግራ ቀኙ ያወጡትን ወጪ በሚመለከት ግራ ቀኙ የዬራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

<u>የልዩነት ሃሣብ</u>

እኔ ስሜ በተራ ቁጥር 2 ስር የተሰየምኩት የችሎቱ ዳኛ ከባልደረቦቼ በሃሣብ የተለየሁ በመሆኑ የልዩነት ሃሣቤን እንደሚከተለው እገልፃለሁ፡፡ አብላጫው ድምጽ ክርክር ባስነሳው ይዞታ ላይ ካሉት 2 ክፈል ጭቃ ቤት ውጭ ሌላው በጋብቻ የተፈራ የጋራ ሃብት ነው በማለት ከወሰነ በኋላ 2ኛ ተጠሪ መብቱን የተወ ስለሆነ ለ1ኛ አመልካች ድርሻው ስለተወ ድርሻው ለ1ኛ ተጠሪ ይተላለፍ ሲል የሰጠው ውሣኔ ክፍል መሻሩ እና የባልና ሚስት የጋራ ሃሣብት ነው ተብሎ መወሰኑ ተገቢና የምስማማበት ነው፡፡

አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በጋብቻ ተሳስረው 4 ልጆች ወልደው እየኖሩ እንደሆነ በግራ ቀኙ የተካደ ያልተካደ ሲሆን፣ እያከራከረ ያለው ቤት በ2ኛ ተጠሪ ስም ስለመገዛቱም እንዲሁ የታመነ ፍሬ ነገር ነው፡፡

1ኛ ተጠሪ ክርክር የተነሳበትን ይዞታ ከ2 ክፍል ጭቃ ቤት ጋር በ2ኛ ተጠሪ ስም ገዛሁ ይበሉ እንጂ በራሳቸው አንድ ምስክር ቤቱን ተከራይቶ ሲኖር እንደነበር ገልጾ ሲመሰክር በይዞታው ላይ አንድ ጭቃ ቤት እና አንድ ቆርቆሮ ቤት የነበረው መሆኑን መመስከሩ ሲታይ 1ኛ ተጠሪ በትክክል በሚያከራክረው ይዞታ ላይ 2 ክፍል ጭቃ ቤት በ2ኛ ተጠሪ ስም ስለመግዛታቸው በራሱ የሚያጠራጥር ነው፡፡

በሌላ በኩል አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ ባልናሚስት በመሆናቸው የተነሳ ከተጋቢዎች በአንዱ ስም የተገዛ ንብረት የግል ንብረት ነው ተብሎ እስካልተገለለ ድረስ የጋራ ንብረት እደሆነ የሚገመት በመሆኑ ወይም ደግሞ እያከራከረ ያለው ቤት በ2ኛ ተጠሪ ስም እስከተገዛ ድረስ 1ኛ ተጠሪ የግል ንብረታቸው ስለመሆኑ የባለቤትነት ማስረጃ በማቅረብ ወይም በስማቸው የገዙት

መሆኑን የሚያረጋግጥ ከሰው ማስረጃ የዘለለ ማስረጃ እስካላቀረቡ ድረስ ቤቱን የጋራ ከመሆን የሚያግደው ነገር አይኖርም፡፡

1ኛ ተጠሪ ራሳቸው ቤቱን በ2ኛ ተጠሪ ስም ገዛሁ በማለት እየተከራከሩ፣ በ2ኛ ተጠሪ እና በአመልካች መካከል ደግሞ ጋብቻ መኖሩ ሳይካድ ይልቁንም በቦታው ላይ ቤቶችን ገንብተው መኖራቸው በፍሬ ነገር ደረጃ በስር ፍ/ቤት ተረጋግጦ ባለበት 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት የግዢ እና ሽያጭ ራሱ ቤቱ በ2ኛ ተጠሪ ስም ስለመገዛቱ እያረጋገጠ 2 ክፍል ቤቶች የ1ኛ ተጠሪ ናቸው ለማለት የሚያስደፍር ነገር አላገኘሁበትም፡፡

በዚህ መነሻነት የስር ፍ/ቤት እያከራከረ ካለው ቤት ውስጥ 2 ክፍል ቤት የ1ኛ ተጠሪ ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ ቤቱና ቦታው በ1ኛ ተጠሪ በ2ኛ ተጠሪ ስም የተገዛ ከሆነ እና በይዞታው ላይም ሁለቱ ተጋቢዎች የእኛ ነው ብለው ቤት ሰርተው እየኖሩበት ከሆነ በምንም አግባብ ሁለቱ ክፍል የጭቃ ቤት የ1ኛ ተጠሪ ነው ተብሎ ሊወሰን የሚችልበት አግባብ ስለሌለ በስር ፍ/ቤት 2 ክፍል የጭቃ ቤት የ1ኛ ተጠሪ ንብረት ነው ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ ህግን መሠረት ያላደረገ ነው ብዬ ስለማምን ከአብላጫው ድምጽ በሃሣብ በመለየት በሚያከራክረው ይዞታ ላይ ያሉት ሁሉም ቤቶች የተጋቢዎቹ የአመልካችና የ2ኛ ተጠሪ እንጂ 1ኛ ተጠሪ ከዚህ ሃሣብት ምንም መብት የላቸው በማለት የስር ፍ/ቤት በዚህ ነጥብ ላይ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት በከፊል ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሰ/መ/ቁ.152968

መስከረም 21 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- ሲ/ር ሐምዚያ ሱለይማን -ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አያለው በቀለ-ጠበቃ ኩራባቸው ጎሳ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ አደማ ልዩ ዞን በአደማ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን አመልካች በቀን 14/02/2009 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ ከተጠሪ ጋር በ1983 ዓ.ም ጀምሮ በባህል ተጋብተው ሲኖሩ አራት ልጆች ማፍራታቸው በመግልጽ አመልካች በቅርብ ጊዜ ውስጥ ባህሪያቸው ስለቀየረ በተለያዩ ጊዜያት የሚደበድቧቸው፤የሚሰድቧቸው እንዲሁም የማያከብሯቸው በመሆኑ ጋብቻው ፈርሶ በጋራ አብረው ያፈሩት ንብረት ድርሻቸው እንዲወስነላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪም ራሷ ባህሪዋን ለውጣ እኔ ያልፈጸምኩት ድርጊት ፈጽመሃል በማለት እኔን መክሰሷ ትክክል አይደለም በማለት ትዳራችን በአመልካች ጥያቄ እና ፍላጎት በመሆኑ በእርሷ ምክንያት የሚፈርስ መሆኑ ተቆጥሮልኝ የሞራል ካሳ እንድትከፍለኝ በማለት ለአቤቱታው መልስ በመስጠት ተከራክረዋል፡፡ ነገር ግን አመልካች የፍቺ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት በመዝገቡ ለጊዜው እንዲዘጋ በማመልከታቸው ምክንያት የመንቀሳቀስ መብታቸው በመጠበቅ ተዘግቶ የነበረ ሲሆን አመልካች የተዘጋው መዝገብ እንዲቀሳቀስ በቀን 24/08/2009 ዓ.ም በተፃፈ ስለአመለከቱ ፍርድ

ቤቱም ተዘግቶ የነበረው መዝገብ እንዲቀሳቀስ በማድረግ የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማና ማስረጃ ከመዘነ በኋላ በቀን 28/09/2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት በግራ ቀኙ የነበረው ጋብቻ በፍቺ እንዲፈርስ ካደረገ ለጋብቻው መፍረስም ተጠሪ ምክንያት በመሆኑ በጋራ አፍርተው ካላቸው ንብረት ውስጥ ከተጠሪ ድርሻ 20 በመቶ ለአመልካች እንዲያካፍል እንዲሁም የሁለት ልጆች ቀለብ በወር ብር 1,500.00/ አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር/ እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ የአሁን ተጠሪ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለአደማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቢያቀርቡም ተቀባይነት ሳያገኝ በትእዛዝ ሰርዞታል፡፡ በመቀጠል ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታው አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ በማሻሻል በተከራካሪዎች መካከል የነበረው ጋብቻ በተጠሪው ጥፋት በመፍረሱ በጋብቻ ውስጥ 20 በመቶ ለአመልካች እንዲያካፍል በማለት የተሰጠው ወሳኔ ውድቅ በማድረግ የልጆች ቀለብ በማጽናት ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ጥር 23 ቀን 2010 ዓ.ም በዛፉው አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት ሚያዚያ 26 ቀን 2010 ዓ.ም የተዛፉ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የአመልካች ጥያቄ ልጆችን ለማሰዳደግ ደፋ ቀና ብዬ እንዲሁም በአሁኑ ወቅት አካል ጉዳተኛ ልጅ በሰው እርዳታ የሚኖር አሸብር አያሌው የሚባለውን ለማሳደግ በጥረት ላይ እያለሁ እና አቅመ አዳም ያልደረሱ አዳን እና ኢለያላ አያሌው የሚባሉትን ለማሳደግ እና ለማስተማር በጥረት ላይ እያለሁ ይህ ተጠሪ በየጊዜው ረብሻ እየፈጠረ አፀያፊ ቃላት እየተናገረ ለዚህ ሁሉ ለትዳር መበተን ዋና ተዋናይ እራሱ ሆኖ እያለ፤እንዲሁም ከእኔ ከአመልካች ጋር በጋብቻ ተሳስረን ወይም ተጋብተን እየኖርን እያለን ከትዳር ውጭ ከሌላ ሴት ጋር በፈጸመው የግብረ ስጋ ግንኙነት አንድ ልጅ የወለደ ለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት በማያሻማ ተመስክሮበት መከላከል ያልቻለ ስለሆነ በገንዘብ መቀጮ ተቀጥቶ እያለ ምንም አይነት ጥፋት

እንዳልፈጸመ ሰው ንብረቱን እኩል እንድንካፈል የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤት የተካሄደውን ክርክር እና ያቀረብኩትን አቤቱታ መርምሮ ከተጠሪ ድርሻ 20% /ሃያ በመቶ/ ለአመልካች ሊከፍል ይገባል የተወሰነው የህግ መሰረት የሌለው በመሆኑ ውድቅ መደረጉ ምንም አይነት መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 69/95 እንደተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 83/96 የፍቺው ምክንያት ለፍቺው አስፈላጊ ባይሆንም ለውጤቱ በተለይም ለጋራ ንብረት ክፍፍሉ ግን ግምት ውስጥ ሊገባ ይችላል፡፡ ለምሳሌ ለፍቺው የተጠየቀው አንደኛው ወገን በፈፀመው ዝሙት ወይም ድብደባ ምክንያት ከሆነ ፍቺው ተወስኖ በሚደረገው የንብረት ክፍፍል ወቅት ንብረቱ በእኩል መከፋፈሉ ቀርቶ ይህንኑ ጥፋት ግምት ውስጥ ያስገባ ክፍፍል ማድረግ ይቻላል፡፡ ምክንያቱም በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 69/95 እንደተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 83/96 አንቀጽ 111 ከባልና ከሚስት ባንዱ የተፈጸመውና ለፍቺው ምክንያት ሆኖ የተገኘው ጥፋት በሌላው ተጋቢ ላይ ጉዳት አስከትሎ ከተገኘ በዳዩ ላደረሰው ጉዳት ተመጣጣኝ የሆነ ካሳ እንዲከፍል ፍርድ ቤቱ ይወስናል፡፡ ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/1/ መሰረት ከጋራ ንብረት በካሳ መልክ ያንደኛውን ተጋቢ ድርሻ አብዛኛውን ወይም ሙሉውን በደል ለተፈጸመበት ወገን እንዲከፈል ሊወሰን ይችላል በማለት ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በርግጥ ከፍቺ ወቅት የሚኖረው የጋራ ሀብት ክፍፍል በአንጽ 117 እንደተመለከተው የጋራ ሀብቱ ለሁለቱም እኩል የማከፋፋል ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ አንቀጽ 111 የአንቀጽ 117 ልዩ ሁኔታ መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡ ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ የአሁን አመልካች የፍቺ ውሳኔ እንዲሰጥ አቤቱታ ሲያቀርቡ እንደምክንያት ያቀረቡት ተጠሪ ባህሪያቸው በመቀየር በተለያዩ ጊዜያት የሚደበድቧቸው፤ የሚሰድቧቸው እና የማያከብሯቸው ከመሆናቸውም በላይ ከትዳር ውጭ ከሌላ ሴት ጋር በፈጸሙት የግብረ ስጋ ግንኙነት አንድ ልጅ የወለዱ መሆናቸው በዚህ ተግባራቸውም በአፋር ክልል ሎጊያ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.392/2009 በቀን 12/07/2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት ጥፋተኛ በማለት በገንዘብ መቀጮ የቅጣት ውሳኔ የተወሰነባቸው መሆኑን በተጠሪ ከመታመኑም በላይ ፍሬ ነገሩን የማጣራትና የመመዘን ስልጣን የተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶችም ያረጋገጡት ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም ከላይ በዝርዝር እንደተመለከትነው በአመልካችና ተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ መፍረስ በተጠሪ ጥፋት መሆኑና በአመልካች ጉዳት ስለመድረሱ ተረጋግጦ እያለ ተጠሪ ለአመልካች ካሳ

የማይከፍሉበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ሲጠቃለል የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤቶች በማሻሻል የሰጠው ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሕግ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

የኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.269768 መጋቢት 7 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.348/1/ መሰረት ተሻሽለዋል፡፡

በአመልካችና ተጠሪ የነበረው ጋብቻ በፍቺ እንዲፈርስ እና ተጠሪ ለልጆች ቀለብ በወር ብር 1,500.00/አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር/እንዲፍል የተሰጠ ውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡

ተጠሪ ለአመልካች ካሳ ሊከፍል አይገባም ሲል የሰጠው ውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡

በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.101604 ግንቦት 28 ቀን 2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ውስጥ በተከራካሪዎቹ መካከል የነበረው ጋብቻ በተጠሪ ጥፋት በመፍረሱ በጋብቻ ውስጥ በጋራ ከተፈራው ንብረት ውስጥ ተጠሪ ከድርሻው ውስጥ 20 በመቶ ለአመልካች እንዲከፍል በማለት የተሰጠው ውሳኔ በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.26872 ሰኔ 21 ቀን 2009 ዓ.ም በትእዛዝ ያጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡

በዚህ ችሎት ለተደረገው ወጭ እና ኪሳራ የግራ ቀኙን ተከራካሪ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

በቀን 17/08/2010 ዓ.ም የተሰጠው እግድ ተነስቷል፣ ይፃፍ፡

መዘገቡ ተዘግተዋል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

የሰበር መዝገብ ቁጥር 213864

ሚያዝያ 28 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- ወ/ሪት ነስሪያ ተካ

ተጠሪ፡- ረጀቦ ከድር

ለምርመራ የተቀጠረው መዝገብ ተመርምሮ ቀጣዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

አመልካች ከተጠሪ ጋር ጋብቻ ለመፈፀም በአካል ቀርባ ወይንም በቤተሰብ ሕጉ በተቀመጠው አግባብ በእንደራሴ ፈቃዷን ሳትሰጥ የሸርዓ ሕጉ በሚደነግገው መሠረት በአባቷ ተወክላ ፈቃዷን ስለሰጠች በግራቀኙ መካከል የሸርዓ ሕጉን መሠረት በማድረግ የተመሰረተው ጋብቻ ሊፈርስ ይጋበል በማለት በየደረጃው ያሉት የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ጋብቻ በተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፈቃድ ብቻ ይመሰረታል በማለት ሕገ መንግስቱ እና የቤተሰብ ሕጉ በአስገዳጅነት የተመለከተውን ሰብአዊ መብት የሚፃረር መሠረታዊ የሕግ ስህተ የተፈፀመበት ነው በማለት በሰበር ለማሳረም ጳጉሜ 4 ቀን 2013 ዓ/ም ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ያስቀርባል ተብሎ መዝገቡ ለችሎት ቀርቧል፡፡

ጉዳዩ የጋብቻ ፍቺን የሚመለከት ሆኖ ተጠሪ በምዕራብ አዘርነት በርበሬ ወረዳ ፍርድ ቤት መስከረም 13 ቀን 2012 ዓ/ም ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- ግራቀኙ በ2009 ዓ/ም በእስልምና ሃይማኖት መሠረት ጋብቻ መስርተው ንብረት ያፈሩ ቢሆንም በግንኙነቱ ለመቀጠል የሚያስችል ሁኔታ በመካከላቸው መፈጠሩን ገልፀው ፤ የግራቀኙ ጋብቻ ፈርሶ ለፍቺው መንስኤ አመልካች በመሆኗ የሞራል ካሳ እንድወሰንለት ጠይቋል፡፡ ክርክሩ አመልካች በሌለችበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ ተሽሮ አመልካች የክርክሩ ተካፋይ እንድትሆን ያቀረበችው አቤቱታ በስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተቀባይነት በማግኘቱ ለክሱ በሰጠችው መልስ፡-

ከተጠሪ ጋር የፈፀሙት የሚፈርስ ጋብቻ አለመኖሩ ፤ ተጠሪ በግራቀኙ መካከል ጋብቻ ተፈጽሟል በሚሉበት ወቅትም ሆነ የፍቺ ጥያቄው በቀረበበት ጊዜ አመልካች በሀገር ውስጥ የሌለች ነዋሪነቷ አረብ ሀገር መሆኑን ፤ ተጠሪ ጋብቻ በሌለበት የፍቺ ጥያቄ ያቀረበው አመልካች በሰው ሀገር የቤት ሠራተኛ ሆና ባገኘችው ገንዘብ የገዛችውን ቤት ለመቀማትና አላግባብ ለመበልግ ካለው ፍላጎት የተነሳ በመሆኑ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ምንም ጋብቻ ሳይኖር የቀረበው የፍቺ ክስ ውድቅ ሆኖ ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንላት ጠይቃለች፡፡

የምዕራብ አዘርነት በርበሬ ወረዳ ፍርድ ቤት የግራቀኙን ምስክሮች ሰምቶ መዝገቡ እንደሚከተለው መርምሯል፡፡ የቤተሰብ ሕጉ በመርህ ደረጃ ሁለቱ ተጋቢዎች በተገኙበት ጋብቻ የሚፈፀም መሆኑን ሲደነግግ በየትኛውም የአፈፃፀም ሥርዓት የተደረገ ጋብቻ እኩል መሆኑን በልዩ ሁኔታ የሚያስገነዝብ በመሆኑ ፤ ግራቀኙ በሌሉበት በውክልና ኒካ መታሰሩ በምስክሮች በመረጋገጡ ፤ በእስልምና ሃማይኖት አንዲት ሴት ለመጋባት በወላጅ አባቷ ፣ አባት ከሌላት በወንድም እያለ በቤተሰብ በኩል በውክልና ኒካ ከታሰረ በኋላ ባልና ሚስት እንደሆኑ ስለሚገመትና የአመልካች ፈቃድ በአባቷ በኩል ተረጋግጦ እሷ በሌለችበት ጋብቻ መደረጉን በቤተሰብ ሕጉ የተደነገገውን ቅድመሁኔታ በሸርዓ ሕጉ የግድ የሚል አለመሆኑን ፍርድ ቤቱ ከሸርዓ ፍርድ ቤት ጠይቆ የተረዳ በመሆኑ ፈቃዴን ባልሰጠሁበት እና በሌለሁበት ጋብቻ ሊደረግ አይችልም የሚለው የአመልካች ክርክር የቤተሰብ ሕጉ እሳቤ የሸርዓ ሕጉ የግድ የሚል ባለመሆኑ ከአከባቢው በሕልና ልማድ ፤ እንዲሁም ከሃይማኖት አንፃር ሲታይ ኒካ ከታሰረ ቀን ጀምሮ ባልና ሚስት እንደሆኑ ስለሚገመት በቤተሰብ ሕጉ የተቀመጠው ቅድመሁኔታ መሟላት ግዴታ አይደለም በማለት የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 75/96 አንቀጽ 13 እና 91(4) መሠረት ጋብቻ መኖሩ ስለተረጋገጠ የአመልካች መቃወሚያ ውድቅ ነው በማለት የፍቺ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በውሳኔው ባለመስማማት ያቀረበችውን ይግባኝ የሥልጤ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 337 በመሰረዙ ጉዳዩን የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት በእስልምና ሃይማኖት ሥርዓት መሠረት ጋብቻ መፈፀሙን ተጠሪ በቂና አሳማኝ በሆነ መልኩ ያስረዳ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች በግራቀኙ መካከል መኖሩን ያተረጋገጡትን ጋብቻ እንዲፈርስ መወሰናቸው በአግባቡ ነው በማለት የሥር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

አመልካች በየደረጃው ያሉት የሥር የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች የሰጡት ፍርድ ፤ ውሳኔ እና ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት በሰበር ለማሳረም ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- ጋብቻን ለመፈፀም በሕጉ የተመለከተው ቅድመ ሁኔታ በሃይማኖት መሠረት የሚፈፀመውን ጋብቻ ጭምሮ ሁሉንም የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓቶችን የሚመለከት ሆኖ ከቅደመ ሁኔታዎቹ አንዱ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 75/1996 አንቀጽ 22(1) ሥር የተመለከተው ጋብቻ ሲፈፀም ተጋቢዎች በአካል ተገኝተው ፈቃዳቸውን በማያሻማ ሁኔታ መግለጽ አስፈላጊነት በየትኛውም ሥርዓት ለሚፈገፀም ጋብቻ በውክልና ጋብቻ እንዳይፈፀም ሕጉ የሚከለክል ሆኖእያለና ጋብቻው ተፈጽሟል በተባለበት ጊዜ አመልካች በሀገር ውስጥ ያልነበረች በግንባር በአካል ቀርባም ሆነ በአባቷ ተወክላ የሰጠችው ፈቃድ ሳይኖር እና አመልካች በአባቷ መወከሏን የሚያስረዳ አግባብነት ያለው ማስረጃ ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ሳይቀርብ ፤ ህጉ በሃይማኖታዊ ሥርዓት ለሚፈፀም ጋብቻ ዕውቅና የሚሰጠው ጋብቻው ማሟላት ያለበትን በሕጉ የተመለከተውን መሰረታዊ መስፈርቶችን አሟልቶ ሲገኝ ሆኖሳለ ፤ የግራቀኙ ጋብቻ በእስልምና ሃይማኖት ሥርዓት የተፈፀመ በመኖኑና ሥርዓቱ ደግሞ በውክልና ጋብቻ መፈፀምን ስለመፈቅድ ፤ ክልከላው በዚህ ሥርዓት የተፈፀመ ጋብቻን አይመለከት በማለት የሕገ መንግስቱንና የቤተሰብ ሕጉን ግልጽ ድንጋጌዎች ወደጎን በማለት ሃይማኖታዊ ሕግን መሠረት በማድረግ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተደረገው ጋብቻ ሳይኖር ጋብቻ እንዳለ ተወስዶ እንዲፈርስ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ የሚፈርስ ጋብቻ የለም ተብሎ እንዲወሰን ጠይቀዋል፡፡

አመልካች ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ የመረመረው የሰበር አጣሪ ችሎቱ፡- አመልካች በአባቷ ወኪልነት በሸሪዓ ሕግ መሠረት የፈፀመችው ጋብቻ ይፍረስ በማለት የመወሰኑን አግባብነት ለአመልካች አባት በክልሉ የቤተሰብ ሕግ አንፃር የተሰጠ ውክልና ስለመኖሩ ተረጋጦ መሆኑን ለማጣራት መዝገቡ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ በሰጡት መልስ፡- በአመልካች እና ተጠሪ መካከል በእስልምና ሃይማኖት መሠረት የተደረገ ጋብቻ መኖሩን አመልካች ሳይክዱ በግራቀኙ መካከል የተደረገው ጋብቻ ሳይሆን መተጫጫት ነው በማለት ስከራከሩ የቆዩ ሲሆን ፤ በግራቀኙ መካከል የተደረገው ጋብቻ በሀገሪቱ በሚልዮን በሚቆጠሩ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ በተመሳሳይ መልኩ የሚፈፀም በመሆኑና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 ቁጥር 10(3) የተሰጠውን ሥልጣን መሠረት አድርጎ የሚሰጠው ውሳኔ በየትኛውም ደረጃ ባለው ፍርድ ቤት ላይ አስገዳጅነት ያለው በመሆኑ

በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ጋብቻ የለም ከተባለ ተመሳሳይነት ባለው መልኩ የተፈፀሙ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ተጋቢዎች ጋብቻ እንዳልተፈፀመ ተቆጥሮ ትልቅ ማኅበራዊ ቀውስ ሊፈጥር ስለሚችል ችሎቱ ጉዳዩን በጥሞ እና በጥንቃቄ እንዲመለከተው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች የተፈፀመ ጋብቻን እንዳልተፈፀመ በማድረግ ስለእስልምና ወይንም ስለሸርዓ በቂ እውቀት የሌለውን የሰበር ሰሚ ችሎቱን በማደናገር ህብረተሰቡ እየኖረበት ያለውን ማኅበራዊ እሴት በመናድ በማኅበረሰቡ መካከል መተማመን እንዳይፈጠር ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ፤ የቤተሰብ ህጉ በሃይማኖት ሥርዓት ጋብቻ እንዲፈፀም ፈቅዶ በሰጠው እውቅና መሠረት በእስልምና ሃይማኖት ተጋቢዎቹ በአካል ኖሩም አልኖሩ ኒካ የሚታሰረው የሴቷ ፈቃደኝነት በቤተሰቧዋ(አባት ፣ አባት ከሌለ በወንድም ፣ ወንድም ከሌለ አጎት) ተጠይቆ በመሆኑ ፤ አመልካችን ወክለው ኒካ በሚያስሩ የአመልካች አባት ፈቃዳኛ መሆናቸው ተረጋግጦ ሃይማኖታዊ ሥርዓቱን ተከትሎ ጋብቻ የተፈፀመ መሆኑ በምስክር የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች በእስልምና ሃይማኖት ሥርዓት ለተፈፀመ ጋብቻ አግባብነት የሌለውን የቤተሰብ ህጉን የውክልና ጽንሰ ሃሳብ በማንሳት በግራቀኙ መካከል ጋብቻ እንዳልተፈፀመ ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ ሆኖ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲፀና ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም ለአባቷ በእሷ ስም ጋብቻ መመስረት የሚያስችለው የውክልና ሥልጣን ያልሰጠች መሆኗንና ግራቀኙ ጋብቻ መሥርተው አብረው አለመኖራቸውን በማንሳት የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑ ለጉዳዩ አግባነት ካለው ሕግ አንፃር እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡ ኅብረተሰብ ሆነ መንግስት ያለቤተሰብ አይኖሩም፡፡ ቤተሰብ የኅብረተሰብ የተፈጥሮ መሠረታዊ መነሻ ነው፡፡ የቤተሰብ መሠረት ደግሞ ጋብቻ ፤ የባልና ሚስት ትዳር ነው፡፡ ጋብቻ ተራ ውል ባለመሆኑ መንግስትም ሆነ ኅብረተሰቡ ጋብቻንና የጋብቻ ውጤትን በልዩ ዓይን ይመለከቷቸዋል፡፡ ስለዚህም መንግስት ለጋብቻ ዕውቅና ከመስጠት ጀምሮ ጋብቻ እንዴት እንደሚመሠረት ፣ የጋብቻ ውጤትን ፣ ፍቺን ፣ የባልና ሚስት ግዴታና መብትን ፣ ልጆችንና የመሳሰሉትን በሚመለከት የሕግ ድንጋጌዎችን በማውጣትና የተለያዩ ተቋማትን በማደራጀት ጥበቃ ያደርጋል፡፡

የሰብአዊ መብቶች ሁሉ አቀፍ መግጫ (Universal Decaration of Human Rights) አንቀጽ 16(2) ጋብቻ የሚፈፀመው ለመጋባት በተፈቃቀዱት ሰዎች ነፃና ሙሉ ፈቃድ ብቻ መሆኑን ያመለክታል፡፡ የሲቪልና የፖለትካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን (International

Covenants on civil and political Rights) አንቀጽ 23(2) ያለተጋቢዎች ነፃ እና ሙሉ ፈቃድ ጋብቻ መመስረት እንደሌለበት ያመለክታል። በሴቶች ላይ የሚደረግ ማንኛውንም አድላዊ ልዩነትን ለማስወገድ የተደረገ ስምምነት (Convention for the Elimination of All forms of Discrimination Against Women) አንቀጽ 16 (1) (ለ) ሴቶች የትዳር ጓደኛን የመምረጥና ጋብቻን በውዴታና በነፃ ፍላጎት ብቻ የመፈፀም መብት እንዳላቸው ይደነግጋል። የኢ/ፌ/ዲ/ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 34(2) ጋብቻ በተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፈቃድ ብቻ እንደሚመሰረት ይደነግጋል። የሕገ መንግስቱ ማብራሪያ ጋብቻ በሁለቱ ተጋቢዎች ነፃ ፈቃድ ካልሆነ በቀር በሌላ ወገን ለምሳሌ በወላጆች ወይንም በሽማግሌዎች ወዘተ ምርጫ እና ውሳኔ እንዳይፈፀም ሕጉ ደንግጎ እያለ ይህን በመተላለፍ ከተጋቢዎቹ ፈቃድ ውጭ የተፈፀመ ጋብቻ ይፀናል ወይስ አይፀናም የሚለው በዝርዝር ሕግ የሚወሰን ሲሆን ፤ እንድያገባ ወይንም እንዲታገባ የተገደደ ወይንም የተገደደች ተጋቢ በማንኛውም ጊዜ ጋብቻውን ለማፍረስ የመጠየቅ መብት አለው / አላት ብቻ ሳይሆን የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 34(2) ጋብቻ በተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፈቃድ ብቻ ይመሰረታል ስለሚል የግዴታ ጋብቻ እንደ ጋብቻ ስለማይቆጠር ተጋቢዎች ጋብቻቸውን ለመቀጠል የተስማሙ እንደሆነ እንኳን ጋብቻው ያለፈውን የትዳር ዘመን በማካተት በአዲስ ውል እንደገና መፈፀም እንዳለበት ያመለክታል። ሕገ መንግስቱ በሃይማኖት እና በባሕል ሥርዓቶች ለሚፈፀም ጋብቻ እውቅና በመስጠት ዝርዝሩ በሕግ እንደሚወሰን አንቀጽ 34(4) ያመለክታል። በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 579 እና 580 እንደቅደምተከተላቸው ለሃይማት እና ለልማድ ጋብቻ እውቅና የተሰጠ ቢሆንም የአሁኑ ከበፊቱ የሚለይበት ትልቁ ነጥብ ለሃይማኖትና ለባሕል ጋብቻዎች ዕውቅና የሚሰጡ ሕጎች ከሕገ መንግስቱ የሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችና ነፃነቶች ጋር ሊጋጩ የማይችሉ መሆናቸውን ፤ በተለይም የወንድ እና የሴት እኩልነት ፣ የጋብቻ በፈቃድ ላይ መመስረት ፣ በጋብቻ አፈፃፀም ፤ በጋብቻው ዘመንና በፍቺ ጊዜ የባልና ሚስት እኩልነት እና የመሳሰሉት መሠረታዊ መብቶች ሊጣሱ ወይንም ሊቀነሱ የማይችሉ መሆኑን የሕገ መንግስቱ ማብራሪያ ያመለክታል። ሕገ መንግስቱ የሀገሪቱ የበላይ ሕግ በመሆኑ ማንኛውም ሕግ ፣ ልማዳዊ አሰራር ወይንም ውሳኔ ከሕገ መንግስቱ ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈፃሚነት እንደሌለው ቁጥር 9(1) ይደነግጋል። ከላይ የተመለከተው ሕገ መንግስታዊ መርህን በዝርዝር ሕግ ሊንፀባረቅ የሚገባው መሠረታዊ መብት በመሆኑ በጋቻ አፈፃፀም የሶስተኛ ወገኖች (ወላጆች ፣ አሳዳሪዎች) ተጽኖ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ለማመልከት በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/192 አንቀጽ 6 ሥር የተጋቢዎች ፈቃድና ፍላጎት በአስፈላጊ ሁኔታዎች ሥር እንዲሰፍር የተደረገው ዋናው አስፈላጊ

ሁኔታ የወደፊት ተጋቢዎች ፈቃድ መሆኑን ለማሳየትም በክፍሉ ውስጥ የመጀመሪያ አንቀጽ ሆኖ መቀረጹን የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ሐተታ ዘምክንያት(ማብራሪያ) ያመለክታል። የፌደራል የቤተሰብ ሕግ ይዘት እና አተገባበሩ በሚል ርዕስ በታተመው መጽሐፍ የተጋቢዎች ፈቃድ ጋብቻን ለመፈፀም መሟላት ካለበቸው ቅድመ ሁኔታዎች ሁሉ ዋነኛ መሆኑን ለማመላከት በክፍሉ በአንደኛ ተራቁጥር መቀመጡ ተመላክቷል። መጽሐፉ በመቀጠልም በአንዳንድ የሀገራች የማኅበረሰብ አካለት ለጋብቻ የፈቃደኝነት መኖር አስፈላጊ ቢሆንም የሚፈለገው ፈቃደኝነት የተጋቢዎቹ ሳይሆን የቤተዘመዱ መሆኑን ፣ የተጋቢዎች ፈቃድ የሚፈለገው ለማጠናከሪያነት እንጅ የወሳኝነት ሚና ያልነበረው መሆኑን ፤ በቀድሞው አስተሳሰብ የሚጋቡት ባልና ሚስቱ ብቻ ሳይሆን ቤተዘሞዶቻቸው ሲሆኑ ፤ በዘመናዊ አስተሳሰብ በቀዳሚነት እና በዋናነት ጋብቻ የተጋቢዎች ጉዳይ በመሆኑ በነፃ እና ሙሉ ፈቃዳቸው ላይ መመስረት ያለበት በመሆኑ ለጉዳዩ አጽኖት ለመስጠት ታስቦ ሕገ መንገስታዊ ድንጋጌው በቤተሰብ ሕጉ ውስጥ እንዳለ እንዲካተት መደረጉን ያብራራሉ።

ጋብቻ በነፃና ሙሉ ፈቃደኝነት ሊመሰርት የሚገባ በመሆኑ በእንደራሴ መፈፀምን ሕጉ ይከለክላል። (የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 12 ይመለከቷል)። የተጋቢዎችን ፈቃድና ፍላጎት ለማረጋገጥ ጋብቻ በሚፈፀሚበት ጊዜና ቦታ ተጋቢዎች በአካል መገኘት ይኖርባቸዋል። ነገር ግን ተጋቢዎች ፈቃድና ፍላጎታቸውን ገልፀው በአንድነት መገኘት የሚያስችላቸው ከባድ ሁኔታ ሲያጋጥም በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ መገኘት የማይችል ተጋቢ ጋብቻ ለመፈጸም ፈቃዱን በማያሻማ መልኩ የገለጸ መሆኑን የፍትሕ ሚኒስትሩ ሲያረጋግጥ በእንደራሴ ጋብቻ ሊፈፀም እንደሚችል አንቀጽ 12(2) ያመለክታል። የቤተሰብ ሕጉ አወቃቀር ሲታይ የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓቶችን ከዘረዘረ በኋላ የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓቶቹ ማሟላት ያለባቸውን ሁኔታዎች በቅደምተከል ያስቀምጣል። እነዚህን መሠረታዊ ሁኔታዎችን አሟልቶ መገኘት ለሁሉም የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓቶች ግዴታ ሆኖ ጋብቻው የሚፈፀሚበት ሥርዓት የሚያስቀምጠውን መስፈርትም በተጨማሪነት ማሟላት እንዳለበት ይጠበቃል። በሕጉ የተመለከተውን መስፈርት አሟልቶ የተደረገ ጋብቻ በየተኛውም ሥርዓት ቢፈፀም ምንም ልዩነት ሳይደረግበት ተመሳሳይ ሕጋዊ ውጤት ያለው መሆኑን አንቀጽ 40 ያመለክታል።

የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 75/1996 ምዕራፍ ሁለት ክፍል አንድ ሥር ልዩ ልዩ ጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓቶችን (በክብር መዝገብ ሹም ፊት የሚፈፀም ፣ በሃይማኖት ሥርዓት እና በባህል ሥርዓት) የሚፈፀሙ መሆኑን ከዘረዘረ በኋላ በዚያው ምዕራፍ በክፍል ሁለት ሥር ሁሉንም ዓይነት ጋብቻ ለመፈፀም

ማለትም በክብር መዝገብ ሹም ፊት ፣ በሃይማኖት ሥርዓት እና በባህል ሥርዓት የሚደረገውን ጋብቻ ለመፈፀም መሟላት የሚገባቸውን ቅድመሁኔታዎችን በአንቀጽ 16 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ሥር ተመልክቷል፡፡ ከቅደመሁኔታዎቹ ውስጥ የሚፀና ጋብቻ ተፈጽሟል ለማለት የሚቻለው ተገቢዎቹ ለመጋባት ነፃና መሉ ፈቃድ ሲሰጡ ብቻ መሆኑን አንቀጽ 16 ሥር በቀዳሚነት ይደነግጋል፡፡ ጋብቻ ሲፈፀም ሁለቱም ተጋቢዎች በግንባር ተገኝተው ፈቃዳቸውን መስጠት ያለባቸው ሲሆን በከባድ ምክንያት ጋብቻውን በአካል ቀርቦ መፈፀም ባለመቻሉ ጋብቻን በውክልና መፈፀም የሚፈልግ ተጋቢ ፈቃዱን በማያሻማ ሁኔታ መግለፁ በፍትሕ ቢሮ ኃላፊ ሲረጋገጥ ብቻ ጋብቻውን በውክልና ሊፈጽም እንደሚችል አንቀጽ 22 ይደነግጋል፡፡ በሕጉ የተመለከቱት ቅደመ ሁኔታዎችን አሟልቶ የተፈፀመ ጋብቻ በየትኛውም የአፈፃፀም ሥርዓት ቢፈፀም ውጤቱ ተመሳሳይ መሆኑን አንቀጽ 49 ያመለክታል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ በ2009 ዓ/ም ከአመልካች ጋር በእስልምና ሃይማኖት መሠረት ጋብቻ መስርተናል በሚሉበት ጊዜ አመልካች በሀገር ውስጥ የሌሉ በአካል ቀርበው ከተጠሪ ጋር ለመጋባት ነፃና ሙሉ ፈቃዳቸውን ያልሰጡ በመሆኑ የሚፈርስ ጋብቻ የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ በግራቀኙ መካከል ጋብቻው ተፈፅሟል በተባለ ጊዜ አመልካች በሀገር ውስጥ አለመኖራቸው አላከራከረም፡፡ ተጠሪ ጋብቻው የተፈፀመው በእስልምና ሃይማኖት ሥርዓት ስለሆነ በዚህ ሥርዓት ለሚፈፀመው ጋብቻ ተገቢዎችን ወክለው ፈቃድ የሚሰጡት ከተጋቢዎቹ ውጪ ያሉ ሌሎች ሰዎች በመሆናቸው የተጋቢዎቹ በአካል መኖርም ሆነ አለመኖር የሚያመጣው ለውጥ ባለመኖሩ እና በቤተሰብ ሕጉ ላይ የተመለከተው ውክልናም በእስልምና ሃይማኖት ሥርዓት ለሚፈፀም ጋብቻ ተገቢነት የሌለው መሆኑን ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን የተመለከተው የምዕራብ አዘርነት በርበሬ ወረዳ ፍርድ ቤት የቤተሰብ ሕጉ በመርህ ደረጃ ሁለቱ ተጋቢዎች በተገኙበት ጋብቻ የሚፈፀም መሆኑን ቢደነግግም በየትኛውም የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት የተደረገ ጋብቻ እኩል በመሆኑ በእስልምና ሃማይኖት አንዲት ሴት ለመጋባት በወላጅ አባቷ ፣ አባት ከሌላት በወንድም እያለ በቤተሰብ በኩል በውክልና ኒካ ከታሰረ በኋላ በአከባቢው በሕልና ልማድ ፤ እንዲሁም ከእስልምና ሃይማኖት አንፃር ባልና ሚስት እንደሆኑ ስለሚገመት በቤተሰብ ሕጉ የተደነገጉት ቅድመሁኔታዎች በሸርዓ ሕጉ የግድ የሚሉ አለመሆኑ ከሸርዓ ፍርድ ቤት ጠይቆ የተረዳ በመሆኑ ፈቃዴን ባልሰጠሁበት እና በሌለሁበት የተደረገ ጋብቻ የለም የሚለው የአመልካች ክርክር የቤተሰብ ሕጉ እሳቤ በሸርዓ ሕጉ የግድ የሚል አይደለም በማለት የአመልካችን ክርክር ውድቅ አድርጎ የፍቺ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ጋብቻ የተደረገበት የአፈፃፀም ሥርዓት ልዩነት ሳይደረግበት በሕግ ፊት እኩል ውጤት አለው መባሉ ጋብቻን ለመፈፀም በሕጉ የተመለከቱት ቅደመሁኔታዎች ለሁሉም የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓቶች ተፈፃሚ እንዳይሆኑ ለማድረግ ሳሆን ሁሉንም የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት የሚመለከቱ ቅድመሁኔታዎችን ያሟላ ጋብቻ ፤ የተፈፀመበት ሥርዓት ታይቶ በውጤቱ ላይ ልዩነት እንዳይኖር ታስቦ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ይህን የእኩልነት መርህ አላግባብ ተጠቅሞ በእስልምና ሃይማኖት ሥርዓት ለሚፈፀመው ጋብቻ የተጋቢዎች ፈቃድ መኖር ተፈፃሚነት እንደሌለው መውሰዱ ተገቢነት የለውም፡፡ የተጋቢዎች ፈቃድ መኖር ግዴታ መሆኑ ከላይ በተመለከቱት የተለያዩ የዓለም አቀፍ ስምምነቶች በአስገዳጅነት ከመደንገጋቸውም በላይ በኢ/ፌ/ዲ/ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 34(2) ጋብቻ በተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፈቃድ ብቻ እንደሚመሰረት በመደንገጉ ፤ ይህ መሠረታዊ ሰብዓዊ መብት ሳይሸራረፍ እንድከበር ቃልበቃል የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 75/1996 በአንቀጽ 16 ሥር የተመለከተው ድንጋጌ በእስልምና ሃይማኖት ሥርዓት ለተፈፀመ ጋብቻ ተፈፃሚነት የለውም ማለቱ በሕጉ የተመለከተውን ግልፅ ክልከላ መተላለፍ ብቻ ሳይሆን በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 13(1) ሥር የተጣለበትን መሰረታዊ መብቶች እና ነጻነቶችን የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታውን አለመወጣቱን ያመለክታል፡፡ ፍርድ ቤቱ የተጋቢዎች ፈቃድ መኖር በእስልምና ሃይማኖት ሥርዓት ለተፈፀመ ጋብቻ የግድ አይደለም ለማለት ያበቃው በሸርዓ ሕጉ ግዴታ አለመሆኑን ከሸርዓ ፍርድ ቤት ጠይቆ መረዳቱን ውሳኔው የሚያመለክት ሲሆን ፤ መደበኛ ፍርድ ቤት የቀረበለትን ክርክር አግባብነት ባላቸው የሕገ መንግስቱ ፣ መደበኛ መሰረታዊ ህጎች እና የሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት ማድረግ እንጅ የሃይማኖት ሕጎችን መሠረት አድርጎ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን የለውም፡፡

የሥር ፍርድ ቤት እንደሚለው እና ተጠሪም በሰበር ችሎቱ ባቀረቡት ክርክር በግራቀኙ መካከል የተደረገው ጋብቻ በእስልምና ሃይማይኖት አንዲት ሴት ለመጋባት በወላጅ አባቷ ፣ አባት ከሌላት በወንድም እያለ በወንድ ቤተሰብ በኩል በውክልና ኒካ ከታሰረ በኋላ በሃይማኖቱ ፣ በአከባቢው በሕልና ልማድ አንፃር ጋብቻ እንደተፈፀ ስለሚቆጠር በቤተሰብ ሕጉ ላይ የተመለከቱት ቅደመሁኔታዎች ለተያዘው ጉዳይ ተገቢነት የለውም የሚለውም ስታይ የሀገሪቱን የበላይ ሕግ የሆነው የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 34(2) ጋብቻ በተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፈቃድ ብቻ እንደሚመሰረት የሚደነግገውን የሚቃረን በመሆኑ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9(1) መሠረት ተቀባይነት ሊኖረው የሚችል አይደለም፡፡ ፍርድ ቤቱ ለውሳኔው የሸርዓ ሕጉን መሠረት ማድረጉም የመንግስትና የሃይማኖት ተቋማትን ሚና መደበላለቅን የሚያመጣ በህገ በመንግስቱ

ለመንግስት ተለይቶ ከተሰጠው ተግባር በመውጣት በሃይማት ጉዳይ ጣልቃ መግባት የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 11 ድንጋጌን የሚፃር ተግባር ስለሆነ ተቀባይነት የለውም፡፡

ሲጠቃለል አመልካች ነጻና ሙሉ ፈቃዳቸውን ሰጥተው ከተጠሪ ጋር ጋብቻ ሳይመሰርቱና ለአንድ ቀን እንኳን አብሮ የመኖር ግዴታቸውን ሳይወጡ ፤ በግራቀኙ መካከል በሕግ ፊት የፀና ጋብቻ ሳይፈፀም የፍቺ ውሳኔ መሰጠቱ የሚነቀፍ በመሆኑ ቀጣዩ ተወስኗል፡፡

ውሳኔ

የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚው ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 16728 ነሐሴ 10 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት ጉዳዩን ያዩት በየደረጃው ያሉት የሥር የክልሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ፍርድ፣ ውሳኔ ፣ ብይን እና ትዕዛዝ በማጽናት የሰጠውን ውሳኔ እና ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት **ተሽሯል**፡፡

በኢ/ፌ/ዲ/ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 34(2) እንዲሁም በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 75/1996 አንቀጽ 16 መሠረት በአመልካች ነፃና ሙሉ ፈቃድ በግራቀኙ መካከል የተፈፀ የሚጸና ጋብቻ የለም በማለት ተወስኗል፡፡

አመልካች እና በተጠሪ መካከል የተፈፀመ ጋብቻ ሳይኖር በፍርድ ቤት የሚሰጥ የፍቺ ውሳኔ የለም ብለናል፡፡

በዚህ መዝገብ ላይ መስከረም 10 ቀን 2014 ዓ/ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ፡፡

በሰበር ክርክሩ የደረሰውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የግላቸውን ይቻሉ፡፡

በዚህ መዝገብ ላይ መስከረም 10 ቀን 2014 ዓ/ም የተሰጠው ዕግድ ተነስቷል፡፡

ውሳኔው ግንቦት 4 ቀን 2014 ዓ/ም በችሎት ተነቧል፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

የስ/መ/ቁ. 204514

የካቲት 30 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች- አቶ ሰይድ ተስፋ - ጠበቃ ታምራት ቸርነት ቀርቧል

ተጠራ- ወ/ሮ ሉባባ ጀማል ቀርቧል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርዱ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ውልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን አንፆኪያ ወረዳ ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ የአመልካች እና የተጠሪ ጋብቻ በፍቺ እንዲፈርስ ከተወሰነ እና የሀብትና ንብረት ክፍፍል ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ከተጠሪ ጋር የጋራ እዳ ብር 380,000.00 እንዳለብን ተማምነን የድርሻዋን ብር 190,000.00 ለመክፈል የተስማማች ቢሆንም ልትከፍል ስላልቻለች በውሉ መሠረት እንድትፈፅም ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቆ ተከራክሯል፡፡

ተጠሪ በበኩሏ በሰጠችው መልስ ጉዳዩ በፍርድ ያለቀ ስለሆነ በድጋሚ ክስ ሊቀርብብኝ አይገባም፤ በስር ፍርድ ቤት በክርክር ላይ እያለን በአመልካች በኩል ያሉት ሽማግሌዎች የንብረት ክፍፍሉን በስምምነት እንጨርስ በማለት አሳስተው አስፈረሙኝ እንጂ በማላውቀው እዳ ልጠየቅ አይገባም፤ ስምምነቱ ህጋዊ ቢሆን ኖሮ በፍርድ ቤት ሊፀድቅ ይችል ነበረ፤ እንዲሁም የስምምነቱ ርዕስ የንብረት ክፍፍል መሆኑን ሲገልጽ ይዙቱ ደግሞ እዳ አለ የሚል ሆኖ እርስ በእርሱ የሚጣረስ ነው የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርባ ክሱ ውድቅ እንዲደረግላት ጠይቃለች፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የስር ወረዳ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ጉዳዩ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው በማለት የአመልካችን አቤቱታ በብይን ውድቅ አድርጎታል። በዚህ ውሳኔ ቅር የተሰኘው አመልካች ይግባኙን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ከዚህ በፊት ግራ ቀኙ ያደረጉትን ስምምነት መሠረት አድርጎ ቀረበ ክርክርም ሆነ የተሰጠ ውሳኔ የለም፤ የግልግል ስምምነቱም ለፍርድ ቤት ቀርቦ መጽደቅ አያስፈልገውም በማለት የወረዳ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ ሽሮ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ የመሰለውን እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ህ/ቁ. 341(1) መሠረት መልሶ ልኮለታል።

የወረዳ ፍርድ ቤቱም መዝገቡን እንደገና አንቀሳቅሶ የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ግራ ቀኙ የጋራ እዳ አለባቸው ከተባለ መጠየቅ ያለበት ብድር አበድረናቸዋል የሚለው ወገን እንጂ አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ ሊያቀርብ አይችልም በማለት ወስኗል። አመልካች አሁንም በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት ይግባኙን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ጉዳዩን ያስቀርባል ብሎ ግራ ቀኙን ካራከረ በኋላ የወረዳ ፍርድ ቤቱ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ጉዳዩን በመለሰበት ነጥብ መሠረት አጣርቶ አልወሰነም፤ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ስምምነት ፀድቋል ወይስ አልፀደቀም ከሚለው ጭብጥ ወጥቶ በግልግል ስምምነቱ ላይ ግራ ቀኙ ያነሷቸውን ክርክሮች በአግባቡ አዳምጦና አከራክሮ የመሰለውን ውሳኔ ይስጥበት በማለት በድጋሚ ጉዳዩን መልሶ ልኮለታል።

ጉዳዩ በድጋሚ የተመለሰለት የወረዳ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረና የማጣሪ ምስክሮችን ጠርቶ ካደመጠ በኋላ በግራ ቀኙ መካል የተደረገው ስምምነት በሁለቱም ነፃ ፈቃድ የተፈፀመ ነው፤ በስምምነቱ መሠረት አመልካች ግዴታዋን ያልተወጣች በመሆኑ ብር 190,000.00 ትክፈል በማለት ወስኗል። ተጠሪ በበኩሏ በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ብታቀርብም አቤቱታዋ ውድቅ ተደርጎባታል። በመቀጠል የሰበር አቤቱታዋን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርባ ግራ ቀኙ ከተከራከሩበት በኋላ ሰበር ሰሚ ችሎቱ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተደረገው የግልግል ስምምነት ፍርድ ቤት ቀርቦ ያልፀደቀ በመሆኑ ህጋዊ ውጤት የለውም በማለት በወረዳው ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፀናውን ውሳኔ በመሻር በተጠሪ ላይ የቀረበው ክስ ተገቢነት የለውም ሲል ወስኗል። ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ በአመልካች የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው።

አመልካች መጋቢት 14 ቀን 2013 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተደረገው የግልግል ስምምነት የፍርድ ቤት ክርክር ካበቃ በኋላ የተፈፀመ ሆኖ እያለ በፍርድ ቤት ካልፀደቀ ተቀባይነት የለውም ተብሎ መወሰኑ፤ ስምምነቱ በፍርድ ቤት ቀርቦ መጽደቅ እንደማይጠበቅበት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ተጠሪ ይግባኝ ያላቀረበችና ይህንን ውሳኔ ባላሻረችበት ስምምነቱ አልፀደቀም ተብሎ ክሱ ውድቅ መደረጉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገበዋል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉም ተጠሪ በተደረላት ጥሪ መሠረት ቀርባ በሰጠችዉ መልስ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበባቸው ነጥቦች በክልሉ ፍርድ ቤቶች የፍሬ ነገር እና የማስረጃ ምዘና ያደረጉባቸው እና የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠባቸው ጉዳዮ ስለሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10(ሐ) እና (መ) መሠረት ይህ ሰበር ችሎት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ሰበር ሰሚ ችሎት መጋቢት 28 ቀን 2009 ዓ.ም በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተደረገው ስምምነት ፍርድ ቤት ቀርቦ ባለመጽደቁ ህጋዊ ውጤት የለውም፣ እንዲሁም አመልካች በስምምነቱ መሠረት የተጣለበትን ተነፃፃሪ ግዴታ አልተወጣም ሲል አቤቱታውን ውድቅ በማድረግ መወሰኑ ህግን መሠረት ያደረገ ስለሆነ ውሳኔው ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክራለች፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ የክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከላይ የተገለፀውን ሲመለል ይህ ችሎትም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም አመልካች ያቀረበዉን ክስ መሰረት በማድረግ ጉዳዩን የተመለከተዉ የወረዳዉ ፍርድ ቤት በመካከላቸዉ የነበረዉ ጋብቻ ከመፍረሱ በፊት ብር 380,000.00 ዕዳ ያለባቸዉ ስለመሆኑ ተጠሪ በነፃ ፍቃዷ ከአመልካች ጋር ባደረገችዉ ስምምነት አምና ለመክፈልም የተስማማች በመሆኑ በስምምነቱ መሠረት ግማሹን ለአመልካች ብር 190,000.00 ልትከፍል እንደሚገባ የወሰነዉ ዉሳኔ በከፍተኛዉ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ የጸና ቢሆንም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይህን ዉሳኔ ሽሮታል፡፡ ሰበር ሰሚዉ ችሎት ዉሳኔዉን ሲሽር መሠረት ያደረገዉም በግራ ቀኝ መካከል የተደረገዉ እና ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የእርቅ ስምምነት ፍርድ ቤት ቀርቦ መጽደቅ እንዳለበት በዉሉ ላይ የተመለከተ ቢሆንም ለፍርድ ቤት ቀርቦ ያልጸደቀ መሆኑን፣ የእርቅ ስምምነቱ ቀደም ሲል በፍርድ ቤት የተሰጠዉን ዉሳኔ ለማስቀረት የተደረገ

በመሆኑ እና እንደዚህ ዓይነት ስምምነት ደግሞ በፍርድ ቤት ቀርቦ ካልጸደቀ ህጋዊ ውጤት የሌለዉ ነዉ እንደሆነ በዚህ ረገድ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 98263 ላይ የተሰጠዉን አስገዳጅ የህግ ትርጉም በዋቢነት በመጥቀስ ስለመሆኑ የዉሳኔዉ ይዘት ያሳያል፡፡

እንደሚታወቀዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ስለመሆኑ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) ላይ ከተመለከተዉ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት ነዉ? ወይም አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ መቼ ነዉ? የሚለዉን ጽንሰ ሃሳብ አስመልክቶ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በበርካታ መዛግብት ላይ በሰጠዉ ዉሳኔ አመላካች መስፈርቶችን ለማስቀመጥ የሞከረ ቢሆንም፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በህግ ደረጃ ወጥ የሆነ ትርጓሜ አልተሰጠዉም ነበር፡፡ ይሁንና ከጥር 13 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ የዋለዉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትርጓሜ ይሰጣል፡፡ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ተግባራቸዉን ተጠያቂነት ባለበት ሁኔታ ዉጤታማ፣ ቀልጣፋ፣ ተደራሽ እና ተገማች በሆነ ሁኔታ እንዲያከናዉኑ ማድረግን አንዱ ዓላማዉ ያደረገዉ ይህ አዋጅ ካካተታቸዉ አዳዲስ ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ለሚለዉ ጽንሰ ሃሳብ ትርጓሜ መስጠቱ እና በክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታይ የሚችልበትን ሁኔታ አስመልክቶ የተለየ ድንጋጌ ማካተቱ ነዉ፡፡ በአዋጁ በትርጉም ክፍል አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግ ያላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣ ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት ከዋናዉ ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ሲሆን ነዉ፡፡

በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል የሰበር አቤቱታ ሲቀርብለት ለአቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ ጉዳይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ ከላይ በዝርዝር ከተመለከቱት ሁኔታዎች ዉስጥ ቢያንስ አንዱን ያሟላ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 10 ላይ ከተመለከቱት ድጋጌዎች የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታዉን ተቀብሎ በሰበር የማየት ስልጣን የሚኖረዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ የሚቃረን ሲሆን እንዲሁም አግባብነት የሌለዉን ህግ በመጥቀስ ወይም ህግን ያላግባብ በመተርጎም የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሆኖ ጉዳዩም አገራዊ ፋይዳን የሚመለከት ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ከዚህም የምንረዳዉ የሰበር አቤቱታ የቀረበበት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ከእነዚህ ሦስቱ ሁኔታዎች ዉጪ ባሉት ሁኔታዎች፣ መሠረታዊ የህግ ስህተትን መስፈርት አስመልክቶ በአዋጁ አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱን የሚያሟላ ሆኖ ቢገኝ እንኳን፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር የማረም ስልጣን የሌለዉ መሆኑን ነዉ፡፡ ስለሆነም ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን በመቃወም የቀረበለት አቤቱታ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ከሆነ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን በመወሰን ረገድ እነዚህኑ ልዩ ሁኔታዎች ማለትም በአዋጁ አንቀጽ 10(1/ሐ) ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ከግምት ዉስጥ የማስገባት ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

ከዚህ አንፃር የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከፍ ሲል በተመለከተዉ መልኩ የሰጠዉ ዉሳኔ በአዋጁ ቁጥር 1234 አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አግባብ ህገ መንግስቱን የሚጥስ፣ አገራዊ ፋይዳ ያለዉን የህዝብ ጥቅም የሚጎዳ ወይም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሚጥስ ይዘት የሌለዉ በመሆኑ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት አይቻልም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

ዉሳኔ

የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 03-907110 ላይ ጥር 17 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍትሐብሔር ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ጸንቷል።

በዚህ ችሎት የተደረገ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የዳኝነት ስልጣን

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰ.መ.ቁ.127995

ጥር 24 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡-1. ተክሊት ይመሰል

2. ተፈሪ ገብሩ

3. ቀነዓ ቂጣታ

4. አይሸሽም መለሰ

5. ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- ብርሃን ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ ነ/ፈጆች አብነት ሹክጌ እና ባይሳ ሚልኬሳ ቀርበዋል

ተጠሪዎች፡-1. አቶ ዳንኤል ተስፋዬ ቀረበ የለም

2. ወ/ሮ ራሔል አበራ ቀርበዋል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍርድ</u>

ይህ የሰበር ጉዳይ የሐራጅ ሽያጭ እንዲፈርስና እንዲታገድ የቀረበ ክስን መነሻ ያደረገ ክርክር ሲሆን፣ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.177079 ግንቦት 8 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ

እንዲታረምልን በማለት የአሁን አመልካች ያቀረበዉን የሰበር አቤቱታ ምርመሮ ለመወሰን ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ በፌዴራል መጀመሪያ ደራጃ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪዎች የሥር ከሳሾች፣ የአሁን አመልካች የሥር 1ኛ ተከሳሽ፣ በዚህ ችሎት የክርክሩ ተከፋይ ያልሆነዉ የሥር 2ኛ ተከሳሽ የኦሮሚያ ጤና ቢሮ ሁኖ ሲከራከሩ የነበረ ሲሆኑ፤ ከሳሾች ባቀረቡት ክስ ከሳሾች ባልና ሚስት መሆናቸዉን በመግለጽ በ1ኛ ከሳሽ የይሳኮር ኮንስትራክሽን ባለቤት እና ስራ አስኪያጅ ሲሆን፣ 1ኛ ከሳሽ በድርጅቱ አማካይነት በባሌ ዞን ዉስጥ የጎሮ ሆስፒታል እና በአርሲ ዞን ዉስጥ ቀርሳ ሆስፒታል ለመገንባት ስምምነት ያደረገ ሲሆን 1ኛ ተከሳሽ ለዚህ ዉል አፈጻጸም የቅድመ ክፍያ ዋስትና ብር 11,600,000 ሰጥቷል፡፡ 2ኛ ተከሳሽ ለዚህ ዋስትና ሲባል በ2ኛ ከሳሽ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ሁለት ካርታ፣ በ1ኛ ከሳሽ ስም ተመዝግቦ የሚገኙ ሶስት መኪኖች በመያዣነት ይዟል፡፡ 2ኛ ተከሳሽ የግንባታ ዉሉን አቋርጧል፡፡

ከ1ኛ ተከሳሽ ጋር የተደረገዉ የቅድመ ክፍያ ዋስትና ዉል ባለመታደሱ እና ጊዜዉ በማለቁ ቀሪ ሆኗል፡፡ ይህ ሆኖ ሳለ ተከሳሾች በፍ/ቤት ሲያደርጉ የነበረዉን ክርክር አቋርጠዉ መዝገቡን በማዘጋት የከሳሾችን ንብረት በሕገ ወጥ መንገድ ሸጠዉ፣ ሎሎቹን ለመሸጥ እየተንቀሳቀሱ ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.445 መሰረት ሽያጩ እንዲፈርስ ወይም እንዲታገድ ወይም በ1ኛ ከሳሽ እና በ2ኛ ተከሳሽ አማካይነት እንዲጣራ እና ለማቀናነስ ወይም ለማቻቻያ እንዲዉል በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ይህን ክስ በተመለከተ የሥር 1ኛ ተከሳሽ ባቀረበዉ መልስ ፍ/ቤቱ ይህን ጉዳይ ለማየት ስልጣን የለዉም፣ በተመሳሳይ ጉዳይ ክስ የቀረበ ስለሆነ ክሱ ድጋሚ ሊቀርብ አይችልም፣ ተከሳሽ በመያዣ የያዛቸዉን ንብረቶች ዕዳዉ ካልተከፈለ ማስጠንቀቂያ በመስጠት በሐራጅ በመሸጥና የባለቤትነት መብቱን በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 3 መሰረት ማዘዋወር ይችላል በማለት ተከራክሯል፡፡ 2ኛ ተከሳሽ በበኩሉ ባቀረበዉ መልስ የተለያዩ መከራከሪያ ነጥቦችን በማቅረብ፣ ተከሳሽ በሐራጅ ሽያጭ ዉስጥ ስላልተሳተፍን ክሱ ስለማይመለከተን በነጻ እንዲንሰናበት በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ በሰጠዉ ብይን ከሳሽ ያቀረበዉ ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.445 መሰረት ጨረታዉ በአግባቡ እየተካሄደ አይደለም የሚል ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት የፍ/ቤቱ ስልጣን ነዉ፣ ይህ ጉዳይ በድጋሚ የቀረበ ነዉ በማለት የቀረበዉ መቃወሚያ ተቀባይነት የለዉም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዉን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

የሥር 1ኛ ተከሳሽ በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ይግባኙን ውድቅ በማድረግ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ትዕዛዘ በመቃወም ለማለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች ግንቦት 15 ቀን 2008 ዓ.ም የተጻፈ አራት ገጽ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአቤቱታዉም ይዘት፡--የአሁን ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ የመያዣ ዉል ግምቱ ብር 11,600,000 ስለሆነ በዚህ ግምት መሰረት ተገቢዉን የዳኝነት ክፍያ ፈጽመዉ ክስ ማቅረብ ሲገባቸዉ፣ በዚህ አግባብ ዳኝነት ሳይከፈል ፋይል መከፈቱ ከፍተኛ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ ለክሱ መመስረት ምክንያት የሆነዉ የመያዣ ዉል ግምት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ስልጣን ነዉ፡፡ ተጠሪዎች በተመሳሳይ ጉዳይ የተለያዩ ክሶችን አቅርበዉ ሶስት መዛግብቶችን አስከፍተዉ ክርክር ላይ ያለ ሆኖ ሳለ ጉዳዩ በድጋሚ የቀረበ አይደለም በማለት የተሰጠዉ ብይን እንዲታረም በማለት በዝርዝር ቅሬታዉን አቅርቧል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታዉ የሚጣራ ጉዳይ አለዉ በማለት የስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ በታዘዘዉ መሰረት ሐምሌ 4 ቀን 2008 ዓ.ም የተጻፈ ሶስት ገጽ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት፡--አመልካች የሥር ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ የሰጠዉን ብይን በመቃወም በመሆኑ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.320 /3/ መሰረት በሥረ ነገሩ ላይ ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በዚህ ብይን ላይ ይግባኝም ሆነ የሰበር አቤቱታ ለማቅረብ ስለማይቻል የቀረበዉ አቤቱታ ከሥነ ሥርዓት ዉጭ ነዉ፡፡ አመልካች የዳኝነት ክፍያን በተመለከተ በሥር ፍ/ቤት ያቀረበዉ መቃወሚያ በሌለበት በክርክር መሐል ሊያቀርብ አይችልም፡፡ ተጠሪ ባቀረቡት ክስ የጠየቁት ዳኝነት የተጠሪዎችን ንብረት ያለአግባብ ለመሸጥ የወጣዉ ጨረታ ትክክል ባለመሆኑ ተገቢ ዳኝነት ተከፍሎ ክሱ ቀርቧል፡፡ ተጠሪዎች የብር 11.6 ሚሊዮን ዳኝነት ወይም መብት ለማስከበር ዳኝነት አልጠየቁም፡፡ አመልካች በተመሳሳይ ጉዳይ ክሶችን አቀርቧል ያለዉን በተመለከተ እነዚህ ክሶች በባህሪያቸዉና በጭብጥም ደረጃ የተለያዩና የማይገናኙ ስለሆኑ የቀረበዉ አቤቱታ ተቀባይነት የለዉም፡፡ የሥር ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ስላለዉ አመልካች ያቀረበዉ አቤቱታ ተሰርዞ የሥር ዉሳኔ እንዲጸናልን በማለት ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች የመልስ መልስ አናቀርብም በማለቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኞቸዉን ክርክር ለሰበር አቤቱታዉ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ

እንዲሁም የአመልካች ባንክ በመያዣ የያዛቸዉን ንብረቶች ለመሸጥ በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት ለሚፈጽመዉ የሐራጅ ሽያጭ መደበኛዉ ፍ/ቤት የማየት ስልጣን አለዉ ወይስ የለዉም? የሚለዉን ነጥብ እንደጭብጥ በመያዝ እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነዉ የአሁን ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ አመልካች በመያዣነት የያዛቸዉን ንብረቶች ያለአግባብ ከሕግ ዉጭ በሐራጅ ስለሸጠ እና ለመሸጥም እየተንቀሳቀሰ ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.445 መሰረት ሽያጩ እንዲፈርስ ወይም እንዲታገድ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸዉን ከሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ ማየት ይቻላል፡፡ የአሁን አመልካች ባቀረበዉ ክርክር ባንኩ በመያዣ የያዛቸዉን ንብረቶች በሐራጅ ለመሸጥ እና ለገዢም ባለቤትነቱን ለማዛወር ስልጣን እንዳለዉ እና ፍ/ቤቱም ጉዳዩን ለማየት ስልጣን እንደሌለዉ በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ ግራ ቀኙቸዉ የሚከራከሩበት ጉዳይ የአመልካች ባንክ በመያዣነት የያዛቸዉ ንብረቶች የሐራጅ ሽያጭ ጋር የተያያዘ መሆኑን የተካዳ አይደለም፡፡ ይህን የግራ ቀኙቸዉን ክርክር በተመለከተ አግባብነት ወይም ተፈጻሚነት ካለዉ ሕግ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምረነዋል፡፡

እንደተመለከተዉ የአሁን አመልካች በዋስትና መያዣነት የያዛቸዉን የተጠሪዎችን የማይንቀሳቀስ እና ልዩ የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችን በሐራጅ ከመሸጥ ጋር የሚያያዝ መሆኑ ግልጽ ነዉ፡፡ በመሆኑም ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያለዉ ሕግ ‹‹በባንክ በመያዣ ስለተያዘ ንብረት የወጣ አዋጅ ቁጥር 97/90›› እንደሆነ የሚያከራክር ጉዳይ አይደለም፡፡ በዚህ አዋጅ መሰረት ባንክ በመያዣነት የያዛቸዉ ንብረቶች ለመሸጥ ያለዉ ስልጣን፣ ከዚህ ሽያጭ ጋር በተያያዘ መደበኛ ፍ/ቤት ያለዉ ስልጣን፣ በዚህ አዋጅ አግባብ ለተፈጸመ የሐራጅ ሽያጭ ጋር በተያያዘ በምን አግባብ ለመደበኛ ፍ/ቤት ጉዳዩ ሊቀርብ እንደሚችል መታየት ያለባቸዉ ነጥቦች ናቸዉ፡፡

የዚህን አዋጅ ዓላማ ከአዋጁ መግቢያ /preamble/ መገንዘብ የሚቻል ሲሆን፣ በመግቢያ ከተመለከቱት መካከል ባንኮች በመያዣ የያዙትን ንብረቶች ለመሸጥ መደበኛ ሥነ ሥርዓት ተከትሎ ለመደበኛ ፍ/ቤት ክስ አቅርቦ ለማስወሰንና ዉሳኔዉን ለማስፈጸም ረጅም ጊዜ በመዉሰዱ፤ ባንኮች ገንዘብ አበድረዉ ወለድ በመሰብሰብ ገቢ የማግኘት ሥራቸዉ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ በማሳደሩ፣ ባንኮች የሚሰጡትን ብድሮች በተቀላጠፈ መንገድ መሰብሰብ እንዲችሉ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር አዋጁ ማስፈለጉን ያመለክታል፡፡ ከዚህም በላይ በአዋጁ አንቀጽ 3 እና 4 እንደተመለከተዉ ባንኮች በመያዣነት የያዙአቸዉን ንብረቶች ተፈላጊዉ ዕዳ ያልተከፈለ እንደሆነ በድንጋጌዎቹ የተመለከተዉን ሥርዓት ተከትሎ ንብረቶቹን በሐራጅ የመሸጥ እና ለገዢዉ ባለቤትነቱን የማዛወር እና ሁለት ጊዜ ሐራጅ ወጥቶ ያልተሸጠ እንደሆነ ንብረቱን በመያዣ

ስምምነቱ ላይ በተመለከተዉ ግምት መዉሰድ እንደሚችሉ እና ወደ ስሙ ለማዛወር ስልጣኑ የባንኮች እንደሆነ ማየት ይቻላል፡፡ ባንክ ይህን የሐራጅ ሽያጭ ሲያካሄድ እንደአግባብነቱ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.394--449 ተፈጻሚ ማድረግ እንደሚችል በአዋጁ አንቀጽ 6 ሥር ተመልክቷል፡፡ ከዚህ ሁሉ መገንዘብ እንደሚቻለዉ ባንክ ለዕዳ በመያዣ የያዘዉን ንብረት በሐራጅ በመሸጥ ዋናዉን ገንዘብ እና ወለድ ለመሰብሰብ ለሚያካሄደዉ የሐራጅ ሽያጭ ሂደት ጋር በተያያዘ ስልጣኑ የባንኩ መሆኑን እና መደበኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ማየት እንደማይችል ነዉ፡፡ መደበኛ ፍ/ቤት ባንክ ያካሄደዉ የሐራጅ ሽያጭ በአግባብ ነዉ ወይስ አይደለም? የሐራጅ ሽያጩ ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚሉትን ነጥቦች አይቶ ለመወሰን ስልጣን እንደሌለዉ መገነዘብ ይቻላል፡፡ መደበኛ ፍ/ቤቶች እነዚህን ነጥቦች በማየት የሐራጅ ሽያጩ የተካሄደዉ በአግባብ ነዉ ወይስ አይደለም? በዚህ ምክንያት ሽያጩ ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚሉትን በመመርመር የሚወስኑ ከሆኑ ከላይ የተመለከተዉን የአዋጁን ዓላማ ሙሉ በሙሉ ዋጋ ሚያሳጣ እና የአዋጁንም ተፈጻሚነት የሚገድብ ይሆናል፡፡ በመሆኑም ሕግ አዉጭዉ ባንክ በመያዣ የያዘዉን ንብረት በሐራጅ በመሸጥ ያበደረዉን ገንዘብ መሰብሰብ እንዲችል በአዋጁ የዘረጋዉን ሥርዓት መደበኛ ፍ/ቤቶች በማክበር ተፈጻሚ ማድረግ ይገባቸዋል እንጂ አዋጁ ለባንክ የሰጠዉን ስልጣን በመንጠቅ ጉዳዩን የማየት ስልጣን አለን በማለት የአዋጁን ዓላማ ዋጋ ማሳጣት የለባቸዉም፡፡ ስለሆነም መደበኛ ፍ/ቤት አንድ ባለዕዳ የሐራጅ ሽያጭ ያለ አግባብ የተደረገ ስለሆነ እንዲፈርስልኝ ወይም እንዲታገድልኝ በማለት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.445 በመጥቀስ ያቀረበዉን ክስ በመቀበል ክርክር በማካሄድ አዋጁ የወጣበትን ዓላማ መና ማስቀረት የለበትም፡፡

በሌላ በኩል ባለዕዳዉ የሐራጅ ሽያጭ በአግባቡ አልተደረገም የሚል ከሆነ በዚህ ምክንያት የደረሰበትን ጉዳት ለይቶ ክስ ማቅረብ እንዳለበት አወጁ ያሳያል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 7 ስለባንክ ተጠያቂነት ሲደነግገዉ ‹‹ባንክ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 የተጠቀሱትን አግባብ ያላቸዉን ድንጋጌዎች በመተላለፍ ሽያጩን በመፈጸሙ በባለዕዳዉ ላይ ለሚደርሰዉ ጉዳት በኃላፊነት ተጠያቂ ይሆናል›› በማለት ይደነግጋል፡፡ የእንግሊዝኛዉ ቅጅ Liability of of the Bank በማለት <<The Bank shall be liable for any damage it causes to the debtor in the process of selling by auction in violation of the relevant provisions of the civil procedure code specified under Article 6 of this Proclamation>> በማለት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ እንደሚቻለዉ አንድ ባለዕዳ ከሐራጅ ሽያጭ ጋር በተያያዘ ጉዳዩን ለመደበኛ ፍ/ቤት ማቅረብ የሚችለዉ የሐራጅ ሽያጩ ያለ አግባብ ከሕግ ዉጭ የተደረገ

ነዉ የሚል ከሆነ፣ በዚህ ምክንያት የደረሰበት ጉዳት ካለ አግባብነት ባለዉ ማስረጃ በማስደገፍ ክስ አቅርቦ ካሳ እንዲከፈለዉ ዳኝነት ከመጠየቅ ዉጭ የሐራጅ ሽያጩ እንዲፈርስ ወይም እንዲታገድለት የሚጠይቅበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ በዚህ ድንጋጌ ደረሰብኝ የሚለዉን ካሳ አግባብነት ባለዉ ማስረጃ በማስደገፍ ስልጣን ላለዉ መደበኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ከመጠየቅ በስተቀር ሐራጁ እንዲፈርስ ክስ ማቅረብ አይችልም፡፡ በመሆኑም መደበኛ ፍ/ቤት በዚህ አዋጅ አግባብ የሚቀርብ ክስ የካሳን ጥያቄ የሚመለከት ካልሆነ በስተቀር ክሱን ተቀብሎ ግራ ቀኞቸዉን አከራክሮ ተገቢ ዉሳኔ ለመስጠት ስልጣን የለዉም፡፡

ይህን አዋጅ መሰረት በማድረግ ባንክ ያካሄደዉ ሐራጅ እንዲፈርስ ወይም ለማከሄድ ያለዉ ሐራጅ እንዲታገድ የሚል ክስ የቀረበ እንደሆነ፣ ፍ/ቤት የፍ/ብ/ሥ/ሕ/ቁ.9 /1/ እና 231 መሰረት ክሱን ተቀባይነት የለዉም በማለት ለባለጉዳዩ መመለስ ይጠበቅበታል፡፡ ነገር ግን ፍ/ቤቱ ክሱን ተቀብሎም ቢሆን ጉዳዩን ለማየት የሥረ ነገር ስልጣን የሌለዉ በመሆኑ፣ በሌለ ተከራካሪ ወገን መቃወሚያ ቢቀርብም ባይቀርብም፣ ፍ/ቤቱ ይህን ጉዳይ ለማየት ስልጣን እንደሌለዉ በተገነዘበ ጊዜ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.9(2) 244 /2/ /ሀ/ እና 245 /2/ መሰረት ክሱን ዉድቅ በማድረግ መዝገቡን መዝጋት አለበት፡፡ መደበኛ ፍ/ቤት በዚህ አግባብ የቀረበዉን ክስ ዉድቅ ማድረግ ሲገባዉ ስልጣን አለኝ በማለት ጉዳዩን ማየት የቀጠለ እንደሆነ ይግባኝ ሊባልበት የሚል ጉዳይ ነዉ ወይስ በክርክሩ ላይ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ አንድ ላይ ይግባኝ የሚቀርበበት ጉዳይ ነዉ? የሚለዉ ነጥብ መታየት ያለበት ጉዳይ ነዉ፡፡

ከዚህ አንጻር የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.320 /1/ እና /2/ እንደሚያመለክተዉ ይግባኝ ሊባልበት የሚችለዉ የመጨረሻ ፍርድ ባገኘ ጉዳይ ላይ እንደሆነ እና ጊዜያዊ አገልግሎት ባለዉ በማናቸዉም ትዕዛዝ ላይ ከሥረ ነገሩ ፍርድ በፊት ይግባኝ ሊባልበት እንደማይችል እና በክርክሩ የመጨረሻ ፍርድ እንደተሰጠ ከሥረ ነገሩ ጋር አጠቃሎ ይግባኝ ማቅረብ እንደሚቻል ነዉ፡፡ ነገር ግን ይህ ችሎት የግራ ቀኞቸዉን ክርክር እንደመረመረዉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.320 /2/ ድንጋጌ ከአዋጅ ቁጥር 97/90 አንጻር መተርጎም እንዳለበት ተገንዝቧል፡፡ በዚህ መሰረት ባንክ በመያዣ የያዘዉን ንብረት በሐራጅ ከመሸጥ ጋር በተያያዘ፣ የካሳ ጥያቄ ካልሆነ ሐራጁ እንዲፈርስ ወይም እንዲቆም ዳኝነት ለመጠየቅም ሆነ ፍ/ቤት ተቀብሎ ለማየት ስልጣን እንደሌለዉ በግልጽ ተደንግጎ እያለ መደበኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አለኝ በማለት ክርክሩን ማየት የሚቀጥል እንደሆነ፣ የአዋጁን ዓላማ ዋጋ የሚያሳጣዉ በሆኑ በሥረ ነገሩ ላይ ፍርድ እስከሚሰጥ ድረስ ሊጠበቅ የሚገባ ጉዳይ አይደለም፡፡ ስለሆነም መደበኛ ፍ/ቤት ሕግ

አዉጭዉ አዋጅ ቁጥር 97/90 ያወጣበትን ዓላማ መና በሚስያቀር ሁኔታ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አለኝ በማለት ክርክሩን ማየት የሚቀጥል እንደሆነ የአዋጁን ዓላማ ከማሳካት አንጻር ጊዜያዊ አገልግሎት ያለዉ ትዕዛዝ ነዉና ይግባኝ ሊባልበት አይችልም ሊባል አይገባም፡፡ መደበኛዉ ፍ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 97/90 በግልጽ ከተደነገገዉ ዉጭ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አለኝ በማለት ክርክሩን ማየት የሚቀጥል እንደሆነ ክርክሩ ከመፍጀዉ ጊዜ የተነሳ ባንክ ያበደረዉን ገንዘብ በመሰብሰብ በወለድ መልክ ማግኘት የሚገባዉን ገቢ የሚያሳጠዉ በመሆኑ እና ያበደረዉን ገንዘብ በተቀላጠፈ መንገድ እንዳይሰበስብ በማድረግ የባንኩን ጠቅም የሚጎዳ መሆኑ ግልጽ እስከሆነ ድረስ በዚህ ጉዳይ ይግባኝ የማይባልበት ምክንያት የለም፡፡ ስለዚህ ይህ ጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.320 /2/ ሥር የሚወድቅ አይሆንም፡፡ ነገር ግን በሥረ ነገሩ ላይ ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት ይግባኝ ሊባልበት የሚችል ጉዳይ ነዉ ብለናል፡፡

በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የአሁን ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ አመልካች በመያዣ የያዛቸዉን ንብረቶች ያለአግባብ ከሕግ ዉጭ በመሸጡ እና ለመሸጥም እየተንቀሳቀሰ በመሆኑ የሐራጅ ሽያጭ እንዲፈርስ ወይም እንዲታገድ የሚል ደኝነት የጠየቁ በመሆኑ፣ ከላይ በተመለከተዉ መሰረት ተጠሪዎች ይህን ክስ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የማቅረብ መብት የላቸዉም፡፡ ተጠሪዎች ይህን ክስ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ፍ/ቤቱ ክሱን ሳይቀበል ለተጠሪዎች መመለስ ነበረበት፡፡ ፍ/ቤቱ ክሱን መቀበል አልነበረበትም እንጂ ከተቀበለም አመልካች ባቀረበዉ መቃወሚያ መሰረት ጉዳዩን አከራከሮ ለመወሰን የሥረ ነገር ስልጣን የለኝም በማለት ክሱን ዉድቅ በማድረግ መዝገቡን መዝጋት ሲገባዉ ክርክሩን ለማየት ስልጣን አለኝ በማለት ክርክሩን ማየት መቀጠሉ የሕግ ድጋፍ የለዉም፡፡ የሥር ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ ለማየት የሥረ ነገር ስልጣን ሳይኖረዉ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አለኝ በማለት ብይን በመስጠቱ፣ አመልካች ይህን ብይን በመቃወም ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ማቅረብ ስለሚችል፣ ፍ/ቤቱ የሥር ፍ/ቤት ብይን በመሻር የሥር ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለዉም በማለት አስተካክሎ መወሰን ሲገባዉ ይህን ሳያደርግ በመቅረት የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት መወሰኑ የሕግ አግባብ የለዉም፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች ይህን ጉዳዩ አይቶ ለመወሰን የሥረ ነገር ስልጣን ሳይኖራቸዉ፣ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አለን በማለት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.233769 በ13/8/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ብይን እና ይህን ብይን በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.177079 ግንቦት 8 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ተሽሯል፡፡

የአሁን ተጠሪዎች የአመልካች ባንክ ለዕዳ ማስከፈያነት በመያዣ የያዛቸዉን ንብረቶች በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት በሐራጅ ከመሸጥ ጋር በተያያዘ የሐራጅ ሽያጩ ያለ አግባብ በሕገ ወጥ መንገድ የተደረገ ነዉና እንዲፈርስልን ወይም እንዲታገድልን በማለት ያቀረቡትን ክስ የሥር መደበኛ ፍ/ቤት ክሱን ተቀብሎ ዉሳኔ ለመስጠት ስልጣን የለዉም፡፡ የሥር መደበኛ ፍ/ቤት በዚህ አግባብ የቀረበዉን ክስ ለማየት ስልጣን ሳይኖራዉ ስልጣን አለኝ በማለት ብይን የሰጣ በመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.320 /2/ ሥር የሚወድቅ ሳይሆን ከሥረ ነገሩ ፍርድ በፊት ይግባኝ ሊባልበት የሚቻል ጉዳይ ነዉ ብለናል፡፡ የአሁን ተጠሪዎች የሐራጅ ሽያጩ ሂደት ያለ አግባብ ከሕግ ዉጭ በመደረጉ የደረሰባቸዉ ጉዳት ያለ እንደሆነ የአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 7 በሚደነግገዉ አግባብ በመደበኛ ፍ/ቤት ክስ በማቅረብ ካሳ ከመጠየቅ ይህ ዉሳኔ የሚከለክላቸዉ አይሆንም ብለናል፡፡

ግራ ቀኞቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

በ25/9/2008 ዓ.ም የተሰጠዉ እግድ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ.መ.ቁ.158634

ህዳር 28 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡....1. ተክሊት ይመሰል

2. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

3. ቀነዓ ቂጣታ

4. ተሾመ ሽፈራው

5. ፀሐይ መንክር

አመልካች፡.....ዳሽን ባንክ አ.ማ - ነ/ፈ አሉላ በሪሁን ቀረቡ

ተጠሪ፡.....ሪቼል ተስፋዬ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች ከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ሁኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ይህ ጉዳይ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.202150 በ06/07/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ ከሳሽ (የአሁን አመልካች) ባቀረበዉ ክስ በግራ ቀኝ መካከል በተደረገዉ የቤት ኪራይ ዉል የቤቱን ኪራይ ከቅጣት፣ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር በድምሩ 179,617.24 እንዲከፍለን እና ቤቱን እንዲያስረክበን በማለት ክሷል፡፡

በዚህ ክስ ላይ በግራ ቀኝ መካከል ጥቅምት 9 ቀን 2008 ዓ.ም በተደረገዉ የቤት ኪራይ ዉል የቤቱን ኪራይ የከፈልን ስለሆነ የቀረበዉ ክስ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን በመመርመር በግራ ቀኛቸዉ መካከል በተደረገዉ የኪራይ ዉል በመካከላቸዉ ያለመግባባት ቢፈጠር ጉዳያቸዉን በእርቅ ወይም በግልግል ዳኛ ለመፍታት የተስማሙ በመሆኑ፣ ግራ ቀኛቸዉ አለመግባባታቸዉን በግልግል ዳኛ ከመፍታት በስተቀር ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለዉም በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የቀረበውን ይግባኝ ውድቅ በማድረግ የሥር ትዕዛዝ በማጽናት ወስኗል። የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ።

የአሁን አመልካች ግንቦት 16 ቀን 2010 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ የአሁን ተጠሪ ባቀረበዉ ክርክር በተደረገዉ የቤት ኪራይ ዉል የቤቱን ኪራይ እንደከፈለ ከመከራከር ዉጪ ስለግልግል ዳኝነት በሁለቱም ወገኖች አልተነሳም። ስለግልግል ዳኝነት በግራ ቀኞችን ባልተነሳበት እና ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸዉ በፍ/ቤት መታየቱ ከማናቸዉም ወገን ተቃዉሞ ባልቀረበበት፣ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ደግሞ ተከራካሪ ወገኖች በዝርዝር ባላቀረቡት ወይም በግልጽ ባላመለከቱት ጉዳይ ላይ ፍርድ መስጠት እንደማይችሉ በሕግ በግልጽ ተደንግጎ እያለ የሥር ፍ/ቤቶች ጉዳዩ በግልግል ዳኝነት ከሚታይ በስተቀር ፍ/ቤቱ የማየት ስልጣን የለዉም በማለት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልን እና በክሳችን መሰረት እንዲወሰንልን፣ በዚህ ምክንያት የደረሰብን ኪሳራ እንዲወሰንልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል።

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በተደረገዉ ስምምነት አለመግባባት ቢፈጠር በእርቅ ወይም በግልግል ዳኛ ለመፍታት የተስማሙ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለዉም በማለት በራሱ ተነሳሽነት የሰጠዉ ዉሳኔ በሕጉ አግባብ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነጥብ ለመመርመር ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ያዘዘ ቢሆንም ተጠሪ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ ቢደረግለትም ባለመቅረቡ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት ይህን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል። እንደመረመርነዉ አመልካች እና ተጠሪ እ.ኤ.አ.ሚያዚያ 1 ቀን 2011 ዓ.ም የቤት ኪራይ ዉል ማድረጋቸዉ የተካደ አይደለም። የአሁን አመልካች ባቀረበዉ ክስ በዚህ ዉል መሰረት ተጠሪ ያልከፈለዉን የቤት ኪራይ ዋጋ እና ከዚህ ጋር ተያያዥነት ያለዉን ክፍያዎች ተጠሪ እንዲከፍል እንዲወሰንልኝ የሚል ነዉ። የአሁን ተጠሪ በበኩሉ በዉሉ መሰረት የሚፈለግበትን የኪራይ ክፍያ መክፈሉን እና ለአመልካች መክፈል ያለበት ክፍያ እንደሌለበት በመግለጽ ተከራክሯል። በግራ ቀኞቸዉ መካከል የተደረገዉ የቤት ኪራይ ዉል ሕግ መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1731 (1) እና የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2945 እና ተከታዮቹ

ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ። በመሆኑም ግራ ቀኞቸዉ በዉሉ የተመለከተዉን መብት የመጠየቅና የመጠቀም፣ ግዴታቸዉን ደግሞ የመወጣት ኃላፊነት አለባቸዉ።

በዚህ አግባብ በግራ ቀኞቸዉ መካከል አለመግባባት የተከሰተ እንደሆነ ዉሉ ምን ይላል? የሚለዉ ነጥብ መታየት ያለበት ጉዳይ ነዉ። የግራ ቀኞቸዉ የቤት ኪራይ ዉል አንቀጽ አምስት አለመግባባት የተከሰተ እንደሆነ አለመግባባቱ የሚፈታበትን አግባብ ይገልጻል። በዚህ መሰረት በግራ ቀኞቸዉ መካከል አለመግባባት የተከሰተ እንደሆነ በዉይይት ለመፍታት ጥረት ማድረግ እንደሚገባቸዉ፣ ይህ ካልሆነ ግራ ቀኞቸዉ አንድ አንድ ሽማግሌ በመምረጥ ለመስማማት ጥረት ያደርጋሉ፣ ልዩነቱ በዚህ መልክ የማያልቅ ከሆነ ግራ ቀኞቸዉ በየበኩላቸዉ ሽማግሌ በመምረጥ እና እንደ አስፈላጊነቱ የመሃል ዳኛ ተመርጦ በግልግል ዳኞች ጉዳያቸዉ ታይቶ እንደሚወሰን ያመለክታል። በዚህ አግባብ መስማማት ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.315 እና በፍ/ብ/ሕ/ቁ.3325 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት ተቀባይነት ያለዉ እንደሆነ ማየት ይቻላል። ይህ የዉል ድንጋጌ እንደሚያመለክተዉ ግራ ቀኞቸዉ ከቤት ኪራይ ዉሉ ጋር በተያያዘ አለመግባባት የተፈጠረ እንደሆነ ጉዳዩ በመደበኛ ፍ/ቤት ቀጥታ ክስ ቀርቦ የሚታይ ሳይሆን ግራ ቀኞቸዉ በተስማሙበት የሙግት መፍቻ ዘዴን ተከትሎ በግልግል ዳኝነት ጉባኤ መሆን እንዳለበት ነዉ፣ ይህም ደግሞ መጀመሪያ በስምምነት ካልሆነ በግልግል ዳኞች ታይቶ ዉሳኔ ሊሰጥበት የሚገባዉ ጉዳይ ነዉ። ይህ ማለት በመደበኛ ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ ቀጥታ ክስ የማይቀርብ መሆኑን ነዉ። ግራ ቀኞቸዉ ክርክሩን ለማየት ስልጣን ያለዉን አካል በስምምነተታቸዉ እስከወሰኑ ድረስ፣ ዉላቸዉን እስካላሻሻሉ ድረስ ይህን የዉል ድንጋጌ ተግባራዊ በማድረግ ጉዳዩ በግልግል ዳኞች እንዲታይ ከሚደረግ በቀር የመደበኛ ፍ/ቤት ስልጣን እንዳሌለዉ ግልጽ ነዉ። የአሁን አመልካች የቤት ኪራይ ዉሉን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ተጠሪ የኪራይ ክፍያ እንዲፈጽምለት ዳኝነት እስከጠየቀ ድረስ፣ አለመግባባትን ለመፍታት በዉሉ የተመለከተዉ ድንጋጌ ደግሞ አይመለከተኝም ተፈጻሚነት የለዉም በማለት ክፍል የዉሉን ድንጋጌ መቀበልና ክፍሉን አለመቀበል የሚቻልበት ሁኔታ የለም። ይህ ክስ በቤት ኪራይ ዉሉ መሰረት ያልተከፈለዉ የኪራይ ክፍያ እንዲፈጸም እና ቤቱን እንዲያስረክብ ዳኝነት የተጠየቀበት በመሆኑ፣ መታየትና ተፈጻሚ መደረግ ያለበት የዉሉ ክፍል ሳይሆን ሙሉ ይዘቱ መሆን አለበት።

በዚህ መሰረት የአሁን አመልካች ዉሉን መሰረት በማድረግ የቤት ኪራይ ዉል እንዲከፈለዉ ዳኝነት የጠየቀ በመሆኑ፣ የዉሉ ሙሉ ይዘት ሲታይ ዉሉ አለመግባባት እንዴት መፈታት

እንዳለበት የራሱን መፍቻ ዘዴ የዘረገ በመሆኑ በዛ አግባብ መታየት ይገባል። አመልካች የቤት ኪራይ ዉሉን እንደማስረጃ አያይዞ አቅርቦ እያለ የሥር ፍ/ቤት የኪራይ መጠን ወይም ተመን የሚመለከተዉን አንቀጽ እንጂ የሙግት አፈታት ዘዴ የሚመለከተዉ ድንጋጌ ማንሳት የለበትም በማለት የሚያቀርበዉ ክርክር ከፍ ሲል የተመለከተዉን ዉል በተዋዋይ ወገኖች መካከል ሕግ ነዉ የሚለዉን የህግ ድንጋጌ የሚቃረን ነዉ። በግራ ቀኞቸዉ መካከል የተደረገዉ የቤት ኪራይ ዉል ሕግ እስከሆነ ድረስ ፍ/ቤቱ ይህን ዉል መሰረት በማድረግ የቀረበዉን ክስ እልባት ለመስጠት የዉሉን ሙሉ ይዘት መፈተሹ አስፈላጊ በመሆኑ በግራ ቀኞቸዉ መካከል አለመግባባት ሲከሰት ምን መሆን እንዳለበት የተደረነገገዉን አንቀጽ ማየቱ ተገቢ ነዉ። ስለሆነም ግራ ቀኞቸዉ የቤት ኪራይ ዉሉን መሰረት በማድረግ እስከተከራከሩ ድረስ ስለግልግል የሚጠቅሰዉ የወሉ ድንጋጌ የማይታይበት ምክንያት የለም። ግራ ቀኞቸዉ በዚህ ረገድ ጉዳያችን በፍ/ቤት ሳይሆን በግልግል ዳኝነት መታየት አለበት በማለት ያቀረቡት ክርክር ባይኖርም የዉሉ አንቀጽ ይኼንን እስካመለከተ ድረስ ፍ/ቤቱ በራሱ ጊዜ የማያነሳበት ምክንያት የለም። ከዚህም በላይ ግራ ቀኛዉ ክርክራቸዉን የሚያይ አካል ስልጣን የወሰኑ በመሆናቸዉ፣ ይህ ደግሞ የስረ ነገር ስልጣን የሚመለከት በመሆኑ፣ በዚህ ረገድ ተከራካሪ ወገኖች በያነሱትም ወይም የቀረበ መቃወሚያ ባይኖርም ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.9 (2)፣ 244 (2፣ ሀ) እና 245 (2) መሰረት በራሱ ተነሳሽነት በመንሳት ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ መስጠት ይገባዋል። በመሆኑም የሥር ፍ/ቤት በራሱ ተነሳሽነት ግራ ቀኞቸዉ መካከል ዉሉን መነሻ ያደረገ አለመግባባት ሲከሰት በግልግል ዳኝነት ከምፈቱት በስተቀር ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለዉም በማለት የሰጡት ዉሳኔ በሕጉ አግባብ ነዉ ብለናል።

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች ግራ ቀኞቸዉ አለመግባባትን በግልግል ዳኝነት ጉባኤ ለመፍታት በተስማሙት መሰረት ከሚታይ በስተቀር ፍ/ቤት ቀጥታ ክስ ተቀብሎ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለዉም በማለት የሰጡት ዉሳኔ በሕጉ አግባብ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት ስለማይቻል የሚከተለዉ ተወስኗል።

<u>ዉ ሳ ኔ</u>

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.202150 በ6/7/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ጸንቷል።

የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ።

ግራ ቀኞቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፌርማ አለበት

የሰ/መ/ቁጥር፡-171335

ህዳር 30 **ቀን** 2012 **ዓ.ም**

ዳኞች ፡- ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካቾች ፡- 1. **ሜሮል ኢንኮርፖሬትድ**

2. **አቶ እዮብ ንዱ ተሰማ**

ተጠሪ ፡- ስዊዲሽ ኢንተርናሽናል ሮድ ኮንሳልቲንግ ኤቢ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል።

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከግልግል ዳኝነት ስልጣን ጋር በተያያዘ የተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል በቀረበ አቤቱታ መነሻ የተደረገ ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረዉ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን አመልካቾች ከሳሾች የነበሩ ሲሆን የአሁን ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበረ።። ከግራ ቀኝ ክርክርና ከስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ መረዳት እንደቻልነዉ ተጠሪ ከኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ትራንዚት ፕሮጀክት ለመገንባት በአማካሪነት ከኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን ጋር በዋና አማካሪነት፣ከአመልካቾች ጋር ደግሞ በቀን 25/10/2004**ዓ/ም እና በቀን** 25/04/2006**ዓ/ም የንኡስ አማካሪነት ዉሎች መዋዋሉን፤ 2ኛ አመልካች የ1ኛ አመልካች ስራ አስኪያጅ እንደሆኑና 1ኛ አመልካች 2ኛ አመልካችን ወደ ኢትዮጵያ በመላክ በባቡር መንገድ እስፔሻሊስትና ሪዝደንት ኤንጂነርነት የማማከር ሙያ በፕሮጀክቱ ለማገልገል እና ተጠሪ**

በዉሎቹ ላይ የተመለከተዉን ክፍያ ለ2ኛ አመልካች ለመክፈል እንደተስማሙ፤ ተጠሪ በዉሎቹ መሰረት መክፈል የሚገባዉን ከአሰሪዬ ክፍያ ስላልተፈጸመልኝ ነዉ ሌላ ጊዜ ደግሞ ተቀንሶ ስለተከፈለኝ ነዉ በሚል እዳዉ መሆኑን ያመነዉን በድምሩ 121,723.69 የአሜሪካን ዶላር ወይም የኢትዮጵያ ምንዛሬዉን ብር 2,735,253.03 በዉሉ በተመለከተዉ የአመልካቾች የባንክ ሂሳብ ገቢ እንዲያደርግ ወይም እንዲከፍላቸዉ እንዲወሰንላቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ ለቀረበበት ክስ ባቀረበዉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከዉል የመነጨ ማንኛዉም አለመግባባት መጀመሪያ በስምምነት ለመፍታት ይህ ካልተቻለ በግልግል ታይቶ እንዲያልቅ በዉሉ አንቀ ጽ 9.1 ስር በግልጽ ስለተስማማን ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የመዳኘት ስልጣን የለዉም በሚል ተቃዉሟል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክርክር ሰምቶና መርምሮ በመ/ቁጥር 199042 ላይ በቀን 18/11/2010 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ ግራ ቀኝ በዉላቸዉ ላይ ከዉሉ የሚመነጭ ማንኛዉም አለመግባባት በሽምግልና እንዲታይ በዉሉ ስለተስማሙ ይህ ስምምነታቸዉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1731 መሰረት የሕግ ያህል አስገዳጅነት ያለዉ በመሆኑ በዚህ መሰረት መስማማታቸዉ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ተቀብሎ እንዳይዳኝ መስማማታቸዉን ስለሚያሳይ እንዲሁም እንዲህ አይነት ስምምነት ከተደረገ መደበኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ተቀብሎ መዳኘት እንደሌለባቸዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 80722 ላይ አስገዳጅ ትርጉም መስጠቱን በመጥቀስ ፍርድ ቤቱ ጉዳዮን የመዳኘት የሥረ ነገር ሥልጣን የለዉም በሚል ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ችሎቱ በመ/ቁጥር 162876 ላይ በቀን 20/03/2011 ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ ይግባኙን በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዟል፡፡አመልካቾች በዚህ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል በቀን 14/06/2011 ዓ/ም ጽፈዉ ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት በአጭሩ ከዚህ የሚከተለዉ ነዉ፡፡

ተዋዋዮች የዉጭ አገር ህጎች ተፈጻሚ እንዲሆኑ መስማማታቸዉ፣ተዋዋዮች ኢትዮጵያዊ አለመሆናቸዉ፣ የመጀመሪያዉን ዉል በኢትዮጵያ ዉስጥ ለሚሰራ ሥራ ከኢትዮጵያ ዉጭ መፈራረማቸዉ፣ ለጉዳዩ አወሳሰን የሚገለግሉ ማስረጃዎች በኢትዮጵያ ዉስጥ መገኘታቸዉ፣ተጠሪ በኢትዮጵያ ዉስጥ የተመዘገበ ድርጅት መሆኑ ጉዳዩ ከኢትዮጵያ ጋር ከፍተኛ ግንኙት ያለዉ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ሊመለከት የሚገባዉ እንደ አገር ዉስጥ ጉዳይ (Domestic Matter) ሳይሆን የአለም አቀፍ የግለሰቦች ሕግ (Private

International Law Matter) መርህ መሰረት በማድረግ መሆን ሲገባዉ እንደ አገር ዉስጥ ጉዳይ በመመልከት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1731፣ 3307፣3345 እና በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 244 እና 315 ስር በኢትዮጵያ የዳኝነት ስልጣንና ሕግ ስር ስለተደረጉ የግልግል ስምምነቶች የተደነገገዉን እና በሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠዉን ትርጉም መሰረት በማድረግ ጉዳዩ የግለሰብ አለም አቀፍ ህግ ጥያቄን የሚያስነሳ ሆኖ እያለ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 11(2/ሀ) እና 5 የተሰጠዉን ስልጣን የሚያሳጣዉን ዉሳኔ መወሰኑ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 54121 ላይ የሰጠዉን አስገዳጅ ትርጉም ጭምር የሚቃረን በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት እንደሆነ፤

ዋናዉ ወል አለም አቀፍ ባህርይ ያለዉ እንደመሆኑ በዚህ ዉል ላይ ያለዉ የግልግል ስምምነት የጸና የግልግል ስምምነት ሊሆን የሚችለዉ (valid arbitration agreement) በግልጽ የግልግል ዳኝነቱ የሚታይበት ቦታ/አገር(Seat of Arbitration)፣ የግልግል ዳኝነቱን የሚመለከተዉ አካል፣የግልግል ጉባኤዉን ማን እና የትኛዉ ፍርድ ቤት እንደሚያቋቁም፣የዚህ አካል ሞያ (Profession)፣ የዳኞች ብዛት፣በግልግል ጉባኤዉ የሚሰጠዉን ዉሳኔ ለመቃወም ቅሬታ እንዴትና የት እንደሚቀርብ፣ጉባኤዉ የሚሰጠዉን ዉሳኔ(award) የት የሚገኘዉ ፍርድ ቤት ያስፈጽማል፣አፈጻጸሙን እንዴት መቃወም እና ቅሬታ ማቅረብ ይቻላል የሚሉ መሰረታዊ የጸና የግልግል ስምምነት ጉዳዮች በግልጽ ሲቀመጡ ሲሆን የግልግል ስምምነቱ እነዚህን ዝርዝሮች የማያሟላ ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤት ገዳዩን እንደተለመደዉ የአገር ዉስጥ ጉዳይ ተመልክቶ ከላይ የተመለከቱትን መሰረታዊ ጉዳዮች የግልግል ስምምነቱ የሚያሟላ መሆን አለመሆኑን ሳይመረምር የግልግል ስምምነቱን፣የኢትዮጵያን ህግና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ በመጥቀስ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የመዳኘት ስልጣን የለዉም ሲል መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት እንደሆነ፤

በዉሉ አንቀጽ 9.1 ስር በተመለከተዉ የግልግል ስምምኑ መሰረት ወደ ግልግል ዳኝነት ሊሄድ የሚችለዉ የዉሉን አተረጓጎም በተመለከተ አለመግባባት ካለ ለመሆኑ በአንቀጹ የመጀመሪያ ፓራግራፍ ለይ በግልጽ ተመልክቶ እያለ የስር ፍርድ ቤት ራሱን ችሎ የማይቆመዉን የአንቀጹን ሁለተኛ ፓራግራፍ ብቻ መሰረት በማድረግ ማንኛዉም ጉዳይ በግልግል ዳኝነት ይታያል ሲል የሰጠዉ ትርጉም በዉሉ አንቀጽ 9.1 ስር የተመለከተዉ ያላገናዘበና ክርክሩም የዉሉን አተረጓጎም የሚመለከት ሳይሆን በማስረጃ ተጣርቶ የሚወሰን በመሆኑ ለግልግል እንዲቀርብ የሚያስገድድ ክርክር ሳይኖር የስር ፍርድ ቤት በተሳሳተ ሁኔታ በመተርጎም ጉዳዩን

ማየት ያለበት የግልግል ጉባኤ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ የስረ ነገር ስልጣን የለውም ሲል መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነዉ ተብሎ እንዲታረምላቸዉ በመጠየቅ አቤቱታቸዉን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን መርምሮ ግራ ቀኙን ያከራከረዉ ነጥብ በግራ ቀኙ ስምምነት አንቀጽ 9/1 ስር እንደተመለከተዉ በግልግል ዳኝነት አማካኝነት እንጂ በፍርድ ቤት ሊዳኝ የሚችል ጉዳይ አይደለም ከሚል ትርጉም የሚያደርስ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነጥብ ይታይ ዘንድ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የሰጠዉን ትእዛዝ ተከትሎ ተጠሪ በቀን 29/08/2011 ዓ/ም የተጻፈ መልስ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱ በአጭሩ የሚከተለዉ ነዉ፡፡

አመልካች ዉሉ አይጸናም ያለዉ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሕግ የተሰጠዉን ዓለም አቀፍ የግለሰብ ሕግን የሚመለከቱ ጉዳዮችን በዉል ሊወሰድበት አይችልም ከሚል መነሻ ቢሆንም አመልካችና ተጠሪዎች ጉዳያቸዉ የሚታይበትን ስርዓት መምረጥ አይችሉም ተብሎ በሕግ እንዳልተከለከለ፤ አለም አቀፍ የግለሰብ ሕግን የሚመለከቱ ጉዳዮችን የመዳኘት ስልጣን የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስልጣን ቢሆንም ይህ ማለት ግን ማንኛዉም የግለሰብ ዓለም ዓቀፍ ሕግን የሚመለከቱ ጉዳይ በግዴታ በዚህ ፍርድ ቤት ብቻ መታየት አለበት ማለት እንዳልሆነ፤ ተዋዋይ ወገኖች በመዋዋል ነጻነታቸዉ ተጠቅመዉ ጉዳያቸዉን የሚዳኝላቸዉን አካል ከወሰኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩ ዓለም ዓቀፍ የግለሰብ ሕግን ይመለከታልና ማየት አለብኝ ለማለት የሚያስችለዉ የሕግ ስርዓት እንደሌለ፤ ጉዳዩ በግዴታ መታየት ያለበት በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ብቻ ነዉ የሚለዉ የአመልካቾች ክርክር የዜጎችን የመዋዋል ነጻነትና የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 3325-3346 የተደነገገዉን የሚጥስ እንደሆነ፤ አመልካች የጠቀሳቸዉ የሰበር ዉሳኔዎችም ዓለም አቀፍ የግለሰብ ሕግን የሚመለከቱ እንጂ ከግልግል ጉባኤ ስምምነት ጋር ተያይዞ የተሰጡ ዉሳኔዎች እንዳልሆኑ፤ በዉሉ አንቀጽ 9.1 ስር ከዉል በመነጨ ወይም ከዉሉ ጋር በተያያዘ በአማካሪዉ እና በንኡስ አማካሪዉ መካከል የሚነሳ ማናቸዉም አለመግባባት (ክርክር) በግልግል ጉባኤ ታይቶ እንደሚወሰን በግልጽ መስማማታቸዉን፤ክስ የቀረበበት ጉዳይም የዉሉን አንቀጽ መተርጎምን የሚጠይቅ ሆኖ እያለ ክርክሩ ዉልን መተርጎም የሚጠይቅ ባለመሆኑ የዉሉ አንቀጽ 9.1 ተፈጻሚነት የለዉም እንዲባል የቀረበዉ ክርክር ተገቢ እንዳልሆነ፤

እንዲሁም በአለም ዓቀፍ የንግድ ምክር ቤት የግልግል ደንብ መሰረት በአለም ዓቀፍ የግልግል ፍርድ ቤት በግልግል ጉባኤ እንዲታይ ስምምነት ስለተደረገ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1733 ስር በተደነገገዉ መሰረት ዉሉ በዚህ ልክ ግልጽ በሆነበት የተዋዋዮች ፈቃድ ምን እንደነበር

መተርጎም ስለሌለበት የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የመዳኘት ስልጣን የለኝም ማለቱ ተገቢ እንደሆነ፤ በግራ ቀኝ የዉል ስምምነት ላይ አለመግባባትን የመፍታት ስልጣን ለግልግል ጉባኤ ሲሰጥ ጉዳዩ በአለም አቀፍ የንግድ ምክር ቤት የግልግል ጉባኤ ደንብ (International Chamber of Commerce Rules of Arbitration) መሠረት የሚመራ መሆኑ በዉሉ ቁጥር 9.1 እና በአባሪ ቁጥር 1 ላይ በግልጽ የሰፈረ በመሆኑ አንድ ተዋዋይ ወገን ይህን ደንብ ለግልግል ጉባኤዉ ስነስርዓት መመሪያ እንደሚሆን በዉሉ ላይ ሲያሰፍር የዓለም ዓቀፍ የግልግል ዳኝነት ፍርድ ቤት (International Court of Arbitration) ጉዳዩን የማየት ስልጣን እንደተቀበለ እንደሚቆጠር በደንቡ አንቀጽ 6/2 ላይ በግልጽ ስላሰፈረ በዚህ ደንብ የዳኝነት ቦታዉ የዚሁ ጉባኤ ዋና መስሪያ ቤት በሚገኝበት ቦታ ሲሆን የባለሙያዎች አመዳደብም ሆነ የግልግል ዳኞች ቁጥር አወሳሰን ምን እንደሚመስል በግልጽ በደንቡ ዉስጥ ሰፍሮ ስለሚገኝ አመልካቾች ይህንን እያወቁ የግልግል ዳኝነት ስምምነቱ ጉድለት አለበት በማለት ፍርድ ቤቱ ዉሉን እንዲያሻሽልላቸዉ ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት የለዉም ተብሎ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ እንዲጸናለት በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡

አመልካቾች ተጠሪ ለሰጠዉ መልስ በቀን 14/09/2011ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የክርክሩ ይዘት ከዚህ በላይ የተመዘገበዉ ሲሆን እኛም ሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ያስቀርባል ብሎ ከያዘዉ ጭብጥ አንጻር ጉዳዩ በግልግል ዳኝነት አካል ሊታይ የሚገባ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚል ጭብጥ በመያዝ ከግራ ቀኝ ክርክር፣ በዉሉ ከተመለከተዉ የግልግል ዳኝነት ስምምነት፣ ከስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ እና አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

ጉዳዩን መርምረን እንደተረዳነዉም በጉዳዩ ላይ ተገቢዉን ዉሳኔ ለመስጠት ይረዳ ዘንድ በመጀመሪያ የግልግል ዳኝነት ምንነትና አቋቋም፣ የግልግል ዳኝነት ስምምነት መያዝ ያለበትን ነገሮች፣ በግልግል ዳኝነት ሊታዩ የሚገባቸዉና በግልግል ዳኝነት መታየት የማችይሉ ጉዳዮች ምንነት በአገራችንና በዓለም አቀፍ ደራጃ ተፈጻሚነት ካላቸዉ ሕጎች አንጻር መመርመር ያስፈልጋል፡፡

ሰዎች በመካከላቸዉ ከፈጠሩት ሕጋዊ ተግባራት (juridical acts) በመነጨ ወይም ከዚህ ጋር በተያያዘ ለወደፊት በመካከላቸዉ የሚፈጠረዉን አለመግባባት ወይም ተፈጥሮ ያለዉን አለመግባባት ከመደበኛ ፍርድ ቤት ዉጭ በግልግል ዳኝነት በኩል ለመፍታት የመዋዋል

ነጻነታቸዉን በመጠቀም መስማማት ይችላሉ፡፡ የግልግል ዳኝነት በስምምነት የሚቋቋመዉበት ዋነኛ ዓላማም ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት በመሄድ የሚያጠፉትን ጊዜ፣ ጉልበትና ገንዘብ ለመቀነስ እንዲሁም ክርክራቸዉ በመደበኛ ፍርድ ቤት በግልጽ ችሎት እየታየ ግላዊ የሆነ ጉዳያቸዉ (ምስጢራቸዉ) ወደአደባባይ እንዳይወጣ ለማድረግ ካላቸዉ ፍላጎት እንደሆነ ይታመናል፡፡

በዚህ መልኩ በጽሁፍ በተዋዋሉት በዋናዉ ዉላቸዉ የሚያደርጉት የግልግል ዳኝነት ስምምነት ቃል (Arbitration Clause) ተብሎ የሚታወቅ ሲሆን አስቀድሞ በመካከላቸዉ ተከስቶ ያለዉን አለመግባባት በግልግል ዳኝነት ለመፍታት ራሱን በቻለ የጽሁፍ ስምምነት የሚያደርጉት የግልግል ዳኝነት ስምምነት ደግሞ Submission

Agreement ተብሎ የሚታወቀዉ ነዉ፡፡ እነዚህ ሁለት አይነት ገጽታ ያላቸዉ አለመግባባትን በግልግል ዳኝነት ለመፍታት የሚደረጉ ስምምነቶች በጠቅላላዉ የግልግል ዳኝነት ስምምነት (Arbitration Agreement) ተብለዉ እንደሚታወቁ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 3325/1 እና 3328 እንዲሁም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 315 ስር የተደነገገዉን አጣምሮ በማንባብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ እንዲሁም በተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ ስር በሚገኝ የአለም አቀፍ የንግድ ሕግ ኮሚሽን (United Nations Commission on International Trade Law /UNCITRAL) አገራት እንደ ተምሳሌት ሕግ (Model Law) እንዲጠቀሙበት ባወጣዉ አንቀጽ 7 እና በዉጭ አገር የግልግል ዳኝነት አካል ታይቶ ለተወሰነ ዉሳኔ(Award) እዉቅና ለማሰጠት እና ለማስፈጸም እ.ኤ.አ በ1958 በወጣዉ የኒዉ ዮርክ ቃል ኪዳን (ይህንን ቃል ኪዳን አገራችን እስካሁን አለማጽደቋን ልብ ይሏል) አንቀጽ 2 ስር ለግልግል ዳኝነት ስምምነት (Arbitration Agreement) ተመሳሳይ ትርጉም መሰጠቱን መረዳት ይቻላል፡፡

በአገራችን በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 315 (2 እና 3) ስር እንደተደነገገዉ በግልግል ዳኝነት ሊዳኙ የማይችሉ ጉዳዮች ናቸዉ ተብሎ በሕግ በግልጽ ከተደነገገዉ እና ከአስተዳደር ዉሎች ጋር ከተያያዘዉ ዉጭ የሆኑ ሕጋዊ ተግባራትን መነሻ ያደረጉ አለመግባባቶች (Arbitrability) በግልግል ዳኝነት ታይተዉ እልባት እንዲያገኙ ለማድረግ ማናቸዉም ችሎታ ያላቸዉ ተዋዋይ ወገኖች የመዋዋል ነጻነታቸዉን በመጠቀም የግልግል ዳኝነት ስምምነት መዋዋል ይቻላሉ፡፡ በአለም አቀፍ የግልግል ዳኝነት ሕግጋት መሰረት (በሞዴል ሕግ አንቀጽ 1 ግርጌ ላይ የተመለከተዉ ትርጉም እና በኒዉ ዮርክ ቃል ኪዳን አንቀጽ 2.1 ስር እንደተመለከተዉ) ተዋዋዮች የመዋዋል ነጻነታቸዉን በመጠቀም በአገራዊ ሕግ (Domestic Law) በግልግል ዳኝነት ሊታዩ አይገባም ተብሎ ገደብ የተጣለባቸዉን ሳያካትቱ በግልግል ዳኝነት ሊታዩ የሚችሉ

ጉዳዮችን (በአብዛኛዉ ከንግድና ከኢንቨስትመንት ጋር የተያያዙትን) መነሻ ያደረጉ አለመግባባቶች በግልግል ዳኝነት ለመዳኘት ስምምነት ማድረግ ይችላሉ፡፡

በተጨማሪም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 3346 ስር በጥቅሉ እንደተገለጸዉና በዚህ ዙሪያ ከተጻፉት የህግ አስተያየቶች መረዳት እንደሚቻለዉ የግልግል ስምምነት ግልጽና በቀላሉ ተፈጻሚ መሆን እንዲችል እንደሁኔታዉ የሚከተሉትን ጉዳዮች የያዘ ሊሆን ይገባል፡፡ተዋዋዮች በስምምነታቸዉ የግልግል ዳኝነትን ሲመርጡ ጉዳያቸዉን የሚዳኝ ተቋማዊ ህልዉና የሌለዉ/የሌላቸዉ/ ገላጋይ ዳኛ/ዳኞች (Ad hoc Arbitration) በስምምነታቸዉ ላይ መምረጣቸዉን አለያም በተቋም ደረጃ የተደራጀ የግልግል ዳኝነት አካል (Institutional Arbitration /Administered Arbitration) በመምረጥ ጉዳያቸዉ ከሁለቱ በአንዱ አካል ታይቶ እልባት እንዲያገኝ መስማማታቸዉን ማሳየት አለባቸዉ፡፡ ተቋማዊ ህልዉና የሌለዉን ገላጋይ ዳኛ (Ad hoc Arbitration) ከመረጡ ገላጋይ ዳኛ መሰየም፣ ወይም ገላጋይ ዳኛዉ የሚሾምበትን መንገድ መግለጽ፣ የግልግል ዳኝነቱ የሚታይበትን ቦታ፣ የግልግል ዳኝነቱ የሚጠቀምበትን ቋንቋ፣ የግልግል ዳኝነቱ የሚመራበትን ስነ ስርዓት ሕግ፣ ለግልግል ዳኛዉ ስለሚከፈለዉ ገንዘብ...ወዘት አስቀድመዉ በስምምነታቸዉ ላይ እንዲገልጹ ይጠበቃል፡፡ በዚህ አግባብ በተለይም ገላጋይ ዳኛ በስምምነታቸዉ ላይ ካልሾሙ ወይም የሚሾምበትን መንገድ ካልገለጹ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 3331/3 እና በተከታዮቹ ድንጋጌዎች እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ከቁጥር 316-319 ስር በተደነገጉ ድንጋጌዎች መሰረት እንዲሁም በስምምነታቸዉ ላይ በሚመርጡት የግልግል ዳኝነት ደንብ መሰረት እንደሚወሰን ስርዓት ተዘርግቷል፡፡

በሌላ በኩል የመረጡት በተቋም ደረጃ የተደራጀ የግልግል ዳኝነት አካል (Institutional Arbitration /Administered Arbitration) ከሆነ ተዋዋዮች በስምምነታቸዉ ላይ ከላይ የተጠቀሱትን ዝርዝር ነገሮች እንዲገልጹ አይገደዱም፡፡ይህም ማለት ገላጋይ ዳኛ የሚሰየመዉ፣ ገላጋይ ዳኛ የሚሾምበት መንገድ ፣ የግልግል ዳኝነቱ የሚታይበት ቦታ፣ የግልግል ዳኝነቱ የሚጠቀምበት ቋንቋ፣ የግልግል ዳኝነቱ የሚመራበትን ስነ ስርዓት ሕግ፣ ለግልግል ዳኛዉ ስለሚከፈለዉ ገንዘብ...ወዘት በመረጡት ተቋም ደንብና አሰራር መሰረት ይወሰናል ማለት ነዉ፡፡

የግልግል ስምምነት እንደማንኛዉም የዉል ስምምነት ልዩ ባህሪዉን ባገናዘበ ሁኔታ በተለያዩ ምክንያቶች ከመነሻዉ ዋጋ አልባ(void) ወይም ፈራሽ (የማይጸና /invalid) ሊሆን ይችላል፡፡ እነዚህም ምክንያቶች የተዋዋዮች የመዋዋል ችሎታ ማጣት፣ የፈቃድ ጉድለት፣ ዓላማዉ የግብረ ገብነት ጉድለት ያለበት መሆን፣ ዓላመዉ ከሕግ ዉጭ ወይም ሕገወጥ መሆንን

(immoral, illegal and unlawful object) ፣ በህግ የተቀመጠለትን የአጻጻፍ ስርዓት ያልተከተለ(የፎርማሊቲ ጉድለት ያለበት) ከመሆን ጋር የሚያያዙ ናቸዉ።

በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 3330(1 እና 2) ስር ከግልግል ዳኝነት ስምምነት አተረጓጎም ጋር የተያያዘ ክርክር ቢነሳ አከራካሪዉ ነጥብ ላይ ዉሳኔ መስጠት እንዲችል በግልግል ስምምነቱ ላይ ለግልግል ዳኛዉ ስልጣን ሊሰጠዉ እንደሚችል እና በተለይ የራሱን ሥልጣን አስመልክቶ የሚነሱ ክርክሮች በራሱ እንዲወስን በግልግል ስምምነቱ ላይ ሊፈቀድለት እንደሚችል ተደንግጓል። ይህም ከላይ በተጠቀሰዉ ተምሳሌታዊ ሕግ (UNCITRAL Model Law እ.ኤ.አ በ1985 ወጥቶ በ2006 እንደተሻሻለዉ) አንቀጽ 16 ስር ከተደነገገዉና በዘመናዊዉ የግልግል ዳኝነት የህግ ዘርፍ The Rule of Competence-Competence ተብሎ ከሚታወቀዉ መርህ ጋር ከሞላ ጎደል የሚመሳሰል ነዉ። ይህ መርህ የግልግል ዳኛዉ የግልግል ዳኝነት ስምምነቱ ዋጋ ያለዉ መሆን አለመሆኑን (ፈራሽ ነዉ ተብሎ የሚቀርብ ክርክር /validity of arbitration agreement) በተመለከተ የሚነሳ ክርክር ጭምር ሰምቶ መወሰን እንዲችል ስልጣን የሚሰጠዉ ቢሆንም ይህ መርህ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 3330/3 ስር እንደተመለከተዉ በአገራችን በከፊል ተቀባይነት ባለማግኘቱ በዚህ ድንጋጌ መሰረት በአገራችን የግልግል ዳኛ የግልግል ዳኝነት ስምምነቱ ዋጋ የለዉም በሚል የሚነሳ ክርክር ሰምቶ በራሱ መወሰን እንዲችል ሥልጣን አልተሰጠዉም። ስለሆነም በአገራችን የግልግል ዳኝነት ስምምነት ዋጋ የለዉም በሚል የሚቀርብ ክርክር ሰምቶ የመወሰን ስልጣን ያለዉ ገላጋይ ዳኛዉ ወይም የግልግል ዳኝነት አካሉ ሳይሆን መደበኛ ፍርድ ቤት ነዉ።

ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመጣ ከላይ በዝርዝር እንደተመለከተዉ ግራ ቀኙን ያከራከረዉ ጉዳይ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ጉዳይ የመዳኘት ስልጣን ያለዉ መደበኛ ፍርድ ቤት ነዉ ወይስ የግልግል ዳኝነት አካል ነዉ የሚለዉ ነዉ። አመልካቾች በዉሉ የተመለከተዉ የግልግል ዳኝነት ስምምነት የግልግል ዳኝነቱ የሚታይበት ቦታ/አገር(Seat of Arbitration)፣ የግልግል ዳኝነቱን የሚመለከተዉን አካል፣የግልግል ጉባኤዉን ማን እና የትኛዉ ፍርድ ቤት እንደሚያቋቁም፣የዚህ አካል ሞያ (Profession)፣ የዳኞች ብዛት፣በግልግል ጉባኤዉ የሚሰጠዉን ዉሳኔ ለመቃወም ቅሬታ እንዴትና የት እንደሚቀርብ፣ ጉባኤዉ የሚሰጠዉን ዉሳኔ(award) የት የሚገኘዉ ፍርድ ቤት ያስፈጽማል፣አፈጻጸሙን እንዴት መቃወም እና ቅሬታ ማቅረብ ይቻላል የሚሉ መሰረታዊ የጸና የግልግል ስምምነት ጉዳዮች በግልጽ ያልያዘ በመሆኑ የግልግል ስምምነቱ ከመጀመሪያዉ ፈራሽ እና ተፈጻሚነት የሌለዉ ነዉ በሚል ተከራክረዋል።

የስር ፍርድ ቤት መዝገብ አስቀርበን እንደተመለከትነዉ የግልግል ስምምነት የሚገኝበት ዋናዉ ዉል የተፈረመዉ በቀን 25/10/2004ዓ/ም (እ.ኤ.አ ጁላይ 12/2012) ሆኖ ዉሉ የተደረገዉም በአሁን ተጠሪና በአሁን 1ኛ አመልካች መካከል ሆኖ የአሁን ተጠሪ ከአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ትራንዚት(ቀባት) የምድር ባቡር ፕሮጀክት ለመገንባት ለፕሮጀክቱ ኢፒሲ ዉል በማድረግ የአሰሪዉ ተወካይ በመሆን የማማከር አግልግሎት ለመስጠት ዉል ማድረጉን ተከትሎ የአሁን 1ኛ አመልካች የማማከር ስራዉን እንዲሰራ የፈጸሙት ንኡስ የማማከር አገልግሎት ዉል ነዉ፡፡ ይህ ዉል በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተዘጋጀ ሲሆን በዚህ ዉል በአንቀጽ 9 ስር ስለግልግል ዳኝነት የሚከተለዉን ስምምነት አድርገዋል፡-

9. ARBITRATION

9.1. ARBITRATION PROCEDURES

The parties shall make every attempt to resolve in an amicable way any dispute concerning the interpretation of this agreement.

Any dispute arising between the consultant and the Sub-Consultant in connection with or arising out of this agreement, which can not be resolved between them in accordance with the terms of this Agreement, shall be finally settled by arbitration in accordance with the rules stated in schedule 1.

Sechedule 1 Project and Agreement Particulars

Clause 9. ARBITRATION - Clause 9.1 ARBITRATION

Any arbitration proceedings in accordance with clause 9.1 shall be in accordance with the rules of the International Chambers of Commerce. የእነዚህ ድንጋጌዎች የአማርኛ ትርጉሞ የሚከተለዉ ነዉ፡-

9. የግልግል ዳኝነት - 9.1 የግልግል አካሄድ

የዚህ ስምምነት አተረጓጎም በተመለከተ ማንኛዉም አለመግባባት ቢኖር ተዋዋይ ወገኖች በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ሁሉንም ጥረቶች ያደርጋሉ፡፡

ከዚህ ስምምነት ጋር በተያያዘ ወይም በተነሳ በአማካሪዉና በንኡስ አማካሪዉ መካከል የተከሰተ ማንኛዉም አለመግባባት በዚህ ስምምነት በተመለከተዉ መሰረት በተዋዋይ ወገኖች መፈታት

ካልቻለ በመጨረሻም በዚህ ውል ሰንጠረዥ 1 ስር በተመለከተዉ ደንብ መሰረት በግልግል ዳኝነት እልባት እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

ሰንጠረዥ 1 ፕሮጀክትና የስምምነቱ ዋና ጉዳዮች

አንቀጽ (Clause) 9. የግልግል ዳኝነት Clause -አንቀጽ (Clause) 9.1 የግልግል ዳኝነት

ማንኛዉም በአንቀጽ 9.1 መሰረት የሚከናወን የግልግል ዳኝነት አካሄድ በዓለም ዓቀፉ የንግድ ምክር ቤት ደንብ መሰረት እንዲከናወን ይደረጋል የሚል ነዉ፡፡

ከላይ በተመለከተዉ መሰረት 1ኛ አመልካች እና ተጠሪ ባደረጉት ስምምነት መሰረት የስምምነታቸዉን አተረጓጎም በተመለከተ የሚነሳ አለመግባባት በራሳቸዉ በመነጋገር ለመፍታት እንዲሁም ከዚህ ስምምነት ጋር በተያያዘ ወይም በተነሳ ማንኛዉንም አለመግባባት ቢከሰትና ሁለቱም ወገኖች በመነጋጋር መፍታት ካልቻሉ በግልግል ዳኝነት እልባት እንዲያገኝ ለማድረግ ተስማምተዋል፡፡ ሆኖም የመረጡት የግልግል ዳኝነት ተቋማዊ ህልዉና ከሌለዉ ገላጋይ ዳኛ (Ad hoc Arbitration) እና በተቋም ደረጃ ከተደራጀ የግልግል ዳኝነት አካል (Institutional Arbitration /Administered Arbitration) የትኛዉን እንደመረጡ በግልግል ስምምነታቸዉ(Arbitration Clause) ላይ ስም በመጥቀስ በግልጽ አላመለከቱም፡፡ ከላይ እንደተመለከተዉ ተቋማዊ ህልዉና የሌለዉ ገላጋይ ዳኛ ሲመረጥና በተቋም ደረጃ የተደራጀ የግልግል ዳኝነት አካል ሲመረጥ የግልግል ዳኝነት ስምምነት ይዘት መሰረታዊ ልዩነት አለዉ፡፡ ከዚህ አንጻር ግራ ቀኝ ስለግልግል ዳኝነት ከላይ በተመለከተዉ መሰረት የተስማሙት ምን ያመላክታል የሚለዉን እንደመረመርነዉ በዉሉ ሰንጠረዥ 1 ስር ባለዉ አንቀጽ 9.1 ስር "ማንኛዉም በአንቀጽ 9.1 መሰረት የሚከናወን የግልግል ዳኝነት አካሄድ በዓለም ዓቀፉ የንግድ ምክር ቤት ደንብ መሰረት እንዲከናወን ይደረጋል፡፡" በሚል የተገለጸዉን ማጤን ጠቃሚ ይሆናል፡፡

ተሻሽሎ ከየካቲት 22 ቀን 2009 ዓ/ም (እ.ኤ.አ. ከማርቻ 01 ቀን 2017) ጀምሮ ተፈጻሚ በሆነዉ በዓለም ዓቀፉ የንግድ ምክር ቤት የግልግል ዳኝነት ደንብ (International Chamber of Commerce (ICC) Arbitration Rules) አንቀጽ 6/2 ስር የሚከተለዉ ተደንግጎ ይገኛል፡፡

ARTICLE 6- Effect of the Arbitration Agreement

2. By agreeing to arbitration under the Rules, the parties have accepted that the arbitration shall be administered by the court. ይህም ወደ አማርኛ ሲለወጥ ፡- ተዋዋይ

ወገኖች የግልግል ዳኝነቱ በዚህ ደንብ መሰረት እንዲከናወን ሲስማሙ የግልግል ዳኝነቱ በዓለም አቀፉ የንግድ ምክር ቤት ስር በሚገኘዉ ነጻ በሆነዉ የዓለም ዓቀፍ የግልግል ፍርድ ቤት (The International Court of Arbitration of the International Chamber of Commerce) እንዲመራ(እንዲተዳደር) እንደፈቀዱ ይቆጠራል እንደማለት ነዉ፡፡

ይህ የደንቡ ድንጋጌ ከላይ ከተጠቀሰዉ የዉሉ ሰንጠረዥ 1 አንቀጽ 9.1 ድንጋጌ ጋር ተጣምሮ ሲነበብ ግራ ቀኝ በግልግል ስምምነታቸዉ የመረጡት አማራጭ ተቋማዊ ህልዉና የሌለዉ ገላጋይ ዳኛ (Ad hoc Arbitration) ሳይሆን በተቋም ደረጃ የተደራጀ የግልግል ዳኝነት አካል (Institutional Arbitration /Administered Arbitration) መሆኑን የሚያሳ ነዉ፡፡ ይህም አካል በዓለም ዓቀፍ የግልግል ዳኝነት ፍርድ ቤት (The International Court of Arbitration of the International Chamber of Commerce) አደራጅነት (አስተዳዳሪነት) በዚህ ተቋም የግልግል ዳኝነት ደንብ በተለይም በአንቀጽ 12 እና 13 በተደነገገዉ መሰረት የሚሰየም/የሚሾም/ ገላጋይ ዳኛ/ዳኞች ይዞ የሚቋቋም የግልግል ዳኝነት አካል(Arbitral Tribunal) ነዉ፡፡

የገላጋይ ዳኞች አሰያየም(አሿሿም) እና ብዛታቸዉ(Nomination/Appointment and number/s of Arbitrator/s) ፣ የግልግል ዳኝነት አካሉ መቀመጫ(Place of the Arbitration)፣ የግልግል ዳኝነቱ የሚመራበት ደንብ (Rules Governing the Proceedings)፣ የግልግል ዳኝነቱ የሚከናወንበት ቋንቋ(Language of the Arbitration) ፣ፍሬ ነገሩ ላይ ተፈጻሚነት ስለሚኖረዉ ሕግ (Applicable Rules of law) እና የመሳሳሉትን ጉዳዮች በተመለተ በግራ ቀኝ በተፈጸመ የግልግል ዳኝነት ስምምነት ላይ በግለጽ ስምምነት ተደርጎ ባይገለጽም ግራ ቀኝ በስምምነታቸዉ ላይ ተጠቃሹ የግልግል ዳኝነት ደንብ ተፈጻሚ እንዲሆን እስከተስማሙ ድረስ እነዚህ ጉዳዮች የሚወሰኑት በደንቡ አንቀጽ 12፣13 እና 18-21 በዝርዝር በተመለከተዉ መሰረት በግልግል ዳኝነት ፍርድ ቤት መሆኑን ከደንቡ ይዘት መረዳት ችለናል፡፡

ስለሆነም አመልካቾች እነዚህ ጉዳዮች በግልግል ዳኝነት ስምምነቱ ላይ ባለመጠቀሳቸዉ ምክንያት የግልግል ዳኝነት ስምምነቱ ፈራሽ ነዉ በሚል ያቀረቡት ክርክር በዉላቸዉ ሰንጠረዥ 1 ስር ባለዉ አንቀጽ 9.1 ስር "ማንኛዉም በአንቀጽ 9.1 መሰረት የሚከናወን የግልግል ዳኝነት አካሄድ በዓለም ዓቀፉ የንግድ ምክር ቤት ደንብ መሰረት ይከናወናል" በሚል የተስማሙትንና የዚህን ደንብ አንቀጽ 6/2ን ያላገናዘበ ክርክር መሆኑን አረጋግጠናል፡፡ ይህም ክርክር የግልግል ዳኝነት ስምምነቱ ዋጋ የለዉም (ፈራሽ) ነዉ በሚል የቀረበ በመሆኑና እንዲህ አይነት ክርክር በግልግል ዳኝነት አካሉ ታይቶ እንዲወሰን የሚፈቅደዉ The rule of Competence-

Competence ተብሎ የሚታወቀዉ መርህ በአገራችን በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 3330/3 ስር እንደተመለከተዉ እዉቅና ስለሌለዉ የግልግል ዳኝነት ስምምነቱ ፈራሽ ነዉ ተብሎ የቀረበዉ ክርክር /validity of arbitration agreement) ሊወሰን የሚገባዉ በመደበኛ ፍርድ ቤት በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ከዚህ አንጻር የቀረበዉን ክርክር ሰምቶ ተንትኖ ባይወስንም የግልግል ዳኝነት ስምምነቱ ፈራሽ እንዳልሆነ በመቁጠር የደረሰበት ድምዳሜ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም።

በተጨማሪም አመልካቾች ለክሱ መነሻ የሆነዉን ጉዳይ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግን (private international law) የሚመለከት በመሆኑ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 11(2/ሀ) መሰረት ጉዳዩን መዳኘት ያለበት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነዉ በሚል ተከራክረዋል። ተጠሪ በበኩሉ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ አለመግባባት ቢፈጠር በግልግል ዳኝነት ታይቶ እልባት እንዲያገኝ ስለተስማማንና እንዲህ አይነት ስምምነት እንዳናደርግ የሚከለክል ሕግ ስለሌለ ጉዳዩ መታየት ያለበት በግልግል ዳኝነት አካል እንጂ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግን እንደሚመለከት ጉዳይ ተቆጥሮ ጉዳዩን መዳኘት ያለበት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነዉ ሊባል አይገባም ሲል ተከራክሯል።

ከዚህ አንጻር የቀረበዉም ክርክር እንደተመረመረዉ በግልግል ዳኝነት ሊታዩ የሚችሉ ጉዳዮችን (Arbitrability) በሚመለከት በአገራችን በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 315 (2 እና 3) ስር እንደተደነገገዉ በግልግል ዳኝነት ሊዳኙ የማይችሉ ጉዳዮች ናቸዉ ተብሎ በሕግ በግልጽ ከተደነገገዉ እና ከአስተዳደር ዉሎች ጋር ከተያያዘዉ ዉጭ የሆኑ ሕጋዊ ተግባራትን መነሻ ያደረጉ አለመግባባቶች በግልግል ዳኝነት ታይተዉ እልባት እንዲያገኙ ለማድረግ ማናቸዉም ችሎታ ያላቸዉ ተዋዋይ ወገኖች የመዋዋል ነጻነታቸዉን በመጠቀም የግልግል ዳኝነት ስምምነት መዋዋል እንደሚችሉ በግልጽ ተደንግጓል። በአገራችን የዉል ሕግ መሰረት የሕጉን አግባብ ተከትለዉ የተቋቋሙ ዉሎች በቋቋሚቸዉ ሰዎች ላይ መብትና ግዴታን ስለሚጥሉ እንደ ሕግ ያህል ተፈጻሚነት እንዳላቸዉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1731/1 ስር ተደንግጓል። እንዲሁም ተዋዋይ ወገኖች ሕግ ከወሰናቸዉና ከከለከላቸዉ ነገሮች በቀር የሚዋዋሉበትን ጉዳይ እንደመሰላቸዉ የመወሰን መብት እንዳላቸዉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1711 ስር በግልጽ ተደንግጓል።

በተያዘዉ ጉዳይ ላይ በ1ኛ አመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገዉ የግልግል ስምምነት ከማማከር ንኡስ ዉሉ የሚነጭ እና ከማማከር ዉሉ ጋር የተያያዘ የስምምነት አተረጓጎም መነሻ ያደረገ አለመግባባት(ክርክር) ጭምር በግልግል ዳኝነት እንዲታይና እልባት እንዲያገኝ

ስምምነት እንዳደረጉ የዉሉ አንቀጽ 9.1 በግልጽ ያሳያል፡፡ ምንም አንኳን የግለሰብ ዓለም ዓቀፍ ሕግ ጉዳይ የሚመለከቱ ክርክሮችን ተቀብሎ በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣን እንዲዳኝ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 11(2/ሀ) መሰረት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሰልጣን የተሰጠዉ ቢሆንም የግለሰብ ዓለም ዓቀፍ ሕግ ጉዳይ የሚመለከቱ ክርክሮች በግልግል ዳኝነት ሊታዩ አይገባም ተብሎ በአገራችን ሕጎች የተጣለ ክልከላ የለም፡፡ ክስ የቀረበበት ጉዳይም ከአስተዳደር ዉል ጋር የተያያዘ ባለመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 315/2 ስር የተመለከተዉ ክልከላ ለዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነነት ያለዉ አይደለም፡፡ ስለሆነም አመልካቾች ጉዳዩ የግለሰብ ዓለም ዓቀፍ ሕግን የሚመለከት በመሆኑ በግልግል ዳኝነት ሊታይ አይገባም በሚል ያቀረቡት ክርክር የሕግ መሰረት ያለዉ ባለመሆኑ አልተቀበልንም፡፡

ሲጠቃለል የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግልግል ዳኝነት ስምምነቱን መሰረት በማድረግ ጉዳዩን የመዳኘት ስልጣን የለኝም ሲል በመወሰኑና ይህንን ዉሳኔ በመቃወም አመልካቾች ያቀረቡትን ይግባኝ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በትእዛዝ በመሰረዙ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ዉ ሳ ኔ</u>

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 199042 ላይ በቀን 18/11/2010 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 162876 ላይ በቀን 27/02/2011 ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ጸንቷል፡፡

ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ደረጃ ያወጡትን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

የዚህ የፍርድ ዉሳኔ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡
ዉሳኔዉ ይታተም ዘንድ ለሚመለከተዉ የፍርድ ቤቱ ክፍል ይተላለፍ፡፡
በትእዛዝ የቀረበዉ መዝገብ ይመለስ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ዮ/መ

የሰ.መ.ቁ.138405

ጥቅምት 20 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡...1. ዳኜ መላኩ

2. ተፈሪ ገብሩ

3. ቀነዓ ቂጣታ

4. ተሾመ ሽፈራዉ

5. ፀሐይ መንክር

አመልካች፡-.....የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሞጆ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

ተጠሪዎች፡-.....1. ዳሽን ባንክ አ.ማ

2. ኤ.አይ.ኤል.ኤፍ.ኤ. ጠቅላላ ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

ጣልቃ ገብ፡-.....የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን

ይህ መዝገብ የተቀጠረዉ ለምርመራ ሲሆን ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍርድ</u>

ይህ የሰበር ጉዳይ የአፈጻጸም ክርክር የሚመለከት ሲሆን ለችሎቱ ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.50115 በ22/6/2009 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበዉን አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡

የጉዳዩ መነሻ ሲታይ በኦሮሚያ ክልል በሉሜ ወረዳ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች አመልካች፣ የአሁን 1ኛ ተጠሪ የፍ/ባለመብት እና የአሁን 2ኛ ተጠሪ የፍርድ ባለዕዳ እንደነበሩ የሥር ዉሳኔ ያሳያል፡፡ የሥር ወረዳ ፍ/ቤት በፍ/ባለመብት እና በፍ/ባለዕዳ መካከል የነበረዉን የአፈጻጸም ክርክር በመመርመር በሰጠዉ ትዕዛዝ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሞጆ ቅርጫፍ ጽ/ቤት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የፍርድ ባለዕዳ ንብረት ላይ የሰጠዉ የእግድ ትዕዛዝ እያለ ትዕዛዙ ሳይነሳ ለፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ተወስኗል በሚል ምክንያት ንብረቱን በጨረታ የሸጠ ስለሆነ ኃላፊነት ስላለበት የፍ/ባለዕዳዉ ንብረት ከተሸጠበት ገንዘብ ብር 396,893.37 ወጪ በማድረግ ለፍ/ባለመብት እንዲከፍል በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የአሁን

አመልካች ይህን ትዕዛዝ በመቃወም አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ አመልካች አቤቱታዉን ማቅረብ የነበረበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.418 መሰረት ሆኖ ሳለ በዚህ አግባብ ስላላቀረበ ተቀባይነት የለዉም በቀደመዉ ትዕዛዝ መሰረት ፈጽሞ እንዲቀርብ አሏል፡፡ የአሁን አመልካች ይህን ትዕዛዝ በመቃወም ይግባኝ ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ይግባኙን ዉድቅ በማድረግ የስር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ ለማሳራም ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ27/6/2009 ዓ.ም የተጻፈ ሶስት ገጽ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአቤቱታዉ ይዘት በአጭሩ፡--ለፍርድ አፈጻጸም እንዲዉል የታዘዙት ዕቃዎች የፍ/ባለዕዳ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ንብረት ሳይሆን የአልፋ ጠቅላላ የንግድ ማህበር ሆኖ ሳለ፣ የአሁን አመልካች የክርክሩ አካል ሳይሆን ሳይከሰስ እና ሳይከራከር ጥፋተኛ ነዉ ተብሎ ለደረሰዉ ጉዳት ኃላፊ ነዉ የተባለበት አግባብ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረምልን ይገባል፡፡ እነዚህ ንብረቶች ደግሞ የፖሊስ የደንብ ልብስ በመሆናቸዉ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ለፍርድ ማስፈጸሚያ ሊይዛቸዉ እንደማይችል ዉሳኔ ተሰጥቶበታል፡፡ ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ እንዲታረምልን በማለት በዝርዝር አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣የሥር ፍ/ቤት በጨረታ የተሸጠዉ ንብረት የፍ/ባለዕዳ ንብረት ስለመሆኑ ባልተጣራበት በዉሳኔ የተመለከተዉን ገንዘብ ለ1ኛ ተጠሪ እንዲከፍል የመወሰኑን አግባብነት፣ ለመመርመር ሲባል አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ ትዕዛዝ በሰጠዉ መሰረት 1ኛ ተጠሪ ሚያዚያ 30 ቀን 2009 ዓ.ም የተጻፈ አምስት ገጽ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡--የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔዎች መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመባቸዉ አመልካች ያቀረበዉ አቤቱታ የፍሬ ነገርና የማስረጃ ምዘና ጉዳይ ስለሆነ ዉድቅ ሆኖ የሥር ዉሳኔ እንዲጸናልን አመልካች ያካሄደዉ ጨረታ ተሰርዞ ካፖርቶቹ እንደገና ተሸጠዉ ለፍርድ ማስፈጸሚያነት እንዲዉሉልን እንዲወሰንልን በማለት አመልክቷል፡፡ የአሁን አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡ የአሁን 2ኛ ተጠሪ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ ቢደረግለትም ባለመቅረቡ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የአሁን ጣልቃ ገብ በ22/7/2009 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ በጣልቃ ገብ እና በ2ኛ ተጠሪ ድርጅት መካከል በተደረገዉ ዉል መሰረት 8,000 የፖሊስ አባላት ካፖርቶች ለማቅረብ ባለመቻላቸዉ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ መስረተን ዉሳኔ ተሰጥቶን በአፈጻጸም ላይ እያለን የአሁን 1ኛ ተጠሪ መብት አለኝ በማለት በአፈጻጸም ላይ ክርክር አቅርቦ አቤቱታዉ

ውድቅ ተደረጓል፡፡ ስለዚህ በእነዚህ ካፖርቶች ላይ መብት ያለን ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.41 መሰረት ወደ ክርክሩ ገብተን እንዲጎከራከር በማለት አመልክቷል፡፡ በዚህ አቤቱታ ላይ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ግንቦት 17 ቀን 2009 ዓ.ም በተጻፈ መልስ ጣልቃ ገብ ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ውድቅ እንዲደረግን በማለት በዝርዝር መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ደግሞ በ1/10/2009 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የአሁን 2ኛ ተጠሪ በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎለት ስላልቀረበ አስተያየት የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙቸዉን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉ በዚህ ጉዳይ እልባት ማግኘት ያለበት ጉዳይ የሉሜ ወረዳ ፍ/ቤት በተሰጠዉ በፍርድ አፈጻጸም የወክልና ስልጣን የሰጠዉን ትዕዛዝ የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ የማየት ስልጣን አለዉ ወይስ የለውም? የአሁን ጣልቃ ገብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.41 መሰረት ያቀረበዉ አቤቱታ በዚህ ችሎት ሊስተናገድ የሚችል ነዉ ወይስ አይደለም? የሚሉትን ነጥቦች እንደጭብጥ በመያዝ መርምሮታል፡፡

በዚህ መሰረት የመጀመሪያዉ ጭብጥ በተመለከተ በ1ኛ ተጠሪ እና በ2ኛ ተጠሪ መካከል በነበረዉ የፍትሓ ብሔር ክርክር የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን 2ኛ ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ ገንዘብ እንዲከፍል ዉሳኔ በመስጠት፣ ፍርዱን ለማስፈጸም ደግሞ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.372 /1/ በሚደነግገዉ መሰረት የፍ/ባለዕዳ ንብረት በአመልካች ጽ/ቤት ዘንድ ታግዶ ይገኛል በሚል ምክንያት የሉሜ ወረዳ ፍ/ቤት እንደፍርዱ እንዲያስፈጽም ያስተላለፈለት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍርድ አፈጻጸም የሉሜ ወረዳ ፍ/ቤትን በመወከሉ የወረዳዉ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ ለማየት ስልጣን ማግኘቱን ማየት ተችሏል፡፡ ስለሆነም በዚህ አግባብ የተወከለዉ የወረዳዉ ፍ/ቤት ያለዉ ስልጣን ምን እንደሆነ ማየቱ አስፈላጊ ነዉ፡፡ በዚህ ረገድ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.374 /1/ እንደሚደነግገዉ ፍርድ አስፈጻሚዉ ፍ/ቤት ስለፍርድ አፈጻጸም የሚሰጠዉ ትዕዛዝና በትዕዛዙም ላይ ይግባኝ ስለሚባልበት ሁኔታ ያለዉ ስልጣን ዋናዉን ፍርድ ከወሰነዉ ፍ/ቤት ሥልጣን ጋር እኩል ሆኖ ይቆጠራል በማለት ደንግጓታል፡፡ በመሆኑም የሉሜ ወረዳ ፍ/ቤት ይህን የአፈጻጸም ክርክር በተመለከተ የሚሰጠዉ ትዕዛዝና በትዕዛዙም ላይ ይግባኝ ስለሚባልበት ሁኔታ ልክ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እንደሰጠዉ ይቆጠራል ማለት ነዉ፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የሉሜ ወረዳ ፍ/ቤት በፍርድ አፈጻጸም የተሰጠዉን ወክልና መሰረት በማድረግ በሰጠዉ ትዕዛዝ ላይ የአሁን አመልካች ይግባኝ ማቅረብ ያለበት

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠዉን ትዕዛዝ በይግባኝ አይቶ ለማረም ስልጣን ወደአለዉ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት የአሁን አመልካች ያቀረበዉን አቤቱታ የሉሜ ወረዳ ፍ/ቤት ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉን ትዕዛዝ በመቃወም ይግባኝ ማቅረብ የነበረበት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ነዉ እንጂ ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አይደለም፡፡ የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ በይግባኝ የማየት ስልጣን የለዉም፡፡ በዚህ ምክንያት የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ በይግባኝ የማየት ስልጣን ሳይኖራዉ አመልካች ያቀረበዉን ይግባኝ በመቀበል የሥር ዉሳኔ በማጽናት የሰጠዉ ትዕዛዝ ከስልጣኑ ዉጭ የተሰጠ ትዕዛዝ ስለሆነ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ብለናል፡፡ የአሁን አመልካች ከፈለገ የሉሜ ወረዳ ፍ/ቤት የሰጠዉን ትዕዛዝ በተመለከተ ይግባኙን ሥልጣን ላለዉ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ማቅረብ ይችላል ብለናል፡፡

ሁለተኛዉን ጭብጥ በተመለከተ የአሁን ጣልቃ ገብ ለክርክር መነሻ በሆኑት የፖሊስ አባላት የደንብ ልብስ ላይ የፍ/ባለዕዳዉን ከሰን ዉሳኔ ተሰጥቶን በፍርድ አፈጻጸም ላይ እያለን የአሁን 1ኛ ተጠሪ መብት አለኝ በማለት አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታዉ ዉድቅ ተደርጎ ካፖርቶቹን እንዲንረከብ ዉሳኔ ስለተሰጠን ወደ ክርክሩ ገብተን እንዲንከራከር በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.41 መሰረት አቤቱታ አቅርቧል፡፡ በዚህ አቤቱታ ላይ የአሁን አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ የየራሳቸዉን መልስ አቅርቧል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.41 ድንጋጌ ይዘትና ዓላማ ሲታይ በሌሎች ተከራካሪ ወገኖች መካከል በሚደረግ ክርክር ወደ ክርክሩ ገብቸ ሳልከራከር ዉሳኔ የሚሰጥ ከሆነ መብቴ ይነካል የሚል ሶስተኛ ወገን ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት አቤቱታዉን ለፍ/ቤቱ ማቅረብ እንደሚችል ያመለክታል፡፡ የድንጋጌ ይዘትና ዓላማ ሲታይ የፍሬ ነገርና የማስረጃ ጉዳይ በዉስጡ ያዘለ ሁኖ እናገኛለን፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ይህ ችሎት በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት መሰረታዊ የሕግ ስህተት ከሚያርም በስተቀር ፍሬ ነገር የማጣራት እና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ስለሌለዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.41 መሰረት የሚቀርብ አቤቱታን ተቀብሎ ለማስተናገድ የሚያስችለዉ ስልጣን የሚያገኝበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ የአሁን ጣልቃ ገብ ደግሞ በግልጽ ከአቤቱታዉ ጋር አያይዞ ያቀረበዉ የተለያዩ ዉሳኔዎችን እንደሰነድ ማስረጃዎች በማድረግ እንደሆነ መገንዘብ ተችሏል፡፡ ስለሆነም ጣልቃ ገብ ያቀረበዉ አቤቱታ ተቀባይነት አለዉ ወይስ የለዉም? ለማለት እነዚህን የሰነድ ማስረጃዎች መመርመር አስፈላጊ ስለሚሆን ይህ ደግሞ የዚህ ችሎት ስልጣን ስር የሚወድቅ ጉዳይ አይሆንም፡፡ ይህ ጉዳይ በአፈጻጸም ደረጃ ላይ የሚገኝ እንደመሆኑ መጠን የአሁን ጣልቃ ገብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.41 በመጥቀስ አቤቱታ ያቀረበዉ ሲታይ አግባብነት ያለዉን የህግ ድንጋጌ

ከመጥቀስ አንጻር ለሚነሳ ጥያቄ ለጊዜው በማለፍ፣ አሁን ግን በአቤቱታው የተጠቀሰው ፍሬ ጉዳይና ተያይዞ ያቀረቡት የሰነድ ማስረጃዎችን ለመመርመር ከዚህ ችሎት ስልጣን ውጭ ስለሆነ ችሎቱ አቤቱታውን ለማስተናገድ የሕግ ስልጣን የለውም፡፡ ስለሆነም የአሁን ጣልቃ ገብ ከፊለገ አግባብነት ባለው የሕግ ድንጋጌ መሰረት ለሉሜ ወረዳ ፍ/ቤት አቤቱታውን ከሚያቀርብ በስተቀር ለዚህ ችሎት ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለን ወድቅ አደርገናል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት፣ የሉሜ ወረዳ ፍ/ቤት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው የፍርድ አፈጻጸም ዉክልና ስልጣን መሰረት የሰጠዉን ትዕዛዝ፣ በይግባኝ የማየት ስልጣን ሳይኖረዉ የሥር ትዕዛዝ በማጽናት የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲሁም ይህ ችሎት የአሁን ጣልቃ ገብ ያቀረበዉን አቤቱታ ለማየት ስልጣን የሌለዉ ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

የምስራቅ ሸዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.50115 በ22/6/2009 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ ከስልጣኑ ዉጭ የሰጠ ስለሆነ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ተሽሯል፡፡

የአሁን አመልካች የሉሜ ወረዳ ፍ/ቤት የሰጠዉ ትዕዛዝ ላይ ቅሬታ ያለዉ እንደሆነ ይግባኙን ስልጣን ላለዉ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ለማቅረብ ይችላል ብለናል፡፡

ይህ ችሎት የአሁን ጣልቃ ገብ ያቀረበዉን አቤቱታ የማየት ስልጣን የለዉም፤ ጣልቃ ገብ ከፊለገ አቤቱታዉን አግባብነት ባለዉ የሕግ ድንጋጌ መሰረት ለሉሜ ወረዳ ፍ/ቤት ለማቅረብ ይችላል ብለናል፡፡

የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ ብለናል፡፡

ግራ ቀኞቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

የሰ/መ/ቁ.181923

ቀን ፡- ግንቦት 26 ቀን 2012 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- የቡራዩ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ጽ/ቤት

ተጠሪ ፡- አቶ ከበደ አበበ

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከሥር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች በሥር ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽ ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪ በአመልካች፣ በሥር 2ኛ ተከሳሽ ዶ/ር ገሥጥ መታፈሪያ እና በሥር 3ኛ ተከሳሽ አቶ ወርቁ ገብረጻዲቅ ላይ ያቀረቡት ክስ በቡራዩ ከተማ በለኩ ከታ ቀበሌ የቤት ቁጥር 102 የሆነ ቤቴንና ንብረቴን አመልካች ከሥር 2ኛና 3ኛ ተከሳሾች ጋር በመሆን አፍርሶ ጉዳት ስላደረሰብኝ ካሣ ብር 288,000.00 እንዲከፍለኝ እና የሥር 2ኛና 3ኛ ተከሳሾች ይዞታውን እንዲለቁልኝ የሚል ነው፡፡ አመልካች ያቀረበው መልስ ተቋሙ ከመቋቋሙ በፊት ለተከናወነ ተግባር ኃላፊነት የለብኝም፡፡ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው፡፡ ተጠሪ የንብረቱ ባለቤት ስለመሆኑ ማስረጃ አላቀረቡም የሚል ነው፡፡ የሥር 3ኛ ተከሳሽ በበኩላቸው አመልካችና እኔ ኦሮሚያ ክልል ስለምንኖር እና ጉዳዩ ኦሮሚያ ክልል ስለተነሳ በፌደራል ፍርድ ቤት ጉዳዩ ሊዳኝ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውን በመመርመር የአመልካች፣ የተጠሪና የሥር 3ኛ ተከሳሽ አድራሻ ኦሮሚያ ክልል ቢሆንም የሥር 2ኛ ተከሳሽ መኖሪያ አድራሻ አዲስ አበባ ከተማ በመሆኑ በተለያዩ ክልል ነዋሪዎች መካከል የሚደረግ

ክርክር የፌደራል ጉዳይ ስለሆነ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን አለው በማለት ሌሎች መቃወሚያዎችን በማለፍ አመልካች ተጠሪ ላይ ላደረሰው ጉዳት ብር 180,200.00 እንዲከፍልና ለተወሰደው ይዞታ ምትክ እንዲሰጥ ሲወስን የሥር 2ኛ ተከሳሽ ዶ/ር ገሥጥ መታፈሪያ እና የሥር 3ኛ ተከሳሽ አቶ ወርቁ ገብረጻዲቅ ላይ የቀረበውን ክስ ወድቅ አድርጓል። አመልካች ይግባኙን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ፍርድ ቤቱ ቅሬታውን ባለመቀበል ሠርዟል።

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው። የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም አመልካችና ተጠሪ የኦሮሚያ ክልል ነዋሪ ነን፤ ቤቱም የሚገኘው ኦሮሚያ ክልል ሆኖ እያለ ጉዳዩ በፌደራል ፍርድ ቤት መታየቱ ስህተት ነው። የኦሮሚያ ክልል ፍርድ ቤትም የፌደራል ጉዳዩን የማየት ውክልና አለው። የሥር ፍርድ ቤቶች ሥልጣን የላቸውም። በሊዝ ሕግ መሠረት ከይዞታዬ አፈናቀሉኝ ካሉ መደበኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ማየት አይችልም። አመልካች ተቋም ከመቋቋሙ በፊት ለተከናወነ ተግባር ኃላፊነት የለብኝም የሚል ነው። የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ የኦሮሚያ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በውክልና የማየት ሥልጣን እያለው በፌደራል ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ መታየቱ ሕጋዊነቱን ለማጣራት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ አዟል። ተጠሪ ያቀረቡት መልስ የተከራካሪዎች መኖሪያ አድራሻ ኦሮሚያ ክልል እና አዲስ አበባ ከተማ በመሆኑ ጉዳዩ የፌደራል ነው። ኦሮሚያ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በውክልና የማየት ሥልጣን ቢኖረውም አዲስ አበባ ከተማ የሚያስችል በመሆኑ ጉዳዩ በፌደራል ፍርድ ቤቶች መታየቱ ተገቢ ነው። በሊዝ ሳይሆን ገበሬ ማህበር እያለ ይገፍው የተጠናልኝ ይዞታ ነው። የማፈናቀል ተግባር ሳይሆን ከሕግ ውጭ ጉዳት ስላደረሱብኝ ነው በፍርድ ቤት ክስ ያቀረብኩት፤ የተሠጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ተብሎ ሊጸና ይገባል ብለዋል። አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሠበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል።

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩ በፌደራል ፍርድ ቤቶች መታየቱ ሕጋዊ መሆን አለመሆኑን? በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል።

እንደመረመርነው ተጠሪ በአመልካች፣ በሥር 2ኛ ተከሳሽ ዶ/ር ገሥጥ መታፈሪያ እና በሥር 3ኛ ተከሳሽ አቶ ወርቁ ገብረጻዲቅ ላይ ያቀረቡት ክስ በቡራዩ ከተማ በለኩ ከታ ቀበሌ የቤት ቁጥር 102 የሆነ ቤቴንና ንብረቴን አመልካች ከሥር 2ኛና 3ኛ ተከሳሾች ጋር በመሆን አፍርሶ ጉዳት ስላደረሰብኝ ካሣ ብር 288,000.00 እንዲከፍለኝ እና የሥር 2ኛና 3ኛ ተከሳሾች ይዞታውን እንዲለቁልኝ የሚል ነው። አሁን አከራካሪ ሆነው ክሱ የክልል ፍርድ ቤት በውክልና

ሊመለከተው የሚችል የፌደራል ጉዳይ ነው ወይስ በፌደራል ፍርድ ቤት የሚታይ ክርክር ነው የሚለውን የሚመለከት ነው።

በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 78(2) መሠረት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ2/3ኛ ድምጽ የፌደራል ከፍተኛ ሆነ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲደራጅ እስካልወሰነ ድረስ የፌደራል ከፍተኛና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን በውክልና ለክልል ፍርድ ቤቶች ተሰጥቷል። ምላሽ የሚያስፈልገው ጉዳይ በውክልና በተሠጠ ሥልጣን ላይ የፌደራል ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን የማየት ሥልጣን አላቸው ወይስ የላቸውም? ኦሮሚያ ክልል ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት አዲስ አበባ ከተማ ከፌደራል ፍርድ ቤት ማስቻያ ከተማ ላይ መገኘቱ በውክልና የተሠጠውን ሥልጣን ከመመልከት አኳያ ያለው ውጤት ምንድን ነው? የሚሉት ጉዳዮች ናቸው።

ክርክሩን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ሲሆን በዚህ ሂደት ከሚመረምራቸው ጉዳዮች መካከል ጉዳዩ ላይ ለመወሰን ሥልጣን ያለው መሆን አለመሆኑ ዋነኛው ነው። የፍርድ ቤት ሥልጣን ብሔራዊ የመዳኘት ሥልጣን (judicial jurisdiction)፣ የሥረ-ነገር ሥልጣን (material jurisdiction) እና የግዛት ወይም ከበባዊ ሥልጣን (local or territorial jurisdiction) በሚል የተከፋፈለ ነው። ብሔራዊ የመዳኘት ሥልጣን ከሀገሮች ሉዓላዊነት፣ የሚሠጠው ፍርድ በሌሎች ሀገሮች ዕውቅና ሊሠጠውና ሊፈጸም የሚችል መሆን አለመሆኑ እና ከተከሳሽ መብት ጋር የተያያዘ መሠረቱ ዓለምአቀፍ ሕግና የታወቁ የሕግ መርሆዎች ሆኖ የአንድ ሀገር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለመመልከት ከተከሳሹ ወይም የክርክሩ ምክንያት የሆነው ተግባር ከተፈጸመበት ወይም አከራካሪ የሆነው ንብረት ከሚገኝበት ቦታ ጋር በቂ የሆነ ግንኙነት ያለው ሆኖ ሲገኝ ወይም ተከሳሽ የሆነው ወገን በሀገሪቱ ፍርድ ቤቶች ለመዳኘት ያለው ፈቃድ ላይ መሠረት በማድረግ የሚወሰን ነው። የሥረ-ነገር ሥልጣን በአንድ ሀገር ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች መካከል በዋነኛነት ይሕ የሥልጣን ዓይነት ታሳቢ የሚያደርገው የፍርድ ቤቱን አቅም ወይም ችሎታ (competence of the court)፣ ፍትሐዊነትን፣ ኢኮኖሚንና የሥራና ሀብት ክፍፍልን መሠረት አድርጎ በገንዘብ ግምት (pecuniary jurisdiction) ወይም በጉዳዩ ዓይነት (subject matter jurisdiction) ወይም ጉዳዩን በመጀመሪያ ሆነ በይግባኝ ደረጃ (original and appellate jurisdiction) የሚያዩት ሥለመሆኑ በፍርድ ቤቶች መካከል የሚመለከቱት ጉዳዩችን የሥልጣን ድልድል የሚደረግበት ነው። የግዛት ክልል ሥልጣን ደግሞ አንድን ጉዳይ ተቀብሎ

ለመስማት እና ለመወሰን ዐቅም ካላቸው ፍርድ ቤቶች መካከል በየትኛው ፍርድ ቤት ቀርቦ መታየት እንዳለበት የሚያመለክት ነው። ያስፈለገበትም ዓላማም ተመሳሳይ የሥረ-ነገር ሥልጣን ያላቸው ግን በተለያዩ ማስቻያ ቦታ ላይ በሚያስችሉ ፍርድ ቤቶች መካከል ለዜጎች ፍትሕ የማግኘት መብትን በቅርብ ለማረጋገጥና ለተከራካሪ ወገኖች ይልቁንም ለተከሳሹና ለምስክሮቹ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ሲባል ነው። ሥልጣኑም በተከራካሪዎች አድራሻ፣ ንብረቱ በሚገኝበት ቦታ፣ ውሉ በተመሠረተበት ወይም በሚፈፀምበት ወይም ጉዳቱ በደረሠበት ቦታ ወይም ተመሳሳይ ምክንያቶችን በመያዝ የሚመለከቷቸውን ጉዳዮች የሚለዩበት ነው። ይሕ ኢትዮጵያ የፌደራል ሥርዓትን ሳትከተል በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ የተቀረጸ የፍርድ ቤቶች የሥልጣን ክፍፍል ሥርዓት ነው።

ኢትዮጵያ የፌደራል የመንግሥት አወቃቀር ሥርዓትን በ1987 ዓ/ም በወጣው የኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት መከተሏን ተከትሎ ሥልጣን በክልሎችና በፌደራል መንግሥት የተከፋፈለ ስለመሆኑ በሕገ-መንግሥቱ ከአንቀጽ 50-52 ላይ ተመልክቷል። በዚህም ክልሎች በሥልጣናቸው ሥር ባሉ ጉዳዮች ሉዓላዊ ሥልጣን አላቸው። ክልሎች እንደ ፌደራል መንግሥት ሕግ-አውጪ፣ ሕግ አስፈጻሚና የዳኝነት አካል ያደራጃሉ። በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 78 መሠረት የዳኝነት አካሉ በፌደራል እና በክልል መንግሥት ደረጃ መቋቋሙ እና በአንቀጽ 80(1)(2) ላይ በፌደራል ጉዳዮች የፌደራል ፍርድ ቤት፤ በክልላዊ ጉዳዮች የክልል ፍርድ ቤት የመጨረሻ ሥልጣን ያለው መሆኑ መመልከቱ በፌደራልና በክልል መንግሥታት መካከል የፍርድ ቤት የሥልጣን ክፍፍል እንዳለ ያሳያል። የፌደራል ወይም የክልል ጉዳዮች የሚለው በጉዳይ ዓይነት የተከፋፈለ ሥልጣን ስለሆነ የፍርድ ቤቶች ሥልጣን የተለየው የሥረ-ነገር ሥልጣንን መሠረት ያደረገ ቢመስልም ጉዳዩ ከሉዓላዊ ሥልጣን እና ክልላዊ ጉዳይ በፌደራል ፍርድ ቤት ቢታይ ከጣልቃገብነት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ጉዳዩ የብሔራዊ ዳኝነት ሥልጣንን የሚያስነሳ ነው። በፌደራል መዋቅር የብሔራዊ የዳኝነት ሥልጣን መሠረቱ ዓለምአቀፍ ሕግ ሳይሆን ሕገ-መንግሥት ነው። ሕገ-መንግሥቱ የፌደራልን ሆነ የክልልን ፍርድ ቤቶች ያቋቋመና አክብረው ለማስከበርም ግዴታ የጣለ ነው። ውጤቱም እንደ ሀገር የሚመረመረው የብሔራዊ የዳኝነት ሥልጣን ከሌላ ሀገር ዜጋ ጋር በተያያዘ እና ሌሎች ሀገሮች ጋር የዲፕሎማቲክ ቅራኔንም ሊፈጥር የሚችል ሲሆን በፌደራልና በክልል መንግሥታት መካከል ያለው ግን በአንድ ሀገር ያሉና በሕገ-መንግሥቱ የሕግ የበላይነትን

በማረጋገጥ አንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማሕብረሰብ ለመፍጠር በሚሠሩ ተቋማትና ዜጎች ላይ፣ የተለያየ ሥልጣን ቢሆንም የጋራ የሆኑ ጉዳዮች ደግሞ ባላቸው መካከል የሚነሳ ስለሆነ የተለየ ነው። በፌደራል መዋቅር የፌደራል መንግሥት ሉዓላዊነቱ በመላው የኢትዮጵያ ግዛት ነው። ነገር ግን በግዛቱ ሥር ሁሉንም በፈቃዱ መወሰንና መፈጸም የማይችል መሆኑን የሚመለከት ነው። ለክልል ፍርድ ቤት ሥልጣን መሠረቱ ግን በግዛት ክልል ሥር ያለ ሠውና ንብረት መሆን አለመሆኑን መሠረት ያደረገ (limited sovereignty) ነው።

በሕገ-መንግሥቱ የሥልጣን ክፍፍሉም የክልል ከፍተኛና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የፌደራል ጉዳዮችን በውክልና ማየት የሚችሉ ሲሆን ክልላዊ ጉዳዮች በክልሎች ሉዓላዊ ሥልጣን ክልል ውስጥ (exclusive jurisdiction of state courts) ያለ በመሆኑ በመርሕ ደረጃ የፌደራል ፍርድ ቤቶች ማየት አይችሉም። ይሕም ክልላዊ ጉዳዮች ላይ የፌደራል ፍርድ ቤቶች የመዳኘት ሥልጣን (judicial jurisdiction) የሌላቸው መሆኑን ሲያሳይ በውክልና እና በጣምራ ሥልጣናቸው ከሚመለከቱት በሥተቀር የክልል ፍርድ ቤቶች የፌደራል ጉዳዮችን ማየት አይችሉም። ከዚህ ጋር ተያይዞ መመርመር ያለበት በሕገ-መንግሥቱ የተመለከተው የፍርድ ቤቶች የጣምራነት ሥልጣን (concurrent jurisdiction) እና የፌደራል ጉዳዮች የሚወሰኑበት ሥርዓት ነው። የፌደራል ጉዳዩች ምን እንደሆኑ በሕገ-መንግሥቱ ያልተወሰነ ቢሆንም በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 3 መሠረት የፌደራል ጉዳዮች ሕገ-መንግሥቱን፣ የፌደራል መንግሥት ሕጎችንና ዓለም አቀፍ ሥምምነቶችን መሠረት ያደረጉ ጉዳዮች (based on laws)፤ በፌደራል ሕግ ተገልጸው በተወሰኑ ባለጉዳዮች (parties) እና በሕግ በተገለጹ ቦታዎች (places) ላይ የሚነሱ ጉዳዮች ናቸው። በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 4 እና 5 መሠረት የተዘረዘሩት የፌደራል ፍርድ ቤት በብቸኝነት ሥልጣኑ የሚመለከታቸው ሕግንና ባለጉዳዮችን መሠረት አድርጎ የተለዩ የፌደራል ጉዳዮች ሲሆን በሌሎች ሕጎች በግልፅ ለፌደራል ፍርድ ቤት የተሠጡ ጉዳዮችን ይጨምራል። የአዋጁን አንቀጽ 11 እና ተከታዮችን ሥንመለከት ደግሞ ቦታን መሠረት በማድረግ አዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተሞች ላይ የሚነሡ ጉዳዮች የፌደራል ፍርድ ቤት የሚመለከታቸው የፌደራል ጉዳዮች ስለመሆናቸው ተደንግጓል።

በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 3 መሠረት ሕግን መሠረት አድርጎ የተለዩት የፌደራል ጉዳዮች ውስጥ የፌደራል መንግሥት ሕጎችን መሠረት ያደረጉ ጉዳዮች

ያለበት በመሆኑና በአዋጁ የትርጉም ክፍል አንቀጽ 2(3) ላይ የፌደራል መንግሥት ሕጎች ማለት በሕግ በተሠጠው ሥልጣኑ ክልል ሥር ያሉ ነባር ሕጎችን የሚጨመር መሆኑ ሲታይ በሕግ በግልጽ የፌደራል ፍርድ ቤት ሥልጣን ሥር ከተመለከቱት ሕግን መሠረት ያደረጉ ጉዳዮች እና በፌደራል ሥልጣን ሥር እንዲታዩ ከተወሰኑት ባለጉዳዮች ውጭ ያሉ የፌደራል ሕግን መሠረት ያደረጉ ጉዳዮች የፌደራልና የክልል ፍርድ ቤቶች በጣምራ ሥልጣናቸው የሚመለከቷቸው ናቸው። ሥለሆነም የፌደራል ሕግን መሠረት ያደረጉ ሌሎች ጉዳዮች እንደተነሱበት ቦታ የፌደራል ፍርድ ቤት ወይም የክልል ፍርድ ቤት በክልላዊ ሥልጣኑ ሊመለከተው ይችላል።

በኢትዮጵያ የፌደራል ሥርዓት መሠረት አድርጎ የተዋቀረው የዳኝነት ሥልጣን የፌደራል እና የክልል ፍርድ ቤቶች ካላቸው የጣምራነት ሥልጣን ባለፈ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 78(2) እና 80(4-6) የፌደራል ፍርድ ቤት በብቸኝነት ሥልጣኑ የሚመለከታቸውን ጉዳዮች የክልል ጠቅላይና ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በውክልና እንዲመለከቱ ሥልጣን ሰጥቷል። ይህም ሕገ-መንግሥቱ የክልል ፍርድ ቤቶችን ማብቃትን (empowerment)፣ የክልሎችን ተሳትፎ ማሳደግ ላይ ዓላማ ያለውና ተቋሞቻቸው ላይ አመኔታ ያለው መሆኑን ያረጋግጣል። በሕገ-መንግሥቱ የዳኝነት አካል በፌደራልና በክልል ደረጃ በየእርከኑ መዋቀሩ ሲታይ አደረጃጀቱ በተዋረደ ያለ አቀራረጽ (dual system) ያለው ቢሆንም የፌደራልና የክልል ጉዳይን የክልል ፍርድ ቤቶች መመልከታቸው የተደባለቀ (integrated system) እንደሚከተልም ያሳያል።

የክልል ፍርድ ቤቶች በጣምራ ሥልጣናቸው በክልል ግዛታቸው የተነሱ ጉዳዮች የመመልከት ሥልጣን ያላቸው በመሆኑ የፌደራል ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን አይኖረውም። ጉዳዩ በክልል ፍርድ ቤት የሚታየው ጉዳዩ የተነሳበትን ቦታና ተከራካሪውን መሠረት በማድረግ ነው። የጣምራነት ሥልጣን መሠረቱ የፌደራል መንግሥት ሕግን መሠረት ያደረገ የፌደራል ጉዳይ በመሆኑ የፌደራል ፍርድ ቤት በፌደራል ጉዳይ ላይ ብሔራዊ የመዳኘት ሥልጣን የለውም ሊባል አይችልም። ነገር ግን በፌደራል ፍርድ ቤት አዋጅ ቁጥር 25/1988 አቀራረጽ መሠረት ከተለዩት ውስን የፌደራል ፍርድ ቤት ሥልጣኖች ውጭ ያሉ በክልል ግዛት የሚነሱ ጉዳዮችን የክልል ፍርድ ቤቶች እንዲመለከቷቸው የተተወ በመሆኑ ጉዳዩ የሥረ-ነገር ሥልጣን ጥያቄ የሚያስነሳ ይሆናል።

በተመሳሳይ የክልል ፍርድ ቤቶች በፌደራል ፍርድ ቤት በብቸኝነት እንዲታዩ የተለዩ ጉዳዮችን (exclusive jurisdiction) በግዛታቸው ባሉ ሠዎች ወይም ንብረቶች ጋር የሚነሱ ሲሆን

በውክልና (delegation) እንዲመለከቱ በሕገ-መንግሥት ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል። በክልል የሚነሱ የፌደራል ጉዳዮች ላይ ጉዳዩ የፌደራል በመሆኑ የፌደራል ፍርድ ቤቶች ብሔራዊ የመዳኘት ሥልጣን አላቸው። በፌደራል ፍርድ ቤት አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 4 እና 5 የተመለከቱት የፌደራል ጉዳዮችን በተከታዮቹ ድንጋጌዎች ለፌደራል ፍርድ ቤቶች የሥረ-ነገር ሥልጣናቸውን ያከፋፈለ በመሆኑ ይህን ሕግ መሠረት ተደርጎ ሲታይ የፌደራል ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለመዳኘት የሥረ-ነገር ሥልጣን እንዳለው ያሳያል። የአፋር፣ የቤንሻንጉል/ጉሙዝ፣ ጋምቤላ፣ ሶማሌና የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልሎች በሕገ-መንግሥቱ ያላቸው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ሥልጣን በውክልና በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የማየት ሥልጣን በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማደራጃ አዋጅ ቁጥር 322/1995 ሲነሳ በእነዚህ ክልሎች የፌደራል ክፍተኛ ፍርድ ቤት መደራጀቱ ታወጀ እንጂ በአምስቱ ክልሎች ግዛቶች የሚነሱ ጉዳዮችን የመመልከት የሥረ-ሥልጣን እንደ አዲስ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አለመሠጠቱ ቀድሞውንም በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 መሠረት የሥረ-ነገር ሥልጣን ተወስኖ ያደረ መሆኑን ያረጋግጣል። የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተሞች ውጭ በእነዚህ ክልሎች ሲደራጅ የማስቻያ ቦታው የተወሰነ በመሆኑ ጉዳዮችን ለማየት የግዛት ክልል ሥልጣን ያገኛል። ይሕም የክልል ፍርድ ቤቶች በግዛታቸው ባሉ ሠዎች ወይም ንብረቶች ጋር የሚነሳ በውክልና የሚመለከቱትን የፌደራል ጉዳይ ውክልናቸው ሳይነሳ ጉዳዩ ለፌደራል ፍርድ ቤት ቀርቦ ከታየ የግዛት ክልል ሥልጣን ክርክር የሚያስነሳ መሆኑን ያስገነዝባል።

ነገር ግን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ከተመለከተው የግዛት ክልል የተለየ ውጤት ያለው ነው። ሥነ-ሥርዓት ሕጉ በሚቀረጽበት ጊዜ የፌደራል ሥርዓት አወቃቀር ባለመኖሩ ተመሳሳይ የሥረ-ነገር ሥልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች በተለያዩ የፌደራልና የክልል መንግሥታት ሥልጣን ክልል ውስጥ በሚሆንበት ጊዜ የሚያስነሳውን ክርክር የሚመለስ አይደለም። የሥነ-ሥርዓት ሕጉ አቀራረጽም ከፌደራል ሥርዓቱ ጋር ተጣጥሞ መተርጎም ይኖርበታል። ጉዳዩ በሥነ-ሥርዓት ሕጉ እንደተቀረጸው የግዛት ክልል ሥልጣን በዋነኛነት አመቺነትን ብቻ መሠረት ያደረገ ነው፤ አመቺ እስከሆነ ድረስ በፌደራል ፍርድ ቤት ሊታይ ይችላል ከተባለ፤ በሕገ-መንግሥቱ የክልል ፍርድ ቤቶች ውክልና ሊነሳ የሚችለው በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 2/3ኛ ድምጽ ብቻ ስለመሆኑ በአንቀጽ 78(2) ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ፤ የክልል ፍርድ ቤቶች በሕገ-መንግሥቱ የተሠጣቸውን የውክልና ሥልጣን በሕጉ በተገለጸው አግባብ ሳይነሳ በፍርድ ቤቶች ውክልናውን የማንሳት ውጤት ያስከትላል። ሕገ-

መንግሥቱ የፌደራል ጉዳይን በውክልና በክልል ፍርድ ቤቶች እንዲታይ የወሰነበትንና ሊያሳካው የፈለገውን ዓላማና ግብ ላይ እንዳይደርስ ያደርጋል። ጉዳዩን የሚመለከተው ፍርድ ቤት የሚወሰነው በሕግ ሆኖ እያለ በክልል ፍርድ ቤት በውክልና ሊታይ የሚችል ሥልጣን በፌደራል ፍርድ ቤት የሚቀርብ ከሆነ ተከራካሪዎች ክሱን የሚያቀርቡበት ፍርድ ቤት የፌደራል ወይስ የክልል ፍርድ ቤት ስለመሆኑ በራሳቸው ምርጫ እንዲያቀርቡ (forum shopping) የሚያደርግ ተገቢ ያልሆነ የዳኝነት አሠጣጥ ሥርዓት እንዲፈጠር ዕድል ይሠጣል። ሥለሆነም በእነዚህ ምክንያቶች የክልል ጠቅላይና ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በሕገ-መንግሥቱ የፌደራል ጉዳዮችን በውክልና እንዲመለከቱ የተሠጣቸውን ሥልጣን መሠረቱ የፌደራል አወቃቀር በመሆኑ ውክልናቸው በሕግ እስካልተነሳ ድረስ ጉዳዮቹ ለፌደራል ፍርድ ቤት ሊቀርቡ አይችሉም። ጉዳዮቹ ቀርበው በፌደራል ፍርድ ቤቶች ከታዩ ውጤቱም አስገዳጅነት ያለውን የፍርድ ቤት ሥልጣን ክፍፍል የሚጥስ ስለሆነ ጉዳዩ በየትኛውም ደረጃ ፍርድ ቤት ሲደርስ በተከራካሪዎች ሆነ በፍርድ ቤቱ የሥልጣን ጥያቄው ተነስቶ ክሱ ውድቅ ሊደረግ የሚገባው ነው።

ወደ ያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ክሱ መሠረት ያደረገው ከውል ውጭ ኃላፊነትን ሲሆን ጉዳት የደረሠበት ንብረት የሚገኘው ሆነ ጉዳቱ የደረሠበት ቦታ ኦሮሚያ ክልል ቡራዩ ከተማ ውስጥ ነው። በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ጉዳት በደረሰ ጊዜ ክሱ የሚቀርበው ንብረቱ በሚገኝበት ቦታ መሆኑን ስለግዛት ክልል የሚደነግገው የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 25(1)(መ) ላይ ተመልክቷል። ይሕም ክሱ ኦሮሚያ ክልል ፍርድ ቤት እንደሚታይ ያስረዳል። በሌላ በኩል የተከራካሪዎችን አድራሻ ስንመለከት አመልካች፣ ተጠሪ፣ እና የሥር 3ኛ ተከሳሽ ኦሮሚያ ክልል ነዋሪ ሲሆን የሥር 2ኛ ተከሳሽ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ናቸው። በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5(2) መሠረት መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች ውስጥ በሆኑ ሠዎች መካከል በሚነሱ ክርክሮች ላይ የመዳኘት ሥልጣን ያለው የፌደራል ፍርድ ቤት ነው። በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 47(1) ከተዘረዘሩት ክልሎች ውስጥ አዲስ አበባ ከተማ ራሷን ችላ ክልል ባትሆንም ከአንድ ክልል በላይ የሚሻገር ጉዳይ የፌደራል መንግሥት ፍላጎትና ጥቅም (federal interest) ያለበት መሆኑን ታሳቢ ተደርጎ የተቀረጸ ሕግ በመሆኑ ጉዳዩ የፌደራል ነው። የፌደራል ጉዳይ ቢሆንም ጉዳዩ የተነሳው በኦሮሚያ ክልል በመሆኑ በሕገ-መንግሥቱ በተሠጠው ውክልና መሠረት መታየት ያለበት በክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው። የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አዲስ አበባ ወይም ሌላ ከተማ ላይ ማስቻሉ ጉዳዩ በውክልና የሚመለከተው ሥልጣን ክልል ውስጥ እስከሆነ ድረስ ልዩነት የለውም። የኦሮሚያ ክልል

በሕገ-መንግሥቱ የተሠጠው የውክልና ሥልጣን ያልተነሳ ስለሆነ የፌደራል አወቃቀሩን መሠረት ያደረገው አስገዳጅነት ያለውን የፍርድ ቤት የግዛት ክልል ሥልጣን ክፍፍል በሚጥስ መልኩ በፌደራል ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ ቀርቦ መታየቱ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 234811 ሐምሌ 15 ቀን 2011 ዓ/ም እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 71721 ጥር 13 ቀን 2011 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የፌደራል ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የለውም በማለት ወስነናል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
አፈጻጸሙ ላይ የተሠጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም/ቶ

-የሰ.መ.ቁ.200482

ህዳር 27 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡....1. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2. ቀነዓ ቂጣታ

3. ፈይሳ ወርቁ

4. ደጆኔ አያንሳ

5. ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካች፡.....ወ/ሮ ሐቢባ ሸምሱ ስሩር - ቀርበዋል

ተጠሪ፡.....አቶ ቴዎድሮስ ገብሩ ብዛ- ቀርበዋል

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍርድ

ይህ የፍቺ ክርክር የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች እና የአሁን ተጠሪ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር። ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.251802 ጥር 26 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ።

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የአሁን አመልካች በሥር ፍ/ቤት ባቀረበችዉ ክስ ከተጠሪ ጋር ግንቦት 12 ቀን 2001 ዓ.ም በግብጽ ሀገር ጋብቻ ፈጽመን አብረን ሲንኖር ህጻን ሊና ቴዎድሮስ የተባለችዉን ልጅ የወለድን ቢሆንም ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ ግንኙነታችን ተቋርጦ በጋብቻ መቀጠል ስላልቻልን ጋብቻችን እንዲፈርስልን በማለት ዳኝነት ጠይቃለች።

የአሁን ተጠሪ በዚህ ክስ ላይ ባቀረበዉ መልስ ከአመልካች ጋር ጋብቻ አልፈጸምንም፣ በጋብቻ ሰነዱ ላይም አልፈረምኩም፣ አመልካች ጋብቻ እንደሌላቸዉ ስለመሆኑ ማስረጃ ተሰጥቷል፤ በግብጽ አገር ጋብቻ የሚፈጸመዉ በፍ/ቤት ነዉ፤ ከአመልካች ጋር በነበረን የግብረ ስጋ ግንኙነት የተጠቀሰችዉን ልጅ ከመዉለዳችን ዉጭ በጋብቻም ሆነ ጋብቻ ሳይፈጽም እንደባልና ሚስት አለመኖራቸዉን ገልጸዉ ጋብቻ በሌለበት የቀረበዉ ክስ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክሯል።

ከዚህ በኋላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን በመስማት፣ ከሚመለከተዉ አካል በማጣራትና የቀረበዉን የሰነድ ማስረጃ በመመርመር ባሳለፈዉ ዉሳኔ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በግብጽ አገር ጋብቻ ስለመፈጸማቸዉ አግባብነት ባለዉ ማስረጃ ባለመረጋገጡ አመልካች የጋብቻ ፍቺ እንዲወሰን ያቀረበችዉ የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት የለዉም፤ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተፈጸመ ጋብቻ የለም፣ የሚሰጥ ፍቺ የለም በማለት ወስኗል። ይህ ጉዳይ በይግበኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.254606 በ20/4/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት ግራ ቀኙን በማከራከር የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል። የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማለወጥ ነዉ።

የአሁን አመልካች ታህሳስ 26 ቀን 2013 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ አመልካች እና ተጠሪ መንግስትን ተቃዉመን ከአገር ተሰደን ለብዙ ጊዜ እንደባልና ሚስት አብረን ሲንኖር ዕድሜዋ 10 ዓመት የሆናትን ልጅ ሊና ቴዎድሮስ የተወለደች ሲሆን በግብጽ አገር የጋብቻ ዉል ያደረግን ሲሆን እኛ በግብጽ አገር በስደት የሚንኖርና ሕጋዊ ነዋሪዎች ባልሆንበት በአገሪቱ በሕጋዊ መንገድ እንደሚኖር ዜጋ የጋብቻ ዉሉ በፍ/ቤት አልተመዘገበም በማለት የጋብቻ ዉል የለም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ። አመልካች ይህን ክርክር ለማስረዳት የሰዉ ምስክሮችን ቆጥረን እያለ የሥር ፍ/ቤቶች ምስክሮቹን ሊቀበሉን አልቻሉም፣ ተጠሪ የጋራ ሀብት ነዉ በማለት በአመልካች ስም ለኮንዶሚኒየም የተቆጠበዉን ገንዘብ ማሳገዱ ጋብቻ መኖሩን እያመነ መሆኑን የሚያሳይ ሆኖ ሳለ የሥር ፍ/ቤቶች ጋብቻ የለም በማለት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በዝርዝር አመልክታለች።

ይህ ችሎት የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት ሚያዚያ 21 ቀን 2013 ዓ.ም በተጻፈ መልስ፡ አመልካች እና ተጠሪ በግብጽ አገር በስደተኞች ካምፕ ጋብቻ ስለመኖሩ የጋብቻ ሰነድ መፈረሙ ተረጋግጧል ይበሉ እንጂ ሰነዱ ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ በኢፌዴሪ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሕጋዊነቱ ተረጋግጦ የገባ ስላልሆነ ሕጋዊ ሆኖ የቀረበ ሰነድ አይደለም ተቀባይነት የለዉም፤ የሥር ፍ/ቤት ከግራ ቀኙ ክርክር አንጻር የሰዉ ምስክሮችን መስማት እንደማያስፈልግ ስላመነበት ማለፉ ትክክል ነዉ፤ አመልካች ከተጠሪ ጋር እንደባልና ሚስት አብረን ኖረናል ያሉት በሥር ፍ/ቤት ያልተነሰ ክርክር ስለሆነ ተቀባይነት የለዉም፤ ለኮንዶሚኒየም የተቆጠበዉን ገንዘብ ያሳገድኩት የጋራ ሀብት ነዉ በሚል ሳይሆን በዚህ ክርክር ምክንያት ለሚደርስብኝ ወጪና ኪሳራ የሚወሰንልኝ ከሆነ ይህን ገንዘብ

ለመወሰድ እንዲችል ነዉ። ስለሆነም የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ በአግባቡና ሕጋዊ ስለሆነ የቀረበዉ አቤቱታ ዉድቅ እንዲሆንልኝ ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልኝ በማለት በዝርዝር ተከራክሯል። አመልካች የሰበር አቤቱታዋን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርባለች።

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል። እንደመረመርነዉ በዚህ ጉዳይ ምላሽ የሚሻዉ ፣ይህ ጉዳይ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግን የሚመለከት ነዉ ወይስ አይደለም? ጉዳዩ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ህግን የሚመለከት ከሆነ ክርክሩን ለማየት የሥረ-ነገር የዳኝነት ያለዉ የትኛዉ ፍ/ቤት ነዉ? የሚሉት ነጥቦች መሆናቸዉን ተገንዝበናል። በዚህ መሰረት አመልካች ካቀረበችዉ ክርክር እና የሥር ፍ/ቤቶች በዉሳኔያቸዉ እንዳመለከቱት አመልካች ከተጠሪ ጋር ጋብቻ ፈጽመናል የሚትለዉ በግብጽ አገር በስደተኞች ካምፕ መሆኑን ጠቅሳ የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን ጋብቻቸዉን በምስክሮች ፊት አስፈጽሟል ያለችበትን የጋብቻ የምስክር ወረቀት የሰጠ መሆኑን እና ተጠሪም ይህን ሰነድ መፈረሙን በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የፎረንሲክ ምርመራ ክፍል መረጋገጡን ነዉ። ተጠሪ ግን ከአመልካች ጋር በግብጽ አገር ጋብቻ አለመፈጸቸዉን፣ በግብጽ አገር ተጋቢዎች ጋብቻ መፈጸም ያለባቸዉ በፍ/ቤት መሆኑን፣ የተባለዉ የጋብቻ ሰነድ አግባብነት ባለዉ ሕግ መሰረት በኢትዮጵያ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተረጋግጦ ወደ አገር ያልገባ መሆኑንና ተቀባይነት ሊኖራዉ እንደማይገባ ገልጾ መከራከሩን መዝገቡ ያሳያል። በግራ ቀኙ መካከል ከሚነሳዉ የፍሬ ነገር እና የህግ ክርክር አንጻር ጉዳዩ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግን [Private International Law] የሚመለከት ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነጥብ መታየት ያለበት ጉዳይ ነዉ።

እንደሚታወቀዉ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግ የዉጭ አካል ተካፋይ የሆነበትን የህግ ክርክር የሚመለከቱ መርሆዎችና ደንቦችን የሚያካተት ነዉ። የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግ ወይም የሕግ ግጭት [Conflict of laws] የሚመለከተዉ በተያዘዉ የህግ ክርክር የትኛዉ ሕግ ተፈጻሚነት እንዳለዉ እና የትኛዉ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን እንዳለዉ የሚወስኑ የህግ መርሆችን ነዉ። የፌዴራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 5 (1፣ ሀ) እና 11 (1፣ ሀ) መሰረት የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግን በሚመለከቱ የፍትሕ ብሔር ጉዳዮችን ለማየት የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣን ያለዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መሆኑን ይደነግጋል።

በዚህ አግባብ አሁን የተያዘዉ ጉዳይ ሲታይ አመልካች ባቀረበችዉ ክርክር ከተጠሪ ጋር ጋብቻ ፈጽመናል ያለችዉ በግብጽ አገር በሚገኘዉ በተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ካምፕ በከፍተኛ

ኮሚሽንና በምስክሮች ፊት መሆኑን ገልጻ ተከራክራለች፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች ከተጠሪ ጋር አድርገናል የሚትለዉ ጋብቻ እንዲፈርስላት ክስ አቅርባ ዳኝነት የጠየቀችዉ በኢትዮጵያ ፍ/ቤት መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡ በዚህ መሰረት ከግራ ቀኙ ክርክር አንጻር በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በግብጽ አገር በሚገኘዉ በተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ካምፕ አመልካች ተፈጽሟል የሚትለዉ ጋብቻ በተመለከተ ሕጋዊ ጋብቻ ተፈጽሟል ለማለት የትኛዉ ሕግ ተፈጻሚነት ይኖረዋል? የሚለዉ ነጥብ ምላሽ የሚያስፈልገዉ ጉዳይ ሆኖ እናገኛለን፡፡ እንዲሁም በግራ ቀኙ መካከል በግብጽ አገር በሚገኘዉ የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ካምፕ ተፈጽሟል የተባለዉ ጋብቻ፣ በሕግ አግባብ የተፈጸመ ጋብቻ ነዉ የሚባል ከሆነና ጋብቻቸዉ በፍቺ ዉሳኔ እንዲፈርስ የሚወሰን እንደሆነ የፍቺ ዉጤት በምን አግባብ ይታያል? የሚለዉ ነጥብ ሊነሳ እንደሚችል ሌላዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የግራ ቀኙን የጋብቻ ይፍረስልን ክርክር በተመለከተ ተፈጻሚነት ያለዉ ሕግ የትኛዉ ነዉ? የሚለዉን ነጥብ መወሰንን ይጠይቃል ማለት ነዉ፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የግራ ቀኙ ክርክር የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግን የሚመለከት ጥያቄ የሚያስነሳ ሆኖ እናገኛለን፡፡ ይህ ጉዳይ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግን የሚመለከት ከሆነ ደግሞ በኢትዮጵያ ዉስጥ የትኛዉ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን አለዉ? የሚለዉ አግባብነት ካለዉ ሕግ አንጻር ታይቶ ምላሽ ሊሰጥበት የሚገባዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 5 (1፣ ሀ) እና 11 (1፣ ሀ) መሰረት የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግን የሚመለከቱ የፍትሕ ብሔር ጉዳዮችን የማየት የመጀመሪያ ደረጃ የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ያለዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መሆኑን ይደነጋገል፡፡ ስለሆነም ፍ/ቤት አንድን ጉዳይ ለማየት የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን አለዉ ወይስ የለዉም? የሚለዉን አስመልክቶ ተከራካሪ ወገኖች ከዚህ አንጻር የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ባያነሱም ፍ/ቤት በራሱ ተነሳሽነት በማንሳት ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ ሊሰጥበት እንዲሚገባዉ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.9 (1)፣ 231 (1፣ ለ)፣ 244 (3) እና 245 (2) ድንጋጌዎች ይዘትና ዓላማ መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች ይህ ጉዳይ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግ ጥያቄን የሚያስነሳ መሆኑን እና ጉዳዩን ለማየት የመጀመሪያ ደረጃ የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ያለዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መሆኑን በመገንዘብ የአሁን አመልካች ያቀረበችዉን ክስ ዉድቅ በማድረግ ስልጣን ላለዉ ፍ/ቤት ጉዳዩን ማቅረብ እንደሚትችል በማመልከት መወሰን ሲገባቸዉ ይህን ባለማድረግ ያሳለፉት ዉሳኔ ከፍ ሲል ከተጠቀሱት ሕጎች አንጻር ተቀባይነት የለዉም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ ለማየት የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ሳይኖረዉ ጉዳዩን አይቶ ያሳለፈዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህን ዉሳኔ ማረም ሲገባዉ በማጽናት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

ዉሳኔ

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.251802 ጥር 26 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.254606 በ20/4/2013 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡

ይህ ጉዳይ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግን የሚመለከት ስለሆነ ጉዳዩን ለማየት የመጀመሪያ ደረጃ የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ያለዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እንጂ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አይደለም ብለናል፡፡

ግራ ቀኞቸዉ ይህን ጉዳይ ስልጣን ላለዉ ፍ/ቤት ከማቅረብ ይህ ዉሳኔ የሚከለክላቸዉ አይሆንም ብለናል፡፡

የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡

ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

ይህ ዉሳኔ ታህሳስ 1 ቀን 2014 ዓ.ም ተነቧል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ጉምሩክ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰ.መ.ቁ.204922

የካቲት 28 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡....1. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2. ቀነዓ ቂጣታ

3. ፈይሳ ወርቁ

4. ደጀኔ አያንሳ

5. ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካች፡.....ኢንተርስቴት ኤክስፕሬስ ትራንስፖርት ኃ/የተ/የግ/ማህበር ፡- የቀረበ የለም

ተጠሪ፡.....የሚሌ አዋሽ ጉምሩክ ጽ/ቤት ፡- የቀረበ የለም

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍርድ</u>

ይህ የተሸከርካሪ ዉርስ ክርክር የተጀመረዉ በፌዴራል ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ሲሆን፣ የአሁን አመልካች የሥር ይግባኝ፣ የአሁን ተጠሪ የሥር መልስ ሰጪ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.190485 በ10/6/2013 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት በማመልከቱ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የሥር ይግባኝ ባይ (የአሁን አመልካች) በፌዴራል ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ባቀረበዉ የይግባኝ ቅሬታ የይግባኝ ባይ ድርጅት ተሸከርካሪ የሆነዉ ኮድ 3-35522/10862 ኢት የሆነዉ የነዳጅ ቦቴ የመኪናዉ አካል ዕቃዎችን ለመደበቅ እንዲያስችል ሆኖ ተለዉጦ ተሰርቶ የኮንትሮባንድ ዕቃ ጭኖ የተገኘ በመሆኑ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 147 (3) መሰረት ተሸከርካሪዉ ዉርስ ሆኖ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ያሳለፈዉ ዉሳኔ ተገቢ አይደለም፤ ይግባኝ ባይ የተሸከርካሪዉ አካል ዕቃዎችን ለመደበቅ በሚያስችል ሁኔታ አድርጎ አልሰራም፤ ሹፌር የተሸከርካሪዉን ከሕግ ዉጭ ሳልቫትዮዉን በድብቅ አስቀድዶ ለሕገወጥ ተግባር አዉሏል፤ ይግባኝ ባይ ይህን ጉዳይ ባላወቀበት ተሸከርካሪዉ ዉርስ ሆኖ ለመንግስት ገቢ መደረጉ ተገቢ አይደለም እንዲሻርልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

የሥር መልስ ሰጪ ባቀረበዉ መልስ የይግባኝ ባይ ተሸከርካሪ የመጠባበቂያ የነዳጅ መያዣ አካል ከመደበኛ አገልግሎት ዉጭ የኮንትሮባንድ ዕቃ መሸሸግ እንዲያስችል ሆኖ የተለወጠ አካል መሰራቱን እና በዚህም የኮንትሮባንድ ዕቃን ጭኖ መገኘቱ በሰዉ እና በሰነድ ማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ፣ ተሸከርካሪዉ ዉርስ ሆኖ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን በመልስ ሰጪ የተሰጠዉ ዉሳኔ እንዲጸናልን በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የፌዴራል ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ጉዳዩን በማጣራት ባሳለፈዉ ዉሳኔ የይግባኝ ባይ ተሸከርካሪ በሆነዉ የኮንትሮባንድ ዕቃዎች የተገኙበት ቦታ በተሸከርካሪዉ ፋብሪካዉ ለመጠባበቂያ ነዳጅ መያዣ ተብሎ የተሰራዉ ታንከር ከኋላ በኩል በአራት ማዕዛን በመቆራረጥና ፍሬም ብረት በማዘጋጀት ከቻንሲዉ ጋር በመበየድ የተቆጠረዉን ላሜራ በጠርዙ በኩል በብሎን እንዲታሰርና እንዲፈታ ተደርጎ ከመደበኛ አገልግሎት ዉጪ ሕገወጥ ዕቃዎችን ለመደበቅ እና ለማጓጓዝ በተለወጠዉ የመደበቂያ አካል ላይ መሆኑን በባለሙያ ሪፖርት የተደረገ በመሆኑ፤ በአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 147 (3፣ ሀ) መሰረት በተሸከርካሪ ላይ ሻግ በመገኘቱ ተሸርካሪዉን ዉርስ አድርጎ ለመንግስት ገቢ ለማድረግ የሚያበቃ ቢሆንም በይግባኝ ተሸከርካሪ ላይ የተደረገዉ ለዉጥ ይግባኝ ባይ በቁጥጥር የሚለያቸዉ ሳይሆን ጥንቃቄ የተሞላበትና ይግባኝ ባይ በቀላሉ እንዳይለያቸዉ ተደርጎ የተሰራ መሆኑን ጉባኤዉ ስለተገነዘበ፣ የይግባኝ ባይ ተሸከርካሪ ዉርስ የሆነዉ በአዋጁ ዉጪ ነዉ በማለት የመልስ ሰጪ በመሻር ወስኗል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የቀረበለትን ይግባኝ በትዕዛዝ በመሰረዝ የጉባኤዉን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

የሥር መልስ ሰጪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን በማከራከር ባሳለፈዉ አከራካሪዉ ተሽከርካሪ በነዳጅ መጠባበቂያ ክፍል ዉስጥ ዕቃ መደበቂያ ሻግ መሰራቱን እና በዉስጡም የጉምሩክ ሥነሥርዓት ያልተፈጸመባቸዉ ዕቃዎች መያዛቸዉን ግራ ቀኙ ያልተካካዱና በማስረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ቢሆንም የሥር ጉባኤ ተሽከርካሪዉ ዉርስ ሆኖ ለመንግስት ገቢ መሆን የለበትም ያለዉ የሥር ይግባኝ ባይ ሻግ መሰራቱን እንደማያዉቅና ቀድሞ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ የለም የሚል ነዉ፡፡ ነገር ግን በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 147 (3፣ ሀ) መሰረት ተሽከርካሪ ዉርስ ሆኖ ለመንግስተ ገቢ የሚሆነዉ በተሽከርካሪዉ አካል የዕቃ መደበቂያ /ሻግ/ የተሰራለት ወይም የተገጠመለት መሆኑን እንጂ የባለቤቱን እዉቀት ያለዉ መሆኑን ከግምት የማያስገባ በመሆኑ፤ ጉባኤዉ በድንጋጌዉ ያልተቀመጠዉን መስፈርት ዉጪ ሻግ መገጠሙን የሥር ይግባኝ ባይ አያዉቅም በማለት ተሽከርካሪዉ ሊወረስ አይገባም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ የህግ ስህተት በመሆኑ ዉሳኔዉ ተሽሯል፤ የሥር መልስ ሰጪ መ/ቤት ተሽከርካሪዉ ዉርስ ሆኖ ለመንግስት ገቢ ሊሆን ይገባል በማለት ያሳለፈዉ ዉሳኔ ጽንፈል በማለት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልከች መጋቢት 20 ቀን 2013 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ የአሁን አመልካች ለክርክር መነሻ በሆነዉ ተሽከርካሪ ላይ የተሰራዉን ሞዲፊኬሽን በቀላሉ የሚለየዉ ወይም የሚቆጣጠረዉ ነዉ ተብሎ የማይገመት ሆኖ ሳለ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በተሽከርካሪዉ ላይ የተሰራዉን መደበቂያ (ሻግ) መሰራቱን ባለቤቱ ያዉቀዋል የሚል ግምት ወስደናል በማለት ያሳለፈዉ ዉሳኔ ያለምንም ተጨባጭ ማስረጃ በመሆኑ፣ አመልካች ይህ መደበቂያ መሰራቱን የማያዉቅና መኪናዉን ለመዉረስ አስቀድሞ የተሰጠዉ ማስጠንቀቂያ ሳይኖር፣ የተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልን፤ የጉባኤዉና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ እንዲጸናልን በማለት በዝርዝር አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣የሥር ፍ/ቤት ተሽከርካሪዉ ሊወረስ ይገባል በማለት የሰጠዉን ዉሳኔ አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 147 (3) አንጻር ለመመርመር ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት በ12/9/2013 ዓ.ም በጻፈ መልስ፡ የአመልካች ንብረት የሆነዉ አከራካሪዉ ተሽከርካሪ ላይ ዕቃዎችን ለመደበቅ እንዲያስችል ሆኖ የተለወጠ ወይም መደበቂያ አካል (ሻግ) የተሰራለበት ወይም የተገጠመለት መሆኑና በዚህ መደበቂያ አካል ዉስጥ የኮንትሮባንድ ዕቃ ጭኖ መገኘቱ

በማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ፣ የተሸከርካሪዉ ባለቤት እዉቀት እንደመስፈርት ያልተቀመጠ በመኖኑ፣ አመልካች ሻግ በሹፌሩ መሰራቱን በማስረጃ አላረጋገጠም፤ በመሆኑም የአመልካች ተሸከርካሪ ዉርስ ሆኖ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን የተወሰነዉ ዉሳኔ ሕግን የተከተለ ስለሆነ የዉርስ ዉሳኔዉ እንዲጸናልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል። የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል። እንደመረመርነዉ የአመልካች ድርጅት ተሸከርካሪ የሆነዉ ኮድ 3-35522/10862 ኢት የሆነዉ የነዳጅ ቦቴ ለመጠባበቂያ ነዳጅ መያዣ ተብሎ የተሰራዉ ታንከር ከኋላ በኩል በአራት ማዕዛን በመቆራረጥና ፍሬም ብረት በማዘጋጀት ከቻንሲዉ ጋር በመበየድ የተቆጠረዉን ላሜራ በጠርዙ በኩል በብሎን እንዲታሰርና እንዲፈታ ተደርጎ ከመደበኛ አገልግሎት ዉጪ ሕገወጥ ዕቃዎችን ለመደበቅ እና ለማጓጓዝ በተለወጠዉ የመደበቂያ አካል (ሻግ) የተሰራበት እና የኮንትሮባንድ ዕቃን በዚህ የዕቃ መደበቂያ ሻግ ዉስጥ ጭኖ ሲያጓጉዝ መያዙን ግራ ቀኙን ያላከራከረና በማስረጃም የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ። ግራ ቀኙን ያከራከረዉ ጉዳይ አመልካች ባቀረበዉ ክርክር በተሸከርካሪዉ የመጠባበቂያ ነዳጅ መያዣ በሆነዉ የመኪናዉ አካል ዉስጥ የተሰራዉ የዕቃ መደበቂያ ሻግ ከአመልካች እዉቀት ዉጭ በሹፌሪ የተሰራ ስለሆነ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 147 (3፣ ሀ) መሰረት ተሸከርካሪዉ ዉርስ ሆኖ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን በቂ ምክንያት ሊሆን አይችልም የሚል ሲሆን፤ ተጠሪ በበኩሉ የአመልካች ንብረት የሆነዉ ተሸከርካሪ የዕቃዎች መደበቂያ ሻግ ተሰርቶለት የኮንትሮባንድ ዕቃዎች ጭኖ ሲያጓጉዝ መያዙ የተረጋገጠ በመሆኑ፣ የአመልካች እዉቀት ከግምት ሳይገባ ተሸከርካሪዉ ዉርስ ሆኖ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ለማድረግ በቂ ምክንያት ነዉ በማለት ተከራክሯል። በመሆኑም እዚህ ላይ ምላሽ ማግኘት ያለበት ጉዳይ ፣የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 147 (3፣ ሀ) መሰረት የኮንትሮባንድ ዕቃዎችን ለማጓጓዝ የዋለዉን ማጓጓጓ ዉርስ ሆኖ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ለማድረግ የኮንትሮባንድ ዕቃዎቹን ለመደበቅ እንዲያስችል ሆኖ የተሰራ፣ የተለወጠ ወይም መደበቂያ አካል የተገጠመለት መሆኑ ብቻ ሳይሆን የባለንብረቱ እዉቅት እንደመስፈርት ተቀምጧል ወይስ አልተቀመጠም? የሚለዉ ነጥብ መሆኑን ተገንዝበናል።

በዚህ መሰረት ከአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 147 (3፣ ሀ) ደንጋጌ መደረት እንደሚቻለዉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር ዉርስ ሆኖ ለመንግስተ ገቢ የሚደረጉትን ዕቃዎች የሚዘረዝር ሲሆን፣ እነዚህን የሚወረሱ ዕቃዎችን ለማጓጓዝ የዋለዉን ማንኛዉም ማጓጓዣ ዉርስ ሆኖ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ከሚያደርጉ ምክንያቶች መካከል አንዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 (ሀ) ሥር የተመለከተዉ ዕቃዎቹን ለመደበቅ እንዲያስችል ሆኖ የተሰራ፣ የተለወጠ ወይም መደበቂያ አካል የተገጠመለት እንደሆነ መሆኑን ይደነግጋል። ከዚህ ደንጋጌ ይዘትና ዓላማ መገንዘብ እንደሚቻለዉ ማጓጓዣዉ ዉርስ ሆኖ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን የሚያደርገዉ በማጓጓዣዉ አካል ላይ የዕቃዎች መደበቂያ ሻግ ተሰርቶለት/ተገጥሞለት መገኘቱ እንጂ ባለንብረቱ ይህን ጉዳይ ያዉቃል ወይስ አያዉቀዉም? የሚለዉን የእዉቀትን ሁኔታ እንደአንድ መስፈርት ያስቀመጠበት አግባብ የለም። የማጓጓዣዉ ባለንብረት ንብረቱን በተመለከተ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል በንብረቱ ላይ የሚደረገዉን ሁሉ ተከታትሎ ሕጋዊ ማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል ተብሎ ይታመናል። እነዚህ የሚወረሱ ዕቃዎች በአገርና በሕዝብ ላይ የሚያደርሱትን ዘርፈ ብዙ ችግሮችና ጉዳቶችን ለመከላከል እንዲቻል፣ የማጓጓዣ ባለንብረት በሚገባ ንብረቱን የመቆጣጠርና የመከታተል እንደነዚህ ዓይነት ዕቃዎችን ለማጓጓዣነት እንዳይዉል የማድረግ ግዴታ የጣለ ነዉ። ስለሆነም በአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 147 (3፣ ሀ) መሰረት በማጓጓዣዉ አካል ላይ የሚወረሱ ዕቃዎች መደበቂያ ሻግ ተሰርቶለት ወይም ተገጥሞለት በዚህ መደበቂያ ሻግ ዉስጥ ዕቃዎቹን ጭኖ መገኘቱ የተረጋገጠ እንደሆነ፣ ማጓጓዣዉ ዉርስ ሆኖ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ለማድረግ በቂ ምክንያት ነዉ እንጂ ባለንብረቱ ያዉቃል ወይስ አያዉቀዉም? ተብሎ ተጣርቶ፣ በዚህ መሰረት የተረጋገጠዉን ፍሬ ነገር መነሻ ተደርጎ ማጓጓዣዉ ዉርስ ሆኖ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን የሚያበቃ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ታይቶ ዉሳኔ የሚሰጥበት አግባብ የለም። በመሆኑም በዚህ ድንጋጌ መሰረት ማጓጓዣዉ ዉርስ ሆኖ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን የሚያስደርገዉ የመደበቂያ ሻግ የተሰርቶለት ወይም የተገጥሞለት ሆኖ፣ የሚወረሱ ዕቃዎችን በሻግ ዉስጥ ጭኖ መገኘቱ እንጂ የባለንብረቱ የእዉቀት ሁኔታ ታሳብ የሚደረግበት አግባብ አይኖርም ማለት ነዉ።

በዚህ መሰረት አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የአመልካች ንብረት የሆነዉ ተሽከርካሪ በተሰራለት የዕቃዎች መደበቂያ ሻግ ዉስጥ የኮንትሮባንድ ዕቃዎችን ጭኖ ሲያጓጉዝ የተያዘ መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ ያልተካደ ጉዳይ ስለሆነ፣ ተሽከርካሪዉ ዉርስ ሆኖ ለመንግስተ ገቢ እንዲሆን ለማድረግ በቂ ምክንያት በመሆኑ፣ የአመልካች እዉቀት ሁኔታ ማረጋገጥን የሚያስፈልግ ጉዳይ አይደለም። በመሆኑም የተጠሪ መ/ቤትም ሆነ የፌዴራል

ጠቅላይ ፍ/ቤት የአመልካች ተሸከርካሪ በዚህ ምክንያት ውርስ ሆኖ ለመንግስት ገቢ ሊሆን ይገባል በማለት ያሳለፉት ዉሳኔ የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80 (3፣ ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 (1) መሰረት ከተሰጠዉ ስልጣን አንጻር አመልካች ያቀረበዉ ቅሬታ የተጠሪ መ/ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ መሆኑን የሚያመለክት ስላልሆነ ተቀባይነት የለዉም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የአመልካች ተሸከርካሪ ዉርስ ሆኖ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ያሳለፈዉ ዉሳኔ በሕግ አግባብ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.190485 በ10/6/2013 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ጸንቷል፡፡

የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡

ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት የደረሳባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ሰበር ሰሚ ችሎት

የሠ/መ/ቁጥር 207462

የካቲት 30 **ቀን** 2014 **ዓ/ም**

ዳኞች ፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች ፡-መገል አይንትኦቨን ትራዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር

ተጠሪ ፡- የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክ አገልግሎት ድርጅት

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ በደረቅ ወደብ በተቀመጠ ንብረት ላይ ጉዳት ሲደርስ ኃላፊነት የሚያስከትሉ እና ኃላፊነት የማያስከትሉ ምክንያቶችን የሚመለከት ነዉ፡፡ አመልካች በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ በመሰረተው ክስ ንብረትነቱ የተጠሪ የሆነው የአመልካች ድርጅት በዲቮትራ ቢቪ ስም ከውጪ ሀገር አንድ ፎርክሊፍት በተጠሪ አማካኝነት አስጭኖ ወደ ሀገር ውስጥ እስከ ሞጆ ደረቅ ወደብ ድረስ አስገብቶ አስፈላጊውን የጉምሩክና ቀረጥ ሥነ ሥርዓት እስከሚፈፀም ድረስ የተጠሪ ቅርንጫፍ ዕ/ቤት በሆነው ሞጆ ደረቅ ወደብ በአደራ እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡ ተጠሪ ፎርክሊፍቱን በጥንቃቄ የመያዝ ሕጋዊ ግዴታ አለበት፡፡ ፎርክሊፍቱ በ12,000.00 የአሜሪካን ዶላር የተገዛ ሲሆን በተጨማሪም አመልካች ብር 599,403.34 ቀረጥና ታክስ ከፍሏል፡፡አመልካች ቀረጥና ታክስ ከፍሎ ፎርክሊፍቱን ከተጠሪ ለመረከብ ሲጠይቀው

ፎርክሊፍቱ ፍፁም ጥንቃቄ በጎደለው አያያዝ በሜዳ ላይ ተጥሎ ተጠሪ ግዴታውን ሳይወጣ በመቅረቱ ምክንያት በፎርክሊፍቱ ላይ ጉዳት እንዲደርስ አድርጓል፡፡የደረሰውን ጉዳት ለማስተካከል ለመለዋወጫ ብር 400,000.00 እና ለእጅ ሥራ ብር 350,000.00 በድምሩ ፎርክሊፍቱን ወደነበረበት ለመመለስ ብር 750,000 እንደሚያስፈልግ አመልካች በባለሙያ እንዲጣራ አድርጎ አረጋግጧል፡፡በመሆኑ ተጠሪ ይህንን ገንዘብ እንዲከፍል እና ፎርክሊፍቱን እንዲያስረክበኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተጠሪ በቀረበበት ክስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማስቀደም በሰጠው መልስ ፎርክሊፍቱ ከወደብ መጋዘን እንዲቀመጥ የተደረገው ፎርክሊፍቱ በትርፍነት የተገኘ እንደሆነ ገልጾ ጉምሩክ ባለው አሠራር መሰረት የጉምሩክ ሥነ ሥርዓቶች እስኪጠናቀቁ ድረስ በጊዜያዊነት በሞጆ ደረቅ ወደብ እንዲቀመጥ በወሰነው መሰረት እንጂ አመልካች እንዳለው አመልካች በሕጋዊ መንገድ አምጥቶ በአደራ የተቀመጠ አይደለም፡፡ ፎርክሊፍቱ ከባህሪው የተነሳ እና የጉምሩክ ፎርማሊቲ እስኪያሟላ ድረስ እንዲቀመጥ የሚደረገዉ ግዜያዊ ማቆያ በደረቅ ወደብ ነዉ፡፡ ተጠሪ በዚህ መንገድ የተጣለበትን ግዴታ በጥንቃቄ ተወጥቷል፡፡ አመልካች በራሱ ጥፋት 3 ዓመት ከ6 ወር በላይ ፎርክሊፍቱን በወደብ መጋዘን በማቆየቱ በጊዜ እርዝማኔ ምክንያት በሂደት ለሚፈጠረው ለውጥ ተጠሪ ተጠያቂ የሚሆንበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በአመልካች ምክንያት ለደረሰው ጉዳት በአዋጅ ቁጥር 588/2000 አንቀፅ 4/3 መሰረት ተጠሪ ኃላፊነት የለበትም፡፡ ተጠሪ ኃላፊ ነው ቢባል እንኳ እቃው የተገዛው 12,000.00 የአሜሪካን ዶላር በመሆኑ የተጠሪ ኃላፊነት በወቅቱ በነበረዉ የኢትዮጵያ ብር ምንዛሪ በብር 18.86 ሂሳብ ብር 226,320.00 ሲመነዘር በወቅቱ በነበረው ምንዛሬ ዋጋ ሊሆን ይገባል፡፡ፎርክሊፍቱ በተጠሪ ቁጥጥር ስር በመሆኑ በባለሙያ ሳይታይ እንደታየ ተደርጎ የቀረበዉ ማስረጃ ተገቢ ባለመሆኑ በገለልተኛ መርማሪ ሊመረመር ይገባል፡፡ተጠሪ ኃላፊነት አለበት ከተባለ በፎርክሊፍቱ ላይ ለደረሰዉ ጉዳት ከላይ በገለጽነዉ መሰረት እንዲካስ ተደርጎ ፎርክሊፍቱ ለተጠሪ እንዲቀር እንዲወሰንልን፡፡ፎርክሊፍቱ ለአመልካች ይመለስ የሚባል ከሆነ ደግሞ አመልካች ፎርክሊፍቱወደ ተጠሪ መጋዘን ከገባበት ከነሀሴ 27 ቀን 2005 ዓ/ም ጀምሮ ያለበትን የመጋዘን ኪራይ እንዲከፍል እንዲወሰንልን ሲል ተከራክሯል፡፡እንዲሁም ፎርኪሊፍቱ እንዲቀመጥ ያዘዘዉ የጉምሩክ ባለስልጣን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 43 መሰረት በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ እንዲታዘዝለት ጠይቋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 19086 ላይ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት የቀረበዉን ክርክርና የጉምሩክ ባለሥልጣን በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ የተጠየቀዉን ዉድቅ በማድረግ ፍሬ ነገሩን

በተመለከት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎችን መርምሮ በቀን 18/10/2012 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ ፎርክሊፍቱ አገር ዉስጥ ገብቶ ከቀን 25/06/2005ዓ/ም ጀምሮ በተጠሪ ዘንድ ለ3 ዓመት ያህል ጊዜ መቀመጡ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡ፎርክሊፍቱ አገር ዉስጥ በትርፍነት እንደገባ ተረጋግጦ አስፈላጊዉን ክፍያ በመፈጸም እንዲረከብ እና አስከዚያ በተጠሪ መጋዘን እንዲቀመጥ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እንደሆነ የቀረበዉ ማስረጃ ያሳያል፡፡ተጠሪ ፎርክሊፍቱን በጥንቃቄ የማስቀመጥ ኃላፊነት አለበት፡፡አመልካች ፎርክሊፍቱ ተጠሪ በአግባቡ አላስቀመጠም ፎርክሊፍቱ ፀሐይና ዝናብ ስለተፈራረቀበት እንደተበላሸ ከመግለጽ ዉጪ ተጠሪ ፎርክሊፍቱን ማስቀመጥ የነበረበትን አላስረዳም፡፡በአንጻሩ ተጠሪ ፎርክሊፊት እንደማንኛዉም መኪኖች የሚቀመጠዉ በግልጽ መጋዘን መሆኑን በማስረጃ አስረድቷል፡፡ፎርክሊፍት በግልጽ መጋዘን የሚቀመጥ ከሆነ ፀሐይና ዝናብ የሚፈራረቅበት መሆኑ የሚታመን ነዉ፡፡አመልካች የሚጠበቅበትን ግዴታ በመወጣት ፎርክሊፍቱን መረከብ ሲገባዉ የሚጠበቅበትን ግዴታ ባለመወጣቱ ለዘረጅም ጊዜ ፎርክሊፍቱ ፀሐይና ዝናብ እንዲፈራረቅበት እንዳደረገ ተረጋግጧል፡፡በፎርክሊፍቱ ላይ ጉዳት የደረሰዉ አመልካች በክሱ ላይ እንደገለጸዉ ፀሐይና ዝናብ ስለተፈራረቀበት ቢሆንም ጉዳቱ የደረሰዉ ፎርክሊፍቱ በግልጽ መጋዘን በመቀመጡ ምክንያት ሳይሆን አመልካች ፎርክሊፍቱን በጊዜዉ ባለመዉሰዱ ምክንያት በመሆኑ ለደረሰዉ ጉዳት ተጠሪ ኃላፊነት የለበትም ሲል ወስኗል፡፡እንዲሁም አመልካች የሚጠበቅበትን የመጋዘን ኪራይ ከፍሎ ፎርክሊፍቱን እንዲወስድ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቢያቀርብም ችሎቱ በመ/ቁጥር 195675 ላይ በቀን 11/06/2013 ዓ/ም በሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ይግባኙን ሰርዞበታል፡፡

አመልካች በቀን 10/09/2013 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉም ከላይ በተገለጸዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታዉ ይዘት በአጭሩ፡- የስር የከፍተኛው ፍርድ ቤት ለውሳኔዉ መሰረት ያደረገው በአዋጅ ቁጥር 588/2008 አንቀፅ 4/3/ን የተደነገገዉን ነው፡፡ ይህ የተጠቀሰው አንቀፅ እቃው የጠፋው ወይም ጉዳት ለደረሰበት ወይም እርክክብ የዘገየው በባለእቃው ምክንያት መሆኑ ከተረጋገጠ የደረቅ ወደቡ ተጠያቂነት አይኖርበትም የሚል ነው፡፡ ወደ አገር የሚገቡ እቃዎች አስፈላጊው የጉምሩክ ፎርማሊቲዎችና ክፍያዎች ተፈፅሞባቸው የእቃው ባለቤት እቃውን እስኪረከብ ድረስ እቃው በጉምሩክ ማቆያዎች እጅ እንደሚቆዩ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2008 አንቀጽ 2/10 እና

2/40 ስር ተደንግጓል፡፡ በዚህ መሰረት እቃው በተጠሪ እጅ በሚቀመጥበት ወቅት ተጠሪ እቃው ላይ ጉዳት ወይም ብልሽት እንዳይደርስበት በጥንቃቄ የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡ ለባለእቃው የሚኖርበትን ኃላፊነት ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 588/2008 አንቀፅ 4/1 ስር በተደነገገዉ መሰረት እቃዉ በደረቅ ወደብ ላይ እያለ...ጉዳት ቢደርስበት...በኃላፊነት እንደሚጠየቅ ተደንግጓል፡፡ይህም የሚያሳየዉ የእቃዉ ባለቤት መክፈል ያለበት አስፈላጊዉን የጉምሩክ ክፍያዎችን ጉምሩክ አሳዉቆት ባለቤቱ ክፍያ ፈጸሞ እቃዉን እስከሚረከብ ድረስ እቃዉን በጥንቃቄ የመጠበቅ ግዴታ ያለበት መሆኑን ነው፡፡ይህ እስከሚሆን ድረስ ተጠሪ ባለእቃዉን ለመረከብ ዘግይቷል የሚል ጥያቄ ሊያነሳ አይችልም፡፡ተጠሪ በአደራ የሚጠብቀዉም በነፃ ሳይሆን ለጠበቀበት ለእያንዳንዱ ቀን ክፍያ በማስከፈል ነው፡፡በአዋጅ ቁጥር 588/2008 አንቀጽ 4/3 ላይ የተገለጸዉ መዘግየት በእቃዎቹ ላይ የሚፈጸመዉ የጉምሩክ ፎርማሊቲዎችና ክፍያዎች እስከሚጠናቀቁ ድረስ ያለዉን ጊዜ የሚመለከት ባለሆነበት የሥር ፍርድ ቤት ይህንን ድንጋጌ አለአግባብ ተፈጻሚ አድርጓል፡፡በዚህ ድንጋጌ የተመለከተዉ ጊዜ መታየት ያለበት አመልካች የጉምሩክ ፎርማሊቲዎችንና ክፍያዎችን ፈጽሞ እቃዉን መረከብ ከሚችልበት ቀን በኋላ ያለዉን ጊዜ የሚመለከት ነዉ፡፡ተጠሪ የአመልካችን ፎርክሊፍቱን በአደራ ለመጠበቅ ስለተረከበ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2718/1 እና 2720 መሰረት ፍርክሊፍቱን በተረከበበት ሁኔታ የማስረከብ እና በፎርክሊፍቱ ላይ ለደረሰበት ጉድለት ኃላፊነት ስላለበት በአመልካች ፎርክሊፍት ላይ የደረሰው ጉዳት በተጠሪ ቸልተኝነት ምክንት እንጂ ከአቅም በላይ በሆነ ሀይል የደረሰ ጉዳት አለመሆኑ እየታወቀ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ኃላፊነት የለበትም ሲል የሰጠዉ ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ይታረመልን በማለት አቤቱታቸዉን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ በአመልካች ፎርክሊፍት ላይ ለደረሰዉ ጉዳት ተጠሪ ኃላፊነት የለበትም የመባሉን አግባብ ከአዋጅ ቁጥር 588/2008 አንቀፅ 4(1 እና 3) አላማና አተገባበር አንፃር ተጠሪ ባለበት እንዲመረመር ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 17/02/2014 ዓ/ም የተፃፈ መልሱን ያቀረበ ሲሆን ይዘቱ በአጭሩ፡- አመልካች ፎርክሊፍቱን በትርፍነት አገር ዉስጥ እንዳስመጣ የሞጆ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በቀን 04/13/2005ዓ/ም ባደረገዉ ፍተሻ አረጋግጧል፡፡ፎርክሊፍቱ የመጣለት የአማራ ብሔራዊ ክልል መንግስት ቴክኒክና የሙያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ በትርፍነት የመጣዉን ፎርክ ሊፍት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 53 መሰረት አስፈላጊዉን ፎርማሊቲ አጠናቆ እንዲረከብ በጉምሩክ ኮሚሽን ቢገለጽለትም እንደማይረከበዉ ለባለስልጣኑ አሳዉቋል፡፡በመሆኑም ባለቤት ያልወሰዳቸው የተተዉ እቃዎች በጊዜያዊነት የሚቆዩትበት ጊዜ ከ60 ቀናት መብለጥ እንደማይችል በአዋጁ

859/2006 አንቀፅ 51 ተደንግጓል፡፡በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 51/7፣57(2/ለ) እና 61 መሰረት ፎርክሊፍቱ በጊዘያዉ የጉምሩክ ክፍት መጋዘን እንዲቆይ ተደርጓል፡፡ተጠሪ የአመልካችን ፎርክሊፍት በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 እና በደረቅ ወደብ አዋጅ 588/2008 መሰረት ባለስልጣኑ እንዲቀመጥ ባዘዘው መሰረት በእቃው ባህርይ መሰረት መሰል ማሽነሪዎች መቀመጥ የሚገባው ቦታ አስቀምጧል፡፡ተጠሪ ከአመልካች ጋር የአደራ ዉል ግንኙነት ስለሌለዉ የተጠሪ ኃላፊነት ሊወሰን የሚገባዉ በእነዚህ ልዩ ሕግጋት መሰረት ነዉ፡፡ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 588/2008 አንቀጽ 4(2 እና 3) ላይ የተወሰነዉ ጊዜ የጉምሩክ ፎርማሊቲ ከመጠናቀቁ በፊት ያለዉን ጊዜ አያካተትም የገለጸዉ የተሳሳተ ነዉ፡፡አመልካች ፎርክሊፍቱን በአዋጁ ከተቀመጠዉ መደበኛ ጊዜም አልፎ ለዓመታት የተወዉ በመሆኑ በግልጽ መጋዘን መቆየት ከሚገባዉ ጊዜ በላይ በመቆየቱ በቆየታዉ በሂደታዊ ለዉጥ የተነሳ የደረሰ ጉዳት ካልሆነ በስተቀር ተጠሪ የፈጸመዉ ጥፋት የለም በማለት የሥር ፍርድ ቤት ክሱን ዉድቅ በማድረጉ የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡ይህ ታልፎ የተጠሪ ኃላፊነት አለበት የሚባል ከሆነ የተጠሪ ኃላፊነት በአዋጅ ቁጥር 588/2008 አንቀጽ 5/1 በወቅቱ በነበረዉ ምንዛሪ መሰረት ብር 226,320.00 ነዉ እንዲባልልኝና አመልካች የመጋዘን ኪራይ እንዲከፍል የተወሰነዉ እንዲጸናልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡አመልካችም የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለመልኩ የተመለከተዉ የግራ ቀኙ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም ሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉን ጭብጥ ከግምት በማስገባት በፎርክሊፍቱ ላይ ለደረሰዉ ጉዳት ተጠሪ ኃላፊነት የለበትም ተብሎ በስር ፍርድ ቤት በተሰጠ ዉሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ፎርክሊፍት ከዉጭ አገር አገር ዉስጥ ገብቶ ከቀን 25/06/2005ዓ/ም ጀምሮ ከ3 ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ በሞጆ ደረቅ ወደብ ላይ በተጠሪ ይዞታ ስር እያለ በፎርክሊፍቱ ላይ ጉዳት እንደደረሰበት ግራ ቀኙ አልተካካዱም፡፡በፎርክሊፍቱ ላይ ጉዳት ያደረሰዉ ምክንያት የፀሐይና የዝናብ መፈራረቅ እንደሆነም ግራ ቀኙ የተማመኑበት ነዉ፡፡ ግራ ቀኙን ያከራከረዉ አመልካች በፎርክሊፍቱ ላይ ጉዳት ሊደርስበት የቻለዉ ተጠሪ በጥንቃቄ ማስቀመጥ ሲገባዉ ፎርክሊፍቱን ሜዳ ላይ ጥሎ ፀሐይና ዝናብ እንዲፈራቅበት በማድረጉ ምክንያት ነዉ በማለት ያቀረበዉ ክርክር ነዉ፡፡ከዚህ አንጻር ተጠሪ ደግሞ ፎርክሊፍት በባህርዉ በደረቅ ወደብ በጊዜያዊ ክፍት መጋዘን የሚቀመጥ እቃ እንደሆነ

በመግለጽ፣ የጉምሩክ ኮሚሽን ፎርክሊፍቱ ከመነሻውም በትርፍነት አገር ውስጥ እንደገባ በፍተሻ በማረጋገጥ አመልካች አስፈላጊውን የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት በማስፈጸምና የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ከፍሎ እስከሚያጠናቅቅ ድረስ ፎርክሊፍቱ በጉምሩክ ጊዜያዊ መጋዘን ውስጥ እንዲቀመጥ የጉምሩክ ኮሚሽን በማዘዙና አመልካች ይህንን ግዴታውን ሳይወጣ ስለቆየ በጊዜ ርዝማኔ ሂደት በፎርክሊፍቱ ላይ ጉዳት ሊደርስበት ችሏል እንጂ በተጠሪ አያያዝ ጉድለት የደረሰ ጉዳት አይደለም በማለት ተከራክሯል። የስር ፍርድ ቤት ከላይ እንደተመለከተው ፎርክሊፍቱ ሊቀመጥ የሚችለው በጊዜያዊ መጋዘን እንደሆነ፣ በፎርክሊፍቱ ላይ ጉዳት የደረሰው አመልካች የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አስፈጽሞ ፎርክሊፍቱን ሳይወስድ ለአመታት በመቆየቱ ምክንያት ፎርክሊፍቱ ፀሐይና ዝናብ ተፈራርቆበት እንጂ በተጠሪ የጥንቃቄ ጉድለት ምክንያት አይደለም በማለት ክሱን ውድቅ በማድረግ ወስኗል።

ደረቅ ወደብ ለባለእቃው ስለሚኖረው ኃላፊነት ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 588/2000 አንቀጽ 4/1 ስር ማንኛውም ዕቃ በደረቅ ወደብ አስተዳደሩ ቁጥጥር ሥር እያለ ቢጠፋ፣ጉዳት ቢደርስበት... በኃላፊነት እንደሚጠየቅ ደንግጓል። በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4/3 ስር እንደተደነገገው ዕቃው የጠፋው ወይም ጉዳት የደረሰበት...በዕቃው ወይም በአጓጓዡ ጥፋት ወይም በዕቃው የተለየ ባህሪ ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑ ከተረጋገጠ የደረቅ ወደቡ ተጠያቂነት አይኖርበትም።በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4/2 መሰረት የተለየ ዉል ወይም ደንብ ከሌለ በስተቀር እቃ ማስረከብ ዘገየ የሚባለው በደረቅ ወደቡ በዉል ወይም በደንብ መሰረት በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን እንዲያስረክብ ጥያቄ ከቀረበለት ጊዜ ጀምሮ በ3 ቀን ጊዜ ውስጥ ማስረከብ ሳይችል ሲቀር እንደሆነ በግልጽ ተመልክቷል።በተያዘው ጉዳይ የክሱ ምክንያት ተጠሪ የፎርክሊፍት ርክክብ አዘግይቷል የሚል ባለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 4/2 ስር የተደነገገው የጊዜ ገደብ ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያለው አይደለም።በያዝነው ጉዳይ የክሱ ምክንያት በተጠሪ ጥፋት ምክንያት በደረቅ ወደብ እንዲቀመጥ በተደረገው ፎርክሊፍት ላይ ጉዳት ደርሷል የሚል ሲሆን በዚህ አዋጅ ላይ ደረቅ ወደቡ አንድ እቃ ለደረሰበት ጉዳት ኃላፊ የሚሆነው እቃው በወደቡ ምን ያህል ጊዜ ቢቆይ ነው ለሚለው ጥያቄ አዋጁ በግልጽ መልስ ስለማይሰጥ ለዚህ ነጥብ ምላሽ ለመስጠት የዚህን አዋጅ ተያያዥ የሆኑ ድንጋጌዎች ከጉምሩክ አዋጅ አግባብነት ካለው ድንጋጌ ጋር አገናዝቦ መመርመር ያስፈልጋል።በዚህ መሰረት ፎርክሊፍቱ ተጠሪ በሚቆጣጠረው ደረቅ ወደብ ላይ ከተቀመጠበት ከ2005ዓ/ም ጀምሮ በመሆኑ በዚህ ጊዜና እና ከዚህ ጊዜ በኋላ ፎርክሊፍቱ በተጠሪ ይዞታ ስር በቆየበት ጊዜ ተፈጻሚ ሲሆኑ የነበሩትን የጉምሩክ አዋጆች መሰረት በማድረግ መርምረናል።

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 2(10/ሀ) ስር በተመለከተዉ ትርጓሜ መሰረት ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ማለት ገቢ ዕቃዎች የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አፈጻጸም ተከናዉኖባቸዉ እስሚለቀቁ ወይም እንደሁኔታዉ ወደ ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን ወይም ወደ መንግስት የጉምሩክ መጋዘን እስኪዛወሩ... በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ሆነዉ የሚቆዩበት ዝግ ወይም ክፍት የእቃ ማከማቻ ሥፍራ ሲሆን ደረቅ ወደብን እንደሚጨምር ተመልክቷል፡፡ለ"ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ" ከዚህ አዋጅ በፊት ተፈጻሚ ሲሆን በነበረዉ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 2/29 ላይ ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ትርጓሜ ተሰጥቶታል፡፡ በያዝነዉ ጉዳይ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ፎርክሊፍት አገር ዉስጥ እንደገባ ተጠሪ ፎርክሊፍቱን በሞጆ ደረቅ ወደብ በጊዜያዊ ክፍት ማከማቻ ስፍራ እንዳስቀመጠና በባህሪዉም ፎርክሊፍት መቀመጥ ያለበት በክፍት የዕቃ መጋዘን(ማከማቻ ስፍራ) ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ተጠሪ ፍርክሊፍቱን በሜዳ ላይ ጥሎ ፀሐይና ዝናብ እንዲፈራረቅበት አድርጓል በሚል ከመግለጽ ባለፈ ፎርክሊፍቱ በክፍት የዕቃ ማከማቻ ስፍራ መቀመጥ አልነበረበትም በማለት መቀመጥ ያለበትን ስፍራ በመግለጽ በማስረጃ አስደግፎ ያቀረበዉ ክርክር የለም፡፡በመሆኑም በዚህ ረገድ የስር ፍርድ ቤት የተጠሪን ክርክር በመቀበል ፎርክሊፍቱ ባለዉ አሰራር መሰረት በጊዜያዉ ክፍት የዕቃ ማከማቻ ስፍራ እንዲቀመጥ እንደሚደረግ አረገገጫለሁ ሲል የደረሰበት ድምዳሜ ተገቢ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ዕቃዎች በጉምሩክ መጋዘን (የጉምሩክ መጋዘን ማለት በአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 2/9 ትርጓሜ መሰረት ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻን ይጨምራል) ዉስጥ ስለሚቆዩበት ጊዜ በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 28/1 እና በአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 51/1 ስር ተደንግጓል፡፡በእነዚህ ተጠቃሾቹ አዋጆች ድንጋጌዎች ስር እንደተመለከተዉ ማንኛዉም በባህር ወይም በየብስ ተጓጉዞ አገር ዉስጥ የገባ ዕቃ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ከገባበት ቀን ጀምሮ በ2 ወር ጊዜ ዉስጥ (ይህ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 859/2006ን ባሻሻለዉ አዋጅ ቁጥር 1160/2011 ላይ 15(አስራ አምስት) ቀናት ሆኖ ተሻሽሏል) አስፈላጊዉ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ተከናዉኖበት ከማከማቻዉ ማዉጣት አለበት፡፡በዚህ ጊዜ ዉስጥ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ከተከናወነ በኋላ በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 28/5 እና በአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 51/6 መሰረት ከ7 የሥራ ቀናት በላይ (ይህ ጊዜ በአዋጅ ቁጥር1160/2011 ላይ 2 የሥራ ቀናት ሆኖ አጥሯል) በማከማቻ ስፍራ እቃዉ ሊቀመጥ እንደማይችል

ተደንግጓል፡፡ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ፎርክሊፍት በተጠሪ በሚተዳደረዉ በሞጆ ደረቅ ወደብ ጊዜያዊ ክፍት የዕቃ ማከማቻ ስፍራ እንዲቀመጥ በተደረገበት በ2005 ዓ/ም እና ከዚህ በኋላ በተጠሪ ይዞታ ስር በቆየበት ጊዜ ተፈጻሚ ሲሆኑ በነበሩት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 28/1 እና በአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 51/1 መሰረት ዕቃዉ በማከማቻ ስፍራዉ ሊቀመጥ የሚችለዉ ለ60 ቀናት ብቻ እንደሆነ ነዉ፡፡ ዕቃዉ(ፎርክሊፍቱ) በጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ስፍራ(መጋዘን) የሚቀመጥበትም ዓላማ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት እንዲፈጸምበት እና ይህ ሥነ ሥርዓት ተፈጽሞ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ዕቃዉ በጉምሩክ ባለስልጣን ቁጥጥር ሥር መሆን ስላለበት ነዉ፡፡

እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 51/7 ስር ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ... የገባ የጉምሩክ ዕቃ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1... ስር በተመለከተዉ ጊዜ ዉስጥ ካልወጣ ወደ መንግስት የጉምሩክ መጋዘን እንዲዛወር እንደሚደረግ ተደንግጓል፡፡በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2/13 ትርጓሜ መሰረት የመንግስት መጋዘን ማለት ደግሞ የጉምሩክ ሕግን በመተላለፍ የተያዙ ወይም የተወረሱ እንዲሁም የተተዉ ዕቃዎች በሽያጭ ወይም በሌላ ሁኔታ እስከሚወገዱበት ጊዜ ድረስ በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ሆነዉ የሚከማቹበት መጋዘን ነዉ፡፡ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ፎርክሊፍት በጉምሩክ ኮሚሽን በተደረገ ፍተሻ በትርፍነት የተገኘ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡እንዲሁም ፎርክሊፍቱ በትርፍነት የተገኘ መሆኑን በመግለጽ የጉምሩክ ኮሚሽን ፎርክሊፍቱ በሞጆ ደረቅ ወደብ እንዲቀመጥ ወስኗል በማለት ተጠሪ በማስረጃ አስደግፎ ያቀረበዉን ክርክር አመልካች ክዶ አልተከራከረም፡፡ በትርፍነት የተገኘ እቃ በአዋጁ አንቀጽ 53 እና 143/2 ስር እንደተደነገገዉ የጉምሩክ ሕግ የመተላለፍ ድርጊት እንደተፈጸመበት የሚቆጠር በመሆኑ እቃዉ በጉምሩክ ባለሥልጣኑ እንዲያዝና ከዚህ እቃ የሚፈለግ ቀረጥና ታክስ ባለዕቃዉ ወዲያዉ እንዲከፍል የሚያስገድደዉ ነዉ፡፡

በተጨማሪም ይህ ምክንያት ዕቃዉ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት በመተላለፍ እንደገባ የሚያስቆጥረዉ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆነ በአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 51/1 ስር በተመለከተዉ 60 ቀናት ጊዜ ዉስጥ አመልካች ለፎርክሊፍቱ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አስፈጽሞ እና የሚጠበቅበትን ቀረጥና ታክስ ከፍሎ ፎርክሊፍቱ እንዲሰጠዉ ሳይጠይቅ ከ3 ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ መቆየቱ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ይህ የአመልካች አድራጎት በአዋጅ ቁጥር 588/2000 አንቀጽ 6/1 እና በአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 51/7 እና 61(2/ሀ) መሰረት ፎርክሊፍቱን እንደተወ ጭምር ሊያስቆጥር የሚችል በመሆኑ፣የተተወ እቃ ደግሞ

በሽያጭ ወይም በሌላ በሕግ በተፈቀደዉ መንገድ ማስወገድ ያለበት የጉምሩክ ኮሚሽን በመሆኑ ኮሚሽኑ ይህንን ሳያደርግ በመቆየቱ ተጠሪ ተጠያቂ የሚሆንበት ሕጋዊ ምክንያት ባለመኖሩ፣ አመልካች በሕጉ በተመለከተዉ ጊዜ ዉስጥ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አስፈጽሞና ተገቢዉን ታክስና ቀረጥ ከፍሎ ሳይረከብ የተወዉን ፎርክሊፍት ላልተወሰነ ጊዜ ተጠሪ ፎርክሊፍቱ ጉዳት እንዳይደርስበት አድርጎ መጠበቅ የሚችልበት የሕግም ሆነ የዉል ግዴታ የለበትም፡፡

እንዲሁም በግራ ቀኙ መካከል የተፈጠረዉ ግንኙነት የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ግንኙነት ላይ የተመሰረተ የዉል ግንኙነት ቢሆንም የጊዜ ገደብ ለሌለዉ ጊዜ እቃዉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት ለመጠበቅ አመልካች የዉል ግዴታ እንዳለበት አመልካች ዉል ጠቅሶ ያቀረበዉ ክርክር የለም፡፡የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 548/1999ም ይህንን ግዴታ በተጠሪ ላይ አይጥልም፡፡በግራ ቀኙ መካከል የዉል ግንኙነት መኖሩ አከራካሪ ባይሆንም የግራ ቀኙ ኃላፊነት የሚወሰነዉ ከላይ በተጠቀሱት ልዩ ሕግጋት በመሆኑ አመልካች በሰበር አቤቱታዉ ላይ ከተጠሪ ጋር የአደራ ዉል ግንኙነት አለን በማል የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2718 እና ተከታዮቹን ድንጋጌዎች ጠቅሶ ያቀረበዉ ክርክር ለተያዘዉ ጉዳይ ተፈጻሚነት ያላቸዉ አይደሉም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል በጉምሩክ አዋጁ ላይ በጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ስፍራ አንድ ዕቃዉ ተቀምጦ ሊቆይ የሚችልበት ጊዜ ለዉስን ቀናት ብቻ እንዲሆን ከተደነገገበት ዓላማዎች ዉስጥ ዋናዎቹ ዓላማዎች ለረጅም ጊዜ ዕቃዉ በጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ በተለይም በክፍት መጋዘን ተቀምጦ የሚቆይ ከሆነ በዉጭ ምንዛሪ ተገዝቶ አገር ዉስጥ በገባ ዕቃ ላይ ጉዳት ስለሚደርስ በዕቃዉ ላይ የሚደርሰዉን ጉዳት ለመቀነስ እና ዕቃዉ በሕጉ በተመለከተዉ ጊዜ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ተፈጽሞበት ለታለመለት አገልግሎት እንዲዉል በማድረግ ለአገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጠቀሜታ እንዲሰጥ ለማስቻል ነዉ፡፡ ከዚህ ጊዜ በላይ ተጠሪ የመጋዘን ኪራይ ስለሚያስከፍል እቃዉን ከክፍት መጋዘን አንስቶ በዝግ መጋዘን ማስቀመጥ አለበት ተብሎ የሚገደድ ከሆነ ተጠቃሾቹ ዓላማዎች ከግብ እንዳይደርሱ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ የእቃዉ ዓይነት ምንም ይሁን ምን ዕቃዉን በዝግ መጋዘን ባለማስቀመጥህ እቃዉ ላይ ጉዳት ደርሷል ተብሎ ተጠሪ ካሳ እንዲከፍል የሚደረግ ከሆነ በጉምሩክ አዋጁ ላይ የተቀመጠዉ የጊዜ ገደብ ዉጤት እንዲያጣ የሚያደርግ ይሆናል፤በተጠሪም ላይ በሕግ ያልተመለከተ ግዴታ መጣል ስለሚሆን የሕግ ድጋፍ አይኖረዉም፡፡ከዚህ አንጻር ሲታይ የሥር ፍርድ ቤት ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ ፎርክሊፍት ላይ ጉዳት ሊደርስበት የቻለዉ አመልካች በሕግ በተመለከተዉ ጊዜ ዉስጥ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት በማስፈጸም እና አስፈላጊዉን ቀረጥና ታክስ ከፍሎ መረከብ

ባለመቻሉ ፎርክሊፊቱ በተቀመጠበት ጊዜያዊ ክፍት ማስቀመጫ ቦታ ለፀሐይና ዝናብ በመጋለጡ ምክንያት እንጂ በተጠሪ የአያያዝ ጉድለት አይደለም በማለት የደረሰዉ ድምዳሜ የሕግ መሰረት ያለዉ ነዉ፡፡በመሆኑም በፎርክሊፍቱ ላይ ጉዳት የደረሰዉ በአመልካች(በባለዕቃዉ) ጥፋት በመሆኑ ለደረሰዉ ጉዳት ተጠሪ ኃላፊነት የለበትም ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች በተሰጠ ዉሳኔ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል የተፈጸመ ስህተት ባለመኖሩ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ዉ ሳ ኔ</u>

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 19086 ላይ በቀን 18/10/2012 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 195675 ላይ በቀን 11/06/2013 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ፀንተዋል፡፡

ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ደረጃ ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ብለናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
በመዝገቡ ላይ የተሰጠ የዕግድ ትእዛዝ ካለ ተነስቷል፤ይጻፍ፡፡መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ባንክ፣ንግድና እንሹራንስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰ/መ/ቁጥር 216672

ግንቦት 1 **ቀን** 2014 **ዓ/ም**

ዳኞች ፡- **ብርሀኑ አመነው**

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- ወ/ሮ ወርቅነሽ ጀቤሳ - ቀረቡ

ተጠሪዎች ፡- 1ኛ. የኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ አክስዮን ማህበር - የቀረበ የለም

2ኛ. አቶ ሚካኤል ማሙዬ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ክርክሩ ከባንክ ለተወሰደ ብድር በመያዣነት የተያዘ ቤት ሽያጭ ውል ይፍረስልኝ ክስ በፍርድ ቤት ሊቀርብ የሚችልበትን ሁኔታ የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩ በተጀመረበት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ፤ ተጠሪዎች እንደየቅደም ተከተላቸው 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ነሐሴ 30 ቀን 2011 ዓ.ም ዕፈው ባቀረቡት ክስ በአመልካች እና በአቶ በቀለ ገመዳ ዲኖ መካከል የነበረው ጋብቻ ጥር 30 ቀን 2008 ዓ.ም በፍቺ የፈረሰ ሲሆን በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 ውስጥ የሚገኝ የቤት ቁጥሩ አዲስ፤ የካርታ ቁጥሩ 10/80/50-2917/11 የሆነን ቤት እኩል እንድንካፈል እና ቤቱን አስይዘን ከ1ኛ ተጠሪ የተበደርነውን ገንዘብ እንድንከፍል የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 37020 በጥቅምት 03 ቀን 2009 ዓ.ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚሁ መሰረት በመዝገብ ቁጥር 118877 የአፈጻፀም ክስ አቅርቤ ቤቱ በሐራጅ ተሸጦ የባንኩ እዳ ከተከፈለ በኋላ የሚቀረውን ገንዘብ እኩል እንድንካፈል ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡ የቀድሞ ባለቤቴ በ2007 ዓ.ም የወሰዱት በ3 ዓመት ነሐሴ 2010 ዓ.ም ተከፍሎ የሚያልቅ ብድርን በየወሩ ሳናቋርጥ ስንከፍል የቆየን ቢሆንም ተጠሪዎች በተጠቀሱት መዝገቦች የተሰጡትን ውሳኔዎች ወደ ጎን በመተው፤ 1ኛ ተጠሪ ለአመልካች ምንም አይነት ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ ቤቱን በጥቅምት 15 ቀን 2009 ዓ.ም ለ2ኛ ተጠሪ በብር 4,250,000.00 መሸጡን ታህሳስ 6 ቀን 2009 ዓ.ም በፍርድ ቤት ችሎት ላይ ለማወቅ ችያለው፡፡ የሽያጭ ውሉ 1ኛ አመልካች ስልጣኑን ያለአግባብ በመጠቀም የተፈጸመ፤ ለሕግ እና ሞራል ተቃራኒ ስለሆነ ውሉ ፈርሶ ቤቱን በአንድነት እና በነጠላ ለአመልካች እንዲያስረክቡ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ መጋቢት 16 ቀን 2013 ዓ.ም ዕፎ ባቀረበው መልስ አመልካች እና የቀድሞ ባለቤታቸው የወሰዱትን ብድር ባለመክፈላቸው መጋቢት 24 ቀን 2008 ዓ.ም በቁጥር ኦኢባ/የቅ/አዋ/405/08 የተፃፈ የ30 ቀን ማስጠንቀቂያ በመስጠት በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀፅ 3 እና በውሉ አንቀፅ 15 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ለ3ኛ ጊዜ በጋዜጣ በወጣ የሀራጅ ማስታወቂያ ቤቱን ለ2ኛ ተጠሪ መሸጡ ህጋዊ ስለሆነ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ስልጣን የለውም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡

2ኛ ተጠሪም መጋቢት 16 ቀን 2013 ዓ.ም ዕፈው ባቀረበው መቃወሚያ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም፤ 1ኛ ተጠሪ በሕግ እና በውል በተሰጠው ስልጣን መሰረት ቤቱን የሸጠ ስለሆነ 2ኛ ተጠሪ ልከሰስ አይገባም፤ ክሱ የክስ ምክንያት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም መቃወሚያውን መርምሮ በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት ባንኮች ለብድር አመላለስ በዋስትና የያዙትን ንብረት በሀራጅ መሸጥ የሚችሉ መሆኑ ተመላክቷል፡፡ ሽያጩ የሐራጅ ስርዓቱን አልተከተለም የሚባል ከሆነ ካሳ ከሚጠየቅ በቀር በመደበኛ ፍርድ ቤት ክስ

የሚቀርብበት አለመሆኑን በሰ/መ/ቁጥር 13914 ውሳኔ የተሰጠበት ስለሆነ ጉዳዩ ላይ ለመወሰን ስልጣን የለኝም በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ይግባኛቸውን ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ተሰርሟል፡፡

አመልካች ህዳር 14 ቀን 2014 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታቸውን ያቀረቡት ይህን የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአቤቱታው ይዘት ባጭሩ በአመልካች እና በቀድሞ ባለቤቱ አቶ በቀለ ገመዳ መካከል በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 37020 በነበረው ክርክር ጥቅምት 3 ቀን 2009 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ የባንኩ እዳ ተከፍሎ ቤቱን እኩል እንድንካፈል ውሳኔ የተሰጠ በመሆኑ የመያዣ ውሉ በሁኔታ ስለፈረሰ 1ኛ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 90/97 መሰረት ተጠቃሚ ሊሆን ስለማይገባ ጉዳዩ በመደበኛ ፍርድ ቤት ሊታይ ይገባል፡፡ የ1ኛ ተጠሪ መብት ቀሪ አልሆነም ቢባል እንኳ የብድር ውሉን ሳናቋርጥ በየወሩ እየከፈልን እያለ፤ ማስጠንቀቂያ ሳይሰጠን የክፍያ ጊዜው ከማብቃቱ ነሐሴ 2010 ዓ.ም በፊት ጥቅምት 15 ቀን 2009 ዓ.ም እና በፍርድ ቤት ውሳኔ ካረፈበት በኋላ መሸጡ በአዋጅ ቁጥር 97/90 ከተሰጠው ስልጣን ውጪ ስለሆነ ጉዳዩ በመደበኛ ፍርድ ቤት የሚታይ ነው፡፡ የአመልካች ዋና የዳኝነት ጥያቄ ሀራጁ የሀራጅ ስርዓትን አልተከተለም የሚል ሳይሆን ከላይ በተገለጹት ምክንያቶች ከጅምሩ የሽያጭ ውሉ መከናወኑ አግባብ አይደለም ሊፈርስ ይገባል የሚል በመሆኑ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለኝም በማለት በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚል ነው፡፡

አቤቱታው በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ አመልካች ተጠሪ ጨረታ ሳያወጣ የሸጠው የቤት ሽያጭ ውል እንዲፈርስ ያቀረቡትን ክስ የስር ፍርድ ቤት አዋጅ ቁጥር 97/90ን በመጥቀስ ጉዳዩን ለመዳኘት ስልጣን የለኝም በማለት ውድቅ ያደረገበትን አግባብ ከአዋጅ ቁጥር 97/90 እና ከቀረበው የክርክር ጭብጥ አኳያ ሊመረመር ይገባዋል በማለት ተጠሪዎች መልሳቸውን እንዲያቀርቡ አዟል፡፡

1ኛ ተጠሪ ጥር 13 ቀን 2014 ዓ.ም ፅፎ ባቀረበው መልስ በአመልካች፣ የቀድሞ ባለቤታቸው እና በ1ኛ ተጠሪ መካከል መስከረም 19 ቀን 2007 ዓ.ም በተፈረመ የብድር ውል ቤቱን በመያዣነት በመያዝ በየ3 ወሩ ተከፍሎ መስከረም 18 ቀን 2010 ዓ.ም የሚጠናቀቅ ብር 800,000 ያበደረ ቢሆንም ብድሩን መክፈል አልቻሉም፡፡ በዚህም ምክንያት በተለያዩ ጊዜያት ብድሩን እንዲከፍሉ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ መክፈል ባለመቻላቸው በመጨረሻ መጋቢት 24 ቀን

2008 ዓ.ም በቁጥር ኦኢባ/አዋ/405/08 የ30 ቀን ማስጠንቀቂያ ከሰጠ በኋላ በጋዜጣ የሀራጅ ማስታወቂያ አስነግሮ ለ3ኛ ጊዜ የወጣው የሀራጅ ማስታወቂያም 30 ቀን አየር ላይ ከቆየ በኋላ ቤቱን በሐራጅ መሸጡ ተገቢ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ማስረጃ መርምሮ በጨረታ ሒደቱ የተፈጸመ ጉድለት አለመኖሩን አረጋግጦ 1ኛ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 3 እና በብድር ውሉ አንቀጽ 15 በተሰጠው ስልጣን መሰረት የተደረገ ሽያጭ ስለሆነ ጉዳዩን ለማየት የስረ ነገር ስልጣን የለኝም ማለቱ ተገቢ ነው፡፡ ለብድር አመላለስ የተያዘን ንብረት የሀራጅ አሻሻጥን እና የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ የሚቀርብ ክስን መደበኛ ፍርድ ቤቶች የመዳኘት ስልጣን የሌላቸው መሆኑን የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 84353 ቅፅ 14 ላይ ውሳኔ የሰጠበት ስለሆነ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተገቢ ነው፡፡ 1ኛ ተጠሪ ጨረታ ሳያወጣ ቤቱን ቢሸጥ እንኳ አመልካች ካሳ ከሚጠይቁ በቀር የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ ሊጠይቁ አይችሉም፡፡ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 37020 ጥቅምት 3 ቀን 2009 እንዲሁም በመዝገብ ቁጥር 118877 ታህሳስ 6 ቀን 2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ የ1ኛ ተጠሪን የቅድሚያ መብት እውቅና የሚሰጥ እንጂ የመያዣ ውሉን የሚያፈርስ ባለመሆኑ አቤቱታው ተገቢነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

2ኛ ተጠሪ በበኩሉ ጥር 13 ቀን 2014 ዓ.ም ፅፎ ባቀረበው መልስ አመልካች እና ባለቤታቸው ከ1ኛ ተጠሪ ለተበደሩት ገንዘብ አከራካሪ የሆነው ቤት በዋስትና ያስያዙ ሲሆን ብድሩን መክፈል ባለመቻላቸው ምክንያት 1ኛ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 97/90፤98/90 እና 216/98 በተሰጠው ስልጣን መሰረት እንደአስፈላጊነቱ በፍሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 394-449 ድንጋጌዎች መሰረት የጨረታ ሒደቱ ተከናውኖ ቤቱን የገዛውት ስለሆነ የሽያጭ ውሉ ሊፈርስ አይገባም፡፡ ባንኩ ሕጉን አልተከተለም ቢባል ባንኳ አመልካች ካሳ ከሚከፈላቸው በቀር በፍርድ ቤት ሀራጁ ሊቆም ስለማይገባ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተገቢ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካች በበኩላቸው የካቲት 3 ቀን 2014 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠውን ውሳኔ አግባብነት በስር ፍርድ ቤት ከተደረጉ ክርክሮች፤ በማስረጃ ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች እንዲሁም ለጉዳዩ ተገቢነት ካለው የሕግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች በዋናነት የሚከራከሩት በአመልካች እና የቀድሞ ባለቤታቸው መካከል ያለው ጋብቻ ከፈረሰ በኋላ ቤቱን እኩል እንድንካፈል እና ብድሩን እንድንከፍል በመወሰኑ የመያዣ ውሉ በሁኔታ ፈርሷል፤ አልፈረሰም ቢባል እንኳ የብድር ገንዘቡን በውሉ መሰረት በየወሩ እየከፈልን እያለ ማስጠንቀቂያ ሳይሰጠን ከብድሩ ማብቂያ ጊዜ ነሐሴ 2010 ዓ.ም በፊት ቤቱ በሀራጅ የተሸጠ ስለሆነ ውሉ እንዲፈርስ የቀረበውን ክስ የስር ፍርድ ቤት ስልጣን የለኝም በማለት ውድቅ ማድረጉ ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡ 1ኛ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች እና የቀድሞ ባለቤታቸው በብድር ውሉ መሰረት ክፍያውን ባለመፈጸማቸው ክፍያውን እንዲፈጽሙ በተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸው ባለመፈጸማቸው በመያዣነት የተያዘውን ንብረት በሐራጅ መሸጡ በአዋጅ ቁጥር 97/90 እና በውሉ አንቀፅ 15 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፤ ጨረታው ጉድለት ቢኖርበት እንኳ ካሳ ከሚጠይቁ በቀር ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ 2ኛ ተጠሪም ይህን የ1ኛ ተጠሪን ክርክር በሚያጠናክር መልኩ መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

የማይንቀሳቀስ ንብረትን በዋስትና የያዘ ባለገንዘብ ባንክ የሚፈልገው እዳ እንዲከፈል በተወሰነው ጊዜ ሳይከፈለው ቢቀር ከ30 ቀናት ያላነሰ ማስጠንቀቂያ ለባለእዳው በመስጠት በመያዣነት የያዘውን የማይንቀሳቀስ ንብረት በሐራጅ ለመሸጥ እና ባለቤትነቱን ለገዢው ማስተላለፍ የሚችል ስለመሆኑ ይህንንም ሲያደርግ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 394-449 የተመላከቱ ድንጋጌዎችን ተግባራዊ ማድረግ ያለበት እና እነኚሕንም ድንጋጌዎች በመተላለፍ ለሚደርስ ጉዳት ለባለንብረቱ ካሳ የመክፈል ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀፅ 3 እና 6 ላይ ተመላክቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይ በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 ውስጥ የሚገኝ የቤት ቁጥሩ አዲስ የካርታ ቁጥሩ 10/80/50-2917/00 የሆነውን ቤት አመልካች እና የቀድሞ ባለቤታቸው የጋራ ንብረት መሆኑ፤ ይህንንም ቤት በመያዣነት ለ1ኛ ተጠሪ አስይዘው መስከረም 19 ቀን 2007 ዓ.ም በተደረገ የብድር ውል ከ1ኛ ተጠሪ ባንክ ገንዘብ መበደራቸው እና 1ኛ ተጠሪ ብድሩ አልተከፈለም በሚል በሐራጅ ጨረታ ቤቱን ለ2ኛ ተጠሪ መሸጡ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡ አመልካች ክስ ያቀረቡት ቤቱ በእዳ ምክንያት የተሸጠው የእዳው የመጨረሻ የመክፈያ ጊዜ ሳይደርስ እና ማስጠንቀቂያ ሳይሰጠኝ በመሆኑ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ያደረጉት የሽያጭ ውል ይፍረስልኝ በሚል ነው፡፡ በመሠረቱ ባንክ በመያዣ የያዛቸውን ንብረቶች በሐራጅ መሸጥ እንደሚችል በአዋጅ ቁጥር 97/90፣ 98/90 እና 216/92 ተመላክቷል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 3 እና 4 መሠረት

እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 216/92 በተደረገው ማሻሻያም ባንኮች ለሰጡት ብድር አከፋፈል በመያዣነት የተቀበሉትን ንብረት የብድር እዳው እንዲከፈለው በተወሰነው ጊዜ ሳይከፈል ከቀረ ከ30 ቀናት ያላነሰ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የመያዣ ንብረቱን በሐራጅ ለመሸጥና ባለቤትነቱንም ለገዥው ለማዘዋወር ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል። ባንኮች ይህንን በሚያደርግቡት ጊዜም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ.394-449 ያሉትን ድንጋጌዎች እንደአስፈላጊነታቸው ተግባራዊ ማድረግ ያለባቸው መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 97/90 በአንቀጽ 6 ላይ ተመላክቷል። ከአዋጁ ድንጋጌዎችም መረዳት የሚቻለው በአበዳሪው ባንክ በዋስትና የተያዘው ንብረት በሀራጅ ከመሸጡ በፊት የብድር ገንዘቡ በመክፈያ ጊዜው ያልተከፈለ መሆኑን ማረጋገጥ እንዳለበት እንዲሁም ይህን ተከትሎ ባንኩ ተበዳሪው የብድር ገንዘቡን እንዲመልስ የ30 ቀን ማስጠንቀቂያ የሰጠ መሆኑን ማረጋገጥ እንዳለበት ነው። ይህ መሆኑ ከተረጋገጠ ባንኩ ያለማንም ጣልቃ ገብነት አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን በመከተል በሐራጅ ሽጦ ለእዳው ክፍያ ማዋል የሚችል ሲሆን በአሻሻጡ ሂደት ባንኩ ሕጉን ባለመከተል የፈፀመው ስህተት ቢኖር እና በዚህም ባለዕዳው ላይ ጉዳት ቢደርስ ለዚህ ጉዳት ባንኩ ለባለእዳው ካሣ የመክፈል ኃላፊነት አለበት። ባለእዳው ባንኩ ያከናወነው የሐራጅ ጨረታ ጉድለት አለበት የሚል ከሆነም ካሳ እንዲከፈለው ክስ ለማቅረብ መብት እና ጥቅም ያለው ሲሆን የሀራጅ ጨረታው ወይም የሽያጭ ውሉ ይፍረስልኝ በሚል ክስ ለማቅረብ ግን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 33/3 እና 231/1/ሀ መሰረት የክስ ምክንያት አይኖረውም። ከዚህ ጋር በተያያዘም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 84353 በቅጽ 14 እንደታተመው የህግ ትርጉም ተሰጥቶበታል። በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን ክስ የክስ ምክንያት አለው ወይስ የለውም? ከሚለው አንጻር መመርመር ሲገባው ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም በሚል ምክንያት ክሱን ውድቅ ማድረጉ ሊታረም የሚገባው መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው።

በመቀጠል የአመልካች ክስ የክስ ምክንያት አለው የለውም የሚለውን ስንመለከት አበዳሪ ባንክ በመያዣ የያዘውን ንብረት በእዳው ምክንያት ከመሸጡ በፊት የ30 ቀን ማስጠንቀቂያ መስጠት እንዳለበት እና እዳውም የበሰለ ወይም የመክፈያ ጊዜው የደረሰ መሆን እንዳለበት በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 3 እና 4 ላይ ተመልክቷል። ይህም ማለት ባንኩ በመያዣ በያዘው ንብረት ላይ የሐራጅ ጨረታ በማውጣት ከመሸጡ በፊት ይህንን በህግ የተጣለበትን ግዴታ መወጣት ይኖርበታል። ነገር ግን ባንኩ የእዳው መክፈያ ጊዜ ከመድረሱ በፊት ንብረቱን በጨረታ የሸጠ ከሆነ የውል ጥሰት ተግባር እንደፈጸመ ይቆጠራል። ባንኩ በመያዣ የያዘውን ንብረት በጨረታ ሽጦ እዳውን የመሰብሰብ መብት የሚኖረው ውሉን ካከበረ እና ተበዳሪው በብድር ውሉ

በተመለከተው አግባብ የሚጠበቅበትን እዳ መክፈል ካልቻለ ነው። ከዚህ ውጪ ባንኩ መያዣ ሰጪው በውሉ መሰረት እዳውን የሚከፍልበት ጊዜ እና ሁኔታ አለማክበሩን ወይም መጣሱን ሳያረጋግጥ በመያዣ የያዘውን ንብረት በሀራጅ የሸጠ እንደሆነ ይህ ተግባር የውል ጥሰት ስለሚሆን እና መያዣ ሰጪው ከህግ ውጪ የባለቤትነት መብቱን ሊያጣ ስለማይገባ በመደበኛ ፍርድ ቤት የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ ክስ የማቅረብ መብት እና ጥቅም ይኖረዋል። በተያዘው ጉዳይ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ካደረጉት ክርክር እና ካቀረቡት የሰበር አቤቱታ መገንዘብ የሚቻለው ዋና የዳኝነት ጥያቄያቸው በአመልካች፣ በቀድሞ ባለቤታቸው እንዲሁም በ1ኛ ተጠሪ መካከል በተደረገው የብድር ውል መሰረት በየወሩ ክፍያ እየፈፀምን ቢሆንም የብድር መክፍያ ጊዜው ከሚጠናቀቅበት ነሐሴ 2010 ዓ.ም በፊት 1ኛ አመልካች ማስጠንቀቂያ ሳይሰጠኝ ቤቱን በሐራጅ መሸጡ ተገቢ አይደለም የሚል ነው። ይህም የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ከመነሻው ብድሩን እየከፈልኩ ባለሁበት ቤቱ በጨረታ መሸጡ አግባብ አይደለም የሚል እንጂ 1ኛ ተጠሪ ጨረታውን ሲያካሒድ በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀፅ 6 እንዲሁም አዋጁን ባሻሻለው አዋጅ ቁጥር 216/92 መሰረት የጨረታ ስርዓቱን አልተከተለም ወይም በፍ/ሥ/ሥ/ሕጉ በተደነገገው አግባብ አልተከናወነም የሚል አይደለም። በመሆኑም ዋናው የክርክሩ ጭብጥ ቤቱ በሀራጅ የተሸጠው አመልካች እዳቸውን ያለማቋረጥ እየከፈሉ ባለበት ነው ወይስ አይደለም? 1ኛ ተጠሪ ቤቱን በሐራጅ የሸጠው የእዳው መክፈያ ጊዜ ሳያልቅ ነው የሚባል ከሆነ የሽያጭ ውሉን ለማፍረስ በቂ ምክንያት ነው ወይስ አይደለም? የሚለው በፍሬ ነገር ደረጃ በሚደረግ ክርክር እና በሚቀርቡ ማስረጃዎች በማረጋገጥ በመደበኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባ (justiciable matter) እና የክስ ምክንያት ያለው ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤት ለተያዘው ጉዳይ ተገቢነት የሌለውን የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ጠቅሶ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠውን ውሳኔ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ማጽናቱ መሰረታዊ የህግ አፈጻጸም እና አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ተከታዩን ወስነናል።

ው ሳ ኔ

1.የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 241914 ግንቦት 17 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 209328 ጥቅምት 19 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽሯል።

2.የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቁጥሩ 241914 የሆነውን መዝገብ አንቀሳቅሶ ከላይ በፍርዱ ውስጥ በተገለጸው አግባብ በተጠሪዎች መካከል የተደረገው የሽያጭ ውል ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን አከራክሮ ተገቢውን እንዲወስን መዝገቡን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሰረት በነጥብ መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡

3.በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ. 211694

የካቲት 28 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- አቶ ታደሰ ዓለምሰገድ-- ጠበቃ ዉብሸት ደምሴ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ቡና ኢንተርናሽናል ባንክ አ/ማ -- ነ/ፈጅ ታደለ ቤዛ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

የሰበር አቤቱታ የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ፤ ተጠሪ ተከሳሽ ነበር፡፡ አመልካች ታህሳስ 01 ቀን 2013 ዓ/ም በተጻፈ ክስ በአመልካችና በአማራ ክልል የውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ልማት ቢሮ መካከል ነሀሴ 12 ቀን 2010 ዓ/ም የተደረገ

የግንባታ ውል ያለ ሲሆን ለቅድመ ክፍያው አመላለስ ቅድመ ክፍያው ከግንባታው ሥራው ዓላማ ውጭ ከዋለ ወይም በግንባታ ውሉ መሠረት ዋስትና የተገባለትን ቅድመ ክፍያ ካልመለሰ የሚከፈል የዋስትና ግዴታ ተጠሪ ለአሠሪው ሰጥቷል፡፡ የዋስትና ግዴታው ከግንባታው ውል አፈጻጸም ጋር ግንኙነት የሌለው ነው፡፡ ተጠሪ በዋስትና ግዴታው ላይ የተመለከቱ ሁኔታዎችና መስፈርቶች መሟላት አለመሟላታቸውን ሳይመረምር አሠሪው የግንባታ ሥራው ባለመሰራቱና ሊሰራ ስለማይችል በሚል በዋስትና የተመለከተው ገንዘብ እንዲከፈለው ሲጠይቀው ተጠሪ ብር 20,551,492.40 ከፍሏል፡፡ ክፍያው የተፈጸመው ከዋስትና ሰነዱ በማይስማማ ጥያቄና ከቅድመ ክፍያው ውል ድንጋጌ ውጭ በመሆኑ አመልካች የማይገደድበት ስለሆነ ውልና ተግባሩ ፈርሶና ተሰርዞ ለዋስትና ግዴታው ለተጠሪ ባንክ የተሰጠ ኮሚሽን እንዲመለስ፣ እንዲሁም በተሰጡ ዋስትናዎች አመልካች የማይገደድ ነው ተብሎ ዋጋ አልባ ወይም ፈራሽ ናቸው ተብሎ እንዲፈርሱ/እንዲሰረዙ እና ወደነበርንበት እንድንመለስ እንዲወሰን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች ክሱን ካቀረቡ በኋላ ታህሳስ 07 ቀን 2013 ዓ/ም በተጻፈ ማመልከቻ በሁኔታ ላይ የተመሰረተ የዋስትና ግዴታውን ባላከበረ መልኩ ክፍያውን ተጠሪ ከፈጸመ በኋላ ለዋስትና ግዴታው የተሰጡ መያዣዎችን ለመሸጥ የሐራጅ ማስታወቂያ ስላወጣ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 154 እና 155 እንዲታድ መጠየቁን ተከትሎ እግድ የተሰጠ ሲሆን ተጠሪ እግዱ እንዲነሳ በመጠየቁ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባንክ በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት ያወጣው ሀራጅ ሊቆም አይችልም በማለት የእግድ ትዕዛዙን አንስቷል፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔ ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን፣ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት የአመልካችን ይግባኝ ባለመቀበል ሠርዟል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚህ ዉሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታው ይዘትም የዋስትና ግዴታው እንዲፈርስ ክስ አቅርበን እያለ፤ ለዚህ የዋስትና ግዴታ የተሰጠው ጠለፋ የንብረት ዋስትና የተሰጠ ይሁን አይሁን በራሱ የሚነሳ ክርክር መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የጠለፋ ዋስን ንብረት የሚሸጠው ቢሆን ያልተገባ የመዳረግ መብት ለአቶ የሱፍ ሰዒድ ስለመፍጠሩ ከወዲሁ ሊረጋገጥ በማይችልበት ተጠሪ በአግባቡ ቢከፍል ኖሮና ባይመለስለት በሚል በዋስትና የያዘውን ንብረት እንዳይሸጥ፣ ቢሸጥ የማይመለስ ጉዳት የሚያስከትል በመሆኑ እንዲታገድ ያቀረብነው ጥያቄ ውደቅ መደረጉ ተገቢ አይደለም፡፡ የዋስትና ሠነድ መሠረት ያደረገው ክርክር በአዋጅ ቁጥር 97/1990 የሚገዛ አይደለም፡፡ አዋጅ ቁጥ 97/90 ለብድር ውል ተፈጻሚነት ያለው ነው፡፡ ስለሆነም በአመልካች ስም የወጣው ጨረታ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ

እስኪታወቅ ማስታወቂያው እንዲታገድ እና የሥር ፍርድ ቤቶች ትዕዛዝ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 211 መሠረት እንዲሽር የሚል ነዉ።

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ የቅድመ ክፍያ ዋስትና ግዴታውን የተወጣው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ክርክር በሥር ፍርድ ቤት በመታየት ላይ ባለበት አመልካች ያቀረቡት የእግድ አቤቱታ ውድቅ መደረጉ አግባብነቱን ግራ ቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ጥሪ ተደርጎላታል። በዚህም መሠረት ተጠሪ ያቀረበው መልስ የዋስትና መስጫ ውሉ አንቀጽ 3 ላይ ክፍያው እንዲከፈል በተጠየቀ ጊዜ ባንኩ ሳይከራከርና በባለዕዳውና በዋስትና ተጠቃሚው መካከል ያለውን አለመግባባት ሳይመለከት የዋስትና ገንዘቡን በሙሉ ወይ በከፊል ለዋስትና ተጠቃሚው ለመክፈል ግዴታ መኖሩን ያሳያል። በአሠሪው በተጠየቀው መሠረት ተጠሪ ገንዘቡን ከፍሏል። ክፍያው የተፈጸመው በዋስትና ሠነዱ ላይ የተቀመጡ ሁኔታዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ ነው። አመልካች ያቀረቡት ክስ ባንኩ የከፈለው ገንዘብ መመለስ እንዳይችልና መብቱን ለመጉዳት ነው። አዋጅ ቁጥር 97/90 ለማንኛውም ዕዳ ተፈጻሚነት ያለው ሕግ ነው። ለዋስትና መስጫ ውል ግዴታ አፈጻጸም ዋስትና ይሆን ዘንድ ታህሳስ 06 ቀን 2011 ዓ/ም በተፈረመ የመያዣ ውል መሠረት ስመ ንብረቱን በአቶ የሱፍ ሰይድ የተመዘገበ መኖሪያ ቤት በመያዣ ይዘናል። ያሲዙት ግለሰብ በሥር ፍርድ ባቀረቡት ጣልቃ ገብ አቤቱታ ለዕዳው አመላለስ ንብረቱን ማሲያዛቸውን አምነዋል። ባንኩ በሕግ ባለው ሥልጣን መሰረት የሐራጅ ማስታወቂያ ማውጣቱ ተገቢ ነው። ባንኮች የሐራጅ ማስታወቂያ ሲያወጡ ፍርድ ቤቶች ሂደቱን ማደናቀፍና እግድ መስጠት እንደሌለባቸው ሰበር ችሎት በተለያዩ መዝገቦች አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቷል። ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤቶች እግዱን ማንሳታቸው የሚነቀፍ አይደለም በማለት ጸንቶ እንዲወሰንለት ዳኝነት ጠይቋል። አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሠበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል።

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የተሰጠው እግድ እንዲነሳ መወሰኑ ሕጋዊነቱን? በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል።

እንደመረመርነው አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ በአመልካችና በአማራ ክልል የውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ልማት ቢሮ መካከል ነሀሴ 12 ቀን 2010 ዓ/ም የተደረገ የግንባታ ውል ያለ ሲሆን ለቅድመ ክፍያው አመላለስ ቅድመ ክፍያው ከግንባታው ሥራው ዓላማ ውጭ ከዋለ ወይም በግንባታ ውሉ መሠረት ዋስትና የተገባለትን ቅድመ ክፍያ ካልመለሰ የሚከፈል

የዋስትና ግዴታ ተጠሪ ለአሠሪው ሰጥቷል። ተጠሪ በዋስትና ግዴታው ላይ የተመለከቱ ሁኔታዎችና መስፈርቶች መሟላት አለመሟላታቸውን ሳይመረምር አሠሪው የግንባታ ሥራው ባለመሰራቱና ሊሰራ ስለማይችል በሚል በዋስትና የተመለከተው ገንዘብ እንዲከፈለው ሲጠይቀው ተጠሪ ብር 20,551,492.40 ከፍሏል። ክፍያው የተፈጸመው ከዋስትና ሰነዱ በማይስማማ ጥያቄና ከቅድመ ክፍያው ውል ድንጋጌ ውጭ በመሆኑ አመልካች የማይገደድበት ስለሆነ ውልና ተግባሩ ፈርሶና ተሰርዞ ለዋስትና ግዴታው ለተጠሪ ባንክ የተሰጠ ኮሚሽን እንዲመለስ፣ እንዲሁም በተሰጡ ዋስትናዎች አመልካች የማይገደድ ነው ተብሎ ዋጋ አልባ ወይም ፈራሽ ናቸው ተብሎ እንዲፈርሱ/እንዲሰረዙ እና ወደነበርንበት እንድንመለስ እንዲወሰን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል። አመልካች ታህሳስ 07 ቀን 2013 ዓ/ም በተጻፈ ማመልከቻ በሁኔታ ላይ የተመሰረተ የዋስትና ግዴታውን ባላከበረ መልኩ ክፍያውን ተጠሪ ከፈጸመ በኋላ ለዋስትና ግዴታው የተሰጡ መያዣዎችን ለመሸጥ የሐራጅ ማስታወቂያ ስላወጣ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 154 እና 155 እንዲታድ መጠየቁን ተከትሎ እግድ የተሰጠ ሲሆን ተጠሪ እግዱ እንዲነሳ በመጠየቁ የሥር ፍርድ ቤቶች ባንክ በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት ያወጣው ሀራጅ ሊቆም አይችልም በማለት የእግድ ትዕዛዙን አንስተዋል።

እግድ በሠው የንብረት መብት አጠቃቀም ላይ ገደብ የሚፈጥር ነው። በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 40(1) ላይ ጥበቃ የተደረገለት ንብረት መብት ላይ ገደብ ለማድረግ ደግሞ በሕግ በግልጽ በተመለከተ፣ ውስን ጉዳይና አፈጻጸሙም መብቱን መልሶ የመውሰድ ያህል ውጤት በማይፈጥር ሁኔታ ውስጥ ብቻ ሊሆን ይገባል የሚለው ስለሠብዓዊ መብት ጥበቃ የተደረጉ የሥምምነት ድንጋጌዎች ሆነ በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ የተቀረጸ የሕግ መርሕ ነው። በፍትሐብሔር ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 154 እና 155 መሠረት የሚሰጥ እግድ፣ የፍትሐብሔር ጉዳዮችን በማየት ላይ ያለ አንድ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት ከሚሰጣቸዉ የተለያዩ ጊዜያዊ የእግድ ትዕዛዞች አንዱ ነዉ (የህጉ አንቀጽ 147-159 ይመለከቷል)። በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 154 ላይ እና በተከታዩ አንቀጽ 155 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ ክርክሩ በማናቸዉም ደረጃ ላይ ባለበት ጊዜ ሌላዉን ተከራካሪ ወገን ሊጎዳ የሚችል አንድ የተወሰነ ተግባር እንዳይፈጸም በፍርድ ቤት የሚሰጥ ትዕዛዝ ነዉ። በእነዚህ ድንጋጌዎች መሠረት እግድ የሚሰጠዉ አንደኛ በንብረቱ ላይ የሚፈጸመዉ ተግባር ሌላዉን ተከራካሪ የሚጎዳ ሲሆን (አንቀጽ 154)፣ ሁለተኛ ክርክሩ ከዉል ጋር የተያያዘ እንደሆነ ዉል እንዳይፈርስ ወይም አንድ ተግባር እንዳይፈጸም የሚያሰጋ ሆኖ ሲገኝ (አንቀጽ 155) ስለመሆኑ ከየድንጋጌዎቹ ይዘት የምንገነዘበዉ ነዉ።

ንብረትን በተመለከተ የሚሰጥ የእግድ ትዕዛዝም ነገሩ በፍርድ እስኪወሰን ወይም ሌላ ትዕዛዝ እስኪሰጥ ድረስ ንብረቱ እንዳለ እንዲቆይ፣ ከመጥፋት እንዲድን ወይም እንዳይበላሽ፣ ለሌላ ሰው ተላልፎ እንዳይሰጥ፣ ወደ ሌላ ስፍራ እንዳይዛወር ወይም እንዳይባክን የሚሰጥ ነው። በዚህ መልኩ የሚሰጥ እግድ ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉን ንብረት የሚመለከት መሆኑንም ልብ ይሏል። በህጉ አንቀጽ 154(ለ) ላይ "ተከሳሹ የባለገንዘቦችን ጥቅም ለመጉዳት ሲል ንብረቱን ለማጥፋት፣ ለሌላ ሰው አሳልፎ ለመስጠት ያቀደ፣ የዛተ፣ ወይም ያሰበ መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ነገሩ በፍርድ እስኪወሰን ድረስ ንብረቱ እንዳለ እንዲቆይ....." በሚል የተገለጸዉ ላይ ላዩን ሲታይ፣ የተከሳሽን ማንኛዉንም ንብረት ማሳገድን የሚመለከት ይመስላል። ይሁንና የተከሳሽ ማናቸዉም ንብረት ሊከበር የሚችልበት ሁኔታ በህጉ አንቀጽ 151 ላይ ተመልክቶ እያለ፣ ህግ አዉጪዉ ለተመሳሳይ ዓላማ ተመሳሳይ ይዘት ያለዉ ሌላ ድንጋጌ በዚህ አንቀጽ ስር በድጋሚ ይደነግጋል ተብሎ አይታሰብም። ይልቁንም በተጨባጩ ዓለም ሲታይ፣ አንዳንድ ባለዕዳዎች የሚጠበቅባቸዉን ዕዳ አለመክፈላቸዉን ተከትሎ ገና ለገና ንብረታቸዉ ለዕዳ ማስፈጸሚያ ይዉላል በሚል ሃሳብ ወይም በሌላ ምክንያት ንብረቶቻቸዉን ሊያጠፉ፣ ለሌላ አካል አሳልፎዉ ሊሰጡ የሚችሉባቸዉ ሁኔታዎች ይኖራሉ። ይህም ሲሆን፣ ባለገንዘቦች ያላቸዉ መፍትሔ ባለዕዳዉ ከዚህ ድርጊቱ እንዲታቀብ ለፍርድ ቤት ክስ በማቅረብ እግድ እንዲሰጣቸዉ ዳኝነት መጠየቅ ነው። ይሁንና የቀረበዉ የእግድ ዳኝነት ጥያቄ ታይቶ ዉሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ንብረቱን የማሸሹ ወይም ለማጥፋት የመሞከሩ ስጋት የሚቀጥል ከሆነ በከሳሽ ላይ ከፍተኛ ወይም የማይመለስ ጉዳት ሊደርስ ይችላል ወይም እግድን አስመልክቶ የቀረበዉንም ዳኝነት ዉጤት አልባ ያደርጋል። በህጉ አንቀጽ 154(ለ) ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌም በዚህ መልኩ ማለትም ተከሳሽ በድንጋጌዉ ላይ የተመለከቱትን ድርጊቶች እንዳይፈጽም እግድ እንዲሰጥ የቀረበዉ ክስ ዉሳኔ እስኪያገኝ ድረስ ተከሳሽ ከድርጊቱ እንዲታቀብ ለጊዜዉ እግድ እንዲሰጥ የሚቀርበዉን ጥያቄ የሚመለከት እንደሆነ መገንዘቡ ተገቢ ነው።

በአጠቃላይ በህጉ አንቀጽ 154 መሠረት የሚሰጥ እግድ ከክሱ ጋር ተያያዥነት ባላቸዉ ንብረቶች ወይም ጉዳዮች ላይ ሲሆን፣ ከሳሽ በቂ ምክንያት ያለዉ መሆኑ በቀረበዉ ክስ መብቱ እስኪረጋገጥ ድረስ ሊካስ የማይችል ጉዳት እንዳይደርስበት ጥበቃ የሚያስፈልገዉ መሆኑንና እግድ ካልተሰጠ የበለጠ ጉዳት የሚደርስበት መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ እንዲሁም የተጠየቀዉ የእግድ ትዕዛዙ ካልተሰጠ ከሳሹ በክሱ የጠየቀዉን ዳኝነት ያጣል፤ የክስ ዓላማም ዋጋ ያጣል የሚል እምነት ፍርድ ቤቱ ሲኖረዉ ስለመሆኑ በአንቀጹ ላይ እንደ ቅድመ ሁኔታ ከሰፈሩት

ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል። የእግድ ትዕዛዝ በመርሕ ደረጃ የቀረበ ክስን መሠረት ያደረገ እና በሥነ-ሥርዓት ሕጉ አግባብ በተመለከቱት መስፈርቶች የሚሰጥ ነው። ዓላማው ደግሞ ክሱ ያለውጤት እንዳይቀርና ፍርድ በሚሰጥበት ጊዜም የሚፈጸምበት ንብረት እንዲኖርና ዜጎች መብታቸውን ማስከበር የሚችሉበትን ዕድል የሚፈጥርና በሂደቱም ፍርድ ቤቶች ላይ ያላቸውን እምነት የሚጨመር ነው።

ተጠሪ እግዱ ሊነሳ ይገባል በማለት የሚከራከረው በዋስትና ግዴታው መሠረት ለግንባታ አሠሪው የቅድመ ክፍያ ዋስትና ገንዘቡን ከፈጸምኩ በኋላ ለዋስትና የተያዘው የመያዣ ንብረትን በአዋጅ ቁጥር 97/1990 መሠረት የመሸጥ ሥልጣን ያለኝ ስለሆነ ሐራጁ ሊቆም አይገባም በማለት ነው። ተጠሪ ባንክ በገባው ግዴታ መሠረት የዋስትና ቦንድ ግዴታውን ከፈጸመ ለተከፈለው ገንዘብ አመልካች ባለዕዳ ስለሚሆን በአዋጅ ቁጥር 97/1990 አንቀጽ 4 መሠረት ባለገንዘብ የሆነው ባንክ መያዣውን የመሸጥ ሥልጣን ይሰጠዋል። አዋጅ ቁጥር 97/1990 ለባንኮች በመያዣ የያዙትን ንብረት በራሳቸው ሽጠው ገንዘቡን ለማስመለስ የሚችሉበትን ሥልጣንና ኃላፊነት የሚዘረዝር ሕግ ነው። አዋጅ ቁጥር 97/1990 መግቢያ ላይ እንደተመለከተው ባንኮች በመያዣ የያዙትን ንብረት ላይ በፍርድ ቤት ክስ አቅርበው ለማስወሰንና ለማስፈጸም የሚወስደው ጊዜ ረጅም ጊዜ በመሆኑና ይሕም ባንኮች ሥራ ላይ ተጽዕኖ በማሳደሩ፣ ለኢኮኖሚው እንቅስቃሴ አመቺ ሁኔታ ለመፍጠር ባንኮች ለተለያዩ የልማትና ንግድ እንቅስቃሴ የሚሰጧቸውን ብድሮችን በተቀላጠፈ መንገድ ለመሰብሰብ እንዲችሉና ለወደፊቱ ጥሩ የንግድ አሠራር ባሕል እንዲዳብር ለማድረግ ለባንክ ብድር በመያዣ የተሰጡ የማይንቀሳቀሱና የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችን ሽያጭ በሚመለከት በሥራ ላይ ያሉ ሕጎችን በማሻሻል አዲስ ሥርዓት መዘርጋትን ዓላማ አድርጎ የወጣ ሕግ ነው። በዚህ ሕግ በመያዣ የተያዘን ንብረት ባንኮች በራሳቸው የመሸጥ መብት የተሰጣቸው ሲሆን መብቱ ገደብ የሌለው (absolute right) ባለመሆኑ ንብረቱን ከመሸጥ ታግዶ እንዲቆይ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንዲሰጥ ጥያቄ ሊቀርብበት ይችላል። በሌላ በኩል የሚኖረው ገደብ ለፋይናንስ ተቋሞች በሕግ የተሰጠውን ሥልጣንና ሕጉ ሊያሳካ የፈለገውን ዓላማ ቀሪ በሚያደርግ አግባብ እንዳይሆን ጥንቃቄ ያስፈልገዋል።

የዋስትናን መሠረታዊ ሃሳብ ባለዕዳዉ ግዴታዉን ያልተወጣ እንደሆነ ይህን ግዴታ ለመወጣት በባለዕዳዉ ለባለገንዘቡ የሚሰጥ ማረጋገጫ ነዉ። ዋስትና በአጠቃላይ የሰዉ (personal security) እና የንብረት (real security) ተብሎ በሁለት የሚመደብ ሲሆን፣ የማይንቀሳቀስ

ንብረትን መያዣ በማድረግ የሚሰጥ ዋስትና (mortgage) በንብረት ዋስትና ስር የሚመደብ ነዉ፡፡ በእኛ አገር የማይንቀሳቀስ ንብረት ዋስትና ምንጩ ዉል፣ ህግ አሊያም ደግሞ የፍርድ ቤት ዉሳኔ ሊሆን እንደሚችል ከፍትሐብሔር ህጋችን አንቀጽ 3041 ቀጥተኛ ንባብ መገንዘብ እንችላለን፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ እንደማንኛዉም ዓይነት ዋስትና ደባል ግዴታን (accessory obligation) የሚጥል ነዉ፡፡ በመሆኑም በህግ ፊት ተፈፃሚነት ይኖረዉ ዘንድ፤ ቅቡልነት ያለዉን ዋና ግዴታ (valid principal obligation) መሠረት ያደረገ፣ አመሠራረቱም ግልጽና የማያሻማ እንዲሁም የገንዘብ መጠኑን የሚገልጽና ከዋናዉ ግዴታ ያልከበደ ሊሆን እንደሚገባ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1923፣ 1924፣ 1926 እና 3045 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡ በህግ አግባብ የተቋቋመ የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ ዉጤቱ ለዋስትናዉ ምክንያት የሆነዉ ዕዳ እስከሚከፈል ድረስ ንብረቱን የመከታተል መብት (right in rem) ለዋስትና ተቀባዩ የሚሰጥ ሲሆን፣ ከዚህም ዉስጥ አንዱ ዋስትና ተቀባዩ ከሌሎች ባለገንዘቦች የቅድሚያ መብት እንዳለዉ በህጉ አንቀጽ 3059(1) ላይ በግልጽ የተመለከተዉ ነዉ፡፡

ተጠሪ የመያዣ መብቱን ያገኘው ከአመልካች ጋር ባለው የውል ግንኙነት ለሚመጣ ዕዳ አቶ ዮሴፍ ሰዒድ በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 16 ያላቸውን ቤት መያዣ በማድረጋቸው ነው፡፡ የተጠሪ የመብት ምንጭ ውል እንደመሆኑ መጠን ውሉ በአመሠራረት ጉድለት ሆነ በውል አፈጻጸም ጋር በተያያዙ ጉዳዮች እንዲፈርስ ወይም እንዲሰረዝ ክርክር ሊቀርብበት እንደሚችል ከፍ/ሕ/ቁ. 1808 እና 1771 እና ተከታይ ድንጋጌዎች የምንገነዘበው ነው፡፡ ባንክ ከሌሎች ተዋዋዮች በተለየ የገባሁት ውል ላይ ክስ ሊቀርብበት አይችልም በሚል ሊከራከር አይችልም፡፡ አመልካችም ክስ ያቀረቡት ይህን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ለመያዣው መሠረት የሆነው ግዴታ ቀሪ ወይም ፍርስ የሚሆን ከሆነ ዋስትና/መያዣው አብሮ ቀሪ የሚሆን ነው፡፡ አመልካች ባቀረቡት ክስ መሠረት የሚወሰንላቸው ቢሆን ከተጠሪ ጋር ያላቸው ግዴታ/ዕዳ ቀሪ ስለሚሆን ለግዴታ ተያያዥ የሆነ የመያዣ ውሎች አብረው ቀሪ ስለሚሆኑ የእግድ ጥያቄው ከክሱ ውጤት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ተጠሪ የመያዣ ንብረቱን ክሱ ውጤት ሳያገኝ አስቀድሞ የሚሸጠው ከሆነ አመልካች ያቀረቡት ክስ ያለውጤት እንዲቀር የሚያደርግና ፍርድ ቢያርፍበት እንኳን ውጤት የሌለውና የማይፈጸም ያደርገዋል፡፡

ዜጎች በፍትሕ ሥርዓቱ የሚጠቀሙት መብታቸውን ለማስከበር ነው፡፡ የመብት ማስከበር መሠረቱ ደግሞ ፍርድን ከማናቸውም መሠናክል ነጻ በማድረግ ማስፈጸም ነው፡፡ ፍርድ ቤቶች

በዚህ አግባብ ኃላፊነታቸውን ካልተወጡ ዜጎች በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 37 ያገኙት ፍትሕ የማግኘት መብትን ማረጋገጥ እና ማስፈጸም አይቻልም፡፡ ውጤቱ ደግሞ መብት ካለመከበሩም በተጨማሪ ፍርድ ቤቶች ላይ እምነት (public trust) እንዳይኖር ያደርጋል፡፡ ስለሆነም ፍርድ ቤቶች ሰብዓዊ መብቶችን ከማስከበር እና የሕግ የበላይነት እንዲኖር ያላቸውን የማይተካ ሚና የመወጣት ግዴታ ያለባቸው በመሆኑና አንዱ መገለጫ የወሰኑትን ውሳኔ የሚፈጸም ስለመሆኑ በሕጉ የተዘረጉ ሥርዓቶችን በመከተል ፍርዱ ያለውጤት ቀሪ እንዳይሆን መከላከል ነው፡፡ በዚህ አግባብ ከተዘረጉ ሥርዓቶች አንዱ ደግሞ የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 154 እና 155 የተመለከተው ሲሆን የድንጋጌዎቹ ዋና ዓላማም ንብረቱን የማሸሹ ወይም የማጥፋት ሂደቶችን በማስቆም በከሳሽ ላይ ከፍተኛ ወይም የማይመለስ ጉዳት እንዳይደርስ መከላከልና የቀረበው ክስም ውጤት አልባ እንዳይሆን ማድረግ በመሆኑ አመልካች ያቀረቡትን የእግድ ጥያቄ ከዚህ ማዕቀፍ መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡

ተጠሪ ቀድም ሲል በሰበር ችሎት የተሰጡ ትርጉሞችን መሠረት በማድረግ የተከራከረ ሲሆን ሰበር ችሎቱ በመዝገብ ቁጥሮች 21270 ሆነ 43226 የተሰጡ ትርጉሞች ባንክ የገባው ውል ላይ እንዳይፈርስ ወይም እንዲሰረዝ ክስ በቀረበ ጊዜ፤ የውሉ መፍረስ ውጤት የመያዣ ውሉን ቀሪ የሚያደርገው ከሆነ ባንክ ያወጣው ሐራጅ እንዲቆም ትዕዛዝ ሊሰጥ አይገባም በሚል የተሰጡ ትርጉሞች ባለመሆናቸው ለተዘያው ጉዳይ ተፈጻሚነት የላቸውም፡፡ በሌላ በኩል ክስ የቀረበበት የዋስትና ውልና የዋስትና ግዴታ ሠነድ/ቦንድ በቅድመ ሁኔታ ወይስ ያለቅድመ ሁኔታ የተደረጉ ናቸው የሚለው ጉዳይ ክሱን በሚመረምረው ፍርድ ቤት እልባት የሚያገኙ ሲሆን የዋስትና ግዴታ ሠነዶች የሦስትዮሽ ውል በመሆናቸው በዋነኛት ያለቅድመ ሁኔታ መሆኑ የሚጠቅመው የዋስትና ግዴታው የተገባለት ተጠቃሚን ነው፡፡ አሁን በተያዘው ጉዳይ የዋስትና ግዴታ ሠነዱ ተጠቃሚው የአማራ ክልል የውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ልማት ቢሮ ሲሆን ተጠሪ ክፍያውን የፈጸመለት በመሆኑ የዋስትና ገዴታው ሠነድ ያለቅድመ ሁኔታ የተደረገ ቢሆን እንኳን እግድ መሠጠቱ የሠነዱ ውጤት ላይ የሚያመጣው ለውጥ ባለመኖሩ እግዱ ሊነሳ የሚገባ አይደለም፡፡ በአጠቃላይ የሥር ፍርድ ቤቶች ተጠሪ የመያዣ መብት ያቋቋመበት ንብረት ላይ የተሰጠው እግድ ሊነሳ ይገባል በማለት የደረሰበት መደምደሚያ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 205184 ሰኔ 18 ቀን 2013 ዓ/ም እና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 262509 ጥር 25 ቀን 2013 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. ተጠሪ በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 16 ቤት ላይ ያወጣው ሐራጅ ታግዶ ሊቆይ ይገባል ብለናል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ በውሳኔው መሠረት እንዲፈጸም አዘናል፡፡ ይጻፍ

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ 212593

ሀምሌ 4 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- ሚስ ሻሮን አና ኢሸተን ፡- አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡-1ኛ. ዶ/ር መላኩ መንግስቱ

2ኛ. ዋጋ ሜዲካል ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጠበቃ ፋሲል አስናቀ -ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ የንግድ ማህበርን የሚመለከት ሲሆን የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 258336 በቀን 04/10/2011 ዓ.ም እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 243487 በቀን 09/09/2013 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለት አመልካች ስለጠየቁ ነው፡፡ ክርክሩ የጀመረው በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች ከሳሽ፤ ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች ነበሩ፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው አመልካች በቀን 16/05/2010 ዓ.ም ባቀረቡት የተሻሻለ አቤቱታ ከሳሽ እና 1ኛ ተከሳሽ ከሌሎች ሁለት ማህበርተኞች ጋር በመሆን ሰኔ 7/2002 ዓ.ም በብር 40,000,000 (አርባ ሚሊየን) ካፒታል 2ኛ ተከሳሽ ማህበርን አቋቁመን የህክምና ስራ ስንሰራ ቆይተናል፡፡ 1ኛ ተከሳሽ በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 8.1 መሰረት ስራ አስኪያጅ እንዲሆኑ ተሰይመዋል፡፡ ነገር ግን በስራ አስኪያጅነታቸው የማህበሩን ስራ ማከናወን ሲገባቸው የስራ ሀላፊነታቸውን ለከሳሽ አሳልፈው በመስጠት በቋሚነት ወደሚኖሩበት ካናዳ ሀገር ሄደዋል፡፡ ከሳሽም የ1ኛ ተከሳሽን ተግባር እና ኃላፊነት በመፈጸም ኩባንያው አሁን ያለበት ደረጃ

ለማድረስ በቅተዋል። ከሳሽ ማህበሩን ስኬታማ ለማድረግ ያበረከቱትን አስተዋጽኦ ከግምት በማስገባት ጥቅምት 04/2007 ዓ.ም በተደረገ ድንገተኛ የባለ አክስዬኖች ስብሰባ መተዳደሪያ ደንቡ ተሻሽሎ ከሳሽ በምክትል ስራ አስኪያጅነት ተሰይመው ስራቸውን በትጋት ሲፈጽሙና ኩባንያውንም ከፍተኛ ስኬት እንዲያስመዘግብ በማድረግ ግዴታቸውን እየተወጡ ባለበት ሁኔታ 1ኛ ተከሳሽ ድርጅቱን እና ማህበርተኞችን የሚጎዳ በርካታ ህገወጥ ተግባራትን ፈጽመዋል። ከዚህም ህገወጥ ተግባራት ውስጥ ባለቤታቸው እና እህታቸው ባለ አክስዬን የሆኑበትን የጃስፔራ ኃ/የተ/የግ/ማህበርን ህንጻ 2ኛ ተከሳሽ ድርጅት እንዲከራይ አድርገዋል፤ 1ኛ ተከሳሽ ድርጅቱ ከቀድሞ የስራ ቦታው ወደ ራሳቸው ህንጻ እንዲቀየር ካደረጉ በኋላ ህንጻው በአግባቡ ያልተጠናቀቀ በመሆኑ ጎርፍ ገብቶ በብዙ ሚሊየን በሚገመቱ የድርጅቱ ንብረቶች ላይ ጉዳት አድርሷል፤ ይህ ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስም የህንጻውን አስፈላጊ የማጠናቀቂያ ስራዎች ለመስራት ፈቃደኛ አልሆኑም፤ 1ኛ ተከሳሽ አቶ አቤል አሰፋ የተባሉ የእህታቸውን ልጅና ሲስተር ጥሩወርቅ የተባሉ የባለቤታቸውን እህት ግልጽነት በሌለው መንገድ የድርጅቱ ተቀጣሪ አድርገዋቸዋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ 1ኛ ተከሳሽ ህዳር 04/2010 ዓ.ም በድንገት ከካናዳ ሀገር በመምጣት በድሪም ላይነር ሆቴል ስብሰባ ይኖራል ብለው ከሳሽ ስብሰባውን በመጠባበቅ ላይ እያለሁ ወደ ስብሰባው የምሄድበትን መኪና እንዳይንቀሳቀስ በማድረግ ውክልና ተነስቷል የሚል ደብዳቤ በመጻፍ የድርጅቱን ማህተም እና ሰነዶችን ነጥቀውኛል። ከሳሽ ከቼክ ፈራሚነት እንድነሳ በማድረግ የእህታቸውን ልጅ አቤል አሰፋን የጋራ ቼክ ፈራሚ አድርገዋል። ይህ ሳይበቃ 1ኛ ተከሳሽ አቶ በሪሁ የተባሉ ግለሰብን ከህግና ከመተዳደሪያ ደንቡ ውጭ ተቀጣሪ ስራ አስኪያጅ አድርገዋቸዋል። አንድ የድርጅት ስራ አስኪያጅ በመደበኛነት መኖር የሚገባው ስራው በሚሰራበት ቦታ ቢሆንም 1ኛ ተከሳሽ ድርጅቱ ከተመሰረት ግዜ ጀምሮ የሚኖሩት ካናዳ ሀገር ነው። ከተዘረዘሩት ጥፋቶች አኳያ 1ኛ ተከሳሽ ድርጅቱን የጥቅም ግጭት በሚታይበት መልኩ እየመሩ የሚገኙ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን የስራ አስኪያጅነት የስልጣን ዘመን አንድ አመት ስለመሆኑ በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ላይ ተመልክቶ እያለ 1ኛ ተከሳሽ በድጋሚ ሳይመረጡ በቋሚነት ስራ አስኪያጅ ሆነው ሊቀጥሉ የሚችሉበት አግባብ የለም። በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ዋና ስራ አስኪያጅ በሌለበት ምክትል ስራ አስኪያጅነት እንድሰራ በግልጽ በመተዳደሪያ ደንቡ ተቀምጦ እያለ 1ኛ ተከሳሽ ስራ እንዳልገባ በመከልከል ቅጥር ስራ አስኪያጁ በእጅ አዙር የዋናውን ስራ አስኪያጅ ተግባር በማከናወን ላይ የሚገኙ በመሆኑ ከሳሽ በ2ኛ ተከሳሽ ድርጅት ውስጥ ያለኝን አክስዮን ገበያ ዋጋ እንዲሁም እዳና ንብረት በማወቅ ለሽያጭ ማቅረብ እንድችል ገለልተኛ ገማች እንዲሰየም እፈልጋለሁ። በመሆኑም 1ኛ ተከሳሽ ድርጅቱን የጥቅም ግጭት

በሚታይበት ሁኔታ እየመሩ በመሆኑ፤ የስልጣን ዘመናቸውም ያበቃ በመሆኑና በኩባንያ ውስጥ ለተፈጠረው ብርቱ ጭቅጭቅ መንስኤ በመሆናቸው ከስራ አስኪያጅነታቸው ተሽረው ባለ አክስዬኖች በፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ሌላ ስራ አስኪያጅ እንዲሰየም እንዲወሰንልኝ፤ 1ኛ ተከሳሽ የፈጸሙት ህገወጥ ቅጥር ውል እንዲሰረዝ እና ተቀጣሪዎች ከኩባንያው እንዲሰናበቱ፤ ዋጋ ገማች ባለሙያ በፍ/ቤት እንዲሰየምልኝ፡፡ ይህ የሚታለፍ ከሆነም 1ኛ ተከሳሽ ኩባንያውን የጥቅም ግጭት በሚታይበት አኳኋን እየመሩ በመሆኑ፤ በከሳሽም ላይ በርካታ ጉዳት እያደረሱ በመሆኑና በተፈጠረው ብርቱ ጭቅጭቅ ምክንያት አብረን መስራት ከማንችልበት ደረጃ ስለደረስን ኩባንያው ፈርሶ የንብረት ክፍፍል እንድናደርግ እንዲወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተከሳሾች በቀን 30/06/2010 ዓ.ም በሰጡት መልስ 1ኛ ተከሳሽ በስራ አስኪያጅነታቸው ሊፈጽሟቸው ሲገባቸው ያልፈጸሟቸው ተግባር እና ሀላፊነት ምን እንደሆነ በክሱ ላይ አልገለጹም፤ 1ኛ ተከሳሽ በቋሚነት ካናዳ አገር ቢኖሩም ኩባንያውን በስራ አስኪያጅነት እንዳይመሩ የሚከለክላቸው ህግ የለም፤ በኩባንያው መተዳደሪያ ደንብና መመስረቻ ጽሁፍ ላይ የስራ አስኪያጅ ስልጣናቸውን ለሌላ ሰው ማስተላለፍ እንደሚችሉ ተደንግጓል፤ 1ኛ ተከሳሽ ከከሳሽ ጋር በኢሜል እና ሌሎች መገናኛ ዘዴዎች እየተገናኙ ድርጅቱን ሲመሩ ቆይተዋል፤ ከኩባንያው ጋር የህንጻ ኪራይ ውል የፈጸመው ጃስፔራ ቢዝነስ የሚባል ኃ/የተ/የግ/ማህበር ሆኖ እያለ 1ኛ ተከሳሽ ኩባንያውን ወደራሳቸው ህንጻ አዛውረው አከራይተዋል የተባለው ሀሰት ነው፤ የኪራይ ውሉንም ከአከራዩ ጋር የፈጸሙትን ከሳሽ ራሳቸው የወከሏቸው ግለሰብ ናቸው፤ ከሳሽ በጎርፍ ምክንያት በኩባንያው ንብረት ላይ ጉዳት ደረሰ ቢሉም ደረሰ የሚሉት ጉዳት ካለ ህንጻ ያከራየውን ድርጅት ከሚጠይቁ በቀር 1ኛ ተከሳሽን ሊጠይቁ አይችሉም፤ በኩባንያው ሰራተኞች ሲቀጠሩ የቅጥር ውል የፈረሙት ከሳሽ ራሳቸው ከመሆናቸውም በላይ የተቀጠሩ ሰራተኞች ለስራ ብቁ እስከሆኑ ድረስ ከመቀጠር የሚከለክላቸው ህግ የለም፤ 1ኛ ተከሳሽ ከሳሽ የሚጠቀሙበትን መኪና አግተው እንዳይንቀሳቀስ አደረጉ የተባለው ሀሰት ነው፤ 1ኛ ተከሳሽ እንደ ስራ አስኪያጅነታቸው ውክልና የመስጠትም ሆነ የመሻር ስልጣን ያላቸው ሲሆን ለከሳሽ የሰጡትን ውክልና መሻራቸው የሚነቀፍበት ምክንያት የለም፤ 1ኛ ተከሳሽ ከሳሽን ከምክትል ስራ አስኪያጅነት አልሻሩም ከማህበር አባልነትም አላሰናበቱም፤ ከሳሽ በኩባንያው ላይ በፈጸሙት ምክንያት ከስራ እንዲታገዱ የተደረገ ሲሆን ይህም ለስራ አስኪያጁ በተሰጠ ስልጣን መነሻነት ነው፤ 1ኛ ተከሳሽ ሰነድም ሆነ ማህተም ከከሳሽ ላይ አልነጠቁም፤ በማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ መሰረት የተሰጣቸውን ስልጣን በመጠቀም ሌላ ሰው ቼክ እንዲፈርም ውክልና መስጠታቸው የጥቅም ግጭት ስለመኖሩ የሚያመለክት አይደለም፤ በተሻሻለው

የማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 8 መሰረት የስራ አስኪያጁ ስልጣን ላልተወሰነ ግዜ የተራዘመ በመሆኑ ከሳሽ የስራ አስኪያጅ ስልጣን ካበቃ በኋላ ይሰራል በሚል ያቀረቡት ተቀባይነት የለውም፤ 1ኛ ተከሳሽ ከማህበሩ መተዳደሪያ ደንብና መመስረቻ ጽሁፍ ውጭ የፈጸሙት ተግባር የለም፤ ህልውና ያለው ማህበር በፍ/ቤት ስራ አስኪያጅ እንዲሾምለት የሚደረግበት አግባብ የለም፡፡ ከሳሽ የኩባንያው አክስዬን ዋጋ እንዲገመትላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ለፍ/ቤት የማይቀርብ ሲሆን በራሳቸው ወጪ ማስገመት ይችላሉ፡፡ ከከሳሽ ጋር የተፈጠረው ግዜያዊ አለመግባባት ኩባንያውን ለማፍረስ የሚያስችል ብርቱ ጭቅጭቅ አለ ለማለት አያስችልም፤ የተፈጠረ የጥቅም ግጭት የለም እንጂ አለ ቢባል እንኳ ሌላ ህጋዊ ውጤት ይኖረዋል እንጂ ማህበሩ እንዲፈርስ አያደርግም፡፡ ከሳሽ ጉዳት ደረሰብኝ የሚሉ ከሆነ መብታቸው እንዲከበር ከመጠየቅ በቀር ማህበሩ እንዲፈርስ መጠየቅ አይችሉም፡፡ በሌሎች የኩባንያው ባለአክስዬኖች መካከል የተፈጠረ አለመግባባት የለም፤ ከሳሽ ድርሻቸውን ለመሸጥ ገለልተኛ ገማች እንዲሰየምላቸው በጠየቁት ዳኝነት መሰረት ድርሻቸው ተገምቶ ተሰጥቷቸው ከማህበር አባልነት ቢሰናበቱ ተቃውሞ የለንም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት ክርክሩንና ማስረጃ ከሰማ በኋላ 1ኛ ተከሳሽ ከስራ አስኪያጅነታቸው እንዲሻሩ የሚያደርግ በቂ ምክንያት ባለመኖሩ ከስራ አስኪያጅነታቸው ሊሻሩም ሆነ ግዜያዊ ስራ አስኪያጅ ሊሾም አይገባም፤ 1ኛ ተከሳሽ የፈጸሙት ህገወጥ የስራ ቅጥር የሌለ በመሆኑ የስራ ቅጥር ውሉ የሚሰረዝበት አግባብ የለም፤ ከሳሽ የአክስዬን ድርሻቸው እንዲገመት የጠየቁበት ምክንያት ምን እንደሆነ በግልጽ ባያስቀምጡም ተከሳሾች ከሳሽ በራሳቸው ወጪ ድርሻቸውን ማስገመት የሚችሉ መሆኑን በመግለጻቸው ከሳሽ ያላቸው የአክስዬን ድርሻ ዋጋው ምን ያህል እንደሆነ የሚገምት ባለሙያ በፍ/ቤቱ ሬጅስትራር በኩል እንዲሾም እና ወጪውን ከሳሽ እንዲሸፍኑ፤ ከሳሽ 1ኛ ተከሳሽ ፈጽመዋቸዋል ያሏቸው ተግባራት 1ኛ ተከሳሽን ከስራ አስኪያጅነት ለማስነሳት በቂ አለመሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የእነዚህ ተግባሮች መፈጸም አለመፈጸም ብቻውን ማህበሩን ሊያስፈርስ የሚያስችል በቂ ምክንያት ተደርገው ሊወሰዱ አይችሉም፤ በክሱ ላይ የተገለጹት ተግባራት በስራ አስኪያጁ መፈጸማቸው ህገወጥ አለመሆናቸው ከተረጋገጠ ደግሞ በእነዚህ ተግባራት የሚፈጠር አለመግባባት የንግድ ማህበሩም ህልውና እንዲያጣ የሚያደርጉ አለመግባባቶች ተከስተዋል ወደፊትም ማህበሩ የተቋቋመበትን አላማ ማሳካት አይችልም የሚያስብል አይደለም፤ 2ኛ ተከሳሽ ማህበር እንዲፈርስ ቢወሰን ከሚያስገኘው ጥቅም ይልቅ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጉዳት የሚያስከትል በመሆኑ ከሳሽ በማህበር አባልነታቸው መቀጠል የማይፈልጉ ከሆነ ማህበሩን

ከማፍረስ ይልቅ ድርሻቸውን በመውሰድ ከአባልነታቸው መውጣት የሚችሉ በመሆኑ ከሳሽ 2ኛ ተከሳሽ ማህበር እንዲፈርስ ያቀረቡትን ጥያቄ ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም፤ ማህበሩ ሊፈርስ አይገባም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ከሳሽ ይግባኝ ለከፍተኛው ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ውሳኔው ጸንቷል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡

አመልካች በቀን 07/12/2013 ዓ/ም ባቀረቡት የሰበር ማመልከቻ ተፈፀመ የሚሉትን ስህተት ዘርዝረው የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ 2ኛ ተጠሪ ማህበር እንዲፈርስ፤ ይህ የሚታለፍ ከሆነ 1ኛ ተጠሪ በርቀት 2ኛ ተጠሪን ቋሚ ስራ ኖሮት መምራት የማይችል በመሆኑ እንዲሻር በማለት ማመልከቻቸውን አቅርበዋል፡፡

ቅሬታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ የጥቅም ግጭት መኖሩን አመልካች ስላየበትና 1ኛ ተጠሪ በሩቅ ሀገር ሆኖ ድርጅቱን መምራት እችላለሁ በማለት ያቀረበውን ሀሳብ የስር ፍ/ቤት ከንግድ ህጉ አላማ አንጻር የተቀበሉበትን አግባብነት ለማጣራት በሚል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪዎች በቀን 19/06/2014 ዓ.ም ባቀረቡት መልስ ክርክራቸውን አጠናክረው በስር ፍ/ቤቶች የተሰጡት ውሳኔዎች እንዲጸኑ ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከፍ ሲል በአጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን የግራ ቀኙን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የተፈጸመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው የአመልካች ቅሬታና የዳኝነት ጥያቄ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ 2ኛ ተጠሪ ማህበር እንዲፈርስ፤ ይህ የሚታለፍ ከሆነም 1ኛ ተጠሪ በርቀት 2ኛ ተጠሪን ቋሚ ስራ ኖሮት መምራት የማይችል በመሆኑ እንዲሻር የሚጠይቅ በመሆኑ እነዚህን የቅሬታ ነጥቦች (ጭብጦች) በቅደም ተከተላቸው እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የማህበሩ በፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፈርስ አመልካች የጠየቁ ሲሆን ተጠሪዎች በበኩላቸው ማህበሩ እንዲፈርስ4 የሚወሰንበት ምክንያት እንደሌለ ተከራክረዋል፡፡ ከማህበርተኞቹ አንዱ ማህበሩ እንዲፈርስ በሚያቀርበው አቤቱታ መነሻነት ፍርድ ቤት የማህበሩን መፍረስ ሊወስን እንደሚችል ሥራ ላይ ከነበረው የንግድ ህግ አንቀጽ 218፣ 258፣ 278፣ 303፣ 495፣ 542፣ 543 እና ተያያዥ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ነገር ግን የንግድ ማህበሩ በፍርድ እንዲፈርስ

ስለተጠየቀ ብቻ የሚፈርስ ሳይሆን ማህበሩን ለማፍረስ የሚያበቃ በቂና ትክክለኛ ምክንያት መኖሩ ሊረጋገጥ ይገባል። በማህበርተኞቹ መካከል ብርቱ ጭቅጭቅና አለመስማማት የተፈጠረ እንደሆነ ለማህበሩ መፍረስ ትክክለኛ ምክንያት እንደሚሆን በንግድ ህጉ አንቀጽ 218(2) ስር ተመልክቷል። ይሁንና በማህበርተኞች መካከል የተፈጠረ አለመግባባት ሁሉ ማህበሩን የሚያስፈርስ ብርቱ ጭቅጭቅና አለመስማማት ተደርጎ እንደማይወሰድ ከህጉ አቀራረጽ፣ ከይዘትና መንፈሱ መረዳት ይቻላል።

በተያዘው ጉዳይ የስር ፍርድ ቤት በ2ኛ ተጠሪ ማህበር አባላት መካከል ጭቅጭቅና አለመግባባት ተፈጥሯል ወይስ አልተፈጠረም? በ1ኛ ተጠሪ ተፈፀመ የሚባለው የሥራ ጉድለትና አለመግባባት ማህበሩ እንዲፈርስ የሚያስችል ነው ወይስ አይደለም? ማህበሩስ ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚሉና ተያያዥ ነጥቦችን ከግራቀኙ ክርክርና ማስረጃዎች ጋር መርምሮ ማህበሩን ለማፍረስ የሚያስችል በቂና አሳማኝ ምክንያት ባለመገኘቱ ሊፈርስ እንደማይገባ፤ 2ኛ ተጠሪ የንግድ ማህበር እንዲፈርስ ቢወሰን ከሚያስገኘው ጥቅም ይልቅ ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል መሆኑን በማረጋገጥ አመልካች በማህበር አባልነት መቀጠል የማይፈልጉ ከሆነ ድርሻቸውን በመውሰድ ከአባልነት መውጣት ስለሚችሉ የማህበሩ ህልውና እንዲቀጥል የማድረጉን አስፈላጊነት ከአጠቃላይ ክርክሩ ተገንዝቦ በዚህ አግባብ ወስኗል። በዚህ መልኩ ማህበሩ ሊፈርስ አይገባም ተብሎ መወሰኑ ደግሞ የንግድ ህጉን ድንጋጌዎች የተከተለ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም።

ሁለተኛው ጭብጥ 1ኛ ተጠሪ በርቀት 2ኛ ተጠሪን ቋሚ ስራ ኖሮት መምራት የማይችል በመሆኑ እንዲሻር የቀረበውን ጥያቄ የተመለከተ ነው። እንደሚታወቀው የማህበሩ ሥራ አስኪያጅ ሆኖ በማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ ወይም በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የተመረጠ ሰው በህጉ፣ በመመስረቻ ጽሁፉ እና መተዳደሪያ ደንቡ የተሰጠውን ሥልጣን (ኃላፊነት) በተገቢው ትጋት መወጣት፣ ጊዜውንም በሥራው ላይ ማዋል፣ ማህበሩንም በአግባቡ መምራትና ማስተዳደር ይጠበቅበታል። የማህበሩ ሥራ አስኪያጅ በመሆን በማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ የተሾመ ወይም በማህበርተኞች የተሾመም ቢሆን የስራ አስኪያጅን መሻር በተመለከተ አቤቱታ ሲቀርብ ፍርድ ቤት ሊቀበለው በሚችለው ተገቢ ምክንያቶች ሊሻር ይችላል። ማንኛውም ማህበርተኛ ቢሆን በሚገባ ምክንያት ሥራ አስኪያጅ እንዲሻር ለፍርድ ቤት ክስ ሊያቀርብ ይችላል። እነዚህን መሰረታዊ ሀሳቦች በክርክሩ ወቅት ሥራ ላይ ከነበረው የንግድ ህጉ አነቀጽ 527 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል።

ስለሆነም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሥራ አስኪያጅ እንዲሻር ከማህበርተኞቹ አንዱ ክስ ሊያቀርብ መቻሉ እና በተገቢ ምክንያቶች በፍርድ ቤት ውሳኔ ከሥራ አስኪያጅነት ሊሻር መቻሉ በህጉ ተቀባይነት ያለው ነው።

ሥራ አስኪያጁ እንዲሻር የሚያደርጉ ተገቢ ምክንያቶች ምን እንደሆኑ በህጉ ተለይተው ተዘርዝረው ባይቀመጡም ለሥራ አስኪያጁ በህጉ ፣ በማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ ፣ በመተዳደሪያ ደንብ፣ እንዲሁም በጠቅላላ ጉባኤዎች በሚተላለፉ ውሳኔዎች የተጣለበትን ኃላፊነት መወጣት ካለመቻል፤ የማህበሩን የዕለት ከዕለት ተግባራት በቅርበት በኃላፊነት አለመምራት፣ ማህበሩ የተቋቋመበትን አላማ ዳር ለማድረስ አለመቻል፣ የማህበሩንና የማህበርተኞችን መብትና ጥቅም የሚጎዱ ተግባራት መፈፃም እና የመሳሰሉት ምክንያቶች እንደ ሁኔታው ተገቢ ምክንያቶች ተብለው የሚወሰዱ ናቸው።

በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ በቋሚነት በካናዳ ሀገር የሚኖሩ መሆናቸውና ራሳቸው ቋሚ ሥራ ያላቸው መሆኑ ግራቀኙን አላከራከረም። 1ኛ ተጠሪ ይህን አምነው ይቀበሉታል። መከራከሪያቸው የሥራ አስኪያጁን በአገር ውስጥ በአካል መገኘት የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች ሲኖሩ ወደ ኢትዮጵያ በተለያየ ጊዜ የሚመጡ በመሆኑ እና በሌሎች ጉዳዮች ደግሞ በኢ-ሜይል የመልዕክት ልውውጥ እያደረጉ ማህበሩን የሚመሩ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

ይሁንና በማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 8(3) ስር የሥራ አስኪያጁ ስልጣንና ተግባራት ተብለው ከ8(3)(1) እስከ 8(3)(12) ድረስ ተዘርዝረዋል። በዚህ መሰረት የማህበሩ ሥራ አስኪያጅ የዘርፍ ሥራ አስኪያጆችን መሾምና መቆጣጠር፣ ማህበሩን በመወከል መፈረም፣ ለማህበሩ ቴክኒካዊ እና አስተዳደራዊ ተግባሮች ኃላፊ መሆን፤ የጠቅላላ ጉባኤና የቦርዱን ውሳኔዎች ሥራ ላይ ማዋል፤ ለማህበሩ የሚከፈል ገንዘብ መቀበል፣ ዕዳ መክፈል፣ የተለያዩ ዕለታዊ ሰነዶችን መፈረም፤ ሰራተኛ መቅጠርና ማስተዳደር፤ የባንክ ሂሳብ ከፍቶ ገንዘብ ገቢ ማድረግና ሂሳቡን በፊርማው ማንቀሳቀስ፤ የግዥና ሽያጭ ማዘዣዎችን መወሰን፤ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር ውል መዋዋል፤ በፍርድ ቤት ክርክር ማህበሩን በመወከል አስፈላጊውን መፈፀም፤ የሂሳብ ወጪና ገቢ መዝገብ በደንቡ እንዲያዝ ማድረግ እንዲሁም እነዚህን ተግባራት በተመለከተ ውክልና መስጠት ሥልጣንና ተግባር እንዳለው ተመልክቷል።

እነዚህ በመመስረቻ ጽሁፉ የተመለከቱ ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት የማህበሩን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ የሚመለከቱ በመሆናቸው 1ኛ ተጠሪ እንዳቀረቡት ክርክር አልፎ አልፎ ከውጭ ሀገር በመምጣት ሊከወን የሚችል አለመሆኑ ግልጽ ነው። ለረዥም ጊዜ በአሁን በአመልካች

ድጋፍ እና በኃላም አመልካች በምክትል ሥራ አስኪያጅነት ተሰይመው ማህበሩን እንዲመሩ በመደረጋቸው ምክንያት ማህበሩ ሲመራና ሲተዳደር ቆይቷል ከሚባል በቀር ለሥራ አስኪያጁ በመመስረቻ ጽሁፉና መተዳደሪያ ደንቡ የተሰጡትን ኃላፊነቶች 1ኛ ተጠሪ በቋሚነት በሚኖሩበት ካናዳ ሀገር ሆነው ወደ ኢትዮጵያ በተለያየ ጊዜ እየመጡ እና በኢ-ሜይል የመልዕክት ልውውጥ እያደረጉ ማህበሩን ይመሩ ነበር ለማለት አይቻልም፡፡ 1ኛ ተጠሪ በዚህ ሰበር ችሎት ካቀረቡት መከራከሪያም መገንዘብ እንደሚቻለው አሁንም ማህበሩን ባሉበት ሀገር ሆነው አልፎ አልፎ በመምጣት እና በመልዕክት ልውውጥ መምራት እንደሚፈልጉ የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በማህበሩ መመስረቻ እና ደንብ የተጣለባቸውን ዝርዝር ኃላፊነት መወጣት የማያስችል ነው፡፡

ሥራ አስኪያጁ በማህበሩ መመስረቻ ጽሁፍና በመተዳደሪያ ደንቡ የተጣለባቸውን ኃላፊነት መወጣት በማይችሉበት ሁኔታና የማህበሩን የዕለት ከዕለት ተግባራትም በቅርበት በኃላፊነት መምራት እንደማይችሉ ከተረጋገጠ ይኸው ሁኔታ 1ኛ ተጠሪን ከማህበሩ ሥራ አስኪያጅነት ለመሻር ተገቢ ምክንያት ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ነው፡፡

ስለሆነም 1ኛ ተጠሪ የኪራይ ውል እርሳቸውና ባለቤታቸው ባለአክስዬን በሆኑበት ጃስፔራ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጋር ህንጻው ሳያልቅ የኪራይ ውል እንዲፈጸም ተጽእኖ አድርገዋል መባሉ፤ በዚህ ተግባር ጎርፍ ገብቶ ጉዳት ደረሰ መባሉ፤ 1ኛ ተጠሪ ዘመዶቻቸውን ግልጽነት በሌለው መንገድ የቀጠሩ መሆኑ፤ የድርጅቱን ማህተም ከአመልካች የነጠቁ እና አላግባብ ያገዷቸው መሆኑ፤ እንዲሁም አመልካች ያለአግባብ ከቼክ ፈራሚነት በማገድ ሌላ በስጋ ዘመድ የሆነ ሰው ቼክ ፈራሚ እንዲሆን ሰይመዋል የማህበሩንም ጥቅም ጎድተዋል የተባሉ ምክንያቶች ሁሉ በተለያየ ምክንያት በስር ፍርድ ቤቶች ውድቅ ቢደረጉም 1ኛ ተጠሪ የ2ኛ ተጠሪ ስራ አስኪያጅ ሆነው ቋሚ የመኖሪያ አድራሻው ካናዳ ሀገር ሆኖ እና ሌላ ቋሚ ስራ ያላቸው ስለመሆኑ ባላከራከረበት ሁኔታ እና መመስረቻ ፅሁፍና በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ የተመለከቱ የሥራ አስኪያጂ የእለት ተዕለት ተግባራትና በፍሬ ነገር ደረጃ በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡ እውነታዎች 1ኛ ተጠሪ 2ኛ ተጠሪን በርቀት እንዲመሩ የማያስችላቸው በሆኑበት ሁኔታ ከሥራ አስኪያጅነት ሊሻሩ አይገባም ተብሎ መወሰኑ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በአጠቃላይ 1ኛ ተጠሪ ከስራ አስኪያጅነት ሊሻሩ ይገባል ተብሎ የቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ መደረጉ በወቅቱ ሥራ ላይ የነበረውን የንግድ ህግ አንቀጽ 527(3) እና (5) ፤ የአዋጅ ቁጥር 1243/2013 አንቀጽ 517(1)፣ እንዲሁም የማህበሩን መመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ

መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ውሳኔው የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 258336 በቀን 04/10/2011 ዓ.ም እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 243487 በቀን 09/09/2013 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ.348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2ኛ ተጠሪ ማህበር ሊፈርስ አይገባም ተብሎ መወሰኑ፤ አመልካች በማህበር አባልነታቸው መቀጠል የማይፈልጉ ከሆነ ድርሻቸውን በመውሰድ ከአባልነታቸው መውጣት የሚችሉ ስለመሆኑ፤ እንዲሁም አመልካች ከማህበሩ ያላቸው የአክሲዮን ድርሻ የገበያ ዋጋ የሚገምት ባለሙያ እንዲሾምና ድርሻቸው እንዲታወቅ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡

1ኛ ተጠሪ ከዋጋ ሜዲካል ኃ/የተ/የግ/ማህበር ስራ አስኪያጅነታቸው እንዲነሱና በምትካቸው ሌላ ሥራ አስኪያጅ እንዲሾም ሊደረግ አይገባም በማለት የተሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡

1ኛ ተጠሪ ከዋጋ ሜዲካል ኃ/የተ/የግ/ማህበር ስራ አስኪያጅነታቸው እንዲሻሩ ወስነናል፡፡

የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ሌላ ሥራ አስኪያጅ የሚሾምበትን ሁኔታ ከግራቀኝ ክርክርና ከህጉ አንጻር ተመልክቶ በተቻለ ፍጥነት ተገቢውን እንዲወሰን ጉዳዩን መልሰናል፡፡

የዚህ ውሳኔ ግልባጭ በአፋጣኝ ለስር ፍርድ ቤት ይድረሰው ብለናል፡፡

በዚህ ፍርድ ቤት ስለተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

የስር ፍርድ ቤት መዝገብ በመጣበት መልኩ ይመለስ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ.መ.ቁ.150290

ሐምሌ 23 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡ 1. ተኽሊት ይመሰል

2. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

3. ቀነዓ ቂጣታ

4. ተሾመ ሽፈራዉ

5. አብዬ ካሳሁን

አመልካች፡....አርቲስት ንዋይ ደበበ - ቀርበዋል፡፡

ተጠሪ፡.....አቶ ኤፍሬም ኤርሚያስ - ጠበቃ አቶ ሙሉጌታ ብሰማ ቀርበዋል፡፡

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍርድ</u>

ይህ ጉዳይ የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች 1ኛ ተከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ እና በዚህ ችሎት የክርክሩ ተካፋይ ያልሆነች ወ/ሮ አምሮት ደግፌ 2ኛ ተከሳሽ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.147071 በ23/2/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች ያቀረበዉን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ዉሳኔ ለመስጠት ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ ከሳሽ (የአሁን ተጠሪ) ባቀረበዉ ክስ 1ኛ ተከሳሽ ከአሜሪካን ሀገር ወደ ሀገር ቤት ለመመለስ ፈለገዉ ገንዘብ እንዳበድረዉ በስልክ ደዉሎ በጠየቀኝ መሰረት 20,000 (ሀያ ሺህ) ዶላር 2ኛ ተከሳሽ መተማመኛ ፈርማ ወስዳ ለ1ኛ ተከሳሽ የሰጠች ቢሆንም ይህ ገንዘብ ስላልተከፈለኝ፣ ፍ/ቤቱ ከእነዚህ ተከሳሾች ኃላፊነቱ የማን እንደሆነ ለይቶ ገንዘቡን ከሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍሉኝ እንደወሰንልኝ በማለት ከሷል፡፡

በዚህ ክስ ላይ 1ኛ ተከሳሽ በሰጠዉ መልስ ይህን ያህል የዉጪ ምንዛሪ ያለፈቃድ ማበደር በወንጀል የሚያስጠይቅ ስለሆነ ዉሉ ሕገ ወጥ ነዉ፣ ከሳሽ በ2ኛ ተከሳሽ በኩል ለ1ኛ ተከሳሽ ሰጥቻለሁ የሚሉት ዶላር በብድር ሳይሆን ለሙዚቃ ኮንሰርት ሥራ የተከፈለ የቅድሚያ ክፍያ

ነዉ፣ 2ኛ ተከሳሽ የፈረሙት ሰነድ ብድር መሆኑን በግልጽ አያሳይም፣ የብድር ዉል የለም፣ ከሳሽ ብድሩን በሰዉ ምስክሮች ለማስረዳት ያቀረበዉ ጥያቄ የሕግ አግባብነት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡ 2ኛ ተከሳሽ በበኩሏ ባቀረበችዉ መልስ እኔ ገንዘቡን ከከሳሽ ተቀበዬ ለተከሳሽ የማድረስ ስራ ብቻ እንጂ ሌላ ሚና የለኝም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር የሰዉ ምስክሮች በመስማት፣ የሰነድ ማስረጃ በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ 1ኛ ተከሳሽ በክሱ የተመለከተዉን 20,000 (ሀያ ሺህ) ዶላር ከከሳሽ መቀበሉን አልካደም፣ ነገር ግን ከሳሽ ገንዘቡ በብድር የተሰጠ ነዉ በማለት ሲከራከር፣ 1ኛ ተከሳሽ ደግሞ ገንዘቡ በብድር ሳይሆን ለሙዚቃ ኮንሰርት የቅድሚያ ክፍያ የተከፈለ ነዉ በማለት የተከራከሩ ሲሆን፣ ከቀረበዉ ማስረጃ መገንዘብ የሚቻለዉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2472 (2) መሰረት የብድር ዉል የሚያቋቁም ማስረጃ የለም፣ ይህ ገንዘብ ለሙዚቃ ኮንሰርት የቅድሚያ ክፍያ የተከፈለ በመሆኑ፣ ከኮንሰርቱ የሚገኘዉን ገቢ በተመለከተ በመ.ቁ.95218 ላይ በተጀመረዉ ክርክር መሰረት በጋራ ሂሳባቸዉ በባለሙያ እንዲሰራ በማድረግ መከፋፈል ይችላሉ በማለት የቀረበዉን ክስ ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

የሥር ከሳሽ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ ይግባኝ ባይ በሥር ፍ/ቤት ያቀረቡት የሰነድ እና የሰዉ ማስረጃ መልስ ሰጪ ይህን ገንዘብ በብድር ዉል መዉሰዳቸዉን ሚዛን በሚደፋ መልኩ የሚያስረዳ በመሆኑ፣ መልስ ሰጪ ደግሞ ገንዘቡን የወሰዱት ለሙዚቃ ኮንሰርት ሥራ የቅድሚያ ክፍያ መሆኑን ያቀረቡት ማስረጃ ስለሌለ፣ መልስ ሰጪ 20,000 (ሀያ ሺህ) ዶላር ወይም ብር 400,000 (አራት መቶ ሺህ) ለይግባኝ ባይ እንዲከፍሉ በማለት የሥር ዉሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይህን ዉሳኔ በማጽናት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች ህዳር 27 ቀን 2010 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር ምንም ዓይነት የብድር ዉል ባላደረኩበት፣ ተጠሪ በሐዋላ ወረቀት ገንዘብ የላኩት ለሥር 2ኛ ተከሳሽ እንጂ ለአመልካች ገንዘብ ባልላከበት፣ ተጠሪ ይህን ገንዘብ ለሥር 2ኛ ተከሳሽ የሰጠዉ አመልካችና ተጠሪ በጋራ ለማከናወን ላቀድነዉ የሙዚቃ ኮንሰርት የቅድሚያ ክፍያ እንጂ በብድር መልክ አይደለም፡፡ በአመልካችና በተጠሪ መካከል በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2472 መሰረት የብድር ዉል መኖሩን የሚያስረዳ ማስረጃ የለም፡፡ በሥር ፍ/ቤት የቀረበዉ ማስረጃ የገንዘብ መቀበያ

ደረሰኝ እንጂ የብድር ዉል የሚያቋቁም አይደለም። በሥር ፍ/ቤት የቀረቡት የሰዉ ምስክሮች በሰጡት የምስክርነት ቃል ገንዘቡ ከኮንሰርት ሥራ ጋር የሚገናኝ መሆኑን መስክሯል። የሥር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሕጉ አግባብ ጉዳዩን በመመርመር የብደር ዉል የለም በማለት ክሱን ዉድቅ በማድረግ ዉሳኔ ሰጥቶ እያለ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሥር ዉሳኔ በመሻር የብድር ዉል አለ በማለት በክሱ የተመለከተዉን ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፍል የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህን ዉሳኔ ማረም ሲገባዉ በማጽናት መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ፣ ወጪና ኪሳራ የመጠየቅ መብቱ እንዲጠበቅልኝ በማለት አመልክቷል።

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣በአመልካችና በተጠሪ መካከል የብድር ዉል አለ የመባሉን አግባብነት፣ ለመመርመር ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት በ6/6/2010 ዓ.ም የተጻፈ ስምንት ገጽ መልስ አቅርቧል። በዚህ ጉዳይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የቀረበዉን ማስረጃ በመመርመር የብድር ዉል መኖሩን እንደሚያረጋገጥ በመገንዘብ አመልካች በክሱ የተመለከተዉን ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፍል የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የጸደዉ ዉሳኔ ምንም ዓይነት የሕግ ስህተት የማይገኝበት ስለሆነ ዉሳኔዉ በአግባቡ ነዉ እንዲባልልን፣ አመልካች በዚህ ክርክር ምክንያት የደረሰብን ወጪዎችና የጠበቃ አበል እንዲተካ እንዲወሰንልኝ በማለት በዝርዝር ተከራክሯል። የአሁን አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኞቸዉን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል። እንደመረመርነዉ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰዉ የአሁን ተጠሪ ለክርክር ምክንያት የሆነዉን ገንዘብ ለአመልካች የሰጠሁት በብድር ነዉ፣ የብድር ዉል አለ ስለዚህ በዉሉ መሰረት አመልካች ይህን ገንዘብ ስላልከፈለኝ እንዲከፍለኝ የሚል ዳኝነት መጠየቁን መገንዘብ ይቻላል። አመልካች በበኩሉ ይህን ገንዘብ መዉሰዱን ሳይክድ ገንዘቡ የተከፈለዉ በጋራ ለሚናዘጋቸዉ የሙዚቃ ኮንሰርት የቅድሚያ ክፍያ ነዉ እንጂ ብድር አይደለም፣ የብድር ዉል የለም በማለት ተከራክሯል።

የግራ ቀኞቸዉ ክርክር ይህ ከሆነ በዚህ ጉዳይ ምላሽ የሚሻዉ በሕጉ አግባብ የተቋቋመ የብድር ዉል አለ ወይስ የለም? የሚለዉ ነጥብ ነዉ። ከዚህ አንጻር የአሁን ተጠሪ የብድር ዉል መኖሩን ለማስረዳት በሥር ፍ/ቤት ያቀረበዉ የሰነድ ማስረጃ ሲታይ ሚያዚያ 6 ቀን 2000

ዓ.ም የሥር 2ኛ ተከሳሽ የፈረሙት የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ፣ በሥር 2ኛ ተከሳሽ ስም በሐዋላ የተለካ ገንዘብ የሚያሳይ ሰነድ እና የሰዉ ምስክሮች መሆናቸዉን የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ የአሁን አመልካች በበኩሉ ባቀረበዉ ክርክር ይህን ገንዘብ በብድር የወሰደ ሳይሆን ለሙዚቃ ኮንሰርት የቅድሚያ ክፍያ የተከፈለ ነዉ በማለት ይህንኑ ለማስረዳት የሰዉ ምስክሮችን የቆጠረ መሆኑን የሥር ዉሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ ከግራ ቀኙቸዉ ክርክር አንጻር የአሁን ተጠሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.259 (1) መሰረት በሕጉ አግባብ የተቋቋመ የብድር ዉል መኖሩን በቅድሚያ የማስረዳት ሸክም እንዳለበት የሚያከራክር አይሆንም፡፡ አመልካች ደግሞ በሕግ አግባብ የተቋቋመ የብድር ዉል እንደሌላ አለኝ የሚለዉን ማስረጃ አቅርቦ የማስረዳት ሸክም እንዳለበት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.259 (2) ሥር ተመልክቷል፡፡ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠዉ ፍሬ ነገር በሕጉ አግባብ የተቋቋመ የብድር ዉል መኖሩን የሚያረጋግጥ መሆን አለመሆኑን መፈተሹ አስፈላጊ ነዉ፡፡

እንደሚታወቀዉ የሚያልቅ ነገር ብድር በተመለከተ እንደአግባብነቱ ተፈጻሚነት ያለዉ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2471-2489 ድንጋጌዎች መሆናቸዉን ማየት ይቻላል፡፡ ስለሆነም የሚያልቅ ነገር የብድር ዉል አለ ለማለት በእነዚህ የህግ ድንጋጌዎች የተመለከቱትን አስገዳጅ ድንጋጌዎች ባከበረ መልኩ መፈጸሙ ሲረጋገጥ ብቻ ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት የገንዘብ ብድር ዉል መኖሩን እና ክፍያ መፈጸሙን ለማረጋገጥ አግባብነት ያለዉን ማስረጃ ምን እንደሆነ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2472 ሥር ተደንግጎ እናገኛለን፡፡ በዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር እንደተመለከተዉ ከ500 (አምስት መቶ) ብር በላይ የተደረገዉን የገንዘብ ብድር ዉል ለማስረዳት የሚቻለዉ የብድር ዉሉን ጽሑፍ በማቅረብ ወይም በፍ/ቤት በተደረገ የእምነት ቃል ወይም መሓላ እንደሆነ ነዉ፡፡ የዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 2 ደግሞ ለብድር ዉል ማናቸዉም ሌላ ዓይነት ማስረጃ ለማቅረብ እንደማይቻል ደንግጓታል፡፡ እንዲሁም ከብር 500 (አምስት መቶ) በላይ የመክፈል ነገር ማስረዳት የሚቻለዉ በዚሁ አግባብ መሆን እንዳለበት የዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 3 ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ተዋዋይ ወገኖች በመካከላቸዉ የገንዘብ ብድር ዉል ለማድረግ መፈለጋቸዉን ሙሉ ፈቃዳቸዉን ተከትሎ የተፈጸመ መሆን እንዳለበት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1678 (ሀ) እና 1679 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ተዋዋይ ወገኖች በዚህ አግባብ የገንዘብ ብድር ዉል ለማድረግ ፈቅደዉ አዉቀዉ ገብቷቸዉ ዉል ያደረጉ እና ዉሉም ደግሞ ከፍ ሲል በተጠቀሰዉ የፍትሓ ብሔር ሕግ ቁጥር 2472 አግባብ የተደረገ መሆን እንዳለበት መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ አመልካች እና ተጠሪ በክስ የተመለከተዉን ገንዘብ ብድር ዉል ለማድረግ ፈልገዉ እና አዉቃዉ የብድር ዉል ማድረጋቸዉን እና ይህም የብድር ዉል መኖሩን በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2472 (1) መሰረት የሚያስረዳ አግባብነት ያለዉ ማስረጃ መቅረቡን የሚያመለክት ነገር የለም፡፡ የአሁን አመልካች የተጠቀሰዉ ገንዘብ የብድር ዉል የለም በማለት ክዶ እስከተከራከረ ድረስ ተጠሪ 20,000 (ሀያ ሺህ) ዶላር ብድር መኖሩን ለማስረዳት አግባብነት ያለዉ ማስረጃ ማለትም በጽሑፍ የተደረገ የብድር ዉል ወይም በፍ/ቤት የተሰጠ የእምነት ቃል ወይም መሓላ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡ ነገር ግን አመልካች በዚህ አግባብ ያቀረበዉ ማስረጃ መኖሩን የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ አያመለክትም፡፡ ከሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ መገንዘብ የሚቻለዉ ተጠሪ የብድር ዉል መኖሩን ለማስረዳት ያቀረበዉ ማስረጃ በሥር 2ኛ ተከሳሽ በሐዋላ የተላከ ገንዘብ፣ የሥር 2ኛ ተከሳሽ የፈረመችዉ መተማመኛ እና የሰዉ ምስክሮች ናቸዉ፡፡ እነዚህ ማስረጃዎች ደግሞ ከፍ ሲል በተጠቀሰዉ የሕግ ድንጋጌ ከብር 500 በላይ የሆነዉን የገንዘብ ብድር ዉል ለማስረዳት አግባብነት ያለዉ ማስረጃዎች አይደሉም፡፡ የግራ ቀኞቸዉ የሰዉ ምስክሮች ቃል ሲታይ በግራ ቀኞቸዉ መካከል የሙዚቃ ኮንሰርት የሥራ ግንኙነት እንደነበረ እና ገንዘቡም የሰጠዉ ከዚህ ግንኙነት ጋር በተያያዘ መሆኑን የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ በመሆኑም የአሁን ተጠሪ ከአመልካች ጋር በሕጉ አግባብ የተቋቋመ የ 20,000 (ሀያ ሺህ) ዶላር የብደር ዉል ማድረጋቸዉን አግባብነት ባለዉ ማስረጃ ማስረዳቱን የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ ግልባጭ የማያመለክት ሆኖ ሳለ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የብድር ዉል አለ በማለት የሰጠዉን ዉሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህን ዉሳኔ ማረም ሲገባዉ በዉሳኔ በማጽናት የሰጡት ዉሳኔ ከፍ ሲል የተጠቀሰዉን የሕግ ድንጋጌ የሚጥስ ነዉ ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በግራ ቀኞቸዉ መካከል በሕጉ አግባብ የተቋቋመ የ 20,000 (ሀያ ሺህ) ዶላር የብድር ዉል መኖሩን የሚያስረዳ አግባብነት ያለዉ ማስረጃ ሳይቀርብ የብድር ዉል አለ በማለት አመልካች ይህን ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፍል የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ በመሆኑ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.182820 በ5/11/2009 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህን ዉሳኔ በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.147071 በ23/2/2010

ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.92571 በ12/3/2009 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ጸንቷል፡፡

በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በሕጉ አግባብ የተቋቋመ የ 20,000 (ሀያ ሺህ) ዶላር ብድር ዉል የለም ብለናል፡፡

በአመልካች እና በተጠሪ መካከላቸዉ በነበረዉ የሙዚቃ ኮንሰርት የሥራ ግንኙነት ጋር በተያያዘ በመ.ቁ.95218 ላይ ክርክር እንደነበር የተገለጸ በመሆኑ ያንን ክርክር ይህ ዉሳኔ የሚያግደዉ አይሆንም ብለናል፡፡

የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡

ግራ ቀኞቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

ጥር 9 ቀን 2010 ዓ.ም የተሰጠዉ የአፈጻጸም እግድ ትዕዛዝ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ.109032

መስከረም 30/2009ዓ.ም

ዳኞች ፦ አልማው ወሌ

ተፈሪ ገብሩ

አብርሃ መሰለ

አብዬ ካሣሁን

እትመት አሠፋ

አመልካች (ቾች)፦ 1. አቶ ስማቸው ከበደ } ጠበቃ - ስንዱ ዓለሙ - ቀረቡ

2. ጂ.ኤች.ሲ.ሚክስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር }

ተጠሪ(ዎች) ፦ ኢንተርኮንቲኔታል ሆቴልስ ኮርፖሬሽን - ጠበቃ ኢዮብ ሐጎስ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል።

<u>ፍርድ</u>

የጉዳዩ መነሻ የሆነው ክርክር የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው። በሥር ፍ/ቤት ተጠሪ ከሳሽ፤አመልካቾች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል። ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ ይዘት ፤ በአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 26 መሠረት በወቅቱ የንግድ ምልክት ምዝገባ ይሰጥ ከነበረው ከኢትዮጵያ ንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ከዚያም በኢትዮጵያ አእምሮአዊ ንብረት ጽ/ቤት እስከ መሥከረም 21 ቀን 2006 ዓ.ም ድረስ ታድሶ የሚገኝ ለ3ኛ ወገን የሆቴል አገልግሎት ለመስጠት የሚያችለው እና በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ብቸኛ ባለቤት እና ተጠቃሚ የሚያደርገው ቁጥር 3741 የሆነ የንግድ ምልክት ሰርትፍኬት የተሰጠው መሆኑን፤ አመልካቾች በአዲስ አበባ ከተማ ኢንተርኮንቲኔንታል አዲስ አበባ ሆቴል በሚል ስም የሚታወቅ ሆቴል ያቋቋሙ እና ያስመዘገቡ መሆኑን፤ አመልካቾች በተጠሪው የንግድ ምልክት ስም በዘረጉት ድህረገጽ በአዲስ አበባ አለምዓቀፍ ኤርፖርት የውጭ እንግዶች መግቢያ በር ላይ በመለጠፍ እና መጓጓዣ በማቅረብ በተጠሪው የንግድ ምልክት ከህግ ውጪ አላግባብ በመጠቀም ላይ መሆናቸውን ገልጾ አመልካች በንግድ ምልክቱ መጠቀም እንዲያቆሙ፤ በተለያዩ ዕቃዎች እና በየቦታው ያሉትን የንግድ ምልክቶች እንዲያስወግዱ፤ በተጠሪው የንግድ

ምልክት ሥም የከፈቱትን ድሕረገጽ እንዲዘጉ እና ሆቴሉ ከተቋቋመበት ጀምሮ ያገኙትን የተጣራ ትርፍ እንዲከፍሉ እንዲወሰንባቸው ዳኝነት የጠየቀ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

አመልካቾች ለቀረበባቸው ክስ በሰጡት መልስ ተጠሪው የሕግ ሰውነት ስለሌለው ክስ ለመመለስ የሚያስችል መብት የለውም፤ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ስላልቀረበ በይርጋ ይታገዳል፤ የንግድ ምልክቶቹም የተለያዩ ናቸው፤ ትክክለኛው የካሳ መጠንም በክሱ አልተመለከተም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል። በፍሬ ነገሩም ላይ ዝርዝር መልስ ሰጥተዋል።

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍ/ቤት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚሰራ የንግድ ድርጅት ሕጋዊ ሰውነት ያገኝ ዘንድ መመዝገቡ አስፈላጊ ነው። ተጠሪው በንግድ መዝገብ ካልተመዘገበ በቀር የንግድ ምልክት ሰርተፍኬት መያዙ ብቻ ሕጋዊ ሰውነት ሊያሰጠው አይችልም ። ተጠሪው በክስ ማመልከቻው ላይ በተገለጸው አድራሻ ላይ በተመለከተው ሐገር ሕግ መሠረት ተመዝግቦ ሕጋዊ ህልውና ያገኘ መሆኑን ገልጾ ያቀረበው ክርክር ሆነ ማስረጃ የለም። በመሆኑም ተጠሪ የሕግ ሰውነት የሌለው ድርጅት በመሆኑ መክሰስም ሆነ መከሰስ አይችልም በማለት ክሱን በብይን ውድቅ አድርጎታል።

ተጠሪ በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቧል። አመልካቾችም በበኩላቸው በሥር ፍ/ቤት ያቀረብናቸው ሌሎች መቃወሚያዎች ያልተስተባበሉ እና የሥር ፍ/ቤትም ሌሎች መቃወሚያዎች ላይ ብይን ሳይሰጥ ያለፈ በመሆኑ በሌሎቹ መቃወሚያዎች ምክንያት ክሱ ተቀባይነት የለውም እዲባልልን በማለት መስቀለኛ ይግባኝ አቅርበዋል።

ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የግራቀኙን አቤቱታ ከመረመረ እና ተጠሪ በውጪ አገር ሕጋዊ ሰውነት የተሰጠው መሆኑን የሚያረጋግጥለትን ማስረጃ በትዕዛዝ ካስቀረበ በኃላ ተጠሪ በውጪ አገር ሕግ መሠረት የህግ ሰውነት የተሠጠው በመሆኑ እና የንግድ ምልክቱንም በባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት ያስመዘገበ በመሆኑ ከንግድ ምልክቱ ጋር በተያያዘ መብቱን ለማስከበር ክስ የማቀርብበት ምክንያት የለም በማለት የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ብይን ሽሮ የስር ፍ/ቤት በቀሪ መቃወሚያዎች ላይ ብይን በመስጠት ክሱ የሚቀጥል ሆኖ ካገኘው ግራቀኙን በፍሬ ጉዳይ ላይ አከራክሮ የመሰለውን ይወስናል በማለት ጉዳዩን መልሶታል። የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ነው።

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፦ በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ወይም ያልተመዘገበ ንግድ ያለው እንደ ኢትዮጵያ ተቆጥሮ በንግድ ምልክት ምዝገባ ወረቀቱ ሊሰራበት የሚችለው ተመዝግቤበታለሁ ከሚለው ሌላ ሀገር ጋር ኢትዮጵያ የእንካ ለእንካ ሥምምነት

ከኖራት ወይም ኢትዮጵያ አባል የሆነችበት ዓለም አቀፍ ውል ካለ ብቻ ነው። ተጠሪ ኢትዮጵያ እና አሜሪካ የእንካ ለእንካ ስምምነት አላቸው አላለም፤ የንግድ ማህበራት የሕግ ሰውነት ማግኘት ይችሉ ዘንድ በንግድ መዝገብ መመዝገብ ይገባቸዋል፤ ተጠሪው በኢትዮጵያ ውስጥ የተመዘገበ የንግድ ሥራ የለውም፤ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 23626 የሰጠው ውሳኔም የንግድ ምልክት ምዝገባን አስመልክቶ በንግድ ህጉ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች የጠጠቀሱት አንቀጾች ትርጓሜ ያላገኙበት ስለሆኑ ከጉዳዩ ጋር አግባብነት የለውም። በመሆኑም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አግባብነት ያላቸውን የሕጉን ድንጋጌዎች በመጣስ የሰጠው ብይን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ነው። የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ችሎት መታየት የሚገባው ሆኖ ስለተገኘ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ግራ ቀኙ በጽሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል።

የጌዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል። እንደመረመረው የዚህንም ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው ዋነኛ ነጥብ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተጠሪው በውጪ አገር የተመዘገበ ድርጅት በመሆኑ እና የንግድ ምልክቱንም በባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት ያስመዘገበ ድርጅት ምልክቱ ጋር በተያያዘ መብቱን ለማስከበር ክስ የማያቀርብበት ምክንያት የለም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ ሆኖ አግኝቶታል።

ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ በውጪ አገር የተመዘገበ ድርጅት ለመሆኑ እና የንግድ ምልክቱንም በባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት ተገቢውን መመዘኛ አሟልቶ ያስመዘገበ ለመሆኑ ፍሬ ነገርን ለማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን ባለው የበታች ፍ/ቤት ተረጋግጧል። አምካቾች ተጠሪ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት የለውም በማለት በዋነኝነት የሚከራከሩት ተጠሪ በኢትዮጵያ ውሥጥ የጠመዘገበ የንግድ ድርጅት አይደለም ኢትዮጵያ እና ተጠሪው የተመዘገበበት አገርም የእንካ ግንኙ ነት የላቸውም በሚል ነው። የንግድ ምልክት እና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 501/98 የወጣበት አንዱ ዓላማ በንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎችን መልካም ሥም እና ዝና ለመጠበቅ በተመሣሣይ ዕቃዎች እና አገልግሎቶች መካከል መሣከርን ለማስወገድ መሆኑ ከአዋጁ መግቢያ መገንዘብ ይቻላል። ተጠሪ አዋጁ በሚፈቅደው አግባብ የንግድ ምልክቱን ያስመዘገበ በመሆኑ እና ድርጅቱ በተመዘገበበት አገር ሕጋዊ ሰውነት የተሰጠው በመሆኑ በአዋጅ አንቀጽ 26/1 እና 2 ድንጋጌ መሠረት ሌሎች ወገኖች የንግድ

ምልክቱን ወይም የንግድ ምልክቱን በሚመስል መለያ ሕዝብን ሊያሳስት በሚችል አኳሀን አላግባብ እንዳይጠቀሙበት ለማድረግ የሚያስችል መብት አለው፡፡ ከአዋጁ ዓላማ አኳያም ተጠሪ በኢትዮጵያ ውስጥ አለመመዝገቡን ምክንያት በማድረግ ክስ ሊያቀርብ አይችልም ሊባል የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ አመልካቾች በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ወይም ያልተመዘገበ ንግድ ያለው እንደ ኢትዮጵያዊ ተቆጥሮ በንግድ ምልክት ምዝገባ ወረቀቱ ሊሰራበት የሚችለው ተመዝግቤበታለሁ ከሚለው ሌላ ሀገር ጋር ኢትዮጵያ የእንካ ለእንካ ሥምምነት ከኖራት ወይም ኢትዮጵያ አባል የሆነችበት ዓለም አቀፍ ውል ካለ ብቻ ነው በማለት ክርክር ያቀረቡ እና ይህ የክርክራቸው ሐሳብም በአዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 2/4 እና 3 ላይ በግልፅ የተቀመጠ ቢሆንም የተጠሪ ክስ ጉዳዩ በቀረበለት ፍ/ቤት ተመርምሮ በአዋጁ መሠረት መብቱን ለማስጠበቅ የሚችል መሆን አለመሆኑ ውሣኔ የሚሰጥበት እንጂ ከወዲሁ ክስ ማቅረብ አይችልም ተብሎ ድምዳሜ የሚወሰድበት አይደለም፡፡

በሌላ በኩል አመልካቾች የንግድ ምዝገባ እና ፈቃድን አስመልክቶ የወጣው አዋጅ ቁጥር 686/2002 የንግድ ማህበራት የሕግ ሠውነት ማግኘት ይችሉ ዘንድ በንግድ መዝገብ መመዝገብ እንዳለባቸው ይደነግጋል በማለት መከራከሪያ አቅርበዋል፡፡ ሆኖም ይህ አዋጅ የተደነገገው ኢትዮጵያ ውስጥ የሚሰራበት የንግድ ሥራ ምዝገባ ሥርአትን አስመልክቶ እንጂ የንግድ ምልክት ምዝገባን አስመልክቶ የተደነገገ አይደለም፡፡ በአዋጁም ሆነ በንግድ ህጉ ላይ በውጪ አገር የተመዘገበ ድርጅት ኢትዮጵያ ውስጥ ካልተመዘገበ በቀር ክስ ለማቅረብ አይችልም በማለት አልተደነገገም፡፡

አመልካቾች የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.23626 የሰጠው ውሣኔም የንግድ ምልክት ምዝገባን አስመልክቶ በንድግድ ህጉ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጐች የተጠቀሱት አንቀጾች ትርጓሜ ያላገኙበት ስለሆኑ ከጉዳዩ ጋር አግባብነት የለውም በማለት ያቀረቡትን ክርክር ተጠቃሹን ውሣኔ መሰረት በማድረግ መርምረነወል፡፡ አመልካቾች በጠቀሱት የሰበር ውሣኔ የቀረበው ክርክር ከንግድ ምልክት ምዝገባ ጋር በተገናኘ የቀረበ ክርክር ሲሆን ፍ/ቤቱም ጉዳዩ የምዝገባ አስፈላጊ በኢትዮጵያ ውስጥየንግድ ስራን ለማካሔድ ነው፤ የንግድ ሥራ እና የነግድ ምልክት ማካሔድ የተለያዩ ተግባራ ናቸው፤ አመልካች በውጭ አገር ተመዝግቦ የህግ ሰውነት ያለው በመሆኑ በኢትዮጵያ ውስጥ የንግድ ምዝገባ ጥያቄ ቢያነስ አስቀድሞ ያገኘውን የህግ ሰወነት የሚያሳጣው አይደለም በማለት አመልካች ክርክር ለማቅረብ መብት አለው በማት ውሳኔ መስጠቱን የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ ውኔ የንገድ ሥራ ምዝገባ እና

የንገድ ምልክት መዝገባ የተለያዩ ተግራ መሆናቸውን፤ የሕግ ሰውነት ያለው እና የንገድ ምልክቱን ያስመዘገበ ሰው ከንግድ ምልክት ጋር በተያያዘ ክስ ማቅረብ የሚችል መሆኑ የሚያሳይ፤ ተጠሪ ከንግድ ምልክት ምዝገባ ጋር አያይዞ ላቀረበ ክርክር አግባብነት ያለው ውሳኔ ነው ከሚባል በቀር አመልካቾች እንደገለጹት ለጉዳዩ አግባነት ያለው ውሳኔ አይደለም፡፡ ሊባል አይገባም፡፡

ሲጠቃለል የንግድ ምልክት እና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 501/98 እና የንግድ ምዝገባ እና ፈቃድን አስመልክቶ የወጣው አዋጅ ቁጥር 686/2002 የተደነገጉበት የየራሳቸው የሆነ ዓላማ ያላቸው በመሆኑ፤ ተጠሪ በውጪ አገር የሕግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት በመሆኑ እና የንግድ ምልክቱንም በሚመለከተው ባለስልጣን መሥሪያ ቤት ያስመዘገበ በመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪ ክስ ለማቅረብ የሚያስች መብት አለው በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ.98150 ሕዳር 11 ቀን 2007 ዓ.ም በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ.134178 ታህሳስ 24 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠውን ብይን በመሻር የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.348/1/ መሰረት ጸንቷል፡፡

በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

በ20/05/207 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው ዕግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፅ/ወ

የኢትዮጲያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰ/መ/ቁጥር 182772

ታህሳስ 29 **ቀን** 2013 **ዓ.ም**

ዳኞች፡- *መዓዛ አሸናፊ*

እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

አመልካች ፡-ቡና ኢንተርናሽናል ባንክ

ተጠሪ ፡- የፌዴራል *ፖ*ሊስ የምሥራቅ ቀጠና ወንጀል ምርመራ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

<u>ፍርድ</u>

ይህ የሰበር መዝገብ ተከፍቶ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ድሬደዋ ምድብ ችሎት ባስከበርኩት ንብረት ላይ የተሰጠ እግድ ይነሳልኝ በሚል አቅርቦት የነበረው አቤቱታ ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱ እና በይግባኝም አለመታረሙ በተሰጠው ውሣኔ ላይ *መሠረታዊ* የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ ሲል አቤቱታ በማቅረቡ ነው።

ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ ላየው ፍ/ቤት አመልካች አቀርቦት የነበረው አቤቱታ እንደሚያሳየው አቶ ዘሪሁን ላቀው መኮንን ለተባለ ግለሰብ ነሐሴ 29 ቀን 2007 ዓ.ም በተፈፀመ የመያዣ ውል *መሠረት* የሠ.ቁ ኢት 3-75500 የሆነ ተሽከርካሪን ግለሰቡ በሙስና ወንጀል በወንጀል በተከሰሱ ጊዜ ተጠሪ ይህን መኪና ያሳገደ በመሆኑ በታገደው ንብረት ላይ የቀዳሚነት መብት ስላለው እግዱ እንዲነሳለት አመልክቷል።

ፍ/ቤቱም የታገደው ንብረት በሙስና ወንጀል የተገኘ ወይም በወንጀል በተገኘ ንብረት የተፈራ መሆን አለመሆኑ ገና ውሣኔ ያላረፈበት በመሆኑ በሙስና የተገኘ ወይም በሙስና በተገኘ ንብረት የተፈራ ከሆነ ደግሞ የተከሣሹ ንብረት ነው ለማለት ስለማይቻል ከወዲሁ ለባንኩ ዕዳ መክፈያ ይሸጥ በሚል የዕግድ ትዕዛዙን ለማንሳት አይቻልም በሚል አቤቱታውን ውድቅ በማድረግ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት ትዕዛዝ ቅር ተሰኝቶ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ቅሬታውን ያቀረበ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አስቀርቦ እና ጉዳዩን መርምሮ ንብረቱ በሙስና ወንጀል ወይንም በወንጀል የተፈራ በሚል ጥርጣሬ የታገደ ከመሆኑ አኳያ የሙሰና ወንጀል ክርክሩ የመጨረሻ እልባት ባላገኘበት የንብረቱ እግድ የሚነሳበት አግባብ የለም በማለት የስር ፍ/ቤት ትዕዛዝን በማጽናት ወስኗል፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት በተሰጠው ፍርድ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ይታረምልኝ ሲል ነሐሴ 20 ቀን 2011 ዓ.ም. የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአቤቱታው ይዘትም በአጭሩ፡- ባንኩ ለግለሰቡ ለሰጠው የብር 715000.00 ብድር ተመላሽ የሠ.ቁ. 03-75500 የሆነው ተሽከርካሪ በመያዣነት ይዟል፡፡ተሽከርካሪው በመያዣ የተያዘው የብድር ገንዘቡ ባይመለስ መኪናውን ሸጦ ገንዘቡን ለማስመለስ በመሆኑ፣ ብድሩን ሲሰጥ ንብረቱን አሳግዶ የቀዳሚነት መብት በንብረቱ ላይ ያለው በመሆኑ ሸጦ ለብድር መክፈያ እንዲያውለው እግድ እንዲነሳለት ጠይቋል፡፡

ንብረቱን እንዲመዘግብልን የፌዴራል ት/ባ/የአ/አ/ት/ቅ/መ/ቤት አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ት/ጽ/ቤት አመልክተንም ቅ/ጽ/ቤቱ የባንኩን የመያዝ መብት በቀዳሚነት በ02/13/2007 ዓ.ም. አረጋግጦ የመዘገበ በመሆኑ ገንዘቡን በብድር ሰጥቷል፡፡

የስር ፍ/ቤት እግዱ አይነሳም ሲል የሰጠው ትዕዛዝ አዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 16/ 3/ ስር ከተቀመጠው የእግድ ትዕዛዝ እንዲነሳ ወይም እንዲሻሻል ሊደረግ እንደሚችል ከተደነገገው ጋር የሚጣረስ በመሆኑ ጉዳዩ የመጨረሻ እልባት ባያገኝም በበቂ ምክንያት ላይ የተመሠረተ ከሆነ ፍ/ቤቱ ሊወስን እንደሚሸል የሚደነግግ ስለሆነ ከዚህ አንፃር ሊመለከትልን ሲገባ፣ የፍ/ቤቱ ትዕዛዝ አስቀድሞ ትርጉም ከተሰጠበት የሰ/መ/ቁ/ 81215 ጋር የሚቃረን በመሆኑ፣ አመልካች የመያዣ መብቱን ያስመዘገበው ጳጉሜን 02 ቀን 2007 ዓ.ም. ሆኖ ፍ/ቤቱ እግድ የሰጠው ደግሞ ግንቦት 28 ቀን 2009 ዓ.ም. በመሆኑና ንብረቱን አስቀድሞ አመልካች ካሳገደ በኋላ መሆኑ፣ ባንኩ ንብረቱን ሲያሳግድ ከማንም አካል በንብረቱ ላይ እግድ የሌለ መሆኑ ሰበር

አስቀድሞ ትርጉም ከሰጠበት የሰ/መ/ቁ/ 16218 ጋር ተገናዝቦ መወሰን ሲገባው እግድ አይነሳም ተብሎ መወሰኑ ስህተት በመሆኑ ሊታረምልን ይገባል ሲል ጠይቋል፡፡

አቤቱታው በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ አመልካች አቶ ዘሪሁን ላቀው ለሰጠው ብድር አመላለስ በመያዣ ውል መሠረት ተበዳሪ ያስያዘው ተሽከርካሪ ላይ የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ እንዲነሳለት አመልካች ያቀረበው አቤቱታ በስር ፍ/ቤት ውድቅ የተደረገበትን አግባብነት ከሰ/መ/ቁ/ 81215 ከተሰጠው ትርጉም አንፃር ለመመርመር ሲባል መልስ ሰጪን ያስቀርባል ተብሎ ጭብጥ በመያዙ መነሻነት መዝገቡ ለችሎቱ ሊቀርብ ችሏል፡፡

አቤቱታው ከማስቀረቢያ ነጥቡ ጋር ለተጠሪ ደርሶት መልስ እንዲያቀርብ መጥሪያ ቢላክለትም ሳይቀርብ በመቅረቱ መልስ የማቅረብ መብቱ ታልፏል፡፡ የፌ/ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በክርክሩ ጣልቃ ልግባ ሲል አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም በስር ፍ/ቤት ተከራካሪ ያልነበረ በመሆኑ በሰበር ደረጃ ጣልቃ ልግባ ሲል ያቀረበውን አቤቱታ ችሎቱ ስላልተቀበለው ውድቅ አድርጐታል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል እኛም የቀረበውን አቤቱታ ከስር ፍ/ቤት ትዕዛዝ ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንፃር እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች አቀርቦት የነበረው አቤቱታ እንደሚያሳየው አቶ ዘሪሁን ላቀው መኮንን ለተባለ ግለሰብ ነሐሴ 29 ቀን 2007 ዓ.ም በተፈፀመ የመያዣ ውል መሠረት የሠ.ቁ ኢት 3-75500 የሆነ ተሽከርካሪን ግለሰቡ በሙስና ወንጀል በወንጀል በተከሰሱ ጊዜ ተጠሪ ይህን መኪና ያሳገደ በመሆኑ ከመከሰሱና ተጠሪ ንብረቱን ከማሳዱ አስቀድሞ በታገደው ንብረት ላይ የቀዳሚነት መብት ስላለው እግዱ እንዲነሳለት አመልክቷል፡፡

ከማስቀረቢያ ነጥቡ አንፃር አመልካች በተሽከርካሪው ላይ የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ እንዲነሳለተ ያቀረበው አቤቱታ በስር ፍ/ቤት ውድቅ መደረጉ ተገቢ ነው ወይንስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ በሰበር ደረጃ በጭብጥነት ተይዞ ሊመረመር የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በአንድ በማይንቀሳቀስ እና ልዩ ተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ በሕግ አግባብ የተቋቋመ የመያዣ መብት በሕግ ጥበቃ የሚደረግለት ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር የፍ/ሕ/ቁጥር 2828፣2857/1/ እና 3059 ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ይዘት ያሳያሉ፡፡ በሕግ አግባብ የተቋቋመው የመያዣ ውል መኖሩ ከተረጋገጠ ደግሞ ይኼው መብት ያለው ሰው ከሌላው ሰው የቀደመ መብት ያለው መሆኑን የድንጋጌዎቹ ጣምራ ንባብ ያስረዳል፡፡ በባንክ በመያዣ ስለተያዙ

የማይንቀሳቀሱ የሚንቀሳቀስ ንብረቶችን አስመልክቶ በወጣው አዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 3 ሲታዩ ደግሞ ባንክ በመያዣ የያዛቸውን ንብረቶች እዳው ሳይከፈለው በቀረ ጊዜ የ30 ቀን ማስጠንቀቂያ ለተበዳሪው በመስጠት ያለማንም ጣልቃ ገብነት በመያዣ የያዘውን ንብረት በመሸጥ ገንዘቡን ገቢ ማድረግ እና ከዚህም ሌላ መያዣ የተቀበለ ባለገንዘብ ከመያዣው ሽያጭ ዋጋ ከሌሎች ባለገንዘቦች ቀድሞ የመቀበል መብት እንዳለውም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2857/1/ ላይ ተደንግጓል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች አንጻር አመልካች ለብድር አከፋፈል በመያዣነት በያዘው ንብረት ላይ የቀደምትነት መብት እንዳለው መገንዘብ ይቻላል፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ አቶ ዘሪሁን ላቀው መኮንን የተባሉ ግለሰብን በሙስና ወንጀል የከሰሰ ሲሆን ለንብረት ማካካሻ ይሆን ዘንድ በግለሰቡ ስም ተመዝግቦ የሚገኘውን እና አመልካች አስቀድሞ ግለሰቡ ለተበደሩት 715,000.00 የዕዳ አመላለስ በሚል በመያቸጉነት የያዘውን የሠ.ቁ. 03-75500 ኢት ተሽከርካሪን በፍ/ቤት አሳግዷል፡፡

የአመልካች ጥያቄም ለዕዳ መክፈያነት የያዝኩትን ንብረት ዕግድ የተሰጠበት በመሆኑ ዕግዱ ተነስቶልኝ ሽጬ ዕዳውን ተመላሽ ላድርግ የሚል ነው፡፡

አመልካች ለግለሰቡ ብድሩን የሰጠው ለእዳው መልካም አመላለስ ይረዳው ዘንድ ተሽከርካሪውን በመያዣ የያዘው በንብረቱ ላይ ምንም ዓይነት ዕዳ እና እገዳ የሌለበት መሆኑን አጣርቶ ከመሆኑም በላይ በግለሰቡ ላይ ተጠሪ ክስ የመሰረተውም ብድሩ ከተሰጠ በኋላ መሆኑ የሚያከራክር ሆኖ አልተገኘም፡፡

በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 81215 መዝገብ ላይ በባንክ በመያዣነት የተያዘ ተሽከርካሪ በሌላ በኩል የጉምሩክ ደንብ በመተላለፍ ወንጀል ባለቤቱ ጥፋተኛነቱ ተረጋግጦበት ተሽከርካሪውም በመንግስት እንዲወረስ ውሣኔ የተሰጠበት እንደሆነ በህግ ፊት ቅድሚያ ተሰጥቶት ሊፈፀም ስለሚገባው ጉዳይ. በባንክ በመያዣነት የተያዘ ተሽከርካሪ ከመያዣው በኋላ በኮንትሮባንድ ወንጀል ምክንያት ለመንግስት ውርስ እንዲሆን በፍ/ቤት የመጨረሻ ፍርድ ባረፈበት ጊዜ ባለመያዣው ንብረቱን በመያዣነት የያዘው አካል የቀዳሚነት መብት ያለው መሆኑን በመግለጽ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡

ይህ ከሆነ ደግሞ ከላይ እንደተመለከትነው የፍ/ብ/ሕ/ ድንጋጌዎቹ ስለመያዣ መብት የደነገጉትን ስንመለከት እና ሰበር ከሰጠው ትርጉም አኳያ ባንኩ በያዘው ንብረት ላይ የቀዳሚነት መብት ያለው መሆኑን የሚያሳዩ በመሆኑ የሰሌዳ ቁጥሩ በተጠቀሰው ንብረት ላይ አመልካች የቀደምትነት መብት ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም አስቀድሞ አመልካች/ ባንኩ/ ለዕዳው መልካም

አመላለስ ሲል በንብረቱ ላይ ሌላ ጠያቂ የሌለበት መሆኑን አረጋግጦ ብድር ያበደረ መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ አንድ ጊዜ ንብረቱን በመያዣነት ከመዘገበ እና ገንዘቡን ወጪ አድርጐ ለተበዳሪው ከከፈለ በኋላ ሌላ ገንዘብ ጠያቂ ካለ በህግ በተሰጠው የቀደምትነት መብት ደረጃ መሠረት ከሚጠይቅ በቀር ባንኩ ባስከበረው ንብረት ላይ ዕግድ በማሰጠቱ ብቻ ባንኩ የቀደምትነት መብቱን የሚያጣበት ህጋዊ ምክንያት የሌለ በመሆኑ ባንኩ ተሸከርካሪው በሙስና በተገኘ ገንዘብ የተገዛ መሆኑን አስቀድሞ ያውቅ እንደነበረ ካልተረጋገጠ በቀር በስር ፍ/ቤቶች በንብረቱ ላይ የተሰጠው ዕግድ ሊነሳ አይገባም ሲሉ የደረሱበት መደምደሚያ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው ብለን ተከታዩን ወስነናል፡፡

ውሣኔ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/171066 በ12/11/2011 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 12782 ታህሳስ 15 ቀን 2011 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

አመልካች ለብድር ዕዳ መያዣነት በያዘው የአቶ ዘሪሁን ላቀው መኮንን ንብረት የሠ.ቁ. ኢት-3-75599 በሆነው ሲኖትራክ ተሽከርካሪ ላይ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክር እየተደረገበት ባለው የመ/ቁ/ 12782 በሆነው መዝገብ ላይ የተሰጠው ዕግድ ሊነሳ ይገባል ብለን ወስነናል፡፡

የሚያከራክረው መኪና በሙስና የተገኘ ነው የሚባል ከሆነ መኪናው ተሸጦ አመልካች ከሚፈልገው የዕዳ ተመላሽ ተራፊ ገንዘብ ካለ እና በግለሰቡ ላይ የወንጀል ጥፋተኝነት ውሣኔ ከተሰጠ ተጠሪ የተረፈውን ገንዘብ የመጠየቅ እንዲሁም የተሸከርካሪውን ቀሪ ዋጋ ያክል ከተሸከርካሪው ባለንብረት ሌላ ንብረት ላይ የመጠየቅ መብቱን ይህ ውሣኔ አያግደውም ብለናል፡፡

ግራ ቀኙ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ያወጡት ወጪ ካለ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

የውሣኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡

መዝገቡ ውሣኔ ስላገኘ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊሪማ አለበት

የሰ/መ/ቁ. 213835

መጋቢት 27 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ- ነ/ፈጂ ኤልሳቤጥ ጌታቸው

ተጠሪዎች- 1. ሲ ጂ ሲ አቨርሲስ ኮንስትራክሽን ሊሚትድ- ጠበቃ ጥላሁን ሰቦቃ

2. ወጋገን ባንክ አ.ማ - ነ/ፈጂ አዲሱ ሀሰን

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ ቼክን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ፣ አመልካች ተከሳሽ፣ እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ እና ሌሎች ሁለት ሰዎች ጣልቃ ገብ በመሆን የተከራከሩ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ባቀረበው ክስ በአመልካች ባንክ ቦሌ መድኃኒዓለም ቅርንጫፍ ካስከፈትኩት ሂሳብ ውስጥ ብር 221,054.40 ቁጥሩ EG 23310195 በሆነ ቼክ ለተከለኃይማኖት ደረጃ ሶስት የጭነት ትራንስፖርት ባለቤቶች እንዲከፈል ያዘዝኩ ቢሆንም ማህበሩ ቼኩን ለክፍያ ለአመልካች ሲያቀርብ ለክፍያ ከቀረበው ቼክ ጋር ተመሳሳይ ቁጥር ለያዘ እና 1ኛ ተጠሪ አውጥቶታል በተባለ ቼክ በቀን መጋቢት 12 ቀን 2010 ዓ.ም ብር 1,800,000.00 ኃይለመለኮት አርያም ለተባለ ግለሰብ ክፍያ ፈጽሚያለሁ በማለት ክፍያ እንዲፈፀምለት ትዕዛዝ ለሰጡለሁለት ማህበር ክፍያ ሳይፈጽም ቀርቷል፤ አመልካች ክፍያ ፈፅሜለታለሁ የሚለው ቼክ በ1ኛ ተጠሪ እጅ የሚገኘው የቼክ ጥራዝ አካል አይደለም፤ ሰነዱንም አላውቀውም፤ ስለሆነም አመልካች የቀረበት ቼክ ላይ ያለው ፊርማ የሂሳቡ ባለቤቶች መሆኑን ሳያረጋግጥ፣ በዳበረው አሰራርም ክፍያው እንዲፈፀም የማረጋገጫ እና የጽሁፍ ማሳወቂያ ደብዳቤ እንዲደርሰኝ ሳያደርግ ያለአግባብ የከፈለውን ገንዘብ ወጪ ከተደረገበት ጊዜ አንስቶ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍል ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

አመልካች በበኩሉ በቀን ጥር 22 ቀን 2011 ዓ.ም ጽፎ በሰጠው መልስ የቼኩ ክፍያ የቀረበው ለወጋገን ባንክ ቦሌ ቅርንጫፍ ሲሆን በቅድሚያ የታዘዘው ኃይለማርያም አርያም ለተባለ ግለሰብ ነው፤ በኋላም ተላልፎ ወይም በጀርባ ተፈርሞ የተከፈለው ከድጃ አብዱራህማን ለተባለች ግለሰብ ወጋገን ባንክ ቦሌ መድኃኒዓለም ቅርንጫፍ በከፈተችው ቁጥሩ 01734649230101 በሆነ ሂሳብ አማካኝነት ነው፤ ወጋገን ባንክ የላከው ቼክ ትክክለኛ እና ለክፍያ ብቁ ስለመሆኑ በቼኩ ጀርባ ላይ በባንኩ ሰራተኞች ፊርማ ለክፍያ ማረጋገጫ የሚሆነውን ለማስገባት ተቀብለናል የሚል ማህተም ቼኩ ላይ ተመቶበት ነበር፤ ለክሱ ምክንያት የሆነውን ቼክም ሆነ የክፍያ ማረጋገጫ ሰነዱን የተለያዩ ቅጾችን በመሙላት ጥርጣሬዎችን በመዘጋት በደንበኛው ጉዳይ ላይ እምነት እንዲኖረን በማድረግ ክፍያውን እንድንፈጽም ያደረገ በመሆኑ ኃፊነት ያለበት ወጋገን ባንክ ነው፤ 1ኛ ተጠሪ ሂሳቡን እንዲያንቀሳቅሱ የፈቀደላቸውን ግለሰቦች ያሳወቀን ሲሆን በቼኩ ላይ ያለው ፊርማ እና ግለሰቦቹ የሰጡት ናሙና የፊርማ ተመሳሳይ ነው፤ ፊርማውን በእይታ ብቻ ከማመሳከር ባለፈ የምናረጋግጥበት የተለየ የቴክኒክ መሳሪያ የለንም፤ ክፍያውን የፈፀምነውም የተለመደውን አሰራር ተከትለን ሲሆን ክፍያውን ለማረጋገጥ ለአመልካች ስልክ ለመደወል ያደረግነው ጥረት አልተሳካም፤ የሂሳብ እንቅስቃሴውን የሚያሳይ የሂሳብ መግለጫ ለ1ኛ ተጠሪ የተላከለት ቢሆንም በ15 ቀን ውስጥ ቅሬታውን አልገለፀም፤ ይህም በወጪና ገቢው ላይ የተስማማ መሆኑን ያሳያል፤ ስለሆነም ከሳሽ ራሱ ኃላፊ ነው ወይም ጣልቃ ገቦችን ከሶ መጠየቅ አለበት ከሚባል በስተቀር ኃላፊነት የለብኝም በማለት ተከራክሯል፡፡

በአመልካች ጠያቂነት 2ኛ ተጠሪ ወደ ክርክሩ ጣልቃ ገብቶ ባቀረበው መልስ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቼክ 1ኛ ተጠሪ በአመልካች ባንክ በከፈቱት ሂሳብ ላይ የተሰጠ ሲሆን በተለመደው አሰራር የቼኩን ትክክለኛነት እና የፈራሚዎቹን ማንነት ማረጋገጥ ያለበት አመልካች ነው፤ እኛ የቼኩን ትክክለኛነት እና ለክፍያ ብቁ መሆኑን ልናረጋግጥ የምንችልበት አግባብ የለም፤ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቼክ የተከፈለው Real Time Gross Settlement በተባለ እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በተቀረፀ ስርዓት ነው፤ ስርዓቱ እንድ ቼክ እንዲከፈለው የታዘዘለት ሰው ሂሳብ ወደ ከፈተበት ባንክ በመቅረብ ክፍያው ወደ ሂሳቡ እንዲከፈል ቼኩን ለባንኩ የሚያስረክብበት እና ቼኩን የተቀበለው ባንክ ደግሞ እንዲከፈል ለታዘዘው ባንክ በመስጠት ከፋዩ ባንክ የቼኩን ትክክለኛነት ካረጋገጠ በኋላ ክፍያ የሚፈፀምበት ስርዓት ነው፤ ቼኩን የተቀበለው ባንክ በቼኩ ጀርባ ላይ ማህተም የሚያደርግ እና ቼኩን ከተከፋዩ ላይ የተቀበለ ስለመሆኑም የማረጋገጫ ሰነድ መስጠቱ ብቻውን የቼኩን ትክክለኛነት የሚያረጋግጥ አይደለም፤ ስለሆነም

ኃለፊነት የለብንም በማለት ተከራክሯል። ሌሎቹን ጣልቃገቦች በሚመለከት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲቀጥል ትዕዛዝ ተሰጥቷል።

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካች በቼኩ ላይ የተመለከተዉን ገንዘብ ለአቅራቢዎቹ ከመክፈሉ በፊት ለክፍያ በቀረበዉ ቼክ ላይ የሰፈረዉ ፊርማ 1ኛ ተጠሪን በመወከል በሚፈርሙት ፈራሚዎች የተፈረመ መሆን ያለመሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን፣ ይህም ለማድረግ የተለየ ሳይንሳዊ አካሄድ አመልካች እንዲከተል ባይጠበቅበትም በቼኩ ላይ የተመለከተዉን ፊርማ የቼኩ ፈራሚዎች ከሰጡት የፊርማ ናሙና አንፃር በዓይን አይቶ ተመሳሳይ መሆኑን ማረጋገጥ እንደሚቻል፤ በዚህ ረገድ ለክፍያ በቀረበዉ ቼክ ላይ የተመለከተዉ ፊርማ በሲስተም ዉስጥ ካለዉ የፈራሚዎች ፊርማ ናሙና ጉዳዩን በያዘዉ ዳኛ ሲታይ የማይመሳሰል መሆኑን መረዳት እንደሚቻል፤ በዓይን እይታ የማይመሳሰል መሆኑን መረዳት እየተቻለ በቸልተኝነት ክፍያዉን በመፈጸም የአመልካች ባንክ በፈጸመዉ ጥፋት ለ1ኛ ተጠሪ ኃላፊነት አለበት። 2ኛ ተጠሪ የክፍያ ማረጋገጫ ደብዳቤ ለአመልካች የላከለት 2ኛ ተጠሪ ስለመሆኑ ባያከራክርም 2ኛ ተጠሪ የ1ኛ ተጠሪን ገንዘብ በአደራ አስቀምጦ በቀጥታ ክፍያ የፈፀመ ባለመሆኑ የቼኩን ትክክለኛነት የማረጋገጥ ግዴታ የለበትም፤ ላረጋግጥ ቢልም የቼኩ ፈራሚዎች የፊርማ ናሙና ስለሌለው አይችልም፤ 2ኛ ተጠሪ የማይመለከተውንና የማይችለውን ነገር ለምን አላደረግክም ተብሎ ኃላፊነት አለብህ ሊባል የሚችልበት የህግ ወይም የውል ምክንያትም የለም፤ የስር 2ኛ እና 3ኛ ጣልቃ-ገቦች አከራካሪውን ገንዘብ የወሰዱት በሃሰት የተዘጋጀ ቼክ እና የክፍያ ማረጋገጫ ደብዳቤዎችን ተጠቅመው ስለመሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ሲሆን ግለሰቦቹ ቀርበው አላስተባሉም፤ አመልካችም በንግድ ህግ ቁጥር 898(1) እና በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2786(1) መሠረት ገንዘቡን የመክፈል ኃላፊነት አለበት፤ የኃላፊነቱን ሁኔታ በሚመለከት ሶስቱም ማለትም አመልካች፣ የስር 2ኛ እና 3ኛ ጣልቃ-ገቦች በአንድነትና በነጠላ ኃላፊነት አለባቸው በማለት ወስኗል። አመልካች በዚህ ውሳኔ ባለማስማማት ይግባኙን ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታው ተሠርዞበታል። ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው። አመልካች በጳጉሜን 03 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው 06 ገጽ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈጽመዋል ያላቸውን ስህተቶች በመዘርዘር በዚህ ችሎት እንዲታረሙለት ጠይቋል። የአቤቱታው ይዘትም በአጭሩ ገንዘቡን ስንከፍል በተለመደው አሰራር እና በህጉ መሠረት የቼኩን ትክክለኛነት በማረጋገጥ፣ በቼኩ ላይ ያለውን ፊርማ የ1ኛ ተጠሪ ፈራሚዎች ከሰጡት ናሙና ጋር በአይን

እይታ በማመሳከር ከፍለን እንዲሁም ይህንኑ የሚሳይ የሰነድ ማስረጃ አቅርበን እያለ ማስረጃ እንዳልቀረበ ተደርጎ ውሳኔ መሰጠቱ፤ 2ኛ ተጠሪ የደንበኛዬን አድራሻ እና ማንነት አረጋግጫለሁ በማለት መሃተብ መትቶ ለአመልካች ልኮ እያለ የአንደኛ ተጠሪን ገንዘብ በአደራ አስቀምጦ በቀጥታ የከፈለ ባለመሆኑ የቼኩን ትክክለኛነት የማረገገጥ ግዴታ ስለሌበት ኃላፊነት የለበትም መባሉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርመሮ የስር ፍርድ ቤት 2ኛ ተጠሪን ከኃላፊነት ነፃ ያደረገበት አግባብ መጣራት አለበት ተብሎ ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቧል፡፡ በዚሁም መሠረት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ 1ኛ ተጠሪ በቀን 22/05/2011 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ የሰበር አመልካቹ የቼክ ሰነዱ ከ1ኛ ተጠሪ እጅ ጠፍቶ ነበረ በማለት በስር ፍርድ ቤት ያላነሳውን የፍሬ ነገር መከራከሪያ ነጥብ በማንሳት መከራከሩ ስነ-ስርዓታዊ አይደለም፤ ያነሳቸው የቅሬታ ነጥቦችም ፍሬ ነገርን እና ማስረጃን የሚመለከቱ በመሆኑ ይህ ሰበር ችሎት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም፤ ገንዘቡን ለ1ኛ ተጠሪ የመተካት ሙሉ ኃላፊነት ያለበት አመልካች ራሱ ነው ሲል የተከራከረ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያላነሳውን ክርክር በማንሳት መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ሲል ያቀረበው ክርክር ተገቢነት የለውም፤ አመልካች ባቀረበው አቤቱታ በብሔራዊ ባንክ የወጣውን መመሪያ ቁጥር 46/2010 የትኛውን ድንጋጌ እንደጣሰ ያቀረበው ክርክር የለም፤ በአከራካሪ ቼክ ክፍያ የተፈፀመላትን ግለሰብ ሂሳብ ስንከፍት በመመሪያው መሠረት ሁሉንም ቅድመ ሁኔታዎች አሟልተን ነበር፤ በቼኩ ጀርባ ላይ ማህተም ማድረጋችን ብቻውን ዋስትና እንደሰጠን የሚያስቆጥርብን ካለመሆኑም በላይ በብሔራዊ ባንክ መመሪያ ውስጥ የሌለ ሃሳብ ነው የሚሉ እና ሌሎች በስር ፍርድ ቤት ያነሳቸውን መከራከሪያዎች በመድገም በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቶ ተከራክሯል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም 1ኛ ተጠሪ ባቀረበዉ ክስ ለጠየቀዉ ዳኝነት መሠረት ያደረገዉ ተገቢዉን ጥንቃቄ የማድረግ ግዴታዉን ባለመወጣት ተመሳስሎ ተዘጋጅቶ በቀረበዉ ተመሳሳይ ቁጥር ባለዉ ቼክ ከሂሳቡ ወጪ አድርጎ ለሦስተኛ ወገን የከፈለዉን ገንዘብ አመልካች የመተካት ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በመጥቀስ ሲሆን፣ አመልካች የሚከራከረዉ ለክፍያዉ

ምክንያት በሆነዉ ቼክ ላይ የተመለከተዉ ፊርማ በባንክ በዳበረዉ የክፍያ አሠራር መሠረት በዓይን ሲታይ ከ1ኛ ተጠሪ ድርጅት ቼክ ፈራሚዎች የፊርማ ናሙና ጋር ተመሳሳይ መሆኑን በማረጋገጥ እንዲሁም ቼክ አቅራቢዉ (ተከፋዩ) ከ2ኛ ተጠሪ ቼኩንና የክፍያ ማረጋገጫ ይዘዉ ቅጽ ሞልተዉ በማቅረባቸዉ ምክንያት ደንበኛዉን በመተማመን በመሆኑ ኃላፊነቱ የ2ኛ ተጠሪ ነዉ በማለት ይከራከራል። አመልካች ኃላፊነቱ የ2ኛ ተጠሪ መሆኑን ጠቅሶ ወደ ክርክሩ እንዲገባ ባቀረበዉ ጥያቄ መሠረት 2ኛ ተጠሪ ወደ ክርክሩ ገብቶ ኃላፊነት የለብኝም የሚልባቸዉን ምክንያቶች በዝርዝር በመጥቀስ የተከራከረ ሲሆን፣ ከፍ ሲል እንደተገለጸዉ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት 2ኛ ተጠሪ ኃላፊነት የለበትም በሚል የወሰነ ሲሆን ለዚህ የሰጠዉ ምክንያትም ክፍያዉ የቀረበዉ ለአመልካች ባንክ እንጂ ለ2ኛ ተጠሪ ባንክ በመሆኑ በቼኩ ላይ የተመለከተዉ ፊርማ የ1ኛ ተጠሪ ፈራሚዎች መሆን ያለመሆኑን አረጋግጦ ክፍያዉን የመፈጸም ኃላፊነት የአመልካች እንጂ የ2ኛ ተጠሪ ኃላፊነት ካለመሆኑም በላይ የቼኩ ፈራሚዎች የፊርማ ናሙና የሚገኛዉ በአመልካች ዘንድ እንጂ በእርሱ ዘንድ ባለመሆኑ 2ኛ በቼኩ ላይ የተመለከተዉ ፊርማ ከ1ኛ ተጠሪ ቼክ ፈራሚዎች ፊርማ ጋር ተመሳሳይ መሆን ያለመሆኑን ሊያረጋግጥ የሚችልበት ሁኔታ የለም በማለት ነዉ። ከዚህ ሁሉ በመነሳት የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልጋቸዉ ጭብጦች፡-

2ኛ ተጠሪን ከኃላፊነት ነፃ በማድረግ የተሰጠዉ ዉሳኔ በአግባቡ ነዉ ወይስ አይደለም? ለክፍያዉ ምክንያት በሆነዉ ቼክ ላይ የተመለከተዉ ፊርማ ከ1ኛ ተጠሪ ቼክ ፈራሚዎች ፊርማ ናሙና ጋር አይመሳሰልም የሚል ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የደረሰበት ድምዳሜ የማስረጃ አቀባበል መርህን መሠረት ያደረገ ነዉ ወይ? የሚሉ ናቸዉ።

ከመጀመሪያዉ ጭብጥ ስንነሳ፣ እንደሚታወቀዉ አንድ ሰዉ ለሌላ ሰዉ በፍትሐብሔር ኃላፊነት የሚኖርበት በህግ ወይም በዉል የተጣለበትን ግዴታ በመጣስ ወይም የተጣለበትን ኃላፊነት ባለመወጣቱ ምክንያቱ ጉዳት ያደረሰ መሆኑ ሲረጋገጥ ነዉ። የፍትሐብሔር ኃላፊነት አለበት በሚል በሌላ ሰዉ ላይ ክስ ወይም ክርክር የሚያቀርብ ሰዉ፣ ክሱ ወይም ክርክሩ የቀረበበት ሰዉ ከህግ ወይም ከዉል የመነጨ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን የማስረዳት ግዴታ ይኖርበታል። በዚህ ረገድ አመልካች 2ኛ ተጠሪ ኃላፊነት አለበት በማለት አጥብቆ የሚከራከረዉ ቼክ አቅራቢዉ ቼኩን እና የክፍያ ማረጋገጫ ሰነዱን በመያዝ ተገቢዉን እና ሌሎች ተያያዥ ቅጽ ሞልቶ ክፍያ እንዲፈጸም ወደ አመልካች ባንክ ለክፍያ ያቀረበዉ 2ኛ ተጠሪ በመሆኑ እና ይህ መሆኑም ጥርጣሬዎችን በመዘጋት በደንበኛዉ ላይ አመልካች እምነት እንዲኖረዉ በማድረግ ለገንዘቡ መከፈል ምክንያት የሆነዉ 2ኛ ተጠሪ መሆኑን በመጥቀስ ነዉ። ከግራ ቀኝ ክርክር

ሂደት መገንዘብ እንደሚቻለዉ 2ኛ ተጠሪ ቼኩን ከደንበኛዉ በመቀበል ለአመልካች ባንክ ሊያስተላልፍ የቻለዉ ብሔራዊ ባንክ በዘረጋዉ Ethiopian Automated Transfer System (EATS) በሚባል ሥርዓት ሲሆን በዚህ ሥርዓት መሠረት የቼኩ ተከፋይ የተሰጠዉን ቼክ ሂሳብ ወዳለዉ እና በዚህ ሥርዓት ዉስጥ ለታቀፈ ባንክ በማቅረብ በቼኩ ላይ የተፃፈዉን ገንዘብ ወደ ሂሳቡ እንዲከፈልለት ቼኩን ሂሳብ ወዳለዉ ባንክ (Requesting Bank) የሚያስረክብበት እና ቼኩን የተቀበለዉም ባንክ ቼኩን ትክክለኛ እና ለክፍያ ብቁ መሆኑን ወይም ክፍያ ለመፈጸም የማያስችል ሌላ ማንኛዉም ምክንያት መኖር አለመኖሩን በማረጋገጥ ክፍያ የሚፈጸምበትን ሥርዓት መሠረት በማድረግ ሲሆን በዚህ የክፍያ ሥርዓት መሠረት ቼኩ በተከፋይ የቀረበለት ባንክ ቼኩን ከደንበኛዉ ከመቀበል እና ለከፋይ ባንክ ከማስተላለፍ ዉጪ ቼኩ ትክክለኛና ለክፍያ ብቁ መሆኑን ወይም ክፍያ የማይፈጸምበት ምክንያት መኖር ያለመኖሩን የማረጋገጥ ኃላፊነት እንደሌለበት እንዲሁም ቼክ አዉጪዉ የከፋዩ ባንክ ደንበኛ በመሆናቸዉ 2ኛ ተጠሪ የቼኩን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሚችልበት ምንም ዓይነት እድል የሌለዉ ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት በተሰጠ ሙያዊ የምስክርነት ቃል መረጋገጡን 2ኛ ተጠሪ ለዚህ ችሎት ባቀረበዉ መልስ የሚከራከር ሲሆን፣ አመልካች በመልስ መልሱ ይህን የተጠሪን ክርክር ክዶ አይከራከርም። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ 2ኛ ተጠሪ ቼኩን ከደንበኛዉ በመቀበል ለክፍያ ብቁ መሆኑን አረጋግጦ ለአመልካች ባንክ ማስተላለፉ፣ አመልካች ለቼክ አቅራቢዉ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ለክፍያ በቀረበዉ ቼክ ላይ የሰፈረ ፊርማ የቼክ አዉጪዉ ፊርማ መሆኑን ለማረጋገጥ ያለበትን ኃላፊነት የሚያስቀር አይደለም። በመሆኑም አመልካች በቼኩ ላይ እንዲተማመን ወይም እንዳይጠራጠር ያደረገዉ 2ኛ ተጠሪ ሞልቶ የላከለት የክፍያ ሰነድ ነዉ በማለት አመልካች የሚያቀርበዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም። ስለሆነም 2ኛ ተጠሪ ኃላፊነት የለበትም በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም።

በሁለተኛነት ወደ ተያዘዉ ጭብጥ ስንመለስ፣ እንደሚታወቀዉ ቼክ የንግድ ወረቀት ከሚባሉ አንዱ ሲሆን እንደቀረበ የሚከፈል፣ በባንክ ተቀማጭ ሂሳብ ያለዉ ሰዉ ገንዘቡ ለእራሱ ወይም ለሌላ ወገን እንዲከፈል ሐተታ የሌለዉ ትዕዛዝ የሚሰጥበት፣ ገንዘብን ተክቶ ክፍያን የሚያቀላጥፍ የንግድ ወረቀት ወይም ሰነድ ስለመሆኑ ከንግድ ህጉ አንቀጽ 732፣ 827፣ 828 እና 854 ድንጋጌዎች ይዘት የምንገነዘበዉ ነዉ። በዚህም መሠረት ቼክ የተሰጠዉ ሰዉ ቼኩን ለባንክ በማቅረብ ክፍያ እንዲፈጸምለት የመጠየቅ መብት ያለዉ ሲሆን፣ በቼክ የክፍያ ጥያቄ የቀረበለት ባንክም ቼኩን ያወጣዉ ሰዉ ፊርማን ጨምሮ በቼክ ላይ መገለጽ የሚገባቸዉ ሌሎች

ሁኔታዎች ተሟልቶ የቀረቡ መሆናቸዉን በማረጋገጥ ቼኩ እንደቀረበለት የመክፈል ኃላፊነት እንዳለበት በንግድ ህጉ አንቀጽ 827 እና 854 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ በቼክ የክፍያ ጥያቄ የቀረበለት ባንክ ክፍያዉን ለአምጪዉ የሚፈጽመዉ በንግድ ህጉ አንቀጽ 896 እና ተከታዮቹ መሠረት በተደረገዉ የአደራ ዉል መሠረት በባንኩ ከተከፈተዉ የደንበኛዉ ሂሳብ በመቀነስ በመሆኑ ክፍያዉን ከመፈጸሙ በፊት ቼኩ ፊርማን ጨምሮ ሌሎች አስፈላጊ ሁኔታዎችን አሟልቶ የቀረበ መሆን አለመሆኑን በጥንቃቄ በማረጋገጥ የደንበኛዉን መብት እና ጥቅም የመጠበቅ በዉል የተጣለበት ኃላፊነት አለበት፡፡ ስለሆነም ባንኩ በአንድ በኩል ቼክ እንደቀረበለት ወዲያዉኑ ክፍያ በመፈጸም የቼክን መሠረታዊ ዓላማ ያገናዘበ አገልግሎት የመስጠት ኃላፊነት ሲኖርበት በሌላ በኩል ደግሞ ገንዘቡ ከደንበኛዉ ሂሳብ ተቀንሶ ደንበኛዉ ላልታዘዘለት ሰዉ ክፍያ እንዳይፈጸም የማድረግ የደንበኛዉን ጥቅም የመጠበቅ ከዉል የመነጨ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡ ይህም ማለት ባንኩ ማድረግ የሚገባዉን ጥንቃቄ ባለማድረግ በቼክ ክፍያ ፈጽሞ ከተገኘ በተከፈለዉ ገንዘብ ልክ ለደንበኛዉ (ለባለ ሂሳቡ) ኃላፊነት ይኖርበታል ማለት ነዉ፡፡

1ኛ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ ሊያቀርብ የቻለዉም በዚሁ መነሻነት ሲሆን፣ አመልካች ከሂሳቡ (ከ1ኛ ተጠሪ ሂሳብ) ወጪ ተደርጎ ለሌላ ሰዉ የተከፈለዉን ገንዘብ ለ1ኛ ተጠሪ ለመተካት ኃላፊነት የሚኖርበት ክፍያዉን የፈጸመዉ በቼኩ ላይ የተመለከተዉን ፊርማ በሲስተሙ ላይ ከተመለከተዉ ፊርማ አንፃር በጥንቃቄ አይቶ እና አመሳክሮ ፊርማዉ 1ኛ ተጠሪን ወክሎ በቼኩ ላይ የሚፈርም ሰዉ ፊርማ መሆኑን አረጋግጦ መክፈል ሲገባዉ ይህን ሳያደርግ ክፍያዉን መፈጸሙ ሲረጋገጥ ነዉ፡፡ በባንክ በተለመደዉ አሠራር መሠረት ባንኩ በቼክ ላይ የተፈረመዉ ፊርማ የቼክ አዉጪዉ ፊርማ መሆኑን የሚያረጋግጠዉ በዓይን እይታ እንጂ ልዩ የፊርማ መመርመሪያ መሣሪያዎችን በመጠቀም አለመሆኑም የሚታወቅ ነዉ፡፡ ይህም ማለት ባንኩ በቼኩ ላይ የተመለከተዉ ፊርማ በዓይን እይታ በሲስተሙ ላይ ካለዉ የፊርማ ናሙና ጋር አንድ ዓይነት መሆኑን አረጋግጦ መክፈሉ ከተረጋገጠ ምንም እንኳ ክፍያዉ የተፈጸመዉ ለማይገባዉ ሰዉ ወይም ተመሳስሎ በቀረበ ፊርማ መነሻነት መሆኑ ቢረጋገጥም ኃላፊነት አይኖርበትም፡፡ “መቃወሚያ ሳይቀርብበት፣ በቅን ልቦና እና ለስራ አፈፃፀም በተለመደዉ አኳያ ቼክ የከፈለ ከፋይ በሚገባ ነፃ እንደወጣ ይቆጠራል (A drawee who in the absence of objection pay a cheque in good faith and in accordance with normal business practice shall be deemed to be validly discharged)” በሚል በንግድ ህጉ አንቀጽ 861 ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌም ይህንኑ የሚያስገነዝብ ነዉ፡፡

የስር ፍርድ ቤት አመልካች ኃላፊነት አለበት በሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰዉ በአመልካች ባንክ ሲስተም ዉስጥ የሚገኘዉን የ1ኛ ተጠሪ ቼክ ፈራሚዎችን የፊርማ ናሙና ክፍያዉ በተፈጸመበት ቼክ ላይ ከሰፈረዉ ፊርማ ጋር የሚመሳሰል መሆኑ አለመሆኑን ዳኛዉ እራሳቸዉ በዓይን በማየት ፊርማዎቹ አይመሳሰሉም በማለት ስለመሆኑ ከዉሳኔዉ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በእርግጥ ከላይ እንደተገለጸዉ አመልካች በቼክ በቀረበለት የክፍያ ጥያቄ መሠረት ክፍያዉን ከመፈጸሙ በፊት በቼኩ ላይ የሰፈረዉ ፊርማ በሲስተሙ ላይ ከተመለከተዉ የአዉጪዉ የፊርማ ናሙና ጋር ተመሳሳይ መሆን አለመሆኑ የሚረጋገጠዉ በአይን እይታ እንጂ በሌላ የመመርመሪያ ማሽን አይደለም፡፡ ክፍያዉን የሚፈጽም ባንክ በቼኩ ላይ ያለዉን ፊርማ ከናሙናዉ ፊርማ ጋር ተመሳሳይ መሆን አለመሆኑን በማረጋገጥ ባንኩ ክፍያዉን የፈጸመዉ ተገቢዉን ጥንቃቄ በማድረግ መሆን አለመሆኑ የሚረጋገጠዉ በምክንያታዊ ሰዉ እይታ ነዉ፡፡ ጥያቄዉ ጉዳዩን የተመለከተዉ ዳኛ በእራሱ እይታ ፊርማዉ የሚመሳሰል መሆን ያለመሆኑን መለየት የመቻሉ ጉዳይ ነዉ፡፡

እንደሚታወቀዉ በክርክር ሂደት የተያዘ የፍሬ ነገር ጭብጥ የሚረጋገጠዉ በማስረጃ ነዉ፡፡ ማስረጃ ሳይቀርብበት ፍርድ ቤቶች በአንድ የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ መድረስ የሚችሉት የፍሬ ነገር ጭብጡ በባህርዉ ፍርድ ቤቶች ግንዛቤ ሊወስዱበት የሚችሉ (judicial notice) ዓይነት ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ ከማስረጃ አቀራረብ እና ምዘና አጠቃላይ መርህ እንዲሁም በፍርድ ቤቶች ከዳበረዉ ልምድ የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡ በተያዘዉ ጉዳይ አከራካሪዉ ጭብጥ በቀረበዉ ቼክ ላይ የተመለከተዉ ፊርማ በሲስተሙ ላይ ከተመለከተዉ ፊርማ ጋር ተመሳሳይ አለመሆኑን በዓይን አይቶ መለየት የሚቻል መሆን አለመሆኑ ነዉ፡፡ በመሠረቱ የሰነድ ማስረጃ ማለት በላዩ ላይ የተፃፈበት፣ የተሳለበት፣ ወይም ማናቸዉም ዓይነት ምልክት የተደረገበት ወይም ድምጽ የተቀዳበት ወይም ድምጽና ምስል የተቀረጸበት ሆኖ ለአስረጅነት የሚቀርበዉም እንደሁኔታዉ የተፃፈዉ ጽሑፍ፣ የተሳለዉ ስዕል፣ ወይም የተደረገዉ ምልክት ወይም የተቀረጸዉ ድምጽ ወይም ምስል ወይም ማናቸዉም ነገር ሊሆን ይችላል፡፡ ማስረጃዉን የሰነድ ማስረጃ የሚያሰኘዉም ወረቀትነቱ ወይም ካሴትነቱ ሳይሆን ለማስረጃነት ተፈልጎ ለፍርድ ቤት የሚቀርበዉ እና ፍርድ ቤት የሚመለከተዉ ፍሬ ነገር በወረቀት፣ ካሴት እና ወዘተ ላይ ሰፍሮ መገኘቱ ነዉ፡፡ ከዚህም የሰነድ ማስረጃ ሁለት መሠረታዊ ባህርያት ያሉት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ የመጀመሪያዉ ወረቀቱ ወይም ካሴቱ ተፈላጊዉን ፍሬ ነገር መያዝ አለመያዙ ሲሆን፣ ሁለተኛዉ ሰነዱ የሚይዘዉ ፍሬ ነገር ፍርድ ቤቱ ለያዘዉ ጭብጥ አግባብነት ያለዉ እና የማስረዳት ብቃቱ ነዉ፡፡ ይህ በመሆኑም ከሰነድ ማስረጃ ጋር በተያያዘ አንድም የሰነዱን ይዘት

(ሰነዱ የተፈለገዉን ፍሬ ነገር በእርግጥም የያዘ መሆን አለመሆኑ) ሁለትም በሰነዱ ላይ መኖሩ የተረጋገጠዉ ፍሬ ነገር በፍርድ ቤቱ የተያዘዉን ጭብጥ ሊያስረዳ የሚችል መሆን አለመሆኑ ነዉ፡፡ ስለሆነም ክርክሩ የቀረበለት ፍርድ ቤት የያዘዉን የፍሬ ነገር ጭብጥ የሚያስረዳ መሆን አለመሆኑን የሰነድ ማስረጃዉ መመርመር እና የመመዘን ኃላፊነት እንዳለበት ሁሉ ከሰነዱ ይዘት ጋር በተያያዘ ክርክር ሲኖርም ይህንኑ በጭብጥነት በመያዝ (የፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 248/ለ/ ይመለከቷል) መርምሮ እና መዝኖ ሰነዱ የያዘዉን ፍሬ ነገር ትክክለኛነት አረጋግጦ ከድምዳሜ ላይ የመድረስ ኃላፊነትም የፍርድ ቤት ሲሆን ይህን የሚያደርገዉም የተለያዩ ማስረጃዎችን በመመርመር እንጂ እራሱ ግምት በመዉሰድ አይደለም፡፡ በማስረጃ መረጋገጥ የሚገባዉን ነገር በእራስ ግምት መዉሰድ ፍርድ ቤቱን እራሱ አስረጂ እራሱ ፈራጅ እንደሆነ የሚያስገምተዉ በመሆኑ ፍርድ ቤቶች ይህን እንዲያደርጉ አይጠበቁም፡፡

ከዚህ አንፃር የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት አመልካች በቼኩ ላይ የተፈረመ ፊርማ በፊርማ ናሙናዉ ላይ ከተመለከተዉ ጋር ተመሳሳይ መሆኑን በማረጋገጥ ክፍያ ፈጽማለሁ በማለት የሚከራከር ከመሆኑ አንፃር በቼኩ ላይ የተፈረመዉ ፊርማ በእርግጥም ከፊርማ ናሙናዉ ጋር አንድ ዓይነት መሆን አለመሆኑ በጉዳዩ ላይ ዉሳኔ ለመስጠት በማስረጃ መረጋገጥ የሚገባዉ ጭብጥ ነዉ፡፡ ይህን ለማረጋገጥ በአስረጅነት የቀረበዉ እራሱ ክፍያ የተፈጸመበት ቼክ ሲሆን በቼኩ ላይ የተመለከተዉ ፊርማ ከናሙና ፊርማ ጋር የሚመሳሰል መሆን አለመሆኑ ገለልተኛ በሆነ አካል ታይቶ የሚረጋገጥ እንጂ ዳኛዉ እራሳቸዉ አይተዉ ግምት ሊወስዱበት የሚገባ አይደለም፡፡ በመሆኑም በቼኩ ላይ የተመለከተዉ ፊርማ ከተጠሪ ከተወሰደዉ የፊርማ ናሙና ጋር አንድ ዓይነት መሆን አለመሆኑን አመልካች በጥንቃቄ የማረጋገጥ ግዴታዉን አልተወጣም በሚል ድምዳሜ ላይ ሊያደርስ የሚያስችል አሳማኝ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪ የጠየቀዉን ገንዘብ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ የማስረጃ አቀራረብ እና የምዘና መርህን ያገናዘበ ባለመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያትም ተከታዩ ዉሳኔ በአብላጫ ድምጽ ተሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 227815 በቀን የካቲት 15 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 206237 በቀን

ሐምሌ 22 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሠረት ተሻሽለዋል፡፡

2ኛ ተጠሪ ኃላፊነት የለበትም በማለት የተሰጠዉ የዉሳኔ ክፍል ጸንቷል፤ ከክርክሩ ዉጪ እንዲሆን ተወስኗል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተዘግቶ የነበረዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ ቼክ ላይ የተመለከተዉ ፊርማ ከ1ኛ ተጠሪ ቼክ ፈራሚዎች የፊርማ ናሙና ጋር በአይን እይታ ተመሳሳይ መሆን አለመሆኑ በፍርድ ቤቱ ወይም በግራ ቀኝ ወይም በተቻለ መጠን ከአመልካች ባንክ ዉጪ በሌሎች ባንኮች ከቼክ ክፍያ ጋር በተያያዘ ልምድ ባላቸዉ የባንክ ባለሙያዎች እንዲታይ ካደረገ በኋላ የቀረበለትን ዉጤት መሠረት በማድረግ አመልካች ኃላፊነት ያለበት መሆን አለመሆኑን በተመለከተ የመሰለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 343(3) መሠረት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡

ይህ ችሎት ህዳር 15 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ እግድ ተነስቷል፡፡

በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

<u>የልዩነት ሀሳብ</u>

ስሜ በተራ ቁጥር 5 ላይ የተጠቀሰው ዳኛ በአብላጫው ድምጽ ከ2ኛ ተጠሪ አንጻር በተሰጠው ውሳኔ የምስማማ ቢሆንም ከ1ኛ ተጠሪ አንጻር የስር ፍርድ ቤት በቼክ ላይ ያለውን ፊርማ በባንክ ለናሙና ከሚገኘው ፊርማ ጋር በራሱ ይመሳሰላል አይመሳሰልም የሚለውን ሰነዶቹን በማየት ብቻ ውሳኔ መስጠት አይችልም በሚል እንደገና ሰነዶቹ ላይ የሚገኙት ፊርማዎች ከአመልካች ባንክ ውጪ ባሉ ሌሎች ባንኮች ውስጥ በሚሰሩ ሰራተኞች ታይቶ ውጤቱ እንዲቀርብ ከተደረገ በኋላ ወይም በሌላ ማስረጃ ተጣርቶ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩ ለስር ፍርድ ቤት ሊመለስ ይገባል በመባሉ ባለመስማማት የሚከተለውን የልዩነት ሃሳብ አስፍሬአለው፡፡

አንድ ባንክ ቼክ ለክፍያ ሲቀርብለት ቼኩ በቼክ አውጭው ለክፍያ የታዘዘ ትክክለኛ ቼክ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት የማጣራት ግዴታ እንዳለበት አከራካሪ አይደለም፡፡ አንድ ሰነድ ቼክን ጨምሮ ትክክለኛ መሆኑ የሚጣራው በሰነዱ ላይ የሰፈሩትን

ጽሁፎች፣ ምልክቶች፣ፊርማዎች እና ሌሎች በሰነዱ ላይ የሰፈሩ ምልክቶችን ትክክለኛነት በማጣራት ነው። በባንክ የተለመደ አሰራር ቼክ ለክፍያ ሲቀርብ የባንኩ ሰራተኛ በቼኩ ላይ ያለውን ፊርማ የቼክ አውጪው መሆኑን በባንኩ በሲስተም ውስጥ ከሚገኘው የቼክ አውጪው የፊርማ ናሙና ጋር በማስተያየት አንድ አይነት መሆኑን ወይም አለመሆኑን በአይን እይታ በማጣራት ክፍያ እንደሚፈጸም ይታወቃል። በተያዘው ጉዳይ አመልካች ለክርክሩ መሰረት የሆነውን ክፍያ በቼክ የፈጸመው ቼኩ ላይ የሚገኘው ፊርማ በባንኩ ከሚገኘው የተጠሪ የፊርማ ናሙና ጋር ተመሳሳይ መሆኑን በአይን እይታ በማጣራት መሆኑን በመግለጽ ክርክር አቅርቧል። አመልካች የሚጠበቅበትን ጥንቃቄ አድርጓል ወይስ አላደረገም ለሚለው እልባት ለመስጠት ጉዳዩን ያየው የስር ፍርድ ቤት አንድም ማጣራት የሚጠበቅበት በቼኩ ላይ የሚገኘው ፊርማ እና በአመልካች ባንክ ውስጥ የሚገኘው የፊርማ ናሙና በአይን ሲታይ ተመሳሳይነት አለው ወይስ የለውም የሚለው ነው። በሁለቱ ሰነዶች ላይ የሚገኙት ፊርማዎች ተመሳሳይነት አላቸው ወይስ የላቸውም የሚለውን ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት እራሱ በህግ በተሰጠው ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ሰነዶቹን በመመልከት እና በመመዘን የሚደርስበት ድምዳሜ እንጂ ከፍርድ ቤት ውጪ ያለ አካል ማስረጃዎቹን መዝኖ ይመሳሰላሉ ወይም አይመሳሰሉም በሚል የሚሰጠውን ማስረጃ መሰረት በማድረግ ሊሆን አይገባም።

በእርግጥ በሰነዶቹ ይዘት ላይ ክርክር ከቀረበ ወይም ፍርድ ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሰነዶቹ የባለሙያ ምርመራ ወይም በፖሊስ የፎረንሲክ ምርመራ እንዲደረግባቸው የማዘዝ ሃላፊነት እንዳለበት ከፍ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 136 ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል። ይሁን እንጂ በባንክ አሰራር ፊርማ በፎረንሲክ ምርመራ እየተጣራ ክፍያ የመፈጸም አሰራርን ተግባራዊ ማድረግ የማይቻል በመሆኑ የፎረንሲክ ምርመራ ውጤቱ አመልካች ተገቢውን ጥንቃቄ አለማድረጉን የሚያሳይ ሊሆን አይችልም። ይህ የፎረንሲክ ምርመራ ውጤት ለጉዳዩ ተገቢነት ያለው ማስረጃ አይደለም ከተባለ ደግሞ ፍርድ ቤቱ በሌላ ባለሙያ ፊርማው እንዲጣራ የማድረግ ሃላፊነት የለበትም። በአይን እይታ ብቻ በሁለት የተለያዩ ሰነዶች ላይ የሚገኙ ፊርማዎች አንድ አይነት መሆኑን ወይም አለመሆኑን ከፍርድ ቤት ውጪ ባለ ሰው እንዲረጋገጥ ማድረግ ፍርድ ቤቱ በህግ የተሰጠውን ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ለሌላ ማስረጃን ለመመዘን በህግ ስልጣን ለሌለው አካል አሳልፎ እንደመስጠት የሚያስቆጥር ነው የሚል እምነት አለኝ። የቀረቡትን ሰነዶች በአይን በመመልከት ፊርማው ይመሳሰላል ወይም አይመሳሰልም የሚለውን መመርመር የፍርድ ቤቱ ከማስረጃ ምዘና ጋር የተያያዘ ሃላፊነት የተወጣ መሆኑን ከሚያሳይ በስተቀር ፍርድ ቤቱ እራሱ ምስክር እራሱ ፈራጅ እንደሆነ የሚያስቆጥረው ነው የሚል እምነት ስለሌለኝ

የስር ፍርድ ቤት እራሱ በቼኩ ላይ ያለው ፊርማ አመልካች ባንክ ውስጥ ከሚገኘው የ1ኛ ተጠሪ ፊርማ ናሙና ጋር በማገናዘብ ተመሳሳይነት የለውም ማለቱ የማስረጃ ምዘና መርህን የተከተለ ነው፡፡ በመሆኑም በስር ፍርድ ቤት በአከራካሪው ቼክ ላይ ያለውን ፊርማ በአመልካች ባንክ ከሚገኘው የ1ኛ ተጠሪ ፊርማ ናሙና ጋር በማገናዘብ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የማስረጃ ምዘና መርህ ጥሰት ተፈጽሞበታል የሚያስብል ሆኖ ስላላገኘሁት ውሳኔው ሊጸና ይገባ ነበር በሚል ከአብላጫው ድምጽ በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ አንድ ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ 237038

ሚያዚያ 30 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

መላኩ ካሳዬ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች፡- ሕብረት ኢንሹራንስ አ.ማ

ተጠሪ፡- ኦሮሚያ ኢንሹራንስ አ.ማ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ የመድን ዋስትና ውልን መሠረት ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የጀመረው የአሁን ተጠሪ ባቀረቡት ክስ ሲሆን 1ኛ. ተከሳሽ አቶ ሽብሬ ሁንዴ፤ 2ኛ. ተከሳሽ አቶ መሪድ ባጫ እንዲሁም 3ኛ ተከሳሽ የአሁን አመልካች ነበሩ፡፡

ከመዝገቡ እንደተረዳነው ተጠሪ ንብረትነቱ የኦሮሚያ ሕብረት ሥራ ባንክ አ/ማ ለሆነው የሰሌዳ ቁጥር 3-A59886 ተሽከርካሪ የመድን ዋስትና ሽፋን የሰጠ ሲሆን የስር 1ኛ ተከሳሽ ንብረት

በሆነው የሰሌዳ ቁጥር 3-A03862 በ2ኛ ተከሳሽ ሲሸከረከር የተጠሪ ደንበኛ ተሸከርካሪ ተገጭቶ ጉዳት ደርሷል። ለግጭቱ መንስኤ የሆነውና በአደጋውም ጥፋተኛ በመሆን ኃላፊነት ያለባቸው የ1ኛ ተከሳሽን መኪና ሲያሽከረክሩ የነበሩት 2ኛ ተከሳሽ መሆናቸው ፖሊስ በሰጠው ማስረጃ ተረጋግጧል። ከሳሽ የደንበኛውን ተሸከርካሪ ለማስጠገን ብር 77,232.37 ወጪ አድርጎ ኃላፊነቱን ተወጥቷል፤ እንዲሁም ለክሱ ማስረጃዎችን ለማስተርጎም ብር 2,069.59 አውጥቷል። ከተከሳሾች የሚከፈለው የካሳ ክፍያ በአጠቃላይ ሲሆን ብር 79,301.96 ሲሆን በመድን ውሉ መሰረት ደንበኛው የከፈሉት የአደጋ መነሻ ዋጋ (excess) ብር 1,500.00 እና 2ኛ ተከሳሽ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነቱን በማመን ለከሳሽ የከፈለው ብር 10,000.00 ከካሳ ገንዘቡ ላይ ሲቀነሱ ከተከሳሾች የሚፈለገው ብር 67,801.96 (ስድሳ ሰባት ሺህ ስምንት መቶ አንድ ብር ከ96/100) ነው። ይህን ገንዘብ 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች በንብረት ባለቤትነት እና በጥፋት፤ እንዲሁም 3ኛ ተከሳሽ ለጉዳት አድራሹ ተሸከርካሪ አስገዳጅ የሶስተኛ ወገን መድን ሽፋን የሰጠ በመሆኑ የመክፈል ኃላፊነት ስላለባቸው የክሱን ገንዘብ ከነወለዱ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል።

ይሁንና ከሳሽ በ1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ላይ ያቀረበው ክስ እንዲቋረጥ ጠይቆ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 278 መሰረት ከክሱ ውጪ እንዲሆኑ ተደርጓል።

3ኛ ተከሳሽ (የአሁን አመልካች) ለክሱ የመጀመሪያ መቃወሚያ እና መልስ አቅርቧል። ባቀረበው መቃወሚያ ከሳሽ በክሱ እንደገለፀው የደንበኛው ተሸከርካሪ በቀን 24/03/1012 ዓ.ም በመገጨቱ ምክንያት ለደረሰው የንብረት ጉዳት ለማስጠገን የከፈለውን ከተከሳሾች ለማስመለስ አደጋው ከደረሰ ከ2 ዓመት ከ 3 ወራት በኃላ ክስ ያቀረበው በቀን 21/06/2014 ዓ.ም በመሆኑ፤ እንዲሁም በማስረጃነት ያቀረበው ደረሰኝ በግልጽ እንደሚያስረዳው ክፍያ የፈፀመው በ08/05/2012 ዓ.ም መሆኑንና የኢንሹራንስ የካሳ ክፍያው ጥያቄ የቀረበው ክፍያ ከተፈፀመ 2 ዓመት በኃላ በመሆኑ ክሱ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2143(1) እንዲሁም በንግድ ህግ ቁጥር 674(2) መሰረት በይርጋ ይታገዳል። ሌሎች ተከሳሾች ለከሳሽ ኃላፊነትን በማመን ክፍያ መፈፀም ጀምረው ቢሆን እንኳ ከ3ኛ ተከሳሽ ዕውቅና እና ፈቃድ ውጪ በመሆኑና ከመድን ውሉ ጋር የተቃረነ ጭምር በመሆኑ በ3ኛ ተከሳሽ ላይ ይርጋ ጊዜውን የሚያቋርጥ አይደለም ብሏል።

በመቃወሚያው ላይ ተጠሪ ባቀረበው ክርክር 2ኛ ተከሳሽ የካቲት 20/2012 እና መጋቢት 8/2012 ዓ.ም ክፍያ በመፈፀማቸው ይርጋውን ያቋርጣል፤ 3ኛ ተከሳሽ ለተሸከርካሪው የመድን

ሽፋን ስለሰጠ 2ኛ ተከሳሽ በፈፀመው ድርጊት ምክንያት ይርጋው ይቋረጣል በማለት ተከራክሯል፡፡

የስር ፍርድ ቤት ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ጭብጥ በመያዝ የመቃወሚያ ክርክሩን መርምሮ የከሳሽ ክስ ምክንያት የሚመነጨው ካሳ ሲከፍል በመሆኑ ከዚህ አንፃር የካሳ ክፍያ የፈፀመው በ08/05/2012 ዓ.ም መሆኑን የክፍያው ደረሰኝ የሚያስረዳ በመሆኑ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሲታሰብ በቀን 21/06/2014 ዓ.ም የቀረበው ክስ 2 ዓመት እንዳለፈው መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይሁንና 2ኛ ተከሳሽ የካቲት 20 እና መጋቢት 8/2012 ዓ.ም ክፍያ ፈጽመዋል፡፡ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1901 መሰረት ባለዕዳ የሆኑ ሁሉ ዕዳው በሙሉ ወይም በከፊል ተከፍሏል ወይም በይርጋ ታግዷል በማለት ባለገንዘቡን መከራከር እንደሚችሉና ከተከሳሾች በአንዱ የተነሳ የይርጋ መቃወሚያ በሁሉም ተከሳሾች ላይ ክሱን የማዘጋት ውጤት የሚኖረው በመሆኑ የይርጋ ጊዜን የማቋረጥ ውጤት ያለው ተግባር ያልተነጣጠለ ኃላፊነት ካለባቸው ባለዕዳዎች በአንዱ ከተፈፀመ ዕዳውን የማመን ተግባር ባይፈፀም እንኳ በሌሎች ተከሳሾች ላይ ተፈፃሚ የማይሆንበትና ይርጋው የማይቋረጥበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም በፍ/ብ/ህ/ቁ 1851(ሀ) በተመለከተው መልኩ 2ኛ ተከሳሽ ዕዳውን በማመን ክፍያ መጋቢት 8/2012 ዓ.ም የፈፀሙ በመሆኑ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሲታሰብ ክሱ 2 ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የቀረበ በመሆኑ በ3ኛ ተከሳሽ ላይ የቀረበው ክስ በይርጋ አይታገድም በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

የስር ፍርድ ቤት የፍሬ ነገር ክርክርና ማስረጃውን መርምሮም 3ኛ ተከሳሽ ብር 65,732.37 ከወለድና ወጪና ኪሳራ ጋር ለከሳሽ እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች በዚህ ብይንና ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ጉድለት የለበትም ተብሎ ይግባኙ ተሰርዟል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡

አመልካች ህዳር 8 ቀን 2015 ዓ.ም ባቀረበው የሰበር ማመልከቻ ተፈፀመ የሚለውን ስህተት በመዘርዘር የስር ፍርድ ቤቶች ያሳለፉት ብይንና ውሳኔ ተሽሮ ክሱ በይርጋ የታገደ ነው ተብሎ እንዲወሰን ጠይቋል፡፡

ቅሬታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ በአመልካች የተነሳው የይርጋ ክርክር የታለፈው ህጉ በአግባቡ ተተርጉሞ ስለመሆኑ ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ ተጠሪ በሰጠው መልስ የስር ፍርድ ቤት የፍ/ብሔር ህጉን ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ የተፈፀመው ክፍያ በሁሉም ተከሳሾች ላይ እንደ ይርጋ ማቋረጫ ምክንያት ሊወሰድ ይገባል በማለት የይርጋ መቃወሚያውን ውድቅ በማድረግ የሰጠው

ውሳኔ የህግ ትርጉም ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ ውሳኔው ሊፀና ይገባል ብሏል። አመልካችም የመልስ መልስ አቅርቧል። መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረው በዚህ ሁኔታ ነው።

በበኩላችን የአመልካች የይርጋ ክርክር የታለፈው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን መርምረናል። በግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር እና በሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንደተመለከተው ተጠሪ ክሱን ያቀረበው በቀን 21/06/2014 ዓ.ም ሲሆን ለክሱ ምክንያት የሆነውን የካሳ ክፍያ ለደንበኛው የፈፀመው ደግሞ በ08/05/2012 ዓ.ም መሆኑ፤ ይህ ጊዜ ሲታሰብ የቀረበው ክስ 2 ዓመት እንዳለፈው አላከራከረም። የስር ፍርድ ቤትም ተቀብሎታል። ይህ በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠው እውነታ ሲሆን እውነታው ከየትኛው ህግ ጋር ሲገናዘብ ነው ለይርጋው ክርክር አወሳሰን አግባብነት የሚኖረው የሚለውን ደግሞ ቀጥለን እንመለከታለን።

ተጠሪ ክሱን ያቀረበው በኢንሹራንስ ገቢው መብት በመዳረግ ነው። በንግድ ሕጉ አንቀጽ 683 መሠረት ኢንሹራንስ ሰጪው በከፈለው ካሣ መጠን ጉዳት እንዲደርስ ባደረጉ ሦስተኛ ወገኖች ላይ ክስ ለማቅረብ ኢንሹራንስ ለገባው ሰው በተከፈለው ገንዘብ መጠን፣ ባሉት መብቶችና ክሶች ኢንሹራንስ ሰጪው ምትክ ሆኖ እንደሚገባ ተመልክቷል። ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 194880፣ 177970 እና ሌሎችም ተመሳሳይ መዛግብት በሰጠው ትርጉም መሰል የኢንሹራንስ የካሳ ክፍያ ጥያቄ ክፍያ ከተፈፀመበት ጀምሮ በ2 ዓመት ውስጥ ክስ ካልቀረበ ጉዳዩ በይርጋ ቀሪ ይሆናል። ስለሆነም ተጠሪ ለክሱ ምክንያት የሆነውን የካሳ ክፍያ ለደንበኛው ከከፈለ ከ 2 ዓመት በኃላ በአመልካች ላይ ያቀረበው ክስ በይርጋ የሚታገድ ነው።

ይህም ሆኖ የስር ፍርድ ቤት የይርጋ መከራከሪያውን ውድቅ ያደረገው የስር 2ኛ ተከሳሽ ይርጋውን የሚያቋርጥ ክፍያ ለተጠሪ በመፈፀሙና ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1901 እና 1851(ሀ) ንባብ አንፃር የይርጋ መቃወሚያ በሁሉም ተከሳሾች ላይ ክሱን የማዘጋት ውጤት የሚኖረውን ያህል የይርጋ ጊዜን የማቋረጥ ውጤት ያለው ተግባር ያልተነጣጠለ ኃላፊነት ካለባቸው ባለዕዳዎች በአንዱ ከተፈፀመ በሌሎች ተከሳሾች ላይ ተፈፃሚ የማይሆንበትና ይርጋው የማይቋረጥበት ምክንያት የለም በሚል ነው።

የፍ/ብ/ህ/ቁ 1901 የባለዕዳዎችን ዕዳ በተመለከተ በመካከላቸው ስላለው የማይከፋፈል አንድነት በሚደነግገው የህጉ ክፍል ውስጥ የሚገኝ ሲሆን የዚህ የህጉ ክፍል አላማ ባለገንዘቡ ስለ ግዴታው አፈፃፀም እንደፈቀደው ኃላፊዎች የሆኑትን ሁሉ ወይም አንዱን ለማስገደድ እንዲችል ለማስቻል ነው። ከዚህ በቀር ያልተነጣጠለ ኃላፊነትን ካስከተለው ጉዳይ ውጪ የሆኑ በአንደኛው ባለዕዳ የተፈፀሙ ተግባራት ሁሉ የሌሎችን ባለዕዳዎች መብት ለማጣበብ ወይም

ዕዳቸው ቀሪ እንዳይሆን እንዲያደርጉ ታስቦ የተደነገገ አይደለም። የፍ/ብ/ህ/ቁ 1901 በግልጽ የሚደነግገው ባለዕዳዎች ስለሚኖርባቸው ግዴታ ሳይሆን ባለዕዳ የሆኑት ሁሉ ዕዳው ተከፍሏል ወይም በይርጋ ታግዷል በማለት ባለገንዘቡን መከራከር ስለመቻላቸው ብቻ ነው።

በሌላም በኩል አንድን ክስ ለማቅረብ በህጉ የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ካለፈ በኋላ ክስ ለማቅረብ የማይቻል ቢሆንም ህጉ ለይቶ ባስቀመጣቸው ምክንያቶች የይርጋው ጊዜ ሊቋረጥ የሚችል እና አዲስ የይርጋ ጊዜ መቆጠር እንደሚጀምር በፍ/ብ/ህ/ቁ 1852(1) ሥር የተመለከተ ሲሆን ይርጋ ከሚቋረጥባቸው ምክንያቶች መካከል ደግሞ ባለዕዳው በራሱ ዕዳውን ሲያምን ፤ ይልቁንም ወለድ ወይም ከዕዳው ላይ በከፊል መስጠቱ እንደሚገኝበት ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1851 (ሀ) መገንዘብ ይቻላል። ከዚህ ድንጋጌ በግልጽ መገንዘብ የሚቻለውም ዕዳን አምኖ ከዕዳው ላይ በከፊል መክፈል ይርጋውን የሚያቋርጠው በዚሁ ባለዕዳ ላይ ብቻ ነው። ከመሰረቱም ይርጋን የተመለከቱ ድንጋጌዎች ሊተረጎሙ የሚገባው ህጉን እንደ አቀራረጹ በጥብቅ በመከተል (strict construction) ነው።

ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ህ/ቁ 1901 እና 1851(ሀ) መሰረት የይርጋ ጊዜን የማቋረጥ ውጤት ያለው ተግባር ያልተነጣጠለ ኃላፊነት ካለባቸው ባለዕዳዎች በአንዱ ከተፈፀመ በሌሎች ተከሳሾች ላይ ተፈፃሚ የማይሆንበትና ይርጋው የማይቋረጥበት ምክንያት የለም በሚል የደረሰበት መደምደሚያ እና ያሳለፈው ብይን በድንጋጌዎቹ በግልጽ የተመለከተውን ያልተከተለና ከተደነገጉበት አላማ የራቀ ነው። ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት ያሳለፈው ብይን የህግ መሠረት ያለው አይደለም ብለናል።

በአጠቃላይ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ ያቀረበው በህጉ በይርጋ ቀሪ ከሆነ በኋላ ሲሆን አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ያሳለፉት ብይንና ውሳኔ በህጉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል።

ው ሳ ኔ

1. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 89181 ግንቦት 11 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና ግንቦት 19/2014 ዓ.ም ያሳለፈው ውሳኔ፤ እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ኮ/መ/ቁ 293670 ነሐሴ 19 ቀን 2014 ዓ.ም ያሳለፈው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል።
2. ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሠረተው ክስ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ወስነናል።
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሣራ የራሳቸውን ይቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

አፈጻጸም

የኢትዮጲያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰ.መ.ቁ 205594

ጥር 27 **ቀን** 2014 **ዓ.ም**

ዳኞች፡- **እትመት አሠፋ**

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- **አቶ ኪነጥበብ አዳነ**

ተጠሪዎች፡- 1. **ከድጃ መሐመድ**

2. **አብዱ ካሳው**

3. **አብዱልቃድር ካሳው**

4. **ካሊድ ካሳው**

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሚያዝያ 01 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 03-30317 በቀን 09/07/2013 የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው።

ጉዳዩ የአፈጻጸም ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተሁለደሬ ወረዳ ፍ/ቤት ነው። በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር በዚህ የሰበር ክርክር የሌሉ እነ ሉባባ ካሳው የአፈጻጸም ከሳሾች፤ የአሁን ተጠሪዎች የአፈጻጸም ተከሳሾች፤ የአሁን አመልካች ደግሞ የጨረታ አሸናፊ በመሆን ተከራክረዋል። አፈጻጸሙን የመራው የወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ያቀረቡለትን የቅድሚያ ግዢ መብት ጥያቄ መርምሮ የጋራ ባለሀብቶች የቅድሚያ የግዢ መብት የሚጠበቅላቸው ቢሆንም ይህ የሚሆነው ግን ይኸው የቀዳሚነት ግዢ ይገባኛል የሚለው ወገን በቅድሚያ ወደ ጨረታው ለመግባት አስፈቅዶ የጨረታ ተሳታፊ ሲሆን እንጂ የጨረታውን ውጤት በመጠባበቅ የሚቀርብ አይደለም፤ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 443 ድንጋጌ ይዘትም የሚያረጋግጠው ይህንኑ ነው፤ ስለሆነም በተጠሪዎች የቀረበው የቅድሚያ ግዢ መብት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት በብይን ውድቅ አድርጎታል።

ተጠሪዎች ይህን ብይን በመቃወም ለደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል። ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ተጠሪዎች የንብረቱ ተካፋይ ስለሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1126 እና 2161 እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 37297 እና 37298 በሰጠው ውሳኔ መሠረት የቀዳሚነት መብት አላቸው በማለት ወስኗል።

አመልካች በበኩላቸው ይህን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል። ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ግራቀኙን ካከራከረ በኃላ የስር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ተመሳሳይ ምክንያት በመስጠት አጽንቶታል።

ተጠሪዎች በተራቸው ይህን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል። አቤቱው የቀረበለት ፍርድ ቤትም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ የስር

ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል።

አመልካች ሚያዝያ 01 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- በፍትሐብሔር ሕጉ ላይ ስለጋራ ባለሀብቶች ቀዳሚ የግዥ መብት የተደነገገቱ ድንጋጌዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 443 የተመለከተውን የቀዳሚነት መብቱን ለማግኘት አስቀድሞ በጨረታ ተወዳዳሪ የመሆን ግዴታ የሚያስቀሩ አይደሉም፤ ተጠሪዎች በጨረታ አልተሳተፉም፤ ተጠሪዎች በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1403 የተመለከተውን ሙሉ ዋጋ የማቅረብ ወይም ዋስትና የመስጠት ግዴቸውን ሳይወጡ ያቀረቡት የቀዳሚነት መብት ጥያቄ አግባብ አይደለም፤ በቀዳሚ የመግዛት መብት የሚፈቀደው ለስጋ ዘመዶች እንጂ ለጋብቻ ዝመዶች አይደለም፤ የቅድሚያ ግዢ መብቱ በጋራ እንዲሰጣቸው ያቀረቡት ጥያቄም ከሕግ ውጪ ነው፤ ስለሆነም በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ የሰበር ተጠሪዎች የጨረታ ተወዳዳሪ ባልሆኑበት የቀዳሚነት መብት አላቸው ተብሎ የተሰጠው የአፈጻጸም ውሳኔ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 403፤ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1403፤1386፤1389 እና 1390 ድንጋጌዎችን በአግባቡ ያገናዘበ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል።

ተጠሪዎች ሚያዝያ 26 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች ሙሉ ዋጋ የማቅረብ የዋስትና ግዴታቸውን አልተወጡም በማለት ያቀረበው ክርክር በስር ፍርድ ቤት ያልቀረበ አዲስ ክርክር ነው፤ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 443 በጨረታ አለመሳተፍ የቀዳሚነት ግዢ መብትን የሚያሳጣ ስለመሆኑ አይደነግግም፤ ተጠሪዎች በጨረታ ከወጣው ንብረት ላይ የድርሻችን መብት ያለን እንጂ ባለዕዳ አይደለንም፤ የጋራ ንብረት ለመካፈል የንብረቱ ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ግምት ውስጥ ሊገባ ይገባል፤ ስለሆነም የክፍፍሉን ድርሻ ለመወሰን የጨረታ አሸናፊ የሆነው አካል እንደማይገዛ እየታወቀ ጨረታው ሊወጣ ይችላል፤ ስለሆነም የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል ነው።

አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል።

የግራቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው። ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል።

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የቻልነው የአሁን አመልካች በጨረታ ተወዳድረው የጨረታ አሸናፊ በሆኑበት ንብረት ላይ የስር የአፈጻጸም ክሳሾች እና የአሁን ተጠሪዎች ድርሻ ያላቸው መሆኑን፤ ንብረቱ በጨረታ ከመሸጡ በፊት አመልካቾች አፈጻጸሙን ለሚመራው ችሎት ያቀረቡት የቀዳሚነት ግዢ መብት ጥያቄ የሌለ መሆኑን፤ ጨረታው ወጥቶ አመልካች የጨረታው አሸናፊ መሆናቸው ከታወቀ በኋላ ተጠሪዎች ለአፈጻጸም ችሎቱ የቀዳሚነት ግዢ መብት እንዲጠበቅላቸው ጥያቄ ያቀረቡ መሆኑን ነው። ስለሆነም በዚህ ችሎት ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው የክርክሩ መሠረታዊ ጭብጥ ተጠሪዎች የጋራ ባለሐብት የሆኑበት ንብረት በጨረታ ከመሸጡ በፊት ያቀረቡት የቀዳሚነት የግዢ መብት ጥያቄ ሳይቀርብ ጨረታው ተከናውኖ የጨረታው አሸናፊ ከታወቀ በኋላ ያቀረቡት የቀዳሚነት ግዢ መብት ጥያቄ ተቀባይነት ሊኖረው ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለው ነው።

በመሠረቱ የጋራ ባለሀብቶች የሆኑ ሰዎች ያልተከፋፈለውን የጋራ ንብረት ከማንኛውም ሶስተኛ ወገን በፊት በቀደምትነት በግዥ የማስቀረት ሕጋዊ መብት ያላቸው ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕገ ቁጥር 1261 (1) የተደነገገ ሲሆን ይህ መብት ተግባራዊ የሚደረግበት ስርዓትም በዚሁ ሕግ ከቁጥር 1386 እስከ 1409 በግልጸ ተደንግጎ ይገኛል። በሌላ በኩል የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 443 ድንጋጌ በፍርድ አፈጻጸም ምክንያት ተይዞ የሚሸጠው የማይንቀሳቀስ ንብረት ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎች በሕብረት የያዙት እና ያልተከፋፈሉት በሆነ ጊዜ ከተካፋዮቹ አንዱ ንብረቱን ለመግዛት በጨረታ ተወዳዳሪ ሆኖ የቀረበ እንደሆነ የፍርድ ባለዕዳው እንደቀረበ ተቆጥሮ የተቀዳሚነት መብት ይሰጠዋል በማለት ይደነግጋል።

ከላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ የሚቻለው የጋራ ባለንብረቱ በጨረታ ተወዳዳሪ የሚሆነው እና የተቀዳሚነት መብት የሚያገኘው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 430 (1) ላይ እንደተደነገገው በሐራጅ የሚሸጠውን ንብረት ያለፈቃድ የመግዛት ክልከላ እንደተደረገበት የፍርድ ባለመብት ሳይሆን የሚሸጠው የማይንቀሳቀስ ንብረት የጋራ ባለሀብት በመሆኑ ምክንያት ብቻ በሕጉ በተጠበቀለት መብት መሰረት መሆኑን ነው። ይህም የጋራ ባለሐብቱ ያለፍርድ ቤት ፈቃድ በጨረታው ለመሳተፍ መብት ያለው መሆኑን የሚያሳይ ነው። ይህን

ካልን ዘንዳ በሕግ በተጠበቀለት መብት መሠረት ያለፍርድ ቤት ፈቃድ በጨረታ ለመወዳደር መብት ያለው የጋራ ባለሐብት በጨረታው ሳይወዳደር ጨረታው ተከናውኖ አሸናፊው ከታወቀ በኋላ የሚያቀርበው የቀዳሚነት የግዢ መብት ጥያቄ ሊፈቀድለት ይገባል ወይስ አይገባም የሚለው ምላሽ ሊጠው የሚገባ መሠረታዊ ነጥብ ነው፡፡

በመሠረቱ አንድ ንብረት በጨረታ እንዲሸጥ ሲደረግ በጨረታው ሒደት ላይ ተሳታፊ የሚሆኑ ሶስተኛ ወገኖች አሉ፡፡ ስለሆነም የፍርድ ባለመብቱ ወይም የፍርድ ባለዕዳው በጨረታ በተሸጠው ንብረት ለይ የሚያቀርቡት ማናቸውም የመብት ጥያቄ ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው የጨረታ አሸናፊውንም የመብት ጥያቄ ባገናዘበ መልኩ ሊሆን ይገባል፡፡ በጨረታ በሚሸጠው ንብረት ላይ የጋራ ባለሐብት በመሆኑ ምክንያት በሕግ የቀዳሚነት መብት የተጠበቀለት ወገን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 443 ላይ በተገለጸው አግባብ ንብረቱን ለመግዛት በጨረታ ተወዳዳሪ ሆኖ ካልቀረበ በቀር ጨረታው ተከናውኖ አሸናፊው ከታወቀ በኋላ የጨረታውን ውጤት አውቆ የሚያቀርበው የቀዳሚነት መብት ጥያቄ በጨረታው አሸናፊ መብት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያለው በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪዎች የቀዳሚነት መብት አላቸው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 03-30317 በቀን 09/07/2013 የሰጠው ውሳኔ እና የደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 46058 በቀን 03/07/2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡

የተሁለደሬ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 22661 በቀን 18/05/2012 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 0109875 በቀን 20/02/2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡

በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

ሚያዝያ 04 ቀን 2013 ዓ.ም በመዝገቡ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የልዩነት ሀሳብ

ስማችን በሶስተኛ እና አራተኛ መስመር ላይ የተጠቀስነው ዳኞች አብላጫው ድምፅ የክልሉን ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ለመሻር በጠቀሰው ምክንያት እና በደረሰበት ድምዳሜ ያልተስማማን በመሆኑ ለልዩነት ያበቃንን ሀሳብ እንደሚከተለው አስፍረናል፡፡

የቅድሚያ ግዥ መብት(Right of Preemption) እና ንብረትን የማስመለስ የቀዳሚነት መብት(Right of Recovery) ሁለቱም በአንድ ንብረት ላይ የሚቋቋሙ የቀደምትነት መብቶች ቢሆኑም ከመብቶቹ ምንጭ እና በአፈፃፀም ረገድ የተለያዩ ናቸው፡፡ በፍትሓ ብሔር ህጋችን ስለቅድሚያ ግዢ መብት በዋናነት የተደነገገው በአንቀፅ 8፤ ምዕራፍ 5 ከቁጥር 1410 እስከ 1443 ስር በተመለከቱት ድንጋጌዎች ነው፡፡ በዚሁ መሰረት የቅድሚያ ግዥ መብት ማለት የአንድ ንብረት ባለሃብት የሆነ ሰው ይህንኑ ሃብቱን ለመሸጥ በሚወስንበት ጊዜ አንዱን ሰው በመምረጥ ሀብቱን እሸጥልሃለው ሲል ለዚሁ ለመረጠው ሰው ከሚገባለት የስምምነት ቃል የሚመነጭ መብት ማለት እንደሆነ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1410(2) ይደነግጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ስር የመብቱ ምንጭ ውል እንደሆነ የተመለከተ ቢሆንም የቅድሚያ ግዥ መብት ከህግም ጭምር የሚመነጭ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1483 እና 1484 ድንጋጌዎችን በአብነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ ስለዚህ በጥቅሉ የቅድሚያ ግዥ መብት ከውል ወይም ከህግ ሊመነጭ ይችላል ማለት ነው፡፡ ይህ መብት ተግባራዊ የሚደረግውም የቅድሚያ ግዥ መብቱ የተቋቋመበት ንብረት ባለሃብት የሆነው ሰው ንብረቱን በሚሸጥበት ጊዜ ወይም ንብረቱ በሃራጅ የሚሸጥ ከሆነም የሃራጅ ሥነ ሥርዓቱ በሚከናወንበት ወቅት በህጉ ተለይቶ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ቀርቦ መብትን በመጠየቅ እና በማረጋገጥ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1417 እስከ 1421 ድንጋጌዎች ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል ንብረትን የማስመለስ የቀዳሚነት መብት(Right of Recovery) በዋናነት የተመለከተው በፍ/ብ/ህጉ ከቁጥር 1386 እስከ 1409 ድረስ በተጠቀሱት ድንጋጌዎች ነው፡፡ በእነዚህ ድንጋዎች መሰረት ንብረትን የማስመለስ መብት ማለት የንብረቱን ዋጋ በመክፈል ንብረቱ ከተላለፈለት ሶስተኛ ወገን እጅ ለማስመለስ በህግ ተለይቶ መብቱ ለተሰጣቸው ሰዎች የተቋቋመ የቀደምትነት መብት ማለት እንደሆነ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1386 ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ይዘት መረዳት እንደሚቻለው መብቱ የሚገኘው ከህግ ብቻ ነው፡፡ መብቱም የተጠቀበው ለማናቸውም ሰው ሳይሆን ለአንድ ንብረት የጋራ

ባለሃብቶች እና በዋናው ባለሃብት ጋር የሥጋ ዝምድና ላላቸው ሰዎች ብቻ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1388፣ 1389 እና 1394 ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በዚህ መልኩ በህግ የተቋቋመው የቀደምትነት መብት ተግባራዊ የሚደረገውም የመብቱ ባለቤት መብቱ የተቋቋመበት ንብረት ለሶስተኛ ወገን ስለመተላለፉ ከተነገረው ቀን አንስቶ በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ መሆኑን፤ ስለንበረቱ መተላለፍ ያልተነገረው ከሆነ ደግሞ ንብረቱ መተላለፉን ካወቀበት ቀን አንስቶ ለጋራ ባለንበረት ከሆነ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ፤ የሥጋ ዘመዶች ከሆኑ ደግሞ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1400 እና 1401 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ መልኩ ንብረቱን እንዲለቅ ለሚደረገው ሶስተኛ ወገን በህግ የተቀመጠው መፍትሄም ንብረቱን የገዛበትን ዋጋ፣ ንብረቱ በእጁ ከገባ በኋላ በንብረቱ ላይ ያወጣውን ወጪ እና በንብረቱ ላይ ያደረገውን መሻሻል እንዲሁም በጉዳዩ ውስጥ ያለአግባብ የመበልፀግ ሁኔታ ተከስቶ ከሆነም ያለአግባብ ስለመበልፀግ በሚደነግገው የፍ/ብ/ህጉ አንቀፅ 2162-2178 መሰረት ተገቢው ክፍያ እንዲከፈለው መጠየቅ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1405 እስከ 1409 ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

እንግዲህ ከሁለቱ የቀደምትነት መብቶች መሰረታዊ ምንጭ እና ተግባራዊ አፈፃፀም ከሚደነግጉት የህጉ ክፍሎች ይዘት በግልፅ መረዳት እንደሚቻለው የቀደምትንት መብቱ በተቋቋመበት ንብረት ሽያጭ ሂደት ቀርቦ መብትን መጠየቅ እና ማረጋጥ ግዴታ የሚሆነው የግዥ የቀደምትነት መብትን (Right of Preemption) በተመለከ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ባለፈ ንብረትን የማስመለስ የቀዳሚንት መብት (Right of Recovery) ያለው ሰው ንብረቱ በማናቸውም መንገድ ለሶስተኛ ወገን መተላለፉን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በህጉ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ቀርቦ መጠየቅ እስከ ቻለ ድረስ ንብረቱን ማስመለስ የሚችል በመሆኑ በንብረት ሽያጭ ሂደት መቅረብ አይጠበቅበትም፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ ተጠሪዎች በአፈፃፀም ምክንያት እንዲሸጥ በተባለው ንብረት ላይ የጋራ ባለሃብቶች ስለመሆናቸው ያልተካደ ፍሬ ነገር ነው፡፡ ተጠሪዎች አፈፃፀሙን ሲመራ ለነበረው ፍርድ ቤት ያቀረቡት ጥያቄም በሀራጅ በተሸጠው ንብረት ላይ የጋራ ባለሃበት ድርሻ ያላቸው መሆኑን በመግለፅ የጫረታው አሸናፊ የሆኑት የአሁን አመልካች ሃራጁን ያሸነፉበትን ዋጋ ከፍለን ንብረቱን እንድናስመልስ ይፈቀድልን የሚል ነው፡፡ ይህ ጥያቄ የጋራ ባለሃብት የሆኑበት እና በአፈፃፀም ለሶስተኛ ወገን የተላለፈን ንብረት ለማስመለስ

የቀረበ የቀደምትነት መብት (Right of Recovery) እንጂ የግዥ የቀደምትነት መብት ይጠበቅልን (Right of Preemption) ጥያቄ አይደለም፡፡ የተጠሪዎች ጥያቄ ይህ ከሆነ ደግሞ በንብረቱ ሽያጭ ሂደት ቀርባችሁ በሀራጁ ላይ ልትካፈሉ ይገባ ነበር የሚባሉበት የህግ መሰረት የለም፡፡

በእርግጥ አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤትም ሆነ በዚሁ ችሎት አብላጫ ድምጽ የያዙት የስራ ባልደረቦቻችን ለውሳኔያቸው መሰረት ያደረጉት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 443 ድንጋጌን ነው፡፡ በመሰረቱ ይህ የሥነ ሥርዓት ህጉ ድንጋጌ በአንድ በአፈፃፀም ምክንያት በሚሸጥ ንብረት ላይ የቀደምትነት መብት ያላቸው ሰዎች ንብረቱ በሚሸጥበት ሀራጅ ላይ ካልተካፈሉ በቀር የቀደምትነት መብት መጠየቅ አይችሉም የሚል አይደለም፡፡ ከዚህ ይልቅ ንብረቱ የበርካታ ሰዎች ያልተከፋፈለ የጋራ ሀብት ከሆነ እና ከእነዚህ የጋራ ባለድርሻዎች ውስጥ አንዱ በሀራጁ ከተሳተፈ ዋናው የፍርድ ባለእዳ እንደቀረበ ተቆጥሮ በሀራጁ ለተሳተፈው የጋራ ባለሃብት በቀዳሚነት የመግዛት መብት ይጠበቅለታል የሚል ነው፡፡

ከመነሻውም ቢሆን የቀደምትነት መብት ምንጩ መሰረታዊ ህግ እንጂ የሥነ ሥርዓት ህግ አይደለም፡፡ የሥነ ሥርዓት ህግ መሰረታዊ ዓላማም በመሰረታዊ ህግ የተቋቋመ መብት የሚፈፀምበትን ሥርዓት ማበጀት ነው፡፡ ከዚህ ውጪ በመሰረታዊ ህግ የተቋቋመ መብት እና ጥቅም በሥነ ሥርዓት ህግ ቀሪ የሚሆንበት የህግ አስተምህሮ የለም፡፡ ከዚህ አንፃር በፍ/ብ/ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 443 ስር የተመለከተው ድንጋጌ ንብረትን የማስመለስ የቀደምትነት መብትን የሚመለከት ባለመሆኑ ለቀረበው ጉዳይ አግባብነት ያለው ድንጋጌ አይደለም፡፡

ሲጠቃለል የአሁን ተጠሪዎች በአፈፃፀም ምክንያት በተሸጠው ንብረት ላይ የጋራ ባለሃብቶች በመሆናቸው እና ንብረቱንም የማስመለስ ከህግ የመነጨ የቀደምትነት መብት ያላቸው በመሆኑ በንብረቱ ሽያጭ ሂደት በተጫራችነት መካፈል ሳያስፈልጋቸው ንብረቱ ከተላለፈለት ከማናቸውም ሰው የሸያጩን ዋጋ ከፍለው የማስመለስ መብት አላቸው፡፡ ከዚህ አኳያ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን የተረዱበት እና ክርክሩን የመሩበት ሁኔታ በፍ/ብ/ህጉ ስለ ንብረት ማስመለስ የቀደምትነት መብት (Right of Recovery) የተመለከተውን ድንጋጌ መንፈስ የተከተለ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍበት

መሰረታዊ የህግ ስህተት ባለመኖሩ ሊፀና ይገባ ነበር በማለት ከስራ ባልደረቦቻችን የተለየ አቋም ይዘናል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ኃ

የሰ.መ.ቁ. 215842

ሚያዝያ 25 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- መዓዛ አሸናፊ

እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ወ/ሮ ቀመሪያ አህመድ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ የሱፍ ሰኒ

2. ወ/ሮ ዘውዲት አብደላ

3. ወ/ሮ እዮባ ሳኒ አልቀረቡም

4. ወ/ሮ ሰውዳ ሳኒ

5. አቶ መዝሚል ሳኒ

6. አቶ መሃመድአሚን ሳኒ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ጥቅምት 19 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 252680 ጥቅምት 23 ቀን 2013 ዓ.ም

የሰጠውን ትዕዛዝ በማጽናት፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 199069 ሐምሌ 30 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የአፈጻጸም ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን 1ኛ ተጠሪ የፍርድ ባለመብት፤ የአሁን አመልካች እና ከ2ኛ -6ኛ ተጠሪዎች ደግሞ የፍርድ ባለዕዳዎች በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ንብረቶቹ የሚሸጡ ከሆነ የቀዳሚነት መብቴ ይጠበቅልኝ በማለታቸው ተጠሪዎችም የቀዳሚነት መብት ጠይቀዋል፡፡

አፈጻጸሙን የመራው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1060(2) እና 1261 (1) መሰረት ተጠሪዎችም በቀዳሚነት የመግዛት መብት አላቸው፤ ንብረቶቹ በሀራጅ ከተሸጡ የፍርድ ባለመብት እና ባለዕዳዎች እንደማንኛውም ሰው በጨረታው ተወዳድረው ለማሸነፍ ከቻሉ ለመግዛት እንሚችሉ ለፍርድ አፈጻጸም ዳሬክቶሬት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ይህንኑ ትዕዛዝ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም አመልካች የቅድሚያ ግዥ መብት እንዲሰጣቸው አመልክተው ተጠሪዎች ጥቅምት 6 ቀን 2013 ዓ.ም በሰጡት አስተያየት የቅድሚያ ግዥ መብት ጥያቄውን እንደሚቃወሙ እና የቅድሚያ መብት እንዲሰጣቸው ጥያቄ አቅርበዋል፤ በግራቀኙ መካከል ስምምነት የሌለ ከሆነ ደግሞ ለአንዱ የጋራ ባለሃብት የቅድሚያ ግዥ መብት የሚሰጥበት የህግ አግባብ የለም፤ ለጋራ ባለሃብቶች ከሌሎች 3ኛ ወገኖች በቅድሚያ የመግዛት መብት ከመስጠት ባለፈ በጋራ ባለሃብቶች መካከል በሁለቱ ወይም ከዚያ በላይ ባሉ የጋራ ባለሃብቶች የቅድሚያ ግዥ መብት ጥያቄ ቢነሳ ከጋራ ባለሃብቶች መካከል ለአንዱ ተለይቶ ሊሰጥ እንደሚችል በህግ የተቀመጠ ድንጋጌ የለም፤ ስለሆነም አንዱ የጋራ ባለሃብት የቅድሚያ ግዥ መብት እንዲሰጠው በግራ ቀኙ መካከል የተደረገ ስምምነት የሌለ መሆኑን ከግራቀኙ ክርክር መረዳት የተቻለ በመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ጥቅምት 19 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፡- አመልካች ከሚች ጋር የነበራቸው የጋራ ባለንብረትነት ከሆነ ልክ እንደ ፍርድ ባለእዳ ተቆጥረው የቀዳሚነት መበት ሊሰጣቸው ይገባል፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካችን የሚች ሚስት ሆነው እያለ እንደ ወራሽ በመቁጠር በፍታብሔር ህግ

ቁጥር 1060(2) መሰረት አመልካች እና ተጠሪዎች የጋራ ባለሃብቶች ናቸው በማለት አመልካች በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1386 እና 1093(2) መሰረት የቀዳሚነት መብት ሊሰጣቸው አይችልም በማለት የሰጠው ውሳኔ ስህተት ነው፤ የተጠሪዎች ጥያቄ የገንዘብ ትርፍ የማግኘት ሲሆን የአመልካች ጥያቄ ደግሞ ከቤቱ ጋር ያላቸው ቁርኝነት ይከበርልኝ ነው፤ ተጠሪዎች አመልካች ያቀረቡትን የቀዳሚነት መብት ባልካዱበት እና የቀዳሚ መብትም ሆነ የመጫረት መብት በግልጽ አቤቱታ ባልጠየቁበት የስር ፍርድ ቤት ለአመልካች ባቀረበችው የአፈጻጸም ክስ ላይ የሰጡትን መልስ መነሻነት በማድረግ የሰጠው ብይን የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 182 እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 33945 እና በመ.ቁ. 54790 ላይ የተሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሚቃረን ነው፤ በመሆኑም በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ትዕዛዝ እና ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ አመልካች የንብረቱ ግማሽ ባለድርሻ በመሆናቸው የቅድሚያ መብት ይሰጠኝ ሲሉ ያቀረቡት ክርክር ውድቅ የመደረጉ አግባብነት ከፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 443 አተገባበር አንፃር ለማጣራት የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

1ኛ ፣ 5ኛ እና 6ኛ ተጠሪዎች ጥር 23 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፡- በግራ ቀኙችን መካከል የመብት መበላለጥ በሌለበት ሁኔታ ለአመልካች የቅድሚያ መብት የሚሰጥበት የህግ አግባብ የለም፤ በህጉ ላይ የማይንቀሳቀስ ንብረት ግማሽ ባለድርሻ የሆነ ሰው የቀዳሚነት ድርሻ ይሰጠዋል የሚል ሃሳብ ቢኖር አንኳን ተጠሪዎች የንብረቱን ግማሽ ባለድርሻ በመሆናችን የቅድሚያ መብት ይሰጠን ብለን አንድ ላይ አፈጻጸሙን ለያዘው ፍርድ ቤት የጠየቅን በመሆኑ የተጠሪዎች ድርሻ ከአመልካች ድርሻ ያንሳል የሚባልበት የህግ አግባብ የለም፤ ከጅምሩ ቤቱ ለኪራይ አገልግሎት ሲውል የነበረ ስለሆነ በቤቱ አካባቢ ማህበራዊ ግንኙነት አልተመሰረተም፤ አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ላይ የጠቀሷቸው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 33945 እና በመ.ቁ. 54790 ላይ የተሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም ለግራ ቀኙችን አፈጻጸም ክርክር አግባብነት የለውም፤ በስር ፍርድ ቤት ከ1ኛ ተጠሪ ውጪ አመልካችን ጨምሮ የፍርድ ባለዕዳዎች መሆናችን በግልጽ ተሰይመን ባለበት ሁኔታ አመልካች ከተጠሪዎች በተለየ መልኩ ቅድሚያ የማግኘት መብት የላትም፤ የስር ፍርድ

ቤት አመልካችን እንደወራሽ ቆጥሯል በሚል የቀረበው ክርክር ሀሰት ነው፤ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ትዕዛዝ እና ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

2ኛ፣ 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች አመልካች መጥሪያ ስለማድረሳቸው በድጋሚ ቃለመሃላ ስላቀረቡ ተጠሪዎች መጥሪያ ደርሷቸው ያልቀረቡ ስለሆነ መልስ በጽሁፍ የማቅረብ መብታቸው ታልፎ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበው የግራ ቀኙ የጽሁፍ ልውውጥ በዚህ ተጠናቋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል እኛም የቀረበውን አቤቱታ በስር ፍ/ቤት በግራ ቀኙ ከተደረገው አጠቃላይ ክርክር እና ከተሰጠ ውሣኔ እንዲሁም ከማስቀረቢያ ነጥቡ አንፃር አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች በስር ፍ/ቤት የግዢ ቅድሚያ መብት እንዲሰጣቸው ያመለከቱ መሆኑን እና ተጠሪዎች በቀረበው ጥያቄ ላይ አስተያየት እንዲሰጡ በፍ/ቤቱ ተጠይቀው የቅድሚያ መብት ጥያቄውን የማይቀበሉ እና የማይስማሙ መሆኑን ገልፀው የቅድሚያ መብት ግዢ እንዲፈቀድላቸው ፍ/ቤቱን ጠይቀው የነበረ መሆኑን ከክርክሩ ይዘት ተመልክተናል፡፡

እያከራከረ ያለው ንብረት በባልና ሚስት የተፈራ እና ባል በሞት በመለየታቸው ምክንያት የድርሻ ክፍፍል ጥያቄ ቀርቦበት ግራ ቀኙ እኩል እንዲካፈሉ በመወሰኑ ምክንያት የቅድሚያ የመግዛት መብት ይገኛል ጥያቄ ነው፡፡ይህንኑ አስመልክቶ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ/ 88275፣160198፣168192 እና በሌሎችም መዛግብት በሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ክፍፍል ስርዓት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስትም ሆነ በክልል ሕግጋት መንግስታት የተረጋገጠውን የእኩልነት መብት መሰረት አድርጎ መከናወን ያለበት መሆኑን፣ ክፍፍሉ የሚከናወንበት ስርዓትም የተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 ከአንቀፅ 90 እስከ 93 ድረስ በቅደም ተከተል ባስመቀጣቸው መንገዶች መሆን፣ የጋብቻ ውጤት የሆነው የጋራ ንብረት ክፍፍል ሊከናወን የሚገባው የእኩልነት መርህን መሰረት አድርጎና የተጋቢዎችን ፈቃድ በመመርኮዝ መሆኑን፣ የተጋቢዎች ስምምነት ከሌለ ደግሞ ክፍፍሉ መፈፀም ያለበት በሕጉ የተመለከተውን ቅደም ተከተል መሰረት አድርጎ ሊሆን እንደሚገባ በመግለጽ ወስኗል፡፡ ይህ ስርአትም በአፈፃፀም ጊዜም ልንከተለው የሚገባ ሥርአት መሆኑን ከውሣኔው ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ክፍፍል በሚከናወንበት ጊዜ የእኩልነት መርህን የተከተለ መሆን ያለበት ስለመሆኑ፣ የጋራ ንብረት ክፍፍል በሚፈፀምበት ጊዜም በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ ድንጋጌዎች መርህ አንፃር ግራ ቀኙ ከተስማሙ በዓይነት የሚካፈሉበት ይህ ካልሆነ ደግሞ በገበያ ዋጋ በጨረታ ተሸጦ እኩል ሊካፈሉ እንደሚገባ አስቀድሞ ከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ/ 37508 እና 35003 በሆነው መዝገብ ላይ የህግ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡ ወደ ያዝነው ጉዳይ ስንመለስ አመልካችና ተጠሪዎች የድርሻ ክፍፍል ይደረግልን የሚሉ ቢሆኑም የሚከፋፈሉት ንብረት አመልካች እና የአመልካች ባለቤት የነበሩት የተጠሪዎች አባት በጋራ ያፈሩትን ንብረት በመሆኑ ተጠሪዎች ሟቹን የጋራ ባለሀብት ተክተው የአባታቸውን ድርሻ ለመካፈል በመሆኑ በንብረቱ ላይ እኩል ባለድርሻ ናቸው፡፡ በመሆኑም የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል ጥያቄ የሚስተናገደው የእኩልነት መርህን ተከትሎ በመሆኑ አመልካች የግዢ ቅድሚያ መብት ይሰጠኝ ብለው የጠየቁ ቢሆንም ተጠሪዎች ግን ቅድሚያ ግዢ መብት ለአመልካች ሊሰጥ አይገባም ይልቁንም ለእኛ ነው ቅድሚያ ግዢ መብት ሊሰጠን የሚገባው በማለት የተከራከሩ በመሆኑ በግራ ቀኙ መካከል በግዢ ቅድሚያ መብት ጥያቄው ላይ ስምምነት ያለመገኘቱን ተረድተናል፡፡

በመሆኑም የግዢ ቅድሚያ መብት ጥያቄው ላይ ግራ ቀኙ ያልተስማሙ በሆነ ግዜ የግዢ ቅድሚያ መብት ጥያቄው ከግራ ቀኙ ለአንዱ ሊፈቀድ የማይገባው እና ንብረቱ በጨረታ ተሸጦ ክፍፍል የሚደረግበት ሲሆን ነገር ግን ግራ ቀኙ እንደማንኛውም ተጫራች በጨረታው ተወዳድረው ንብረቱን ማስቀረት ከሚችሉ በቀር የቅድያ መብት ጥያቄው ለእኔ ሊሰጥ ይገባው ነበር በሚል የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ሊታረም ይገባል በማለት አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ውሣኔ የሚነቀፍና መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም ብለን ተከታዩን ወስነናል፡፡

ውሣኔ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በይ/መ/ቁ/ 199069 በ30/11/2013 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 252680 በ23/2/2013 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡

በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በግራ ቀኙ የወጣ ወጪ ካለ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

የውሣኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡

መዝገቡ ውሣኔ ስላገኘ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፌርማ አለበት

<u>የሃሣብ ልዩነት</u>

እኔ በአራተኛው ተራ ቁጥር ስሜ የተጠቀሰው ዳኛ አብላጫው ድምፅ ግራ ቀኙ ባልተስማሙበት የግዢ ቅድሚያ መብት ሊጠበቅ የሚችልበት የህግ አግባብ የለም በማለት የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ በማፅናት በሰጠው ውሳኔ ያልተስማማሁ በመሆኑ ያለኝን የልዩነት ሀሳብ እንደሚከተለው አሰፍሬያለሁ ።

አመልካች የተቀዳሚነት መብት ይሰጠኝ አቤቱታ ያቀረቡት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.443 መሰረት ሲሆን በዚህ ድንጋጌ መሰረትም በአፈፃፀም ምክንያት የሚሸጠው የማይንቀሳቀስ ንብረት ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎች በህብረት የያዙት እና ያልተከፋፈሉት ከሆነ ከተካፋዮቹ አንዱ ንብረቱን ለመግዛት በጨረታ ተወዳዳሪ ሆኖ ቀርቦ በንብረቱ ላይ ድርሻ ከሌለው የጨረታው ተሳታፊ ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ ከፍተኛ ዋጋ ካቀረቡ በንብረቱ ላይ ድርሻ ላለው የጨረታ ተሳታፊ የቅድሚያ መብት የሚሰጥበትን የህግ አግባብ የሚደነግግ ሲሆን በኔ እምነት በሰ/መ/ቁ.160198 የተሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም ይህንን የድንጋጌውን መንፈስ የተከተለ ነው ብዬ ስማላምንና በድንጋጌው ላይ በምንም መልኩ ያልተካተተውን የንብረቱን ተጋሪዎች ስምምነት በመስፈርትነት ያስቀመጠ የህግ ትርጉም በመሆኑ አስገዳጅ ውሳኔው በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 27 መሰረት ከሰባት ያላነሱ ዳኞች ለተሰየሙበት የሰበር ችሎት ቀርቦ አስገዳጅ የህግ ትርጉሙ ሊሻሻል ይገባል እንጂ ይህንን አስገዳጅ የህግ ትርጉምና በሰበር መ/ቁ.168192 የተሰጠውን ከሀራጅ ሽያጩ በፊት ስላለው የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል በስምምነት አንዱ ወገን የሌላኛውን ድርሻ ከፍሎ ስለሚያስቀርበት አግባብ ትርጉም የተሰጠበትን እንዲሁም በሰ/መ/ቁ.88275 መልሶ ስለመግዛት መብት (Recovery Right) የተሰጠን አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት በማድረግ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊፀና አይገባም ነበር በማለት ከስራ ባልደረባዎቼ በሀሳብ ተለይቼያለሁ።

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፌርማ አለበት

ወንጀል

የሰ/መ/ቁ.118227

ቀን 29/07/2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተፈሪ ገብሩ

ቀነዓ ቂጣታ

አይሸሽም መለስ

ጸሐይ መንክር

አመልካች፡- ኮሎኔል ዓለም ትኩዕ -ቤተሰብ ወንድወሰን ተፈራ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የምእራብ እዝ ወታደራዊ ዓቃቤ ሕግ ሻንበል ፋንታ ሳሌ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች ወታደራዊ ማዕረግ "ኮሎኔል" ሆኖ እያለ በዳኝነት የተሰየሙት መኮነኖች ከአመልካች ጋር ቢያንስ አቻ ማዕረግ ያላቸው መሆን ሲገባቸው፣ አመልካች የተከሰሱበት ወንጀል ከአምስት ባላነሱ ዳኞች፣ ሊታይ ይገባው የነበረ መሆኑንና አለመሆኑን በሰበር ችሎት አጣርቶ ለመወሰን የሚል ጭብጥ ተመስርቶ ነው፡፡ ቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት ሚያዚያ 27 ቀን 2007 ዓ.ም ፍርድ የሰጠው፣ የዳኞችን ስምና ማዕረግ ሳይሰይም ዳኞች "አልተለወጡም" በማለት በመሆኑ፣ የአመልካችን ጉዳይ በዳኝነት አይተው ፍርድ የሰጡትን ዳኞች ስም፣ ማዕረግና ጉዳዩን ለማየት በዳኝነት የተሰየሙትን ዳኞች ቁጥር ለማረጋገጥ፣ የቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት የመዝገብ ቁጥር 268/07 በትእዛዝ በማስቀረብ ተመልክተናል፡፡

ይህ የሰበር ችሎት በትእዛዝ ካስቀረበው የቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት የመዝገብ ቁጥር 268/2007 እንደተረዳነው የአመልካች ጉዳይ የታየው ሶስት ዳኞች በተሰየሙበት የቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት ችሎት መሆኑንና ጉዳዩን በዳኝነት ካዩት ውስጥ ሰብሳቢው ዳኛ የኮሎኔል ማዕረግ ያላቸው፣ ሌሎች ሁለት ዳኞች ደግሞ የሻንበል ማዕረግ ያላቸው መሆኑን ተረድተናል፡፡ የአመልካችን

ጉዳይ ያለው ቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት ችሎት የዳኞቹን ማዕረግ፣ ሙሉ ስም በፍርዱ ላይ አለመግለጹ የፍርድ አጻጻፍ ስህተት ያለበት መሆኑን ያሳያል። በሌላ በኩል ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ስንመለከተው፣ አመልካች በወንጀል ተጠርጥሮ የተያዘው የካቲት 14 ቀን 2007 ዓ.ም መሆኑንና የአመልካች ጉዳይ ለቀዳሚው ወታደራዊ ፍ/ቤት ተጠሪ የወንጀል ክስ ያቀረበው የካቲት 14 ቀን 2007 ዓ.ም መሆኑን በትእዛዝ ካስቀረብነው መዝገብ ተረድተናል።

ይህም የአመልካች ጉዳይ በቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት በሚታይበት ጊዜ፣ የሰበር አጣሪ ችሎት ጭብጥ ለመያዝ መሰረት ያደረጋቸው አዋጅ ቁጥር 27/1988 ፣ በአዋጅ ቁጥር 123/90 እና በአዋጅ ቁጥር 343/95 እንደተሻሻለ ከታህሳስ 24 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ስራ ላይ በዋለው በአዋጅ ቁጥር 809/2006 በአንቀጽ 74 ንዑስ አንቀጽ 1 ሙሉ በሙሉ የተሻሩ መሆኑን ተረድተናል። ከዚህ አንጻር ሲታይ በአዋጅ ቁጥር 809/2006 አንቀጽ 45 ከአምስት አመት በታች በሚያስቀጣ ወንጀል የተከሳሽ ሰው አንድ ዳኛ በሚሰይምበት ችሎት ከአምስት አመት በላይ በሚያስቀጣ ወንጀል የተከሰሰ ሰው ሶስት ዳኞች በሚሰየሙበት ችሎት የሚታይ መሆኑ በንዑስ አንቀጽ 1 እና በንዑስ አንቀጽ 2 በግልጽ ተደንግጓል። የዳኞችን ማዕረግ በተመለከተም በቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት ከሚሰየሙ ዳኞች መካከል ቢያንስ ሰብሳቢው ዳኛ በወንጀል ተጠርጥሮ ከተከሰሰው ሰው የበለጠ ወይም አቻ ማእረግ ሊኖረው የሚገባ መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 809/2006 አንቀጽ 45 ንዑስ አንቀጽ 7 በግልጽ ተደንግጓል።

አመልካች በወንጀል ተጠርጥሮ በተከሰሰበት ጊዜ፣ አዋጅ ቁጥር 27/88 በአዋጅ ቁጥር 123/90 እና በአዋጅ ቁጥር 343/95 እንደተሻሻለ ሙሉ በሙሉ ተሽሯል። አመልካች ጉዳዩ ሲታይ የተሻሩና ተፈጻሚነት የሌላቸውን አዋጆች መሰረት በማድረግ የቀረበው የሰበር አቤቱታ የሕግ መሰረት እና ድጋፍ የለውም። የአመልካች ጉዳይ የታየው ከታህሳስ 24 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ በዋለው አዋጅ ቁጥር 809/2006 አንቀጽ 45 ንዑስ አንቀጽ 2 በተደነገገው መሰረት ሶስት ዳኞች በተሰየሙበት ቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት መሆኑንና በዳኝነት የተሰየሙት ሶስት ዳኞች ውስጥ ሰብሳቢው ዳኛ የአዋጅ ቁጥር 809/2006 አንቀጽ 45 ንዑስ አንቀጽ 7 በሚደነግገው መሰረት ከአመልካች ጋር አቻ የሆነ “የኮሎኔል” ማዕረግ ያላቸው መሆኑን አረጋግጠናል። በመሆኑም የአመልካች ጉዳይ በወቅቱ ስራ ላይ የነበረውን የአዋጅ ቁጥር 809/2006 በሚደነግገው መሰረታዊ የሆኑ የዳኞች ቁጥርና ማዕረግ ተሟልቶ በመሆኑ አመልካች የሕጉን መሰፈርት በማያሟላ ችሎት ታይቶ የተሰጠው ፍርድ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታና የሕግ መሰረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም።

የሰበር አጣሪ ችሎት አመልካችን ጉዳይ ለዚህ ሰበር ችሎት ሲያቀርብ ከመሰረተው ጭብጥ አንጻር፣ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ፣ የአመልካች ጉዳይ በታየበት ወቅት ስራ ላይ የነበረውን አዋጅ ቁጥር 809/2006 ድንጋጌዎች ያላገናዘበ በመሆኑ ውድቅ ተደርጓል። በማስከተል መታየት ያለበት የቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ያስተላለፉት የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔ ተገቢነት ያለው መሆኑ ወይም አለመሆኑ ሆኖ አግኝተነዋል። አመልካች የተሰጠባቸውን የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔ በመቃወም የሰበር አቤቱታው ያቀረበ ሲሆን ተጠሪ በፍርድ ቤቱ መልእክት ክፍል መጥሪያ ደርሶት መልሱን ባለማቅረቡ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል።

አመልካች በወታደራዊ ዓቃቤ ሕግ ያቀረበበት አራት የወንጀል ክሶች የተገለጹትን የወንጀል ድርጊቶች ማለት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ አንቀጽ 306/3/ የተመለከተውን በመተላለፍ በጥር ወር 2007 ዓ.ም አስራ አምስት ጥይት ለቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጸጥታ ሃይል ድጋፍ እናደርጋለን ብለው ወስደው ማጥፋታቸው፣ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና 306/1/ የተመለከተውን በመተላለፍ አንድ ክላሽ ጠመንጃ ከሰላሳ ጥይትና ከአንድ ካዝና ጋር መውሰዱና በ 2006 ዓ.ም በወንጀል ሕግ ቁጥር 306/3/ የተመለከተውን በመተላለፍ አስራ አምስት ሺ ጥይት ወስዶ ማጥፋቱና የተጠሪን የሰውና የጽሑፍ ማስረጃ የሰማውና የመረመረው የቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት በማረጋገጥ፣ አመልካች የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ብይን ሰጥቶ፣ አመልካች የመከላከያ ማስረጃ አሰምቷል። የአመልካች ማስረጃ የተጠሪን ማስረጃ ለማስተባበል የማይችል ተዓማኒነትና ክብደት የሌለው በመሆኑ አመልካች ከላይ የተገለጹትን ወንጀሎች የፈጸመ ጥፋተኛ ነው በማለት ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድ ቤቱ በሕግ የተሰጠውን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን መሰረት በማድረግ ወስኗል።

ቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት የደረሰበት የፍሬ ጉዳይና የማስረጃ ምዘና መደምደሚያ ትክክል መሆኑን በማረጋገጥ ወታደራዊ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በትእዛዝ አጽንቶታል። ይኸ ሰበር ችሎት ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ በመመዘን ሂደት የተፈጸመ ስህተት መኖሩን ወይም አለመኖሩን የማጣራትና በሰበር አይቶ የማረም ስልጣን የለውም። በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3/ሀ/ እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 አልተሰጠውም። በመሆኑም አመልካች ያለበቂ ማስረጃ ጥፋተኛ መባሌ ተገቢ አይደለም በማለት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ የሕግ መሰረት እና ድጋፍ የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም።

አመልካች ቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የሰጡትን የጥፋተኛነት ውሳኔ በመቃወም ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ውድቅ ከተደረገ በማስከተል መታየት ያለበት በአመልካች

ላይ የተወሰነው የቅጣት ውሳኔ ተገቢነት ያለው መሆኑ ነው፡፡ ቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት በአመልካች ላይ የቅጣት ውሳኔ የወሰነው አመልካች በወንጀል ሕግ 306/3/ ጥፋተኛ የተባለባቸውን ሁለት ወንጀሎች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 61/2/ መሰረት በአንድ በማጠቃለል፣ ወንጀሉ ከባድ /ከፍተኛ/ ደረጃ በመመደብና መነሻ አስራ ስድስት ዓመት ጽኑ እስራት ይዟል፡፡ አመልካች በወንጀል ህግ 306 (1) ጥፋተኛ ለተባለበትን ወንጀል ደረጃው ከፍተኛ ነው በማለት አምስት ዓመት ጽኑ እስራት መነሻ ቅጣትነት ይዞ በመደመር 21 ዓመት ጽኑ እስራት መነሻ ቅጣት እድርጎ ይዟል ይህም በመመሪያ ቁጥር 2/2006 በእርከን 36 ላይ የሚያርፍ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ተጠሪ ካቀረባቸው የቅጣት ማክበጃዎች ውስጥ ሁለት የቅጣት ማክበጃ የሚቀበል ቅጣቱ እርከን ስልሣ ስምንት ላይ አሳርፎታል፡፡ ከዚህ በኋላ አመልካች ካቀረባቸው የቅጣት ማቅለያ ምክንያት አራት የቅጣት ማቅለያዎችን በመቀበል ለእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት አንድ እርከን በመቀነስ እርከን 34 ላይ አሳርፎታል፡፡ የቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድ ቤት አመልካች በእርከን 34 በተመለከተው ከፍተኛው ቅጣት በአስራ ስምንት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የወታደራዊ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን የቅጣት ውሳኔ አጽንቶታል፡፡

አመልካች ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን *መመሪያ* ቁጥር 2/2006 *መሠረት* በማድረግ የቅጣት ውሳኔውን አክብደው መወሰናቸው በተለይም *መመሪያው* ሊያዝልኝ የሚገቡ የማቅለያ ምክንያቶችን ውድቅ በማድረግ የሰጡቱት የቅጣት ውሳኔ ስህተት ስላለበት በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ በእኛ በኩል አመልካች ባቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ

(ሀ) የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያወጣቸው *መመሪያ* ቁጥር 1/2002 እና *መመሪያ* ቁጥር 2/2006 አሁን ባሉበት ሁኔታ ለወታደራዊ ወንጀሎች ተፈፃሚ ማድረጉ የወንጀል ህጉንና የቅጣት አወሳሰን *መሠረታዊ* ዓላማ ሊያሳጣ የሚችል ነው ወይስ አይደለም?

(ለ) የቅጣት አወሳሰን *መመሪያዎቹ* አሁን ባሉበት ሁኔታ በወታደራዊ ወንጀሎች ላይ ተፈፃሚ ማድረግ ምን ውጤት ይኖረዋል?

(ሐ) ለወታደራዊ ወንጀሎች *መሠረታዊ* ባህሪ በወንጀሎች የሚፈፀሙበትን ሁኔታ ጊዜና ወንጀሎቹ የሚፈፅሙበትን ምክንያት ያስከተሉትን ወይም ሊያስከትል የሚችሉትን ጉዳት ያገናዘበ የወታደራዊ የቅጣት አወሳሰን *መመሪያ* የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ማውጣት ይገባዋል ወይስ አይገባውም ? *መመሪያ* ሊወጣ ይገባል ከተባለ *መመሪያው* እስከሚወጣ ወታደራዊ

ወንጀሎችን የመዳኘት ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤት የቅጣት ውሳኔ የሚሰጡት በምን ሁኔታ ነው የሚሉትን የህግ ጭብጦች መመርመርና ማየት አስፈላጊ ሆኖ አግንተነዋል፡፡

10. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወንጀል ህጉና በሌሎች ህጎች የወንጀል ቅጣት ህግ አውጭው የደነገገባቸው ወንጀሎች በመፈፀሙ ሰዎች ላይ ፍርድ ቤቶች የሚወስኑትን የቅጣት ውሳኔ ትክክለኛነትና አንድ ወጥነት ለማረጋገጥ እንዲቻል የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ እንደሚያወጣ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 88 ንዑስ አንቀጽ 4 "የቅጣት አወሳሰን ትክክለኛነትና አንድ ወጥነት ለማረጋገጥ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ manual ይወጣል በማለት በግልጽ የደነገገ ሲሆን የወንጀል ህጉ አንቀጽ 88 ንዑስ አንቀጽ 4 የእንግሊዚኛው ቅጅ `in order to insure correctness and uniformly of sentencing the federal supreme court show issue manual relating sentencing በማለት ደንግጓል፡፡

11. ይህም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ የማውጣት ስልጣን ከህግ አውጭው በግልጽ ድንጋጌ የተሰጠው በመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወታደራዊ ወንጀሎች ላይ ቅጣት ስለሚወሰንበት ሁኔታና አሠራር የቅጣን ማክበጃና ማቅለያ ሁኔታዎች ደረጃ አመጣጥ ስርዓትና የቅጣት እርከንና ሬንጅ የሚደነግግ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ለወታደራዊ ወንጀሎች በቂ ዕውቀትን ክህሎት ካለቸው ወታደራዊ ባስልጣናትና ባለሙያዎች ጋር በመመካከር አውጥቶ ስራ ላይ እንዲውል የማድረግ ስልጣን ያለው መሆኑን የሚያሳይ ነው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወንጀል ህግ አንቀጽ 88 ንዑስ አንቀጽ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ለወታደራዊ ወንጀሎች የሚያገለግል የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ማውጣት የሚችል መሆኑ የሚያከራክር ነጥብ አይደለም፡፡ አከራካሪ የሚሆነው የፌዴራል ፍርድ ቤት በወንጀል ህግ አንቀፅ 88 ንዑስ አንቀጽ 4 የተሰጠውን መሠረት በማድረግ የወጣውን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 እና መመሪያ ቁጥር 2/2006 በወታደራዊ ወንጀሎች ላይ ቅጣት ለመወሰን ጥቅም ላይ ቢውሉ የህግን መሠረታዊ ዓላማ ለማሰካት ያስችላሉ ወይስ አያስችሉም የሚለው ነው

12 የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አውጥቶ ስራ እንደውሉ ያደረጋቸው መመሪያ ቁጥር 1/2002 እና መመሪያ ቁጥር 2/2006 በመመሪያው ደረጃ ያልወጣላቸው ወንጀሎች ደረጃ ለማውጣት የሚያገለግሉ ጠቅላላ ይዘት ያላቸው ደንቦችንና በመመሪያዎች ደረጃ የወጣላቸውን ውስን የወንጀል አይነቶች ላይ ፍርድ ቤቶች ቅጣት ሲወስን ሊከተሉት የሚገባውን ስርዓት

የሚደነግግ ይዘት ያላቸው ናቸው መመሪያዎቹ የወጡት በወንጀል ህጉና በሌሎች የወንጀል ቅጣት በሚደነግጉ የህግ ማዕቀፎችን በመተላለፍ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ደረጃ አወጣጥ የቅጣት እርከን የቅጣት ማቅላይ ምክንያትና የቅጣን ማክበጃ ምክንያቶች አያያዝ ጠቅላላ በሆነ መንገድ ለመመዘንና የቅጣት አወሳሰን ስርዓቱን ለመዘርጋት ነው።

13. የወጡት መመሪያዎች በአገሪቱ ውስጥ የሚፈፀሙ ሁሉም አይነት ወንጀሎች ላይ ተፈፃሚ እንዲሆነው የተቀረጸ በመሆናቸው የአገር መከላከያ ሰራዊት ስኬታማነት ጥብቅ የስነ ስርዓትና የዲስፕሊን ልቅና ለማረጋገጥ ታልመውና በወታደራዊ አገልግሎት ሒደት ወታደሮችና የጦር መኮንኖች እንደፈፅም በህጉና አግባብነት ባለው አካል የታዘዙበትን ባለመፈፀሙ ወይም እንዳይፈፅም የተከለከለውን ተግባር ፈፅሞ በመገናኘታቸው ወታደሮች በህጉ ኃላፊ ናቸው የተባሉ ሌሎች ሰዎች በወንጀል ተጠያቂ የሆኑባቸውን ወታደራዊ ወንጀሎችና ወታደራዊ ወንጀሎቹ ዝርዝር ይዘትና ወንጀሎች የሚያስከትሉትን ቅጣት በልዩ ሁኔታ ህግ አውጭው በወንጀል ህጉ በክፍል ሶስት ከአንቀጽ 293 እስከ አንቀጽ 339 በዝርዝር ደንግጓል።

14. እነዚህ ህግ አውጭው በልዩ ሁኔታ የደነገጋቸው የወታደራዊ ወንጀሎች ድንጋጌዎች ማናቸውም ወታደር ወይም የጦር መኮንን ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት የሚፈፅማቸው የወንጀል አይነቶች የወንጀሎቹን መሠረታዊ ይዘትና ባህሪያ በወንጀሎች ወታደሩ ወይም የጦር መኮንኑ የፈፀመበት ምክንያት ወንጀሎች በጦርነት ቀጠና ወይም በሰላም ቀጠና የተፈፀመ መሆኑን ወንጀሎቹ በጦርነት ቀጠና ወይም በሰላም ቀጠና የተፈፀመ መሆኑን ወንጀሎቹ የወገን ጦር በጦርነት ላይ እያለ ወይም በሰላማዊ ጊዜ የተፈፀመ መሆናቸውን ወንጀሉ በወገን ጦር ግዳጅ አፈፃፀም ላይ ያስከተለውን ጉዳት ወይም በሌላ መንገድ ባይታራምና ባይሸፈን ኖሮ በወገን ጦር ላይ ሊያስከትል ይችል የነበረውን ጉዳት በማመዛዘን ቅጣቱን አክብዶ ወይም አቅልሎ መወሰንን የሚጠይቁ ናቸው።

15 ይህም ወታደራዊ ወንጀሎች በመሠረታዊ ይዘታቸው ተመሣሣይ ቢሆንም በባህሪያቸው ተለዋዋጭነት ያላቸውና እንደ ወንጀሎች አፈፃፀም ባህሪና ሁኔታ እየመዘነ የተለያየ መጠን ያላቸውን የወንጀል ቅጣቶችን መወሰን የሚጠይቁና ይህንንም ለማድረግ እንድችሉ ለወታደራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች ሰፊ ፈቀደ ስልጣን መስጠትን የሚጠይቁ ናቸው። ይህም ማለት ተመሳሳይ ቁጥር ያለው ጥይት ወይም መሣሪያ እንደጣሩ ወይም እንዲባክን በማድረግ ወንጀል የፈፀመ አቻ ማዕረግ ያላቸው የጦር መኮንኖች እንደጠሩ ወይም እንዲባክን ያደረጉት ንብረት ዋጋ እኩልና ተመጣጣኝ ቢሆኑም ወንጀሉን በፈፀሙት ምክንያት ሁኔታ በመለያያቱ ምክንያት ብቻ

የተለያያ የወንጀል ቅጣት ሊጣልባቸው የሚችል መሆኑን የሚያመለክት ነው። ይህም ማለት አንደኛ የጦር መኮንን ጥይትና መሣሪያ የማባከን ወንጀል የፈፀመው በቁጥጥርና ክትትል ችግር ወይም የወገን ጦር እንደጎዳ አስቦ አለመሆኑና ከጠላት ጦር ጋር ምንም አይነት ሚስጥራዊ ግንኙነት ያሌለው መሆኑ ቢረጋገጥና ተመሣሣይ ወንጀል የፈፀመው አቻ ባለማዕረግ መኮንኑ ጥይቱ ወይም መሣሪያው እንደጠፉ ያደረገው የወገን ጦር የትጥቅ ችግር እንዲገጥመውና ለጠላት ጥቃት ተጋላጭ አድርጎ ለመቆየት በማሰብ ከጠላት ጋር ሚስጥራዊ ግንኙነት በማድረግና የወገን ጦር በቂ ጥይትና መሣሪያ እንዳይደርሳውና ጉዳት እንዲደርስበት በማሰብ ይህንንም ሆንብሎና አቅዶ የፈጸመው መሆኑ ቢረጋገጥ የቅጣት ውሳኔ ወጥነት ለማረጋገጥ ሲባል በሁለቱ አቻ ማዕረግ ባለቸው የጦር መኮንኖች ላይ ሊወሰን የሚገባው እኩልና አንድ አይነት ቅጣት ሊሆን አይገባም። ከዚህ አንፃር የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አውጥቶ ስራ ላይ የዋለቸው የቅጣት አወሳሰን መመሪያዎች፣ ወንጀል የሰሩትን የጦር መኮንኖች ማዕረግ፣ ጥፋተኛ የተባለበትን የህግ ድንጋጌ፣ በወንጀል ድርጊት የጠፋውን የመንግስት ሀብት መጠን በጥቅሉ በማየት የወንጀል ደረጃ እንዲወጣና የማቅሊያና ማክበጃ ሁኔታዎች ታይተው ያለውን የወንጀል ቅጣት እርከን መሰረት በማድረግ ቅጣት እንዲወሰን የሚደነገጉ በመሆናቸው ከላይ የገለጽናቸውን የወታደራዊ ወንጀሎች አፈፃጸም ስልት ልዩ ባህሪ፣ ምክንያትና ሌሎች ሁኔታዎችን በዝርዝር መርምሮና መዝኖ ቅጣት ለመወሰን በሚያገለግሉበት አግባብ ታስቦባቸው የተቀረጹ አይደሉም።

16. በወታደራዊ ወንጀሎች የቅጣት ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት፣ ሁለት ተመሳሳይ የሆነ ወንጀል በፈጸሙ ወታደሮች ወይም የጦር መኮንኖች ላይ የተለያየና ከፍተኛ ልዩነት ያላቸው የቅጣት ውሳኔዎች እንዲሰጡ የወታደራዊ ፍርድ ቤት ዳኞችን የሚያስገድዷቸው በርካታ ክስተቶችና ነባራዊ ነገሮች ያጋጥማሉ። ይህም ማለት ከፍያለ ገንዘብ የሚያወጣ ስንቅ የመስረቅ ወንጀል በሰላም ቀጣና ውስጥ የፈጸምን አንድ ወታደርና የወገን ጦር በአስቸጋሪ ሁኔታና በስንቅ እጥረት ውስጥ በሚገኝበት ሁኔታ ዋጋው ዝቅተኛ የሆነ ስንቅ የመስረቅ ወንጀል የፈጸመ ወታደር ጥፋተኛነታቸው ከተረጋገጠ በኃላ የወገን ጠሪ በአስቸጋሪ ሁኔታና በስንቅ እጥረት ላይ በሚገኝበት ጊዜ፣ ከነበረው ውስን ስንቅ ዝቅተኛ መጠን ያለውን በሰረቀው የወገን ጦር ላይ ከፍተኛ ችግር ወታደር ላይ ከፍተኛ ችግር በፈጠረው ላይ ከፍ ባለቅጣት እንዲቀጣ ውሳኔ መስጠት የሚያስገድድ ሁኔታዎች የመኖሩ መሆኑን ከግምት ውስጥ የሚያስገባ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ካልወጣ በስተቀር አሁን ስራ ላይ ባሉት መመሪያዎች ይህንን መሰረታዊ አላማ ለማሳካት የሚቻል አይደለም።

17. ከላይ የገለጽናቸው ሁኔታዎች የሚያሳዩት ወታደራዊ ወንጀሎቹን ለመዳኘት ላይ የሚገኙ ወታደራዊ ፍርድ ቤቶች ጥፋተኛው የፈጸመውን ወንጀል ይዘት፣ የወንጀል አፈፃጸም ስልትና የወንጀሉን ባህሪ፣ ወንጀሉን የፈጸመበትን ጊዜ ወንጀሉን የፈጸመበት ስፍራ ወንጀሉን ሁኔታ፣ ወንጀሉን ለመፈጸም ያነሳሳውን ምክንያት የፈጸመው ወንጀል በወገን ጦር ላይ ያስከተለው ጉዳት ወይም ክትትል የነበረውን ጉዳት በክርክር በመመርመርና በመመዘን ቅጣቱን አክብደው ወይም አቅልለው ለመወሰን የሚያስችል ሰፊ ፈቃድ ስልጣን ካልተሰጣቸው የወንጀል ህጉ ወታደራዊ ወንጀሎቹን በልዩ ሁኔታ ያደረገበትንና መሰረታዊ ዓላማና ወንጀሎች ሲፈጽም ጥፋተኛውም ሆነ ሌላው የመከላከያ ኃይል ተሰማርተውበት ከነበረው ወታደራዊ ግዳጅ ልዩ ባህሪና አስቸጋሪ ሁኔታ ጋር በሚጣጣም መንገድ የቅጣት ውሳኔ ለመስጠት አይችሉም።

18. በመሆኑም ስለወታደራዊ አገልግሎትና ወታደራዊ አገልግሎትና ወታደራዊ ግዳጅ አፈፃጸም ሂደት ወንጀሎች ፈጽመው ስለሚችልበት ምክንያት የወንጀል አፈፃጸም ባህሪ፣ የወታደራዊ ወንጀሎች አፈፃጸም ስልት፣ ወንጀሉ የተፈጸመበት ጊዜና ስፍራ እንደዚሁም ሁኔታ እንዲሁም የተፈጸመው ወይም የተሞከረው ወንጀል በመከላያ ሀይሉ ወኔ፣ ወይም ሞራን/ብቃት ላይ ያስከተለውን ጉዳት ወይም ሊያስከትል ይችል የነበረውን ጉዳት ግንዛቤ ውስጥ የሚያስገባ በዘርፍ በዕውቀትና ክህሎት እንደዚሁም ያዳበረ ልምድ ያላቸው ወታደራዊ መኮንኖችና ባለሙያዎች ተሳታፊ በሆኑበትና በዝርዝር የተጠና ጥናትን መሰረት በማድረግ ራሱን የቻለ ልዩ የወታደራዊ ወንጀሎች የቅጣት አወሳሰን መመሪያን ሊወጣ ይገባዋል።

19. የቅጣት አወሳሰን መመሪያ በማውጣት ለረዥም ጊዜ ስራ ላይ በማዋል የረዥም ጊዜ ተሞክሮና ያካበተ ልምድ ያላቸው እንደሰሜን አሜርካ መንግስታት ህብረት /usA/ ያሉ አገኖች ሌሎች ወንጀሎችና ሲቭሎች ለሚፈጽሟቸው ወንጀሎች ላይ ቅጣት ለመወሰን ታስበው የወጡ የቅጣት አወሳሰን መመሪያዎች ባያደራጀውና ባያካፍሉ የተቋመ ፍርድ ቤቶች እንዲፈጽሙ ግዴታ የማይጥሉ መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል። ከዚህ አንፃር ሲታይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያወጣቸው የቅጣት አወሳሰን መመሪያዎች የወንጀል ህጉ በልዩ ሁኔታ ከተዘረዘሩት ወታደራዊ ወንጀሎች ልዩ ባህሪ ከግንዛቤ ውስጥ ያላስገባና፣ የመመሪያዎች የግቦች ጠቅላላ የሆነ ይዘት ያላቸው፣ በመመሪያዎቹ ለወታደራዊ ወንጀሎች ደረጃ ያልወጣላቸው አሁን ባሉበት አቀራረጽና ይዘታቸው ወታደራዊ ፍርድ ቤቶች በእለት ከእለት ስራቸው ተፈፃ እንዲያደርጓቸው በአስገዳጅነት ቢቀመጡ የወንጀል ህጉ ወታደራዊ ወንጀሎቹን በክፍል ሶስት በልዩ ሁኔታ የመረመረበትንና የደነገገበትን መሰረታዊ ዓላማ ለማሳካት የማይችሉና ዳኞች ወታደሩ ወይም

የጦር መኮነኑ ወንጀሉን ሲፈጽም ተሰጥቶት የነበረውን ግዳጅ፣ ወንጀሉ የተፈጸመበትን ሁኔታና ሌሎች ከላይ ባስፈጸመው በሰፊው የዘረዘርናቸውን ልዩ ሁኔታዎች በማገናዘብና ለእያንዳንዱ ልዩ ሁኔታ በመመዘን ቅጣት አቅለው ወይም አክብደው እንዲወስኑ በወንጀል ህጉና በእያንዳንዱ ወታደራዊ ወንጀል በሚደነግግ ድንጋጌ የተሰጣቸውን ሰፊ ፈቅደ ስልጣን የሚያሳጣ ስለመሆን ይሆናል፡፡

20. ከላይ በዝርዝር የገለጽናቸውን መሰረታዊ ሁኔታዎች መነሻ በማድረግ ቀዳማዊ ወታደራዊ ፍርድ ቤት ለዚህ ክርክር መነሻ በሆነው ጉዳይ ላይ፣ ለአመልካች ላይ ቅጣት የወሰነው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 በመከተል፣ አመልካች የፈጸመው የወንጀል ህግ አንቀጽ 306/1/ እና የወንጀል ህግ አንቀጽ 306/3/ በቅጣት አወሳሰን በመመሪያው ደረጃ ያልወጣላቸው በመሆኑ ደረጃ በማውጣትና ለእያንዳንዱ ማክበጃ ምክንያት አንድ እርከን ከፍ በማድረግ ለእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት አንድ እርከን በመቀነስ እንደሆነ ተረድተናል፡፡ ይህም አመልካች ወንጀሉን የፈጸመበትን ሁኔታ፣ የአመልካችን ተሰማርቶበት የነበረውን ወታደራዊ ግዳጅ፣ በግዳጅ አፈፃጸሙ ያስመዘገባቸውን ድሎችና ወንጀሉ ያስከተለውን ጉዳት አጠቃላይ የወታደራዊ ወንጀል ባህሪን በዝርዝር ለማየት የማያስችል በመሆኑ ቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚ የወታደራዊ ፍርድ ቤት፣የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት በማድረግ በአመልካች ላይ የቅጣት ውሳኔ መወሰናቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

21 በአመልካች ላይ የቅጣት መወሰን ያለበት የቅጣት አወሳሰን መመሪያውን መሰረት በማድረግ ሳይሆን ከቅጣት አወሳሰን መመሪያው ውጭ የወንጀል ህጉን የቅጣት አወሳሰን መርሆችና የወንጀል ህግ አንቀጽ 320 የእያንዳንዱን ወታደራዊ ወንጀል መሰረታዊ ባህሪ፣ ወንጀሉ የተፈጸመው በሰላም ወይም በጦርነት ጊዜ መሆኑና ወታደራዊ ወንጀሉ ያደረሰውን ጉዳትም ሊያደርስ የነበረውን ጉዳት በአንድ በኩል፣ ጥፋተኛው ከዚያ በፊት የነበረው ባህሪ፣ በግዳጅ አፈፃጸም ሂደት የፈጸመው ጀብዱ፣ ወታደራዊ ግዳጅ በሚፈጸምበት ጊዜ የደረሰበት ጉዳትና የከፈለውን መስዋዕትነት፣ የቤተሰብ ሁኔታውን ሌሎች በወታደራዊ አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት በቅጣት ለማቅለል የሚያስችሉ ምክንያቶችን በሌላ በኩል በማመዛዘን መሆን ይኖርበታል፡፡

22. ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች ለሌሎች ወታደሮችና ዝቅተኛ መኮንኖች አርዓያ መሆን ሲገባው በርካታ መጠን ያለው ጥይት በኃላፊነት ወሰደ እንደጠፋ ማድረጉ፣ አመልካች ለተደራራቢ የወንጀል ድርጊት የፈጸመ መሆኑ በወንጀል ህግ አንቀጽ 320 መሰረት ቅጣት

አክብዶ ለመወሰን የሚያስችሉ ምክንያቶች መሆናቸውን ተገንዝበናል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ወንጀሉን የፈጸመው የወገን ጦር በጦርነት ላይ ባለበት ጊዜ ሳይሆን በሰላማዊ ሁኔታ እያለ በመሆኑ፣ አመልካች እድሜ ልኩን ወታደራዊ ግዳጅ በቆራጥነት ሲፈጽም የኖረና ለዚህም የተለያዩ ጊዜዎች የተለያዩ ሽልማቶች የተሸለሙ መሆኑን፣ አመልካች በተለያዩ አውደ ውጊያዎች ወታደራዊ ግዴታውን በቆራጥነት ሲፈጸም ከአምስት ጊዜ በላይ የአካል የቆሰለ መሆኑን፣ አመልካች ከዚህ በፊት ወንጀል ፈጽሞ የማያውቅና ቤተሰብ አስተዳደሪ መሆኑ ቅጣቱን አቅልሎ ለመወሰን የሚያስችሉ ምክንያቶች መሆናቸውን በማገናዘብ በወንጀል ህግ አንቀጽ 88 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት የአመልካችን ግላዊ ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት አመልካች ከጥፋቱ ሊያርመውና ሊያስተምረው በሚችል በአስር አመት ጽኑ እስራ ሊቀጣ ይገባል በማለት የቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድ ቤትና የወታደራዊ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰጡትን የጥፋኝነት ውሳኔ በማጽናት የቅጣቱን ውሳኔ ብቻ በወንጀል ስነ-ስርዓት ህግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2/ለ/2/ መሰረት በማሻሻል ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

የቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድ ቤት የወንጀል መዝገብ ቁጥር 268/07 የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔና የወታደራዊ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥ 234/07 የሰጠው የጥፋኝነት ውሳኔ በማጽናት የቅጣት ውሳኔውን በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2/ለ/2 መሰረት በማሻሻል ወስነናል፡፡

ከወታደራዊ ወንሎች ባህሪያት ጋር በሚጣጣም መንገድ ተቀርጾው ካልወጡ በስተቀር አሁን በስራ ላይ ያሉት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 እና መመሪያ ቁጥር 2/2006 በአስገዳጅነት ወታደራዊ ፍርድ ቤቶች ወታደራዊ ወንጀሎች ላይ ቅጣት ሲወስኑ ተፈፃሚነት ሊኖራቸው አይገባም በማለት ወስነናል፡፡

አመልካች በዚህ ጉዳይ ተጠርጥሮ እጁ ከተያዘበት የካቲት 14 ቀን 2007 ዓ/ም ጀምሮ በሚታሰብ አስር አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስነናል፡፡

የቅጣት ውሳኔውን እንዲያስፈጽም ለክፍሉ ማረሚያ ቤት ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ **የሰ/መ/ቁጥር 219862**

ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት **ግንቦት 26 ቀን 2014ዓ/ም**

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ተድላ ክፍሌ ኦሻ ፡- አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ከኦሮሚያ ጠቅላይ ዐ/ሕግ ዳኘ አማረ ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 391980 ጥር 4ቀን 2014ዓ/ም በዋለው ችሎት አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም ሲል መዝጋቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም ተብሎ እንዲታረም አመልካች በመጠየቁ ስለጠየቀ ነው፡፡

ጉዳዩ በሰው አካል ላይ ከባድ ጉዳት ማድረስ ወንጀልን በሚመለከት የቀረበ ክርክር ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አርሲ ዞን የዲገሉና ጢጆ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ ሐምሌ 6ቀን 2011ዓ/ም በተባፈ ክሱ የአሁን አመልካችን አንደኛ ተከሣሽ በማድረግ እንዲሁም አቶ ደጀኔ ከበደን ሁለተኛ ተከሣሽ በማድረግ ወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1)(ሀ) እና 555(ለ) የሚደነግገውን በመተላለፍ በጋራ ሆነው በሰው አካል ላይ ጉዳት ለማደረስ አስበው ሚያዚ 19ቀን 2013ዓ/ም ከምሽቱ 2፡00 አረቢ ቀበሌ ልዩ ቦታው ቱሉ ገራ

ከሚባለው ስፍራ የግል ተበዳይ ሐብታሙ ሙላቱን አመልካች በከዘራ የግራ ጭንቅላቱ ላይ መቶ በመፈንከት ጥድ ላይ ሲጥለው የቀኝ ዓይኑ አካባቢ አጥንት ወደ ውስጥ በመስበር ጉዳት መድረሱን ሁለተኛው ተከሣሽ በበኩሉ በወደቀበት በዱላ ቀኝ ትክሻውን በመምታት ከበድ የአካል ጉዳት መድረስ ወንጀል ፈጽሟል የሚል ክስ አቅርበዋል፡፡

አመልካች ክዶ የተከሣሽነት ቃል መስጠቱን ተከትሎ የተጠሪ ምስክሮችና በተበዳይ ላይ ደረሰ የተባለውን ጉዳት የሚያረጋግጥ የሕክምና ማስረጃ እንዲሁም ማስረጃው ከተደመጠ በኋላ በግል ተበዳይ ላይ የደረሰው የአካል ጉዳት ምን ደረጃ ላይ እንዳለ ተመርምሮ እንዲቀርብ የሰጠውን ትዕዛዝ ተከትሎ የቀረበው የምርምራ ውጤት በመመዘን በግል ተበዳይ ላይ የደረሰው ጉዳት የዳነ መሆኑ እና ቋሚ ጉዳት አለመሆኑ ተረጋግጧል በሚል አመልካቹ ተከሠሠበትን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 555(ለ) ወደ 556(2) በመቀየር እንዲከላከል አዟል፡፡ አመልካች ሶስት መከላከያ ምስክሮች አቅርቧል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካችንና ሁለተኛ ተከሣሽ የነበረው የተጠሪን ክስና ማስረጃ አላስተባበሉም ሲል በወንጀል ሕግ አንቀጽ 556(2) ጥፋተኛ ብሎ ሁለቱም እያንዳንዳቸው በስድስት ወር ቀላል እስራት እንዲቀጣ ወስኖበታል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር የተሰኘው ተጠሪ የይግባኝ አቤቱታውን ለአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ የግራ ቀኙ ክርክሩ ከተመረመረ በኋላ የስር ፍርድ ቤት በግል ተበዳይ ላይ የደረሰው የአጥንት ስብራት ድኗል በሚል አንቀውን መቀየሩ ተገቢ አይደለም ምክንያቱም ጉዳቱ ሊመዘን የሚገባው ጉዳቱ በደረሰበት ጊዜ እንጅ ከጉዳጡ በኋላ የሚመጣውን ውጤት መሰረት አድርጎ ሊሆን አይገባም ሲል ውሣኔውን አሻሽሎ አመልካችን በወንጀል ሕግ አንቀፅ 555(ለ) ስር ጥፋተኛ ብሎ በሁለት ዓመት ከዘጠኝ ወር እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር የተሰኘው አመልካች የይግባኝ እና የሰበር አቤቱታውን በየደረጃው ለሚገኙት የክልሉ ፍርድ ቤቶች ያቀረበ ቢሆንም ስላልተለወጠ የያዝነውን የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ አመልካች ጥር 16ቀን 2014ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታው አንድ ሰው በሌላ ሰው አካል ላይ ጉዳት አድርሷል በሚል ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 555፣556 እና 560 መካከል በየትኛው እንደሚከሰስ የሚወሰነው የጉዳቱን መጠን መሰረት አድርጎ እንደሆነ በመደንገጉ የወረዳው ፍርድ ቤት ይህን ታሳቢ በማድረግ አንቀፁን ከ555 ወደ 556 መቀየሩ ተገቢ ሆኖ ሣለ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተገቢ ባልሆነ ምክንያት መሻሩ፣ አንቀፁ መቀየሩ ተገቢ ነው ቢባል እንኳ በግል ተበዳይ ላይ የደረሰው የአጥንት መሰበር በአመልካች ድርጊት ሣይሆን ሲወድቅ በመታው

እንጨት ምክንያት ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት ተረጋጠበት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 555(ለ) ጥፋተኛ ተብሎ በዚሁ መሰረት ቅጣት መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው ተብሎ እንዲታረምለት ጠይቋል።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በስር የአርሲ ዞን የዲገሉኛ ጦጆ ወረዳ ፍርድ ቤት የግል ተበዳይ ላይ የደረሰው የአጥንት ስብራት የዳነ መሆኑ ተረጋግጧል በሚል 0/ህግን ክስ ድንጋጌ ወደ 556(2) ቀይሮ የጥፋተንነት ውሣኔ ከሰጠ በኋላ ጉዳዩን በይግባኝ የያው የፍርድ ቤት ወደ 555(ለ) በመመለስ ጥፋተኛ በሚል የወሰነበትን አግባብት ከወንጀል ሕ አንቀጽ 555 እና ከሰበር መዝገብ ቁጥር 156221 ከተሰጠው ትርጉም እንዲመረመር ለዚህ ችሎት ቀርቧል።

ተጠሪ በበኩሉ ግንቦት 26ቀን 2014ዓ/ም በተፃፈ መልሱ በጥቅሉ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ አንቀፁን ወደ 555 ቀይሮ አመልካችን ጥፋተኛ ብሎ ቅጣት መወሰኑ ተገቢ ነው የሚልበትን ምክንያት በመዘርዘር እንዲፀናለት ተከራክሯል። አመልካች የሰበር አቤቱታውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርቦ የግራ ቀኙ ክርክር ተጠናቋል።

ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከትነው የጉዳዩን አመጣጥና የግራ ቀኙ ክርክር ሲሆን ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ

አመልካች በስር ፍርድ ቤት ጥፋተኛ የተባለበትን ድንጋጌ ከ556 ወደ 555 በመቀየር ቅጣት መወሰኑ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን በሚመለከት ውሣኔ ለመስጠት የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱን ውሣኔ ከግራ ቀኙ ክርክር እና ጉዳዩ አግባብት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ተመርምሯል።

እንደተመረመረው ከይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ ጀምሮ በየደረጃው በሚገኙት የክልሉ ፍርድ ቤቶችና በዚህ ችሎት ጭምር አከራካሪ የሆነው ጉዳይ በግል ተበዳይ የቅንድብ የአጥንት ስብራት በመዳኑ አመልካች ጥፋተኛ መባል የሚገባው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 555 ነው ወይስ 556 የሚለው ጉዳይ ነው።

በመሰረቱ በአንድ የወንጀል ድርጊት የደረሰው የአካል ጉዳት ከባድ ነው ወይስ ቀላል ነው ለሚለው አከራካሪ ነጥብ መልስ የሚሰጠው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 555 ድንጋጌ ነው። በአንድ የወንጀል ድርጊት ምክንያት በሰዎች አካል ላይ ጉዳት ከደረሰና በደረሰው ጉዳት ምክንያት የተጎጅውን ሕይወት የሚያሰጋ ከሆነ ወይም ጉዳቱ በሰውነቱም ሆነ በአእምሮው ላይ ለዘወትር ጠንቅ የሚያተርፍ ከሆነ ወይም ከአካሉ ወይም አስፈላጊ ከሆኑ ብለቶች መካከል አንዱ ወይም

ከዚያ በላይ ሲጎድል፣ በጉዳቱ ምክንያት አስፈላጊው ብልት አገልግሎት እንዳሰጥ ሲሆን ወይም በሚያሰቅቅና ጉልህ ሆኖ በሚታይ ሁኔታ የተጎጅው መልክ ሲበላሽ፤ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ሌላ ከባድ የሆነ ጉዳትን ወይም በሽታን የሚያስከትል ጉዳት ሲደርሰበት እንደሆነ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 555 ይደነግጋል፡፡

በቀረበልን ጉዳይ የግል ተበዳይ በአመልካች ድብደባ የተፈፀመበት መሆኑና በአመልካችና በሁለተኛ ተከሳሽ ድብደባ ምክንያት የግል ተበዳይ እንጨት ላይ በመውደቁ የቅንድቡ አጥንት ተሰብሮ የነበረ መሆኑም በበቂ ማስረጃ ተረጋግጦ በመከላከያ ማስረጃ ያልተስተባበለ ፍሬ ነገር ነው፡፡ በሌላ በኩል በግል ተበዳይ ላይ የደረሰው የቅንድብ አጥንት ስብራት ከጊዜ በኋላ መዳኑ በሕክምና ማስረጃ የተረጋገጠ ነው፡፡ በመሆኑም ቀደም አንድ ሰው በሌላ ሰው አካል ላይ በፈፀመው የድብደባ ድርጊት የአጥንት ስብራት መድረሱ ቢረጋገጥና ቆይቶ ስብራቱ መዳኑ ቢረጋገጥ ጉዳያ የደረሰው ሰው ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው ቀላል የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ነው ወይስ በከባድ የሚለው ጉዳይ መልስ ማግኘት ይኖርበታል፡፡ ከዚህ ነጥብ ጋር በተያያዘ ይኸው ችሎት አንድ ያአካል ጉዳት ከባድ የአካል ጉዳት ነው የሚባለው የደረሰው ጉዳት ሊድን ወይም ሊጠገን የማይችል መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ ስለመሆኑ በመዝገብ ቁጥር 156521 ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

በዚህ መሰረት በግል ተበዳይ የደረሰው ስብራት መልሶ የዳነ መሆኑ በሕክምና ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ይሕ ስብራት በተጎጅው ላይ ዘላለማዊ የሆነ ጠንቅ የሚያተርፍ ስለመሆኑ ወይም የተሰበረው የአካል ክፍል አገልግሎት እንዳይሰጥ ስለማድረጉ ወይም የተሰበረውን የአካል ክፍል በሚያሰቅቅና ጉልሕ ሆኖ በሚታይ መልኩ መልኩን ያበላሸ ስለመሆኑ ክርክር አልቀረበም በማስረጃም አልተረጋገጠም፡፡

በመሆኑም አንድ ሰው በፈፀመው በአካል ላይ ጉዳት ወንጀል የተጎጅው አጥንት መሰበሩ የተረጋገጠ ቢሆንም ስብራቱ መዳኑ በባለሙያ ከተረጋጠና በስብራቱ ምክንያት ጉዳቱ በደረሰበት ሰው በሰውነቱም ሆነ በአእምሮው ላይ ለዘወትር ጠንቅ የሚያተርፍ ስለመሆኑ ወይም ከአካሉ ወይም አስፈላጊ ከሆኑ ብሶቶች መካከል አንዱ ወይም ከዚያ በላይ መጉደሉ፣ በጉዳቱ ምክንያት አስፈላጊው ብልት አገልግሎት አለመስጠቱ ወይም በሚያሰቅቅና ጉልህ ሆኖ በሚታይ ሁኔታ የተጎጅው መልክ መበላሸቱ፤ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ሌላ ከባድ የሆነ ጉዳትን ወይም በሽታን የሚያስከትል መሆኑ ክልተረጋገጠ በስተቀር የወንጀል ሕግ አንቀጽ 555 ተላልፎ ከባድ የአካል ጉዳት ፈፅሟል ተብሎ ሊቀጣ አይገባም፡፡ ስለዚህ የአመልካች ድርጊት የሚሸፈነው የስር

ፍርድ ቤቱ እንደወሰነው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 556(2) ድንጋጌ ስር እንጅ በወንጀል ህግ አንቀጽ 555(ለ) ስላልሆነ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ውሣኔ

የአሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እና ይግባኝ ሰሚ ችሎቱች እንደቅደም ተከተላቸው በመዝገብ ቁጥር 391980 ጥር 4ቀን 2014 ዓ/ም በመዝገብ ቁጥር 384767 ታሕሳስ 6ቀን 2014ዓ/ም የሰጧቸው ትዕዛዛት፤ የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዘገብ ቁጥር 98 829 ሕዳር 17ቀን 2014ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2)(ለ)(2) መሰረት ተሽሯል፡፡

በአርሲ ዞን የዲገሉና ጦጀ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዘገብ ቁጥር 40897 ጥቅምት 9ቀን 2014ዓ/ም የሰጠው የጥፋተኝትና የቅጣት ውሣኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2)(ለ)(2) መሰረት ፀንቷል፡፡

ትዕዛዝ

በዚህ ውሣኔ መሰረት በስር ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካች እንዲቀጣ ከተወሰነው የእስራት ቅጣት ያልተፈፀመ ካለ የስር ወረዳ ፍርድ ቤቱ ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ታዟል፤ የውሣኔው ቅጅ ይላክለት፡፡

መዝገቡ እልባት ያገኘ በመሆኑ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

የሰ.መ.ቁ 231232

የካቲት 30 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

ሐብታሙ እርቅ ይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካች፡- አቶ ሳምሶን ተሾመ - ጠበቃ አድነው አቡሼ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፍትሕ ሚኒስቴር ዓቃቤሕግ - አልቀረቡም

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሐምሌ 14 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 279834 መጋቢት 20 ቀን 2014 ዓ.ም በአመልካች ላይ ያስተላለፈው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና መጋቢት 30 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 225052 ሠኔ 17 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

ጉዳዩ ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች እና በስር 2ኛ ተከሳሽ ላይ ያቀረበው ክስ ይዘት በአጭሩ፡- ተከሳሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 692(1) ድንጋጌን በመተላለፍ የማይገባ ብልጽግና ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ በቀን 24/11/2013 ዓ.ም በግምት ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ሲሆን በአራዳ ክፍለከተማ ወረዳ 01 ልዩ ቦታው አምባሳደር አካባቢ የግል ተበዳይ ዘሪሁን ገረሱን አመልካች ኢንቨስትመንት አብረን እንሰራለን የላስቲክ ወንበሮች እና ባቄላ አሸገን ወደ ውጪ እንልካለን ዶላር እናባዛለን በማለት አሳሳች ነገር በመናገር 2ኛ ተከሳሽ ጥሬ ገንዘብ ብር 556,320 እና 3,500 የአሜሪካ ዶላር በኢትዮጲያ ሲመነዘር ብር 159,600 በአጠቃላይ ብር

715,920 የወሰዱበት በመሆኑ በዋና ወንጀል አድርጊነት ተካፋይ በመሆን በፈጸሙት የማታለል ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው።

ተከሳሾች ክሱ ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ መቃወሚያ አቅርበው ውድቅ የተደረገ ሲሆን የእምነት ክሕደት ቃላቸውን ሲጠየቁ ድርጊቱን አልፈጸምንም ብለው ክደው በመከራከራቸው ፍርድ ቤቱ የዓቃቤሕግን ማስረጃ ከሰማ በኋላ ክሱን እንዲከላከሉ ሲል ብይን ሰጥቷል። አመልካችም በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 143/2 መሠረት ቃሉን የሰጠ ሲሆን የመከላከያ ማስረጃውን አስቀርቦ አሰምቷል። ፍርድ ቤቱም በመቀጠል የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ በአመልካች የቀረበው መከላከያ ማስረጃ በዓቃቤሕግ በኩል የቀረበውን ማስረጃ ጥርጣሬ ላይ የሚጥል አይደለም በማለት በተከሰሰበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 692(1) ድንጋጌ መሠረት ጥፋተኛ በማለት ቅጣቱን አስልቶ በሁለት ዓመት ከሶስት ወር ጽኑ እሥራት እና በብር 6,000 / ስድስት ሺህ የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ሲል ወስኗል። አመልካች ቅጣቱ እንዲገደብ ያቀረበውን ጥያቄ በሚመለከት ደግሞ ከወንጀሉ አደገኝነት አኳያ አስተማሪነት ስለሌላው ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ አድርጎታል።

አመልካች ይህን ወሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ይግባኙ ተቀባይነት አላገኘም።

አመልካች ሐምሌ 14 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- አመልካች ገንዘቡን እንዳልተቀበልኩ ተረጋግጧል፤ ባንኮቹ በደረሳቸው ትዕዛዝ የግል ተበዳይ ምንም ዓይነት ዶላር እንዳላወጣ ለፍርድ ቤቱ አረጋግጠዋል፤ አመልካች የተከሰስኩት ባልተፈጸመ ወንጀል እና ባልፈጸምኩት ድርጊት ነው፤ አመልካችን ጥፋተኛ ለማስባል በተከሰስኩበት ሕግ እና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 23/2 ላይ የተቀመጠው የሕጉ መስፈርት አልተሟላም፤ በምክንያት እና ውጤት መካከልም ግንኙነት የለም፤ አመልካች ቅጣት ለመገደብ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ያሟላሁ በመሆኑ ቅጣቱ ሊገደብ ይገባ ነበር፤ ስለሆነም እነኚህ ሁኔታዎች ታልፈው በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ በስር ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ የተላለፈው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ አግባብነት ከማስረጃ ምዘና መርህ አንጻር እና ሌሎች ተያይዥ ነጥቦችን ለማጣራት የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል።

ተጠሪ ነሐሴ 30 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው መልስ ይዘት በአጭሩ፡- በስር ፍርድ ቤት የተፈጠረ የሕግ አተረጓጎም ስሕተት የለም፤ አመልካች የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈጸሙ በዓቃቤሕግ ማስረጃ በሚገባ ተረጋግጧል፤ አመልካች በክሱ የተጠቀሰውን ገንዘብ ራሱ ባይቀበልም ከተጠያቂነት ነጻ አያደርገውም፤ የዓቃቤሕግ ክስ አመልካች የኢንቨስትመንት ስራ እንሰራለን ወንበር እና ባቄላ አሸገን ወደ ውጪ እንልካለን ዶላር እናባዛለን በሚል የግል ተበዳይን ሲያታልል ሌላኘው ግብረአበሩ ገንዘቡን ተቀብሎ ተሰውሯል የሚል ነው፤ የግል ተበዳይ ገንዘቡን በሕገወጥ መንገድ ይዘዋል የሚባል ከሆነ በሌላ ራሱን በቻለ ሕግ የሚታይ እንጂ ገንዘቡ ከባንክ ስለመውጣቱ አልተረጋጠም የሚል መከራከሪያ ሊቀርብ አይገባም፤ የአመልካች ግብረአበር ገንዘቡን ከግል ተበዳይ ተቀብሎ የወሰደ በመሆኑ የግል ተበዳይ ላይ ጉዳት አልደረሰም ማለት አይቻልም፤ አመልካች ድርጊቱን የፈጸመው የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ነው፤ የግል ተበዳይም በአመልካች ድርጊት ምክንያት የራሳቸውን ጥቅም የሚጎዳ ድርጊት አድርገዋል፤ አመልካች ቅጣቱን ለማስገደብ የሚችሉ ቅድም ሁኔታዎች አሚልተው አላቀረቡም፤ ስለሆነም የገደብ ጥያቄው ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው የሚል ነው።

አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል።

የግራቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው። ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል።

ዓቃቤሕግ በስር ፍርድ ቤት ክስ ያቀረበው አመልካች እና የስር 2ኛ ተከሳሽ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተሳታፊ በመሆን የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 692(1) ድንጋጌን ተላልፈው የማይገባ ብልጽግና ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ በግል ተበዳይ ላይ የማታለል ወንጀል ፈጽመዋል በሚል ነው። በዚሁ ክስ ላይም የአመልካች ተሳትፎ ለግል ተበዳዩ ኢንቨስትመንት አብረን እንሰራለን የላስቲክ ወንበሮች እና ባቄላ አሸገን ወደ ውጪ እንልካለን ዶላር እናባዛለን በማለት አሳሳች ነገር በመንገር የግል ተባዳዩ ለስር 2ኛው ተከሳሽ በክሱ የተመለከተውን የገንዘብ መጠን እንዲሰጡ ማድረግ ስለመሆኑ በግልጽ ተጠቅሷል። ይህም የግል ተበዳዩ በአመልካች ድርጊት ምክንያት ገንዘቡን ሊሰጡ የቻሉ መሆኑን ወንጀሉ በአመልካች እና በስር 2ኛ ተከሳሽ ተሳትፎ የተፈጸመ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ስለሆነም አመልካች በክሱ የተገለጸውን ገንዘብ ስላልተቀበልኩ ጥፋተኛ ልባል አይገባም በማለት

የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም። በሌላ በኩል ዓቃቤሕግ አመልካች ዶላር እናባዛለን በማለት አሳሳች ነገር በመናገር የግል ተበዳዩ 3,500 የአሜሪካ ዶላር በኢትዮጲያ ሲመነዘር ብር 159,600 ለስር 2ኛ ተከሳሽ ሰጥተዋል በማለት የገለጸውን ፍሬነገር መሠረት በማድረግ አመልካች ጥፋተኛ የመባሉን አግባብነት እንደሚከተለው መርምረናል።

የወንጀል ሕግ አንቀጽ 692/1 ማንም ሰው የማይገባ ብልጽግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ አሳሳች የሆኑ ነገሮችን በመናገር የራሱን ማንነት ወይም ሁኔታ በመሰወር ወይም መግለጽ የሚገባውን ነገር በመደበቅ ወይም የሌላውን ሰው የተሳሳተ እምነት ወይም ግምት በመጠቀም በማድረግም ሆነ ባለማድረግ ሌላውን ሰው አታሎ የራሱን ወይም የሶስተኛ ወገንን የንብረት ጥቅም የሚጎዳ አድራጎት እንዲፈጽም ያደረገው እንደሆነ በድንጋጌው የተመለከተውን ቅጣት ይቀጣል በማለት ይደነግጋል። ከድንጋጌው ይዘት በግልጽ መገንዘብ እንደሚቻለው የማታለል ወንጀሉ የሚፈጸምበት ሰው የማታለል ተግባሩን የሚፈጽመው ሰው በፈጸመው የማታለል ተግባር ምክንያት የራሱን ወይም የሶስተኛ ወገንን የንብረት ጥቅም የሚጎዳ አድራጎት የሚፈጽም ከሆነ የማታለል ተግባሩን የፈጸመው ሰው ለድርጊቱ ተጠያቂ የሚሆን መሆኑን ነው። ከዚህ ውጪ የማታለል ድርጊቱ ተፈጽሞብኛል የሚለው ሰው አብሮ የወንጀሉ ፍሬ ተጠቃሚ ለመሆን የተስማማ ከሆነ የማታለል ተግባር ተፈጽሞብኛል ለማለት አይችልም።

በያዝነው ጉዳይ ዶላሩን በሚመለከት አመልካች ፈጸሙት የተባለው ተግባር ዶላር እናባዛለን በማለት የግል ተበዳዩ ዶላሩን ለስር 2ኛ ተከሳሽ እንዲሰጡ አድርገዋል የሚል ነው። ይህም የግል ተበዳዩ ዶላሩ ተባዝቶ ሲመጣ አብረው ከወንጀሉ ፍሬ ለመጠቀም ያቀዱ መሆናቸውን የሚያሳይ እንጂ በአመልካች ድርጊት ምክንያት ተታለው ዶላሩን የሰጡ መሆኑን የሚያሳይ አይደለም። ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች በፈጸሙት የማታለል ድርጊት ምክንያት የግል ተበዳይ 3,500 የአሜሪካ ዶላር በኢትዮጲያ ሲመነዘር ብር 159,600 ለስር 2ኛ ተከሳሽ ሰጥተዋል በማለት የሰጡት የውሳኔ ክፍል መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል። ስለሆነም አመልካች በወንጀል ሕጉን አንቀጽ 692(1) ድንጋጌን መሠረት ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው ኢንቨስትመንት አብረን እንሰራለን የላስቲክ ወንበሮች እና ባቄላ አሸገን ወደ ውጪ እንልካለን በሚል ያልሆነውን ነኝ በማለት የራሱን ሁኔታ በመሰወር እና ማንነቱን እና ስራውን በመደበቅ ነጋዴ መስሎ ለስራ በሚል ከግል ተበዳይ ላይ ጥሬ ገንዘብ ብር 556,320 ወስደዋል በሚለው ብቻ ሊሆን ይገባል።

አመልካች የማታለል ወንጀል ፈጽሞ ጥፋተኛ የተባለበት የገንዘብ መጠን በዚህ ችሎት የተለወጠ ቢሆንም በቅጣት አወሳሰን መመሪያው ላይ የወንጀል ደረጃውን የማይለውጠው በመሆኑ ቅጣቱን በድጋሚ ማስላት አላስፈለገም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1.የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 279834 መጋቢት 20 ቀን 2014 ዓ.ም በአመልካች ላይ ያስተላለፈው የጥፋተኝነት ውሳኔ፤ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 225052 ሠኔ 17 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡

2.ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተለገጸው ምክንያት አመልካች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 692(1) ድንጋጌን በመተላለፍ አሳሳች ነገሮችን በመናገር የግል ተበዳይን አታሎ 3,,500 የአሜሪካ ዶላር በኢትዮጲያ ሲመነዘር ብር 159,600 ለስር 2ኛ ተከሳሽ እንዲሰጡ አድርጓል በማለት በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡

3.አመልካች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 692(1) ድንጋጌን መሠረት ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው ኢንቨስትመንት አብረን እንሰራለን የላስቲክ ወንበሮች እና ባቄላ አሸገን ወደ ውጪ እንልካለን በሚል ያልሆነውን ነኝ በማለት የራሱን ሁኔታ በመሰወር እና ማንነቱን እና ስራውን በመደበቅ ነጋዴ መስሎ ለስራ በሚል ከግል ተበዳይ ላይ ጥሬ ገንዘብ ብር 556,320 ወስደዋል በሚለው ብቻ ነው በማለት ወስነናል፡፡

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አሥሪና ሠራተኛ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰበር መ/ቁ/195390

የካቲት 26 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡ አቶ ኃይሉ ምትኩ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ሪዬስ ኢንጂነሪንግ አክሲዮን ማህበር ጠ. አብደላ አሊ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የስራ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካች ከሳሽ በመሆን በአሁኑ ተጠሪ ላይ ያቀረበው ክስ አመልካች በተጠሪ ድርጅት ከህዳር 6 ቀን 1978 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ጥር 09 ቀን 2010 ዓ.ም በሲኒየር ኢምፖርተር መኮንንነት ሥራ መደብ በወር ብር 21600 እየተከፈለኝ እያገለገልኩኝ ተጠሪ ያለፍቃዴ በመቀለ ቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅ አድርገው ሲሾሙኝ ሹመቱን እንዳልተቀበልኩኝ አሳውቄ በቀድሞ ስራ መደብ እየሰራሁ ተጠሪ የመቀሌ ቅርንጫፍ ስራ መሪነት ላይ አልተገኘም

በማለት ጥር 01 ቀን 2010 ዓ.ም በህገ ወጥ መንገድ የስራ ውል በመቋረጡ በግዴታ ያለትምህርት ዝግጅትና የስራ ልምድ የተደረገው ሹመት አግባብ እንዳልሆነና ስንብቱ ህገወጥ ነው ተብሎ በህጉ የተቀመጡ ክፍያዎች እንዲከፈሉ ዳኝነት ጠይቋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የሰጠው መልስ ከህዳር 06 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ አመልካች በህብረት ስምምነት መሰረት በእድገት የመቀሌ ቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጅ ተደርጎ ተሹሟል፣ ነገር ግን አመልካች የተጠሪ ትእዛዝ በማክበር መቀሌ ሄደው መስራት ሲገባቸው ወደ ተመደበበት ቦታ ላይ እንዲገኙ በተደጋጋሚ ያሳሰበውና በትዕግስት ቢጠብቅም አመልካች በተመደቡበት ቦታ ላይ ተገኝተው ሪፖርት አላደረጉም፣ስለዚህ አመልካች በህጉ አግባብ ስለተሰናበቱ የሚከፈላቸው ክፍያ የለም በማለት ክሱ ውድቅ እንዲደረግ መከራከሩን መዝገቡ ያሳያል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ ተጠሪ የአመልካችን የስራ ውል በማቋረጥ ያሰናበተበት አግባብ አመልካች የተሰጠዉን ምደባና ዝዉዉር ተቀብሎ በተመደበበት ቦታ ስራ ላይ ባለመገኘቱ ነዉ በሚል ስንብቱ ህጉን የተከተለ ነው በማለት ሌሎች የተጠየቁ ክፍያዎች ውደቅ በማድረግ አመልካች ያልተጠቀሙበት የአመት እረፍት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈል እንዲሁም በአመልካች ስም ተቀማጭ የተደረገው የመጠባበቂያ ክፍያ ፕሮቪደንት ፈንድ ታስቦ ወጪ ተደርጎ እንዲከፈል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ ፍ/ቤቱም አመልካች በተመደቡበት ቦታ ተዛውረው የመስራት ግዴታ አለባቸው ወይ? የሚል ጭብጥ በመያዝ የግራ ቀኝ ክርክር መርምሮ በእርግጥ አሰሪው ሥራው ውጤታማ ይሆን ዘንድ ሰራተኞችን በፈለገበት ቦታ መድቦ የማሰራት አስተዳደዊ ስልጣን ያለው መሆኑን፤ነገር ግን አንድ ሰራተኛ የስራ መሪ ሲሆን በአሰሪና ሰራተኛ ህጉ የተሰጡትን መብቶችን ሊገለገልባቸው የማይችል በመሆኑ ሠራተኛው በስራ መሪነት ሲመደብ ወይም ሲሾም የአሰሪው አስተዳደራዊ መብት ብቻ ሳይሆን የሰራተኛውም ፍቃደኝነት የግድ ይላል፣ በተጨማሪ አሰሪው በፈለገበት ቦታ መድቦ ወይም አዛውሮ የማሰራት አስተዳደራዊ መብቱ ሊጠቀምበት የሚችለው ሰራተኛው በፊት ያገኝ የነበረውን መብትና ጥቅም እስካልተነካ ድረስ ብቻ በመሆኑ አመልካች በተሾመበት ቦታ በአሰሪና ሰራተኛ ህጉ የተደነገጉትን መብቶች ሁሉ ሊያገኝ እንደሚችል ተጠሪ ያቀረበው መከራከሪያም ሆነ ማስረጃ የለም፡፡ ስለዚህ አመልካች በመቀሌ ቅርንጫፍ በተመደቡበት ቦታ ሥራ ላይ አልተገኙም በሚል የስራ ውሉን መቋረጡ ሕገወጥ ነው በማለት የጠየቁትን የካሳ ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እና ወጪና ኪሳራ እንዲከፈላቸው ሲወስን የስራ ስንብት

ክፍያን በተመለከተ አመልካች የፕሮቪደንት ፈንድ ሽፋን ያላቸው ስለሆነ ክፍያው አይገባቸውም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ሲሆን የአመልካች አቤቱታ ነጥብ የስራ ስንብት ክፍያ እና የፕሮቪደንት ፈንድን በተመለከተ የተሰጠ ውሳኔ ላይ ነዉ፡፡የአመልካች አቤቱታ ይዘት ባጭሩ፤ አንድ ሰራተኛ የስራ ስንብት ክፍያ በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 39/1/ለ/ እና አዋጅ 494/1998 አንቀጽ 2/ሰ/ መሰረት የማይከፈለው በገዛ ፈቃዱ ስራ ሲለቅና የፕሮቪደንት ፈንድ ሽፋን ያለውና በጡረታ ህግ የተመለከተው መደበኛ የጡረታ ዕድሜ ላይ ደርሶ ከስራ ሲገለል እንደሆነ ያስረዳል፣ ነገር ግን አሰሪ በራሱ አነሳሽነት አመልካችን በህገወጥ መንገድ ከስራ ካሰናበተ ስንብቱ ህገወጥ በመሆኑ ምክንያት ብቻ ሰራተኛው የስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት አለው፡፡የስር ፍ/ቤት ስንብቱ ህገወጥ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ የፕሮቪደንት ፈንድ ስለሚከፈለው የስራ ስንብት ክፍያ ሊከፈል አይገባም ሲል የደረሰበት መደምደሚያ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ የስራ ስንብት ክፍያ እንዲከፈል እንዲታዘዝልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ፕሮቪደንት ፈንድን አስመልክቶ ክርክር ቀርቦ እያለ በዝምታ መታለፍ አግባብ መሆን አለመሆን ተጠሪ ባለበት ለማጣራት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዟል፡፡

በተጠሪ ጠበቃ በኩል የቀረበው መልስ ባጭሩ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ በአመልካች ስም ተቀማጭ የተደረገው የመጠባበቂያ ክፍያ (ፕሮቪደንት ፈንድ) ታስቦ ወጪ ተደርጎ እንዲከፈል ተወስኗል፡፡ስለዚህ አመልካች የስር ፍ/ቤት የፕሮቪደንት ፈንድ እንዲከፈለኝ አልወሰነልኝም ብሎ ያቀረበው ክርክር ከፍርድ ቤቱ ውሳኔ ጋር የሚቃረን ነው፡፡የከፍተኛ ፍ/ቤትም አመልካች የፕሮቪደንት ፈንድ የሚከፈላቸው በመሆኑ የስራ ስንብት ክፍያ ሊፈፀም አይገባም ሲል የጠቀሰው የፕሮቪደንት ፈንድ እንዲከፈላቸው መወሰኑ ነው፡፡የስራ ስንብት ክፍያን በተመለከተ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተለያዩ መዝገቦች ላይ የፕሮቪደንት ፈንድ ሽፋን ያለው ሰራተኛ የስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት የሌለው መሆኑን አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቶበታል፡፡ስለዚህ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ አመልካች ያቀረበው አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች አቤቱታውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነው በተጠሪ አነሳሽነት የተደረገዉ የሥራ ዉል ማቋረጥ ዉሳኔ ህገ ወጥ ነዉ ተብሎ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የተሰጠ ዉሳኔ በበላይ ፍርድ ቤት የተለወጠ ስለመሆኑ የቀረበ ክርክር የለም፡፡ስንብቱ ህገ ወጥ ነዉ መባሉን ተከትሎ ልዩ ልዩ ክፍያዎች ማለትም ካሳ እና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እንዲከፈል በስር ፍርድ ቤት መወሰኑን መዝገቡ ያሳያል፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤት ከተወሰነዉ በተጨማሪ የስንብት ክፍያ እና የፕሮቭደንት ፈንድ ያለአግባብ ታልፏል የሚል ሲሆን ሰበር አጣሪ ችሎቱ የያዘዉ ጭብጥ የፕሮቭደንት ፈንድ በሚመለከት ብቻ ቢሆንም የአመልካች የሰበር አቤቱታ እንደሚያሳየዉ እና ተጠሪም አጥብቆ የተከራከረዉ አመልካች የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ ስለሆነ የስንብት ክፍያ አይገባዉም የሚል በመሆኑ የስንብት ክፍን በሚመለከት በስር ፍርድ ቤት ዉድቅ መደረጉ ተገቢ መሆን አለመሆኑም ጭምር የዚህ ሰበር ችሎት ዉሳኔ የሚያሻዉ ነጥብ ሆኖ አግኝተናል፡፡ በአሰሪና ሰራተኛ መካከል በህግ አግባብ የተቋቋመ የስራ ዉል የሚቋረጥባቸው መንገዶች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 23 ስር የተደነገገ ሲሆን ዉሉ በአሰሪዉ ወይም በሰራተኛው አነሳሽነት ወይም በህግ በተደነገገው መሰረት ወይም በህብረት ስምምነት ወይም በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ሊቋረጥ እንደሚቻል የሚያመለክት ነዉ፡፡አሰሪዉ ወይም ሰራተኛዉ ከእነዚህ ምክንያቶች ወይም ሁኔታዎች በአንዱ ወይም በሌላ ምክንያት የስራ ዉል ለማቋረጥ ሲፈልግ ህጉ ያስቀመጣቸዉን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት ወይም ሂደቱን መከተል አስፈላጊ መሆኑን የህጉ ዝርዝር ይዘት ያስገነዝባል፡፡ ይህም እንደነገሩ ሁኔታ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወይም ያለማስጠንቀቂያ የስራ ዉል ሊቋረጥ የሚችልባቸዉ ሁኔታዎችን መኖሩን ያመለክታል፡፡በአሰሪዉ አነሳሽነት ስራ ዉል ከሚቋረጥባቸዉ ሁኔታዎች አንዱ ሰራተኛዉ በስራ ላይ በሚፈጽመዉ ጥፋት ነዉ፡፡የአዋጁ አንቀጽ 27/1/ እንደሚያመለክተዉ በህብረት ስምምነት በሌላ አካኋን ካልተወሰነ በስተቀር የሥራ ዉልን ያለማስጠንቀቂያ ማቋረጥ የሚቻለዉ በዚህ ድንጋጌ ስር ከተዘረዘሩት ጥፋቶች ወይም ምክንያቶች ዉስጥ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ድርጊት በሰራተኛዉ መፈጸሙ ሲረጋገጥ ነዉ፡፡ የሥራ ውል በተለያዩ ምክንያቶች ሲቋረጥ የሚኖረው ውጤትም እንደዚሁ በሕጉ በዝርዝር ተመልክቷል፡፡በተለይም ለሠራተኛው ሊጠበቁ የሚገቡ የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞችና መብቶች በአዋጅ ቁ/ 337/96 በምእራፍ ሦስት በዝርዝር ተመልክተዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ የሥራ ስንብት ክፍያ በሚመለከት የተቀመጠው ድንጋጌ አንቀጽ 39 ጠቅላላ ሁኔታን የሚዘረዝር ሲሆን ከዚህም ዝርዝር ሁኔታዎች መረዳት የሚቻለው

የሥራ ስንብት ክፍያን የማግኘት ጉዳይ የሁሉም የሥራ ውል መቋረጥ ውጤት ሳይሆን ለውስንና የተገደቡ ምክንያቶች ብቻ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ በአሰሪ አነሳሽነት የተደረገዉ የስራ ዉል ማቋረጥ ህገ ወጥ ነዉ መባሉን ተከትሎ የስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብትን የሚመለከት ነው፡፡በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 39 ስር እንደተመለከተዉ የስራ ስንብት ክፍያ ለሰራተኛዉ ከሚከፈልባቸዉ ሁኔታዎች አንዱ በህግ ከተደነገገዉ ዉጭ በአሰሪዉ አነሳሽነት የስራ ወል ሲቋረጥ ለሰራተኛዉ የስራ ስንብት ክፍያ በአሰሪዉ የሚከፈለዉ ስለመሆኑ በንኡስ አንቀጽ 1/ለ/ስር ተመልክቷል፡፡የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 በአዋጅ ቁጥር 494/98 ተሻሽሎ አንቀጽ 39(1) ስር ተጨማሪ ሁኔታዎችን ያካተተ መሆኑ እና አሁን በስራ ላይ ያለዉ አዋጅ ቁጥር 1156/11 አንቀጽ 39/1/ለ/ ተመሳሳይ ይዘት ያለዉ መሆኑ ልብ ይለዋል፡፡

ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ የሚቻለዉ በአስሪዉ አነሳሽነት የተደረገዉ የስራ ዉል ማቋረጥ ከህግ አግባብ ዉጪ መሆኑ ከተረጋገጠ አስሪዉ የስራ ስንብት ክፍያ ለሰራተኛዉ የመክፈል ግዴታ ያለበት መሆኑን ነዉ፡፡ስለዚህም ህገ ወጥ የሥራ ዉል መቋረጥን ተከትሎ የሚከፈል የስራ ስንብት ክፍያ ጋር ተይይዞ ሌላ ተጨማሪ ቅድመ ሁኔታ በህጉ አልተመለከተም፡፡ይሁንና የስር ፍርድ ቤቶች የስንብት ክፍያ ለአመልካች አይገባዉም በማለት ዉሳኔ የሰጡት ይህ ሰበር ችሎት በመ/ቁ/35197 እና 37048 ላይ የሰጠዉን የህግ ትርጉም በመመርኮዝ ስለመሆኑ ከዉሳኔዉ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ የሰበር ችሎቱ ዉሳኔ ይዘት የሚያሳየዉ ሰራተኛዉ ከዓምስት ዓመት ያላነሰ አገልግሎት ኖሮት ነገር ግን ስራዉን በራሱ ፈቃድ ከለቀቀ እና የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ መሆኑ ከተረጋገጠ የስራ ስንብት ክፍያ በተደራቢነት ሊከፈለዉ አይገባም የሚል ነዉ፡፡(ሰበር መ/ቁ/ 35197 እና 37048 ቅጽ 8 ይመለከቷል)፡፡የሰበር ችሎቱ ዉሳኔ መሰረት ያደረገዉ አዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2/ ሰ እና ሸ/ ድንጋጌ አተገባበር ላይ የተነሳ ክርክር ለመፍታት ያለመ ነዉ፡፡በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ ህገ ወጥ ስንብት ዉጤት የሚመለከት በመሆኑ ተጠቃሹ የሰበር ችሎቱ ዉሳኔ ለተያዘዉ ጉዳይ አግባብነት የለዉም፡፡

በመሆኑም አመልካች የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ ነዉ በሚል ምክንያት የስራ ስንብት ክፍያ አይገባዉም የሚለዉ የተጠሪ ክርክርም ሆነ የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ የስራ ዉሉ ከህግ አግባብ ዉጪ መቋረጡን ተከትሎ የሥራ ስንብት ክፍያ እንደሚከፍል በግልጽ የሚደነግገዉን የአሰሪና

ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 39/1/ለ/ ድንጋጌ ይዘት ያላገናዘበ ስለሆነ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡

ሁለተኛው የአመልካች ቅሬታ ነጥብ የፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያን የሚመለከት ሲሆን የሥር ፍርድ ቤቶች በዝምታ አልፈዉታል የሚል ነዉ፡፡የሥር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ይዘት ሲታይ ለአመልካች የፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያ ሊከፈለዉ እንደሚገባ ያሳያል፡፡ነገር ግን መጠኑ ምን ያህል ነዉ የሚለዉን አጣርተዉ አሃዙን በግልጽ አላስቀመጡም፡፡ይህ መሆኑ ደግሞ ለአፈጻጸም አስቸጋሪና በአፈጻጸም መዝገብ ላይ ሌላ የፍሬ ነገር ክርክር እንዲደረግ የሚጋብዝ ስለሚሆን ስነ ስርዓታዊ አይደለም፡፡ስለሆነም ፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያን አስመልክቶ የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ በመጠን ረገድ ግልጽነት የሌለዉ በመሆኑ ተገቢዉ ማጣራት ተደርጎ የማያሻማ ዉሳኔ ሊሰጥበት ይገባል ብለናል፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ዉ ሳ ኔ</u>

1ኛ/የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/222095 ላይ 08/08/2012ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2ኛ/ በተጠሪ አነሳሽነት የተደረገዉ የሥራ ዉል ማቋረጥ ከህግ ዉጭ ነዉ ተብሎ ካሳ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ እና ፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያ ለአመልካች እንዲከፈል በስር ፍርድ ቤት የተሰጠዉ ዉሳኔ ጸንቷል፡፡በተጨማሪም ተጠሪ የስንብት ክፍያ ለአመልካች ሊክፍለዉ ይገባል ብለናል፡፡

3ኛ/የስንብት እና የፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያ መጠን በተመለከተ ተገቢዉን ማጣራት አድርጎ ዉሳኔ እንዲሰጥ በማለት መዝገቡን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 343/1/ መሰረት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መልሰናል፡፡ይጸፍ፡፡

4ኛ/በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተደረገው ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጥ

የሰ/መ/ቁ. 202341

ሐምሌ 30 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች- አቶ ሀብታሙ አሻግሬ - ቀረቡ

ተጠሪ- የኢትዮጵያ አየር መንገድ - ነ/ፈጅ ሃ/መርያም ብርሃኔ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የስራ ስንብትን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የጀመረውም በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር አመልካች ከሳሽ፣ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን የተከራከሩ ሲሆን አመልካች በቀን 25/07/2011 ዓ.ም ባቀረው ክስ በተጠሪ ድርጅት ውስጥ በደንበኞች አገልግሎት ሱፐርቫይዘርነት ሳገለግል ቆይቼ በሙስና ወንጀል ተጠርጥሬ ክስ ቀርቦብኝ ስከራከር ቆይቼ በታህሳስ ወር 2011 ዓ.ም በነፃ ተሰናብቻለሁ፤ ተጠሪው ሆን ብሎ ክሱ እንዲቀርብብኝ ያደረገ ሲሆን ከእስር ከተፈታሁ በኋላ ወደ ስራዬ ለመመለስ ስጠይቅ ከቀን 11/06/2011 ዓ.ም ጀምሮ የስራ ውሌ የተቋረጠ መሆኑን በደብዳቤ ገልፆልኛል፤ ነገር ግን ስንብቱ ህጋዊ ባለመሆኑ ወደ ስራየ እንድመለስ፣ የሁለት ዓመት ከአምስት ወር ደሞዝ እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ፤ ይህ ካልሆነ ደግሞ የሁለት ዓመት ከአራት ወር ደሞዝና ጥቅማጥቅምን ጨምሮ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 40 እና 41 መሠረት ካሳና የስራ ስንብት ክፍያ እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ በቀን 27/07/2011 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ የአመልካች የስራ ውል የተቋረጠው አመልካች ከስድስት ወር በላይ በስራው ላይ ባለመገኘቱ ነው፤ ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውሌ ተቋረጠ ለሚለው በድርጅቱ 10ኛው የህብረት ስምምነት መሠረት በእስር ምክንያት ከስድስት ወር በላይ ከስራው የቀረ ሰራተኛን ያለማስጠንቀቂያ ማሰናበት እንደሚቻል

ተደንግጓል፤ አመልካች ከቀረበበት የወንጀል ክስ በነፃ መሰናበቱ ብቻውን ስንብቱን ህገ-ወጥ አያደርገውም፤ ላልተሰራ ስራም ደሞዝ ለመክፈል አንገደድም፤ እንዲሁም የስራ ምስክር ወረቀት ክሊራንስ ሲያቀርብ ይሰጠዋል በማለት ክሱ ውድቅ እንዲደረግለት ጠይቋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ አመልካች ከሁለት ዓመት በላይ ቢታሰርም ጥፋተኛ አልተባለም፤ ጥፋተኛ ባልተባለበት የስራ ውሉ መቋረጡ ተገቢ ስላልሆነ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው ካለ በኋላ አመልካች ወደ ስራው እንዲመለስ ቢደረግ ክርክሩ ረዥም ጊዜ የወሰደ ስለሆነና ግንኙነቱ ቢቀጥል ችግር ሊያስከትል ስለሚችል ወደ ስራው ሊመለስ አይገባም በማለት ካሳ ብር 50,742.00፣ የስራ ስንብት ክፍያ ብር 22,409,67 በድምሩ ብር 73,151.67 እንዲከፈለው እና የምስክር ወረቀት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲሰጠው በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች ወደ ስራ ልትመለስ አይገባም ተብሎ የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ይግባኙን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ይግባኙ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 337 *መሠረት* ተሠርዞበታል፡፡ ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነውን የሰበር አቤቱታ ያቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች በቀን 05/06/2013 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው 04 ገጽ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈጽመዋል ያላቸውን ስህተቶች በመዘርዘር በዚህ ችሎት እንዲታረሙለት ጠይቋል፡፡ የአቤቱታው ይዘትም በአጭሩ ሰራተኛው ወደ ስራው ተመልሶ በአሰሪውና በሰራተኛው መካከል የስራ ግንኙነቱ ቢቀጥል ከፍተኛ የሚባል ችግር ወይም የስራ ግንኙነቱን የሚያሻክር ችግር ይፈጠራል ተብሎ ከታመነ ሰራተኛው ካሳ ተከፍሎት ሊሰናበት እንደሚችል ቢደነገግም የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ምክንያት ግን በአመልካች እና በተጠሪ የተደረገው ክርክር ብዙ ጊዜ ወስዷል የሚል ሲሆን ይህም ህጉን የተረጎመበት መንገድ መሠረታዊ ስህተት ያለበት መሆኑን ያሳያል፤ ክርክሩ ሊረዝም የቻለው በኮቪድ 19 ቫይረስ ምክንያት ፍርድ ቤቶች ዝግ በመሆናቸው ነው፤ ተጠሪ አመልካች ወደ ስራ ቢመለስ ችግር ይፈጠራል በማለት ያቀረበው መከራከሪያ ብቻ መሠረት ተደርጎ ወደ ስራ ልትመለስ አይገባም መባሉ ከዚህ በፊት ይህ ችሎት የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ያላገናዘበ ስለሆነ ውሳኔው ተሽሮ ወደ ስራ እንድመለስ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ጉዳዩ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ክርክሩ ረዥም ጊዜ የወሰደው ከአመልካች አቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ከመሆኑ አንፃር የስር ፍርድ ቤት ወደ ስራ ሊመለስ አይገባም ሲል የሰጠው ውሳኔ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43(3) ድንጋጌን ያገናዘበ ነበር ወይ? የሚለው መጣራት ያለበት

መሆኑ ስለታመነበት ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቧል። ተጠሪም መልስ እንዲሰጥበት ጥሪ ተደርጎለት በቀን 27/07/2013 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ አመልካች ከዚህ ቀደም ይሰራበት የነበረው የስራ መደብ አመልካች ሲሰራበት በነበረበት ጊዜ ካለው የአሰራር ስርዓት ሙሉ በሙሉ የተቀየረ ሲሆን አመልካች ወደ ስራ ይመለስ ቢባል ቢያንስ የስድስት ወር መደበኛ ስልጠና እና የስድስት ወር ተግባራዊ ስልጠና ይጠይቃል፤ ይህ ደግሞ ተጠሪን ከፍተኛ ወጪ የሚያስወጣ እና ጉዳት የሚያስከትል ነው፤ እንዲሁም አመልካች ናሁ ተቪ በተባለ የቴሌቪዥን ሚዲያ ላይ በመቅረብ ስሙን ቀይሮ በመጋቢት ወር 2012 ዓ.ም በተሰራ እና "ከአየር መንገድ ጣሪያ ስር ያሉ ጉዶች" በተባለ ፕሮግራም ላይ ቀርቦ ድርጅቱ የሰራተኛ ሰብዓዊ ክብር የማይጠብቅ እና በፖሊሲ ደረጃ ህገ-ወጥ ፖሊሲዎችን ቀርፆ ሰራተኞች ላይ በደል እንደሚፈጽም፤ ሰራተኞቹን በንቀት የሚያስተዳድር እንደሆነ በመግለጽ የሃሰት መረጃ በመስጠት የድርጅቱን መልካም ስም እና ዝና የሚጎዳ ድርጊት በመፈፀም ከድርጅቱ ጋር ያለው የስራ ግንኙነት ስለተበላሸ ወደ ስራ ሊመለስ አይገባም በማለት ተከራክሯል። አመልካች በበኩሉ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቶ ተከራክሯል።

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀውን ሲመስል ይህ ችሎትም የአመልካችን የሠበር አቤቱታ በሰበር አጣሪ ከተያዘው ጭብጥ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል። እንደመረመረዉም አመልካች ከስራ የተሰናበተበት አግባብ ህገ ወጥ ስለመሆኑ አላከራከረም። ግራ ቀኝን ያከራከረዉ ጉዳይ ስንብቱ ህገ ወጥ ነዉ ከተባለ አመልካች ወደ ስራዉ የማይመለስበት ህጋዊ እና አሳማኝ ምክንያት መኖር ያለመኖሩ ነዉ። አንድ ሠራተኛ ከስራ የተሰናበተበት ሁኔታ ህገ ወጥ መሆኑ ከተረጋገጠ ዉጤቱን በመወሰን ረገድ በአንድ በኩል ሠራተኛዉን ወደ ስራዉ በመመለስ የሠራተኛዉን የስራ ዋስትና ማረጋገጥ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በሠራተኛዉ ወደ ስራ መመለስ ምክንያት በአሠሪዉ ላይ ሊደርስ የሚችለዉን ጉዳት ግምት ዉስጥ በማስገባት በሁለቱም በኩል ያሉትን ተፃራሪ ጥቅሞችን ማስታረቅ በሚቻል መልኩ ሊሆን ይገባል። የስራ ክርክሮችን የሚወስነው አካል ከስራ ግንኙነቱ ጠባይ የተነሳ የስራ ግንኙነቱ ቢቀጥል <u>ከፍተኛ ችግር</u> (ሰረዝ የተጨመረበት) ያስከትላል ብሎ ካመነ ሰራተኛው ወደ ስራው መመለስ ቢፈልግ እንኳን ካሳ ተከፍሎት እንዲሰናበት ለመወሰን እንደሚችል በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 እንቀፅ 43(3) ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌም ይህንኑ የሚያስገነዝብ ነዉ። ከዚህ የአዋጁ ድንጋጌ አቀራረጽ መገንዘብ የሚቻለዉም ስራዉ በህገ-ወጥ መንገድ የተቋረጠበት ሠራተኛ ወደ ስራዉ ተመልሶ ለመስራት ፍላጎት ያለዉ መሆኑ ከተረጋገጠ፣

ክርክሩ የቀረበለት የስራ ክርክር ችሎት ሠራተኛዉ ወደ ስራዉ እንዲመለስ የመወሰን ግዴታ ያለበት ሲሆን ሠራተኛዉ ካሳ ተከፍሎት እንዲሰናበት መወሰን የሚችለዉ ወደ ስራዉ መመለሱ በአሠሪዉ ስራ ላይ ከፍተኛ ችግር የሚያስከትል መሆኑን የተረዳ እንደሆነ ብቻ መሆኑን ነዉ፡፡ ስለሆነም የስራ ክርክሩን የሚያይ ፍርድ ቤት ሠራተኛዉ ወደ ስራዉ ሊመለስ አይገባም በሚል ድምዳሜ ላይ ከመድረሱ በፊት የሠራተኛዉ ወደ ስራዉ መመለስ በአሠሪዉ ላይ ከፍተኛ ችግር የማድረስ ዉጤት የሚያስከትል መሆን አለመሆኑን በአግባቡ የማጤን እና የመመርመር ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

ከዚህ አንፃር የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት ተጠሪ አመልካች ወደ ስራ ሊመለስ አይገባም በማለት በዚህ ችሎት ባቀረበዉ መልስ አመልካች በናሁ ቲቪ ላይ ቀርቦ ባደረገዉ ቃለ ምልልስ የሐሰት መረጃ በመስጠት የተጠሪን ድርጅት መልካም ስም እና ዝና የሚጎዳ ድርጊት በመፈጸሙ ምክንያት በመካከላቸዉ የነበረዉ የስራ ግንኙነት እንደተበላሸ እና በሌላ በኩል የስራ ግንኙነቱ ከፍተኛ መተማመንን እንደሚጠይቅ እንዲሁም በመደቡ ላይ ተመድቦ ለመስራት የስድስት ወር መደበኛ ስልጠና እና የስድስት ወር ተግባራዊ ስልጠና የሚጠይቅ መሆኑን በመጥቀስ ይከራከራል፤ ይሁንና አመልካች ይህን መፈጸሙ እንዲሁም ስልጠና መስጠት አስፈላጊ መሆኑ ቢረጋገጥም እንኳ ብቻዉን አመልካች ወደ ስራዉ እንዳይመለስ ምክንያት ሊሆን ይችላል ወይ? የሚል ጥያቄ እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠሪ ይህን ክርክር በስር ፍርድ ቤት ስለማንሳቱ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ይዘት አያሳይም፡፡ ይልቁንም በዚህ ረገድ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያቀረበዉ ክርክር ግንኙነቱ ከተቋረጠ ረጅም ጊዜ በመሆኑ ወደ ስራ ሊመለስ አይገባም የሚል ነዉ፡፡ ከላይ እንደተመለከተዉ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ወደ ስራዉ ሊመለስ አይገባም ሲል ሲወስን መሠረት ያደረገዉም ይህንኑ ነዉ፡፡ ይሁንና ግንኙነቱ ከተቋረጠ ረጅም ጊዜ መሆኑ ግንኙነቱ ቢቀጥል በአዋጁ አንቀጽ 43(3) ላይ በተመለከተዉ አግባብ በተጠሪ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ይደርሳል በሚል ድምዳሜ ላይ የሚያደርስ አይሆንም፡፡

ከዚህ ሁሉ አንፃር ሲታይ አመልካች ወደ ስራ ሊመለስ አይገባም በማለት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ የፀናዉ ዉሳኔ የስራ ዉል በህገ ወጥ መንገድ የተቋረጠበት ሠራተኛ ወደ ስራ ሊመለስ እንደሚገባዉ በመርህ ደረጃ በአዋጁ አንቀጽ 43(3) ላይ የተመለከተዉን ድንጋጌ ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. አመልካች ወደ ስራ ሊመለስ አይገባም በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 97197 በቀን 24/02/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 257833 በቀን 14/04/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት ይህንኑ በማጽናት የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ይህ ዉሳኔ እስከተሰጠበት ቀን ድረስ ያለዉን የአመልካችን የአንድ ዓመት ዉዝፍ ደመወዝ ከፍሎ አመልካችን ወደ ስራዉ እንዲመልስ ተወስኗል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጥ

የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰ/መ/ቁጥር 197540

ጥቅምት 29 **ቀን** 2014ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ሐብታሙ እርቅይሁን

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ አበበ ብርሃን አድማሴ አልቀረቡም፡፡

ተጠሪ፡- የፌደራል ጠቅላይ ዐ/ህግ የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 179154 ጥር 12ቀን 2012ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ የሰጠውን የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሣኔ ማፅናቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ተብሎ እንዲታረምለት አመልካች ስለጠየቁ ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች 1ኛ ተከሣሽ፣ አቶ ጌታሰው ተሰማ 2ኛ ተከሣሽ፣ አቶ

በላይነህ ፈንታ 3ኛ ተከሣሽ፣ አቶ አክሊሉ ብርሃን 4ኛ ተከሣሽ እና አቶ አብዮት ተስፋዬ 5ኛ ተከሣሽ ነበሩ።።

ተጠሪ ነሐሴ 03 ቀን 2009ዓ/ም በተፃፈ ክሱ አመልካችና ሌሎች ተከሣሾች የወንጀል ሕግ አንቀፅ 32(1)(ሀ)(ለ)፣33 እና የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣዉን አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 10(3) ስር የተደነገገዉን በመተላለፍ አመልካችና 2ኛ ተከሳሽ በፌዴራል ጠቅላይ ዐ/ህግ የኢኮኖሚክ ነክ ወንጀሎች ዳይሬክቶሬት ዐ/ሕግ ሆነው በመስራት ላይ እያሉ ቀደም ሲል የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤት አብረዋቸዉ ይሰሩና ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ በተለያዩ የግል ስራ ተሰማርተዉ ከሚገኙ 3ኛ፣4ኛና 5ኛ ተከሳሾች ከነበሩት ጋር በመመሳጠር በእነ ሲ/ሲ/ኤስ ኮም ሰርቪስ ሶሉሽን ኃ/ተ/የ/ገግ/ማህበር ተብሎ በሚጠራዉ መዝገብ የወንጀል ምርመራዉን ከመምራት ጀምሮ ክትትል ሲያደርጉ ቆይተዉ በድርጅቱና ሰራተኞች ላይ የወንጀል ክስ ከመሰረቱ በኋላ በዋስ እንዲወጡ ክሱን በማቅለልና በኃላም በነፃ እንድለቀቁ ለማድረግ ሚ/ር ደ.ዩና ሚ/ር ው ጐንግ ከተባሉት ቻይናያውን ጉቦ ለመቀበል አቅደዉ፡-

1ኛ) 4ኛ ተከሳሽ የነበረው ለሚ/ር ዱ.ዮ ስልክ ደውሎ በአካል ለማግኘት ቀጠሮ አስይዞ ፍሬንድሽፕ ህንፃ 3ኛ ፎቅ ላይ ካለዉ ካፍቴሪያ ካኘው በኋላ በታክስ ማጭበርበር ወንጀል ድርጅታችሁ መከሰሱን አዉቃለሁ ክሱን የያዙት አበበ (አመልካችን)ና ጌታሰዉ የተባሉትን ዐቃቢያነ-ሕግ አውቃቸዋለሁ ብሎ ፎቶ ግራፋቸውን አሣይቶ በቀረበበት ክስ እንደሚረዳው ገልጾ በሌላ ጊዜ ለዐቃቢያነ ሕግ 3 ሚሊዮን ለራሱ 1.5 ሚሊዮን ብር እንዲከፍሉት ማግባባቱን፤

2ኛ) 3ተኛ ተከሳሽ የነበረው በበኩሉ የግል ተበዳዮች ለአመልካችና 2ተኛ ተከሳሽ ገንዘቡን በቀጥታ ሣይቀበሉ ከግል ተበዳዮች ጉቦ እንዲቀበሉና ለማድረግ ራሱም የድርሻዉን ለማግኘት አስቦ ከሌሎች ተከሳሾች ጋር ተመሳጥሮ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ/ም ለተበዳይ ስልክ ደዉሎ በታክስ ጉዳይ ክስ ካቀረቡበት ዐቃቢያነ ሕግ ጋር ቅርበት ያለው መሆኑን ገልፆ ከዚህ በኋላም በቢሮው ውስጥ አመልካችኛ 2ኛ ተከሣሽ እንዲገኙ አድርጎ ካስተዋወቃቸው በኋላ ለሚ/ር ዱ.ዩ ደውሎ 5,000,000 (አምስት ሚሊዮን) ብር ከከፈሉ ክሱ እንዲሚቋረጥ ነግሮ ሲያግባባው ሚ/ር ዱ.ዩ በበኩሉ ገንዘቡን ሲከፍል አመልካችና 2ኛ ተከሣሽ እንዲኖሩ ከተስማማ በኋላ ሐምሌ 10ቀን 2009 ዓ/ም ከምሽቱ 3፡00 ቦሌ ኤርፖርት ጀርባ በ5ኛ ተከሣሽ መኪና እንዲመጡ አደርጎ ከአመልካችና ከ2ኛ ተከሣሽ ጋር እንዲገናኙ በማድረግ በጥሬ ገንዘብ ሐምሳ ሽኅ ብር በቼክ 4.95 ሚሊዮን ብር ቼክ በመቀበሉን

3ኛ) 5ተኛ ተከሣሽ በበኩሉ የግል ተበዳዮች 3ኛ ተከሳሽን አምነው ገንዘቡን እንዲሰጡትና እንዲቀበል ለማድረግ በማሰብ ሐምሌ 6ቀን 2009 ዓ/ም አመልካችና 2ኛ ተከሣሽ 3ኛ ተከሣሽ ቢሮ እንዲገኙ በማድረግና የሚከፈላቸውን ገንዘብ ተወያይተው እንዲሚገልፀለት ለሚ/ር ዱዩ በመንገሩና ገንዘቡን በተቀባበሉ ጊዜም አመልካችንና 2ኛ ተከሣሽን በራሱ መኪና ይዞ በቦታው መገኘቱን

4ኛ) አመልካችና ሁለተኛ ተከሣሽ ገንዘቡን ለመቀበል ከሌሎች ተከሣሾች ጋር በመመሣጠር የግል ተበዳዮች ዐ/ሕጎችን ማግኘት አለብን ብለው ስለጠየቁ በተያዘው ቀጠሮ መሰረት ሐምሌ 6ቀን 2009ዓ/ም ቦሌ ፍሬንድ ሽፕ ሕንፃ በሚገኘው 3ኛ ተከሣሽ ቢሮ መገኘታቸውን፤ ገንዘቡን ከከፈሉት ከሚ/ር ዱዩና ሚ/ር ኸርንግን ከተባሉት ቻይናውያን ጋር መተዋወቃቸውን፤ እንዲሁም ሐምሌ 10ቀን 2009ዓ/ም ከምሽቱ 3፡00 በሚሆንበት ጊዜ ቦሌ ኤርፖርት በ5ኛ ተከሣሽ መኪና ውስጥ ሆነው ገንዘቡን ለ3ኛ ተከሣሽ እንዲሰጥ ለሚ/ር ዱ.ዩ መንገራቸውን በመዘርዘር በጠቅላላው አመልካችና ሌሎች ተከሣሾች ሙሉ ሐሳባቸው ተካፋይ በመሆን 50 ሽሕ በጥሬ ገንዘብ 4,950,000.00 በቼክ ጉቦ ሲቀበሉ እጅ ከፍንጅ ስለተያዙ የሙስና ወንጀልን ፈፅመዋል በማለት ክስ አቅርቦባቸዋል፡፡

አመልካችና ሌሎች ተከሳሾች ያቀረቡት የክስ መቃወሚያ ውድቅ ሲደረግ ድርጊቱን አልፈፀምንም ሲሉ የእምነት ክህደት ቃላቸውን በማስመዝገባቸው የተጠሪ ምስክሮችና የሰነድ ማስረጃዎች ቀርበው ተደምጠዋል፡፡ የስር ከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ ያቀረባቸውን ማስረጃዎች መርምሮ አመልካችን ጨምሮ ሌሎች ተከሣሾች የወንጀል ሕግ አንቀፅ 32(1)(ሀ)፣ 33 እና የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 10(3) የሚከለክለውን በመተላለፍ ጉቦ የመቀበል የሙስና ወንጀል ፈፅመዋል በሚል መሆኑን አመልካችም ከግል ተበዳዮች በ3ተኛ ተከሳሽ በኩል ጉቦ ለመቀበል አስቦ ሐምሌ 5ቀን 2009 ዓ/ም 3ኛው ተከሣሽ ቢሮ በመገኘት ከግል ተበዳዮች ጋር ከተዋወቀ በኋላ ሐምሌ 10ቀን 2009ዓ/ም ከምሽቱ 3፡30 ሲሆን 3ኛ ተከሣሽ በክሱ ላይ የተገለፀውን ገንዘብ ሲቀበል 5ተኛ ተከሣሽ መኪና ውስጥ በመሆን የግል ተበዳይ ገንዘቡን እንዲሰጥ ስለማድረጉ ተመስክሮበታል ካለ በኋላ የአመልካችን የስልጣን ደረጃ ግምት ውስጥ በማስገባት የተከሰሰበትን የሕግ ድንጋጌ ወደ አንቀፅ 10(2) በመቀየር እንዲከላከል ብይን ሰጥቷል፡፡

በዚህ መሰረት አመልካች በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 142(3) መሰረት ለፍርድ ቤቱ ከሰጠው ቃል በተጣሪ ከሌሎች ተከሳሾች የጋራና የግል መከላከያ ማስረጃ አቅርቧል፡፡ ከፍተኛው ፍርድ

ቤትም የአመልካችን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካች የተጠሪን ማስረጃ አላስተባበለም ሲል አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 10(2) የሚደነግገውን ክልከላ በመተላለፍ ጉቦ መቀበል የሙስና ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው ሲል ፍርድ ሰጥቶ በአራት ዓመት ፅኑ እስራትና በአምስት ሽህ ብር መቀጮ እንዲቀጣ ወስኖበታል፡፡ ይህን ውሣኔ በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ስላፀናው አመልካች ይህን የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡

አመልካች ጥቅምት 23ቀን 2013ዓ/ም ፅፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታው በቀረበበት ክስ ተከሳሽ ሆነው የክርክሩን ሂደት እስከ ምስክር መስማት ድረስ የተከታተሉትን ተከሳሾች የቀረበባቸው ክስ ተቋርጦ ወደ ምስክር በማዞር በተጠሪ የተገባላቸውን የተስፋ ቃልና የደረሰባቸውን መገደድ መሰረት በማድረግ በአመልካች ላይ እንዲመሰክሩ ተደርጎ የሰጡትን ምስክርነት ቃል መሰረት በማድረግ ጥፋተኛ መባሉ፤ የቀረበበት ክስ ከ3ኛና 5ተኛ ተከሣሽ ጋር በመሆን በግል ተበዳዮች ላይ የቀረበባቸውን የወንጀል ክስ ለማቅለል፣ በዋስትና እንዲወጡና በኋላም እንዲለቀቁ ለማድረግ ጉቦ ተቀብላችኋል በሚል ሀኖ ሣለ በክሱ ላይ ባልተጠቀሰና በማስረጃ ባልተረጋገጠ ድርጊት ክስ እንዲነሣ አደርጋለሁ በሚል ጉቦ መቀበሉ ተረጋግጧል በሚል ጥፋተኛ መባሉ፤ ወንጀሉ ተፈፀመ ከተባለበት ቀን በማግስቱ ስራ ቦታው ተገኝቶ ስራውን በመስራት ላይ ሣለ እንደሚፈለግ ተነግሮት ተወስዶ ሣለ ወንጀሉን ሲፈፅመም እጅ ከፈንጅ እንደተያዘ በማስመሰል ጥፋተኛ መባሉ፤ የስር ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን ማስረጃ ከነሙሉ ይዘቱ መመዘን ሲገባው አመልካችን ጥፋተኛ ሊያስብል የሚችለውን ብቻ በመምረጥ እንዲሁም ባልቀረበና ሕጋዊነት በሌለው ማስረጃ ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው ክርክር በመዘርዘር እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ከአመልካች ጋር በሙስና ወንጀል ተከሰው ፍርድ ቤት የቀረቡት ተጠርጣሪዎች ክስ ተነስቶላቸው በአመልካች ላይ በምስክርነት እንዲቀርቡና እንዲሰሙ ተደርጎ አመልካችን በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 10(2) ስር ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣት የተወሰነበትን አግባብ ከአዋጁ አንቀፅ 8 ድንጋጌና ሌሎች አግባብነት ካላቸው ሕግጋት እንዲሁም ከመሰረታዊ የክርክር አመራር መርሆዎች አንፃር እንዲመረመር ተጠሪም የመልስ ክርክር እንዲያቀርብ ታዞ የግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር ተጠናቋል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ጥር 21 ቀን 2013ዓ/ም በተፃፈ መልሱ በጥቅሉ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ማስረጃ ምዘናን መሰረት ያደረገ መሆኑን ሰበር ሰሚ ችሎት ማስረጃን የመመዘን የዳኝነት

ስልጣን ያልተሰጠው መሆኑን፣ በስር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር አመልካች ወንጀሉን ለመፈፀሙ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ቀርቦበት ባለማስተባበሉ ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣት መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚያስብል አለመሆኑን በመዘርዘር የስር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ እንዲፀናለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ ክርክር አቅርቧል፡፡

ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከትነው የጉዳዩን አመጣጥና በማስቀረቢያ ነጥቡ ላይ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን

ክርክር ሲሆን በአንድ በኩል ከአመልካች ጋር ጉቦ የመቀበል የሙስና ወንጀል ፈፅመዋል ተብለው ክስ የቀረበባቸውን ተከሣሾች ክስ ተነስቶላቸው ወደ ምስክርነት ተለውጠው ከእነርሱ ጋር ተከሣሽ በነበረው አመልካች ላይ የምስክርነት ቃል እንዲሰጡ ተደርጎ አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱን ከአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 8 ድንጋጌና ከወንጀል ማስረጃ ተገቢነት(ተቀባይት) መርህ አንፃርና በሌላ በኩል አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ በተቀጣበት ድንጋጌ ተከሣሽ የነበሩት የተጠሪ ምስክሮች ከእነሱና በአመልካች ላይ የቀረበውን የተጠሪ ማስረጃ ካዳመጡ በኋላ መጨረሻ ላይ ወደ ምስክርነት ተለውጠው የሰጡት ምስክርነት ሊሰጠው ከሚገባው ክብደት ወይም ዋጋ አንፃር የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን በሚመለከት መልስ ለመስጠት ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣት የተወሰነበት የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 10(2) የሚደነግገውን ክልከላ በመተላለፍ ጉቦ በመቀበሉ የሙስና ወንጀል መፈፀሙ በተጠሪ ማስረጃ በበቂ ሁኔታ ተረጋግጦበት አላስተባበለም ተብሎ ነው፡፡ አመልካች ጉቦ የመቀበል የሙስና ወንጀል መፈፀሙን ለማረጋጥ ተጠሪ ምስክሮች፣ ልዩ ልዩ የፅሁፍና የሰነድ ማስረጃዎች አቅርቧል፡፡ ከተጠሪ ምስክሮች መካከል በ7ኛና በ8ኛ ተራቁጥር የተደመጡት የተጠሪ ምስክሮች ከአመልካች ጋር በግበረ-አበርነት ጉቦ ተቀብለዋል ተብለው ክስ ቀርቦባቸው በመካዳቸው ወንጀሉን የፈፀሙ መሆኑን ለማስረዳት የተጠሪ ስድስት ምስክሮች ከተደመጡ እና የሰነድ ማስረጃም ከቀረቡባቸው በኋላ የአዋጁን አንቀፅ 8 ድንጋጌን መሰረት በማድረግ ወደ ምስክርነት የተለወጡ ስለመሆናቸው የክርክሩ አመጣጥ ያስገነዝባል፡፡

አመልካች ከእሱ ጋር ተከሣሽ የነበሩት ምስክሮች የቀረበባቸውን ክስ ስለካዱ የተጠሪ ማስረጃ ከተደመጠ በኋላ በዚያው ክስ ላይ ምስክር ሆነው ቀርበው መደመጣቸው መሰረታዊ የሕግ

የተፈፀመበት ነው በሚል የሚያቀርበው ክርክር የማስረጃ ተገቢነት ወይም ተቀባይነት (admissibility of evidence) መርህንና የሰጡት የምስክርነት ቃል ሊሰጠው የሚገባውን ክብደት ወይም ዋጋ መሰረት ያደረገ ነው። የማስረጃ ተገቢነት ወይም ተቀባይነት ክርክሩ የአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 8(1) ድንጋጌን የጣሰ ነው በሚል ነው። ለአመልካች ክርክር ተገቢውን ሕጋዊ መልስ ለመስጠት የአዋጅ ቁጥር881/2007 አንቀፅ 8(1) ድንጋጌ የፀረ ሙስና ልዩ ልዩ የሥነ ስርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/1997 እንደተሻሻ አዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀፅ 41 ጋር ተጣምሮ መታየት ይኖርበታል። እነዚህ ድንጋጌዎች በሙሉ የሙስና ወንጀሎችን ግበረ-አበርነት የፈፀሙ ሰዎች ከክስ ነፃ የሚሆኑበትንና ወደ ምስክር የሚዞሩበትን መንገድ እንዲሁም ከክሱ ነፃ ማድረጉና ወይም ወደ ምስክርነት ማዞሩ መቸ እንደሚፈፀም የሚደነግጉ ናቸው። በጥቅሉ የሚመለከተው የሕግ አስፈፃሚው አካል በአንድ ተፈፅመዋል በተባለ የሙስና ወንጀል በግብረ-አበርነት ተካፋይ የነበረ ሰው የወንጀሉ ምርምራ ተጠናቆ ወደ ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት ስለተፈፀመው የሙስና ወንጀል ድርጊትና ስለተካፋዮች ሚና ጠቃሚ መረጃ ከሰጠው ከክሽ ነፃ ሊያደርገውና ከፊለገም ከተከሣሽነት ወደ ምስክርነት ማዞር እንደሚችል ተደንግጓል። የእነዚህ ድንጋጌዎች አይነተኛ ዓላማ ወንጀሉን የሚያጋልጡ ሰዎች በቂ ማበረታቻ አግኝተው የሙስና ወንጀል ፈፀሚዎች የፈፀሙት ወንጀል እና በሙስና ያካበቱት ንብረት ተደብቆ እንዳይቀር ወደ ሕግ ቀርበው ተገቢ ቅጣት እንዲወሰንባቸው ለማስቻል፤ የሙስና ወንጀል መርምሪዎችም በቂ ማስረጃ እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር ታስቦ የተደነገጉ እንጅ አመልካች እንደሚያቀርበው ክርክር የሙስና ወንጀል ግብረ-አበርነት ፈፅሚል ተብሎ ክስ የቀረበበት ሰው አንዴ ክስ ከቀረበበት በኋላ ክሱ ተነስቶለት ምስክር ሆኖ መቅረቡን ከጅምሩ ተገቢነት ወይም ተቀባይት የሌለው (inadmessible) ማስረጃ መሆኑን ለመደንገግ ታስቦ አይደለም። በዚህ ጉዳይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 163947 ውሣኔ ሲሰጥ ተመሣሣይ አቋም በመያዝ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል። በመሆኑም የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣው አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 8(1) የተደነገገው የሙስና ወንጀልን በግብረ-አበርነት የፈፀሙ ሰዎች ክስ ከቀረበባቸው በኋላ ክሱ ተነስቶላቸው ወደ ምስክርነት መዞራቸውን ለመከልከል ይህ ታልፎም በምስክርነት ከቀረቡም ከወዲሁ ተገቢነት ወይም ተቀባይነት እንዳይኖራቸው ለመደንገግ ታስቦ የተደነገገ ባለመሆኑ አመልካች በዚህ ረገድ የሚያቀርበው ክርክር የሕግ መሰረት የለውም ብለናል።

በሌላ በኩል መርመር የሚኖርበት ነጥብ በግብረ-አበርነት የሙስና ወንጀል የፈፀሙ ሰዎች ወደ ምስክርነት ዞረው የሰጡት ምስክርን ቃል በፍርድ ቤቶች ሲመዘን ሊሰጠው የሚገባው ክብደት ወይም ዋጋ ምን ለሆን ይገባል የሚለው ይሆናል፡፡ በሙስና ወንጀል በግብረ-አበርነት ተካፋይ የሆነ ሰው ከክስ ነፃ ሆኖ የሚሰጠው ምስክርነት ቃል ክብደት ማንኛውም ምስክር ከሚሰጠው ምስክርነት እኩል ዋጋ እንዳለው የአዋጅ ቁጥር 434/1997 እንደተሻሻለ አዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀፅ 41(5) ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም ክስ ከመቅረቡ በፊት ጠቃሚ ማስረጃ የሰጡ ሰዎች ከተከሻስነት ወደ ምስክርነት ተቀይረው በሌሎች ግበረ-አበሮቻቸው ላይ የሰጡት ምስክርነት ዋጋ ልዩነት ሣይደረግበት እንዲመዘን ሕጉ ጥበቃ አድርጓል፡፡

የዚህን ችሎት መልስ የሚያሻው ጉዳይ ከሳሽ ወገን አንድን የሙስና ወንጀል በግብር-አበርነት ፈፅመዋል በሚል ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች ላይ ክስ ካቀረበና ማስረጃ ማሰማት ከጀመረ በኋላ የተወሰኑትን ተከሣሾች ክስ አንስቶ ክስ ባልተነሳላቸው ተከሳሶች ላይ ምስክር እንዲሆኑ አድርጎ ቀድሞ ተከሣሽ የነበሩት ሰዎች የሰጡት ምስክርነት ቃል ዋጋው ምን ሊሆን ይገባል የሚለው ነጥብ ነው፡፡ ይህ ነጥብ መልስ ሊያገኝ የሚችለው የማስረጃ ምዘና መርህን መሰረት በማድረግ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ለጉዳዩ ቀጥተኛ መልስ የሚሰጥ የሕግ ድንጋጌ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግም ሆነ በፀረ-ሙስና ልዩ የስነ-ስርዓትና የማስረጃ ሕግ ማግኘት አይቻልም፡፡ በሌላ በኩል ለፍርድ ቤት በቀረበ ማናቸውም የወንጀል ክስ ምስክር ሆኖ የቀረበ ሰው ይመሰክራል ተብሎ የሚጠበቀው ስለተያዘው አከራካሪ ጭብጥ በቀጥታም ይሁን በተዛዋሪ የሚያውቀውን እንደሚሆን የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 137(1) ይደነግጋል፡፡ ይህ ማለት አንድ ምስክር የሰጠው የምስክርነት ቃል ወንጀሉ ከመፈፀሙ፣ ከተፈፀመ ወይም እና በተፈፀመበት ወቅት በቀጥታም ይሁን በተዛዋሪ ስለወንጀሉ መፈፀም ወይም አለመፈፀም ስለሚያውቀው እውነት ብቻ ይመሰክራል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ የተሰጠ ምስክርነት ቃል የሚሰጠው ዋጋ ወይም የአስረጅነት ደረጃና በግበረ-አበርነት የተከሰሰበትን ወንጀል በሚዳኘው ችሎት ተከሣሽ ሆኖ ቀርቦ የከሳሽን ሙሉ ማስረጃ ክርክር አዳምጦ ያገኘውን ግንዛቤ አስቀድሞ ስለጉዳዩ የነበረውን እውቅና በማዳበር እንዲሁም የከሣሽ ወገንን የማስረጃ ክፍተት እና ፍላጎት ከተረዳ በኋላ የተገባለትን የተስፋ ቃል እያሰበ በጫና ውስጥ ሆኖ የሰጠው ምስክርነት ቃል ሊሰጠው የሚገባው ዋጋ እኩል ሊሆን አይገባም፡፡

በቀረበልን ጉዳይ ተጠሪ በምስክርነት ካቀረባቸው ሰዎች መካከል 7ኛ ምስክር አቶ ጌታሰው ተሰማ እና 8ኛ ምስክር አቶ አክሊለ ብርሀን የተባሉት ምስክር ከመሆናቸው በፊት አመልካች

ጥፋተኛ የተባለበትን ጉቦ በመቀበል የሙስና ወንጀል ከአመልካች ጋር በግብረ-አበርነት ፈፅመዋል ተብለው ሁለተኛና አራተኛ ተከሣሾች ነበሩ፡፡ እነዚህ ምስክሮች በተጠሪ ምስክርነት ከመደመጣቸው በፊት የቀረበባቸውን ክስ ክደው በመከራከራቸው ስድስት የተጠሪ ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል እና በአጠቃላይ የክርክሩን ሂደት በችሎት ተከታትለዋል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣት እንዲቀጣ ካስቻሉት ማስረጃዎች እነዚህ ምስክሮች የሰጡት ምስክርነት ቃል ትልቅ ክብደት የተሰጠው መሆኑን የውሣኔው ቅጅ ያስገነዝባል፡፡ የተጠሪ ማስረጃ በፍርድ ቤቱ ተደምጦ መጨረሻ ላይ የተጠቀሱት የተጠሪ ምስክሮች ከተከሣሽነት ወደ ምስክርነት እንዲቀየሩ የመወሰኑ ምክንያት በሌሎች የተጠሪ ማስረጃዎች አመልካችንና ሌሎች ተከሣሾችን ጥፋተኛ ማስባል እንደማይቻል ስለታመነበት መሆኑን የተጠሪ መስሪያ ቤት የበላይ ሀላፊዎች ለአመልካች መከላከያ ምስክሮች የገለፁላቸው መሆኑንም መስክረዋል፡፡

በያዝው ጉዳይ ላይ ተገቢውን ውሣኔ ለመስጠት ከተከሳሽነት ወደ ምስክርነት የተቀየሩት ምስክሮች ከሰጡት ምስክርነት ቃል ውጪ ሌሎች ምስክሮችና ማስረጃዎች በአመልካች ላይ ካረጋገጡት ፍሬ ነገር አኳያ የስር ፍርድ ቤቱ የደረሰበትን መደምደሚያ ተገቢነት መርምረናል፡፡ በዚህም መሰረት ከ1ኛ እስከ 3ኛ ተራቁጥር የተመዘገቡት የተጠሪ ምስክሮች በጥቅሉ አመልካች ጥፋተኛ በተባለበት ወንጀል ምርምራ ላይ የተሣተፉ እንዲሁም አመልካች እንደሚያቀርበው ክርክር ለመከሰሱ ምክንያት የሆነውንና በግል ተበዳይ ላይ የተጣራውን የታክስ ማጭበርበር ወንጀል ከአመልካች ጋር የመረመሩ ሰዎች መሆናቸውን ከገለፁ በኋላ አመልካች ብሩን ሲቀበል እጅ ከፈንጅ ተያዘ ተብሎ ክስ ቢቀርብበትም በእለቱ እንዳልነበር የመሰከሩ ናቸው፡፡ አራተኛ ምስክር ብሩ ለ3ኛ ተከሣሽ ሲሰጥ እጅ ከፈንጅ ተያዘ በተባለበት ቀን ብሩ በተያዘበት ሕንፃ ጥበቃ ሰራተኛ ቢሆንም ብሩ ሲያዝ አመልካች አብሮ ስለመያዙ አልመሰከረም፡፡ አምስተኛና ስድስተኛ ምስክሮች የግል ተበዳይ ድርጅት ሰራተኛ እና ስራስኪያጅ የሆኑ ቻይናውያን ሲሆኑ አመልካችን በሚመለከት የሙስና ወንጀሉ ፍፃሜ እንዲያገኝ ከጅምሩ ጀምሮ አመቻችቷል በተባለው 3ኛ ተከሣሽ ቢሮ ማግኘታቸውን ነገር ግን ስጉዳዩ አመልካች ጋር የተነጋገሩበት ነገር አለመኖሩን መስክረዋል፡፡ በተጨማሪም ስድስተኛ ምስክር ገንዘቡን ለሶስተኛ ተከሣሽ በሰጠበት እለት በቦታው አመልካችን አግኝቶት ገንዘቡን ለሶስተኛ ተከሣሽ እንዲሰጠው ነግሮኛል ሲል የመሰከረ ቢሆንም በቦታው አብሮት የነበረው አምስተኛ ምስክር ገንዘቡን ለሶስተኛ ተከሣሽ እሱና ስድስተኛ ምስክር ሲሰጡት አመልካች አለመኖሩን መስክሯል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ሶስተኛ ምስክር የነበረውና አመልካችና ሌሎች ተከሣሾች ጉቦ ሲቀበሉ እጅ ከፈንጅ ለመያዝ በበላይ

አመራር የታዘዘው የፖ/ሊስ አባል ገንዘቡን ከሶስተኛ ተከሣሽ መኪና ውስጥ ሲይዙ አመልካች በቦታው እንዳልነበር መስክሯል፡፡ በሶስተኛ፣ በአምስተኛ እና በስድተኛ ምስክር መካከል የተፈጠረው ልዩነት እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካች ገንዘቡን ለመቀበል በቦታው ከተገኘ በፖ/ሊሶች ለምን አልተያዘም የሚለውን ጥያቄ በስር ፍርድ ቤት በነበረው ማስረጃ ክርክር መልስ ያላገኘ ጥያቄ ሆኖ ማለፉን የውሣኔው ቅጅ ያስገነዝባል፡፡ ሌሎች የፅሁፍና የሰነድ ማስረጃዎችም ራሣቸውን ችለው አመልካችን ጥፋተኛ ሊያስብሉ የሚችሉ ማስረጃዎች አለመሆናቸውን የውሣኔው ቅጅ ያስገነዝባል፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍርድ ቤት በአንድ በቀረበ የወንጀል ክስ ምስክር ሆኖ የቀረበ አንድ ምስክር የሚሰጠው ምስክርነት ቃል ወንጀሉ ከመፈፀሙ፣ ከተፈፀመ ወይም እና በተፈፀመበት ወቅት በቀጥታም ይሁን በተዛዋሪ ስለወንጀሉ መፈፀም ወይም አለመፈፀም ስለሚያውቀው እውነት ብቻ መሆን እንደሚገባው የሚደነግገውን የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 137 መርህ በመጣስ 7ኛ እና 8ኛ የተጠሪ ምስክሮች ከአመልካች ጋር በግበረ-አበርነት በተከሰሰቡት የሙስና ወንጀልን ለማስረዳት የቀረቡትን የተጠሪ ሙሉ ማስረጃዎች አዳምጠው ያገኙትን ግንዛቤ እንዲሁም የከሣሽ ወገንን የማስረጃ ክፍተት እና ፍላጎት ከተረዱ በኋላ የተገባላቸውን የተስፋ ቃል እያሰቡ አመልካችን ሊጠቅም የሚችል ምስክርነት ቃል ቢሰጡ የተገባላቸው የክስ መነሣት ቀርቶ በተከሣሽነት እንደሚቀጥሉ እያሰቡ በጫና ውስጥ ሆነው የሰጡትን ምስክርነት ቃል ነው በሚል በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 141 ድንጋጌ መሰረት አመልካች መከላከል ሣያስፈልገው በነፃ እንዲሰናበት መወሰን ሲገባው መከላከል እንዲጀምር ማዘዙ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 141 እና 142(1) መርህን መሰረት ያላደረገ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው ተከታዩ ተወስኗል፡፡

<u>ውሣኔ</u>

1) የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 203074 ግንቦት 8ቀን 2011 እና ግንቦት 26ቀን 2011 ዓ/ም የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ እንዲሁም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 179154 ጥር 12 ቀን 2012ዓ/ም የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 195(2)(ለ)(2) መሰረት ተሽሯል፡፡
2) አመልካች የወንጀል ሕግ አንቀፅ 32(1)(ሐ)፣33 እና የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 10(3) ድንጋጌን በመተላለፍ ጉቦ የመቀበል

የሙስና ወንጀል መፈፀሙን የሚያረጋግጥ በቂና ለጉዳዩ ገልልተኛ ማስረጃ ቀርቦ ያልተረጋገጠበት በመሆኑ የቀረበበትን ክስ መከላከል ሳያስፈልገው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 141 መሰረት በነፃ እንዲሰናበት ተወስኗል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የመ/ቁ/212950

ህዳር 30/2014 ዓ.ም

ዳኞች፡ ሰለሞን አረዳ

እትመት አሰፋ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡ አቶ ቶቼኖ ቶማ

ተጠሪ፡ የደቡብ ክልል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጠቷል፡፡

<u>ፍርድ</u>

ጉዳዩ የውንብድና ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩም የተጀመረው የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ የወንጀል ህግ አንቀፅ 670 ድንጋጌን ጠቅሶ በወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ የክሱም ይዘት አመልካች የተጠቀሰውን የወንጀል ህግ ድንጋጌን በመተላለፍ የማይገባውን ብልፅግና ለራሱ አልያም ለሌላ ሰው ለማስገኘት አስቦ በክሱ ዝርዝር ውስጥ በተገለፀው ቀን፣ ቦታ እና ሰዓት የግል ተበዳይ ወደሆኑት ወ/ሮ አበበች ባደቦ የንግድ

ቤት በመሄድ የተበዳይን ጉረሮ አንቆ በመያዝ አንገታቸው ላይ የነበረ የዋጋ ግምቱ ብር 50,000(ሃምሳ ሽህ) የሚያወጣ 20 ግራም የወርቅ ሀብል፤ እንዲሁም ባንኮኒ ውስጥ የነበረውን ብር 20,000(ሃያ ሺህ) ወስዶ በጓሮ በኩል ያመለጠ በመሆኑ የውንብድና ወንጀል ፈፅሟል የሚል ነው።

አመልካች ለዚሁ ክስ በሰጠው መልስ ድርጊቱን እና ጥፋተኝነቱን ክዶ በመከራከሩ የዐቃቤ ህግ ምስክሮች ቀርበው እንዲሰሙ ከተደረገ በኋላ እንደክሱ አቀራረብ አስረድተዋል በሚል አመልካች ክሱን እንዲከላከል ታዟል። አመካችም አራት መከላከያ ምስክሮችን አሰምቷል። የመከላከያ ምስክሮቹም አመልካች እና የግል ተበዳይ ባል አና ሚስት የነበሩ መሆኑን፤ ክስ የቀረበበት ድርጊት ተፈፀመ ከተባለ በኋላ በዚያው ጉዳይ ሁለቱን ለማሸማገል ሽምግልና ተቀምጠው የነበረ መሆኑን፤ በዚሁ ጊዜ የግል ተበዳይን ስለድርጊቱ ሲጠይቋቸው አመልካች ንብረት ዘርፎኛል በሚል የከሰሷቸው ዘወትር ሰክሮ እየሄደ ስለሚረብሻቸው እንጂ የተወሰደባቸው ንብረት እንደሌላ የነገሯቸው መሆኑን ተናግረዋል። ጉዳዩን የያዘው ፍርድ ቤትም ለጉዳዩ አወሳሰን ይረዳኛል በማለት የሸማግሌዎቹ ሰብሳቢ የነበሩትን ፓስተር ታደሰ ታንቱ የተባሉትን ግለሰብ አስቀርቦ ሰምቷል። ተጨማሪ ምስክሩም አመልካች እና የግል ተበዳይ ባልና ሚስት መሆኑቻውን፤ ክስ የቀረበበት ጉዳይ ተፈፀመ ከተባለ በኋላ የሁለቱን ጉዳይ በሽምግልና የተመለከቱ መሆኑን፤ በሽምግልናው ላይም የግል ተበዳይ በእርግጥም ዝርፊያ ተፈፅሞባቸው እንደሆን በሚል የጠየቋቸው መሆኑን፤ ተበዳይም አመልካች ዘወትር ሰክሮ ንግድ ቦታቸው እየሄደ ስለሚረብሻቸው ለመከላከል በሚል የከሰሷቸው እንጂ የተፈፀመባቸው ውንብድና እንደሌለለ የነገሯቸው መሆኑን ገልፀዋል።

ከዚህ በኋላ ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙ ክርክር መርምሮ እና የቀረቡትን ማስረጃዎች መዝኖ የዐቃቤ ህግ ክስ እና ማስረጃ ተስተባብሏል በሚል አመልካችን ከቀረበባቸው ክስ በነፃ አሰናብቷል። ይህንኑ ውሳኔ በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች በመከላከያ ማስረጃው ያስመሰከረውን ፍሬ ነገር አስምልክቶ በዋናው ክርክር ወቅት በመስቀልኛ ጥያቄ ያስተባበለው ነገር የለም፤ ከተበዳይ ጋር ተደርጓል የተባለውን የእርቅ ስምምነት አስምልክቶም በጽሑፍ የቀረበ የእርቅ ስምምነት የለም፤ የድርጊቱ አፈፃፀምም አመልካች ከግል ተበዳይ ጋር የነበረው ጋብቻ ከተቋረጠ በኋላ ጉልበቱን በመጠቀም ለማስቀጠል ፍላጎት ያለው መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ ድርጊቱ ከውንብድና ወንጀል ይልቅ በማስገደድ መጠቀም ወንጀልን የሚያቋቁም ነው በማለት ክስ የቀረበበትን አንቀፅ ወደ አንቀፅ 713

በመቀየር አመልካችን ጥፋተኛ ብሎት በ1 ዓመት ከ2 ወር ቀላል እስራት እና በብር 2,000(ሁለት ሺህ) የገንዘብ ቅጣት እንዲቀጣ ወስኗል። አመልካች ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም።

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ነው። አመልካች ነሓሴ 14/2013 ዓ.ም በተሻሬ የሰበር አቤቱታ በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያለውን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሶ በዚህ ችሎት እንዲታረምለት ጠይቋል። የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉ ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል።

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም አመልካች የዐቃቤ ህግ ክስ እና ማስረጃን አላስተባበለም በሚል በወንጀል ህግ አንቀፅ 713 ስር ጥፋተኛ ተብሎ የመቀጣቱን አግባብነት በወንጀል ጉዳት ተከሳሽ የሆነ ሰው በመከላከያ ማስረጃው ማስረዳት ከሚጠበቅበት የማስረዳት ደረጃ አኳያ መርምሯል።

በወንጀል ጉዳይ ዐቃቤ ህግ ያቀረበውን ክስ አስረድቷል የሚባለው ባቀረባቸው ማስረጃዎች ክሱን በቂ እና አሳማኝ በሆነ መልኩ ሲያስረዳ እንደሆነ የወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 141 ይደነግጋል። በወንጀል ክሱ ተከሳሽ የሆነው ሰውም የቀረበበትን ክስ አስምልክቶ ማስተባበያ ማስረጃ እንዲያቀርብ የሚታዘዘው ይኸው ሲረጋገጥ ስለመሆኑ ከወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 141 እና 142 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል። ከዚህ ጋር ተያይዞ አንድ ሊነሳ እና መልስ ሊሰጠው የሚገባው ነጥብ "በወንጀል የተከሰሰ ሰው በመከላከያ ማስረጃው ማስረዳት/ማረጋገጥ/ የሚጠበቅበት የማስረዳት ደረጃ ምን ያክል ነው?" የሚለው ነው። በሌላ አገላለፅ በወንጀል ተከስሶ ክሱን እንድከላከል ከተነገረው ተከሳሽ የሚጠበቀው ዐቃቤ ህግ ባስረዳው ልክ በመከላከያ ማስረጃው በቂ እና አሳማኝ በሆነ መልኩ መረጋገጥ ነው ወይስ የዐቃቤ ህግ ማስረጃ ላይ ጥርጣሬ እንዲፈጠር ማድረግ ነው እንደማለት ነው።

እንግዲህ ከላይ እንደተመለከተው በወንጀል የተከሰሰ ሰው መከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ የሚታዘዘው በዐቃቤ ህግ ማስረጃ የተረጋገጠበትን ክስ እና ማስረጃን እንዲያስተባብል ነው። ማስተባበል ማለት ደግሞ የተከሳሹን የወንጀል ድርጊት እና ጥፋተኝነት አረጋግጠዋል በተባሉት ማስረጃዎች ላይ በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ ጥርጣሬ እንዲፈጠር በማድረግ በማስረጃዎቹ የማስረዳት አቅም ላይ መተማመን እንዳይኖር ማድረግ ስለመሆኑ ከማስረጃ ህግ መሰረተ ሀሳብ እና በዚሁ ዙሪያ ከተደረጉ የምርምር ፅሁፎች የምንረዳው ጉዳይ ነው። ይህ ደግሞ ከተከሰሰው ሰው የሚጠበቀው በመከላከያ ማስረጃው በቂ እና አሳማኝ በሆነ መልኩ ማስረዳት ሳይሆን

የዐቃቤ ህግ ማስረጃን አስመልክቶ ቀድሞ በተያዘው አቋም ላይ ጥርጣሬን መፍጠር ብቻ መሆኑን ያስገነዝባል።

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ዐቃቤ ህግ ክሱን ለማረጋገጥ ያቀረበው የሰው ምስክር ብቻ ነው። ቀርበው የተሰሙት የዐቃቤ ህግ ምስክሮችም እንደ ክሱ አቀራረብ አመልካች በግል ተበዳይ ላይ የውንብድና ወንጀል ሲፈጽም መመልከታቸውን ተናገረዋል። ሆኖም አመልካች ከተከሰሰበት የወንጅል ድርጊት ጋር በተያያዘ በአመልክች እን የግል ተበዳይ መካከል ሽምግልና ተቀምጠው የነበሩት የአመልካች መከላከያ ምስክሮች እና በፍርድ ቤት ትዕዛዝ በማጣሪያ ምስክርነት የተሰሙት ሽማግሌዎቹ ሰብሳቢ የግል ተበዳይዋ በሽምግልናው ላይ አመልካችን በወንጀል የከሰሷችው ዘወትር ሰክሮ በመሄድ ስለሚረብሻቸው እንጂ የፈፀመባቸው የወንብድና ድርጊት እንደሌለ የነገሯቸው ስለመሆኑ ተናግረዋል። በእንዚህ አሸማጋይ ሽማግሌዎች ይህ ሁኔታ መረጋገጡ ቀድሞ በተሰሙት የዐቃቤ ህግ ምስክሮች የምስክርነት ቃል ላይ ጥርጣሬ እንዲኖር የሚያደርግ ነው።

ጉዳዩ ይህ ሆኖ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአመልካች እና የግል ተበዳይ መካከል ተደርጓል የተባለው የእርቅ ስምምነት በፅሁፍ አልቀረበም፤ እንዲሁም አመልካች በመከላከያ ማስረጃው ያረጋገጠውን ፍሬ ነገር በመስቀልኛ ጥያቄ አልጠየቀም በሚል ምክንያት የአመልካችን መከላከያ ማስረጃ ውድቅ ማድረጉ የቀረበው ጉዳዩ የወንጀል ክርክር መሆኑን እና በወንጀል ጉዳይ ተከሳሽ የሚጠበቅበትን የማስረዳት ደረጃ ያላገናዘበ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል።

<u>ውሳኔ</u>

1. የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/34748 ላይ ግንቦት 04/2013 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ እና ይህንኑ ውሳኔን በማፅናት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/36060 ላይ ነሐሴ 04/2013 የሰጠው ትዕዛዝ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁር 195(2(ለ(2))) መሰረት ተሽሯል።
2. የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/46898 ላይ ታህሳስ 19/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካችን ከተከሰሰበት ወንጀል ነፃ በመልቀቅ የሰጠው ውሳኔ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 195(2(ለ(2))) ፀንቷል።

ትዕዛዝ

1. አመልካች በዚህ መዝገብ ላይ ከተከሰሰበት ወንጀል በነፃ የተሰናበተ በመሆኑ በሌላ ወንጀል የማይፈለግ መሆኑን አረጋግጦ በአስቸኳይ ከእስር እንዲለቀው ለሚገኝበት ማረሚያ ቤት ይፃፍ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ.መ.ቁ 176890

ግንቦት 25 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱአለም

አመልካች፡- አቶ ቢንያም አብዱልቃድር

ተጠሪ፡- የኦሮምያ ክልል ፍትህ ቢሮ ዓቃቤሕግ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ግንቦት 05 ቀን 2011 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የወልመራ ፍ/ቤት በመ.ቁ 67564 ጥቅምት 23 ቀን 2011 ዓ.ም የኤግዚቢት ጉዳይ ለብቻ ተለይቶ ውሳኔ ሊሰጥበት አይቻልም በማለት የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት በየደረጃው ያሉ የክልሉ ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ በወንጀል ጉዳይ በኤግዚቢትነት የተያዘ ተሽከርካሪ ይለቀቅልኝ በማለት የቀረበን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ ዘላለም ጉተማ፤ ጌቱ ቡዲቴ እና አቡሼ ብሩ በተባሉ ሶስት ግለሰቦች ላይ ባቀረበው የወንጀል ክስ የአሁን አመልካች ንብረት የሆነ የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-49426 የሆነው ተሽከርካሪ በኤግዚቢትነት ቀርቧል፡፡ ተጠሪ በስር ተከሳሾች ላይ ያቀረበው ክስ የዓቃቤሕግ ማሥረጃ ከተሰማ በኋላ ተከሳሾች እንዲከላከሉ ብይን ተሰጥቶ ስላልቀረቡ ፖሊስ ተከሳሾችን በሚያገኝበት ጊዜ ዓቃቤሕግ መዝገቡን ማንቀሳቀስ ይችላል ተብሎ መዝገቡ የተዘጋ ስለመሆኑ ከሰበር አቤቱታው ጋር ተያይዞ የቀረበልን የውሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ የአሁን አመልካች መዝገቡ ከተዘጋ በኋላ ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት አቤቱታ በኤግዚቢትነት የቀረበው መኪና እንዲመለስላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም አቤቱታውን መርምሮ ጉዳዩ ተከሳሾቹ አምልጠው የመጨረሻ ውሳኔ ሳያገኝ የቀረ በመሆኑ ኤግዚቢቱ ሊመለስ አይችልም በማለት ውሳኔ ከሰጠ በኋላ በተሰጠው ወሳኔ ላይ ይግባኝ ተጠይቆበት ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ በመሻር የተያዘው መኪና ይወረሳል ወይስ አይወረስም በሚለው ላይ አዋጅ ቁጥር 980/2016 አንቀጽ 49/2 ን ለማስፈጸም በወጣው ደንብ እና መመሪያ መሠረት ግልጽ በሆነ ሁኔታ ከሕግ ውጪ ለንግድ የታሸገ ውሃ የተጫነበት መኪና ይወረሳል የሚለው ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ተጣርቶ እንዲወሰን በማለት ለስር ፍ/ቤት ጉዳዩን መልሶለታል፡፡

የወረዳው ፍ/ቤት ጉዳዩ ከተመለሰለት በኋላ ክስ የተመሰረተበት አንቀጽ ሕጋዊ ፈቃድ ሳይኖረው የተያዘ ሰው የተያዙት የንግድ ዕቃዎች እና አገልግሎት ሲሰጥበት የነበረው ዕቃ እንደሚወረስ በግልጽ አስቀምጧል፤ በኤግዚቢትነት የተያዘው መኪና ውሳኔ ሳያገኝ ተከሳሾች ጠፍተዋል፤ የተዘጋውን መዝገብ በመኪናው ብቻ በማንቀሳቀስ በኤግዚቢት ላይ ብቻ ውሳኔ የሚሰጥበት ሁኔታ አይኖርም፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 21 በሰ.መ.ቁ 126017 በኤግዚቢት ተይዞ ፍ/ቤት በቀረበ አንድ ንብረት ላይ ውሳኔ መስጠት የሚቻለው ዋናው መዝገብ የመጨረሻ ውሳኔ ካገኘ በኋላ እንደሆነ በግልጽ ተወስኗል፤ ስለዚህ የቀረበውን የኤግዚቢት ጉዳይ ብቻ በመለየት ለባለንብረት ይመለስ ወይም በመንግስት ይወረስ ለማለት የሚቻለው መዝገቡ የመጨረሻ ውሳኔ ካገኘ በኋላ ነው፤ ጉዳዩ ተከሳሾች በሌሉበት ለመቀጠል የሚችል አይደለም፤ መመሪያው ፍቃድ ሊሰረዝ የሚችልበትን ሁኔታ እንጂ ኤግዚቢት የሚወረስበትን ሁኔታ የሚያስቀምጥ አይደለም፤ በመሆኑም የኤግዚቢት ጉዳይ ለብቻው ተለይቶ ውሳኔ ሊሰጥበት ስለማይችል የአመልካች አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው በትዕዛዝ ውድቅ ተደርጓል። አመልካች በመቀጠል ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበዋል። አቤቱታው የቀረበላቸው ፍ/ቤቶች ግራቀኙን ካካራከሩ በኋላ የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንተዋል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- ተሸከርካሪው የአመልካች ንብረት መሆኑን አቃቤሕግ ራሱ በክሱ ገልጿል፤ አመልካች ክሱ የሚመለከተኝ ስለመሆኑ አልተገለጸም፤ የንግድ ፈቃድ ሳይኖራቸው የሽያጭ ስራ ሲያከናውኑ የተያዙ እና ክስ የተመሰረተባቸው ሌሎች ሰዎች ሆነው ሳለ እና የተያዘው ዕቃ በሕግ ክልከላ የተደረገበት ዕቃ ባልሆነበት ሁኔታ የአመልካች ንብረት በኤግዚቢትነት መያዙ አግባብ አይደለም፤ ፍ/ቤቱ ተከሳሾችን በዋስትና መልቀቁ እና ተከሳሾች መቅረታቸው ከአመልካችም ሆነ ከአመልካች ንብረት ጋር የሚያያዝ አይደለም፤ ተከሳሾችን ተከታትሎ የማቅረብ ግዴታ ያለበት ፖሊስ እና ዓቃቤሕግ ነው፤ ለሕገወጥ ንግድ የዋለ ዕቃ ሊወረስ እንደሚችል በአዋጁ ስለተጠቀሰ ብቻ ከወንጀሉ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው ተሸከርካሪ ሊወረስ ይችላል የሚል ትርጉም በመስጠት ተሸከርካሪው ገደብ ለሌለው ጊዜ ታስሮ እንዲቆይ የተሰጠው ውሳኔ አግባብ አይደለም፤ ተከሳሾቹ አልተገኙም በሚል ምክንያት አመልካች ንብረቱን እንዳጣ የተሰጠው ውሳኔ በሕገመንግስቱ የተጠበቀልኝን በንብረት የመገልገል መብት የሚጻረር በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የአመልካች ንብረት የሆነው ተሸከርካሪ በኤግዚቢትነት በተያዘበት የወንጀል ክስ ላይ ተከሳሾች የነበሩት ግለሰቦች በዋስትና ወጥተው ባለመቅረባቸው ምክንያት በተገኙበት ጊዜ መዝገቡ እንዲንቀሳቀስ ተብሎ በተዘጋበት ሁኔታ አመልካች ንብረቱ እንዲለቀቅላቸው ያቀረቡትን ጥያቄ በየደረጃው ያሉት የክልሉ ፍ/ቤቶች ውድቅ የማድረጋቸውን አግባብነት በአመልካች ሕገመንግስታዊ የንብረት ባለቤትነት መብት ላይ ከሚኖረው ውጤት አኳያ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል። ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል።

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- በስር ተከሳሾች ላይ የቀረበው ክስ የአዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 49/2 ድንጋጌን በመተላለፍ የአመልካች ንብረት በሆነው የጭነት መኪና ሕጋዊ የንግድ ፈቃድ ሳይኖራቸው የታሸገ ውሃ ጭነው በመሸጥ ላይ እንዳሉ ተይዘዋል የሚል ነው፤ የስር

ፍ/ቤት የዓቃቤሕግን ማስረጀ ከሰማ በኋላ ተከሳሾች ,እንዲከላከሉ ብይን ሰጥቷል፤ ተከሳሾች መከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ቀጠሮ ተሰጥቶአቸው ስላልቀረቡ ዓቃቤሕግ የማንቀሳቀስ መብቱ ተጠብቆ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ተከሳሾች የተከሰሰቡበት አንቀጽ ማንም ሰው ሕጋዊ ፈቃድ ሳይኖረው የንግድ ዕቃዎችን ይዞ ከተገኘ እንደሚወረስ ይደነግጋል፤ ዋናው ጉዳይ ውሳኔ ሳያገኝ በኤግቢትነት በቀረበ ንብረት ላይ ውሳኔ ሊሰጥ እንደማይችል በሰ.መ.ቁ 126017 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተሰጠበት በመሆኑ ይህንኑ መሠረት በማድረግ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ጭብጥ ከግራቀኙ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የቻልነው የአሁን ተጠሪ በስር ፍ/ቤት የወንጀል ክስ ያቀረበው በሌሎች ግለሰቦች ላይ መሆኑን እና በአመልካች ላይ የቀረበ የወንጀል ክስ የሌለ መሆኑን፤ በመዝገቡ ተከሳሾች ላይ የቀረበው ክስ የአዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 49/2 ድንጋጌን በመተላለፍ ሕጋዊ የንግድ ፈቃድ ሳይኖራቸው የአመልካች ንብረት በሆነው የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3- 49426 በሆነው ተሽከርካሪ የታሸገ ውሃ ጭነው በመሸጥ ላይ እንዳሉ ተይዘዋል የሚል መሆኑን፤ ይህንኑ ክስ ለማስረዳትም ዓቃቤሕግ ተሽከርካሪውን በኤግዚቢትነት ያቀረበ መሆኑን፤ የመዝገቡ ተከሳሾች የቀረበባቸውን ክስ እንዲከላከሉ ብይን ከተሰጠ በኋላ ባለመቅረባቸው ፖሊስ ተከሳሾችን በሚያገኝበት ጊዜ ዓቃቤሕግ መዝገቡን ማንቀሳቀስ ይችላል ተብሎ መዝገቡ የተዘጋ መሆኑን፤ የአሁን አመልካች መዝገቡ ከተዘጋ በኋላ በኤግዚቢትነት የተያዘው ተከሽከርካሪ ንብረታቸው መሆኑን በመግለጽ ተሽከርካሪው እንዲመለስላቸው የጠየቁ መሆኑን፤ ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት ዋናው ጉዳይ ውሳኔ ሳያገኝ ኤግዚቢቱ ሊለቀቅ አይችልም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አድርጎት የነበረ መሆኑን፤ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ተጠይቆበት ከመመሪያው አንጻር ታይቶ እንዲወሰን በማለት በነጥብ ለወረዳው ፍ/ቤት የተመለሰ መሆኑን፤ የወረዳው ፍ/ቤትም ጉዳዩ ከተመለሰለት በኋላ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 126017 በኤግዚቢት ተይዞ ፍ/ቤት በቀረበ አንድ ንብረት ላይ ውሳኔ መስጠት የሚቻለው ዋናው መዝገብ የመጨረሻ ውሳኔ ካገኘ በኋላ እንደሆነ ውሳኔ የሰጠበት በመሆኑ የኤግዚቢት ጉዳይ ለብቻው ተለይቶ ውሳኔ ሊሰጥበት አይችልም በማለት

የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ ያደረገ መሆኑ እና ይህ ውሳኔም በየደረጃው ባሉ የክልሉ ፍ/ቤቶች የጸና መሆኑን ነው።

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት ለውሳኔው መሠረት ያደረገው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 126017 የሰጠውን አስገዳጅ ውሳኔ በመሆኑ እና ተጠሪም ይህንኑ ውሳኔ መነሻ በማድረግ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት የሚከራከረ በመሆኑ በቅድሚያ ተጠቃሹ ውሳኔ በዚህ መዝገብ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለው መሆን አለመሆኑን በቅድሚያ መለየት አስፈላጊ ሆኖ ስላገኘነው እንደሚከተለው ተመልክተነዋል።

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 126017 በሰጠው ውሳኔ ላይ የቀረበው ጉዳይ በመዝገቡ ተከሳሽ የሆነው የፖሊስ ጽ/ቤት የአዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጸ 27/11 በመተላለፍ ተሽከርካሪዬን የያዘብኝ ስለሆነ እንዲለቀቅ ይወሰንልኝ በሚል የቀረበ የፍትሐብሔር ክስ ነው። ተከሳሽ በሰጠው መልስ መኪናው እንዲለቀቅልኝ በማለት ክስ ያቀረበው ከሳሽ የሆነው ግለሰብ የመኪናው ሹፌር እና ባለቤት መሆኑን፤ በወቅቱ ጭኖት የነበረው ስኳር ሕገወጥ ሆኖ ስለተገኘ ስኳሩ እና ተሽከርካሪው ኤግዚቢት ሆኖ የወንጀል ክስ የቀረበ መሆኑን፤ ተከሳሽ በዋስትና ወጥቶ በመታጣቱ መዝገቡ ለጊዜው የተዘጋ መሆኑን በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግለት ጠይቋል። ይህ ጉዳይ በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች ክርክር ሲደረግበት ቆይቶ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተጠቃሹ መዝገብ በሰጠው ወሳኔ በኤግዚቢትነት የተመለከተ ከወንጀል ክሱ ጋር የተያያዘ ንብረት በመንግስት ሊወረስ የሚገባ ስለመሆኑ ወይም ለባለንብረቱ ሊመለስ የሚገባ ስለመሆኑ ውሳኔ የሚሰጠው የወንጀል ክሱን ተፈጥሮ እና ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን የወንጀል ሕጉን እና የወንጀል ሥነ- ሥርዓት ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ የወንጀል ክሱን በሚመለከተው አካል ነው፤ የወንጀል ክሱን ለማየት ስልጣን ለሌለው ፍ/ቤት ክስ ቀርቧል በሚል ከወንጀል ክሱ ጋር በተያያዘ በወንጀል ችሎቱ ዳኝነት ታይቶ ውሳኔ ሊያርፍበት የሚገባ ንብረት በፍትሐብሔር ክስ ማስመለስ አይቻልም፤ በወንጀል ጉዳይ በኤግዚቢትነት የተያዘ ንብረት በፍርድ ውሳኔ የሚያገኘው በወንጀሉ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ሲሰጥ ለባለንብረቱ ይመለስ ወይም ለመንግስት ገቢ ይሁን ተብሎ ሲወሰን ወይም ተገቢውን የሕግ ስርዓት ተከትሎ ስልጣን ባለው አካል ትዕዛዝ ሲተላለፍ እንጂ በወንጀል ክስ ውሳኔ እየተጠባበቀ ባለ መዝገብ ላይ የተያዘውን ኤግዚቢት የፍትሐብሔር ክስ እንዲቀርብ ተደርጎ በዚህ ክስ መነሻነት ንብረቱ ይለቀቅ በማለት ውሳኔ የሚሰጥበት የሕግ አግባብ የለም በማለት የወሰነ መሆኑን የውሳኔው ይዘት በግልጽ ያመለክታል።

በያዝነው ጉዳይ አከራካሪ የሆነው በኤግዚቢትነት የተያዘው ተሽከርካሪ ይመለስልኝ በሚል የቀረበ ክርክር በመሆኑ ሰበር ሰሚ ችሎቱ ከላይ በተገለጸው መዝገብ አስቀድሞ በሰጠው ወሳኔ በኤግዚቢትነት የተመለከተ ከወንጀል ክሱ ጋር የተያያዘ ንብረት በመንግስት ሊወረስ የሚገባ ስለመሆኑ ወይም ለባለንብረቱ ሊመለስ የሚገባ ስለመሆኑ ውሳኔ የሚሰጠው የወንጀል ክሱን ተፈጥሮ እና ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን የወንጀል ሕጉን እና የወንጀል ሥነ- ሥርዓት ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ የወንጀል ክሱን በሚመለከተው አካል ነው። የወንጀል ክሱን ለማየት ስልጣን ለሌለው ፍ/ቤት ክስ ቀርቧል በሚል ከወንጀል ክሱ ጋር በተያያዘ በወንጀል ችሎቱ ዳኝነት ታይቶ ውሳኔ ሊያርፍበት የሚገባ ንብረት በፍትሐብሔር ክስ ማስመለስ አይቻልም በማለት የሰጠው ውሳኔ በእጃችን ካለው ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያለው እና እኛም የምንቀበለው ነው። ሆኖም በእጃችን ባለው ጉዳይ ላይ አመልካች አቤቱታ ያቀረቡት ዓቃቤሕግ ድርጊቱን ፈጽመዋል ባላቸው ሌሎች ግለሰቦች ላይ ባስከፈተው የወንጀል ክስ መዝገብ ላይ በመሆኑ፤ የመዝገቡ ተከሳሾች እንዲከላከሉ ብይን ከተሰጠ በኋላ ባለመቅረባቸው ፖሊስ ባቀረባቸው ጊዜ የማንቀሳቀስ መብት ተጠብቆ መዝገቡ በትዕዛዝ የተዘጋ በመሆኑ፤ ዓቃቤሕግ ይህን ትዕዛዝ ያስለወጠ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃም ሆነ ያቀረበው ክርክር የሌለ በመሆኑ እና የአሁን አመልካች በወንጀል ክሱ ላይ ተከሳሽ አለመሆኑ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ከላይ በተገለጸው መዝገብ የሰጠው ውሳኔ ሙሉ ለሙሉ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ገዢ ውሳኔ አድርጎ በመውሰድ ጉዳዩን ከመወሰን ይልቅ እነኚህን ሁኔታዎች ታሳቢ በማድረግ ኤግዚቢትን በሚመለከት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕጉ ላይ ከተደነገጉት ድንጋጌዎች እና አመልካች ካላቸው የንብረት መብት ጋር በማገናዘብ መወሰን ተመራጭ ሆኖ አግኝተነዋል።

በወንጀል ክስ ላይ ኤግዚቢት ሆነው በቀረቡ ማናቸውም ነገሮች ላይ የፍ/ቤቱ መዝገብ ሹም ቁጥር እና ምልክት በማድረግ በተጠበቀ ስፍራ የሚያስቀምጣቸው መሆኑን የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 97 ድንጋጌ ላይ የተመለከተ ሲሆን ይህም ሀላፊነት በመሠረታዊነት የፍ/ቤቶች ሀላፊነት መሆኑን ከድንጋጌው ይዘት መገንዘብ ይቻላል። በዚህ አግባብ የተመዘገቡት እና የተቀመጡ ኤግዚቢቶች ነገሩ በሚሰማበት ዕለት ከሳሽ በሆነው ዓቃቤሕግ ለፍ/ቤቱ መቅረብ ያለባቸው ስለመሆኑም የዚሁ ሕግ ቁጥር 124/2 ድንጋጌ ይዘት ያስገነዝበናል።

ከላይ በተቀመጡት ድንጋጌዎች አግባብ ኤግዚቢት ሆኖ የቀረበው ማናቸውም ነገር በመንግስት ሊወረስ የሚገባ ስለመሆኑ ወይም ለባለንብረቱ ሊመለስ የሚገባ ስለመሆኑ ፍ/ቤቱ በወንጀሉ

ጉዳይ ላይ ውሳኔ ሲሰጥ አብሮ የሚወሰን ወይም እንደአስፈላጊነቱ በወንጀሉ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በሚቀርብ አቤቱታ መነሻነት ትዕዛዝ የሚሰጥበት ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ ዓቃቤሕግ በመዝገቡ ተከሳሾች ላይ ያቀረበው ክስ ታይቶ ተከሳሾቹ እንዲከላከሉ ብይን ከተሰጠ በኋላ ተከሳሾች ባለመቅረባቸው ምክንያት የማንቀሳቀስ መብቱ ተጠብቆ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ዓቃቤሕግ ይህን ትዕዛዝ ያስለወጠ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃም ሆነ ክርክር አላቀረበም፤ በሌላ በኩል ተከሳሾችን ለማቅረብ ጥረት እያደረገ ስለመሆኑም በመግለጽ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ ከሳሽ የሆነው ዓቃቤሕግ ይህን ባለማድረጉ ምክንያት ተከሳሾች ባለመቅረባቸው የተዘጋው የወንጀል መዝገብ ተንቀሳቅሶ ጉዳዩ መቼ ውሳኔ እንደሚያገኝ አይታወቅም፡፡ ይህም በወንጀሉ ጉዳይ ተከሳሽ ያልሆኑት አመልካች ተሸከርካሪ እስከመቼ ድረስ በኤግዚቢትነት ተይዞ ይቆያል? የሚለውን መሠረታዊ ጥያቄ የሚያስነሳ ነው፡፡

በሌላ በኩል በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 40/1 ማናቸውም ኢትዮጲያዊ ዜጋ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ የተከበረለት መሆኑ፤ ይህም መብት በሌላ ሁኔታ በሕግ እስካልተወሰነ ጊዜ ድረስ ንብረት የመያዝ እና በንብረቱ የመጠቀም ወይም የሌሎችን ዜጎች መብቶች እስካልተቃረነ ጊዜ ድረስ ንብረትን የመሸጥ፤ የማውረስ ወይም በሌላ መንገድ የማስተላለፍ መብቶችን የሚያካትት መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ከሳሽ የሆነው ዓቃቤሕግ ተከሳሾች እንዲከላከሉ ብይን ከተሰጠ በኋላ ባለመቅረባቸው ምክንያት መዝገቡን በመዝጋት የተሰጠውን ትዕዛዝ እስካላስለወጠ ወይም ተከሳሾችን አፈላልጎ ለማግኘት ተገቢውን ጥረት አድርጎ በመዝገቡ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥ ባላደረገበት ሁኔታ ኤግዚቢት ሆኖ የተያዘው የአመልካች ተሸከርካሪ ሊለቀቅ አይገባም በማለት የሚያቀርበው ክርክርም ሆነ ፍ/ቤቱ የኤግዚቢት ጉዳይ ተነጥሎ ውሳኔ ሊሰጥበት አይችልም ሲል የደረሰበት መደምደሚያ የአመልካች ተሸከርካሪ ገደብ ለሌለው ጊዜ በሌላ አካል እጅ እንዲቆይ የሚያደርግ ነው፡፡ ይህም አመልካች በሕገመንግስቱ በተከበረላቸው የንብረት መብት መሠረት በንብረታቸው እንዳይገለገሉ የማድረግ ውጤት ያለው እና ይብዛም ይነስም ንብረቱ በሐገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ሊኖረው በሚገባ ድርሻ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚፈጥር ነው፡፡ ስለሆም እነኚህን ሁኔታዎች ታሳቢ በማድረግ ኤግዚቢት ሆኖ የተያዘው የአመልካች ንብረት የሆነው የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3- 49426 የሆነው ተሸከርካሪ ለአመልካች እንዲመለስ ማድረግ ፍትሐዊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በየደረጃው ያሉት የክልሉ ፍ/ቤቶችም ጉዳዩን በዚህ አግባብ በማየት መወሰን ሲገባቸው የኤግዚቢት ጉዳይ ብቻውን ተነጥሎ ውሳኔ ሊሰጥበት

አይችልም በማለት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል። ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል።

ዉሳኔ

1. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የወልመራ ፍ/ቤት በመ.ቁ 67564 ጥቅምት 23 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 18026 ሕዳር 13 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 292814 ታሕሳስ 18 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 306137 ሚያዝያ 08 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል።
2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት የአመልካች ንብረት የሆነው የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3- 49426 የሆነው ተሽከርካሪ ለአመልካች ይመለስ።

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል። ይመለስ።

የማይነበብ የሦስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የልዩነት ሃሳብ

እኛ ስማችን በተራ ቁጥር 3 እና 5 ስር የተሰየምነው የችሎት ዳኞች በዚህ መዝገብ አብላጫ ድምጽ ኤግቢት ሊመለስ ይገባል በሚል የሰጠው ውሳኔ አስቀድሞ ከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/126017 ላይ ተሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም ጋር የሚቃረን ሆኖ ስላገኘነው እንደ፣ሚከተለው የልዩነት ሃሳባችንን ገልፀናል።

በቀረበው ጉዳዩ እያከራከረ ያለው ተሽከርካሪ በኤግዚቢትነት የተያዘው በወንጀል ጉዳይ ክስ ቀርቦ መሆኑ ተረጋግጧል። በወንጀል የተከሰሱ ሰዎች ላይ ክርክር ቀጥሎ ፍርድ ያልተሰጠና ይልቁንም የወንጀሉ ጉዳይ ለጊዜው የተቋረጠ ሲሆን የተቋረጠበት ምክንያት ደግሞ ተከሳሾች ባለመገኘታቸው ነው።

የአብላጫ ድምጽ አንድ ወንጀል የወንጀል ጉዳይ ለጊዜው በሚቋረጥበት ጊዜ የወንጀል ጉዳይ መቼ ተንቀሳቅሶ ውሳኔ እንደሚሰጥበት የማይታወቅ መሆኑን በማንሳት ፣ ዐቃቤ ሕግም

ተከሳሾችን አቅርቦ ለጉዳዩ እልባት እንዲሰጥበት እስካላደረገ ድረስ ኤግዚቢት ተይዞ ሊቆይ አይገባም በሚል ነው፡፡

በትክክልም አንድ የወንጀል ጉዳይ ለጊዜው ሲቋረጥ መቼ መዝገብ ቀርቦ መቼ ውሳኔ ተሰጥቶ ኤግዚቢት የሆነ ንብረት ሊለቀቅ ይችላል የሚለው በሚቀርቡ ጉዳዮች የየመዛግብቱ ችግር ሆኖ የቆየ በመሆኑ አንድ መፍትሄ ሊያገኝ የሚገባው በመሆኑ የአብላጫው ድምጽ አቋምን እኛም የምንጋራው ቢሆንም አስቀድሞ ከላይ በተጠቀሰው የሰበር መዝገብ ላይ ግን አንድ በወንጀል ጉዳይ ኤግዚብት የተደረገን እና በቁጥጥር ስር የዋለን ንብረት የፍርድ ውሳኔ ሊያገኝ የሚገባው የወንጀሉ ክስ ላይ አስቀድሞ እልባት ሲያገኝ ነው በሚል የሠጠው ውሳኔ በዚህ መዝገብ ለቀረበውም ጥያቄ አግባብነት ያለው በመሆኑ ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ ውሳኔ ፀንቶ ባለበት መዝገብ ኤግዚቢት እንዲመለስ የቀረበውን ክስ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚገባው ባለመሆኑ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ሊፀና ይገባው ነበር ብለን ከአብላጫው ድምጽ በሃሳብ ተለይተናል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት

የኢትዮጲያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት

የመ.ቁ.203253

የካቲት 25/2014 ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡ አቶ በሪሁን አጥናፍ አልተጠሩም

ተጠሪ፡ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የቀረበ የለም

አቤቱታ አቅራቢ፡ መኳንንት ቢምር

መዝገቡ በውሳኔ ከተዘጋ በኋላ ለችሎት ሊቀርብ የቻለው አቤቱታ አቅራቢ ህዳር 27/2014 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ በዚህ መዝገብ ላይ አመልካችን አስምልክቶ መስከረም 28/2014 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ እርሱንም የሚጠቅመው መሆኑን ገልፆ የውሳኔው ውጤት በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 196(2) መሰረት ተፈፃሚ እንዲሆንለት በማመልከቱ ምክንያት ነው፡፡ የቀረበው አቤቱታ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ክርክሩ የተጀመረው የአሁን ተጠሪ በዚህ መዝገብ ላይ ቀድሞ ውሳኔ ያገኘውን አመልካችን እና የአሁን አቤቱታ አቅራቢን ጨምሮ በሶስት ተከሳሾች ላይ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ህግ አንቀፅ 32(1(ሀ)) እና 669(1(ለ)) ድንጋጌን ጠቅሶ በሰሜን አቼፈር ወረዳ ፍ/ቤት ባቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ በቀረበው ክስ ውስጥ የአሁን አቤቱታ አቅራቢ 3ኛ ተከሳሽ ነበር፡፡ የክሱም ጭብጥ አቤቱታ አቅራቢው ከስር ፍርድ ቤት 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ከነበሩት ጋር በመሆን የተጠቀሰውን የወንጀል ህግ ድንጋጌን ተላልፈው መስከረም 28 ለ29 ቀን 2013 ዓ.ም አጥቢያ ከሌሊቱ 7፡30 ሰዓት አካባቢ የተለየ ጠባቂ የሌለውን እና ለይስማዕላ ከተማ ህዝብ የውሃ አገልግሎት የሚሰጠውን ግምቱ ብር 160,000 (አንድ መቶ ስልሳ ሽህ ብር) የሆነ የውሃ ኮንትሮል ፓኔል ቦርድ ሰርቀው ወስደው በተደረገ ጥቆማ 1ኛ ተከሳሽ የነበረው ተይዞ ወደተከራየው ቤት ሲወሰድ 1ኛ ተከሳሽ ቤቱን እንዲከፍት ሲጠየቅ “ቁልፍ ጠፍቶብኛል” በማለቱ የቤቱ ቁልፍ ተሰብሮ ሲገባ ከአመልካች እና የአሁን አቤቱታ አቅራቢ ጋር እቃው በቤቱ ውስጥ የተገኘ በመሆኑ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ከባድ የስርቆት ወንጀል ፈፅመዋል የሚል ነው፡፡

ተከሳሾቹም ቀርበው ክሱን ሳይቃወሙ 1ኛ ተከሳሽ የነበረው የተከሰሰበትን የስርቆት ወንጀል ብቻውን ስለመፈፀሙ ገልፆ ድርጊቱን እና ጥፋተኝነቱን በሙሉ በማመኑ በሰጠው የእምነት ቃል ብቻ ጥፋተኛ ተብሏል፡፡ አመልካች እና አቤቱታ አቅራቢ ደግሞ በቤቱ የተገኙት በእንግድነት ሲሆን የስር ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽ የነበረው ቤቱን ቆልፎባቸው በመሄዱ ምክንያት ሲጠብቁት በቤቱ ውስጥ ከመገኘታው ውጭ ክስ የቀረበበትን ወንጀል ያልፈፀሙ መሆኑን ገልፀው ክደው ተከራክረዋል፡፡

በዚሁ ምክንያት አመልካች እና አቤቱታ አቅራቢን አስመልክቶ የዐቃቤ ህግ ምስክሮች ከተሰሙ በኋላ እንዲከላከሉ ሲነገራቸው መከላከያ ማስረጃ የሌላቸው መሆኑን በመግለፃቸው ታልፎ በተከሰሱበት አንቀፅ ስር ጥፋተኛ ተብለው እያንዳንዳው በ6(ስድስት) ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ተወስኗል፡፡ ይኸው ውሳኔ በየደረጃ ባሉት የክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶችም ፀንቷል፡፡

በዚህ መዝገብ ላይ አመልካች የሆነው ይህንኑ ውሳኔን በመቃወም ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርቦ የግራ ቀኙ ክርክር ከተሰማ በኋላ መስከረም 28/2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ አመልካች በነፃ ተሰናብቷል፡፡ በአሁን አቤቱታ አቅራቢ የቀረበው ጥያቄም የስር ፍርድ ቤቶን ውሳኔ ተቃውሜ የሰበር አቤቱታ ያላቀረበኩ ቢሆንም

በዚህ መዝገብ ላይ አመልካችን አስመልክቶ የተሰጠው ውሳኔ የሚጠቅመኝ በመሆኑ ውጤቱ ለእኔም ተፈፃሚ ሊሆን ይገባል የሚል ነው፡፡ ተጠሪ በዚህ ጥያቄ ላይ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሰረት ሁለት ጊዜ ተለዋጭ ቀጠሮ ጠይቆ ጥር 27/2014 ዓ.ም ከተያዘው የምርመራ ቀን በፊት የጽሑፍ መልሱን ከመዝገብ እንዲያያይዝ የታዘዘ ቢሆንም አላቀረበም፡፡

ችሎቱም የቀረበውን አቤቱታ ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ በመሰረቱ ስልጣን ባለው የዳኝነት አካል በወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣ ሰው ጥፋተኛ ከተባለበት ወንጀል በነፃ ሊሰናበት አልያም በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ሊሻሻል የሚገባው ጥፋተኛ የተባለው ሰው የሥነ ሥርዓት ህጉ በሚፈቅደው መሰረት የይግባኝ ቅሬውን አቅርቦ በሚያሰማው መከራከሪያ መነሻነት ስለመሆኑ በወንጀል ጉዳይ የይግባኝ ክርክር ስለሚመራበት ሁኔታ ከሚደነግገው የወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት አምስተኛ መፀሐፍ አንደኛ አንቀፅ ከቁጥር 181 እስከ 195 ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

መርሆው ይህ ቢሆንም በስር ፍርድ ቤት በጋራ ከተከሰሱ ሰዎች ውስጥ አንዱ ይግባኝ ጠይቆ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ይግባኝ ባዩ የሚጠቅም በሆነ ጊዜ ከይግባኝ ባይ ጋር በጋራ የተከሰሱት ሰዎችም ይግባኝ ቢሉ ኖሮ በተሰጠው ውሰኔ ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችሉ የነበረ ለመሆኑ ከተረጋገጠ ውሳኔው ይግባኝ ላላቀረቡት ተከሳሾችም ጭምር ተፈፃሚ መሆን የሚገባው ስለመሆኑ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 196(1(ሀ) እና (ለ)) ይደነግጋል፡፡ በወንጀል ጥፋተኛ የተባለ ሰው ሌላ ሰው በተከራከረበት ጉዳይ በተሰጠ ውሳኔ ተጠቃሚ እንዲሆን በዚህ ድንጋጌ ስር የተመለከተው ሁኔታ ከላይ ለተጠቀሰው መርሆ ልዩ ሁኔታ/በስተቀር/ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡ የዚህ ቁጥር ድንጋጌ በሰበር ሰሚ ችሎት ታይቶ ውሳኔ ላገኘ ጉዳይም ተፈፃሚነት ያለው ለመሆኑ ይኸው ችሎት ከዚህ ቀደም በሰ/መ/ቁ/96378 እና 101056 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡

በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 196 ስር የተመለከተው ድንጋጌው ልዩ ሁኔታ/በስተቀር/ በመሆኑ ተፈፃሚ የሚሆንበት መመዘኛዎች ተለይተው ተቀምጠዋል፡፡ አንደኛው አመልካቹ ባልተከራከረበት ጉዳይ የተሰጠው ውሳኔ እርሱን የሚጠቅመው ሆኖ ሲገኝ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ አመልካቹ ይግባኝ ቢል/የሰበር አቤቱታ አቅርቦ ቢሆን/ ኖሮ በተሰጠው ፍርድ/ውሳኔ ተጠቃሚ ሊሆን ይችል የነበረ ከሆነ የሚሉት ናቸው፡፡ በእርግጥ አመልካቹ ተከራካሪ ባልሆነበት የተሰጠው ውሳኔ ለእርሱ ጠቃሚ የሚሆነው በምን ሁኔታ እንደሆነ ድንጋጌው የሚገልፀው ነገር

የለም፡፡ ሆኖም ድንጋጌው ልዩ ሁኔታ እንደመሆኑ መጠን ስለይግባኝ ክርክር አመራር የተቀመጠውን መርሆ በማያፋልስ መልኩ በጠባቡ ሊተረጎም እንደሚገባ ይታመናል፡፡

በዚሁ መሰረት አንድ ሰው በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 196 መሰረት ቀድሞ በተሰጠ ፍርድ/ውሳኔ/ ተጠቃሚ ለመሆን የሰበር ተከራካሪውም ሆነ የሰበር አቤቱታ ያላቀረበው ሰው ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡበት ወንጀል አንድ ሲሆን እና ውሳኔው የግል ሁኔታን መሰረት ያደረገ ሳይሆን በቀጥታ ከህግ አተረጓጎም እና አተገባበር ጋር የተያያዘ ሊሆን ይገባል፡፡ በሌላ መልኩ በወንጀል የተፈረደባቸው ሰዎች በርካታ ቢሆኑም ጥፋተኛ የተባሉበት ወንጀል አንድ ካልሆነ ወይም ወንጀሉ አንድ ቢሆንም እንኳን የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔው የግል ሁኔታን መሰረት በማድረግ የተሰጠ ከሆኑ ከእነርሱ መሀል አንዱ ይግባኝ/የሰበር አቤቱታ/ አቅርቦ በእርሱ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ይግባኝ ላላለው ፍርደኛ ተፈፃሚ ሊሆን አይገባም ማለት ነው፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ አመልካች እና አቤቱታ አቅራቢ የተከሰሱት በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆኑ ከስር ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽ ጋር በመሆኑ ከባድ የስርቆት ወንጀል ፈፅመዋል በሚል ነው፡፡ በዚህ የወንጀል ድርጊት ውስጥ የአመልካችም ሆነ የአሁን አቤቱታ አቅራቢ የወንጀል ተሳትፎ ተብሎ የተገለፀው ተሰረቀ ከተባለው ዕቃ ጋር በተያያዘ የስር ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽ የነበረው በጥርጣሬ ተይዞ ለብርበራ ወደ ቤቱ ሲወሰድ የአሁን አመልካች እና አቤቱታ አቅራቢ በቤቱ ውስጥ በሩ በውጭ ተቆልፎባቸው ተገኝተዋል የሚል ነው፡፡ ቀድሞ በተሰጠው ውሳኔ ላይ አመልካች በነዛ የተሰናበተውም የቀረበው ክስ አመልካቹ ተሰረቀ ከተባለው ዕቃ ጋር ቤት ውስጥ ተቆልፎበት ከመገኘቱ ውጭ በወንጀል ድርጊቱ ውስጥ የአመልካቹ የወንጀል ተሳትፎ ምን እንደነበር ክስ ከቀረበበት የወንጀል ህጉ ወንጀል ማቋቋሚያ ፍሬ ነገር አንፃር ተለይቶ የተጠቀሰ ነገር የለም፤ በማስረጃም ያልተረጋገጠ በመሆኑ ወንጀል ተፈፅሟል ለማለት አይቻልም በሚል ምክንያት ነው፡፡ ይህ ውሳኔ የግል ሁኔታን መሰረት ያደረገ ሳይሆን አመልካችም ሆነ የአሁን አቤቱታ አቅራቢ ፈፅመዋል ከተባሉት የወንጀል ድርጊት አለመኖር ጋር የተያየዘ ነው፡፡ አመልካችም ሆነ አቤቱታ አቅራቢ ፈፅመዋል ተብሎ በክሱ ዝርዝር የተመለከተው ተግባር አንድ ዓይነት በመሆኑ እና ለቀደመው ውሳኔ መሰረት የሆነው ወንጀል አልተፈፀመም የሚል በመሆኑ ውሳኔው ለአሁን አቤቱታ አቅራቢም የሚጠቅመው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

1. በዚህ መዝገብ ላይ መስከረም 28 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/03-99294 ላይ ታህሳስ 13/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ በመሻር የተሰጠው ውሳኔ ለአሁን አቤቱታ አቅራቢ አቶ መኳንንት ቢምር የሚጠቅም ሆኖ በመገኘቱ ውሳኔው በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 196(1(ሀ) እና (ለ)) ተፈፃሚ እንዲሆንለት ተደርጎ ከቀረበበት ክስ በነፃ ተሰናብቷል፡፡
2. በውሳኔ ተራ ቁጥር 1 ስር በተሰጠው ውሳኔ መሰረት አቤቱታ አቅራቢ አቶ መኳንንት ቢምር በሌላ ወንጀል የማይፈለግ መሆኑን አረጋግጦ በአስቸኳይ ከእስር እንዲለቀው ለሚገኝበት የክልሉ ማረሚያ ቤት አስተዳዳር ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

አ/መ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ልዩ ልዩ

የኢትዮጲያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰበር መዝገብ ቁጥር 208865

የካቲት 29 **ቀን** 2014 **ዓ/ም**

ዳኞች ፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- ወ/ሮ እቴነሽ መለሰ-መከተ አዘናው ተወካይ- ቀርቧል

ተጠሪ፡- ማራናታ የቤት ህብረት ሥራ ማህበር-አልቀረቡም

ለምርመራ ተቀጥሮ የነበረው መዝገብ ተመርምሮ ቀጣዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

የሰሜን ሸዋ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 133343 **ህዳር** 25 **ቀን** 2013 **ዓ/ም በዋለው ችሎት ተጠሪ አመልካችን ከማኅበሩ ማሰናበቱ አግባብ ነው በማለት የሰጠውን ውሳኔ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደብረ ብርሀን ምድብ በመዝገብ ቁጥር** 0121252 **ጥር** 28 **ቀን** 2013 **ዓ/ም በዋለው ችሎት ማጽናቱ እንዲሁም ሰበር አጣሪ ችሎት መጋቢት** 8 **ቀን** 2013 **ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር** 103071 **የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ሰህተት አልተገኘበትም በማለት የአመልካችን**

የሰበር አቤቱታ ወድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት በሰበር ለማሳረም አመልካች ሰኔ 7 ቀን 2013 ዓ/ም የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ መዝገቡ ለችሎት ቀርቧል፡፤

ጉዳዩ አመልካችን ከተጠሪ ማህበር አባልነት በማሰናበት የተሰጠ ውሳኔ እንዲሰረዝ ለሸዋሮቢት ከተማ አስተዳደር ወረዳ ፍርድ ቤት የቀረበ ክስ ሆኖ አመልካች በከሰሻነት ተጠሪ ደግሞ በ1ኛ ተከሳሽነት ተከራክረዋል፡፡ የክስ አቤቱታው ይዘትም፡- አመልካች ተወልደው ለ17 ዓመታት በመምህርነት ባገለገሉበት ሸዋሮቢት ከተማ የቤት መስሪያ ቦታ ስላልነበራቸው በመምህርነታቸው በተጠሪ ማህበር ተደራጅተው ለአምስት ዓመት የቤት መስሪያ ቦታ ለማግኘት በመጠባበቅ ላይ እያሉ ባለቤታቸው የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ወንጀል መከላከል ባልደረባ በመሆናቸው ከጥቀምት ወር 2012 ዓ/ም ከትዳር አጋራቸው ወደሉበት አዲስ አበባ ከተማ ትምህርት ቢሮ ዝውውር ተደርጎላቸው ፤ በከተማው በማስተማር ላይ ቢሆኑም ዋና መኖሪያቸው ሸዋሮቢት ከተማ ሆኖ እያለ ፣ የአማራ ክልል ባወጣው ደንብ ቁጥር 150/2000 እና መመሪያ ቁጥር 28/2009 አንድ መምህር ሲያስተምርበት ከነበረው ከተማ ወደ ሌላ ከተማ ሲዛወር ከማኅበር እንደሚሰናበት ባልተደነገገበት ሁኔታ እንዲሁም የሥር 2ኛ ተከሳሽ አመልካችን ከማኅበር አባልነት ለማሰናበት ስልጣን ሳይኖረው አመልካች ወደ አዲስ አበባ ከተማ ስለተዛወሩ ተጠሪን ከማህበሩ እንዲያሰናብት የፃፈለትን ደብዳቤ መሰረት አድርጎ ተጠሪ አመልካችን ከማህበሩ ማሰናበቱን የገለፀላት መሆኑን በመግለፅ ፤ መደበኛ ነዋሪነቷ ሸዋሮቢት ሆኖ እያለ እና በአዲስ አበባ ከተማ የመኖሪያ ቤት ተጠቃሚ እንዳልሆነች በማስረጃ ተረጋግጦ ባለበት ተጠሪ አመልካች ከማህበር እንድትሰናበት መወሰኑ አላግባብ ስለሆነ ውሳኔው ተሰርዞ አመልካች ወደ ማኅበሩ እንድትመለስ እንዲወሰን ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪም በመልሱ፡- አመልካች የማኅበሩን የስራ ክልል ለቃ ስለሄደች በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 14(4) መሰረት ከማኅበሩ እንድትሰናበት የሥር 2ኛ ተከሳሽ እንዳሳወቃቸው ለአመልካች በማሳወቅ ፤ ከ23 የማኅበሩ አባላት አራቱ ብቻ ባልተገኙበት ምልዐተ ጉባዔ ተሟልቶ አመልካች ከማኅበሩ እንድትሰናበት የተላለፈ ውሳኔ በመሆኑ አመልካች ያቀረቡት ክስ ውድቅ ሆኖ ተጠሪ ከማኅበሩ እንድትሰናበት ያስተላለፈው ውሳኔ ተቀባይነት አግኝቶ እንዲፀና ጠይቀዋል፡፡ የሥር 2ኛ ተከሳሽም አመልካችን ከማኅበር ስላላሰናበተ የቀረበበት ክስ ተገቢነት የለውም በማለት ተቃውሞ በፍሬ ነገሩ ላይም መልስ ሰጥቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም በሥር 2ኛ ተከሳሽ የተነሳውን መቃወሚያ በመቀበል ከክርክሩ አሰናብቶ በፍሬ ነገሩ ላይ ግራቀኙን

አከራክሮ እና የአመልካችን ምስክሮች ሰምቶ በሰጠው ውሳኔ ፤ አባላት ከማኅበሩ የሚሰናበቱበት ምክንያት በአዋጁ የተሸፈነ ሲሆን በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 14(4) ሥር የተቀመጠው አንድ አባል የማኅበሩን የሥራ ክልል ለቆ ከሄደ ከማኅበሩ ይሰናበታል በማለት የሚደነግግ ቢሆንም በአዋጁ ቁጥር 64(2) ሥር ማንኛውም ከአዋጁ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ፣ ደንብ ፣ መመሪያ እና የተለምዶ አሰራር በአዋጁ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት እንደማይኖረው የደነገገ በመሆኑ የማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 14(4) ሥር የተመለከተው አዋጁን የሚቃረን በመሆኑ ተፈፃሚነት ሊኖረው የማይገባ ሲሆን ፤ መተዳደርሪያ ደንቡ አዋጁን አይቃረንም ቢባል እንኳን አመልካች የምትተዳደርበት ንብረቷ ፣ መኖሪያዋ እና ማህበራዊ ህይወቷ ያለው ሸዋሮቢት ከተማ መሆኑ በዝውውር ምክንያት የሥራ ቦታዋ አዲስ አበባ ቢሆንም እየተመላለሰች የምትሰራ መሆኑ በማስረጃ ስለተረጋገጠ እንዲሁም አመልካች ከማኅበሩ እንድትሰናበት የተያዘው ቃለጉባኤ አባላት ሳይሰባሰቡ በአንድ ሰው ብቻ ቀደም ብሎ የተዘጋጀ በጉዳዩ ላይ አባላት የሰጡትን ሃሳብ ያላካተተ በመሆኑ አመልካች ከማኅበሩ መሰናበቷ አግባብ አይደለም በማለት ወስኗል።

ጉዳዩን ተጠሪ ባቀረቡት ይግባኝ የተመለከተው የሰሜን ሸዋ ዞን መስተዳድር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመምህራን መኖሪያ ቤት መሥሪያ ቦታ አሰጣጥና የተገነቡ ቤቶች ድልድል ማስፈፀሚያ ደንብ ቁጥር 150/2009 ተፈፃሚነት ወሰኑ በክልሉ በመንግስት ትምህርት ቤቶች በማስተማር ሥራ ላይ ተሰማርተው ለሚገኙ መምህራን ብቻ ሆኖ የደንቡ መሰረታዊ ዓላማም በመንግስት ትምህርት ቤቶች ለሚያስተምሩ መምህራን ምቹ ሁኔታን በመፍጠር የመምህራን ፍልሰት በመቀነስ የትምህርት ጥራትን ማረጋገጥ መሆኑን መረዳት የሚቻል ሲሆን ፤ አመልካች አዲስ አበባ ከተማ ተዛውራ የምትሰራ መሆኑ በሯሷ ምስክሮች ጭምር የተረጋገጠ በመሆኑ ፤ በአማራ ክልል ውስጥ በሚገኙ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ለሚያስተምሩ መምህራን በልዩ ሁኔታ ተጠቃሚ ለማድረግ በወጣው የሕግ ማዕቀፍ መሰረት ለመጠቀም የምታቀርበው ክርክር ተገቢነት የሌለው ሆኖ ፤ ተጠሪ አመልካችን ከማኅበሩ ያሰናበተበት አግባብ የማኅበሩን ሕገ ደንብ እና ሌሎች ሕጎችን መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር ስንብቱ ሕገ ወጥ ሊባል የሚችል አይደለም በማለት የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ የሻረ ሲሆን ፤ ይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም አመልካች በመምህርነቷ ከሸዋሮቢት ወደ አዲስ አበባ ከተማ ዝውውር የተደረገላት መሆኑ የታመነ ፍሬ ነገር በመሆኑ መምህርነት የሙሉ ጊዜ ሥራ በመሆኑ ፤ ምንም እንኳን የአመልካች ምስክሮች ሸዋሮቢት ከተማ ለቃ እንዳልሄደች እና እንደምትመላለስ የገለፁ ቢሆንም ፤ ከቦታ ርቀት አንፃር እና አመልካች ወደ አዲስ አበባ ለመዛወር ከጠየቀበችበት

ምክንያት አንባር አሳማኝ ባለመሆኑ እና የፍትሐብሔር ሕጉን ቁጥር 185 ድንጋጌን ሊያስነሳ የሚችል አጠራጣሪ የመኖሪያ ስፍራ ስለሌለ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 183 ድንጋጌ መሰረት የጉዳዮቿ እና ጥቅሞቿ ዋና ስፍራ የሙሉ ጊዜ ሥራዋን የምትሰራበት አዲስ አበባ ከተማ ሲሆን ከተጠሪ የሥራ ክልል የለቀቀች በመሆኑ የማሕበሩ መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 9(2) እና 14(4) ሥር የተደነገገው በመተላለፍ ግዴታዋን ባለመወጣቷ የተሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት የሰሜን ሸዋ ዞን መስተዳድር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔን ያፀና ሲሆን ፤ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አጣሪ ችሎቱም የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አልተገኘበትም በማለት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ሰርዞታል፡፡

አመልካች በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ በሰበር ለማሳረም ያቀረቡት አቤቱታ ይዘት፡- አመልካች በሳምንት አልያም በአስራ አምስት ቀን የምትመላለስ መሆኑ ፤ ማሕበራዊ ሕይወቷ ፣ ዕድሯ እና የቤት ንብረቷ በሸዋሮቢት ከተማ እንደሚገኝ ፣ ከአዲስ አበባ ከተማ የቤት ተጠቃሚ ያለመሆኗ ተረጋግጦ እያለ የፍትሐብሔር ሕጉን ቁጥር 185 ድንጋጌ በሚፃረር መልኩ የሥራ ዝውውር በማድረጓ ብቻ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 90 ፣ 32 እና 41 በሚቃረን መልኩ ፤ መደበኛ መኖሪያዋን እንደቀየረች መቆጠሩ ፤ የማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ በጠቅላ ጉባኤ ያልፀደቀ ረቂቅ ሆኖ ተፈፃሚነት የሌለው ከመሆኑም በላይ በአዋጅ ቁጥር 220/2007 ቁጥር 18 ሥር ከተደነገገው ውጭ አንድ አባል የማህበሩን የሥራ ክልል ለቆ ከሄደ እንደሚሰናበት ተጨማሪ መስፈርት መደንገጉ አዋጁን የሚቃረን በመሆኑ ተፈፃሚነት የሌለው ሆኖ ሳለ የስር ፍርድ ቤቶች ለውሳኔያቸው መሰረት ማድረጋቸው ፤ አመልካች በመምህርነት ሳይሆን እንደማንኛውም ነዋሪ ቦታ ለማግኘት ተደራጅታ ሁሉን ነገር ብታሟላም መንግስት በጊዜ ቦታውን ባለማቅረቡ ምክንያት የቤት መስሪያ ቦታ ሳታገኝ የሥራ ዝውውር በማድረጓ ተወልዳ አድጋ ለ17 ዓመት በመምህርነት ባገለገለችበት ከተማ የቤት መስሪያ ቦታ እንዳታገኝ ከተጠሪ ማኅበር መሰናበቷ መሰረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ውሳኔው ተሽሮ የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ ፀንቶ ወደ ማኅበሩ እንድትመልስ እንዲወሰን አመልክተዋል፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎቱ አመልካች በሥራ ዝውውር እንጅ መደበኛ የመኖሪያ አድራሻቸውን ያልቀየሩ ማኅበራዊ ኑሮአቸው ሸዋሮቢት ከተማ መሆኑን የሸዋሮቢት ከተማ አስተዳደር ወረዳ ፍርድ ቤት በሰነድ እና በሰው ማስረጃ አጣርቶ የሰጠው ውሳኔ ጉዳዩን በይግባኝ ያዩት ፍርድ ቤቶች አመልካች ከማኅበሩ ሊሰናበቱ ይገባል ያሉበትን አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 220/2007 ዓላማ አንፃር መጣራት አለበት በማለቱ ተጠሪ በሰጠው መልስ፡- አመልካች በቋሚነት በዝውውር አዲስ አበባ

ከተማ በመምህርነት እየሰራች ለመሆኑ በአቤቱታዋ ጭምር አረጋግጣ ባለችበት ሁኔታ አድራሻዬ ሸዋሮቢት ነው የሚለው መከራከሪያ አግባብነት የሌለው ከመሆኑም ባሻገር የመንግስት ሰራተኞች ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ቦታ አንድ መኖሪያ እንደሚኖራቸው የሚደነግገውን የፍትሐብሔር ሕጉን ቁጥር 179 የሚቃረን ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ፤ የማኅበሩ የሥራ ክልል ሸዋሮቢት ከተማን ለቃ በዝውውር አዲስ አበባ ከተማ በቋሚነት እየሰራች በመሆኑ በማኅበሩ ደንብ መሰረት በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ከአባልነት መሰናበቷ ሕጋዊ ሆኖ እያለ አመልካች ያቀረበችው የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት ሊኖረው የማይገባ መሆኑን ፤ አባላት በበቂ ምክንያት ከማኅበር ሊሰናበቱ እንደሚችል በአዋጁ የተቀመጠ ሲሆን ለማሰናበት የሚያበቁት ምክንያቶች ደግሞ በማኅበሩ ደንብ ላይ በግልጽ በመቀመጣቸው በአዋጅ ቁጥር 220/2007 አንቀጽ 18 መሰረት ጠቅላላ ጉባኤ አባላትን ሲያሰናብት የሰሩትን ጥፋት በዝርዝር ማስቀመጡ አስፈላጊ በመሆኑ አመልካች በጠቅላላ አባላት በፀደቀው ደንብ መሰረት በበቂ መክንያት ከማኅበሩ ተሰናብታ እያለ የማኅበሩ ደንብ ቁጥር 14(4) ድንጋጌ የአዋጅ ቁጥር 220/2007 ቁጥር 18 ድንጋጌን እንደሚቃረን የቀረበው መከራከሪያ የአዋጁንና የደንቡን ዓላማ ከግምት ያስገባ አለመሆኑን ፤ አመልካች ከአማራ ክልል ውጭ በመምህርነት እየሰራች የደንብ ቁጥር 150/2009 ቁጥር 3 እና 4 ድንጋጌን በሚቃረን መልኩ ወደ ማኅበር አባልነት ለመመለስ የምታቀርበው አቤቱታ አግባነት የሌለው መሆኑን ፤ በጠቅላላ ጉባዔ ፀድቆ እና አግባብ ባለው ባለሥልጣን ተመዝግቦ ለማኅበሩ ህጋዊ ሰርተፍኬት ተሰጥቶ ባለበት የማኅበሩን መተዳደሪያ ደንብ ረቂቂ ነው በማለት አመልካች የምታቀርበው መከራከሪያ ተገቢ ባለመሆኑ ይግባኝ ሰሚዎቹ የሥር ፍርድ ቤቶች የሸዋሮቢት ከተማ አስተዳደር ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን መሻራቸው የሚነቀፍ ባለመሆኑ ለሰበር ቅሬታው መሰረት የሆነው ውሳኔ ፀንቶ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ሆኖ ከወጪ እና ኪሳራ ጋር እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል። አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑ እንደሚከተለው ተመርምሯል። አመልካች ለ17 ዓመታት በመምህርነት ባገለገሉበት ሸዋሮቢት ከተማ የቤት መስሪያ ቦታ ስላልነበራቸው የአማራ ክልል ባወጣው ደንብ ቁጥር 150/2000 እና መመሪያ ቁጥር 28/2009 መሰረት አድርጎ በተጠሪ ማህበር ተደራጅተው ለአምስት ዓመት የቤት መስሪያ ቦታ ለማግኘት በመጠባበቅ ላይ እያሉ ባለቤታቸው የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ወንጀል መከላከል ባልደረባ በመሆናቸው የትዳር አጋራቸው ወደሉበት አዲስ አበባ ከተማ ትምህርት ቢሮ በጥቅምት ወር

2012 ዓ/ም ዝውውር ተደርጎላቸው በከተማው በማስተማር ላይ ቢሆኑም መደበኛ መኖሪያቸው ሸዋሮቢት ከተማ ሆኖ እያለ እና በአዲስ አበባ ከተማ የመኖሪያ ቤት ተጠቃሚ እንዳልሆኑ ተረጋግጦ እያለ ተጠሪን የሥር 2ኛ ተከሳሽ ከማህበሩ እንዲያሰናብት የፃፈለትን ደብዳቤ መሰረት አድርጎ ተጠሪ አመልካችን ከማህበሩ ማሰናበቱን አግባብ ባለመሆኑ ውሳኔው ተሰርዞ ወደ ማኅበር አባልነታቸው እንዲመለሱ እንዲወሰንላቸው ላቀረቡት ክስ ተጠሪ በሰጠው ምላሽ፡- የስራ ክልል ለቃ ስለሄደች በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 14(4) መሰረት ከማኅበሩ እንድትሰናበት የሥር 2ኛ ተከሳሽ እንዳሳወቃቸው ለአመልካች በመግለፅ ምልዐተ ጉባዔ ተሟልቶ አመልካች ከማኅበሩ እንድትሰናበት የተላለፈ ውሳኔ እንዲፀና ጠይቀዋል። አመልካች በተጠሪ ማኅበር የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታን ለማግኘት የተደራጁት በመምህርነት ባገኙት ልዩ መብት መሆን አለመሆኑ? በመምህርነት ያገኙት ልዩ መብት ነው ከተባለ በመምህርነት ሙያቸው የትዳር አጋራቸው ወደ አሉበት አዲስ አበባ ከተማ ዝውውር በማግኘታቸው ለመምህራን የተሰጠውን ልዩ መብት አላግባብ ተጠቅመዋል ተብሎ ከማኅበር አባልነታቸው ሊሰረዙ ይገባል? የሚሉትን ጭብጦች ለጉዳዩ ተገቢነት ካለው ሕግ አንፃር ማየት ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል። የመምህርነት ሙያ ለሀገር ሁለንተናዊ ዕድገት የሚጫወተው ቁልፍ ሚና ለማሳካት የበኩሉን ጉልህ አስተዋጽኦ የሚያበረክት በመሆኑ መምህራን የሚጠበቅባቸውን ሙያዊ ግዴታቸውን በተነቃቃ መንፈስ መወጣት እንዲችሉ ጥራት ያለው ትምህርት ለመስጠት በሙያው ብቃት ያላቸው መምህራን ፍልሰት ለመቀነስ የመኖሪያ አካባቢን በማመቻቸት ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮቻቸውን በማቃለል ቤተሰቦቻቸው እና መላው ህብረተሰቡ ለሙያው አዎንታዊ አመለካከት ኖሯቸው የበኩላቸውን ድጋፍ እንዲያደርጉ የህግ ማዕቀፍ አውጥቶ ተግባራዊ ማድረግ ታምኖበት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመምህራን መኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ አሰጣጥና የተገነቡ ቤቶች ድልድል ለማስፈፀም ደንብ ቁጥር 150/2009 የወጣ መሆኑን ደንቡ ያመለክታል። እነዚህ ለመምህራን የሚደረጉት ማትጊያዎች በሚያስተምሩት አካባቢ በመንግስት ወይንም በህዝብ ተሳትፎ የሚሰሩ ቤቶችን በነፃ ወይንም በተመጣጣኝ ኪራይ ማግኘት ፣ በሚያስተሚሩበት ቦታ ወይንም አካባቢ በሚገኝ ቀበሌ እና ከተማ የቤት መስሪያ ቦታ እንዲሰጣቸው ጥያቄ ባቀረቡ ጊዜ እንደማንኛው ዜጋ በማኅበር ተደራጅተው በህጉ የተመለከተውን መስፈርት አሟልተው የቤት መሥሪያ ቦታን ከአነስተኛ ፣ መካከለኛ እና ሜትሮፖሊታን ከተሞች ማግኘት የሚችሉ መሆኑን ከደንቡ ቁጥር 6 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል። መምህራን በሚሰሩበት ወረዳ ውስጥ ካሉት ከተሞች መካከል በመረጡት ከተማ ቤት የመስራት ፍላጎት ኖሯቸው መመሪያ ቁጥር 28/2009

በሚፈቅደው መሠረት እንደማንኛውም ዜጋ 14 እና ከዚያ በላይ ሆነው በማኅበር ተደራጅተውና ከቤት መስሪያ ዋጋው 20 በመቶ መቆጠባቸውን አረጋግጠው ቦታ መጠየቅ የሚችሉ መሆኑን ቁጥር 6(4) ያመለክታል። ደንብ ቁጥር 150/2009 መምህራን ተደራጅተው የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ለማግኘት በተለየ ያስቀመጠው ነገር ቢኖር በከተማ ለመኖሪያ ቤት መስሪያ ከሚዘጋጀው ቦታ ውስጥ 20-30 በመቶ የሚሆነው ለመምህራን ቅድሚያ ተሰጥቶ የሚመደብ መሆኑ ቁጥር 6(6) ,7(4), 8(5) እና 9(5) ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል። መምህራን እንደ ማንኛውም ዜጋ በመኖሪያ ህብረት ሥራ ማኅበራት ተደራጅተው የከተማ መኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታን ከሚያገኙ በቀር በመምህርነታቸው የተለየ መብት ተሰጥቷቸዋል ብሎ ለመናገር ብዙም የሚያስደፍር አይደለም። የተለየ መብት ተሰጥቷቸዋል ቢባል እንኳን በመጀመሪያ ደንቡ የወጣበት ዓላማ መነሻ ያደረገው የአማራን ብሔራዊ ክልላዊ መንግስትን ቢሆንም ጥራት ያለው ትምህርት ለዜጎች ማዳረስ እንደ ሀገር የተያዘ መዳረሻ ግብ በመሆኑ አመልካች በያዙት ሙያ ወደ አዲስ አበባ ከተማ ዝውውር ስላገኙ መብቱን ከዓላማው ውጪ ተጠቅሞበታል የሚያስብል አይሆንም። ሁለተኛ አመልካች በህገ መንግስቱ አንቀጽ 33(2) በዜግነታቸው ህግ የሚያስገኘውን መብት ጥበቃ እና ጥቅም የማግኘት መብት ያላቸው በመሆኑ በአንቀፅ 41(1) እና 32(1) መሰረት እንደቅደምተከተላቸው በመረጡት የመምህርነት ሙያ መሰማራት እና በመረጡት የሀገርቱ አካባቢ የመኖር መብታቸውን ማንኛውም የመንግስት አካል የማክበርና ማስከበር ኃላፊነት እና ግዴታ ያለበት መሆኑን የህገ መንግስቱ አንቀጽ 13(1) ይደነግጋል። አመልካች ባለትዳር መሆናቸው እና የባለቤታቸው ሥራ ቦታ አዲስ አበባ መሆኑ ግራቀኙን ያላከራከረ ሲሆን ፤ ባልና ሚስት አብሮ ለመኖር የሚገደዱ መሆኑና ተለያይተው መኖር የሚችሉት ለተወሰ ጊዜ መሆኑን የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 64(1) እና 66(1) ያስገነዝባሉ። አመልካች ከትዳር አጋራቸው ለማገናኘት ሲባል ዝውውር መደረጉ በቤተሰብ ሕጉም ሆነ በሲቭል ሰርቪስ ህጉ ተቀባይነት ያለው ሆኖ እያለ አመልካች በመምህርነታቸው ከአዲስ አበባ ከተማ የቤት ተጠቃሚ መሆናቸው ባልተረጋገጠበት ፣ አመልካች በደንብ ቁጥር 150/2009 ቁጥር 10 መሰረት በራሳቸውም ሆነ በትዳር አጋራቸው ስም አስቀድሞ የተመዘገበ የመኖሪያ ቤት ወይንም ቦታ ያላቸው መሆኑ ክርክር እና ማስረጃ ባልቀረበበት ፤ እንዲሁም ቦታ ለማግኘት የተደረጀ ሰው በሥራ ወደ ሌለ ቦታ በመዛወሩ ምክንያት ከመኖሪያ ቤት የጎበረት ሥራ ማኅበር አባልነቱ ይሰረዛል የሚል በአዋጅ ቁጥር 220/2007 ቁጥር 18 ሥር ባልተደነገገበት የአመልካች ከማኅበር አባልነት መሰረዝ ሕጉን የተከተለ አይደለም። በአነስተኛ ፣ መካከለኛ እና ሜትሮፖሊታን ከተማ አስተዳደሮች

የሚያስተምሩ መምህራን ቁጥር ከ14 በታች በሆነ ጊዜ በተናጥል በሊዝ መነሻ ዋጋ የቤት መሥሪያ ቦታ የማግኘት መብት አላቸው፡፡ (ደንብ ቁጥር 7(3) , 8(3) እና 9(3) ድንጋጌን ይመለከቷል፡፡) ስለዚህ የመኖሪያ ቤት መሥሪያ ቦታ ማግኘት መብት በማኅበር በመደራጀት የሚገኝ ሳይሆን ከሕግ የሚመነጭ ነው፡፡ በአዋጁ ቁጥር 220/2007 የመደራጀት ዓላማው ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮችን በጋራ ጥረት በመቋቋምና በማስወገድ ፣ በግል ቢሰራ የሚደርሰውን ጉዳት እና ኪሳራ በመከላከል የእያንዳንዱን ጉዳት እና ኪሳራ በመቀነስ የአባላቱን ጥቅም ማስከበር መሆኑን ከቁጥር 4(4) እና 4(8) ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡ ምንም እንኳን የማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ አባላት ከማኅበሩ የሚወጡበትና የሚመለሱበትን ሁኔታ የሚያካትት መሆኑ በአዋጁ ቁጥር 14 (2) (ሰ) ሥር የተደነገገ ቢሆንም ድንጋጌው መታየት ያለበት ከአባልነት መብት እና ግዴታቸውን ከመወጣት አንፃር እንጅ ፤ የአባላቱን ጥቅም በተሻለ መልኩ ለማስጠበቅ የተቋቋመ ማኅበር በህጉ ያልተቀመጠውን መስፈርት በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ በማስፈር አባላቱን ባልተገባ ምክንያት ከማኅበር በማሰናበት በህግ የሚያገኙትን መብት ማሳጣት በማኅበር የመደራጀት ዓላማ አይደለም፡፡ ሲጠቃለል አመልካች በመምህርነታቸው የቤት መሥሪያ ቦታ ለማግኘት በተጠሪ ማኅበር ተደራጅተው በመጠባበቅ ላይ እያሉ በመምህርነት ሙያቸው የትዳር አጋራቸው ወደሚሰሩት አዲስ አበባ ከተማ በመዛወራቸው ምክንያት ከተጠሪ ማኅበር መሰናበታቸው ከላይ በዝርዝር በተመለከቱት ምክንያቶች ተገቢነት የሌለው በመሆኑ ቀጣዩ ተወስኗል፡፡

ውሳኔ

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪው ችሎት በመዝገብ ቁጥር 103071 መጋቢት 8 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ ፣ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ደብረ ብርሀን ምድብ በመዝገብ ቁጥር 0121252 ጥር 28 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ ፤ ውሳኔ እና ትዕዛዝ እንዲሁም የሰሜን ሸዋ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0133343 ህዳር 25 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ ፣ ውሳኔ እና ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት **ተሽሯል**፡፡

2 የሸዋሮቢት ከተማ አስተዳደር ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 17584 ሐምሌ 14 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ ፣ ውሳኔ እና ትእዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) *መሠረት* **ፀንቷል**።

3 በስበር ክርክሩ የደረሰውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የግላቸውን ይቻሉ።

4 ውሳኔው መጋቢት 5 ቀን 2014 ዓ/ም በችሎት ተነቧል።

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት